# በውኑ በውኃውና በመንፈሱ ዳግም ተወልዳችኋልን?

ፓውል ሲ. ጆንግ

# Worldwide websites of The New Life Mission

The Official Website of The New Life Mission
**www.nlmission.com** or **www.bjnewlife.org**

Please find your vernacular websites below.
You can download Christian e-books and request Christian books for free.
Feel free to visit our websites below right now!

**A**
www.nlmafghanistan.com
www.nlmafrikaans.com
www.nlmalbania.com
www.nlmamharic.com
www.nlmangola.com
www.nlmarabemirates.com
www.nlmarabic.com
www.nlmargentina.com
www.nlmarmenia.com
www.nlmaruba.com
www.nlmaustralia.com
www.nlmaustria.com

**B**
www.nlmbahamas.com
www.nlmbahrain.com
www.nlmbangladesh.com
www.nlmbelarus.com
www.nlmbelgium.com
www.nlmbengali.com
www.nlmbenin.com
www.nlmbhutan.com
www.nlmbolivia.com
www.nlmbotswana.com
www.nlmbrasil.com
www.nlmbriton.com
www.nlmbrunei.com
www.nlmbulgalia.com
www.nlmburkinafaso.com
www.nlmburundi.com

**C**
www.nlmcameroon.com
www.nlmcanada.com
www.nlmcebuano.com
www.nlmchichewa.com
www.nlmchile.com
www.nlmchin.com
www.nlmchina.com
www.nlmcolombia.com
www.nlmcongo.com
www.nlmcostarica.com
www.nlmcotedivoire.com
www.nlmcroatia.com
www.nlmczech.com

**D**
www.nlmdenmark.com
www.nlmdioula.com
www.nlmdominica.com
www.nlmdrcongo.com
www.nlmdutch.com

**E**
www.nlmecuador.com
www.nlmegypt.com
www.nlmelsalvador.com
www.nlmequatorialguinea.com
www.nlmethiopia.com

**F**
www.nlmfinland.com
www.nlmfrance.com
www.nlmfrench.com

**G**
www.nlmgabon.com
www.nlmgeorgian.com
www.nlmgerman.com
www.nlmgermany.com
www.nlmghana.com
www.nlmgreek.com
www.nlmgrenada.com
www.nlmguatemala.com
www.nlmgujarati.com

**H**
www.nlmhaiti.com
www.nlmhindi.com
www.nlmholland.com
www.nlmhonduras.com
www.nlmhungary.com

◎ Some of these websites may not work because they are still under construction.

# Worldwide websites of The New Life Mission

I
www.nlm-india.com
www.nlmindonesia.com
www.nlmiran.com
www.nlmiraq.com
www.nlmisrael.com
www.nlmitaly.com

J
www.nlmjamaica.com
www.nlmjapan.com
www.nlmjavanese.com

K
www.nlmkannada.com
www.nlmkazakhstan.com
www.nlmkenya.com
www.nlmkhmer.com
www.nlmkinyarwanda.com
www.nlmkirghiz.com
www.nlmkirundi.com
www.nlmkorea.com

L
www.nlmlatvia.com
www.nlmluganda.com
www.nlmluo.com

M
www.nlmmadi.com
www.nlmmalagasy.com
www.nlmmalayalam.com
www.nlmmalaysia.com
www.nlmmarathi.com
www.nlmmauritius.com
www.nlmmexico.com
www.nlmmindat.com
www.nlmmizo.com
www.nlmmoldova.com
www.nlmmongolia.com
www.nlmmyanmar.com

N
www.nlmnepal.com
www.nlmnewzealand.com
www.nlmnigeria.com
www.nlmnorthkorea.com
www.nlmnorway.com

P
www.nlmpakistan.com
www.nlmpanama.com
www.nlmperu.com
www.nlmphilippines.com
www.nlmpoland.com
www.nlmportugal.com
www.nlmportuguese.com
www.nlmprcongo.com

Q
www.nlmqatar.com

R
www.nlmromania.com
www.nlmrussia.com
www.nlmrwanda.com

S
www.nlmsaudiarabia.com
www.nlmserbian.com
www.nlmshona.com
www.nlmsingapore.com
www.nlmslovakia.com
www.nlmslovene.com
www.nlmsolomon.com
www.nlmsouthafrica.com
www.nlmspain.com
www.nlmspanish.com
www.nlmsrilanka.com
www.nlmsuriname.com
www.nlmswahili.com
www.nlmswaziland.com
www.nlmsweden.com
www.nlmswiss.com

T
www.nlmtagalog.com
www.nlmtaiwan.com
www.nlmtamil.com
www.nlmtanzania.com
www.nlmtelugu.com
www.nlmthailand.com
www.nlmtogo.com
www.nlmtonga.com
www.nlmturkey.com

U
www.nlmuganda.com
www.nlmukraine.com
www.nlmurdu.com
www.nlmusa.com

V
www.nlmvenezuela.com
www.nlmvietnam.com

Z
www.nlmzambia.com
www.nlmzimbabwe.com
www.nlmzou.com

# ይህ «የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል» በመጽሃፍ ቅዱስ መሰረት በትክክል ለመስበክ የተጻፈ የዘመናችን የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው።

ብዙዎቻችሁ ከውኃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን ወንጌል እንደማታውቁ የታወቀ ነው ስለዚህም በእያንዳንዱ ስብከት ላይ በኢየሱስ የጥምቀት ወንጌልና በመስቀሉ ላይ ትኩረት ለማድረግ ሞክሬአለሁ።

ኢየሱስ ባይጠመቅ ኖሮ መስቀሉ ለሁላችንም ትርጉም አልባ ይሆን ነበር በእርሱ ጥምቀት ላይ ደጋግሜ ያተኮርኩባቸው ምክንያቶቼ እነዚህ ናቸው

አላማዬ ይህን ለናንተ ግልፅ ማድረግ ነው ሁላችሁም በውሃውና (የኢየሱስ ጥምቀት) በመንፈሱ ወንጌል እስክትባረኩ ድረስም ልደጋግምላችሁ እወዳለሁ።

ከኃጢያት ለመዳን ሁላችሁም በእርሱ የጥምቀት ወንጌልና መስቀል ወደ ማመን ትመጡ ዘንድ በጉጉት እመኛለሁ እነዚህ ስብከቶችም ዳግም ትወለዱ ዘንድ እንደሚመሩዋችሁ እርግጠኛ ነኝ።

### በውኑ

# በውኃውና
# በመንፈሱ

### ዳግም ተወልዳችኋልን?

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

# በውኑ
# በውኃውና በመንፈሱ
# ዳግም ተወልዳችኋልን?

**PAUL C. JONG**

**ሄፍዚባህ አሳታሚ ድርጅት**
የኒው ላይፍ ሚሽን አገልግሎት
ሴኡል፣ ኮሪያ

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

*በውኑ በውኃውና በመንፈሱ ዳግም ተወልዳችኋልን?*

---

የታተመው ©2012 በሄፍዚባህ ማተሚያ ቤት
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡ የዚህ መጽሐፍ የትኛውም ክፍል ከባለቤቱ የጽሁፍ ፈቃድ ውጭ በኤሌክትሪካል፣ መካኒካል ፎቶ ኮፒ ማድረግን መቅዳትን ወይም ማንኛውንም መረጃ የሚይዝ ወይም ይዞ የሚያስቀር ሲስተምን ጨምሮ በማንኛውም መልክ ወይም በማንኛ ውም መንገድ ማባዛት ወይም ማሰራጨት ክልክል ነው፡፡
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት *ከ1954ቱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ* ነው፡፡

ISBN 978-89-6532-755-4

**Website :** http://www.nlmission.com
http://www.bjnewlife.org
http://www.nlmbookcafe.com
**E-mail :** newlife@bjnewlife.org

**ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር** (www.amazon.com) **በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡**

# ምስጋና

ጌታ የደህንነትን ቃሎች ስለሰጠንና ከውሃና ከመንፈስ ዳግም በምንወለድበት ወንጌል ስለባረከን የምስጋና ጸሎት ማቅረብ እንወዳለን::

ለዚህ መፅሐፍ ሕትመት በዋጋ የማይተመን አገልግሎቶችን ያበረከቱትን ሪቨረ. ጆን ኬ. ሺንንና እህት ሳንግሚን ሊን ጨምሮ ይህንን መፅሐፍ ለተረጎመችው ለሚስስ ጁንግፒል ሱንግ በሔፍሲባ ፐብሊሺንግ ሐውስ ላሉ ወንድሞችና እህቶች በንንግዎን ናሽናል ዩኒቨርሲቲ ላለችው ሌላይን ዳዌና ለኮርያ ታይምሱ ሮስ ዋላስ ለእግዚአብሄር አገልጋዮች በሙሉ ምስጋና አቀርባለሁ ሁሉም ለዚህ መጽሐፍ በትጋት ሰርተዋል እንደገና ምስጋና ለሁላችሁም ይሁን::

ይህ መፅሐፍና እርሱን የሚያጅቡት የቴፕ ካሴቶች ብዙ ነፍሳቶች ዳግም እንዲወለዱ እንደሚያግዙ ተስፋ አደርጋለሁ እጸልያለሁም ከእኛ ጋር ጠንክረው ለሰሩት ሁሉ እንደገና ልባዊ ምስጋናን ማቅረብ እፈልጋለሁ::

ጌታችን በኢየሱስ በሚያምኑት አማካኝነት ከውኃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን ወንጌል በመላው አለም እናሰራጭ ዘንድ እንዲፈቅድልን ከልቤ እመኛለሁ::

ጌታን በማይሞት እምነት አመሰግናለሁ::

**PAUL C. JONG**

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፓውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::



# መቅድም

## ከውኃና ከመንፈስ ዳግም መወለድ አለብን

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ሲፈጥር ዘላለማዊ ዓለማትን ገነትንና ገሃነምንም ፈጥሮዋል ሰውንም በአምሳሉ ፈጠረ ነገር ግን የመጀመሪያው ሰው አዳም በእግዚአብሔር ፊት ኃጢያትን ስለሰራ ሰዎች ሁሉ አንዴ መሞት ነበረባቸው *«ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደተመደበባቸው» (ዕብራውያን 9:27)*

የስጋችን መሞት ወደ ዘላለማዊ ህይወት የሚመራን መተላለፊያ መንገድ ነው ኃጢያት የሌለባቸው ሰዎች ዘላለማዊ ወደሆነው የሰማይ አለም ይገቡና የእግዚአብሔር ልጆች በመሆን ይደሰታሉ ኃጠያተኞች ደግሞ ወደ *«እሳቱና ዲኑ ባህር» (ራእይ 20:10)* ተጥለው ለዘላለም ቀንና ለሊት ይሠቃያሉ::

ስለዚህ የሰው ልጅ በሙሉ ዳግም መወለድ አለበት በእምነቶቻችን አማካይነት ዳግም መወለድ ከኃጢያቶቻችን ሁሉ መዳንና ጻድቃን መሆን ይኖርብናል ዘላለማዊ ወደሆነው መንግስተ ሰማይ ልንገባ የምንችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- *«እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም» (ዮሐንስ 3:5)* «ከውኃና ከመንፈስ ዳግም መወለድ» ወደ እግዚአብሔር መንግስት የምንገባበት ብቸኛ መንገድ ነው::

ታዲያ ዳግም እንድንወለድ የሚፈቅድልን ይህ «ውኃ» እና «መንፈስ» ምንድነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ውሃ»

የሚያመለክተው «የኢየሱስን ጥምቀት» ነው።

አምላክ የሆነው ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ የተጠመቀው ለምንድን ነው? ትህትናውን ለማሳየት ነበር? ራሱን መሲህ አድርጎ ለማወጅ ነበርን? አልነበረም።

ኢየሱስ *«በእጆችን መጫን»* አማካይነት *(ዘሌ 16:21)* በአጥማቂው ዮሐንስ ሲጠመቅ ይህ የሰውን ዘር ኃጢያቶች በሙሉ ያስወገደ *«የአንድ ሰው የፅድቅ ተግባር» (ሮሜ 5:18)* ነበር።

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የመቤዠትን የምህረት ህግ ለእስራኤል ሰጠ ይህ የሆነው በስርየት ቀን በዚያ አመት የተሰሩት የእስራኤል ሐጢያቶች በሙሉ እጆቹን «በሚለቀቀው ፍየል» ራስ ላይ በመጫን ሐጢያቶችን ሁሉ ወደዚያ የሚለቀቅ ፍየል ላይ በሚያስተላልፈው ሊቀ ካህን በአሮን አማካይነት ስርየትን ማግኘት ይችሉ ነበር።

እነዚህ ዘላለማዊን የስርየት መስዋዕት የሚተነብዩ የመገለጥ ቃሎች ነበሩ የሰብአዊ ዘር ኃጢያቶች በሙሉ በአብ ፈቃድ መሰረት የሰው ስጋ ለብሶ ወደመጣው ኢየሱስ ለአንዴና ለዘላለም መተላለፋቸውን የሚገልጥ እውነት ነው እርሱም የአሮን ዘርና የሰው ዘር ሁሉ ወኪል በሆነው በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ።

ኢየሱስ ሲጠመቅ ለዮሐንስ እንዲህ አለው *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው።» (ማቴዎስ 3:15)*

እዚህ ላይ *«እንዲህ»* ማለት ጽድቅ ሁሉ ስለሁላችን ይፈተም ዘንድ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ለማስተላለፍ «እጆችን መጫን» ማለት ነው «ጽድቅ» የሚለው ቃል በግሪክ *«ዲካዮሱን»* ማለት ሲሆን ትርጉሙም «እጅግ ያማረ ሁኔታ» ወይም «ጻድቅ ወይም ገጣሚ ከመሆን አንደምታ

ጋር በጠባይ ወይም በምግባሮች ቀና መሆን» ማለት ነው::

ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት ለሰዎች ሁሉ ቅንና ተገቢ በሆነ ሁኔታ ጽድቅን ሁሉ ፈጽሞዋል ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት የሰዎችን ሐጢያቶች በሙሉ ስለወሰደ በሚቀጥለው ቀን አጥማቂው ዮሐንስ እንዲህ በማለት መሰከረ *«በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ:- እነሆ የአለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ::» (ዮሐንስ 1:29)*

ኢየሱስ የሰው ልጆችን ኃጢያቶች በሙሉ በጫንቃዎቹ ላይ ተሸክሞ ወደ መስቀል ሄደ በጥምቀቱ አማካይነት በራሱ ላይ ለወሰዳቸው ሐጢያቶች በሙሉም ፍርድን በይፋ ተቀበለ *«ተፈፀመ»* በማለትም በመስቀል ላይ ሞተ*(ዮሐንስ 19፣30)* ኃጢያታችንን በሙሉ በራሱ ላይ ወስዶ በኛ ፋንታ ሙሉ ፍርድን ተቀበለ::

## ውኃው ማለትም የኢየሱስ ጥምቀት የደህንነት ምሳሌ ነው

ስለዚህ «በኢየሱስ ጥምቀት የሚያምን እምነት» ከሌለን መዳን አንችልም ሐዋርያው ጴጥሮስ ውኃው ማለትም የኢየሱስ ጥምቀት *«ምሳሌው ሆኖ ያድነናል»* ያለው ለዚህ ነው *(1ኛ ጴጥሮስ 3:21)*

ዛሬ በኢየሱስ የሚያምኑ አብዛኞቹ ሰዎች በኢየሱስ ጥምቀት «በውኃው» አያምኑም የሚያምኑት በመስቀል ላይ ሞቱ ብቻ ነው ይህ አይነቱ እምነት ግን ኃጢያተኞችን ያድናልን? በኢየሱስ ደም ብቻ በማመን ከኃጢያቶቻችን ሁሉ መዳን እንችላለን? ይህስ ደህንነትን ሊሰጠን ይችላል?

አይሰጠንም በኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞት በማመን ብቻ በእግዚአብሄር ፊት መዳን አንችልም::

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሕዝበ እስራኤል የስርየትን መስዋዕት ሲያቀርቡ መስዋዕቱን ከመግደላቸው በፊት አስቀድመው እጆቻቸውን በእንስሳው አናት ላይ ጭነው ኃጢያቻቸውን ወደ እርሱ ካላስተላለፉ መሰዋዕቱ ትክክል አይሆንም ነበር ስለዚህ በጥምቀቱ ሳያምኑ በኢየሱስ መስቀል ብቻ ማመን ስህተትና ሕገ ወጥነት ይሆናል::

ስለዚህ ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ ብሏል *«ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ ያድነናል ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ነው::» (1ኛ ጴጥሮስ 3:21)*

በኖህ ዘመን በታላቁ «ውሃ» (ጎርፍ) ያላመኑ ሰዎች እንደጠፉ ሁሉ አሁንም «በውሃው» «በኢየሱስ ጥምቀት» የማያምኑ ሰዎች መጥፋታቸው የተረጋገጠ ነው::

ወደ እውነተኛ ደህንነት የሚመራን ምሉዕ የሆነው እምነት *«በውኃ በደም በመጣው--ኢየሱስ ክርስቶስ» (1ኛ ዮሐንስ 5:6)* በኢየሱስ ክርስቶስ ያለው እምነት ነው::

ሐዋርያው ዮሐንስም ትክክለኛው እምነት *«በመንፈሱ በውሃውና በደሙ ምስክርነት» (1ኛ ዮሐንስ 5:8)* ማመን እንደሆነ ተናግሯል::

እውነተኛውን እምነት የሚያዋቅረው እንዲህ ያለ ማመን ነው «ኢየሱስ ራሱ እግዚአብሔር ነው እንዲሁም የሰው ስጋን ለብሶ በድንግል ማርያም ስጋ በኩል ወደ ምድር በመምጣት የሰው ዘር ሁሉ ወኪል በሆነው በአጥማቂው ዮሐንስ በዮርዳኖስ በመጠመቅ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ተሸክሞ ወደ መስቀል ሄደ ስለ ሁላችንም ይፋ የሆነውን ፍርድ ተቀበለ» ስለዚህ ወንጌል ያለ «ኢየሱስ ጥምቀት» ያለ «ውሃው» ምሉዕ ሊሆን አይችልም ምንም ያህል

በኢየሱስ አጥብቀን ብናምንም ወንጌሉን ሳናምን ከቶውኑም ዘላለማዊ ደህንነትን ማግኘት አንችልም።

# እውነተኛው ወንጌል ከቤተክርስቲያን የጠፋበት ታሪካዊ መሠረት

በዚህ ዘመን እውነተኛው «የውኃና የመንፈስ ወንጌል» እንዲህ ብርቅዬ የሆነውና በምትኩ ሐሰተኛ ወንጌሎች በስፋት በመላው አለም የሚሰራጩት ለምንድነው?

ኢየሱስ ከሙታን ከተነሳና ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ሐዋርያቶች ይህንን «የውኃና የደም ወንጌል» አስተማሩ አዲስ ኪዳንን በጥንቃቄ ካነበብነው «የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል» በግልጽ የሰበኩት ጳውሎስን ጴጥሮስንና ዮሐንስን ጨምሮ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ብቻ ሳይሆኑ የጥንቷ ቤተክርስቲያን ሐዋርያቶችና ሰራተኞች ሁሉ ነበሩ።

ዲያብሎስ ለጊዜውም ቢሆን ወንጌልን ደረጃ በደረጃ ለመለወጥና የሕይወትን ሐይል ከቤተክርስቲያን ለመውሰድ ሲያሴር ነበር ስለዚህ በ313 ኢ.ም ከወጣው የሚላን ድንጋጌ ዘመን ጀምሮ የክርስቲያን ቤተክርስቲያን በጥንቃቄ በተጠመደው የዲያብሎስ ወጥመድ ተይዛ ነበር የሮም ንጉሰ ነገስት ፖለቲካዊ ሐይሎች ክርስትና የመንግስት ሐይማኖት ሆኖ እንዲታወቅ በማድረግ በልዋጩ የፖለቲካ መረጋጋትን አግኝተው ነበር።

«ወደ ቤተክርስትያን የገባውን ሁሉ ማጥመቅ» በመጥቀስ የሮም ንጉሰ ነገስት በተለያዩ ብዙ ቅኝ ግዛቶቹ ውስጥ ያለውን አንድነት ጠብቆ አቆየ።

የሐዋርያቶች የእምነት መግለጫ የሐይማኖት ስልጠና መሰረት ሆኖ እንዲተካ የተደረገውም ከእነዚህ ሁኔታዎች የተነሳ

ነበር በዚያ ምክንያት «*በሐይልና በመንፈስ ቅዱስ ብዙም መረዳት» (1ኛ ተሰሎንቄ 1:5)* የተሰጠን «ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በሚገባ የሚጣጣመው ወንጌል» ማለትም «የውኃና የመንፈስ ወንጌል» በሐሰተኛ ወንጌል ተተካ ሰይጣን እንዳቀደውም ማንም ዳግም እንዲወለድ የማይፈቅደው የሐሰት ወንጌል በመላው አለም ተስፋፋ::

ከሚላኑ ድንጋጌ በኋላ ለብዙ ሺህ አመታት የክርስትና ዘመን መላውን የአውሮፓ አለም አሽመደመደው ምንም እንኳን ሰዎችን ወደ «ቃሉ ጸጋውና እምነት» እንዲመለሱ የሚያግባቡ ተከታታይ አዳዲስ የጠሐድሶ እንቅስቃሴዎች ቢነሱም አንዳቸውም እውነተኛ ወንጌል የሆነውን «የውኃና የደምን ወንጌል» አላገኙም::

ይህ እውነተኛ ወንጌል ከሐዋርያቶች ዘመን ጀምሮ ቃሉን በተከተሉት ጥቂቶች እጅ ሕያው ሆኖ ተጠብቆ ነበር መሬት ውስጥ ዘልቆ እንደተሰወረና ዝቅ ባሉ ሸንተረሮች ላይ ዳግመኛ እንደሚፈልቅ ምንጭ በመላው አለም ይሰራጭ ዘንድ ዳግመኛ በመጨረሻው ዘመን ብቅ አለ::

## በዚህ ዘመን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጻፈው መሰረት የኢየሱስን ጥምቀት ወንጌል የሚሰብክ የመጀመሪያው መጽሐፍ ይህ ነው::

በዚህ ዘመን በቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ በተጻፈው መሰረት የኢየሱስን ጥምቀትና ደም ወንጌል ለመስበክ የመጀመሪያው መጽሐፍ ይህ ነው እውነተኛው ወንጌል እርሱ በጥምቀቱ አማካይነት ኃጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደና በመስቀል ላይም ለኃጢያቶቻችን በሙሉ ፍርድን እንደተቀበለ

በግልጽ ይነግረናል ከዚህ መጽሐፍ በበለጠ «የውኃውንና የደሙን ወንጌል» ይበልጥ ግልጽ በሆነ መንገድና በታማኝት የሚሰብክ ሌላ መጽሐፍ እንደሌለ እርግጠኛ ነኝ፡፡

ኢንተርኔት ለምርምርና ለእውቀት ግኝት ጠቃሚ መሳርያ በሆነበት በዛሬው አለም የኢየሱስን ጥምቀት ምስጢር የሚያውቁና እውነተኛውን ወንጌል የሚሰብኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተጻፈውም የኢየሱስን ጥምቀት ምስጢር የሚያውቁና በእምነት የሚሰብኩ አንዳንድ አጋር ሰራተኞችን ለማግኘት ሞክሬ ነበር እስከ አሁን ድረስ ግን አልተሳካልኝም ስለዚህ ይህንን መጽሐፍ በእንግሊዝኛ ለማተም ወስኛለሁ፡፡

ጉርፉ መላውን አለም በሚሸፍንበት ጊዜ ውኃው ለአለም በሙሉ ይተርፍ ይሆናል ነገር ግን ማንም የሚጠጣው ጥሩ ውሃ አይሆንም በተመሳሳይ መንገድ አስመሳይ ወንጌልን የሚሰብኩ ብዙ «የእግዚአብሔር አገልጋዮች» ተብዬዎች አሉ ነገር ግን እውነተኛውን ሕይወት የሚሰጠን ማንም የለም፡፡

በየቀኑ ከያዕቆብ ጉድጓድ ስትጠጣ የነበረችው ሳምራዊቷ ሴት መንፈሳዊ ጥማቷን ማርቻት አልቻለም ነገር ግን ከኢየሱስ ዘንድ የህይወትን ውሃ በጠጣች ጊዜ ደህንነትን አገኘች መንፈሳዊ ጥሟንም ወዲያውኑ ለዘላለም አረቻች፡፡

በኢየሱስ ውስጥ ያለው የህይወት ውሃ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባለው እያንዳንዱ ሸንቁርና ክፍል ውስጥ እየፈሰሰ ነው ከዚህ የሚጠጣ ሁሉ ለዘላለም ከሐጢያቱ ይድናል ይህ ሰው ዳግመኛ በሐጢያት አይታሰርም ነገር ግን በዙሪያው ያሉትን የሌሎች ነፍሳቶች ጥማት ለማርቻት ሕያው ውሃ ከውስጡ ይፈልቃል፡፡

# የእግዚአብሔር ሰራተኞች ሰባራውን ጠጋኝ እንሁን

እኛ እየኖርን ያለነው ወደ አለም ፍፃሜ በተቃረበ ዘመን ላይ ነው ይህ ዘመን የሰው ዘር ሐጢያቶች ጽዋውን የሞሉበትና የእግዚአብሄርም ጻድቅ ፍርድ የቀረበበት ዘመን ነው አንዳንድ ሳይንቲስቶች «ዶሊ» የተባለች በግ በዘረ መል ያራቡበት ዘመን ነው ሰዎችም በዘረ መል የተፈለፈሉ ሰብአዊ ፍጡራኖችን ለመቀበል ተዘጋጅተዋል::

ዛሬ እኛ ሌላ የባቤል ግንብ እየገነባን ነው የሰው ዘር እንደዚህ ያሉ ነገሮችን ለመጨረሻ ጊዜ የሞከረው እግዚአብሄር ቋንቋቸውን በመደባለቅ በምድር ሁሉ ላይ በበተናቸው ጊዜ ነበር ታላቁ መከራ የእግዚአብሄር ጻድቅ ቁጣዎች በቅርቡ ገና ዳግም ባልተወለዱ የጠፉ ነፍሳቶች ላይ የሚወርድበት ጊዜ አሁን ነው::

ስለዚህ ይህን መጽሐፍ በጥንቃቄ እንድታነቡት እጠይቃችኋለሁ «ዳግም ከውኃውና ከመንፈሱ እንድትወለዱም» እፀልይላችኋለሁ ይህ መጽሐፍ ወንጌልን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጻፈው መሰረት በግልጽ ይሰብካል ስለዚህ እንዲህ ተብሎዋል፡-

ይህን መጽሐፍ በጥልቀት የሚያነብ ማንኛውም ሰው በትክክል ዳግም መወለድ አይሳነውም ጌታችን ኢየሱስ እንዲህ ብሎዋል *«ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ፡- እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው::» (ዮሐንስ 8:31-32)* በዚህ መጽሐፍ አማካይነት የእውነትን ቃሎች አውቃችሁ ከኃጢያትና ከሞት ነጻ ውጡ! በእርሱ ድናችሁም ዘላለማዊ ህይወትን አግኙ!

«የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል» በመስበክ የጠፉትን

ነፍሳት ለማዳን የአብን ስራ በጋራ እንስራ፡፡ እውነተኛው ወንጌል በመላው አለም እንደሚያበራ ከልቤ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እውነተኛው ወንጌል በእውነት ቃሎች የዘመኑን የክርስትና እምነት ስብራት እንድትጠግኑ እንደሚያደርጋችሁ እርግጠኛ ነኝ፡፡

*«ከድሮ ዘመን የፈረሱት ህንጻዎች ይሰራሉ፣ የብዙ ትውልድ መሠረትም ይታነጻል፣ አንተም፡- ሰባራውን ጠጋኝ፣ የመኖሪያ መንገድን አዳሽ ትባላለህ» (ኢሳይያስ 58:12)*

ብዙዎቻችሁ ከውኃውና ከመንፈሱ ዳግም የመወለድ ወንጌል ጋር እንደማትተዋወቁ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ስለዚህ በእያንዳንዱ ስብከት ውስጥ በኢየሱስ ጥምቀትና መስቀል ላይ ትልቅ ትኩረት ለማድረግ ሞክሬአለሁ፡፡

የኢየሱስ ጥምቀት ባይኖር ኖሮ በመስቀል ላይ መሞቱ ለሁላችንም ትርጉም የለሽ ይሆን ነበር፡፡ በእርሱ ጥምቀት ላይ ደጋግሜ ትኩረት የማደርግባቸው ምክንያቶች እነዚህ ናቸው፡፡

የኔ አላማ ይህን ለእናንተ ግልፅ ማድረግ ነው፡፡ ሁላችሁም በውኃውና (በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት) በመንፈሱ ወንጌል እስክትባረኩ ድረስ፣ ልደጋግምላችሁ እወዳለሁ፡፡

ከኃጢያት ለመዳን ሁላችሁም በእርሱ የጥምቀትና የደም ወንጌል ወደማመን እንድትመጡ በጉጉት እጠብቃለሁ፡፡ ይህ መጽሐፍ ከውሃውና ከመንፈሱ ዳግም ትወለዱ ዘንድ እንደሚመራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ✉

# ማውጫ

## ክፍል አንድ--- ስብከቶች


1. ለመዳን አስቀድመን ስለ ሐጢያቶቻችን ማወቅ አለብን
(ማርቆስ 7፡8-9፣ 20-23) ---------------------------------------- 22

2. ሰዎች ኃጢያተኞች ሆነው የተወለዱ ናቸው
(ማርቆስ 7፡20-23) ---------------------------------------------- 42

3. ነገሮችን በሕጉ መሰረት ብናደርግ ሕጉ ሊያድነን
ይችላልን? (ሉቃስ 10፡25-30) ----------------------------------- 58

4. ዘላለማዊው ቤዛነት
(ዮሐንስ 8፡1-12) ----------------------------------------------- 84

5. የኢየሱስ ጥምቀትና የኃጥያቶች ስርየት
(ማቴዎስ 3፡13-17) ------------------------------------------- 122

6. ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው በውሃ፣
በደምና በመንፈስ ነው
(1ኛ ዮሐንስ 5፡1-12) -------------------------------------------- 182

7. የኢየሱስ ጥምቀት ለሐጢያተኞች የደህንነት ምሳሌ ነው
(1ኛጴጥሮስ3፡20-22) ------------------------------------------ 226

8. የተትረፈረፈው ስርየት ወንጌል
(ዮሐንስ 13፡1-17) ------------------------------------------- 248



ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።

# ክፍል ሁለት--- አባሪ


**1. የደህንነት ምስክርነቶች ------------------------------------------- 330**

**2. ተጨማሪ ማብራርያ --------------------------------------------- 354**

**3. ጥያቄዎችና መልሶቻቸው -------------------------------------- 392**



**ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር** (www.amazon.com) **በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።**

# ስብከት 1

## ለመዳን አስቀድመን ስለ

## ሐጢያቶቻችን ማወቅ አለብን

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::



ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

# ለመዳን አስቀድመን ስለ ሐጢያቶቻችን ማወቅ አለብን

**« ማርቆስ 7:8-9 »**

**«የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጥሳችሁ፣ ጽዋን ማድጋንም እንደማጠብ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ:: ይህንም የመሰለ ብዙ ሌላ ነገር ታደርጋላችሁ:: እንዲህም አላቸው:- ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል::»**

**« ማርቆስ 7:20-23 »**

**«እርሱም አለ:- ከሰው የሚወጣው፣ ሰውን የሚያረክስ ያ ነው:: ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት ስንፍና ናቸውና፣ ይህ ክፋው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል::»**

በመጀመሪያ ኃጢያት ምን እንደሆነ ለማብራራት እወዳለሁ:: በእግዚአብሔር የተብራሩ ሐጢያቶች አሉ በሰው የተብራሩም ኃጢያቶች አሉ:: በጥንቱ የግሪክ ቃል ኃጢያት ማለትም «ሃማርቲያ» «ኢላማን መሳት» ማለት ነው:: በሌላ አገላለፅ፣ ስህተት የሆነን ነገር ማድረግ ማለት ነው:: የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ አለመታዘዝ ኃጢያት ነው::

በመጀመሪያ ሰው ስለ ሐጢያት ያለውን አመለካከት እንመልከት::




ኃጢያትን የምንገነዘበው በሕሊናዎቻችን አማካይነት ነው:: ቢሆንም ሰው ሐጢያትን ሲለካ ከማህበራዊ አመጣጡ ከአእምሮ ሁኔታው ካለበት ሁኔታዎችና ሕሊና አንጻር ይለያያል::

ስለዚህ ለኃጢያት የሚሰጠው ማብራሪያ ከሰው ሰው የተለያየ ነው:: በእያንዳንዱ ሰው መለኪያዎች ላይ ተመስርቶ አንዱ ድርጊት ሐጢያት ሆኖ ሊታይ ወይም ላይታይ ይችላል እግዚአብሄር የሕጉ 613 አንቀጾች ፍጹም የሆኑ የሐጢያት መለኪያ ሆነው እንዲያገለግሉ የሰጠው ለዚህ ነው::

ከዚህ በታች ያለው ምስል የሰው ልጆችን ኃጢያት ያብራራል::




በማህበራዊ ስርአቶች ላይ ተመስርተን በሕሊናዎቻችን ላይ የሐጢያትን መለኪያዎች ከቶውኑም ማስቀመጥ አይገባንም::

በሕሊናዎቻችን የምንሰራቸው ሐጢያቶች እግዚአብሄር ሐጢያት ብሎ ከገለጠው ጋር አይስማሙም ስለዚህ ሕሊናዎቻችንን ማድመጥ የለብንም ነገር ግን የሐጢያትን መለኪያዎች በእግዚአብሄር ትዕዛዛት ላይ መመስረት ይገባናል፡፡

እያንዳንዳችን ሐጢያት ምን እንደሆነ የራሳችን እሳቤ አለን አንዳንዶች ሐጢያትን የራሳቸው ጉድለቶች አድርገው ሲመለከቱት ሌሎች ደግሞ በተዛባ ባህርይ ላይ የተመሰረተ ነገር እንደሆነ አድርገው ያስቡታል፡፡

ለምሳሌ በኮርያ ሰዎች የወላጆቻቸውን መቃብሮች በሳር ይሸፍኑዋቸውና እስኪሞቱ ድረስ የመንከባከቡን ሐላፊነት እንዲወስድላቸው ያደርጋሉ ነገር ግን በፓፑዋ ኒው ጊኒ ውስጥ ካሉት ኋላ ቀር ነገዶች አንዱ የሞቱ ወላጆቻቸውን የሚያከብሩት ሬሳውን ከቤተሰብ አባላት ጋር በመመገብ ነው (ሬሳውን ከመብላታቸው በፊት ይቀቅሉት እንደሆነ እርግጠኛ አይደለሁም) ሬሳው በትሎች እንዳይበላ መከላከላቸው እንደሆነ አምናለሁ ይህ ባህል ሰው ስለ ሐጢያት ያለው እሳቤ በጣም የተለያየ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚደረግ ሰናይ ምግባር በሌላው ማህበረሰብ ውስጥ አረመኔያዊነት ሆኖ ሊቆጠር ይችላል *«የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጥሳችሁ፣ ጽዋን ማድጋንም እንደማጠብ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ፡፡ ይህንም የመሰለ ብዙ ሌላ ነገር ታደርጋላችሁ፡፡ እንዲህም አላቸው፡- ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል፡፡» (ማርቆስ 7:8-9)* የኛ አካላዊ ገፅታ በእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ዋጋ የለውም ምክንያቱም እግዚአብሔር የልባችንን ጥልቅ ያያልና፡፡

# የሰው መስፈርት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢያት ነው

*በጣም አሳሳቢው ኃጢያት ምንድን ነው?*

*የእግዚአብሔርን ቃል*
*መናቅ ነው።*

እንደ ፈቃዱ ከመኖር መውደቅ በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያት ነው ቃሉን ከአለማመን ጋርም ተመሳሳይ ነው የእግዚአብሄርን ትዕዛዛት እንደናቁትና በራሳቸው ወጋዊ ትምህርቶች ላይ ይበልጥ ጠቀሜታ እንዳኖሩት ፈሪሳውያን መኖር ሐጢያት እንደሆነ እግዚአብሄር ተናግሮዋል ኢየሱስ ፈሪሳውያኖችን እንደ ግብዞች ቆጥሮዋቸዋል።

«የምታምኑት በየትኛው አምላክ ነው? በእርግጥ እኔን ታከብሩኛላችሁ ከፍስ ታደርጉኛላችሁ? በስሜ ትኮራላችሁ ነገር ግን በእርግጥ ታከብሩኛላችሁ?» ሰዎች ውጫዊ ገጽታዎቻችንን ብቻ ተመልክተው ቃሉን ሊንቁ ይችላሉ በጣም አሳሳቢው ሐጢያት የእርሱን ቃል መናቅ ነው ይህንን ታውቃላችሁን?

ከድክመቶቻችን የመነጩ የአመጽ ምግባሮች ተራ በደሎች ናቸው ፍጹማን ባለመሆናችን የምንሰራቸው ስህተቶችና የምንፈጽማቸው ጥፋቶች መሰረታዊ ሐጢያቶች ሳይሆኑ ስህተቶች ናቸው እግዚአብሄር ሐጢያቶችን ከበደሎች ለይቶዋቸዋል የእርሱን ቃል የሚንቁ ሰዎች ስህተቶች ባይኖሩባቸውም እንኳን ሐጢያተኞች ናቸው በእግዚአብሄር ፊት ታላቅ ሐጢያተኞች ናቸው ኢየሱስ ፈሪሳውያንን የወቀሰው ለዚህ ነው።

ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ድረስ ያሉትን መጽሐፎች በያዘው ፔንታቱክ ውስጥ ምን እንደምናደርግና ምን ማድረግ እንደሌለብን የሚነግሩን ትዕዛዛቶች አሉ እነዚህ የእግዚአብሄር ቃል የእርሱ ትዕዛዛቶች ናቸው እነርሱን 100 በመቶ ልንጠብቃቸው አንችል ይሆናል ነገር ግን የእርሱ ትዕዛዛት መሆናቸውን መቀበል አለብን እርሱ ከመጀመሪያ ጀምሮ እነርሱን ሰጥቶናል እኛም የእግዚአብሄር ቃል አድርገን ልንቀበላቸው ይገባናል፡፡

*«በመጀመሪያ ቃል ነበር፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበር፡»* በመቀጠልም እንዲህ አለ፡- *«ብርሃን ይሁን አለ፣ ብርሃንም ሆነ፡፡»* እርሱ ሁሉን ፈጠረ፡፡ ከዚያ በኋላም ሕጉን አጸና፡፡

*«ቃልም ስጋ ሆነ፣ ጸጋና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ» (ዮሐንስ 1፡1,14)* እግዚአብሄር ራሱን የሚገልጥልን እንዴት ነው? ራሱን የሚገልጥልን በትዕዛዛቶቹ በኩል ነው ምክንያቱም እግዚአብሄር ቃልና መንፈስ ነውና ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን ምን ብለን እንጠራዋለን? የእግዚአብሄር ቃል ብለን እንጠራዋለን፡፡

እዚህ ላይ እንዲህም ተብሏል፡- *«ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እጅግ ንቃችኋል»* በእርሱ ሕግ ውስጥ 613 አንቀጾች አሉ ይህንን አድርግ ያንን ግን አታድርግ ወላጆችህን አክብር ወዘተ...፡፡ በዘሌዋውያን ውስጥ ወንዶችና ሴቶች እንዴት መመላለስ እንደሚገባቸውና አንድ የቤት እንስሳም ገደል ውስጥ ሲወድቅ ምን እንደሚያደርጉ ተጽፎዋል...በሕጉ ውስጥ እንደዚህ ያሉ 613 አንቀጾች አሉ፡፡

እነዚህ የሰው ቃሎች ስላልሆኑ ደጋግመን ልናስብባቸው ይገባናል የእርሱን ሕጎች በሙሉ መጠበቅ ባንችልም ቢያንስ እነርሱን ማወቅና እግዚአብሄርን መታዘዝ ይገባናል፡፡

በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ ትክክል ያልሆነ አንድ ምንባብ እንኳን አለ? ፈሪሳውያን የእግዚአብሄርን ትዕዛዛት ትተው የሰዎችን ወጎች ከትዕዛዛቱ በላይ አድርገው ያዙ ከእግዚአብሄር ቃሎች ይልቅ የሽማግሌዎቻቸው ቃሎች ይበልጥ ክብደት ነበራቸው ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ያየው ይህንን ነበር እርሱን እጅግ ያቆሰለው ሕዝቡ የእግዚአብሄርን ቃል ቸል ማለቱ ነበር፡፡

እግዚአብሄር ሐጢያቶቻችንን እንድናውቅ ለማድረግና እርሱ ቅዱስ የሆነ የእውነት አምላክ መሆኑን ሊያሳየን የሕጉን 613 አንቀጾች ሰጠን እኛ ሁላችን በእርሱ ፊት ሐጢያተኞች ስለሆንን በእምነት መኖርና እርሱ ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሳ ከእግዚአብሄር ዘንድ ወደ እኛ በተላከው ኢየሱስ ማመን ይገባናል፡፡

የእርሱን ቃል የሚንቁና በቃሉ የማያምኑ ሰዎች ሐጢያተኞች ናቸው የእርሱን ቃል መጠበቅ ያልቻሉ ሰዎችም እንደዚሁ ሐጢያተኞች ናቸው የእርሱን ቃል መናቅ አሳሳቢ ሐጢያት ነው እንዲህ ያለውን የከበደ ሐጢያት የሚሰሩ ሰዎች መጨረሻቸው ሲዖል ይሆናል በእርሱ ቃል አለማመን በእርሱ ፊት እጅግ አስከፊ ሐጢያት ነው፡፡

## እግዚአብሔር ሕጉን ለእኛ የሰጠበት ምክንያት

*እግዚአብሔር ለምን ሕጉን ሰጠን?*

*ኃጢያቶቻችንንና የእነርሱንም ቅጣት እንድናገናዝብ ለማድረግ ነው፡፡*

እግዚአብሄር ሕጉን ለእኛ የሰጠበት ምክንያት ምን ነበር? ሐጢያቶቻችንን ተገንዝበን ወደ እርሱ እንድንመለስ ለማድረግ ነበር ሐጢያቶቻችንን እንድንገነዘብና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ቤዛነትን እንድናገኝ የሕጉን 613 አንቀጾች ሰጠን እግዚአብሄር ሕጉን የሰጠን ለዚህ ነው::

ሮሜ 3:20 እንዲህ ይላል *«ኃጢያት በህግ ይታወቃልና»* ስለዚህ እግዚአብሄር ሕጉን ለእኛ የሰጠበት ምክንያት በእርሱ እንድንኖር ሊያስገድደን አልነበረም::

ታዲያ ከሕጉ የምናገኘው እውቀት ምንድነው? እኛ ሕጉን በሙላቱ ለመጠበቅ በጣም ደካሞች መሆናችንንና በፊቱም የከፋን ሐጢያተኞች መሆናችንን ነው ከ613ቱ የሕጉ አንቀጾች የምንገነዘበው ምንድነው? በሕጉ ለመኖር ያለንን ጎዶሎነትና አቅመ ቢስነት እንገነዘባለን እኛ የእግዚአብሄር ፍጡራኖች በእርሱ ፊት አቅመ ቢስ ፍጥረታቶች እንደዚሁም የከፋን ሐጢያተኞች ነን በሕጉ መሰረትም የሁላችንም መጨረሻ ሲዖል ሊሆን ይገባው ነበር::

ሐጢያቶቻችንንና በሕጉ ለመኖር አቅመ ቢስነታችንን ስንገነዘብ ምን እናደርጋለን? ፍጹም የሆንን ፍጥረታቶች ለመሆን እንሞክራለን? አይደለም እኛ ሐጢያተኞች መሆናችንን መቀበል በኢየሱስ ማመን በእርሱ የውሃና የመንፈስ ደህንነት አማካይነት ቤዛነትን ማግኘትና እርሱን ማመስገን አለብን::

እርሱ ሕጉን የሰጠን ሐጢያቶቻችንን እንድንገነዘብና ለእነዚያ ሐጢያቶችም የሚገባንን ቅጣት እንድናውቅ ለማደረግ ነበር ስለዚህ ያለ ኢየሱስ ከሲዖል መዳን እንደማይቻል እንገነዘባለን ኢየሱስን አዳኛችን አድርገን ብናምን ቤዛነትን እናገኛለን እርሱ ሕጉን የሰጠን ወደ አዳኙ ኢየሱስ እንዲመራን ነበር::

እግዚአብሄር ሕጉን የፈጠረው እኛ ምን ያህል ፍጹም

ሐጢያተኞች እንደሆንን እንድንገነዘብ ለማድረግና ነፍሳችንን ከዚህ ሐጢያት ለማዳን ነው እርሱ ሕጉን ሰጠን ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱ በመውሰድም ሊያድነን አንድ ልጁን ኢየሱስን ላከልን በእርሱ ማመን ሊያድነን ይችላል::

እኛ ከሐጢያታችን ነጻ ለመውጣት የእርሱ ልጆች ለመሆንና እንደገና ወደ እግዚአብሄር ክብር ለመመለስ በኢየሱስ ማመን የሚገባን ተስፋ ቢስ ሐጢያተኞች ነን::

በቃሉ አማካይነት መረዳት ማሰብና መወሰን ይገባናል ምክንያቱም ሁሉም ነገር የሚፈልቀው ከእርሱ ነውና በቃሉ አማካይነትም የቤዛነትን እውነት መረዳት ይገባናል ትክክለኛውና እውነተኛው እምነት ይህ ነው::

## በሰው ልብ ውስጥ ያለው ምንድን ነው?




እምነት መጀመር ያለበት በእግዚአብሔር ቃል ነው እኛም በቃሉ አማካይነት በእርሱ ማመን ይገባናል ካላመንን ስህተት ላይ እንወድቃለን ያም የተሳሳተና እውነተኛ ያልሆነ እምነት ይሆናል::

ፈሪሳውያንና ጸሐፍት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ባልታጠቡ

እጆች እንጀራ ሲበሉ ባዩ ጊዜ ከእግዚአብሄር ቃል አንጻር ቢያዩት ኖሮ ባልነቀፉዋቸውም ነበር ቃሉ ከውጭ ወደ ሰው የሚገባ ማንኛውም ነገር እርሱን/እርስዋን እንደማያረክስ ይነግረናል ምክንያቱም ወደ ሆድ ገብቶ ልብን ሳይነካ ከሰውነት ይወጣልና::

በማርቆስ 7፡20-23 እንዲህ ተብሎዋል *«እርሱም አለ፣ ከሰው የሚወጣው ሰውን የሚያረክስ ያ ነው:: ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣው ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትእቢት፣ ስንፍና ናቸውና ይህ ክፉ ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል»* ኢየሱስ ሰዎች ከሐጢያት ጋር ስለተወለዱ ሐጢያተኞች እንደሆኑ ተናግሮዋል::

ይህ ምን ማለት እንደሆነ ይገባችኋልን? እኛ ሐጢያተኞች ሆነን የተወለድነው ሁላችንም የአዳም ዘሮች ስለሆንን ነው ነገር ግን እውነቱን ማየት አልቻልንም ምክንያቱም የእርሱን ቃሎች በሙሉ አልተቀበልናቸውም አላመንናቸውም ታዲያ በሰው ልብ ውስጥ ምን አለ?

የላይኛው ምንባብ እንዲህ ይላል *«ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣው ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትእቢት፣ ስንፍና ናቸውና ይህ ክፉ ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል::»* ከሰው ልቦች ውስጥ ሁሉም አይነት ክፋቶች ይወጡና ያረክሱታል::

በመዝሙረ ዳዊት ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«የጣቶችህን ስራ ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ፣ ጨረቃና ከዋክብትን አንተ የሰራኻቸውን፣ ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጎበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?» (መዝሙር 8፡3-4)::*

እግዚአብሄር ራሱ የሚጎበኘን ለምንድነው? እርሱ የሚጎበኘን ስለሚወደን ስለፈጠረንና ለእኛ ለሐጢያተኞች ስለሚያዝን ነው እርሱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ደምስሶ ሕዝቡ አድርጎናል እግዚአብሔር ራሱ የጎበኘን ለምንድን ነው? የጎበኘን ስለሚወደን፣ ስለፈጠረንና በኛ በኃጢያተኞቹ ስለተቀየመ ነው፡፡ ኃጢያቶቻችንን ሁሉ ይቅር ብሎ የራሱ ሕዝቦች አድርጎናል፡፡ *«አቤቱ ጌታችን ስምህ በምድር ላይ እንዴት ተመሰገነ!»* ንጉሥ ዳዊት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይህንን መዝሙር የዘመረው እግዚአብሄር የሐጢያተኞች አዳኝ እንደሚሆን በተረዳ ጊዜ ነበር፡፡

በአዲስ ኪዳንም ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንኑ መዝሙር ደግሞታል እኛ የእግዚአብሄር ፍጥረቶች የፈጣሪ ልጆች መሆን መቻላችን አስገራሚ ነገር ነው ይህ የሆነው በእርሱ ርህራሄ የተነሳ ብቻ ነው የእግዚአብሄር ፍቅር ይህ ነው፡፡

ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሄር ሕግ ለመኖር መሞከር ለእግዚአብሄር የድፍረት ተግዳሮት እንደሆነ መገንዘብ ይገባናል ከድንቁርና የሚመነጭም የዕብሪት ዝንባሌ ነው ሕግን ለራስ በመጠበቅና ለእንደዚህ አይነቱ ሕይወት አምርሮ ለመጸለይ በመታገል ከእርሱ ፍቅር ውጭ መኖር ትክክል አይደለም እኛ ራሳችንን ከሕግ በታች ያለን ሐጢያተኞች እንደሆንን አድርገን መገንዘብና በኢየሱስ ውሃና ደም ቤዛነት ማመን አለብን፡፡

ቃሉ በማርቆስ 7:20-23 ላይ ተጽፎዋል *«እርሱም አለ፣ ከሰው የሚወጣው ሰውን የሚያረክስ ያ ነው፡፡ ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣው ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትእቢት፣ ስንፍና ናቸውና ይህ ክፉ ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል፡፡»*

ኢየሱስ ሰውን የሚያረክሰው ከውስጡ የሚወጣው

በውስጡ ያሉት ሐጢያቶች እንደሆኑ ተናግሮዋል እግዚአብሄር የሰጠው ንጹህ ያልሆነ ምግብ እንኳን ሊያረክሰን አይችልም ፍረጥታት የሚያረክሱን ከሰዎች የሚወጡት ነገሮች ማለትም ሐጢያቶች ናቸው ሁላችንም የአዳም ዘሮች ሆነን ተወልደናል ታዲያ የምንወለደው? ከምን ጋር ነው? አስራ ሁለት ሐጢያቶችን ይዘን እንወለዳለን ይህ ትክክል አይደለምን?

ሐጢያቶችን ሳንሰራ መኖር እንችላለን? ከሐጢያት ጋር ስለተወለድን ሐጢያት በመስራት እንቀጥላለን ሕጉን ስለምናውቅ ሐጢያት መስራት ማቆም እንችላለን? በትዕዛዛቶቹ መኖር እንችላለን? አንችልም::

በሕጉ ለመኖር አብዝተን በሞከርን ቁጥር እየከበደን ይሄዳል ገደቦቻችንን ማወቅና ያለፉ ዝንባሌዎቻችንን መተው ይገባናል ያን ጊዜ ትሁት በሆኑ ልቦች የሚያድነንን የኢየሱስን ጥምቀትና ደም መቀበል እንችላለን::

የሕጉ 613 አንቀጾች በሙሉ በጎና ጻድቅ ናቸው ሰዎች ግን በእናቶቻቸው ማህጸኖች ውስጥ ከተጸነሱበት ጊዜ ጀምሮ ሐጢያተኞች ናቸው የእግዚአብሄር ሕግ ትክክል እንደሆነና እኛ ግን በራሳችን ጻድቃን መሆን ፈጽሞ የማንችል ሐጢያተኞች ሆነን እንደተወለድን ስንገነዘብ በውሃው በደሙና በመንፈሱ ወንጌል የእግዚአብሄር የምህረት ርህራሄና የኢየሱስ ቤዛነት እንደሚያስፈልገን ወደ ማወቅ እንመጣለን ገደቦቻችንን ስናውቅ --በራሳችን ጻድቃን መሆን እንደማንችልና ስለ ሐጢያቶቻችንም ወደ ሲዖል እንደምንሄድ-- በኢየሱስ ቤዛነት ላይ ከመደገፍ በቀር ልናደርገው የምንችለው ነገር የለም::

መዳን እንችላለን በራሳችን በእግዚአብሄር ፊት ትክክለኛ ወይም ሰናይ መሆን እንደማንችል ልናውቅ ይገባናል ስለዚህ እኛ ለሲዖል የታጩን ሐጢያተኞች እንደሆንን በእግዚአብሄር በማመን «አምላኬ እባክህ ከሐጢያቶቼ አድነኝ ራራልኝ»

በማለት እግዚአብሄር እንዲራራልን ልንጸልይ ይገባናል ያን ጊዜ እግዚአብሄር በእርግጥም በቃሉ ይገናኝናል በዚህ መንገድ መዳን እንችላለን::

*የዳዊትን ጸሎት እንመልከት:- «የሚያጠፋ ቃልን ሁሉ፣ የሸንገላ ቃልን ወደድህ::» (መዝሙር 51:4)*

ዳዊት ወደ ሲዖል ለመወርወር የሚያበቃው ክፋት የተሞላበት የሐጢያት ክምችት እንደነበር አወቀ ነገር ግን በእግዚአብሄር ፊት «ጌታ ሆይ ሐጢያተኛ ብለህ ከጠራኸኝ ሐጢያተኛ ነኝ ጻድቅ ብለህ ከጠራኸኝ ጻድቅ ነኝ ካዳንከኝ እድናለሁ ወደ ሲዖል ከላክኸኝ መጨረሻዬ ሲዖል ይሆናል» በማለት በእግዚአብሄር ፊት አመነ::

ትክክለኛው እምነትና የመዳኛው መንገድ ይህ ነው በኢየሱስ ቤዛነት ለማመን ተስፋ የምናደርግ ከሆንን ልንሆን የሚገባን እንደዚህ ነው::

## ኃጢያቶቻችን ምን እንደሆኑ በትክክል ማወቅ አለብን

ሁላችንም የአዳም ዘሮች ስለሆንን ሁላችንም በልቦቻችን ውስጥ ፍትወቶች አሉብን ነገር ግን እግዚአብሄር ምን ይነግረናል? እርሱ በልቦቻችን ውስጥ ምንዝርና ቢኖርም እንዳናመነዝር ይነግረናል በልባችን ውስጥ ነፍስ ማጥፋት አለ እግዚአብሄር ግን ምን ይነግረናል? እንዳንገድል ይነግረናል ሁላችንም በልባችን በወላጆቻችን ላይ እናምጽባቸዋለን እርሱ ግን እንድናከብራቸው ይነግረናል የእርሱ ቃል ትክክልና ሰናይ እንደሆነ እኛ ግን ሁላችንም በልቦቻችን ውስጥ ሐጢያት እንዳለብን መገንዘብ ይገባናል::

ይህ ትክክል ነው ወይስ አይደለም? ፈጽሞ ትክክል ነው

ስለዚህ በእግዚአብሄር ፊት ምን ማድረግ ይገባናል? ሁላችንም የሐጢያት ክምችቶችና ተስፋ የሌለን ሐጢያተኞች መሆናችንን ማመን ይኖርብናል ትላንትና ሐጢያት ስላልሰራን ትላንትና ጻድቃን ዛሬ ግን ሐጢያቶችን ስለሰራን ዛሬ ሐጢያተኞች ነን ብለን ማሰብ ትክክል አይደለም ሐጢያተኞች ሆነን ተወልደናል ምንም ነገር ብናደርግ አሁንም ሐጢያተኞች ነን በኢየሱስ ጥምቀት በእምነት አማካይነት ቤዛነትን ማግኘት ያለብን ለዚህ ነው::

ሐጢያተኞች የሆንነው በምግባሮቻችን ማለትም በማመንዘር ነፍስ በመግደል በሌብነት አይደለም...ሐጢያተኞች የሆንነው ሐጢያተኞች ሆነን ስለተወለድን ነው አስራ ሁለት አይነት ሐጢያተኞችን ይዘን ተወልደናል በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኞች ሆነን ስለተወለድን በራሳችን ጥረቶች ከቶውኑም በጎ መሆን አንችልም በጎ ለመሆን ብቻ እናስመስላለን::

ሐጢያተኛ አስተሳሰቦችን ይዘን ተወልደናል እነዚህን ሐጢያቶች ባንሰራ እንኳን እንዴት ጻድቃን ልንሆን እንችላለን? በራሳችን በእግዚአብሄር ፊት ፈጽሞ ጻድቃን ልንሆን አንችልም ጻድቃን ነን ብንል ይህ ግብዝነት ነው ኢየሱስ ፈሪሳውያንንና ጻሐፍትን *«ግብዝ ፈሪሳውያንና ፀሐፍት»* ብሎ ጠርቶዋቸዋል ሰዎች ሐጢያተኞች ሆነው ተወልደዋል በዕድሜ ዘመናቸውም በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያት ይሰራሉ::

በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ከማንም ጋር አልተጣላሁም ማንንም አልደበደብኩም መርፌ ብትሆን ከማንም አልሰረቅሁም የሚል ሰው እየዋሸ ነው ምክንያቱም ሰዎች ሐጢያተኞች ሆነው ተወልደዋልና ያ ሰው ውሸታም ሐጢያተኛና ግብዝ ነው እግዚአብሄር እርሱን/እርስዋን የሚያየው እንደዚህ ነው::

ሰው ሁሉ ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ ሐጢያተኛ ነው አንዲት የሐጢያት ድርጊት ባትሰሩ እንኳን ለሲዖል የታጯችሁ

ናችሁ ከሕጉና ከትዕዛዛቱ አብዛኛውን ብትጠብቁም አሁንም ወደ ሲዖል ለመሄድ የታጫችሁ ሐጢያተኛ ናችሁ::

ታዲያ እነዚህን ዕጣ ፈንታዎች ምን እናድርጋቸው? እግዚአብሄር እንዲራራልን ልንጠይቀውና ከሐጢያቶቻችን ለመዳንም በእርሱ ላይ ልንደገፍ ይገባናል እርሱ ካላዳነን ሲዖል እንወርዳለን ዕጣ ፈንታችን ያ ነው::

በእርግጥም ሐጢያተኞች እንደሆኑ የሚያምኑት የእግዚአብሄርን ቃል የተቀበሉ ሰዎች ብቻ ናቸው እነርሱ በእምነት ጻድቃን እንደሚሆኑም ያውቃሉ ስለዚህ ቃሉን ሳያውቁ መናቅና ገሸሽ ማድረግ እጅግ የከፋ ሐጢያት እንደሆነ ያውቃሉ የእርሱን ቃል የተቀበሉ ሰዎች ከዚህ ቀደም ሐጢያተኞች ቢሆኑም ጻድቃን ናቸው እነርሱ በጸጋው ከቃሉ ዳግም ተወልደዋል እጅግ የተባረኩም ናቸው::

## በስራቸው ለመዳን የሚሞክሩ ሰዎች አሁንም ሐጢያተኞች ናቸው




ገላትያ 3:10 እና 11ን እናንብ:- *«ከሕግ ስራ የሆኑት ሁሉ በእርግማን በታች ናቸውና፣ በሕግ መጽሐፍ በተፃፉት ሁሉ*

*ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና። ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎአልና ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንደማይጸድቅ ግልጥ ነው።»*

እንዲህ ተብሎዋል *«...በሕግ መጽሐፍ በተፃፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና»* በኢየሱስ እናምናለን ብለው የሚያስቡ ነገር ግን በስራዎቻቸው ለመጽደቅ የሚሞክሩ ሰዎች የተረገሙ ናቸው በስራዎቻቸው ለመጽደቅ የሚሞክሩ ሰዎች ያሉት የት ነው? ከእግዚአብሄር እርግማን በታች ነው።

እግዚአብሔር ሕግን የሰጠን ለምንድን ነው? እርሱ ሕግን የሰጠን ኃጢያቶቻችንን እንድንገነዝብ ነው። (ሮሜ 3:20) እኛ ለሲዖል የታጨን ሐጢያተኞች መሆናችንንም እንድናውቅ ይፈልጋል።

የእግዚአብሄር ልጅ በሆነው የኢየሱስ ጥምቀት እመኑ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም ተወለዱ ያን ጊዜ ከሐጢያቶቻችሁ ድናችሁ ጻድቃን ትሆናላችሁ የዘላለም ሕይወትን አግኝታችሁም ሰማይ ትገባላችሁ በልባችሁ እምነት ይኑራችሁ።

## በአለም ላይ እጅግ ዕብሪተኛው ኃጢያት ምንድነው?



በእርሱ በረከት እምነት ስላለን ተባርከናል እግዚአብሔር በእርሱ ቃል እምነት ያላቸውን ያድናል::

ዛሬ ግን በምዕመናኖች መካከል በእግዚአብሄር ሕግ ለመኖር የሚሞክሩ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ በሕጉ ለመኖር መሞከራቸው የሚያስመሰግን ነው ነገር ግን እንዴት ይቻላል?

በእግዚአብሄር ሕግ ለመኖር መሞከር ምን ያህል ሞኝነት እንደሆነ መገንዘብ አለብን አብዝተን በሞከርን ቁጥር ይበልጥ እየከበደ ይሄዳል *«እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው»* ይላል ለመዳን ዕብሪታችንን መጣል ያስፈልገናል::

## ለመዳን የራሳችንን መለኪያዎች መተው አለብን

*ለመዳን ምን ማድረግ አለብን?*

*የራሳችንን መለኪያዎች መተው መቻል አለብን::*

ሰው መዳን የሚችለው እንዴት ነው? ይህ የሚቻለው እሱ/እሷ ሐጢያተኛ መሆናቸውን ሲያውቁ ነው እስከ አሁን ድረስ ያልዳኑ ብዙ ሰዎች አሉ ምክንያቱም የተሳሳቱ እምነቶቻቸውንና ጥረቶቻቸውን መተው አልቻሉም::

እግዚአብሄር ሕጉን አጥብቀው የያዙ ሰዎች የተረገሙ ናቸው ይላል በኢየሱስ ካመኑ በኋላ በሕጉ ለመኖር በመሞከር ቀስ በቀስ ጻድቃን እንደሚሆኑ የሚያምኑ ሰዎች የተረገሙ ናቸው እነርሱ በእግዚአብሄር ያምናሉ ነገር ግን ለመዳን በሕጉ

መሰረት መኖር እንደሚገባቸው ያምናሉ።

የተወደዳችሁ ወዳጆቼ በስራዎቻችን ጻድቃን መሆን እንችላለን? እኛ ጻድቃን መሆን የምንችለው በኢየሱስ ቃል በማመን ብቻ ነው ቤዛነትን የምናገኘው ያን ጊዜ ብቻ ነው እኛ ቤዛነትን የምናገኘው በኢየሱስ ጥምቀት በደሙና በአምላክነቱ እምነት ሲኖረን ብቻ ነው።

እግዚአብሄር ጻድቃን እንሆን ዘንድ የእምነትን ሕግ መንገድ እንዲሆነን ያዘጋጀልን ለዚህ ነው የውሃውና የመንፈሱ ቤዛነት ያረፈው በሰዎች ስራዎች ላይ ሳይሆን በእግዚአብሄር ቃል እምነት ላይ ነው እግዚአብሄር በእምነት አማካይነት አድኖናል እግዚአብሄር ደህንነታችንን ያቀደውና የፈጸመው እንደዚህ ነው።

በኢየሱስ ያመኑትስ ያልዳኑት ለምንድነው? የውሃውንና የመንፈሱን ቤዛነት ቃል ስላልተቀበሉ ነው እኛም እንደ እነርሱ በእንከን የተሞላን የነበርን ሰዎች ግን በእግዚአብሄር ቃል ላይ ባለን እምነት ቤዛነትን አግኝተናል።

ሁለት ሰዎች ወፍጮ ላይ ቢሰሩ አንዱ ሰው ከተወሰደ በኋላ እንኳን የቀረው ሰው ስራውን ይቀጥላል የቀረው ሰው የሚያመላክተው ገና ቤዛነትን ያላገኘውን ሰው ነው አንዱ ተወስዶ ሌላው የቀረው ለምንድነው?

አንዱ የእግዚአብሄርን ቃል ሰምቶ በማመኑ ሌላው ግን ሕጉን ለመጠበቅ ጠንክሮ በመስራቱና ውሎ አድሮም ወደ ሲዖል ስለተጣለ ነው ያ ሰው በእግዚአብሄር ላይ ለመንጠልጠል እየሞከረ ነበር እግዚአብሄር ግን በእግሩ ላይ እየተሳበ የሚሄድ ሰው ይመስል አራገፈው ሰው ሕጉን ለመጠበቅ በመሞከር ወደ እግዚአብሄር እየተሳበ ለመንጠልጠል ቢሞክር በእርግጠኝነት ወደ ሲዖል ይጣላል።

በውሃውና በመንፈሱ እምነት መዳን የሚኖርብን ለዚህ ነው።

*«ለሕግ ስራ የሆኑት ሁሉ በእርግማን በታች ናቸውና፣ በሕግ መጽሐፍ በተፃፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም፣ ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና:: ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎአልና ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንዳይጸድቅ ግልጥ ነው::» «ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጻልና::» (ገላትያ 3:10-11፣ ሮሜ 1:17)*

በእግዚአብሄር ቃል አለማመን በፊቱ በእርሱ ፊት ሐጢያት ነው በተጨማሪም የእግዚአብሄርን ቃል በራስ መለኪያዎች መሰረት ወደ ጎን ገሸሽ ማድረግም እንደዚሁ ሐጢያት ነው እኛ ሰዎች ሁላችንም ሐጢያተኞች ሆነን ስለተወለድንና በዘመናችንም ሁሉ ሐጢያት በመስራት ስለምንቀጥል በእግዚአብሄር ሕግ መኖር አንችልም በየሄድንበት ስፍራ ጥቂት ከዚህ ጥቂት ከዚያ ሐጢያት እንሰራለን እኛ ከስጋ እንደሆንንና ሐጢያት ከመስራት ማምለጥ እንደማንችል መገንዘብ ይኖርብናል::

ሰው አንድ ትልቅ የእበት ባልዲን ይመስላል ያንን እበት ተሸክመነው ለመዞር ብንሞክር በየመንገዱ ይንጠባጠባል እኛም እንደዚያ ነን በየሄድንበት ሁሉ ሐጢያትን እናንጠባጥባለን ልታስቡት ትችላላችሁን?

አሁንም ድረስ ቅዱሳን ነን እያላችሁ ታስመስላላችሁን? ማንነታችሁን በግልጥ ብታውቁ በከንቱ ቅዱሳን ለመሆን መሞከራችሁን አቁማችሁ በውሃውና በኢየሱስ ደም ታምኑ ነበር::

ገና ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች ግትርነታቸውን ጥለው በእግዚአብሄር ፊት የከፉ ሐጢያተኞች መሆናቸውን ማመን አለባቸው ያን ጊዜ ወደ ቃሉ ተመልሰው እንዴት በውሃውና በመንፈሱ እንዳዳናቸው ይረዳሉ:: በመንፈስ እንዴት እንዳዳናቸው ከቃሉ መረዳት አለባቸው:: ✉

# ስብከት 2

## ሰዎች ኃጢያተኞች ሆነው

---

## የተወለዱ ናቸው

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።



ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።።

# ሰዎች ኃጢያተኞች ሆነው
# የተወለዱ ናቸው

**« ማርቆስ 7:20-23 »**

**«እርሱም አለ፡- ከሰው የሚወጣው፣ ሰውን የሚያረክስ ያ ነው:: ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኰል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት ስንፍና ናቸውና፣ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል::»**

## ሰዎች ግራ ተጋብተው በራሳቸው ምናቦች ውስጥ ይኖራሉ




ከሁሉ በፊት አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ እወዳለሁ ራሳችሁን የምታዩት እንዴት ነው? ጥሩ ወይም መጥፎ እንደሆናችሁ ታስባላችሁን? ምን ይመስላችኋል?

ሰዎች ሁሉ የሚኖሩት በራሳቸው ምናቦች ውስጥ ነው እንደምታስቡት መጥፎ ላትሆኑ ትችላላችሁ እንደምታስቡትም

ጥሩዎች አትሆኑ ይሆናል።

የተሻለ የእምነት ሕይወትን የሚመራ ማን ይመስላችኋል? ራሱን/ራስዋን ጥሩ እንደሆኑ አድርገው የሚያስቡት? ወይስ ራሱን/ራስዋን መጥፎ አድርገው የሚያስቡት?

የኋለኞቹ ናቸው ሌላ ጥያቄ ልጠይቃችሁ ይበልጥ የመዳን ዕድል ያለው ማነው ብዙ ሐጢያቶችን የሰራ ወይስ ጥቂት ሐጢያቶችን ብቻ የሰራው? በርካታ ሐጢያቶችን እንደሰራ የሚያምን ሰው ብዙ የመዳን ዕድል አለው ምክንያቱም ግለሰቡ የከፋ ሐጢያተኛ መሆኑን አምኖዋልና ይህ ሰው ኢየሱስ ለእርሱ ያዘጋጀለትን የቤዛነት ቃል በተሻለ መንገድ መቀበል ይችላል።

ራሳችንን በትክክል ስንመለከት የሐጢያት ክምችቶች ብቻ እንደሆንን የተረጋገጠ ነው ሰዎች ምንድናቸው? ሰው *«የክፉ አድራጊዎች ዘር»* ብቻ ነው በኢሳይያስ 59 ላይ በሰዎች ልቦች ውስጥ ሁሉም አይነት በደሎች እንደሚገኙ ተጠቅሶዋል ስለዚህ ሰዎች የሐጢያት ክምችቶች መሆናቸው ግልጽ ነው ነገር ግን ሰውን *«የክፉ አድራጊዎች ዘር»* አድርጎ መግለጡ ትክክለኛ መግለጫ ነው ራሳችንን በቅንነት ከተመለከትን ክፉዎች መሆናችን ግልጽ ነው ለራሳቸው እውነተኞች የሆኑ ሰዎች ወደዚህ ተመሳሳይ ድምዳሜ ላይ መድረስ አለባቸው።

ራሳችንን በትክክል ስንመለከት ተራ የሐጢያት ክምችቶች መሆናችን ግልጽ ነው ሰዎች ምንድናቸው? ሰው *«የክፉ አድራጊዎች ዘር»* ነው ኢሳይያስ 59 በሰዎች ልቦች ውስጥ ሁሉም አይነት በደሎች እንዳለ ይናገራል ስለዚህ ሰዎች የሐጢያት ክምችቶች መሆናቸው ግልጽ ነው ነገር ግን የሰውን ዘር የሐጢያት ክምችት አድርገን ብንገልጠው ብዙዎች አይስማሙም ነገር ግን ሰውን *«የክፉ አድራጊዎች ዘር»* አድርጎ መግለጡ ትክክለኛ መግለጫ ነው ራሳችንን በቅንነት ብንመለከት ክፉ ሰዎች መሆናችን ግልጽ ነው ለራሳቸው እውነተኞች የሆኑ

ሰዎች እዚህ ድምዳሜ ላይ መድረስ አለባቸው::

ነገር ግን አብዛኛው ሰው በእርግጥም የሐጢያት ክምችት መሆኑን ለማመን አሻፈረኝ የሚል ይመስላል ብዙዎች ተመችቶዋቸው ይኖራሉ ምክንያቱም ራሳቸውን ሐጢያተኞች አድርገው አይቆጥሩምና እኛ ክፉዎች ስለሆንን በሐጢያት የተሞላ ስልጣኔን ፈጥረናል ይህ እውነት ባይሆን ኖሮ ሐጢያት ለመስራት እጅግ ባፈርን ነበር ሆኖም ብዙዎቻችን ሐጢያቶችን ስንሰራ አናፍርም::

ሕሊናቸው ግን ያውቃል እያንዳንዱ ሰው «ይህ አሳፋሪ ነው» ብሎ የሚነግረው ሕሊና አለው አዳምና ሔዋን ሐጢያት ከሰሩ በኋላ በዛፎች መካከል ተሸሸጉ ዛሬ ብዙ ሐጢያተኞች የሐጢያት ባህል ከሆነው ብልሹ ባህላችን በስተ ጀርባ ተደብቀዋል የእግዚአብሄርን ፍርድ ለመሸሽ አብረዋቸው ባሉ ሐጢያተኞች መካከል ተደብቀዋል::

ሰዎች በራሳቸው ምናቦች ተታልለዋል ከሌሎች ይልቅ በጣም ሰናይ እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን ያስባሉ ስለዚህ አንዳንድ መጥፎ ዜናዎችን ሲሰሙ በቁጣ «ሰው እንዴት እንዲህ ያሉ ነገሮችን ያደርጋል? ሰው እንዴት ያንን ያደርጋል? ልጅ በወላጆቹ ላይ እንዴት ያንን ያደርጋል?» በማለት ይጮሃሉ እነርሱ ራሳቸው እነዚህን ነገሮች እንደማያደርጉ ያምናሉ::

የተወደዳችሁ ወዳጆች ራሳችሁን ለማወቅ በጣም አስቸጋሪ ነው ራሳችንን በትክክል ለማወቅ በመጀመሪያ የሐጢያቶችን ስርየት መቀበል አለብን ሰዋዊ ባህሪያችንን በትክክል ለማወቅ ረጅም ጊዜ ይወስድብናል እስከ ዕለተ ሞታችንም ድረስ ይህንን ፈጽሞ የማናውቅ ብዙዎች እንኖራለን::

# ራሳችሁን እወቁ

*ራሳቸውን የማያውቁ ሰዎች*
*የሚኖሩት እንዴት ነው?*

*ኃጢያተኛ ማንነታቸውን ለመደበቅ*
*በመሞከር የግብዝነትን ኑሮ*
*ይኖራሉ*

አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን በትክክል የማያውቁ ሰዎች ያጋጥሙናል፡፡ ሶቅራጥስ «ራስህን እወቅ» ብሎዋል ነገር ግን ብዙዎቻችን በልባችን ውስጥ ምን እንዳለ አናውቅም፣ መግደል፣ ስርቆት፣ ስስት፣ ክፋት፣ ማታለል፣ ብልሹነት፣ መመቅኘት...

ራሱን የማያውቅ ሰው በከንፈሮቹ ላይ የእባብ መርዝ እያለ ስለ በጎነት ይናገራል ምክንያቱም ሰውየው የማያመልጥ ሐጢያተኛ ሆኖ መወለዱን ስለማያውቅ ነው፡፡

በዚህ አለም ላይ እውነተኛ ባህሪዎቻቸውን የማያውቁ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ ራሳቸውን አታለዋል ሕይወታቸውንም በራሳቸው መታለሎች ውስጥ ሙሉ በሙሉ ሸፍነው ይኖራሉ ራሳቸውን በማታለላቸው ማንነታቸውን ወደ ሲዖል እየወረወሩ እንደሆኑ አይረዱም፡፡

# ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ያለ ማቋረጥ ኃጢያትን ያንባጥባሉ

*እነርሱ ሲያል የሚገቡት ለምንድን ነው?*

*ራሳቸውን ስለማያውቁ ነው፡፡*

ማርቆስ 7፡21-23ን እንመልከት፡- *«እርሱም አለ፡- ከሰው የሚወጣው፣ ሰውን የሚያረክስ ያ ነው፡፡ ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት ስንፍና ናቸውና፣ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል»* የሰው ልጆች ልብ ከተጸነሱበት ዕለት አንስቶ በኃጢያት የተሞላ ነው፡፡

የሰው ልብ ከብርጭቆ የተሰራና እስከ አፍ ገደፉ ድረስ በቆሻሻ ፈሳሽ ማለትም በሐጢያቶቻችን የተሞላ ነው ብለን እናስብ ይህ ሰው ወደኋላና ወደፊት ሲንቀሳቀስ ምን ይፈጠራል? ቆሻሻው ፈሳሽ (ሐጢያት) በየቦታው ይንጠባጠባል፡፡

እኛ የሐጢያት ክምችቶች የሆንን ሰዎች ሕይወታችንን የምንኖረው ልክ እንደዚህ ነው በየሄድንበት ሁሉ ሐጢያትን እናንጠባጥባለን የሐጢያት ክምችቶች ስለሆንን በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ሐጢያት እንሰራለን፡፡

ችግሩ እኛ የሐጢያት ክምችቶች ወይም በሌላ አነጋገር የሐጢያት ዘሮች መሆናችንን አለማወቃችን ነው እኛ የሐጢያት ክምችቶች ነን ከተወለድንበት ቀን አንስቶም በልባችን ውስጥ ሐጢያት አለ፡፡

የሐጢያት ክምችቶች ሊፈስሱ ተዘጋጅተዋል ነገር ግን ሰዎች በተፈጥሮዋቸው ሐጢያተኞች መሆናቸውን አያምኑም ሌሎች ወደ ሐጢያት እንደሚመሩዋቸው ስለሚያስቡ መጥፎዎቹ እነርሱ አይደሉም።

ሰዎች ሐጢያቶችን ከሰሩ በኋላ እንኳን ራሳቸውን ንጹህ አድርገው ለማጠብ የሚያስፈልገው ብቸኛው መጠይቅ ሐጢያትን መጥረግ እንደሆነ ያስባሉ ሐጢያት በሰሩ ቁጥር ለራሳቸው ስህተቶቹ የእነርሱ እንዳልሆኑ በመናገር ራሳቸውን በመጥረግ መቀጠል ነው ራሳችንን ስላነጻን ብቻ እያንጠባጠቡ መቀጠል ትክክል ነው ማለት ነው? ደጋግመን ያለ ማቋረጥ መጥረግ ይኖርብናል።

ብርጭቆው በሐጢያት ሲሞላ መፍሰሱን ይቀጥላል ውጭውን መጠራረግ ምንም ጥቅም የለውም ውጭውን በሰናይ ምግባሮቻችን አዘውትረን ብንጠርገውም ብርጭቆው በሐጢያት እስከተሞላ ድረስ ጥቅም የለውም።

እኛ ብዙ ሐጢያት ይዘን ስለተወለድን ምንም ያህል ሐጢያት በየመንገዱ ብናንጠባጥብ ልቦቻችን ከቶውኑም ባዶ አይሆኑም ስለዚህ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ሐጢያቶችን እንሰራለን።

ሰው በእርግጥም የሐጢያት ክምችት እንደሆነ የማያውቅ ከሆነ ሐጢያተኛ ባህሪውን በመደበቅ ይቀጥላል ኃጢያት በሁሉም ሰው ልብ ውስጥ ያለ ስለሆነ ውጭውን በማጽዳት አይወገድም ትንሽ ሐጢያት ስናንጠባጥብ በጨርቅ እንጠርገዋለን እንደገና ስናጠባጥብ በትልቅ ጨርቅ...በፎጣ ከዚያም በመወልወያ...እንጠርገዋለን ቆሻሻውን ደጋግመን የምንጠርገው ከሆነ ይነጻል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ነገር ግን ደጋግሞ መንጠባጠቡን ይቀጥላል።

ይህ የሚቀጥለው እስከ መቼ ይመስላችኋል? ሰውየው

እስኪሞት ድረስ ይቀጥላል ሰዎች እስከሚሞቱበት ቀን ድረስ ሐጢያትን ያደርጋሉ ለመዳን በኢየሱስ ማመን የሚኖርብን ለዚህ ነው ለመዳን በመጀመሪያ ራሳችንን ማወቅ ያስፈልገናል:: ይህ ነገር እስከ መቼ ድረስ የሚቀጥል ይመስላችኋል? ያ ሰው እስኪሞት ድረስ እንዲሁ እያለ ይቀጥላል:: ሰዎች እስከመሞቻ ቀናቸው ድረስ ኃጥያት መስራታቸውን ይቀጥላሉ:: ለዚህም ነው ምህረት ለማግኘት በኢየሱስ ማመን ያለብን:: ምህረት እንድናገኝ፣ በመጀመሪያ ራሳችንን ማወቅ አለብን::




ከሁለቱ ቆሻሻ የተሞሉ ብርጭቆዎች ጋር ሊነጻጸሩ የሚችሉ ሁለት ሰዎች አሉ እንበል ሁለቱም ብርጭቆዎች በሐጢያት የተሞሉ ናቸው አንዱ ራሱን ተመልክቶ «ኦ! እኔ እንዲህ ያለሁ ሐጢያተኛ ሰው ነኝ» ይላል ከዚያም ተስፋ ይቆርጥና ሊረዳው የሚችል ሰው ለመፈለግ ይሄዳል::

ሌላው ሰው ግን በእርግጥ ክፉ ሰው እንዳልሆነ ያስባል በውስጡ ያለውን የሐጢያት ክምችት ማየት ስለማይችል ብዙም ሐጢያተኛ እንዳልሆነ ያስባል በሕይወት ዘመኑ ሁሉ የተንጠባጠበውን መጥረጉን ይቀጥላል በአንድ ጎን ያለውን ያጸዳል ከዚያም በሌላ ጎን ያለውን ያጸዳል...ወዲያው ደግሞ ወደ ሌላው ወገን ይሄዳል...::

መንጠባበጥን ለማስወገድ ሲሉ በተቻላቸው መጠን ትንሽ

ሐጢያት ለመስራት በመሞከር ሕይወታቸውን በጥንቃቄ የሚኖሩ ብዙ ሰዎች አሉ ነገር ግን አሁንም ደረስ በልባቸው ውስጥ ሐጢያት ስላለባቸው ይህ ምን ጥሩ ነገር ያመጣል? ጠንቃቃ መሆን ወደ ሰማይ አያቀርባቸውም «ጠንቃቃ መሆን» በምትኩ ወደ ሲዖል በሚወስደው ጎዳና ላይ ያስቀምጣቸዋል፡፡

ውድ ወዳጆች «ጠንቃቃ መሆን» የሚመራው ወደ ሲዖል ብቻ ነው ይህንን ትምህርት በልባችን ውስጥ ማኖር ይገባናል ሰዎች ጠንቃቆች ሲሆኑ ሐጢያቶቻቸው ብዙ አይንጠባጠቡ ይሆናል ነገር ግን አሁንም ሐጢያተኞች ናቸው፡፡

በሰው ልብ ውስጥ ምን አለ? ሐጢያት? ብልሹነት? አዎ! ክፉ አሳቦች? አዎ! ስርቆት አለ? አዎ! ዕብሪት? አዎ!

በተለይ እንደዚያ ማድረግ ሳንማር ሐጢያት ስናደርግና ክፉ ነገር ስንሰራ የሐጢያት ክምችቶች የመሆናችንን እውነታ ከማመን በቀር ምንም ማድረግ አንችልም፡፡

ይህ ወጣት ሳለን አይታወቅ ይሆናል ነገር ግን በዕድሜ እየገፋን ስንሄድ እንዴት ነው? ወደ ከፍተኛ ትምህርት ወደ ኮሌጅና ወ.ዘ.ተ ስንገባ በውስጣችን ያለው ነገር ሁሉ ሐጢያት እንደሆነ እንገነዘባለን ይህ እውነት አይደለምን? እውነት ለመናገር ሐጢያተኛ ተፈጥሮዎቻችንን መደበቅ አንችልም ትክክል? ሐጢያትን ከማንጠባጠብ በቀር ማድረግ የምንችለው ነገር የለም ያን ጊዜ «ይህንን ማድረግ አይገባኝም ነበር» በማለት እንጸጸታለን ነገር ግን በእውነት ለመለወጥ አዳጋች ሆኖ እናገኘዋለን ለምን እንደዚህ ይሆናል? ምክንያቱም እያንዳንዳችን የሐጢያት ክምችት ሆነን ስለተወለድን ነው፡፡

ጠንቃቆች በመሆን ብቻ ንጹህ አንሆንም ሙሉ በሙሉ ለመዳን እኛ ማወቅ የሚያስፈልገን የሐጢያት ክምችቶች መሆናችንን ነው መዳን የሚችሉት ኢየሱስ ያዘጋጀውን ቤዛነት በምስጋና የሚቀበሉ ናቸው፡፡

«ብዙ ስህተት አልሰራሁም ወይም በጣም ብዙ ሐጢያት አልሰራሁም» ብለው የሚያስቡ ሰዎች ኢየሱስ ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ እንደወሰደና ለሲዖል የታጩ እንደነበሩ የማያምኑ ናቸው እያንዳንዳችን ከሐጢያት ጋር ስለተወለድን በውስጣችን የሐጢያት ክምችት እንዳለብን ማወቅ ይኖርብናል::

ሰው «ከዚህች ትንሽ ሐጢያት መዳን ብችል ኖሮ ብዙ ስህተት ባልሰራሁ ነበር» ብሎ የሚያስብ ከሆነ በኋላ ላይ ከሐጢያት ነጻ ይሆናልን? ነገሩ ከቶውኑም ይህ ሊሆን አይችልም::

የዳነ ሰው የሐጢያት ክምችት መሆኑን ያውቃል ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጠመቅ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደና ስለ እኛ በሞተ ጊዜም የሐጢያቶችን ደመወዝ እንደከፈለ ከልቡ ያምናል::

ብንድንም ባንድንም ሁላችንም በምናብ ውስጥ ለመኖር ያዘነበልን ነን እኛ የሐጢያት ክምችቶች ነን እንደዚያ ነን ልንድን የምንችለው ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደ ስናምን ብቻ ነው::

## እግዚአብሔር «ቅንጣት ታህል» ኃጢያት ያለባቸውን ሰዎች አልተቤዣቸውም



እግዚአብሄር «ቅንጣት ሐጢያት» ብቻ ያለባቸውን ሰዎች አያድንም እግዚአብሄር «አምላኬ ያለብኝ እኮ ቅንጣት ሐጢያት ነች» የሚሉትንም ቢሆን ትኩረት አያደርግባቸውም እርሱ የሚራራላቸው «አምላኬ ሆይ እኔ የሐጢያት ክምችት ነኝ እባክህ አድነኝ» የሚሉትን ሰዎች ነው «አምላኬ ሆይ አንተ ብታድነኝ እድናለሁ በተደጋጋሚ ሐጢያት ከመስራት መቆጠብ እንደማልችል ስለማውቅ ከእንግዲህ ወዲያ ለንስሐ አልጸልይም እባክህ አድነኝ» የሚሉ ፍጹም ሐጢያተኞች ናቸው::

እግዚአብሄር ሙሉ በሙሉ በእርሱ የሚታመኑትን ያድናቸዋል እኔም ራሴ በየቀኑ የንስሐ ጸሎቶችን ለመጸለይ ሞክሬአለሁ ነገር ግን የንስሐ ጸሎቶች ከቶውኑም ከሐጢያት ነጻ አላወጡኝም ስለዚህ በእግዚአብሄር ፊት ተንበርክኬ «አምላኬ ሆይ እባክህ ራራልኝ ከሐጢያቶቼም ሁሉ አድነኝ» በማለት ጸለይሁ እንዲህ የሚጸልዩ ሰዎች ይድናሉ በእግዚአብሄር ቤዛነትና በአጥማቂው ዮሐንስ በተከናወነው የኢየሱስ ጥምቀት ወደ ማመን ይመጣሉ ይድናሉም::

እግዚአብሄር የሚያድነው ራሳቸውን የሐጢያት ክምችቶች የክፉ አድራጊ ዘሮች አድርገው የሚያውቁትን ሰዎች ብቻ ነው «እኔ የሰራሁት ይህችን ኢምንት ሐጢያት ብቻ ነው እባክህ ለዚህ ሐጢያት ይቅር በለኝ» የሚሉ ሰዎች አሁንም ድረስ ሐጢያተኞች ስለሆኑ እግዚአብሄር ሊያድናቸው አይችልም እግዚአብሄር የሚያድናቸው ፍጹም የሐጢያት ክምችቶች መሆናቸውን የሚያምኑትን ሰዎች ብቻ ነው::

በኢሳይያስ **59:1-2** ላይ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል *«እነሆ የእግዚአብሔር እጅም ከማዳን አላቋረጠችም፣ ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም፣ ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፣ እንዳይሰማም ኃጢያታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል::»*

እኛ የሐጢያት ክምችቶች ሆነን ስለተወለድን እግዚአብሄር በፍቅር ሊመለከተን አይችልም ይህ የሆነበት ምክንያት እጁ ስላጠረች ጆሮው ስለከበደች ወይም ይቅርታውን ስንጠይቀው ሊሰማን ስለማይችል አይደለም።

እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ይነግረናል፡- *«ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፣ እንዳይሰማም ኃጢያታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል»* በልቦቻችን ውስጥ ብዙ ኃጢያት ስላለ በሮቹ ምንም ያህል ወለል ብለው ቢከፈቱም ሰማይ ልንገባ አንችልም።

እኛ የሐጢያት ክምችቶች የሆንን ሰዎች ሐጢያት በሰራን ቁጥር ይቅርታን ብንጠይቅ እግዚአብሄር ልጁን በተደጋጋሚ መግደል ሊኖርበት ነው እግዚአብሔርም ይህን ለማድረግ አይፈልግም እርሱ እንዲህ ብሎዋል «በየቀኑ ሐጢያቶቻችሁን ይዛችሁ ወደ እኔ አትምጡ ከሐጢያቶቻችሁ ሁሉ ያድናችሁ ዘንድ ልጄን ልኬላችኋለሁ እናንተ መረዳት የሚገባችሁ ነገር ቢኖር እርሱ ሐጢያቶቻችሁን መውሰዱንና ያም እውነት መሆኑን መቀበል ብቻ ነው ከዚያም ለመዳን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እመኑ እኔ ለእናንተ ለፍጡራኖቼ የሰጠኋችሁ እጅግ ታላቁ ፍቅር ይህ ነው።»

የነገረን ይህንን ነው «በልጄ እመኑና የሐጢያቶቻችሁንም ስርየት ተቀበሉ እኔ የእናንተ አምላክ ለሐጢያቶቻችሁና ለበደሎቻችሁ ስርየት የገዛ ልጄን ላክሁ በልጄ አምናችሁ ዳኑ።»

ራሳቸውን የሐጢያት ክምችቶች እንደሆኑ አድርገው የማያውቁ ሰዎች ለእያንዳንዱ ትንሽ ሐጢያታቸው የእርሱን ይቅርታ ይጠይቃሉ የሐጢያቶቻቸውን አስከፊ ክብደት ሳያውቁ በፊቱ ቀርበው «እባክህ ይህችን ትንሽ ሐጢያት ይቅር በለኝ ከእንግዲህ ወዲህ ይህችን ሐጢያት አልሰራም» ብለው ይጸልያሉ።

እግዚአብሄርን በእነዚህ ጸሎቶች ሊያታልሉትም ይሞክራሉ እኛ ሐጢያት የምንሰራው አንድ ጊዜ ብቻ አይደለም ነገር ግን እስክንሞት ድረስ በየጊዜው ሐጢያት እንሰራለን እስከ መጨረሻው የሕይወታችን ቀን ድረስ ይቅርታን በመጠየቅ እንቀጥላለን ምክንያቱም ሐጢያት መስራትን ማቆም አንችልምና ስጋችንም እስክንሞት ድረስ የሐጢያትን ሕግ ያገለግላልና፡፡

ለአንዲት ትንሽ ሐጢያት ይቅርታን ማግኘት የሐጢያትን ችግር አይፈታም ምክንያቱም በየቀኑ በርካታ ሐጢያቶችን እንሰራለንና ስለዚህ ከሐጢያት ነጻ መሆን የምንችልበት ብቸኛ ው መንገድ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወደ ኢየሱስ ማስተላለፍ ነው፡፡

*የሰው ተፈጥሮ ምንድን ነው?*

*የኃጢያቶች ክምችት ነው፡፡*

መጽሐፍ ቅዱስ የሰዎችን ኃጢያቶች ይዘረዝራል *«እጃችሁ በደም፣ ጣታችሁም በበደል ረክሳለች፣ ከንፈራችሁም ሐሰትን ተናግሯል፣ ምላሳችሁም ኃጢያትን አሰምቷል፡፡ በጽድቅም የሚጠራ በእውነትም የሚፈርድ የለም፣ በምናምንቴ ነገር ታምነዋል ሃሰትንም ተናግረዋል፣ ጉዳትን ጸንሰዋል በደልንም ወልደዋል፡፡ የእባብን እንቁላል ቀፈቀፉ፣ የሸረሪትንም ድር አደሩ፣ እንቁላላቸውንም የሚበላ ሰው ይሞታል፣ እንቁላሉም ሲሰበር እፉኝት ይወጣል፡፡ ድሮቻቸውም ልብስ አይሆኑላቸውም፣ በስራቸውም አይሸፈኑም፣ ስራቸውም የበደል*

*ሥራ ነው፣ የግፍም ሥራ በእጃቸው ነው:: እግሮቻቸው ወደ ክፋት ይሮጣሉ፣ የንጹሑውን ደም ለማፍሰስ ይፈጥናሉ፣ አሳባቸው የኃጢያት አሳብ ነው:: ጉስቁልናና ቅጥቃጤ በመንገዳቸው አለ:: የሰላምን መንገድ አያውቁም፣ በአካሄዳቸውም ፍርድ የለም:: መንገዳቸውንም አጣመዋል፣ የሚሄድባትም ሁሉ ሰላምን አያውቅም::» (ኢሳይያስ 59:3-8)*

የሰዎች ጣቶች በበደል ረክሰዋል በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የሚያደርጉትም ነገር ሐጢያት ነው እነርሱ የሚያደርጉት ነገር ሁሉ ክፉ ነው ከንፈራችንም *«ሐሰትን ተናግሮዋል»* ከአፋችን የሚወጡት ነገሮች ሁሉ ውሸቶች ናቸው::

*«ዲያብሎስ ሃሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል» (ዮሐንስ 8:44)* ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች «የምነግርህ እውነቱን ነው...በእርግጠኝነት እየነገርሁህ ነው የምናገረው እውነት ነው...» ማለት ይወዳሉ ነገር ግን እነርሱ የሚናገሩት ሁሉ ውሸት ነው እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈው ነው «ዲያብሎስ ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል::»

ሰዎች በባዶ ቃሎች ታምነው ውሸቶችን ይናገራሉ ሰዎች ክፋትን ጸንሰው በደልን ይወልዳሉ የእባብን እንቁላሎች ቀፍቅፈዋል የሸረሪት ድሮችንም አድርተዋል እግዚአብሄር እንዲህ ይላል *«እንቁላላቸውንም የሚበላ ሰው ይሞታል፣ እንቁላሉም ሲሰበር እፉኝት ይወጣል»* በልባችሁ ውስጥ የእባብ እንቁላሎች እንዳለ ይናገራል የእባብ እንቁላሎች! በልባችሁ ውስጥ ክፋት አለ በውሃውና በደሙ ወንጌል በማመን መዳን የሚኖርብን ለዚህ ነው::

ስለ እግዚአብሄር መናገር በምጀምርበት ጊዜ ሁሉ «ኦ ውዴ እባክህ ስለ እግዚአብሄር አትንገረኝ አንድ ነገር ለማድረግ በምሞክርበት ጊዜ ሁሉ ሐጢያት ከውስጤ ይንጠባጠባል እንደ ጎርፍ ይፈስሳል በየቦታው ሐጢያት ሳላንጠባጥብ አንዲት

እርምጃ አልራመድም ምንም ላደርገው አልችልም እኔ እጅግ በሐጢያት ተሞልቻለሁ ተስፋ የለኝም ስለዚህ ቅዱስ ስለሆነው አምላክ አትንገረኝ» የሚሉ ሰዎች አሉ፡፡

ይህ ሰው የሐጢያት ክምችት እንደሆነ በእርግጠኝነት አውቋል እግዚአብሄር በፍቅሩ ወንጌል አማካይነት ሙሉ በሙሉ እንዳዳነው ግን አያውቅም መዳን የሚችሉት ራሳቸውን የሐጢያት ክምችቶች እንደሆኑ አድርገው የሚያውቁ ሰዎች ናቸው፡፡

ሁሉም ሰው እንደዚያ መሆኑ እውነት ነው ሁሉም ሰው በየሄደበት ስፍራ ሁሉ ያለ ማቋረጥ ሐጢያትን ያንጠባጥባል ሰዎች ሁሉ የሐጢያት ክምችቶች ስለሆኑ ሐጢያት እንደ ጎርፍ ይፈስሳል እኛ እንደዚህ ካለው ኑሮ መዳን የምንችልበት ብቸኛው መንገድ የእግዚአብሄር ሐይል ነው ይህ የሚያስገርም አይደለምን? በተበሳጩ ወይም በተመቻቸው ቁጥር ሐጢያትን የሚያንጠባጥቡ ሰዎች መዳን የሚችሉት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ብቻ ነው ኢየሱስ የመጣው እኛን ለማዳን ነው፡፡

እርሱ ሐጢያቶቻችን በሙሉ ፈጽሞ ደምስሶዋቸዋል የሐጢያት ክምችቶች መሆናችሁን አምናችሁ ዳኑ፡፡ እርሱም የሁላችንንም ኃጢያት አውጥቶልናል፡፡ የኃጢያት ክምር መሆናሁን እመኑና ዳኑ፡፡ ✉

# ስብከት 3

## ነገሮችን በሕጉ መሰረት

## ብናደርግ ሕጉ ሊያድነን

## ይችላልን?

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::




**ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር** (www.amazon.com) **በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።**

# ነገሮችን በሕጉ መሰረት ብናደርግ ሕጉ ሊያድነን ይችላልን?

**« ሉቃስ 10:25-30 »**

**«እነሆም:- አንድ አዋቂ ሊፈትነው ተነስቶ:- መምህር ሆይ፣ የዘላለምን ህይወት እንድወርስ ምን ላድርግ? አለው:: እርሱም በህግ የተጻፈው ምንድር ነው? እንዴትስ ታነባለህ? አለው:: እርሱም መልሶ:- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፣ ባልንጀራህንም እንደራስህ ውደድ አለው:: ኢየሱስም:- እውነት መለስህ፣ ይህን አድርግ በሕይወትም ትኖራለህ አለው:: እርሱ ግን ራሱን ሊያጸድቅ ወድዶ፣ ኢየሱስን:- ባልንጀራዬስ ማነው? አለው:: ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ:- አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ በወንበዴዎች እጅም ወደቀ:: እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም በህይወትና በሞት መካከልም ጥለውት ሄዱ::»**

*የሰዎች እጅግ ትልቁ ችግር ምንድን ነው?*

*በብዙ የተሳሳቱ ውዥንብሮች ውስጥ መኖራቸው ነው::*

**ሉቃስ 10:28** *«ይህን አድርግ በህይወትም ትኖራለህ::»*

ሰዎች በብዙ የተሳሳቱ ውዥንብሮች ውስጥ ይኖራሉ በተለይ በዚህ ረገድ የተጋለጡ ይመስላል አዋቂዎች ይመስላሉ ነገር ግን በቀላሉ ይታለላሉ ክፉ ጎኖቻቸውንም አያውቁዋቸውም የተወለድነው ራሳችንን ሳናውቅ ነው ነገር ግን አሁንም ድረስ ራሳችንን እንደምናውቅ ሆነን እንኖራለን ሰዎች ራሳቸውን ስለማያውቁ መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ሐጢያተኞች እንደሆንን ይነግረናል::

ሰዎች ስለ ሐጢያቶቻቸው ኑባሬነት ይናገራሉ ሰዎች ጥሩ ነገር ማድረግ ያቃታቸው ይመስላል ነገር ግን ራሳቸውን ጥሩ ሰው አድርገው ለመግለጥ ያዘነብላሉ በአንደበታቸው ሐጢያተኞች እንደሆኑ ቢናገሩም ስለ በጎ ስራዎቻቸውና ስለ ምግባራቸው ይመጻደቃሉ::

በውስጣቸው ምንም መልካም ነገርም ሆነ መልካም የማድረግ አቅም እንደሌላቸው አያውቁም ስለዚህ ሌሎችን ለማታለል ይሞክራሉ አንዳንድ ጊዜም ራሳቸውን ያታልላሉ «ፈጽሞ ክፉዎች ልንሆን አንችልም በውስጣችን አንድ ጥሩ ነገር መኖር አለበት::»

ስለዚህ ሌሎችን ተመልክተው ለራሳቸው «ያንን ባያደርግ እመኛለሁ ባያደርገው ጥሩ ይሆንለት ነበር እንደዚህ ተናግሮ ቢሆን ኖሮ ጥሩ ይሆንለት ነበር ወንጌልን በዚህና በዚህ መንገድ ቢሰብክ የሚሻለው ይመስለኛል ከእኔ በፊት የዳነው እርሱ ነው ልክ እንደዳነ ሰው መንቀሳቀስ ይገባው ነበር እኔ የዳንኩት በቅርቡ ነው ነገር ግን ብዙ ብማር ኖሮ ከእርሱ ይበልጥ ብዙ የተሻለ ነገር አደርግ ነበር» ይላሉ::

እነርሱ በተጎዱ ጊዜ ሁሉ በልባቸው ቢላዋ ይስላሉ «ጠብቅ ብቻ እኔ እንዳንተ እንዳልሆንኩ ታያለህ አሁን ከእኔ የቀደምህ መስሎ ይሰማህ ይሆናል ነገር ግን ጠብቅ ብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኋለኞች ፊተኞች ይሆናሉ ተብሎ ተጽፎዋል ይህ እኔን

እንደሚመለከት አውቃለሁ ጠብቅ አሳይሃለሁ» ሰዎች ራሳቸውን ያታልላሉ።

እርሱ በሌላው ሰው ቦታ ቢሆን ኖሮ በተመሳሳይ መንገድ ምላሽ ቢሰጥም አሁንም ይፈርዳል ምስባክ ላይ ሲቆም ስለ ለበሰው ልብስ አብዝቶ ስለሚያስብ ድንገት ሲኮላተፍ ራሱን ያገኘዋል ሰዎች ጥሩ ነገር የማድረግ አቅም እንዳላቸው ሲጠየቁ አብዛኞቹ ሰዎች በአንደበታቸው እንደሌላቸው ይናገራሉ በልባቸው ግን እነርሱ ራሳቸው አቅሙ እንዳላቸው ይቀባዥራሉ ስለዚህ እስኪሞቱ ድረስ ሰናይ ለመሆን አብዝተው ይሞክራሉ።

እነርሱ በልባቸው ውስጥ «በጎነት» እንዳለና በጎ ነገር የማድረግ አቅም እንዳላቸው ያስባሉ እነርሱ ራሳቸው ጥሩዎች እንደሆኑም ያምናሉ ምንም ያህል ለረጅም ጊዜ ሐይማኖተኞች ሆነው ቢቆዩም በተለይ በእግዚአብሄር አገልግሎት ውስጥ ትልቅ እመርታ ላይ በደረሱት ሰዎች መካከል «እኔ ለጌታ ይህንንና ያንን ማድረግ እችላለሁ» ብለው የሚያስቡ አሉ።

ነገር ግን ጌታን ከሕይወታችን ካስወጣነው በእርግጥ ጥሩ ነገር ማድረግ እንችላለን? በሰዎች ውስጥ ጥሩ ነገር አለ? በጎ ስራዎችን እያደረግን በእርግጠኝነት መኖር እንችላለን? ሰዎች በጎ ነገር የማድረግ አቅም የላቸውም ነገሮችን በራሳቸው መንገድ ለማድረግ በሞከሩ ቁጥር ሐጢያት ይሰራሉ አንዳንዶች በኢየሱስ ካመኑ በኋላ በራሳቸው ጥረት ጥሩዎች ለመሆን ሲሞክሩ ኢየሱስን ገለል ያደርጉታል በሁላችን ውስጥ ያለው ክፋት ነው ስለዚህ የምንተገብረውም ክፋትን ብቻ ነው በራሳችን (የዳኑትም ቢሆኑ) ልናደርግ የምንችለው ነገር ሐጢያትን ብቻ ነው ይህ የስጋችን ተጨባጭ ሁኔታ ነው።

*እኛ ሁልጊዜ የምንሰራው*
*በጎ ነገር ነው ወይስ ክፋት?*

*ክፋት::*

«የኢየሱስን ስም አመስግኑ» በሚለው የመዝሙር መጽሐፋችን ውስጥ እንዲህ የሚል መዝሙር አለ «♪ያለ ኢየሱስ ተሰናክለን እንወድቃለን እኛ ባህርን ያለ መቅዘፊያ እንደምታቋርጥ መርከብ ዋጋ ቢሶች ነን ♪» ከኢየሱስ ውጭ ከሆንን መስራት የምንችለው ሐጢያትን ብቻ ነው ምክንያቱም ክፉዎች ነንና የጽድቅ ስራዎችን የመስራት አቅም የሚኖረን ከዳንን በኋላ ብቻ ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሎዋል *«የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና፣ ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም» (ሮሜ 7:19)* ሰው ከኢየሱስ ጋር ከሆነ አሳሳቢ አይደለም ነገር ግን ከኢየሱስ ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር ከሌለ በእግዚአብሄር ፊት በጎ ምግባሮችን ለማድረግ ይሞክራል ነገር ግን ሰውየው ብዙ በሞከረ ቁጥር ይበልጥ ክፋትን ያደርጋል::

ንጉስ ዳዊትም እንደዚሁ ተመሳሳይ የሆነ የውርስ ተፈጥሮ ነበረው አገሪቱ ሰላማዊና የለማች በሆነች ጊዜ አንድ ምሽት በሰገነቱ ላይ ለመንሸራሸር ወጣ እዚያም አንድ ፈታኝ ምስል አየና በፍትወት ደስታ ወደቀ ጌታን በረሳ ጊዜ ምን ይመስል ነበር? በእርግጥም ክፉ ሰው ሆኖ ነበር ከቤርሳቤህ ጋር አመነዘረ ባልዋን ኦርዮንንም አስገደለ ነገር ግን በራሱ ውስጥ ያለውን ክፋት ማየት አልቻለም በፋንታው ለድርጊቶቹ ማማኻኛዎችን አቀረበ::

አንድ ቀን ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ መጥቶ እንዲህ አለው *«እግዚአብሔርም ናታንን ወደ ዳዊት ላከ፣ ወደ እርሱም መጥቶ አለው:- በአንድ ከተማ አንዱ ባለጠጋ፣ አንዱም ድሃ የሆኑ ሁለት ሰዎች ነበሩ:: ባለጠጋውም እጅግ ብዙ በግና ላም ነበረው:: ለድሃው ግን ከገዛት አንዲት ታናሽ በግ በቀር አንዳች አልነበረውም:: አሳደጋትም፣ ከልጆቹም ጋር በእርሱ ዘንድ አደገች እንጀራውንም ትበላ፣ ከዋንጫውም ትጠጣ፣ በብብቱም ትተኛ ነበር፣ እንደልጁም ነበረች:: ወደ ባለጠጋውም እንግዳ በመጣ ጊዜ ከበጉና ከላሙ ወስዶ ለዚያ ወደእርሱ ለመጣው እንግዳ ያዘጋጅለት ዘንድ ሳሳ፣ የዚያንም የድሃውን ሰው በግ ወስዶ ለዚያ ለመጣው ሰው አዘጋጀ::» (2ኛ ሳሙኤል 12:1-4)*

ዳዊትም *«ይህን ያደረገው ሰው በእርግጠኝነት መሞት አለበት!»* አለ እጅግም ተቆጣ ስለዚህም እንዲህ አለ «እርሱ የራሱ የሆኑ ብዙ እያሉት ከእነርሱ መውሰድ ይችል ነበር ነገር ግን ለእንግዳው ማዕድን ለማቅረብ ሲል የደሃውን ሰው ጠቦት ወሰደ እርሱ መሞት ይገባዋል!» ያን ጊዜ ናታን እንዲህ አለው *«ያ ሰው አንተ ነህ»* ኢየሱስን ካልተከተልነውና አብረነው ካልሆንን ዳግም የተወለዱትም ቢሆኑ እነዚህን ክፉ ነገሮች ሊያደርጉ ይችላሉ::

ነገሩ ለሰው ሁሉ ለታማኞቹም ሳይቀር ተመሳሳይ ነው ከኢየሱስ ውጭ ከሆንን ሁልጊዜም እንሰናከላለን ክፋትንም እናደርጋለን በውስጣችን ክፋት ቢኖርም ኢየሱስ ስላዳነን ዛሬም እንደገና እናመሰግነዋለን *«♪ከመስቀሉ ጥላ ስር ማረፍ እፈልጋለሁ♪»* ልቦቻችን በክርስቶስ የቤዛነት ጥላ ስር ያርፋሉ ነገር ግን ከጥላው ወጥተን ራሳችንን የምንመለከት ከሆንን ፈጽሞ ማረፍ አንችልም::

# እግዚአብሔር በሕጉ ፊት የእምነትን ጽድቅ ሰጥቶናል

*ከእምነትና ከሕግ ቀዳሚው የትኛው ነው?*

*እምነት ነው።*

ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሄር ከመጀመሪያውም የእምነትን ጽድቅ እንደሰጠን ተናግሮዋል ይህንኑ ለአዳምና ለሔዋን ለአቤልና ለቃየን ለሴትና ለሔኖክ ለኖህ ለአብርሃም ለይስሐቅ በመጨረሻም ለያዕቆብና ለአስራ ሁለቱ ልጆቹ ሰጥቶዋቸዋል ሕግ ሳይኖር እንኳን ከቃሉ ውስጥ በተገኘው የእምነት ጽድቅ አማካይነት በእግዚአብሄር ፊት ጻድቀዋል በቃሉ ላይ ባላቸው እምነት አማካይነት ተባርከው ዕረፍትን አግኝተዋል።

ዘመናት አለፉ የያዕቆብ ዘሮችም በዮሴፍ ምክንያት ለ400 አመታቶች ባሪያዎች ሆነው በግብጽ ኖሩ ከዚያም እግዚአብሄር በሙሴ አማካይነት ወደ ከንአን ምድር መራቸው ነገር ግን በ400 የባርነት አመታት ወቅት የእምነትን ጽድቅ ረሱ።

ስለዚህ እግዚአብሄር በሰራው ተአምር ቀይ ባህርን አሻገራቸው ወደ ምድረ በዳም መራቸው ወደ ሲን ምድረ በዳ ሲደርሱም በሲና ተራራ ሕግን ሰጣቸው አስርቱን ትዕዛዛትና 613 ዝርዝር አንቀጾችን የያዘውን ሕግ ሰጣቸው *«እኔ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔር ነኝ ሙሴ ወደ ሲና ተራራ ይምጣ ሕጉንም እሰጣችኋለሁ»* ከዚያም ለእስራኤል ህዝብ ህግን ሰጠ።

*«ሐጢያትን እንዲያውቁ» (ሮሜ 3:20)* ሕጉን ሰጣቸው

ይህን ያደረገው ምን እንደሚወድና ምን እንደሚጠላ እንደዚሁም ጽድቁንና ቅድስናውን ሊያስታውቃቸው ነው፡፡

ለ400 አመታቶች በግብጽ ባሪያዎች የነበሩ የእስራኤል ሕዝብ በሙሉ ቀይ ባህርን ተሻገሩ እነርሱ የአብርሃምን አምላክ የይስሐቅን አምላክና የያዕቆብን አምላክ ከቶውንም አልተገናኘ ተም አላወቁትምም፡፡

በእነዚያ 400 አመታቶች ባሮች ሆነው ሲኖሩ ሳሉ የእግዚአብሄርን ጽድቅ ረስተው ነበር በወቅቱ መሪ አልነበራቸውም መሪዎቻቸው ያዕቆብና ዮሴፍ ነበሩ እነርሱ ግን ከረጅም ጊዜ በፊት ሞተዋል ዮሴፍ እምነቱን ለልጆቹ ለምናሴና ለኤፍሬም ማስተላለፍ ተስኖታል፡፡

ስለዚህ ጽድቁን ስለረሱ ጌታቸውን እንደገና ፈልገው ማግኘ ት አስፈለጋቸው እግዚአብሄር አስቀድሞ የእምነትን ጽድቅ ከዚያም ሕጉን የሰጣቸው እምነታቸውን ከረሱ በኋላ እንደነበር በአእምሮዋችን መያዝ ይኖርብናል ሕጉን የሰጣቸው ወደ እርሱ እንዲመለሱ ነበር፡፡

እርሱ እስራኤልን ለማዳንና የራሱ ሕዝቦች ለማድረግ እንዲገረዙ ነገራቸው፡፡

እነርሱን የጠራበት አላማ ሕጉን በማጽናት እየኖረ እንዳለ እንዲያውቁና ሁለተኛም በፊቱ ሐጢያተኞች እንደነበሩ እንዲያውቁ ነው እግዚአብሄር በሰጣቸው የመስዋዕት ስርአት አማካይነት ድነው ወደፊቱ እንዲቀርቡና የእርሱ ሕዝቦች እንዲሆኑ ፈለገ የራሱ ሕዝብም አደረጋቸው፡፡

የእስራኤል ሕዝብ የዳነው በሚመጣው መሲህ በማመን በሕጉ የመስዋዕት ስርአት በኩል ነበር ነገር ግን የመስዋዕቱ ሕግም በጊዜ ሒደት ውስጥ ደብዝዞ ነበር ያ መቼ እንደሆነ እንመልከት፡፡

በሉቃስ ወንጌል 10፡25 ላይ ኢየሱስን የፈተነ አንድ ሕግ

አዋቂ ተጠቅሶዋል ይህ ሕግ አዋቂ ፈሪሳዊ ነበር ፈሪሳውያን በእግዚአብሄር ቃል ለመኖር የሚጥሩ ከልክ በላይ ወግ አጥባቂ ሰዎች ነበሩ በመጀመሪያ አገራቸውን ለመጠበቅ ከዚያም በእግዚአብሄር ሕግ ለመኖር ሞክረዋል እስራኤልን ከሮም ነጻ የማውጣት ራዕያቸውን ለማሳካት ሲሉ በስሜት የሚነዱና አመጽን ወደ ማድረግ የሚያዘነብሉ ቀናተኞችም ደግሞ ነበሩ፡፡




ዛሬም እነርሱን የሚመስሉ አንዳንድ የሐይማኖት ሰዎች አሉ እነርሱ «የአለምን ጭቁን ሕዝቦች አድኑ» በሚሉ መፈክሮች ማሕበራዊ እንቅስቃሴዎችን ይመራሉ እነርሱ ኢየሱስ የመጣው ድሆችንና ጭቁኖችን ለማዳን እንደሆነ ያምናሉ ስለዚህ በሴሚናሪዎች ውስጥ የስነ መለኮትን ትምህርት ከተማሩ በኋላ በፖለቲካ ውስጥ ይሳተፋሉ በእያንዳንዱ የማህበራዊ መስክ «የተጨቆኑትን ለማዳን» ይሞክራሉ፡፡

እነርሱ «ሁላችንም በቅዱሱና በደጉ ሕግ እንኑር...በሕጉ በእርሱ ቃሎች እንኑር» ይላሉ ነገር ግን የሕጉን ትክክለኛ ትርጉም አይረዱትም የሕጉን መለኮታዊ መገለጥ ሳይገነዘቡ በሕጉ ፊደል ለመኖር ይሞክራሉ፡፡

ስለዚህ ከክርስቶስ በፊት ለ400 አመታቶች በእስራኤል ነቢያቶች የእግዚአብሄር አገልጋዮች አልነበሩም ማለት እንችላለን

ከዚህ የተነሳ እረኛ የሌላቸው የበጎች መንጋ ሆኑ::

እነርሱ ሕግም ሆነ እውነተኛ መሪ አልነበራቸውም እግዚአብሄርም በወቅቱ በነበሩት ግብዝ የሐይማኖት መሪዎች በኩል ራሱን አልገለጠም አገሪቱም የሮም መንግስት ቅኝ ግዛት ሆነች ስለዚህ ኢየሱስ በምድረ በዳ ሲከተሉት ለነበሩት ለእነዚያ የእስራኤል ልጆች ተርበው እንደማይሰዳቸው ነገራቸው በወቅቱ ይሰቃዩ የነበሩት ብዙዎች ስለነበሩ እረኛ ለሌላቸው መንጎች ራራላቸው::

እንዲህ ባሉ ስልጣኖች ላይ የተቀመጡ ሕግ አዋቂዎችና ሌሎች መብቶች የነበሩዋቸው ሰዎች ነበሩ ፈሪሳውያን ከወግ አጥባቂው የይሁዲነት የዘር ግንድ የሚመደቡ ነበሩ በጣም ኩሩዎች ነበሩ::

ይህ ሕግ አዋቂ በሉቃስ 10:25 ላይ ኢየሱስን እንዲህ ሲል ጠየቀው *«የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ?»* በእስራኤል መካከል ከእርሱ የተሻለ ሰው እንዳልነበር ያሰበ ይመስላል ስለዚህ ይህ የሕግ አዋቂ (ቤዛነትን ያላገኘ ሰው) ኢየሱስን «የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ?» በማለት ተገዳደረው::

የሕግ አዋቂው የእኛ ነጸብራቅ ነው ኢየሱስን እንዲህ ሲል ጠየቀው *«የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ?»* ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት *«በሕግ የተጻፈው ምንድነው? እንዴትስ ታነባለህ?»*

እርሱም እንዲህ ሲል መለሰ *«ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፣ ባለንጀራህንም እንደራስህ ውደድ አለው::»*

ኢየሱስም መልሶ:- *«እውነት መለስህ፣ ይህን አድርገህ በሕይወትም ትኖራለህ አለው::»*

ፈጽሞ ጥሩ ነገር ማድረግ የማይችል የሐጢያት ክምር

ክፉ ሰው መሆኑን ሳያውቅ ኢየሱስን ተገዳደረው ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ጠየቀው ስለዚህም ኢየሱስ *«በህግ የተጻፈው ምንድር ነው? እንዴትስ ታነባለህ? አለው::»*

*በሕግ የተጻፈውን የምታነቡት*
*እንዴት ነው?*

*እኛ ሕጉን ልንጠብቅ የማንችል*
*ኃጢያተኞች ነን::*

*«እንዴትስ ታነባለህ?»* ኢየሱስ በዚህ ምንባብ ሰው እናንተንና እኔን ጨምሮ ሕጉን እንዴት እንደሚያውቅና እንደሚረዳ ይጠይቃል::

በዚህ ዘመን ብዙ ሰዎች እንደሚያደርጉት ይህም የሕግ አዋቂ እንደዚሁ እግዚአብሄር ሕጉን የሰጠው እንዲጠብቀው እንደነበር አሰበ ስለዚህ እንዲህ ሲል መለሰ *«ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፣ ባለንጀራህንም እንደራስህ ውደድ አለው::»*

ሕጉ እንከን የለበትም እርሱ የሰጠን ፍጹም ሕግ ነው ጌታን በፍጹም ልባችን በፍጹም ነፍሳችን በፍጹም ሐይላችንና በፍጹም አሳባችን እንድንወደውና ባልጀራዎቻችንም እንደ ራሳችን እንድንወዳቸው ነግሮናል አምላካችንን በፍጹም ልባችንና ሐይላችን መውደዳችን ትክክል ነው ነገር ግን ይህ ፈጽሞ ሊጠበቅ የማይችል ቅዱስ ትዕዛዝ ነው::

*«እንዴትስ ታነባለህ?»* ማለት ሕጉ ትክክል ነው አንተ ግን እንዴት ትረዳዋለህ? ማለት ነው ሕግ አዋቂው እግዚአብሄር ሕጉን የሰጠው እንዲታዘዘው እንደሆነ አሰበ ነገር ግን

የእግዚአብሔር ሕግ የተሰጠን በደሎቻችንን ሙሉ በሙሉ በማጋለጥ ጉድለቶቻችንን መገንዘብ እንችል ዘንድ ነው «ሐጢያት ሰርታችኋል አትግደሉ ስላችሁ ገድላችኋል ለምን አመጻችሁብኝ?»

ሕጉ በሰዎች ልቦች ውስጥ ያሉትን ሐጢያቶች ያጋልጣል ወደዚህ እየመጣሁ ሳለሁ በአንድ እርሻ ላይ የበሰሉ ሃብ ሃቦችን አየሁ እንበል እግዚአብሔር በሕጉ መሰረት «እነዚህን ሃብ ሃቦች ቀጥፈህ እንዳትበላ እንደዚያ ካደረግህ ታዋርደኛለህ» ብሎ አስጠንቅቆኛል «አዎ አባት ሆይ» «እርሻው የአቶ እከሌና እከሌ ስለሆነ ፈጽሞ መቅጠፍ አይገባህም» «አዎ አባት ሆይ፡፡»

ፈጽሞ መቅጠፍ እንደሌለብን በሰማን ቅጽበት የመቅጠፍ ዝንባሌ ይሰማናል አንድን ስፕሪንግ ወደታች ብንወጥረው ተመልሶ ይነጥራል የሰዎችም ሐጢያቶች ልክ እንደዚህ ናቸው፡፡

እግዚአብሔር ፈጽሞ ክፉ ምግባሮችን ማድረግ እንደሌለብን ነግሮናል እግዚአብሔር ቅዱስ ፍጹምና ያንን የማድረግ አቅም ያለው ስለሆነ እንደዚያ ማለት ይችላል በሌላ በኩል እኛ «ፈጽሞ» ሐጢያት አለመስራት አንችልም «ፈጽሞ» ሙሉ በሙሉ ጥሩዎች መሆን አንችልም በልባችን ውስጥም «ፈጽሞ» ጥሩ ነገር የለም ለምን? ምክንያቱም ሰዎች በልቦቻቸው ውስጥ ፍትወቶች አሉባቸውና ፍትወቶቻችንን ከመተግበር ውጭ ልናደርግ የምንችለው ነገር የለም የምናመነዝረው በልቦቻችን ውስጥ ምንዝርና ስላለ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ማንበብ አለብን በመጀመሪያ ሙከራዬ ቃሉን ከፊደሉ ጋር አገናዘብኩ ኢየሱስ ለእኔ በመስቀል ላይ እንደሞተ አንብቤ እንባዎቼን መቆጣጠር አልቻልኩም እኔ እንዲህ ያለሁ ክፉ ሰው ነበርሁ እርሱም ለእኔ በመስቀል ላይ ሞተልኝ...ልቤ ክፉኛ ስለቆሰለ በእርሱ አመንሁ ከዚያም እንዲህ

ብዬ አሰብሁ «ማመን የሚኖርብኝ ከሆነ በቃሉ መሰረት አምናለሁ::»

ዘጸአት 20ን ሳነብ እንዲህ ይላል «በፊቴ ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» በዚህ ትዕዛዝ መሰረት የንስሐ ጸሎት ጸለይሁ በፊቴ ሌሎች አማልክቶች የነበሩ ስለመሆናቸው ስሙን በከንቱ ጠርቼ እንደሆነ ወይም ለሌሎች አማልክቶች ሰግጄ እንደሆነ ለማስታወስ አእምሮዬን ፈተሽሁ ለቅድመ አያቶቼ ክብር በሚደረጉ ስርአቶች ወቅት ብዙ ጊዜ ለሌሎች አማልክቶች እንደሰገድሁ ተገነዘብሁ ሌሎች አማልክቶችን የመቆራኘት ሐጢያት ሰርቼ ነበር::

ስለዚህ «ጌታ ሆይ ለጣዖታት ሰግጃለሁ ለዚህም ፍርድ ይገባኛል እባክህ ሐጢያቶቼን ይቅር በለኝ ደግሜ ከቶውንም እንዲህ አላደርግም» የሚል የንስሐ ጸሎት ጸለይሁ ከዚያ በኋላ አንድ ሐጢያት የተወገደ መሰለኝ::

በመቀጠል ስሙን በከንቱ የጠራሁበት ጊዜ ይኖር እንደሆነ ለማስታወስ ሞከርሁ ያን ጊዜ ለመጀመሪያ ጊዜ በእግዚአብሄር ማመን ስጀምር አጨስ እንደነበር አስታወስሁ ጓደኞቼ «ሲጋራ በማጨስ እግዚአብሄርን እያዋረድከው አይደለምን? ክርስቲያን እንዴት ያጨሳል?» ብለው ነገሩኝ::

ይህ ስሙን በከንቱ ከመጥራት ጋር ተመሳሳይ ነው አይደል? ስለዚህ ደግሜ እንዲህ ስል ጸለይሁ «ጌታ ሆይ ስምህን በከንቱ ጠርቻለሁ እባክህ ይቅር በለኝ ማጨስ አቆማለሁ» ስለዚህ ሲጋራ ማጨስን ለማቆም ሞከርሁ ነገር ግን ለአመት ያህል ገባ ወጣ እያልሁ ማጨሴን ቀጠልሁ ሲጋራ ማጨስ ማቆም በእርግጥም አስቸጋሪ እንዲያውም አዳጋች ነበር በመጨረሻ ግን ሙሉ በሙሉ ሲጋራ ማጨስ አቆምሁ ሌላ ሐጢያት እንደተወገደ ታወቀኝ::

ቀጣዩ *«የሰንበትን ቀን ቀድሰው»* የሚለው ነበር ይህ ማለት

በየእሁዶቹ ሌሎችን ነገሮችን ማድረግ ወይም ገንዘብ ማግኘት አይገባኝም ማለት ነው...ያንንም ደግሞ አቆምሁ፡፡

«አባትህንና እናትህን አክብር» የሚል ደግሞ ነበር ርቄ ሳለሁ ላከብራቸው ችዬ ነበር ቅርባቸው መሆኔ ግን የበሽታ ምንጭ ነበር «ኦ እንዴት ያለ ነገር ነው በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያት ሰርቻለሁ ጌታ ሆይ እባክህ ይቅር በለኝ» የንስሐ ጸሎት ጸለይሁ፡፡

ነገር ግን ዳግመኛ ወላጆቼን ማክበር አልቻልኩም ምክንያቱም ያን ጊዜ ሁለቱም ሞተው ነበርና ምን ላደርግ እችላለሁ? «ጌታ ሆይ እባክህ ይህንን ከንቱ ሐጢያተኛ ይቅር በለው ለእኔ በመስቀል ላይ ሞተሃል» እንደምን አመስጋኝ ነበርሁ!

በዚህ መንገድ ሐጢያቶቼን አንድ በአንድ እንደፈታሁ አሰብሁ አትግደል አታመንዝር አትመኝ...የሚሉ ሌሎች ሕጎችም ነበሩ አንዱንም ሕግ እንኳን እንዳልጠበቅሁ እስከተረዳሁበት ቀን ድረስ ሌሊቱን ሁሉ ጸልያለሁ ነገር ግን የንስሐ ጸሎት መጸለይ አስደሳች እንዳልሆነ ታውቃላችሁ እስቲ ስለዚህ እናውራ፡፡

ስለ ኢየሱስ ስቅለት ባሰብሁ ጊዜ ምንኛ ስቃይ እንደነበር ሐዘኑ ተሰምቶኛል እርሱም ቃሎቹን ማክበር ላልቻልነው ለእኛ ሞተ እንዴት እንደወደደኝ በማሰብና እውነተኛ ደስታ እንደሰጠኝ በማመስገን ሌሊቱን ሁሉ ሳለቅስ አደርሁ፡፡

ቤተክርስቲያን አዘወትር የነበረበት የመጀመሪያው አመት በጥቅሉ በጣም አመቺ ነበር በቀጣዮቹ ሁለት አመታቶች ግን የንስሐ ልቅሶ ማልቀስ ይበልጥ አስቸጋሪ እየሆነብኝ ሄደ ምክንያቱም ለብዙ ጊዜ እንባዎቼን አፍስሼ ስለነበር እንባዎቼ እንዲወርዱ በጣም ማሰብ ነበረብኝ፡፡

እንባዎቼ የማይወርዱ ከሆኑም ብዙውን ጊዜ ለጸሎት ወደ ተራሮች ሄጄ ለ3 ቀናት እጦማለሁ ያን ጊዜ እንባዎች ይመጣሉ

በእንባዎቼ እታጠባለሁ ወደ ማህበረሰቡ እመለሳለሁ በቤተክርስቲያን ውስጥም አለቅሳለሁ::

በዙሪያዬ ያሉ ሰዎችም «በተራሮች ላይ በምታደርጋቸው ጸሎቶች በጣም ቅዱስ ሆነሃል» ይሉኛል እንባዎቹ ግን እንደገና መድረቃቸው አልቀረም ሦስተኛው አመት በጣም አስቸጋሪ ነበር በጓደኞቼና አብረውኝ ባሉት ክርስቲያኖች ላይ የሰራሁዋቸውን ስህተቶች እያሰብኩ እንደገና አለቀስሁ ይህ ከሆነ ከ4 አመታት በኋላ እንባዎቼ እንደገና ደረቁ በአይኖቼ ውስጥ የእንባ ዕጢዎች ነበሩ ነገር ግን ዳግመኛ መስራት አልቻሉም::

ከ5 አመታት በኋላ ምንም ያህል በርትቼ ብሞክርም ማልቀስ አልቻልሁም ንፍጤ መዝረብረብ ጀመረ ከሁለት ተጨማሪ አመታት በኋላ ራሴን ስለጠላሁ እግዚአብሄር እንደገና ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንድመለስ አደረገኝ::

## ሕጉ ሐጢያትን ማወቂያ ነው




በሮሜ 3:20 ላይ እንዲህ እናነባለን:- *«ኃጢያት በሕግ ይታወቃልና»* በመጀመሪያ ይህ ጥቅስ ለሐዋርያው ጳውሎስ የተላከ የግል መልዕክት ብቻ እንደሆነ በማጤን እኔ በመረጥኋቸው ቃሎች ብቻ ለማመን ሞከርሁ እንባዎቼ ከደረቁ በኋላ ግን ሐይማኖታዊ

የሆነውን የእምነት ሕይወቴን መቀጠል አልቻልሁም፡፡

ስለዚህ በተደጋጋሚ ሐጢያትን ስራሁ በልቤ ውስጥም ሐጢያት እንዳለና በሕጉ መኖርም እንደማይቻል ተረዳሁ ልሸከመው አልቻልኩም ነገር ግን ሕጉንም ደግሞ መተው አልቻልኩም ምክንያቱም ሕጉ የተሰጠው እንድታዘዘው ነው ብዬ አምኜ ነበርና በመጨረሻም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን የሕግ አዋቂ መሰልኩ የእምነትን ሕይወት መቀጠል ለእኔ በጣም አስቸጋሪ ሆነብኝ፡፡

ብዙ ሐጢያት ስለነበረብኝ ሕጉን ሳነብ በልቤ እያንዳንዳቸውን አስርቱን ትዕዛዛት ስተላለፍ እነዚያን ሐጢያቶች መገንዘብ ጀመርሁ በልብ ሐጢያትን መስራትም እንደዚሁ ሐጢያትን መፈጸም ነው እኔም በሕጉ የማምን አክራሪ አማኝ ሆንሁ፡፡

ሕጉን ስጠብቅ ደስተኛ ነበርሁ ሕጉን መጠበቅ ባልቻልሁ ጊዜ ግን ጭንቀታም ብስጩና ሐዘንተኛ ሆንሁ ውሎ አድሮም በሁሉም ነገር ላይ ተስፋ ቆረጥሁ ከመጀመሪያው «አይደለም ሕጉ ሌላ ትርጉም አለው ሕጉ የሚያሳይህ የሐጢያት ክምር መሆንህን ነው ገንዘብን ተቃራኒ ጾታንና ውብ የሖኑ ነገሮችን ሁሉ ትወዳለህ ከእግዚአብሄር ይበልጥ የምትወዳቸው ነገሮች አሉህ የአለምን ነገሮች መከተል ትፈልጋለህ ሕጉ የተሰጠህ እንድትጠብቀው ሳይሆን በልብህ ውስጥ ክፋት ያለብህ ሐጢያተኛ መሆንህን ራስህን እንድታውቅ ነው» የሚለውን የሕጉን እውነተኛ እውቀት እንዲህ ተምሬ ብሆን ኖሮ ነገሩ እንዴት ቀላል መሆን በቻለ ነበር፡፡

ያን ጊዜ አንድ ሰው እውነቱን አስተምሮኝ ቢሆን ኖሮ ለ10 አመታት ያህል ባልተሰቃየሁ ነበር ስለዚህ ወደዚህ ግንዛቤ ከመምጣቴ በፊት ለ10 አመታት ያህል ከሕግ በታች ሆኜ ስኖር ነበርሁ፡፡

አራተኛው ትዕዛዝ «የሰንበትን ቀን ትቀድስ ዘንድ አስብ» የሚል ነው ያ ማለት በሰንበት መስራት አይገባንም ማለት ነው እነርሱ በእሁድ ቀን ረጅም ርቀቶችን በመኪና ሳይሆን በእግራችን መጓዝ እንደሚገባን ያስተምራሉ ወደምሰብክበት ስፈግራ በእግር መሄድ በጣም ተገቢና ተወዳሽ እንደሆንሁ አሰብሁ እኔም የምሄደው ሕጉን ለመስበክ ነበር ስለዚህ የምሰብከውን መተግበር እንደሚገባኝ ተሰማኝ ይህንን ለመተው መዘጋጀት በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡

እዚህ ላይ «እንዴትስ ታነባለህ?» ተብሎ እንደተጻፈ ይህንን ጥያቄ ስላልተረዳሁት ለ10 አመታት ያህል ተሰቃየሁ የሕግ አዋቂውም እንደዚሁ ይህንኑ ነገር የተረዳው በተሳሳተ መንገድ ነበር ሕጉን ቢታዘዝና ተጠንቅቆ ቢኖር በእግዚአብሄር ፊት እንደሚባረክ አሰበ፡፡

ኢየሱስ ግን «እንዴትስ ታነባለህ?» አለው ሰውየው መልሱን የሰጠው በሕግ ላይ በተመሰረተው እምነቱ መሰረት ነበር ያን ጊዜ ኢየሱስ ለሰውየው «አዎ በትክክል መልሰሃል ሕጉን እንደተጻፈው ተቀብለኸዋል ልትጠብቀው ሞክር ብትጠብቀው በሕይወት ትኖራለህ ባትጠብቀው ግን ትሞታለህ የሐጢያት ደመወዝ ሞት ነው ባትጠብቀው ትሞታለህ» አለው (የሕይወት ተቃራኒ ሞት ነው አይደል?)

የሕግ አዋቂው ግን አሁንም ድረስ አልተረዳም ይህ የሕግ አዋቂ እንደ እናንተና እንደ እኔ እንደ ማናችንም ነው እኔ የስነ መለኮትን ትምህርት ለ10 አመታት ያህል አጥንቻለሁ ሁሉን ሞክሬአለሁ ሁሉን አንብቤአለሁ ፆሜአለሁ ራዕዮችን አይቻለሁ በልሳንም ተናግሬአለሁ...መጽሐፍ ቅዱስን ለ10 አመታት ያህል አንብቤአለሁ አንዳች ነገርም ለመፈጸም ጓጉቼ ነበር በመንፈሳዊ ሁኔታ ግን አሁንም ድረስ እውር ሰው ነበርሁ፡፡

ሐጢያተኛ አይኖቹን ሊከፍትለት የሚችል ሰው ማግኘት

ያለበት ለዚህ ነው ያም ሰው ጌታችን ኢየሱስ ነው ሰዎች «አሃ! ሕጉን ፈጽሞ መጠበቅ አንችልም ሕጉን ለመጠበቅ ምንም ያህል ጠንክረን ብንሞክርም እየሞከርን ብቻ እንሞታለን ኢየሱስ ግን በውሃውና በመንፈሱ ሊያድነን መጥቶዋል! ሐሌሉያ!» ብለው ሊገነዘቡ ይችላሉ ውሃውና መንፈሱ ሊያድነን ይችላል ይህ የእግዚአብሄር ጸጋ ስጦታ ነው ስለዚህ ጌታን እናመሰግነዋለን::

እኔ ተስፋ ቢስ ከሆነው የሕግ አጥባቂነት መስመር ለመመረቅ በመብቃቴ ዕድለኛ ነኝ አንዳንዶች ግን እስከሚሞቱበት ቀን ድረስ ዕድሜ ዘመናቸውን በሙሉ ስነ መለኮትን በከንቱ ያጠናሉ እውነትንም ፈጽሞ አይገነዘቡም አንዳንድ ሰዎች ለአስርተ አመታት ድረስ ወይም ከትውልድ እስከ ትውልድ ድረስ ያምናሉ ነገር ግን ፈጽሞ ዳግም አይወለዱም::

ሕጉን በፍጹም መጠበቅ እንደማንችል ስንገነዘብ ሐጢያተኛ ከመሆን ተመርቀን በኢየሱስ ፊት እንቀርብና የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እንሰማለን ኢየሱስን ስንገናኝ ከፍርዶችና ከኩነኔዎች ሁሉ ተመርቀን እንወጣለን እኛ እጅግ የከፋን ሐጢያተኞች ነን ነገር ግን እርሱ በውሃና በደም ስላዳነን ጻድቃን ሆነናል::

ኢየሱስ በእርሱ ፈቃድ ውስጥ ፈጽሞ መኖር እንደማንችል ነግሮናል ይህንኑም ለሕግ አዋቂው ነግሮታል እርሱ ግን አልገባውም ስለዚህ እንዲገባው ለማገዝ አንድ ታሪክ ነገረው::

*ሰዎችን ከእምነት ሕይወት እንዲወድቁ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?*

*ኃጢያት*

*«አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ። በወንበዴዎች እጅም ወደቀ፤ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም፣ በሕይወትና በሞት መካከልም ትተውት ሄዱ» (ሉቃስ 10፡30)* ኢየሱስ ይህንን ምሳሌ ለሕግ አዋቂው የነገረው ይህ ሰው በወንበዴዎች እንደተደበደበና በሞትና በሕይወት መሃል እንደነበረ ሁሉ እርሱም በሕይወት ዘመኑ ሁሉ እንዲህ እንደተቸገረ እውነቱን እንዲያውቅ ነው።

አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ ኢያሪኮ ስጋዊውን አለም ስታመላክት ኢየሩሳሌም ደግሞ የሐይማኖትን ከተማ ታመላክታለች በሕግ የሚመጻደቁ ሰዎች የሞሉባት ቃስ የእምነት ከተማ ታመላክታለች ይህ ታሪክ በኢየሱስ የምናምነው በሐይማኖታዊ መንገድ ብቻ ከሆነ እንደምንጠፋ ይነግረናል። *«አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ። በወንበዴዎች እጅም ወደቀ፤ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም፣ በሕይወትና በሞት መካከልም ትተውት ሄዱ» (ሉቃስ 10፡30)* ኢየሩሳሌም ብዙ ሕዝብ ያለባት ትልቅ ከተማ ነበረች በዚያ ሊቀ ካህኑ ካህናቶች ሌዋውያንና ብዙ ታዋቂ የሐይማኖት ሰዎች ነበሩ እነርሱ በሕጉ ለመኖር ሞከሩ ነገር ግን ውሎ አድሮ ወደቁ ወደ ኢያሪኮም ወረዱ በአለም (ኢያሪኮ) ውስጥ መውደቃቸውን ቀጠሉ ወንበዴዎችን ከመገናኘት ማምለጥ አልቻሉም።

ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ የሄደው ሰው ወንበዴዎች ያገኙትና ልብሱን ይዘርፉታል *«ልብሶቹን መግፈፍ»* ማለት ጽድቁን አጥቷል ማለት ነው እኛ በሕግ መኖር ለሕጉም መኖር አይቻለንም ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 7፡19-20 ላይ እንዲህ ብሎዋል *«የማልወደውንና ክፉን ነገር አደርጋለሁና፣ ዳሩ ግን የምወደውንና ጥሩውን ነገር አላደርገውም። የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን፣ ያን የማድርገው አሁን እኔ አይደለሁም። በእኔ የሚኖር ኃጢያት ነው እንጂ።»*

በጎ ነገር ማድረግና በእርሱ ቃሎች መኖር ብችል እመኛለሁ በሰው ልብ ውስጥ ግን ክፉ አሳቦች ምንዝርና ዝሙት ነፍስ መግደል መስረቅ ክፉ ምኞት ማታለል መጎምጀት መዳራት ስድብ ትዕቢት ተንኮል ስንፍና አሉ (ማርቆስ 7:21-23)::

እነዚህ ነገሮች በልባችን ውስጥ ስላሉና ደጋግመው ስለሚወጡ ማድረግ የማንፈልገውን እናደርጋለን ማድረግ የሚገባንንም አናደርግም በልቦቻችን ውስጥ ያሉትን እነዚያን ክፉቶች ደጋግመን እናደርጋቸዋለን ዲያብሎስ የሚያደርገው ነገር ቢኖር ሐጢያት እንድንሰራ ትንሽ ግፊት ማድረግ ብቻ ነው::

## በሰው ዘር ሁሉ ልብ ውስጥ ያሉት ሐጢያቶች




በማርቆስ 7 ላይ እንዲህ ተብሎዋል *«እርሱም አለ፡- ከሰው የሚወጣው፣ ሰውን የሚያረክስ ያ ነው ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት ስንፍና ናቸውና፣ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል::»*

ኢየሱስ በሰው ልብ ውስጥ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣

መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት ስንፍና እንዳሉ ይነግረናል፡፡

ሁላችንም በልባችን ውስጥ ነፍስ መግደል አለ ነፍስ የማይገድል ማንም የለም እናቶች በልጆቻቸው ላይ «አይደለም ያንን እንዳታደርግ ያንን እንዳታደርግ ነግሬሃለሁ ያንን እንዳታደርግ ደጋግሜ ነግሬሃለሁ ዳግመኛ ያንን ብታደርግ እገልሃለሁ ያንን እንዳታደርግ ብያለሁ» በማለት ይጮሃሉ ያ ነፍስ መግደል ነው ሳታስቡ በምትናገሩዋቸው ቃሎች ልጆቻችሁን በአእምሮዋችሁ ውስጥ ትገድሉዋቸው ይሆናል፡፡

ልጆቻችን በሕይወት መኖር አለባቸው ምክንያቱም በፍጥነት ከእኛ ያመልጣሉና ነገር ግን ቁጣችንን በሙሉ በእነርሱ ላይ የምናፈስስ ከሆነ ልንገድላቸው እንችል ይሆናል አንዳንድ ጊዜ ራሳችንን እናስጨንቃለን «ኦ አምላኬ! ለምንድነው ያንን ያደረግሁት?» ልጆቻችንን ከመታናቸው በኋላ ጠባሳዎቹን ተመልክተን ያንን በማድረጋችን ወፈፌዎች እንደሆንን እናስባለን ያንን ከማድረግ አንመለስም ምክንያቱም በልባችን ውስጥ ነፍስ መግደል አለና፡፡

ስለዚህ *«የማልወደውን አደርጋለሁና»* ማለት ክፉዎች ስለሆንን ክፉ ነገር እናደርጋለን ማለት ነው ሰይጣን እኛን በሐጢያት ለመፈተን በጣም ይቀለዋል፡፡

አንድ ያልዳነ ሰው በቅርቡ የሞተው ታላቁ የኮርያ መነኩሴ ሱንግቾል እንደሚያደርገው ፊቱን ወደ ግድግዳው አዙሮ በማሰላሰል ለ10 አመታት በአንድ ጎጆ ውስጥ ተቀመጠ እንበል ፊቱን ወደ ግድግዳው አዙሮ እስከተቀመጠ ድረስ ጥሩ ነው ነገር ግን ምግብ የሚያመጣለትና ሰገራውን የሚጠርግለት ሰው ያስፈልገዋል፡፡

ከሰው ጋር መገናኘት ይኖርበታል ወንድ ከሆነ ችግር የለውም ነገር ግን ውብ ሴት ናት እንበል በአጋጣሚ ካያት

በመቀመጥ ያጠፋው ጊዜ ሁሉ ከንቱ ይሆናል «ማመንዘር የለብኝም ይህ በልቤ ውስጥ አለ ነገር ግን ላስወግደው ይገባኛል ላባርረው ይገባኛል አይሆንም ከአእምሮዬ ውጣ!»

ነገር ግን እርስዋን ባየበት ቅጽበት ውሳኔው በሙሉ ይተናል ሴቲቱ ከሄደች በኋላ ልቡን ይመለከታል የ5 አመት የምንኩስና ልምምዶቹ ሁሉ ከንቱና ፍሬ ከርሲ ሆነዋል።

ለሰይጣን የሰውን ጽድቅ መንጠቅ በጣም ቀላል ነው ሰይጣን ማድረግ ያለበት ነገር እርሱን/እርስዋን ጥቂት ገፋ ማድረግ ብቻ ነው ሰው ሳይድን ሐጢያት ላለመስራት ቢታገል በሐጢያት ውስጥ መውደቁን ይቀጥላል ያ ሰው በየእሁዱ አስራቱን በታማኝነት ይከፍል 40 ቀን ይጾም የ100 ቀን የንጋት ጸሎቶችን ይጸልይ ይሆናል...ሰይጣን ግን በሕይወት ውስጥ ጥሩ በሚመስሉ ነገሮች ይፈትነውና ያስተዋል።

«በካምፓኒ ውስጥ ቁልፍ ቦታ ልሰጥህ እወዳለሁ ነገር ግን አንተ ክርስቲያን ስለሆንህ እሁድ አትሰራም መስራት ትችላለህ እንዴ? ቦታው ትልቅ ቦታ ነው ለ3 እሁዶች ሰርተህ በወር አንድ ጊዜ ብቻ ቤተክርስቲያን መሄድ ትችላለህ ያን ጊዜ እንዲህ ባለው ከፍተኛ ክብር ትደሰታለህ ወፍራም ደመወዝም ይኖርሃል እንዴት ነው?» በዚህ ከ100 ሰዎች ምናልባት 100ዎቹም ይገዙ ይሆናል።

ይህ የማይሰራ ከሆነ ሰይጣን በሴቶች ፍትወት በቀላሉ በሚጠመዱ ሰዎች ላይ ሌላ ብልሃት ይጠቀማል ሰይጣን በፊቱ አንዲት ሴት ያቆምለታል እርሱም እግዚአብሄርን ወዲያውኑ ረስቶ ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ በፍቅር ይወድቃል የሰው ጽድቅ የሚገፈፈው በዚህ መንገድ ነው።

በሕጉ ለመኖር የምንሞክር ከሆንን በመጨረሻ የሚተርፈን ነገር ቢኖር የሐጢያት ቁስል ስቃይና መንፈሳዊ ድህነት ብቻ ነው ጽድቅን ሁሉ እናጣለን *«ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ*

*በወንበዴዎች እጅም ወደቀ፣ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም፣ በሕይወትና በሞት መካከልም ትተውት ሄዱ።»*

ይህ ማለት በቅዱስ አምላክ ፈቃድ እየኖርን በኢየሩሳሌም ለመቆየት ብንሞክር ከድክመቶቻችንና የተነሳ በየጊዜው እንሰናከላለን ውሎ አድሮም እንጠፋለን ማለት ነው። እንጠፋለን።

በእግዚአብሄር ፊት የንስሐ ጸሎት ትጸልዩ ይሆናል «ጌታ ሆይ ሐጢያት ሰርቻለሁ እባክህ ይቅር በለኝ ዳግመኛ ይህንን ፈጽሞ አላደርግም ይህ በእርግጥ የመጨረሻ እንደሆነ ቃል እገባልሃለሁ ይህን አንድ ጊዜ ብቻ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ እማጸንህማለሁ።»

ይህ ግን ፈጽሞ ማለቂያ የለውም ሰዎች ሐጢያት ሳይሰሩ በዚህ አለም ላይ መኖር አይችሉም ለአንድ ሁለት ጊዜ ያህል ሐጢያትን ማስወገድ ይችሉ ይሆናል ነገር ግን ዳግመኛ ሐጢያት አለመስራት የማይቻል ይሆናል ስለዚህ በተደጋጋሚ ሐጢያቶችን ከመስራት በቀር ማድረግ የምንችለው ነገር የለም «ጌታ ሆይ እባክህ ይቅር በለኝ» ይህ የሚቀጥል ከሆነ ከቤተክርስቲያንና ከሐይማኖታዊ ሕይወታቸው ያፈነግጣሉ በሐጢያቶቻቸው ምክንያትም ከእግዚአብሄር ይርቃሉ ውሎ አድሮም መጨረሻቸው ሲዖል ይሆናል።

ወደ ኢያሪኮ መጓዝ ማለት በስጋዊው አለም ውስጥ መውደቅ ማለት ነው ከኢየሩሳሌም መራቅና ወደ አለም መጠጋት ማለት ነው በመጀመሪያ ኢየሩሳሌም ገናም ቅርብ ነበረች ነገር ግን ሐጢያትን የመስራትና ንስሐ የመግባት ዑደት ሲደጋገም ራሳችንን በኢያሪኮ የቀለጠ ከተማ ውስጥ እናገኘዋለን ሙሉ በሙሉ በአለም ውስጥ ወድቀን እንገኛለን።

*መዳን የሚችሉት*
*እነማን ናቸው?*

*የራሳቸውን ጽድቅ ማቆም*
*የተዉ ሰዎች*
*ናቸው::*

ወደ ኢያሪኮ የሄደውን ሰው እነማን አገኙት? ወንበዴዎች አገኙት ሕጉን የማያውቅና በሕጉ የሚኖር ሰው ልክ ያበደ ውሻ የሚኖረውን አይነት ሕይወት ይኖራል ይጠጣል የትም ቦታ ይተኛል የትም ቦታ ይሸናል ይህ ውሻ በነጋታው ተነስቶ የራሱን እዳሪ ይበላል እንዲህ አይነት ሰው ውሻ ተብሎ የሚጠራው ለዚህ ነው እርሱ መጠጣት አያውቅም ነገር ግን ይጠጣና በነጋታው ንስሐ ይገባል ይህንን ሒደት ደጋግሞ ያደርገዋል::

ነገሩ ወደ ኢያሪኮ ሲሄድ ወንበዴዎች የተገናኙትን ሰው ይመስላል ቆስሎ በሞትና በሕይወት መሃከል ቆየ ይህ ማለት በልቡ ውስጥ ያለው ሐጢያት ብቻ ነበር ማለት ነው ሰው ማለት ይህ ነው::

ሰዎች የሐይማኖት ማህበረሰብ በሆነችው በኢየሩሳሌም ውስጥ በሕጉ ለመኖር እየሞከሩ በኢየሱስ ያምናሉ ነገር ግን በልባቸው ውስጥ ሐጢያቶች አሉባቸው በሐይማኖታዊ ሕይወታቸው የሚያሳዩት ነገር ሁሉ የሐጢያትን ቁስል ብቻ ነው በልባቸው ውስጥ ሐጢያት ያለባቸው ሰዎች በመጨረሻ ወደ ሲዖል ይወረወራሉ ይህንን ያውቁታል ነገር ግን ምን እንደሚያደርጉ አያውቁም እናንተና እኔም ተመሳሳይ በሆነችው ሐይማኖታዊ ከተማ ውስጥ ያለን አይደለንምን? አዎ ሁላችንም

በተመሳሳይ መንገድ እዚያው ነበርን፡፡

የእግዚአብሄርን ሕግ በተሳሳተ መንገድ የተረዳው የሕግ አዋቂ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ቢታገልም ቆስሎ መጨረሻው ሲዖል ይሆናል እርሱም እንደ እናንተና እንደ እኔ ከእኛ እንደ አንዱ ነው፡፡

ሊያድነን የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው በዙሪያችን በጣም አዋቂ የሆኑ ሰዎች አሉ ሁልጊዜም ስለሚያውቁት ነገር ይመጻደቃሉ ሁሉም በእግዚአብሄር ሕግ እንደሚኖሩና ለራሳቸውም እውነተኞች እንደሆኑ ያስመስላሉ አካፋን አካፋ ብለው አይጠሩትም ነገር ግን ሁልጊዜም ታማኝ ለመመስል ውጫዊ ገጽታዎቻቸውን ያሰማምራሉ፡፡

በእነርሱ መካከል ወደ ኢያሪኮ ሲሄዱ በወንበዴዎች የተደበደቡና በሞትና በሕይወት መካከል ሆነው የተተዉ ሐጢያተኞች አሉ እኛ በእግዚአብሄር ፊት ተሰባሪዎች መሆናችንን ማወቅ ይኖርብናል፡፡

በእርሱ ፊት «ጌታ ሆይ አንተ ካላዳንከኝ ሲዖል እወርዳለሁ እባክህ አድነኝ እውነተኛውን ወንጌል ብቻ መስማት ብችል በረዶም ይሁን ማዕበል ወደምትፈልገው ሁሉ እሄዳለሁ ብቻዬን ከተውከኝ ሲዖል እወርዳለሁ እንድታድነኝ እለምንሃለሁ» በማለት ማመን አለብን፡፡

መዳን የሚችሉት ወደ ሲዖል እየነጎዱ መሆናቸውን የሚያውቁና በጌታ ላይ ተንጠላጥለው የራሳቸውን ጽድቅ መከተልን ለመተው የሚሞክሩ ሰዎች ናቸው በራሳችን ጥረቶች ፈጽሞ መዳን አንችልም፡፡

እኛ በወንበዴዎች እጅ የወደቀውን ሰው እንደምንመስል መረዳት አለብን፡፡ ✉

# ስብከት 4

## ዘላለማዊው ቤዛነት

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::



ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

# ዘላለማዊው ቤዛነት

**« ዮሐንስ 8:1-12 »**

***«ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ሄደ ማለዳም ደግሞ ወደ መቅደስ ደረሰ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡ ተቀምጦ ያስተምራቸውም ነበር። ጻፎችና ፈሪሳውንም በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ በመካከልም እርስዋን አቁመው:- መምህር ሆይ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች ሙሴም እንደዚህ ያሉት በድንጋይ እንዲወገሩ አዘዘን አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ? አሉት የሚከሱበትንም እንዲያገኙ ሊፈትኑት ይህን አሉት ኢየሱስ ግን ጎንበስ ብሎ በምድር ላይ በጣቱ ጻፈ መላልሰው በጠየቁት ጊዜ ግን ቀና ብሎ:- ከእናንተ ኃጢያት የሌለበት አስቀድሞ ይውገራት አላቸው ደግሞም ጎንበስ ብሎ በምድር ላይ በጣቱ ጻፈ እነርሱም ይህንን ሲሰሙ ህሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሎች ጀምሮ ወደኋላ አንዳንድ እያሉ ወጡ ኢየሱስም ብቻውን ቀረ ሴቲቱም በመካከል ቆማ ነበረች ኢየሱስም ቀና ብሉ ከሴቱቱ ሌላ ባላየም ጊዜ:- አንቺ ሴት እነዚያ ከሳሾችሽ በየት አሉ? የፈረደብሽ የለምን? አላት እርስዋም ጌታ ሆይ አንድስ እንኳ አለች ኢየሱስም:- እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ኃጢያትን አትስሪ አላት ደግሞም ኢየሱስ:- እኔ የአለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የህይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።»***

*ኢየሱስ ያስወገደልን ኃጢያት ምን ያህል ነበር?*

*የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ነው።*

ኢየሱስ ዘላለማዊ ቤዛነትን ሰጥቶናል ኢየሱስን አዳኙ አድርጎ ቢያምን በዚህ አለም ላይ ቤዛነትን ማግኘት የማይችል አንድም ሰው የለም እርሱ ሁላችንንም ዋጅቶናል በሐጢያቶቹ የሚሰቃይ ሐጢያተኛ ካለ ኢየሱስ በጥምቀቱና በስቅለቱ ከሐጢያቶች ሁሉ እንዴት እንዳዳነው የተሳሳተ እሳቤ በመያዙ ነው።

ሁላችንም የደህንነትን ምስጢር ማወቅና ማመን አለብን ኢየሱስ በጥምቀቱ ሐጢያቶቻችንን ሁሉ ወስዶ በመስቀል ላይ በመሞት የሐጢያቶቻችንን ፍርድ ተሸክሞዋል።

ከሐጢያቶች ሁሉ ዘላለማዊ ቤዛነት በሆነው የውሃውና የመንፈሱ ደህንነት ማመን ይገባችኋል አስቀድሞ ጻድቃን ባደረጋችሁ በእርሱ ታላቅ ፍቅርም ማመን አለባችሁ ለደህንነታችሁ ሲል በዮርዳኖስ ወንዝና በመስቀል ላይ ባደረገው ነገር እመኑ።

ኢየሱስ የተደበቁ ሐጢያቶቻችንንም በሙሉ አውቋል አንዳንድ ሰዎች ስለ ሐጢያት የተዛባ እሳቤ አላቸው አንዳንድ ሐጢያቶች ሊቤዡ አይችሉም ብለው ያስባሉ ኢየሱስ ሁሉንም እያንዳንዳቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ዋጅቶዋቸዋል።

ኢየሱስ ያላስወገደው አንድም ሐጢያት በዚህ አለም ላይ የለም እርሱ በዚህ አለም ላይ ያሉትን ሐጢያቶች በሙሉ ስለደመሰሰ እውነቱ ምንም ሐጢያተኞች የሌሉ መሆናቸው ነው

ወንጌል ሐጢያቶቻችሁን ወደፊት የምትሰሩዋቸውን ሐጢያቶች ሳይቀሩ እንደዋጀ ትገነዘባላችሁን? በዚህ አምናችሁ ዳኑ ክብርንም ሁሉ ለእግዚአብሄር ስጡ።

# ዝሙት ስትፈፅም የተያዘችው ሴት

*በምድር ላይ ምን ያህል ሰዎች ዝሙትን ይፈፅማሉ?*

*ሁላቸውም።*

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ስምንት ላይ ዝሙት ስትፈፅም ስለተያዘች ሴትና ኢየሱስም እንዴት እንዳዳናት እናያለን እርስዋ የተጋራችውን ጸጋ መቀበል እንወዳለን ሰዎች ሁሉ በሕይወታቸው በአንድ ወቅት ዝሙት እንደሚፈጽሙ መናገር ማጋነን አይደለም እያንዳንዱ ሰው ዝሙት ይፈጽማል።

እንደዚያ የማታስቡ ከሆነ ምክንያቱ ይህንን ሁልጊዜ ስለምናደርገው የማናደርግ መስሎ ስለሚታየን ነው ለምን? በሕይወታችን ውስጥ በጣም እየዘሞትን ስለምንኖር ነው።

በዮሐንስ 8 ላይ ያለችውን ሴት ስመለከት በእኛ መካከል ዝሙት ፈጽሞ የማያውቅ ሰው ስለ መኖር አለመኖሩ አስባለሁ ዝሙት ስትፈፅም እንደተያዘችው ሴት ዝሙት ያልፈጸመ ማንም ሰው የለም ሁላችንም አድርገነዋል ነገር ግን እንዳላደረግን እናስመስላለን።

እንደተሳሳትሁ ታስባላችሁን? አልተሳሳትሁም ጠለቅ ብላችሁ በጥንቃቄ ተመልከቱ በምድር ላይ የሚኖር እያንዳንዱ

ሰው ይህንን አድርጓል እነዚህ ሰዎች ሴቶች በመንገድ ላይ ሲሄዱ አተኩረው በመመልከት በሃሳባቸውና በድርጊቶቻቸው በየትኛውም ጊዜ በየትኛውም ስፍራ ዝሙት ይፈጽማሉ::

እነርሱ እያደረጉት እንዳለ አያውቁም እስከሚሞቱበት ቀን ድረስ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የማይቆጠር ዝሙት እንደፈጸሙ የማይገነዘቡ ብዙ ሰዎች አሉ የተያዙት ብቻ ሳይሆኑ እኛም ያልተያዝነው ሁሉ ዝሙትን ፈጽመናል ሰዎች ሁሉ በአእምሮዋቸውና በድርጊቶቻቸው ዝሙትን ይፈጽማሉ ይህ የሕይወታችን ክፍል አይደለምን?

ተበሳጫችሁ? ይህ እውነት ነው ስለዚህ ነገር የምንሸፋፍነው ስለምናፍር ነው እውነቱ ሰዎች በዚህ ዘመን ሁልጊዜም የሚዘሙቱ መሆናቸው ነው ነገር ግን እየዘሞቱ መሆናቸውን አያውቁም::

ሰዎች በነፍሳቸውም ደግሞ ዝሙትን ይፈጽማሉ እኛ በእግዚአብሄር የተፈጠርን ሰዎች በዚህ ምድር ላይ የምንኖረው መንፈሳዊ ዝሙትንም ደግሞ እንደምንፈጽም ሳንረዳ ነው ሌሎች አማልክቶችን ማምለክ መንፈሳዊ ዝሙትን ከመፈጸም ጋር ተመሳሳይ ነው ምክንያቱም የሰው ዘር ሁሉ ባል ጌታችን ነውና::

ድርጊቱን ስትፈጽም የተያዘችው ሴት እንደተቀረነው ሰዎች ሰው ነበረች እኛ የተቤዠን ሰዎች የተቀበልነውን የእግዚአብሄር ጸጋም ተቀብላለች ግብዞቹ ፈሪሳውያን ግን በፊታቸው አቁመው ዳኞች የሆኑ ይመስል ጣቶቻቸውን በእርስዋ ላይ ቀስረው በድንጋይ ሊወግሩዋት ተዘጋጁ እነርሱ ራሳቸው ንጹህ የሆኑና ፈጽመው ዝሙትን ያልፈጸሙ ይመስል ሊወቅሱዋትና ሊፈርዱባት ተዘጋጁ::

አጋር ክርስቲያኖች ራሳቸውን የሐጢያት ክምር አድርገው የሚያውቁ ሰዎች በእግዚአብሄር ፊት በሌሎች አይፈርዱም

እነርሱ ራሳቸውም በሕይወት ዘመናቸው ዝሙትን እንደሚፈጽሙ በማወቅ ሁላችንንም የዋጀንን የእግዚአብሄር ጸጋ ይቀበላሉ በእግዚአብሄር ፊት ቤዛነትን ለማግኘት ብቁ የሚሆኑት ዝሙትን የፈጸሙ ሐጢያተኞች መሆናቸውን የሚገነዘቡ ሰዎች ብቻ ናቸው::

## የእግዚአብሔርን ጸጋ የሚያገኘው ማነው?




የእርሱን ጸጋ የሚቀበለው ዝሙትን ሳይፈጽም በንጽህና የኖረው ነው ወይስ ጸጋውን የሚቀበለው ሐጢያተኛ ስለመሆኑ የሚያምን የማይረባው ሰው ነው? ጸጋን የሚቀበለው የእርሱን የተትረፈረፈ የቤዛነት ጸጋ የተቀበለው ሰው ነው ራሳቸውን መርዳት የማይችሉ ደካሞችና ረዳተ ቢሶች ቤዛነትን ይቀበላሉ በእርሱ ጸጋ ውስጥ ያሉት እነርሱ ናቸው::

ሐጢያት እንደሌለባቸው የሚያስቡ ሰዎች ቤዛነትን ሊያገኙ አይችሉም የሚዋጅ ምንም ነገር ሳይኖር እንዴት የቤዛነቱን ጸጋ ሊቀበሉ ይችላሉ?

ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ዝሙትን ስትፈጽም የተያዘችውን ሴት እየጎተቱ በኢየሱስ ፊት በማቅረብ *«መምህር ይህች ስታመነዝር ተያዘች ምን ትላለህ?»* ብለው ጠየቁት ሴቲቱን ወደ እርሱ ያመጡዋትና የፈተኑት ለምንድነው?

እነርሱ ራሳቸው ብዙ ጊዜ ዝሙትን ፈጽመዋል ነገር ግን ስህተቱን በእርሱ ላይ ለማኖር በመሞከር እርስዋን በኢየሱስ በኩል ሊፈርዱባትና ሊኮንኑዋት እየሞከሩ ነበር።

ኢየሱስ በአእምሮዋቸው ውስጥ ያለውን አውቋል ስለ ሴቲቱም ቢሆን ሁሉን አውቋል ስለዚህ እንዲህ አለ *«ከእናንተ መካከል ሐጢያት የሌለበት ሰው አስቀድሞ ይውገራት»* አለ ያን ጊዜ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ከሽማግሌው ጀምሮ እስከ ልጁ ድረስ አንድ በአንድ ሄዱ ኢየሱስና ሴቲቱም ብቻቸውን ቀሩ።

ትተው የሄዱት የሐይማኖት መሪዎች የነበሩት ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ነበሩ እነርሱ ራሳቸው ሐጢያተኞች ያልነበሩ ይመስል ስታመነዝር በተያዘችው ሴት ላይ ሊፈርዱ ተዘጋጅተው ነበር።

ኢየሱስ ፍቅሩን በዚህ አለም ላይ አወጀ እርሱ የፍቅር አስተናባሪ ነው ኢየሱስ ለሰዎች ምግብን ሰጥቶዋል ሙታንን አስነስቷል የመበለቲቱን ሴት ልጅም በሕይወት አኑሮታል የቢታንያውን አልአዛርን ለምጻሞችን ፈውሶዋል ከሞት አስነስቶታል ለድሆችም ተአምራቶችን አድርጓል የሐጢያተኞችን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶ ደህንነትን ሰጥቶዋቸዋል፡

ኢየሱስ ይወደናል እርሱ ማንኛውንም ነገር ማድረግ የሚችል ሁሉን ቻይ አምላክ ነው ፈሪሳውያንና ጸሐፍት ግን ጠላታቸው እንደሆነ አሰቡ ሴቲቱን ወደ እርሱ ይዘው የመጡትና የፈተኑት ለዚህ ነው።

እንዲህ በማለት ጠየቁት *«መምህር ሆይ፣ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች ሙሴም እንደዚህ ያሉት በድንጋይ እንዲወገሩ አዘዘን አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ?»* ይወግሩዋት ዘንድ እንደሚነግራቸው አሰቡ ለምን? በእግዚአብሄር ሕግ ላይ በተጻፈው መሰረት ብንፈርድባት ዝሙትን የፈጸመ ሰው ሁሉ ያለ ምንም አድልዎ መወገር ይኖርበታል።

ሁሉም መወገር ይኖርባቸዋል ሁሉም ሲያል ለመውረድ የታጩ ናቸው የሐጢያት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን ኢየሱስ እንዲወግሩዋት አልነገራቸውም በፈንታው እንዲህ አለ *«ከእናንተ ኃጢያት የሌለበት አስቀድሞ ይውገራት አላቸው»*

*እግዚአብሄር 613ቱን የህግ አንቀፆች የሰጠን ለምንድን ነው?*

*ኃጢያተኞች መሆናችንን እንድንገነዘብ ነው።*

ሕጉ ቁጣን ያመጣል እግዚአብሄር ቅዱስ ነው ሕጉም ደግሞ ቅዱስ ነው ይህ ቅዱስ ሕግ በ613 አንቀጾች ተከፋፍሎ ተሰጥቶናል እግዚአብሄር 613 የሕግ አንቀጾችን የሰጠን ሐጢያተኞችና ጎዶሎ ፍጡራን መሆናችንን ሊያሳየን ነው ሕጉ ለመዳን የእግዚአብሄርን ጸጋ መናፈቅ እንደሚኖርብን ያስተምረናል ይህንን ሳናውቅ በሕጉ ውስጥ ስለተጻፈው ብቻ የምናስብ ከሆንን እጅ ከፍንጅ እንደተያዘችው ሴት በድንጋይ ተወግረን እንሞት ነበር።

የእርሱን ሕግ እውነት ያላወቁት ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በሴቲቱ ላይና ምናልባትም በእኛም ላይ እንደዚሁ ድንጋይ መወርወር እንደሚችሉ አስበው ይሆናል ነገር ግን ራሱ ሐጢያተኛ ሆኖ ረዳተ ቢስ በሆነችው ሴት ላይ ድንጋይ ለመወርወር የደፈረ ማነው? እጅ ከፍንጅ ብትያዝም በዚህ አለም ላይ ማንም ሰው ድንጋዮችን ሊወረውርባት አልተቻለውም።

ሴቲቱና እያንዳንዳችን በሕጉ መሰረት ብቻ ብንፈረድ እኛም ሆንን ሴቲቱ አስከፊ ፍርድ እንቀበል ነበር ነገር ግን ኢየሱስ እኛ ን ሐጢያተኞችን ከሐጢያቶቻችንና ከትክክለኛ ፍርድ አዳነን በሐጢያቶቻችን ሁሉ ላይ የእግዚአብሄር ሕግ በተጻፈው መሰረት በጥብቅ በእኛ ላይ ተተግብሮ ቢሆን ኖሮ ከመካከላችን በሕይወት መቆየት የሚችል ማን ነበር? እያንዳንዳችን መጨረሻችን ሲዖል ይሆን ነበር።

ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ግን ሕጉን ያወቁት በተጻፈው መሰረት ብቻ ነበር የእርሱ ሕግ በትክክል ተተግብሮ ቢሆን ኖሮ እነርሱ እንደፈረዱባት ሴት በእርግጠኝነት ይገድላቸው ነበር የእግዚአብሄር ሕግ ለሰዎች የተሰጠው ሐጢያቶቻቸውን ማወቅ እንዲችሉ ነበር ነገር ግን ሕጉን በተሳሳተ መንገድ ስለተረዱትና በተሳሳተ መንገድ ስለተገበሩት ተቸገሩ።

የዛሬዎቹም ፈሪሳውያን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳሉት ፈሪሳውያን ሕጉን የሚያውቁት በተጻፈው መሰረት ብቻ ነው የእግዚአብሄርን ጸጋ ፍትህና እውነት መረዳት ይገባቸዋል ለመዳንም የቤዛነትን ወንጌል መማር አለባቸው።

ፈሪሳውያን እንዲህ አሉ *«ሕጉ እንደዚህ ያሉት በድንጋይ እንዲወገሩ አዘዘን አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ?»* ድንጋዮቻቸውን ይዘው በድፍረት ጠየቁ ኢየሱስ ስለዚህ ጉዳይ የሚናገረው አንዳች ነገር አይኖረውም ብለው በእርግጠኝነት አሰቡ ኢየሱስ በወጥመዳቸው እንዲገባ ጠበቁት።

ኢየሱስ በሕጉ መሰረት ፈርዶ ቢሆን ኑሮ፣ እርሱንም በድንጋይ በወገሩት ነበር አላማቸው ሴቲቱንና ኢየሱስን መውገር ነበር ኢየሱስ ሴቲቱን እንዳይወግሩዋት ቢናገር ኢየሱስ በእግዚአብሄር ሕግ ላይ አላግጦዋል በማለት ተሳድቦዋል ብለው ይወግሩት ነበር ይህ አስከፊ ሴራ ነበር!

ኢየሱስ ግን ቆም ብሎ በጣቱ በመሬት ላይ ጻፈ እነርሱም

«ምን ማለትህ ነው? በመሬት ላይ የምትጽፈውስ ምንድነው? ጥያቄያችንን ብቻ መልስ ምን ትላለህ?» ብለው መጠየቃቸውን ቀጠሉ ጣቶቻቸውን በኢየሱስ ላይ ቀስረው መተንኮሳቸውን ቀጠሉ፡፡

ያን ጊዜ ኢየሱስ ተነስቶ ከእነርሱ መካከል ሐጢያት የሌለበት የመጀመሪያውን ድንጋይ እንዲወረውርባት ነገራቸው ከዚያም ጎንበስ ብሎ በመሬት ላይ መጻፉን ቀጠለ ይህንን የሰሙት ሰዎች ሕሊናቸው ስለወቀሳቸው ከሽማግሌው ጀምሮ እስከ ታናሹ ድረስ አንድ በአንድ ትተው ሄዱ ኢየሱስም በፊቱ ከቆመችው ሴት ጋር ብቻውን ቀረ፡፡

## *«ከእናንተ ኃጢያት የሌለበት አስቀድሞ ይውገራት አላቸው፡፡»*




ኢየሱስም እንዲህ ሲል ተናገራቸው፡- *«ከእናንተ ኃጢያት የሌለበት አስቀድሞ ይውገራት አላቸው»* በመሬት ላይ መጻፉንም ቀጠለ ከሽማግሌዎቹ አንድ ሁለቱ ተመልሰው መሄድ ጀመሩ ብዙ ሐጢያቶችን የሰሩት ሽማግሌዎቹ ፈሪሳውያን መጀመሪያ ሳይሄዱ አልቀሩም ወጣቶቹም ትተው ሄደዋል

ኢየሱስ በመካከላችን ቆሞ እኛ ደግሞ በሴቲቱ ዙሪያ ቆመን እናስብ ኢየሱስ ከመካከላችን አንዱ አስቀድሞ በሴቲቱ ላይ እንዲወረውር ቢነግረን ምን ታደርጋላችሁ?

*መጻፉንም* ቀጠለ ኢየሱስ በመሬት ላይ ሲጽፍ የነበረው ምንድነው? እኛን የፈጠረን እግዚአብሄር ሐጢያቶቻችንን በሁለት የተለያዩ ቦታዎች ላይ ይጽፋል::

በመጀመሪያ ኃጢያቶቻችንን በልባችን ጽላት ላይ ይጽፋል *«የይሁዳ ኃጢያት በብረት ብዕርና በተሾለ ዕብነ አልማዝ ተጽፎአል፣ በልባቸው ጽላትና በመሠዊያቸው ቀንዶች ተቀርጾአል::» (ኤርምያስ 17:1)*

እግዚአብሄር የእኛ ምሳሌ በሆነችው በይሁዳ በኩል ይናገረናል የሰዎች ሐጢያቶች በብረት ብዕርና በተሾለ ዕብነ አልማዝ ተጽፈዋል በልቦቻችን ጽላት ላይ ተመዝግበዋል ኢየሱስ አጎንብሶ ሰዎች ሁሉ ሐጢያተኞች መሆናቸውን በመሬት ላይ ጻፈ::

እግዚአብሄር ሐጢያት እንደምንሰራ ያውቃል ሐጢያቶችንም በልቦቻችን ጽላት ላይ ቀርጾታል በመጀመሪያ ስራዎቻችንን የተሰሩ ሐጢያቶችን መዝግቦዋል ምክንያቱም እኛ በሕጉ ፊት ደካሞች ነንና ሐጢያቶች በልቦቻችን ውስጥ ስለተመዘገቡ ሕጉን ስንመለከት ሐጢያተኞች እንደሆንን እንገነዘባለን እርሱ እነዚህ ሐጢያቶች በልቦቻችንና በሕሊናዎቻችን ላይ እንደተመዘገቡ ስለሚያውቅ እኛ በእርሱ ፊት ሐጢያተኞች እንደሆንን እናውቃለን::

ኢየሱስ በመሬት ላይ ለመጻፍ ለሁለተኛ ጊዜ አጎነበሰ መጽሐፍ ቅዱስም ደግሞ ሐጢያቶቻችንን ሁሉ በእግዚአብሄር ፊት በምግባር መጽሐፎች ውስጥ እንደተጻፉ ይናገራል (ራዕይ 20:12) የእያንዳንዱ ሐጢያተኛ ስምና ሐጢያቶቹ በመጽሐፍ ውስጥ ተጽፈዋል በግለሰቡ የልብ ጽላት ላይም ተጽፈዋል

ሐጢያቶቻችን በምግባር መጽሐፎችና በልቦቻችን ጽላት ላይ ተጽፈዋል::

ሐጢያቶች በወጣቱም ሆነ በሽማግሌው በእያንዳንዱ ሰው የልብ ጽላት ላይ ተጽፎዋል በኢየሱስ ፊት ስለ ሐጢያታቸው የሚናገሩት አንዳች ነገር የማይኖረው ለዚህ ነው ሴቲቱን ለመውገር የሞከሩት ሰዎች በእርሱ ቃሎች ፊት ረዳተ ቢስ ነበሩ::

*በነዚህ ሁለት ቦታዎች የተጻፉት ኃጢያቶቻችን የሚሰረዙት መቼ ነው?*

*በልባችን የውሃውንና የኢየሱስን ደም ቤዛነት ስንቀበል ነው::*

ነገር ግን የእርሱን ደህንነት ስትቀበሉ በምግባር መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ሐጢያቶቻችሁ በሙሉ ይደመሰሳሉ ስማችሁም በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ይመዘገባል ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ያለ ሰዎች ሰማይ ይገባሉ በጎ ምግባሮቻቸው ማለትም በዚህ አለም ላይ ለእግዚአብሄር መንግስትና ለጽድቁ ያከናወኑዋቸው ነገሮችም እንደዚሁ በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ተመዝግበዋል ከሐጢያቶቻቸው የዳኑ ሰዎች ወደ ዘላለማዊነት ስፍራ ይገባሉ::

የእያንዳንዱ ሰው ሐጢያቶች በሙሉ በሁለት ስፍራዎች ላይ እንደተጻፉ ይታወስ ስለዚህ ማንም ሰው እግዚአብሄርን ማታለል አይችልም በልቡ ሐጢያትን ያልሰራ ወይም ያላመነዘረ

ሰው የለም ሰዎች ሁሉ ሐጢያተኞችና እንከን የሞላባቸው ናቸው::

የኢየሱስን ቤዛነት በልቦቻቸው ውስጥ ያልተቀበሉ ሰዎች በሐጢያቶቻቸው ከማዘን በቀር ማድረግ የሚችሉት ነገር የለም እርግጠኞች አይደሉም በሐጢያቶቻቸው ምክንያት እግዚአብሄርንና ሌሎች ሰዎችን ይፈራሉ ነገር ግን የውሃውንና የመንፈሱን የቤዛነት ወንጌል በልባቸው ውስጥ በተቀበሉበት ቅጽበት በልቦቻቸው ጽላቶችና በምግባር መጽሐፎች ውስጥ የተጻፉት ሐጢያቶች በሙሉ ይነጻሉ ከሐጢያቶቻቸውም ሁሉ ይድናሉ::

በሰማይ የሕይወት መጽሐፍ አለ በውሃውና በመንፈሱ የቤዛነት ወንጌል የሚያምኑ ሰዎች ስሞችም በመጽሐፉ ውስጥ ስለተጻፈ ሰማይ ይገባሉ ሰማይ የሚገቡት በዚህ አለም ላይ ሐጢያት ስላልሰሩ ሳይሆን በውሃውና በመንፈሱ የቤዛነት ወንጌል በማመን ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ስለዳኑ ነው ይህ *«የእምነት ሕግ»* ነው:: *(ሮሜ 3:27)*

*አጋር* ክርስቲያኖች ጸሐፍትና ፈሪሳውያንም በምንዝርና ድርጊት እጅ ከፍንጅ እንደተያዘችው ሴት ሐጢያተኞች ነበሩ::

ሐጢያተኞች እንዳልሆኑ ራሳቸውንና ሌሎች ሰዎችን በማታለል ስለሚያሳምኑ ብዙ ሐጢያቶችን መፈጸማቸው እርግጥ ነው የሐይማኖት መሪዎቹ ሕጋዊ ፈቃድ ያላቸው ሌቦች ነበሩ በሌላ አነጋገር የነፍሳት ሌቦች የሕይወት ዘራፊዎች ነበሩ እነርሱ ራሳቸው ገና ያልተዋጁ ሆነው ሳሉ ሌሎችን በስልጣን ለማስተማር ደፍረዋል::

በሕጉ መሰረት ኃጢያት የሌለበት ማንም ሰው የለም ሰው ግን ጻድቅ የሚሆነው ሐጢያት ስላልሰራ ሳይሆን ከሐጢያቶቹ ሁሉ ስለዳነ ነው ይህ ሰው በሕይወት መጽሐፍ ላይ ተጽፎዋል ዋናው ነገር የሰውየው ስም በሕይወት መጽሐፍ ላይ መጻፉ

ወይም አለመጻፉ ነው ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ሐጢያቶችን ሳይሰሩ መኖር ስለማይችሉ በመጽሐፉ ውስጥ ለመጻፍ የዘላለም ቤዛነትን ማግኘት አለባቸው::

በሰማይ ተቀባይነት ማግኘታችሁ የሚመሰረተው በእውነተኛው ወንጌል በማመናችሁ ወይም በአለማመናችሁ ነው የእግዚአብሄርን ጸጋ መቀበላችሁ ወይም አለመቀበላችሁ የሚወሰነው የኢየሱስን ደህንነት በመቀበላችሁ ላይ ነው የተያዘችው ሴት ምን ደረሰባት? በጉልበቶችዋ ተንበርክካና አይኖችዋን ጨፍና ይሆናል ምክንያቱም እንደምትሞት ታውቅ ነበርና ምናልባትም በፍርሃት ሳታለቅስና ንስሐ ሳትገባ አልቀረችም ሰዎች ለራሳቸው ታማኞች የሚሆኑት ሞት ሲገጥማቸው ነው::

«ኦ አምላኬ መሞት የሚገባኝ መሆኑ ትክክል ነው እባክህ ነፍሴን በእጆችህ ተቀበል ራራልኝም ኢየሱስ ሆይ እባክህ ራራልኝ» ኢየሱስ የቤዛነትን ፍቅር እንዲሰጣት ተማጸነችው «አምላኬ ሆይ ከፈረድክብኝ ይፈረድብኛል ሐጢያት የለብሽም የምትል ከሆነም ሐጢያቶቼ ይደመሰሳሉ ጉዳዩ ያንተ ነው» ምናልባትም እነዚህን ሁሉ ነገሮች ሳትል አልቀረችም ሁሉም ነገር ለኢየሱስ እንደተተወ መስክራ ይሆናል::

በኢየሱስ ፊት የቀረበችው ሴት «ተሳስቻለሁ እባክህ ምንዝርናዬን ይቅር በለኝ» አላለችም እንዲህ አለች «እባክህ ከሐጢያቶቼ አድነኝ ሐጢያቶቼን ብትዋጅ እድናለሁ ባትዋጅ ሲያል እወርዳለሁ የአንተን ቤዛነት እሻለሁ የእግዚአብሄር ፍቅር ያስፈልገኛል እንዲራራልኝም እፈልጋለሁ» አይኖችዋን ጨፍና ሐጢያተኝነቷን ተናዘዘች::

ኢየሱስም *«ከሳሾችሽ ከወዴት አሉ? ማንምስ አልፈረደብሽምን?»* በማለት ጠየቃት እርስዋም *«ማንም፣ ጌታዬ»* በማለት መለሰች::

ኢየሱስም እንዲህ አላት *«እኔም አልፈርድብሽም»* ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ በተቀበለው ጥምቀቱ አማካይነት አስቀድሞ ሐጢያቶችዋን በሙሉ ስለወሰደና እርስዋም ቀድሞውኑም ስለተዋጀች አልፈረደባትም::

## *«እኔም አልፈርድብሽም»* አላት

*ሴትየዋ በኢየሱስ ተፈርዶባት ነበርን?*

*አልተፈረደባትም::*

ይህች ሴት በኢየሱስ ደህንነት ተባረከች ከሐጢያቶችዋ ሁሉ ተዋጀች ጌታችን ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደዋጀና እኛም ሁላችን ጻድቃን እንደሆንን ይነግረናል::

እርሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም የነገረን ይህንኑ ነው በዮርዳኖስ ወንዝ በመጠመቅ ለወሰዳቸው ሐጢያቶችም ዋጋ ለመክፈል በመስቀል ላይ ሞተ እርሱ በጥምቀቱ ቤዛነትና በመስቀል ላይ በከፈለው ፍርድ የሚያምኑትን ሁሉ እንደተቤዠ ይናገራል ሁላችንም የተጻፈው የኢየሱስ ቃል ያስፈልገናል ቃሉንም አጥብቀን መያዝ ያስፈልገናል ያን ጊዜ ሁላችንም በቤዛነት እንባረካለን::

«አምላኬ ሆይ በፊትህ ሰናይ ነገር የለኝም በውስጤ ጥሩ ነገር የለም ከሐጢያቶቼ በቀር የማሳይህ ምንም ነገር የለም ኢየሱስ የቤዛነት ጌታዬ እንደሆነ ግን አምናለሁ እርሱ

በዮርዳኖስ ወንዝ ሐጢያቶቼን በሙሉ ወስዶ በመስቀል ላይ አስተሰርዮዋቸዋል በጥምቀቱና በደሙም ሐጢያቶቼን በሙሉ ወስዶዋል ጌታ ሆይ በአንተ አምናለሁ፡፡»

የዳናችሁት እንዲህ ነው ኢየሱስ «አይኮንነንም» የእግዚአብሄር ልጆች የምንሆንበትን መብት ሰጥቶናል እርሱ በውሃውና በመንፈሱ ቤዛነት የሚያምኑትን ሰዎች ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ ወስዶ ጻድቃን አድርጎዋቸዋል፡፡

ውድ ወዳጆች! ሴቲቱ ድናለች በምንዝር የተያዘችው ሴት በጌታችን በኢየሱስ ቤዛነት ተባርካለች እኛም ደግሞ እንደዚያ ልንባረክ እንችላለን ሐጢያቶቹን አውቆ እግዚአብሄር እንዲራራለት የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው በኢየሱስ በውሃውና በመንፈሱ ቤዛነትም የሚያምን ማንኛውም ሰው ከእግዚአብሄር ዘንድ የቤዛነትን በረከት ይቀበላል በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኝነታቸውን የሚያምኑ ሰዎች ሊድኑ ይችላሉ ነገር ግን ሐጢያቶቻቸውን የማያውቁ ሰዎች በዚህ ቤዛነት ሊባረኩ አይችሉም፡፡

ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች ወስዶዋል (ዮሐንስ 1፡29) በአለም ላይ የሚኖር ማንኛውም ሐጢያተኛ በኢየሱስ ቢያምን መዳን ይችላል ኢየሱስ ለሴቲቱ *«እኔም አልፈርድብሽም»* አላት አልፈርድብሽም ያላት ሐጢያቶችዋ በሙሉ ቀድሞውኑም በእርሱ ጥምቀት አማካይነት ወደ እርሱ ስለተላለፉ ነው እርሱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በራሱ ላይ ወስዶዋል በእኛ ፋንታም ለእነዚያ ሐጢያቶች ተኮንኖዋል፡፡

# በኢየሱስ ፊት ቤዛነትን ማግኘት አለብን

*የሚበልጠው የትኛው ነው*
*የእግዚአብሄር ፍቅር ወይስ*
*የእግዚአብሄር ፍርድ?*

*የእግዚአብሔር ፍቅር ነው።*

በእጆቻቸው ድንጋዮችን ይዘው የነበሩት ፈሪሳውያን እንደዚሁም የዛሬዎቹ የሐይማኖት መሪዎች ሕጉን በፊደሉ መሰረት ይተረጉሙታል ሕጉ እንዳናመነዝር ስለሚነግረን እነዚህን ሐጢያቶች የሚሰራ ሰው መወገር እንዳለበት ያምናሉ እነርሱ እንደማያመነዝሩ እያስመሰሉ ሴቶችን በፍትወት አይኖቻቸው እየሰረቁ ያያሉ እነርሱ መቤዠትም ሆነ መዳን አይችሉም ፈሪሳውያንና ጸሐፍቶች የዚህ አለም ሞራሊስቶች ነበሩ ኢየሱስ የጠራቸው ሰዎች አልነበሩም እነዚህ ሰዎች «አልፈርድባችሁም» የሚለውን ፈጽሞ አልሰሙም።

እነዚያን የሚያስደስቱ ቃሎች የሰማችው በምንዝር የተያዘችው ሴት ብቻ ነበረች በእርሱ ፊት እውነተኞች ከሆናችሁ እናንተም ደግሞ እንደ እርስዋ መባረክ ትችላላችሁ «አምላኬ ሆይ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ አመነዝራለሁ ይህንን የማላውቀው በተደጋጋሚ ስለማደርገው ነው እኔ በእያንዳንዱ ቀን ይህንን ሐጢያት ብዙ ጊዜ አደርገዋለሁ።»

«አምላኬ ሆይ እኔ እንደዚህ ነኝ እባክህ አድነኝ» በማለት ሕጉንና መሞት የሚገባንና በእግዚአብሄር ፊት በቅንነት መቅረብ የሚገባን ሐጢያተኞች የመሆናችንን እውነታ ስንቀበል

እግዚአብሄር በቤዛነቱ ይባርከናል።
የኢየሱስ ፍቅር የሆነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል የእግዚአብሄርን ቅን ፍርድ አሸንፎዋል *«እኔም አልፈርድብሽም»* እርሱ አይኮንነንም እርሱ «ድናችኋል» ብሎናል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የርህራሄ አምላክ ነው ከአለም ሐጢያቶችም ሁሉ አድኖናል።
አምላካችን የፍትህ አምላክና የፍቅር አምላክ ነው የውሃውና የመንፈሱ ፍቅር ከፍርዱም የላቀ ነው።
የኛ እግዚአብሔር የፍርድና የፍቅር አምላክ ነው። የጥምቀቱና የመንፈስ ቅዱሱ ፍቅርም ከፍርዱ የበለጠ ነው።

## ፍቅሩ ከፍርዱ ይበልጣል

*እርሱ ሁላችንንም የዋጀን ለምንድነው?*

*ፍቅሩ ከፍርዱ ስለሚበልጥ ነው።*

እግዚአብሄር የራሱን ፍትህ ለማጠናቀቅ ፍርዱን ተግብሮ ቢሆን ኖሮ በሐጢያተኞች ሁሉ ላይ ፈርዶ ሲያል በላካቸው ነበር ነገር ግን ከፍርድ ያዳነን የኢየሱስ ፍቅር ስለሚበልጥ እግዚአብሄር አንድ ልጁን ኢየሱስን ላከው ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በራሱ ላይ ወስዶ ስለ ሁላችንም ቅን

ፍርድን ተቀበለ አሁን ኢየሱስን አዳኙ አድርጎ የሚያምን ማንኛ ውም ሰው የእርሱ ልጅና ጻድቅ ይሆናል ፍቅሩ ከፍርዱ ስለሚበልጥ ሁላችንንም አድኖናል፡፡

እግዚአብሄር በፍርዱ ብቻ ስላልኮነነን ልናመሰግነው ይገባናል አንድ ጊዜ ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ጸሐፍትንና ደቀ መዛሙርቶቻቸውን እንዲህ አላቸው «ምህረትን እወዳለሁ መስዋዕትንም አይደለም የሚለውን ሄዳችሁ ተማሩ ሐጢያተኞችን ለንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና» (ማቴዎስ 9፡13) አንዳንድ ሰዎች «አምላክ ሆይ በየቀኑ የምሰራቸውን ሐጢያቶች ይቅር በለኝ» እያሉ በመጸለይ በየቀኑ ላም ወይም ፍየል እያረዱ በእግዚአብሄር ፊት ያቀርቡ ይሆናል እግዚአብሄር የሚፈልገው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ላይ ያለንን አመኔታ እንጂ ቁርባኖቻችንን አይደለም እንድንዋጅና እንድንድን ይፈልጋል ፍቅሩን ሊሰጠንና አመኔታችንን ሊቀበል ይፈልጋል ይህንን ሁሉ ማየት ትችላላችሁን? ኢየሱስ ፍጹም የሆነውን ደህንነቱን ሰጥቶናል፡፡

ኢየሱስ ኃጢያትን ይጠላል ሆኖም ግን በእግዚአብሔር አምሳል ለተፈጠርነው ሰዎች የሚያቃጥል ፍቅር አለው የእርሱ ልጆች ሊያደርገንና በጥምቀቱና በደሙ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ሊደመስስ የወሰነው ከፍጥረት በፊት ነው እግዚአብሄር የፈጠረን ውሎ አድሮ ሊዋጀን በኢየሱስ ሊያለብሰንና የራሱ ልጆች ሊያደርገን ነው እርሱ ለፍጥረቶቹ ያለው ፍቅር ይህ ነው፡፡

እግዚአብሄር ትክክለኛ በሆነው ሕጉ መሰረት ቢፈርድብን ኖሮ እኛ ሐጢያተኞች ሁላችንም በሞትን ነበር እርሱ ግን በጥምቀቱና በመስቀል ላይ በሆነው የልጁ ፍርድ አማካይነት አዳነን ታምናላችሁን? ይህንን ከብሉይ ኪዳን እናረጋግጥ፡፡

# አሮን በሚለቀቀው ፍየል ላይ እጆቹን ጫነ

*የእስራኤልን ሐጢያቶች ወኪላቸው ወደሆነው የሚለቀቅ ፍየል ያስተላለፈው ማነው?*

*ሊቀ ካህኑ*

የዚህ አለም ሐጢያቶች በሙሉ በብሉይ ኪዳን ስርአትና በአዲስ ኪዳን ጥምቀት በሚያምነው እምነት አማካይነት ተሰርየዋል በብሉይ ኪዳን የእስራኤሎች አመታዊ ሐጢያቶች በሙሉ እጆቹን አንዳች እንከኖች በሌሉበት ሕያው ፍየል ራስ ላይ በጫነው ሊቀ ካህን አማካይነት ስርየትን አግኝተዋል፡፡

*«አሮንም ሁለቱን እጆች በሕያው ፍየል ራስ ላይ ይጭናል በላዩም የእስራኤል ልጆች በደል ሁሉ መተላለፋቸውንም ሁሉ ኃጢያታቸውንም ሁሉ ይናዘዛል በፍየሉም ራስ ላይ ያሸክመዋል በተዘጋጀው ሰውም እጅ ወደ ምድረ በዳ ይሰደዋል፡፡» (ዘሌዋውያን 16:21)*

በብሉይ ኪዳን ዘመን ስርየትን ያገኙት እንደዚህ ነበር አንድ ሰው ከዘወትር ሐጢያቶቹ ለመዳን እንከን የሌለበት በግ ወይም ፍየል ወደ መገናኛው ድንኳን ያመጣና በመሰውያው ላይ ያቀርበዋል እጆቹን በመስዋዕቱ ራስ ላይ ይጭናል ከዚያም ሐጢያቶቹ ወደ መስዋዕቱ ይተላለፋሉ መስዋዕቱም ይታረዳል ካህኑም ደሙን በመሰውያው ቀንዶች ላይ ይቀባዋል፡፡

በመሰውያው በአራቱ ማዕዘናት ላይ ቀንዶች ነበሩ እነዚህ ቀንዶች የሚያመላክቱት በራዕይ 20:12 ላይ የተጻፉትን የምግባር መጽሐፎች ነው ቀሪው የመስዋዕቱ ደምም በመሬቱ

ላይ ይፈሳል መሬቱ የሚያመላክተው የሰውን ልብ ነው ምክንያቱም ሰው የተፈጠረው ከአፈር ነውና ሕዝቡ የዘወትር ሐጢያቶቹን ስርየት ያገኘው በዚህ መንገድ ነው።

ነገር ግን በየቀኑ የሐጢያት ቁርባኖችን ማቅረብ ስለማይችሉ ለአመታዊዎቹ ሐጢያቶቻቸው ሁሉ በአመት አንድ ጊዜ ስርየትን እንዲያገኙ ፈቀደላቸው ይህ የስርየት ቀን በሆነው በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን የሚከናወን ነበር በዚያ ቀን የእስራኤሎች ሁሉ ወኪል የሆነው ሊቀ ካህኑ ሁለት ፍየሎችን አቅርቦ የሕዝቡን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እነርሱ ያስተላልፍና ለእስራኤል ሕዝብ ማስተሰረያ ያደርግ ዘንድ በእግዚአብሄር ፊት ያቀርባቸዋል።

*«አሮንም ሁለቱን እጆች በሕያው ፍየል ራስ ላይ ይጭናል፣ በላዩም የእስራኤል ልጆች በደል ሁሉ መተላለፋቸውንም ሁሉ ኃጢያታቸውንም ሁሉ ይናዘዛል በፍየሉም ራስ ላይ ያሸክመዋል በተዘጋጀው ሰውም እጅ ወደ ምድረ በዳ ይሰደዋል።»*

እግዚአብሄር የእስራኤልን ሊቀ ካህን አሮንን ወኪላቸው እንዲሆን ሾመው እያንዳንዱ ሰው በግሉ እጆቹን በመስዋዕቶቹ ላይ ከሚጭን ይልቅ የሕዝቡ ሁሉ ወኪል የሆነው ሊቀ ካህን የአመቱን ሐጢያቶች ለማስተሰረይ እጆቹን በሕያው ፍየል ላይ ይጭን ነበር።

እርሱ በእግዚአብሄር ፊት የእስራኤልን ሐጢያቶች በሙሉ ይተርካል «አምላክ ሆይ የእስራኤል ልጆችህ ሐጢያትን ሰርተዋል ጣዖታትን አምለከናል የሕግህን አንቀጾች ተላልፈናል ስምህን በከንቱ ጠርተናል ሌሎች ጣዖታትን ሰርተን ከአንተ ይልቅ ወደናቸዋል የሰንበትን ቀን ቅዱስ አድርገን አልጠበቅንም ወላጆቻችንን አላከበርንም ገድለናል አመንዝረናል ሰርቀናል... ቅንአትንና ጥልን ተግብረናል።»

እርሱ ሐጢያቶችን ሁሉ ዘረዘረ «አቤቱ የእስራኤል ሕዝብም ሆነ እኔ ከሕግህ አንዳቸውንም መጠበቅ አልቻልንም ከእነዚህ ሁሉ ሐጢያቶች ለመዳን እጆቼን በዚህ ፍየል ራስ ላይ ጭኜ እነዚያን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ አስተላልፋለሁ» ሊቀ ካህኑ በሕዝቡ ሁሉ ፋንታ እጆቹን በመስዋዕቱ ላይ ጭኖ ሐጢያቶችን ሁሉ ወደ መስዋዕቱ ያስተላልፋል እጆችን መጫን ማለት «ማስተላለፍ» ማለት ነው:: (ዘሌዋውያን 1:1-4፤16:20-21)

*በብሉይ ኪዳን ዘመን ስርየት የተፈጸመው እንዴት ነበር?*

*እጆችን በሐጢያት መስዋዕቱ ራስ ላይ በመጫን ነበር::*

እግዚአብሄር የመስዋዕቱን ስርአት ለእስራኤል ሕዝብ የሰጣቸው ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ እንዲያስተላልፉና እንዲድኑ ነው ሰው እንከን የሌለበትን የሐጢያት መስዋዕት ማዘጋጀት እንደሚገባውና ያ መስዋዕትም በእርሱ ምትክ መሞት እንዳለበት በግልጽ አስቀምጦዋል የግለሰብ ሐጢያተኞች ቤዛነት የሚከናወነው እንደዚህ ነበር::

በስርየት ቀን ግን የሐጢያት መስዋዕቱ ይታረድና ደሙ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ተወስዶ በስርየት መክደኛው ላይ ሰባት ጊዜ ይረጫል በዚህም የእስራኤል ሕዝብ በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን ከአመቱ ሐጢያት ስርየትን ያገኛሉ::

ሊቀ ካህኑ መስዋዕቱን ለማቅረብ የሚገባው ብቻውን ነው ሰዎች ግን በውጭ ተሰብስበው በሊቀ ካህኑ የኤፉድ ቀሚስ

ዘርፍ ላይ ያሉትን የወርቅ ቃጭሎች ያደምጣሉ ደሙ በስርየት መክደኛው ላይ ሲረጭ የወርቅ ቃጭሎቹ ሰባት ጊዜ ይደውላሉ ያን ጊዜ ሕዝቡ ሐጢያቶቻቸው ስርየትን ስላገኙ ይደሰታሉ የወርቅ ቃጭሎቹ ድምጽ የሚያመላክተው የአስደሳቹን ወንጌል ድምጽ ነው፡፡

ኢየሱስ የሚወደው አንዳንድ የተመረጡ ሰዎችን ነው የሚያድናቸውም እነርሱን ብቻ ነው የሚለው አባባል እውነት አይደለም ኢየሱስ በጥምቀቱ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለአንዴና ለዘላለም አስወግዶዋል ሐጢያቶቻችን በየቀኑ ሊዋጁ ስለማይችሉ በአንድ ጊዜ ተደምስሰዋል፡፡I

በብሉይ ኪዳን ስርየት የሚሰጠው በሐጢያት መስዋዕቱ ላይ እጅ በመጫንና በደም ነበር አሮን በሕዝቡ ሁሉ ፊት እጆቹን በሕያው ፍየል ራስ ላይ ጭኖ ሕዝቡ በአመቱ ውስጥ የሰራቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ዘረዘረ በእስራኤሎች ሁሉ ፊትም ሐጢያቶችን ወደ ፍየሉ አስተላለፈ ሊቀ ካህኑ በሚለቀቀው ፍየል ላይ እጆቹን ከጫነ በኋላ የሕዝቡ ሐጢያቶች ወዴት ሄዱ? ሁሉም ወደ ፍየሉ ተላልፈዋል፡፡

ከዚያም ፍየሉ «በተዘጋጀው ሰው» ይሰደዳል የእስራኤሎችን ሐጢያቶች በሙሉ የተሸከመው ፍየል ውሃና ሳር ወደሌለበት ምድረ በዳ ይወሰዳል ከዚያም ፍየሉ በምታቃጥለው ጸሐይ እየነደደ በምድር በዳ ይቅበዘበዝና በመጨረሻም ይሞታል ፍየሉ የሞተው ለእስራኤላውያን ሐጢያቶች ነው፡፡

ይህ የእግዚአብሄር ፍቅር የቤዛነት ፍቅር ነው በዚያ ዘመን የአመቱ ሐጢያቶች ስርየትን የሚያገኙት በዚህ መንገድ ነው እኛ የምንኖረው ግን በአዲስ ኪዳን ዘመን ነው ኢየሱስ ወደ አለማችን ከመጣ 2000 አመታት ሆነውታል እርሱ መጥቶ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተሠጠውን ተስፋ ፈጸመ መጥቶም ከሐጢያቶቻችንን ሁሉ ዋጀን፡፡

# ሁላችንንም ለመዋጀት

*የኢየሱስ ትርጉም*
*ምንድን ነው?*

*ሕዝቡን ከኃጢያቶቻቸው*
*የሚያድን አዳኝ ማለት ነው።*

ማቴዎስ 1:20-21ን እናንብብ *«እርሱ ግን ይህን ሲያስብ እነሆ የጌታ መልኣክ በህልም ታየው፣ እንዲህም አለ- የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ እርስዋ የፀነሰችው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ ልጅም ትወልዳለች እርሱም ሕዝቡን ከኃጢያታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።» (ማቴዎስ 1:20-21)*

በሰማይ የሚኖረው አባታችን የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለማንጻት ልጁን ወደዚህ አለም ለመላክ ሲል የድንግል ማርያምን ሰውነት ተበደረ ወደ ማርያም መልአክን ልኮም እንዲህ አላት *«እነሆ ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ»* ይህ ማለት በማርያም በኩል የሚመጣው ወንድ ልጅ አዳኝ ይሆናል ማለት ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ማለት ሕዝቡን ከሐጢያቶቻቸው የሚያድን ማለትም አዳኝ ማለት ነው።

ታዲያ ኢየሱስ ሁላችንንም ከሐጢያቶቻችን እንዴት አዳነን? ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ የወሰደው በዮርዳኖስ ወንዝ በተቀበለው ጥምቀት አማካይነት ነው

አጥማቂው ዮሐንስ ባጠመቀው ጊዜ የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ ተላልፈዋል እስቲ ማቴዎስ 3፡13-17ን እናንብብ፡፡

*«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃው ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ እርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም ድምጽ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ፡፡»*

ኢየሱስ ሁላችንንም ከሐጢያቶቻችን ሊያድነን ወደ አጥማቂው ዮሐንስ ሄደ ውሃ ውስጥ ገብቶም በዮሐንስ ፊት ራሱን ዝቅ አደረገ «ዮሐንስ አሁን አጥምቀኝ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድና ሐጢያተኞችንም ሁሉ ከሐጢያቶቻቸው ለማዳን ሐጢያቶቻቸውን በጥምቀት መውሰድ ያስፈልገኛል አሁኑኑ አጥምቀኝ! ፍቀድ!»

ስለዚህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባል ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ በዚያች ቅጽበትም ሐጢያቶቻችንን የዋጀው የእግዚአብሄር ጽድቅ በሙሉ ተፈጸመ፡፡

እርሱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ የወሰደው በዚህ መንገድ ነው የእናንተም ሐጢያቶች በሙሉ እንደዚሁ ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል ይህ ገብቶዋችኋልን?

በኢየሱስ ጥምቀትና መንፈስ ቤዛነት አምናችሁ ዳኑ፡፡




እግዚአብሄር የአለም ሐጢያቶች ለሐጢያት በሚቀርበው መስዋዕት ላይ በእጆች መጫን እንደሚወገዱ አስቀድሞ ለእስራኤል ተስፋ ሰጥቶዋል ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው በግሉ እጆቹን በፍየሉ ራስ ላይ መጫን ስለማይቻለው እግዚአብሄር አሮንን ለሕዝቡ ሁሉ መስዋዕትን ማቅረብ እንዲችል ሊቀ ካህን አድርጎ ቀደሰው እርሱም አመታዊውን ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ በአንድ ጊዜ ለሐጢያት በቀረበው መስዋዕት ራስ ላይ አስተላለፈ የእግዚአብሄር ጥበብና የቤዛነቱ ሐይል ይህ ነበር

እግዚአብሄር መላውን አለም ለማዳን ልጁን ኢየሱስን ላከው የሐጢያቱም መስዋዕት ተዘጋጀ እጆቹን በኢየሱስ ራስ ላይ የሚጭንና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ የሚያስተላልፍ የሰው ዘር ሁሉ ወኪል መኖር ነበረበት ያም ወኪል አጥማቂው ዮሐንስ ነበር እግዚአብሄር የሰውን ዘር ሁሉ ወኪል ከኢየሱስ አስቀድሞ እንደላከው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎዋል፡፡

ይህም የሰው የመጨረሻው ሊቀ ካህን አጥማቂው ዮሐንስ ነበር በማቴዎስ 11:11 ላይ እንደተጻፈው *«እውነት እውነት እላችኋለሁ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሳም»* እርሱ ብቸኛው የሰዎች ወኪል ነው እግዚአብሄር ዮሐንስን የሰዎች ሁሉ ወኪል አድርጎ የላከው

ኢየሱስን እንዲያጠምቅና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ እንዲያስተላልፍ ነበር።

በምድር ላይ ያለው ስድስት ቢሊዮን ሕዝብ አሁኑኑ ወደ ኢየሱስ ቀርበው ሐጢያቶቻቸውን ለማስተላለፍ እጆቻቸውን በኢየሱስ ላይ ቢጭኑ ምን ይፈጠር ነበር? በዚህ አለም ላይ የሚኖረው ከስድስት ቢሊዮን በላይ የሚሆን ሕዝብ እጆቻቸውን በኢየሱስ ላይ ቢጭኑ ደስ የሚል ትዕይንት አይታይም አንዳንድ ስሜታቸውን መቆጣጠር የማይችሉ ሰዎች በጣም ስለሚጫኑት ጸጉሩ በሙሉ ከላዩ ላይ ይረግፋል ስለዚህ እግዚአብሔር በጥበቡ ወኪላችን ሆኖ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ወደ ኢየሱስ እንዲያስተላልፍ ዮሐንስን ሾመው።

በማቴዎስ 3:13 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«ያን ጊዜ ኢየሱስም በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ»* ይህ የሆነው ኢየሱስ 30 አመት በሆነው ጊዜ ነበር ኢየሱስ የተገረዘው በተወለደ በ8 ቀኑ ነበር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ 30 አመት እስኪሆነው ድረስ ስለ እርሱ የተጻፉት ነገሮች ጥቂቶች ናቸው።

ኢየሱስ 30 አመት እስኪሆነው ድረስ የጠበቀበት ምክንያት በብሉይ ኪዳን መሰረት ሕጋዊ የሰማይ ሊቀ ካህን ለመሆን ነበር እግዚአብሔር በዘዳግም ውስጥ ሊቀ ካህኑ በሊቀ ክህነት ማገልገል ከመቻሉ በፊት ቢያንስ 30 አመት ሊሆነው እንደሚገባ ለሙሴ ነግሮታል ኢየሱስ ሰማያዊ ሊቀ ካህን ነበር ይህንን ታምናላችሁን?

በአዲስ ኪዳን በማቴዎስ 3:13-14 ላይ እንዲህ ይላል *«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን፦ እኔ በአንተ ልጠመቅ ይገባኛል አንተ ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር»* የሰው ዘር ወኪል ማነው? አጥማቂው ዮሐንስ ነው የሰማይ ወኪልስ ማነው? ኢየሱስ

ክርስቶስ ነው ወኪሎቹ ተገናኙ ታዲያ የሚበልጠው ማነው? የሰማይ ወኪል እንደሚበልጥ የታወቀ ነው::

በዚያ ዘመን ለነበሩት የሐይማኖት መሪዎች *«የእፉኝት ልጆች! ንስሐ ግቡ!»* በማለት የጮኸው አጥማቂው ዮሐንስ ድንገት በኢየሱስ ፊት ትሁት ሆነ *«እኔ በአንተ እጠመቅ ዘንድ ይገባኛል እንጂ አንተ ወደ እኔ ትመጣለህን?»*

እዚህ ላይ ኢየሱስ እንዲህ አለ *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና»* ኢየሱስ የእግዚአብሄርን ጽድቅ ለመፈጸም ወደዚህ አለም መጣ ይህም አጥማቂው ዮሐንስ ባጠመቀው ጊዜ ተፈጸመ::

*«ያን ጊዜ ፈቀደለት ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃው ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ እርግብ ሲወርድ በእርሱም ላይ ሲመጣ አየ እነሆም ድምፅ ከሰማይ መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ::»*

እርሱ በተጠመቀ ጊዜ የሆነው ይህ ነው እርሱ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በወሰደ ጊዜ የሰማይ ደጆች ተከፈቱ::

*«ከመጥምቁም ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግስተ ሰማያት ትገፋለች ግፈኞችም ይናጠቋታል::» (ማቴዎስ 11:12)*

የእግዚአብሄር ነቢያትና ሕጉ ሁሉ እስከ አጥማቂው ዮሐንስ ድረስ ትንቢት ተናገሩ *«ከመጥምቁ ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግስተ ሰማያት ትገፋለች ግፈኞች ይናጠቋታል»*. በእርሱ ጥምቀት የሚያምን ሁሉ ያለምንም ገደብ መንግስተ ሰማይ መግባት ይችላል::

# *«እኔም አልፈርድብሽም»*

*ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለምን ተፈረደበት?*

*የኛን ኃጢያት በሙሉ ስለወሰደ ነው::*

ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠምቆ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ በኋላም በምንዝር ለተያዘችው ሴት *«እኔም አልፈርድብሽም»* አላት እርሱ በዮርዳኖስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ስለወሰደ ለእነዚህ ሐጢያቶችም መኮነን የነበረበት እርሱ ራሱ ስለነበር ሴቲቱን አልኮነናትም::

ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ደምስሶዋል *«የሐጢያት ደመወዝ ሞት»* ስለሆነ በመስቀል ላይ የሚደርስበትን ስቃይ ምን ያህል ፈርቶ እንደነበር ማየት እንችላለን እግዚአብሄር ይህንን ፍርድ እንዲያስወግድለት በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ሦስት ጊዜ ጸልዮ ነበር ኢየሱስ እንደ ሌሎች ሰዎች ሁሉ ስጋና ደም ስለነበር ስቃዩን መፍራቱ ተገቢ ነው ኢየሱስ ፍርዱን ለመፈጸም መድማት ነበረበት::

በብሉይ ኪዳን ለሐጢያት የሚቀርቡት መስዋዕቶች የሐጢያቶችን ዋጋ ለመክፈል ይደሙ እንደነበር ሁሉ እርሱም በመስቀል ላይ መስዋዕት መሆን ነበረበት ቀደም ብሎ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል አሁን ለእኛ ቤዛነት ሲል ሕይወቱን መስጠት ነበረበት በእግዚአብሄር ፊት ፍርድን መቀበል እንደነበረበት አውቋል::

ኢየሱስ በልቡ ውስጥ ምንም ኃጢያት አልነበረበትም ነገር

ግን በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ ስለተላለፉ አሁን እግዚአብሄር በልጁ ላይ ፈረደ ስለዚህ በመጀመሪያ ደረጃ የእግዚአብሄር ፍትህ ተፈጸመ በሁለተኛ ደረጃ እርሱ ለደህንነታችን ሲል ፍቅሩን ሰጠን ስለዚህ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መኮነን ነበረበት፡፡

«እኔም አልኮንንሽም አልፈርድብሽምም» አቅደንም ሆነ ሳናቅድ አውቀንም ሆነ ሳናውቅ የሰራናቸው ሐጢያቶቻችን በሙሉ በእግዚአብሄር ይፈረድባቸዋል፡፡

ሆኖም እግዚአብሄር አልፈረደብንም እግዚአብሄር በጥምቀቱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በራሱ ላይ በወሰደው በኢየሱስ ላይ ፈረደ እግዚአብሄር ከፍቅሩና ከርህራሄው የተነሳ በሐጢያተኞች ላይ ሊፈርድ አልፈለገም ጥምቀቱና በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደሙ እርሱ ለእኛ ያለው የቤዛነት ፍቅሩ ነበር *«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር እንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና፡፡» (ማቴዎስ 3:16)*

ፍቅሩን የምናውቀው በዚህ መልኩ ነው ኢየሱስ በምንዝር የተያዘችውን ሴት አልኮነናትም፡፡

እርስዋ በምንዝርና ድርጊት ተይዛ ስለነበር ሐጢያተኛ መሆንዋን አውቃለች እርስዋ በልብዋ ውስጥ ሐጢያት የነበረባት ከመሆንዋም በላይ ይህንን ሐጢያት በስጋዋም ተሸክማ ነበር ሐጢያትዋን የምትክድበት ምንም መንገድ አልነበረም ነገር ግን ኢየሱስ ሐጢያቶችዋን በሙሉ እንደወሰደ ስላመነች ዳነች እኛም በኢየሱስ ቤዛነት ብናምን እንድናለን ይህንን እመኑ! ለራሳችን ጥቅም ነው፡፡

*በጣም የተባረኩት*
*እነማን ናቸው?*

*ኃጢያት የሌለባቸው*
*ናቸው።*

ሁሉም ሰዎች ኃጢያትን ይሰራሉ ሰዎች ሁሉ ዝሙትን ይፈጽማሉ ነገር ግን ሰዎች ሁሉ ስለሰሩት ሐጢያቶቻቸው አልተፈረደባቸውም ሁላችንም ሐጢያት ሰርተናል ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት የሚያምኑ ሰዎች በልቦቻቸው ሐጢያት አልባ ናቸው በኢየሱስ ደህንነት የሚያምን ሰው እጅግ ደስተኛ ሰው ነው ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ የዳኑ ሰዎች እጅግ የተባረኩ ናቸው በሌላ አነጋገር አሁን በኢየሱስ ጻድቃን ናቸው።

እግዚአብሄር በሮሜ 4:7 ላይ ስለ ደስታ ነግሮናል *«ዓመጻቸው የተሰረየላቸው ኃጢያታቸውም የተከደነላቸው ብፁዓን ናቸው»* ሁላችንም እስከምንሞትበት ጊዜ ድረስ ሐጢያት እንሰራለን የእርሱን ሕግ ካወቅን በኋላም ሐጢያት በመስራት እንቀጥላለን እኛ በጣም ደካሞች ነን።

እግዚአብሄር ግን በአንድያ ልጁ ጥምቀትና ደም አድኖን ለእናንተ እና ለእኔ ዳግመኛ ሐጢያተኞች እንዳይደለን አሁን በፊቱ ጻድቃኖች መሆናችንን ነገረን የእርሱ ልጆች እንደሆንም ነገረን።

የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል የዘላለም ቤዛነት ወንጌል ነው ይህንን ታምናላችሁን? እርሱ የሚያምኑ ሰዎችን ጻድቃን የተዋጁና የራሱ ልጆች ብሎ ጠርቶዋቸዋል በዚህ አለም ላይ እጅግ ደስተኛው ሰው ማነው? በእውነተኛው ወንጌል ያመነና የዳነ ሰው ነው ድናችኋልን?

ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን ሲወስድ ያስቀረው አለን? የለም በጥምቀቱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶዋል ይህንን እመኑ እመኑና ከሐጢያቶቻችሁ ሁሉ ተዋጁ ዮሐንስ 1:29ን እናንብብ።

## ልክ በመጥረጊያ እንደተጠረገ ያህል




*«በነገው ዮሐንስ ኢየሲስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ- እነሆ የዓለምን ኃጢየት የሚስወግድ የእብዚአብሔር በግ!» (ዮሐንስ 1:29)*

*«እነሆ የዓለምን ኃጢየት የሚስወግድ የእብዚአብሔር በግ!»*

አጥማቂው ዮሐንስ በዮርዳኖስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ አስተላለፈ በነገውም ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ የሚያስወግድ የእግዚአብሄር በግ እንደሆነ መሰከረ እርሱ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በጫንቃው ተሸከመ።

የአለም ሐጢያቶች ሁሉ የሚያመላክቱት ሰዎች ከፍጥረት ጀምሮ እስከ መጨረሻ ድረስ የሚሰሩዋቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ነው ኢየሱስ ከ2000 አመታት በፊት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶ አዳነን የእግዚአብሄር በግ በመሆኑም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወሰደ ስለ እኛም ተኮነነ።

እኛ ሰዎች የምንሰራው ማንኛውም ሐጢያት ወደ ኢየሱስ ተላልፎዋል እርሱም የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ የወሰደ የእግዚአብሄር በግ ሆነ።

ኢየሱስ ትሁት ሆኖ የአለምን ሐጢያተኞች በሙሉ የሚያድን ሰው ሆኖ ወደዚህ አለም መጣ እኛ ሐጢያት የምንሰራው ደካሞች ክፉዎች መሐይሞች ገልቱዎችና ጎዶሎዎች ስለሆንን ነው በሌላ አነጋገር ሐጢያት የምንሰራው የሁላችንም አያት ከሆነው ከአዳም ሐጢያትን ስለወረስን ነው እነዚህ ሁሉ ሐጢያቶች ተጠርገው በዮርዳኖስ ወንዝ ላይ በወሰደው ጥምቀት በኢየሱስ ራስ ላይ ተጫኑ እርሱም በመስቀል ላይ በስጋው ሞት ሁሉንም አስወገደ ተቀበረ እግዚአብሄር ግን በሦስተኛው ቀን ከሙታን አስነሳው።

እርሱ አሁን የሐጢያተኞች ሁሉ አዳኝ ድል አድራጊና ፈራጅ ሆኖ በእግዚአብሄር ቀኝ ተቀምጦዋል እርሱ እኛን ደጋግሞ ማዳን አይኖርበትም እኛ ለመዳን ማድረግ ያለብን በእርሱ ማመን ነው የሚያምኑ ሰዎች የዘላለም ሕይወት ይጠብቃቸዋል የማያምኑ ሰዎች ግን ጥፋት ይጠብቃቸዋል ሌላ ምርጫ የለም።

ኢየሱስ ሁላችሁንም አድኖዋችኋል እናንተ በምድር ላይ እጅግ ደስተኛ ሰዎች ናችሁ በድክመቶቻችሁ ምክንያት ወደፊትም ሐጢያት እንደምትሰሩ የታወቀ ነው እርሱ ግን እነዚያንም ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል።

በልባችሁ ውስጥ የቀረ አንዳች ሐጢያት አለን? —የለም—

ኢየሱስ ሁሉንም ወስዶታል? —አዎን! ወስዶታል።—

ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ ናቸው ማንም ሰው ከባልንጀራው በላይ ቅዱስ አይደለም ነገር ግን ብዙ ሰዎች ግብዞች ስለሆኑ በእርግጥ ሐጢያተኞች ሆነው ሳሉ ሐጢያተኞች እንዳልሆኑ ያምናሉ ይህ አለም ሐጢያትን የሚንከባከብ የጥላ ቤት ነው።

ሴቶች ከቤታቸው ሲወጡ ሊፒስቲክ ይቀባሉ ፊታቸውን ያሰማምራሉ ጸጉራቸውን ይጠቀልላሉ ምርጥ ልብሶችን ይለብሳሉ ታኮ ጫማ ያደርጋሉ... ወንዶችም ደግሞ ጸጉራቸውን ለመቆረጥ ወደ ጸጉር ቤት ይሄዳሉ ራሳቸውን ያሰማምራሉ ንጹህ ሸሚዝ ይለብሳሉ አዲስ የመጣ ከረባት ያደርጋሉ ጫማቸውን ያሳምራሉ፡፡

ነገር ግን በውጭ ሲታዩ መስፍንና እትጌ መስለው ቢታዩም ውስጣቸው ግን ፈጽሞ የረከሰ ነው፡፡

ገንዘብ ሰዎችን ደስተኛ ያደርጋልን? ጤና ሰዎችን ደስተኛ ያደርጋልን? አያደርግም ሰዎችን እውነተኛ ደስተኞች የሚያደርጋቸው የዘላለም ቤዛነት የሐጢያቶች ሁሉ ይቅርታ ብቻ ነው ሰው ከውጭ ሲታይ ምንም ያህል ደስተኛ ቢመስል በልቡ ውስጥ ሐጢያት ካለበት ይህ ሰው ምስኪን ነው ይህ ሰው በፍርድ ፍርሃት ውስጥ ይኖራል፡፡

የዳነ ሰው ቡቱቶ ቢለብስም እንኳን እንደ አንበሳ ደፋር ነው በልቡ ውስጥ ሐጢያት የለም «ጌታ ሆይ አመሰግናለሁ እኔን ሐጢያተኛውን አዳንከኝ ሐጢያቶቼን በሙሉ ደመሰስህ እኔ ፍቅርህን ለመቀበል የተገባሁ አይደለሁም ነገር ግን ስላዳንከኝ አመሰግንሃለሁ እኔ ለዘላለም ከሐጢያቶቼ ድኛለሁ ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን!»

የዳነ ሰው በእርግጥም ደስተኛ ሰው ነው በእርሱ የቤዛነት ጸጋ የተባረከ ሰው በእርግጥም ደስተኛ ሰው ነው፡፡

*«የአለምን ሐጢያት የሚያስወግደው የእግዚአብሄር በግ»* ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ስለወሰደ እኛ ሐጢያት የለብንም እርሱ በመስቀል ላይ ደህንነትን *«ፈጽሞልናል»* የእናንተንና የእኔን ጨምሮ ሐጢያቶቻችን በሙሉ *«በአለም ሐጢያት»* ውስጥ ስለተካተቱ ሁላችንም ድነናል፡፡

# በእግዚአብሔር ፍቃድ

*በኢየሱስ ክርስቶስ*
*ውስጥ ስንሆን በልባችን ውስጥ*
*ኃጢያት ይኖራልን?*

*በፍጹም አይኖርም*

ውድ ወዳጆች በምንዝር የተያዘችው ሴት በኢየሱስ ቃሎች አመነችና ዳነች ታሪክዋ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው በእርሱ የዘላለም ቤዛነት ስለተባረከች ነበር ሆኖም ግብዞቹ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ከኢየሱስ ሸሹ፡፡

በኢየሱስ ብታምኑ የሚጠብቃችሁ ሰማይ ነው ኢየሱስን ብትተዉት ግን ሲዖል ትወርዳላችሁ በእርሱ የጽድቅ ምግባሮች ብታምኑ ሰማይ ይሆንላችኋል በእርሱ ስራዎች የማታምኑ ከሆነ ግን ሲዖል ይሆንባችኋል ቤዛነት በማንኛውም ሰው ውጥኖች የሚገኝ ሳይሆን በኢየሱስ ደህንነት የሚገኝ ነው፡፡

ዕብራውያን 10ን እናንብብ- *«ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር አምሳል ሳየሆን የነገር ጥላ አለውና ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር የሚያቀርቡት በዚያ መስዋዕት የሚቀርቡትን ሊፈጽም ከቶ አይችልም እንደዚህማ ባይሆን የሚያመልኩት አንድ ጊዜ ነፅተው ከዚያ በኋላ በህሊናቸው ኃጢያትን ስላላወቁ ማቅረብን መተው አልነበረምን? ነገር ግን በዚያ መስዋዕት በየዓመቱ የኃጢያት መታሰቢያ አለ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢያትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና ስለዚህ ወደ አለም ሲገባ- መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን*

*አዘጋጀህልኝ፣ በሙሉ በሚቃጠል መሥዋዕትና ስለ ኃጢያት በሚሠዋ መሥዋዕት ደስ አላለህም በዚያን ጊዜ- እነሆ በመፅሐፍ ጥቅልል ስለ እኔ እንደተጻፈ አምላኬ ሆይ ፍቃድህን ላደርግ መጥቻለሁ አለሁ ይላል በዚህ ላይ- መሥዋዕትንና መባን በሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕትንም ስለ ኃጢአትም የሚሠዋ መሥዋዕትን አልወደድህም በእነርሱም ደስ አላለህም ብሎ እነዚህም እንደ ህግ የሚቀርቡት ናቸው ቀጥሎ እነሆ አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ ብሎአል ሁለተኛ ውን ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል። በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል።» (ዕብራውያን 10:1-10)*

*«በእግዚአብሔር ፍቃድ»* ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በአንድ ጊዜ ለመውሰድ ሕይወቱን ሰጠ በአንድ ጊዜም ተኮነነ ትንሳኤንም አገኘ።

ስለዚህ ተቀድሰናል *«ተቀድሰናል» (ዕብራውያን 10:10)* የሚለው የተጻፈው ተፍጻሜትን በሚያሳየው የአሁን ጊዜ ነው ይህ ማለት ቤዛነታችን ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል ዳግመኛም መጠቀስ አያስፈልገውም ማለት ነው እናንተ ተቀድሳችኋል።

*«ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት በዕለት እያገለገለ ኃጢያትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉት እነዚያ መስዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሟል እርሱ ግን ስለ ኃጢያት አንድን መስዋዕት አንዴ ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ ጠላቶቹም የእግሩ መረጋገጫ እስኪሆኑ ድረስ ወደ ፊት ይጠብቃል አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና።» (ዕብራውያን 10:11-14)*

ሁላችሁም ለዘላለም ተቀድሳችኋል ነገ ሐጢያቶችን ብትሰሩ እንደገና ሐጢያተኞች ትሆናላችሁን? ኢየሱስ እነዚያንም ሐጢያቶች ደግሞ አልወሰደምን? ወስዶዋል እርሱ ወደፊት

የሚሰሩ ሐጢያቶችንም ደግሞ ወስዶዋል፡፡

*«መንፈስ ቅዱስም ደግሞ ለዚህ ይመሰክርልናል ከዚያ ወራት በኋላ ከእርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እፅፈዋለሁ ብሎ ከተናገረ በኋላ ኃጢያታቸውንና ዓመፃቸውንም ደግሜ አላስብም ይላል የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ሐጢያት ማቅረብ የለም፡፡» (ዕብራውያን 10:15-18)*

*«የእነዚህም ስርየት»* የሚለው ሐረግ እርሱ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ አስተሰርዮአል ማለት ነው ኢየሱስ አዳኛችን ነው የእናንተም የእኔም አዳኝ ነው በኢየሱስ ማመን አድኖናል ይህ የኢየሱስ ቤዛነት ነው ከእግዚአብሄር የተሰጠ እጅግ ታላቁ ጸጋና ስጦታም ነው ከሐጢያቶቻችን ሁሉ የተዋጀነው እናንተና እኔ ከሰዎች ሁሉ እጅግ የተባረክን ነን! ✉

# ስብከት 5

## የኢየሱስ ጥምቀትና

## የኃጥያቶች ስርየት

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግገን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡



ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

# የኢየሱስ ጥምቀትና የኃጥያቶች ስርየት

**« ማቴዎስ 3፡13-17 »**

**«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ፡፡ ዮሐንስ ግን- እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር ኢየሱስም መልሶ- አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃው ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ እርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ፡፡»**

## አሁንም ድረስ በኃጢያት የሚሰቃይ ይኖራልን?

*ከኃጢያት ጋር ያለን ቁርኝት አብቅቷልን?*

*አዎን፡፡*

እግዚአብሄር አምላካችን የሐጢያትን እግር ብረቶች ከሰዎች ሁሉ ላይ ቆርጦዋል ከሐጢያት በታች ሆነው

የተጨቆኑ ሰዎች ሁሉ የሐጢያት ባሮች ናቸው ጌታችን ግን በቤዛነቱ ፈጽሞ ነጻ አወጣቸው ሐጢያቶቻችንን በሙሉ አስወገደ አሁንም ድረስ በሐጢያት የሚሰቃይ ሰው አለን?

ከሐጢያት ጋር ያለን ጦርነት እንዳበቃ መረዳት ይኖርብናል ዳግመኛ በፍጹም በሐጢያት አንሰቃይም ኢየሱስ በጥምቀቱና በደሙ በዋጀን ጊዜ የሐጢያት ባርነታችን አብቅቷል የእግዚአብሄር ልጅ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ አስተሰርዮአል እግዚአብሄር ለዘላለም ነጻ ባወጣን በኢየሱስ አማካይነት የሐጢያቶቻችንን ሁሉ ዋጋ ከፍሎዋል፡፡

ምን ያህል ሰዎች በሐጢያቶቻቸው እንደሚሰቃዩ ታውቃላችሁን? ይህ የጀመረው በአዳምና በሔዋን ዘመን ነው ሰዎች ከአዳም በወረሱት ሐጢያቶች ተሰቃይተዋል፡፡

አምላካችን ግን በዘፍጥረት 3፡15 ላይ የተጻፈውን ቃል ኪዳን አደረገ ቃል ኪዳኑም ሐጢያተኞችን በሙሉ የሚያድን መሆኑ ነበር እርሱ ሰዎች በውሃውና በመንፈሱ በኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕትነት በኩል እንደሚዋጁ ተናግሮዋል ጊዜው ሲደርስም እግዚአብሄር በመካከላችን ይኖር ዘንድ አዳኛችንን ኢየሱስን ላከው፡፡

አጥማቂውን ዮሐንስንም ከኢየሱስ በፊት እንደሚልከው ቃል ገብቶ ቃሉን ጠብቋል፡፡

ማርቆስ 1፡1-8 እንዲህ ይላል *«የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ፡፡ እነሆ መንገድን የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ ተብሎ በነብዩ በኢሳያስ እንደ ተጻፈ ዮሐንስ በምድረ በዳ እያጠመቀ የንስሐንም ጥምቀት ለኃጢአት ስርየት እየሰበከ መጣ የይሁዳም አገር ሁሉ የኢየሩሳሌምም ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር ኃጢኣታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ*

*ከእርሱ ይጠመቁ ነበር ዮሐንስም የግመል ጠጉር ለብሶ በወገቡ ጠፍር ይታጠቅ አንበጣና የበረሃ ማርም ይበላ ነበር ተጎንብሼ የጫማውን ጠፍር መፍታት የማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ በኋላዬ ይመጣል እኔ በውኃ አጠመቃችኋለሁ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል እያለ ይሰብክ ነበር።»*

# አጥማቂው ዮሐንስ የወንጌል ፋና ወጊና መስካሪ




በግሪክ *«ባፕቲዞ»* የሚባለው ጥምቀት በመሰረቱ «መስረግ» ማለት ነው «መታጠብን መቀበርን መጥለምን ወይም ማስተላለፍን» ደግሞ ያመላክታል ኢየሱስ ሲጠመቅ የእግዚአብሄር ጽድቅ ተፈጸመ «ጽድቅ» በግሪክ *«ዲካዮሱኔ»* ነው ትርጓሜው «ጻድቅ መሆን» ማለት ነው «በጣም ተገቢ» «በጣም ተስማሚ» ወይም «እጅግ ያማረ ሁኔታ» ማለትም ጭምር ነው።

ኢየሱስ የተጠመቀው እጅግ ተስማሚና ተገቢ በሆነ ሁኔታ አዳኝ መሆን ይችል ዘንድ ነው ስለዚህ በኢየሱስ ጥምቀትና

መስቀል የሚያምኑ ሰዎች ከእግዚአብሄር ዘንድ የቤዛነትን ስጦታ ይቀበላሉ፡፡

በአዲስ ኪዳን አጥማቂው ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው ሊቀ ካህን ነበር ማቴዎስ 11፡10-11ን እንመልከት ጥቅሱ አጥማቂው ዮሐንስ የሰው ዘር ወኪል እንደሆነ ይናገራል በአዲስ ኪዳን ዘመን ሊቀ ካህን በመሆኑ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ አስተላለፈ በዚህም የብሉይ ኪዳንን ክህነት አገለገለ፡፡

ኢየሱስ ራሱ ስለ ዮሐንስ መስክሮዋል በማቴዎስ 11፡13-14 ላይ እንዲህ ብሎዋል *«ነቢያት ሁሉና ሕጉ እስከ ዮሐንስ ድረስ ትንቢት ተናገሩ ልትቀበሉትስ ብትወዱ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ ነው»* ስለዚህ ኢየሱስን ያጠመቀው አጥማቂው ዮሐንስ የሊቀ ካህኑ አሮን ዘርና የመጨረሻው ሊቀ ካህን ነበር፡፡(ሉቃስ 1፡5፤ 1ኛ ዜና 24፡10)

ታዲያ ዮሐንስ ከግመል ጠጉር የተሰራ ልብስ ለብሶ ብቻውን በምድረ በዳ የኖረው ለምንድነው? ሊቀ ክህነትን ለመቀበል ነበር አጥማቂው ዮሐንስ የሰው ዘር ሁሉ ወኪል በመሆኑ በሰዎች መካከል መኖር አልቻለም ስለዚህ ለሕዝቡ *«እናንተ የእፉኝት ልጆች ንስሐ ግቡ!»* በማለት ጮኸ ሰዎችን ሐጢያቶቻቸውን ወደሚወስድላቸው ወደ ኢየሱስ ለመመለስም የንስሐ ፍሬ እንዲሆንላቸው አጠመቃቸው አጥማቂው ዮሐንስ እጆቹን በኢየሱስ ራስ ላይ በጫነ ጊዜ የአለምን ሐጢያቶች ወደ ኢየሱስ አስተላልፎዋል፡፡

# ሁለት የጥምቀት አይነቶች

*መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎችን ያጠምቅ የነበረው ለምንድን ነበር?*

*ሰዎች ለሐጢያቶቻቸው ሁሉ ንስሐ እንዲገቡና ለደህንነታቸውም በኢየሱስ ጥምቀት እንዲያምኑ ለመምራት ነው::*

አጥማቂው ዮሐንስ ሰዎችን አጠመቀ ከዚያም ኢየሱስን አጠመቀው የመጀመሪያው ሐጢያተኞች ወደ እግዚአብሄር እንዲመለሱ የሚጠራ «የንስሐ ጥምቀት» ነበር በዮሐንስ በኩል የእግዚአብሄርን ቃሎች የሰሙ ብዙ ሰዎች ጣዖቶቻቸውን ትተው ወደ እግዚአብሄር ተመልሰዋል::

ሁለተኛው ጥምቀት የኢየሱስ ጥምቀት የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ የተላለፉበት ጥምቀት ነበር አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስ የእግዚአብሄርን ጽድቅ ይፈጽም ዘንድ አጠመቀው በሌላ አነጋገር ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ የተጠመቀው ሰዎችን ሁሉ ከሐጢያቶቻቸው ለማዳን ነበር:: (ማቴዎስ 3፡15)

ዮሐንስ ኢየሱስን ለምን አጠመቀው? እግዚአብሄር በእርሱ የሚያምኑ ሰዎች ይድኑ ዘንድ የአለምን ሐጢያቶች ለመደምሰስ ሲል ዮሐንስ ሐጢያቶችን በሙሉ ወደ ኢየሱስ እንዲያስተላልፍ ፈቀደ::

አጥማቂው ዮሐንስ የሰው ዘር በሙሉ በቤዛነት ወንጌል በማመን ንስሐ እንዲገባና ከሐጢያቶቹ ሁሉ እንዲነጻ በጥምቀት

አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ የማስተላለፍና ስለ ኢየሱስ የመመስከር ተልዕኮ የተሰጠው የእግዚአብሄር ባሪያ ነበር ስለዚህ ዮሐንስ ብቻውን በምድረ በዳ መኖር ነበረበት በአጥማቂው ዮሐንስ ዘመን ሕዝበ እስራኤል በሙሉ ተበላሽቶና እስከታች ድረስ በስብሶ ነበር፡፡

ስለዚህ እግዚአብሄር በብሉይ ኪዳን በሚልክያስ 4፡5-6 ላይ እንዲህ አለ *«እነሆ- ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል፡፡»*

በእግዚአብሄር አይን ከዚህ ቀደም የሆዋን ሲያመልኩ የነበሩ የእስራኤል ሕዝቦች በሙሉ ተበላሽተው ነበር በእርሱ ፊት ጻድቅ ሰው አልነበረም ለምሳሌ በተለይ የመቅደሱ የሐይማኖት መሪዎች ካህናት ሕግ አዋቂዎችና ጸሐፍቶች እስከ ታች ድረስ በስብሰው ነበር እስራኤሎችና ካህናቶቻቸው በእግዚአብሄር ሕግ መሰረት ተገቢ መስዋዕቶችን አላቀረቡም፡፡

ካህናት እግዚአብሄር ለሐጢያቶቻቸው ስርየት የሰጣቸውን እጆችን የመጫንና ደምን የማቅረብ ስርአት ትተውት ነበር በሚልክያስ ዘመን የነበሩት ካህናት ተገቢውን የመስዋዕት ስርአት እጆችን መጫንና የመስዋዕቱን እንስሳ ደም ማቅረብ ትተው ነበር፡፡

ስለዚህ አጥማቂው ዮሐንስ ከእነርሱ ጋር መቆየት አልቻለም ወደ ምድረበዳ ሄዶ ጮኸ ምን አለ?

የነቢዩን የኢሳይያስን ቃሎች በመጥቀስ በማርቆስ 1፡2-3 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«እነሆ መንገድን የሚጠርግ መልክተኛ ዬን በፊትህ እልካለሁ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ፡፡»*

የምድረ በዳው ድምጽ ሰዎች የንስሐ ጥምቀት እንዲቀበሉ

ነገራቸው መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው «የንስሐ ጥምቀት» ምንድነው? አጥማቂው ዮሐንስ የጮኸለት ጥምቀት ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ በሚወስድላቸው በእርሱ አምነው ይድኑ ዘንድ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ የሚመልስ ጥምቀት ነበር ወደ ደህንነት የሚመራቸው የንስሐ ጥምቀት ነበር፡፡

«ንስሐ ግቡ ተጠመቁም አዳኛችን ኢየሱስም ሐጢያቶቻችሁን በሙሉ ለመውሰድ በተመሳሳይ መንገድ ይጠመቃል» የአጥማቂው ዮሐንስ ጩኸት ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች እንደሚወስድና ሰዎች ሁሉ ወደ እግዚአብሄር ተመልሰው እንዲድኑ በመስቀል ላይ የሚኮነን መሆኑን የሚያውጅ ጩኸት ነበር፡፡

*«እኔ በውኃ አጠመቃችኋለሁ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል» «በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል»* ማለት ሐጢያቶቻችሁን ሁሉ ማንጻት ማለት ነው ማጥመቅ ማለት «ማጠብ» ማለት ነው በዮርዳኖስ ወንዝ የሆነው የኢየሱስ ጥምቀት የእግዚአብሄር ልጅ እኛን ለማዳን እንደተጠመቀና ሐጢያቶቻችንን ሁሉ እንደወሰደ ይነግረናል፡፡

ስለዚህ ከሐጢያተኛ ኑሮዋችን ተመልሰን በእርሱ ማመን አለብን እርሱ የአለምን ሐጢያቶች የወሰደ የእግዚአብሄር በግ ነው አጥማቂው ዮሐንስ የመሰከረለት የቤዛነት ወንጌል ይህ ነው፡፡

## ለኃጢያቶች ስርየት የሊቀ ካህኑ ተግባር




በነጻ የሚታደል መጽሐፍ ለመጠየቅ www.nlmission.com

ነብዩ ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ ተንብዮ ነበር *«ለኢየሩሳሌም ልብ ተናገሩ የተቀጠረችበት ወራት እንደተፈፀመ፣ ኃጢያትዋም እንደተሰረየ ከእግዚአብሔርም እጅ ስለ ኃጢአትዋ ሁሉ ሁለት እጥፍ እንደ ተቀበለች ወደ እርስዋ ጩኹ፡፡» (ኢሳይያስ 40:2)*

ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም ሳስቀር ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወሰደ የአዳም ሐጢያት አሁን ያሉት ሐጢያቶችና ወደፊት የሚሆኑት ሐጢያቶችም እንደዚሁ በእርሱ ጥምቀት ታጥበዋል እርሱ ሁላችንንም ዋጅቶናል ሁላችንም ስለ እግዚአብሄር ቤዛነት ማወቅ ይገባናል፡፡

ከሐጢያቶቻችን ለመዳን አጥማቂው ዮሐንስ በጥምቀት ዘዴ አማካይነት ሐጢያቶችን በሙሉ ወደ ኢየሱስ እንዳስተላለፈ በሚናገረው ወንጌል ማመን አለብን፡፡

«እግዚአብሄር ፍቅር ስለሆነ በልቦቻችን ውስጥ ሐጢያት ቢኖርም በኢየሱስ በማመን ብቻ መንግስተ ሰማይ መግባት እንችላለን» ብለን በማሰብ የተሳሳተ መረዳት መያዝ አይገባንም፡፡

ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ቤዛነትን ለማግኘት አጥማቂው ዮሐንስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ባስተላለፈበት ጥምቀትና መስቀል ማመን ይኖርብናል አጥማቂው ዮሐንስ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ያስተላለፈው «በውሃ» ነው፡፡

እግዚአብሄር እኛን ለማዳን ያደረገው የመጀመሪያው ነገር ዮሐንስን ወደዚህ አለም መላክ ነበር አጥማቂው ዮሐንስ የእግዚአብሄር መልዕክተኛ ስለሆነ በጥምቀቱ አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ያስተላለፈ የንጉስ አምባሳደር ሆኖ ተላከ የሰው ዘር ሁሉ ሊቀ ካህን በመሆንም አገለገለ፡፡

እግዚአብሄር መልዕክተኛውን አጥማቂውን ዮሐንስን እንደላከልን ነግሮናል *«በፊትህ መልዕክተኛን እልካለሁ»* በፊትህ ማለት በኢየሱስ ፊት ማለት ነው እግዚአብሄር ዮሐንስን

ከኢየሱስ በፊት ለምን ላከው? በጥምቀት አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ የእግዚአብሄር ልጅ ወደሆነው ወደ ኢየሱስ ለማስተላለፍ ነበር *«መንገድን በፊትህ ያዘጋጃል»* የምንባቡ ትክክለኛ ትርጉም ይህ ነው::

እኛ ድነን ሰማይ መሄድ እንችል ዘንድ መንገዱን የጠረገው ማነው? አጥማቂው ዮሐንስ ነው «በአንተ» ማለት ኢየሱስ ሲሆን «የኔ» ማለት ደግሞ እግዚአብሄር ራሱ ነው ስለዚህ *«መልዕክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ እርሱም መንገድን በፊትህ ያዘጋጃል»* ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሰማይ እንገባ ዘንድ መንገዳችንን የሚጠርገው ማነው? ሐጢያቶቻንን በሙሉ እንዳነጻቸው እንድናምን አጥማቂው ዮሐንስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወደ ኢየሱስ አስተላለፈ የእርሱ ተግባር ኢየሱስ ክርስቶስን በማጥመቅ ሐጢያቶቻችንን ማስተላለፍ ነው እኛ እውነቱን አምነን እንድንድን ያስቻሉን ኢየሱስና ዮሐንስ ነበሩ::

ደህንነታችን የተመሰረተው ምን ላይ ነው? የእግዚአብሄር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በሰራቸው የጽድቅ ስራዎችና የእግዚአብሄር መልዕክተኛ የሆነው አጥማቂው ዮሐንስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ ያስተላለፈ በመሆኑ እውነታ ላይ በማመን አለማመናችን ላይ ነው እግዚአብሄር አብ ልጁን የሚያጠምቀውን መልዕክተኛውን አስቀድሞ በመላክ የሰው ዘር ወኪል አደረገው በዚህም ለእኛ የቤዛነትን ስራ ፈጸመ::

እግዚአብሄር በኢየሱስ ላመኑ ሰዎች የደህንነትን መንገድ ያዘጋጅላቸው ዘንድ ልጁን እንዲያጠምቅለት አጥማቂውን ዮሐንስን ላከው ዮሐንስ ኢየሱስን ያጠመቀበት ምክንያት ይህ ነው ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ መጠመቁ ሰዎች ሁሉ በኢየሱስ አምነው ሰማይ ይገቡ ዘንድ የሰው ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ የተላለፉበት የእግዚአብሄር ቤዛነት ፍጻሜ ነበር፡

ሰዎች ወደፊት የሚሰሩዋቸው ሐጢያቶችም እንደዚሁ በጥምቀቱ አማካይነት ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል ኢየሱስና አጥማቂው ዮሐንስ አብረው ሁላችንም ሰማይ የምንገባበትን መንገድ አዘጋጁልን በዚህ መንገድ እግዚአብሄር በአጥማቂው ዮሐንስ አማካይነት የቤዛነትን ምስጢር ገለጠ፡፡

ዮሐንስ የሰው ዘር ወኪል በመሆን ቤዛነታችን አምነን ሰማይ እንገባ ዘንድ ኢየሱስን አጠመቀው በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶችን በሙሉ ወደ ኢየሱስ አስተላለፈ አስደሳቹ የቤዛነት ዜና ወንጌል ይህ ነው፡፡

## መጥምቁ ዮሐንስ ለምን ተወለደ?




በሚልክያስ 3:1 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«እነሆ መልክተኛዬን እልካለሁ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል»* መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ማንበብ ይኖርባችኋል እግዚአብሄር መልዕክተኛውን ከኢየሱስ ፊት ለምን ላከው? አጥማቂው ዮሐንስ ከኢየሱስ 6 ወራት ቀደም ብሎ ለምን ተወለደ?

መጽሐፍ ቅዱስ ስለምን እንደሚናገር መረዳት ይኖርብናል

ብሉይ ኪዳን የሊቀ ካህኑን የአሮንን ተግባር ያትታል አሮን የሙሴ ታላቅ ወንድም ነበር እግዚአብሄርም እርሱንና ልጆቹን ካህናት አድርጎ ቀባቸው ሌሎቹ ሌዋውያን ዕቃዎችን በማሰናዳት ሕብስትን ለመጋገር ዱቄትን በመለወስ ከእነርሱ በታች ሆነው ይሰሩ ነበር የአሮን ልጆች ደግሞ በተቀደሰው ድንኳን ውስጥ መስዋዕትን ያቀርቡ ነበር::

የአሮን ልጆች የተቀቡት በመካከላቸው እኩል የስራ ድርሻ እንዲኖራቸው ነው ነገር ግን የስርየት ቀን በሆነው በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን የሕዝቡን አመታዊ ሐጢያቶች ለማስተሰረይ የሚቀርበውን መስዋዕት የሚያቀርበው ግን ሊቀ ካህኑ ብቻ ነበር::

በሉቃስ 1:5 ላይ ስለ አጥማቂው ዮሐንስ የዘር ሐረግ የተጻፈ ታሪክ አለ ኢየሱስን በትክክል ለመረዳት ይህንን የእግዚአብሄር መልዕክተኛ በትክክል ማስተዋል ይኖርብናል ስለ ኢየሱስ ብዙ የማሰብ አዝማሚያ አለን ነገር ግን ከእርሱ በፊት ስለመጣው አጥማቂው ዮሐንስ ብዙ ቸል እንላለን እንድታስተውሉ ልረዳችሁ እወዳለሁ::

*«የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ:: እነሆ መንገድህን የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ» (ማርቆስ 1:1-2)* የሰማይ ወንጌል ሁሌም የሚጀምረው በአጥማቂው ዮሐንስ ነው::

ስለ አጥማቂው ዮሐንስ በሚገባ ስንማር የኢየሱስን የቤዛነት ወንጌል በግልጽ መረዳትና ማመን እንችላለን ይህ የአገሮችን ሁኔታዎች ለመረዳት በመላው አለም የተላኩትን አምባሳደሮች ከመስማት ጋር ተመሳሳይ ነው ስለ አጥማቂው ዮሐንስ ስናውቅ የእግዚአብሄርን ቤዛነት በሚገባ መረዳት እንችላለን::

ሆኖም በዚህ ዘመን በጣም ብዙ ክርስቲያኖች የዮሐንስን

ጠቃሚነት አለማየታቸው ምንኛ ያሳዝናል! እግዚአብሄር አጥማቂውን ዮሐንስን የላከው ስለተሰላቸና የሚያደርገው ሌላ ነገር ስላጣ አይደለም የአዲስ ኪዳን አራቱም ወንጌሎች በሙሉ ስለ ኢየሱስ ቤዛነት ከመናገራቸው በፊት ስለ አጥማቂው ዮሐንስ ይናገራሉ::

የዘመኑ ወንጌላውያን ግን እርሱን ፈጽሞ ችላ ብለውት ለመዳን በኢየሱስ ማመን ብቻ በቂ እንደሆነ ለሰዎች ይናገራሉ እነርሱ ሰዎችን በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ሐጢያተኞች ሆነው እንዲኖሩና በመጨረሻም ሲዖል እንዲወርዱ እየነዱዋቸው ነው ክርስቲያኖች በሙሉ የአጥማቂውን ዮሐንስን ሚና ሳይረዱ በኢየሱስ ብቻ ቢያምኑ ክርስትና ወደ አለም ሐይማኖት ይዘቅጥ ነበር እውነትን የማታውቁ ከሆነ እንዴት ከሐጢያቶቻችሁ መዳን ትችላላችሁ? የማይቻል ነው::

የቤዛነት ወንጌል ያን ያህል ቀላል ያን ያህልም መናኛ አይደለም በጣም ብዙ ሰዎች ኢየሱስ በመስቀል ላይ ለእኛ ስለሞተ ቤዛነት ያረፈው በመስቀሉ ላይ ባለን እምነት እንደሆነ ያስባሉ ነገር ግን ሐጢያቶችን የማስተላለፉን የተሟላ እውነት ሳታውቁ በስቅለቱ ብቻ የምታምኑ ከሆነ እምነታችሁ ምንም ያህል ብርቱ ቢሆንም የዚህ አይነቱ እምነት ወደ ምሉዕ ደህንነት አያደርሳችሁም::

እግዚአብሄር አጥማቂውን ዮሐንስን የላከው ቤዛነት እንዴት እንደሚፈጸምና ኢየሱስም የአለምን ሐጢያቶች እንዴት እንደሚወስድ አለም ያውቅ ዘንድ ነው ኢየሱስ በራሱ ላይ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ የወሰደ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን የምንረዳው ሙሉውን እውነት ስናውቅ ብቻ ነው::

አጥማቂው ዮሐንስ ስለ ቤዛነት እውነት ነግሮናል ኢየሱስ አምላክና እውነተኛ ብርሃን እንደሆነ እንዴት ሊመሰክር እንደመጣ ነግሮናል ያ ብርሃን እርሱ እንዳልነበረ እርሱ ግን

የብርሃን ምስክር እንደሆነ አስረግጦ ተናግሮዋል በዮሐንስ 1 ላይም ኢየሱስ ክርስቶስን በማጥመቅ የቤዛነትን ወንጌል ያዘጋጀው እርሱ እንደሆነ መስክሮዋል::

አጥማቂው ዮሐንስ ስለ ቤዛነት የመሰከረው ምስክርነት ባይኖረን ኖሮ እንዴት በኢየሱስ ማመን እንችል ነበር? እኛ ኢየሱስን ፈጽሞ አላየነውም የመጣነው ከተለያዩ ባህሎችና ሐይማኖቶች በመሆኑ የሆዋን አምላካችን አድርገን ማመኑ እንዴት ይቻል ነበር?

በመላው አለም ላይ እንዲህ ያሉ የተለያዩ ሐይማኖቶች ያሉ በመሆናቸው ኢየሱስን እንዴት ማወቅ ይቻለን ነበር? ኢየሱስ በእርግጥም የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በራሱ ላይ በመውሰድ ያዳነን የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን እንዴት ማወቅ ይቻለን ነበር?

ከመጀመሪያው የቤዛነትን ቃሎች ለማግኘትና ኢየሱስ አዳኛ ችን መሆኑን ለማወቅ ብሉይ ኪዳንን መመልከት ይኖርብናል ትክክለኛ እምነት እንዲኖረን ትክክለኛ እውቀት ማግኘት ይኖርብናል በኢየሱስ አምነን ለመዳን አጥማቂው ዮሐንስ የመሰከረለትን የቤዛነት ወንጌልና እርሱም በዚያ ውስጥ ያለውን ሚና ማወቅ ይኖርብናል በኢየሱስ የተሟላ እምነት እንዲኖረን ስለ ቤዛነት እውነቱን ማወቅ ይኖርብናል::

ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አለ *«እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል»* በኢየሱስ ውስጥ ያለውን የቤዛነት እውነት ማውቅ ይኖርብናል::

# በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ማስረጃዎች

*አራቱ ወንጌሎች*
*የሚጀምሩት ከምን አይነት*
*ነጥብ ነው?*

*ከመጥምቁ ዮሐንስ*
*አመጣጥ ነው።*

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን ማስረጃዎች በሙሉ ለመመርመር ወደፊት እንግፋ አራቱ ወንጌሎች ስለ አጥማቂው ዮሐንስ ስለ ማንነቱ ለምን «የሰው ዘር ወኪል» ወይም «ሊቀ ካህን» ተብሎ እንደተጠራ በእርሱ በኩልም የአለም ሐጢያቶች በሙሉ እንዴት ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉና ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በራሱ ላይ ወስዶ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ የሚናገሩትን እንመልከት።

አራቱም ወንጌሎች በሙሉ የሚጀምሩት በአጥማቂው ዮሐንስ በመሆኑ እውነታ ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባናል ዮሐንስ 1:6 በወንጌል ውስጥ ከሚገኙት እጅግ ጠቃሚ እውነታዎች አንዱን ይጠቅሳል የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ የማስተላለፉን ተግባር ማን እንደፈጸመው ይነግረናል *«ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበር ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ ይህ ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ ለምስክር መጣ።» (ዮሐንስ 1:6-7)*

ቃሉ እንዲህ ይላል *«ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ»* እርሱ *«ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ»* መጣ ብርሃኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይህ ማለት ሁሉ በእርሱ ያምኑ ዘንድ ዮሐንስ ስለ

ኢየሱስ መመስከር ነበረበት ማለት ነው እስቲ ማቴዎስ ምዕራፍ 3ን በቅርበት እንመልከት፡፡

ማቴዎስ 3፡13-17 እንዲህ ይላል *«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን- እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃው ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ እርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም፣ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ፡፡»*




አጥማቂው ዮሐንስ በአለም ላይ ያሉትን ሐጢያቶች ስርየት በሙሉ ለመፈጸም ኢየሱስን አጠመቀው ኢየሱስ ከዮሐንስ የተቀበለው ጥምቀት ለደህንነታችን እጅግ አስፈላጊ ሁነት ነበር ነገር ግን ሙሉውን እውነት በሚገባ ለመረዳትና ለማመን በመጀመሪያ አጥማቂውን ዮሐንስን በጥልቀት ማጥናት ይኖርብናል፡፡

ሉቃስ 1:1-14 እንዲህ ይላል *«የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን በኛ ዘንድ ስለተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበር ሚስቱም ከአሮን ልጆች ነበረች ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበረ ሁለቱም በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ ኤልሳቤጥም መካን ነበረችና ልጅ አልነበራቸውም ሁለቱም በእድሜያቸው አርጅተው ነበር እርሱም በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል እንደ ካህናት ስርዓት ወደ ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ ለማጠን ዕጣ ደረሰበት በዕጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይፀልዩ ነበር የጌታም መልዓክ በዕጣኑ መሰውያ ቀኝ ቆሞ ታየው ዘካርያስም ባየው ጊዜ ደነገጠ ፍርሃትም ወደቀበት መልአኩም እንዲህ አለው- ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ ደስታና ተድላም ይሆንልሃል በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል።»*

እዚህ ላይ የኢየሱስ ደቀ መዛሙር የሆነው ሉቃስ የዮሐንስን የዘር ሐረግ በዝርዝር ይነግረናል የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የሆነው ሉቃስ የዮሐንስን የዘር ሐረግ ከመጀመሪያው ጀምሮ አብራርቷል ሉቃስ ባህሉ ሌላ ለሆነውና ስለ ጌታ ለማያውቀው ቴዎፍሎስ ለሚባል ሰው ወንጌልን አስተምሮት ነበር።

ስለዚህ የሐጢያተኞች አዳኝ ስለሆነው ኢየሱስ ያስተምረው ዘንድ ሉቃስ የአጥማቂውን ዮሐንስን የዘር ሐረግ በስፋት

ሊያብራራለት እንደሚያስፈልገው አሰበ እኛም ደግሞ ከተለያዩ ዘሮች የመጣን አህዛቦች ስለሆንን ደረጃ በደረጃ በተለየ መንገድ ካልተብራራልን የኢየሱስን ደህንነት መረዳት አንችልም ዝርዝሮቹ ምን እንደሆኑ ፈልገን እናግኝ፡፡

ሉቃስ 1:5-9 እንዲህ ይተርካል *«በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበር ሚስቱም ከአሮን ልጆች ነበረች ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበረ ሁለቱም በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ ኤልሳቤጥም መካን ነበረችና ልጅ አልነበራቸውም ሁለቱም በእድሜያቸው አርጅተው ነበር፡ እርሱም በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል እንደ ካህናት ስርዓት ወደ ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ ለማጠን ዕጣ ደረሰበት፡፡»*

እዚህ ላይ ዘካርያስ በክህነቱ ስርአት መሰረት እግዚአብሄርን እያገለገለ ሳለ አንድ ሁነት ተከሰተ ሉቃስ ዘካርያስ የአሮን ዘር እንደነበር በግልጽ መስክሮዋል ዘካርያስ በየትኛው ክፍል ተራ ውስጥ ነበር? ይህ በጣም ወሳኝ ነጥብ ነው፡፡

እርሱ እንዲህ አብራርቷል *«እርሱም በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል»* ሉቃስ ስለ ዘካርያስ በሚገባ ያውቅ ስለነበር ዘካርያስንና ኤልሳቤጥን በመጥቀስ የቤዛነቱን ወንጌል እንዳብራራ ማየት እንችላለን፡፡

አጥማቂው ዮሐንስ ለዘካርያስና ከአሮን ሴት ልጆች አንዷ ለነበረችው ለሚስቱ ለኤልሳቤጥ ተወለደ አሁን የዮሐንስን አባት የዘካርያስን የዘር ሐረግ እንመልከት፡፡

# የአጥማቂው ዮሐንስ የዘር ሐረግ

*መጥምቁ ዮሐንስ*
*የማን ዘር ነበር?*

*የሊቀ ካህኑ*
*የአሮን ነው፡፡*

የአጥማቂውን የዮሐንስን የዘር ሐረግ ለመረዳት ከብሉይ ኪዳን 1ኛ ዜና 24፡1-19ን ማንበብ ይኖርብናል፡፡

*«የአሮንም ልጆች ሰሞን ይህ ነው የአሮን ልጆች ናዳብ፣ አብዩድ፣ አልዓዛር፣ ኢታምር ነበሩ ናዳብና አብዩድ ግን ልጆች ሳይወልዱ ከአባታቸው በፊት ሞቱ አልዓዛርና ኢታምርም ካህናት ሆኑ ዳዊትም ከአልዓዛር ልጆች ከሳዶቅ ጋር ከኢታምርም ልጆች ከአቢሜሌክ ጋር ሆኖ እንደ አገልግሎታቸው ሥርዓት ከፍሎ መደባቸው የአልዓዛርም ልጆች ከአለቆች ከኢታምር ልጆች አለቆች በልጠው ተገኙ እንዲህም ተመደቡ ከአልዓዛር ልጆች እንደ አባቶቻቸው ቤቶች አሥራ ስድስት፣ ከኢታምርም ልጆች እንደ አባቶቻቸው አሥራ ስምንት አለቆች ነበሩ ከአልዓዛርና ከኢታምርም ልጆች መካከል የመቅደሱና የእግዚአብሔር አለቆች ነበሩና እነዚህና እነዚያ እንዲህ በዕጣ ተመደቡ ከሌላውያንም ወገን የነበረው የናትናኤል ልጅ ጸሐፊው ሸማያ በንጉሡና በአለቆቹ ፊት በካህኑ በሳዶቅና በአብያታርም ልጅ በአቢሜሌክ ፊት በካህናቱና በሌዋውያኑ አባቶች ቤቶች አለቆች ፊት ጻፋቸው አንዱንም የአባት ቤት ለአልዓዛር አንዱንም ለኢታምር ጻፈ፡፡*

*መጀመሪያውም ዕጣ ለዮአሪብ ወጣ፣ ሁለተኛው ለዮዳኤ፣*

*ሦስተኛው ለካሪም፣ አራተኛው ለሥዖሪም፣ አምስተኛው ለመልክያ፣ ስድስተኛው ለሚያሚን፣ ሰባተኛው ለአቆስ፣ ስምንተኛው ለአብያ፣ ዘጠነኛው ለኢያሱ፣ አሥረኛው ለሴኬንያ፣ አሥራ አንደኛው ኤልያሴብ፣ አሥራ ሁለተኛው ለያቂም፣ አሥራ ሦስተኛው ለኦፓ፣ አሥራ አራተኛው ለየሼአብ፣ አሥራ አምስተኛው ለቢልጋ፣ አሥራ ስድስተኛው ለኢሜር፣ አሥራ ሰባተኛው ለኤዚር፣ አሥራ ስምንተኛው ለሃፊጼጽ፣ አሥራ ዘጠነኛው ለፈታያ፣ ሀያኛው ለኤዜቄል፣ ሀያ አንደኛው ለያኪን፣ ሀያ ሁለተኛው ለጋሙል፣ ሀያ ሦስተኛው ለድላያ፣ ሀያ አራተኛ ው ለመዓዝያ:: የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዳዘዘ፣ አባታቸው አሮን እንደሰጣቸው ሥርዓት ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚገቡበት የአገልግሎታቸው ሥርዓት ይህ ነበር::»*

ቁጥር 10ን እንደገና እናንብብ ቁጥር 10ን ደግመን እናንብበው *«ሰባተኛው ለአቆስ ስምንተኛው ለአብያ»* በንጉሥ ዳዊት ዘመን በጣም ብዙ ካህናት ስለነበሩ ስርአቱን ተከትሎ ለሚከናወኑት አገልግሎቶች ስርአተ ደንብ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነበር ስለዚህ መስዋዕቱ በስርአት ይቀርብ ዘንድ ዳዊት ለአሮን ልጆች ለእያንዳንዳቸው ክፍለ ተራዎችን መደበ (ሁላችሁም እንደምታውቁት አሮን የሙሴ ታላቅ ወንድም ነበር እግዚአብሄር በእስራኤል ሕዝብ ፊት ሙሴን ወኪሉ አሮንን ደግሞ የተቀደሰው ድንኳን ሊቀ ካህን አድርጎ ሾማቸው::)

ሌሎቹ ሌዋውያን በሙሉ ከካህናቱና ከአሮን በታች ነበሩ ካህናት የሆኑት ልጆቹም በእግዚአብሄር ፊት በመስዋዕቶቹ ሁሉ ላይ ተሹመው ነበር ዳዊት ክፍለ ተራዎችን ከመመደቡ በፊት የአሮን ዘሮች የነበሩት ካህናት በየጊዜው ዕጣዎችን መጣል ነበረባቸው ይህም ብዙ ግራ መጋባትን ፈጥሮ ነበር::

ስለዚህ ዳዊት እያንዳንዱን ሰሞን ስርአት በማስያዝ አንድ ተራ ክፍል አዘጋጀ በአንድ ክፍለ ተራ ውስጥ ከአሮን የልጅ

ልጆች የሚጀምሩ ሃያ አራት ሰሞኖች የነበሩ ሲሆን ስምንተኛው አብያ ነበር ቃሉ እንዲህ *«ከአቢያ ወገን የሆነ ዘካሪያስ የሚባል ካህን ነበር»* ስለዚህ ዘካርያስ ከአብያ ክፍል የሆነ ካህን ነበር እነርሱ ሁለቱም የሊቀ ካህኑ የአሮን ዘሮች ነበሩ::

የአጥማቂው ዮሐንስ አባት ከአብያ ክፍል የሆነው ካህኑ ዘካርያስ ነበር እነርሱ የሚጋቡት ከቤተሰቦቻቸው አባሎች ጋር እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ እናውቃለን::

ያዕቆብም ያገባው ከእናቱ ወገን የአጎቱን ሴት ልጅ ነበር ይህ ማብራሪያ ጥልቅ ጠቀሜታ ያለው የዘር ሐረግ ነው *«ከአቢያ ወገን የሆነ ዘካሪያስ የሚባል ካህን ነበር»* ይላል::

ስለዚህ እርሱ በእርግጥም የአሮን ዘር ነበር ማን? የአጥማቂው ዮሐንስ አባት ዘካርያስ:: ይህ የኢየሱስን ቤዛነት የአጥማቂውን ዮሐንስን አገልግሎትና የአለም ሐጢያቶች ወደ ኢየሱስ መተላለፋቸውን የሚያብራራ ጠቃሚ እውነታ ነው::

## ካህናት ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉት የአሮን ልጆች ብቻ ናቸው




ታዲያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የአሮን ልጆች ካህናት

ሆነው ማገልገል እንደሚገባቸው የተዘረዘረው የት ቦታ ነው? እስቲ እንመልከተው::

ዘኁልቁ 20:22-29 እንዲህ ይላል *«ከቃዴስም ተጓዙ የእስራኤልም ልጆች ማኅበር ሁሉ ወደ ሖር ተራራ መጡ እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን በኤዶምያስ ምድር ዳርቻ ባለው በሖር ተራራ እንዲህ ብሎ ተናገራቸው- አሮን ወደ ወገኑ ይከማች በመሪባ ውኃ ዘንድ በቃሌ ላይ ስላመጻችሁ ለእስራኤል ልጆች ወደ ሰጠኋት ምድር አይገባም አሮንንና ልጁን አልዓዛርን ይዘህ ወደ ሖር ተራራ ላይ አምጣቸው ከአሮንም ልብሱን አውጣ ልጁንም አልዓዛርን አለበሰው አሮንም በዚያ በተራራው ራስ ላይ ሞተ ሙሴና አልዓዛርም ከተራራው ወረዱ ማኅበሩም ሁሉ አሮን እንደ ሞተ ባየ ጊዜ የእስራኤል ቤት ሁሉ ለአሮን ሠላሳ ቀን አለቀሱ::»*

በዘጸአት ውስጥ የእግዚአብሄር ቃል የሊቀ ካህኑ የአሮን ልጆች ክህነቱን መውሰድ እንደሚገባው የተሾመውም ልጅ አባቱ እንዳደረገው 30 አመት ሲሆነው ሊቀ ክህነቱን መውሰድ እንደነበረበት በመናገር የመዘገበው ነገር አለ::

ዘፀዓት 28:1-5 እንዲህ ይላል *«አንተም ወንድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይተህ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ ወደ አንተ አቅርብ አሮንን የአሮንንም ልጆች ናዳብን አብዮድንም አልዓዛርንም ኢታምርንም አቅርብ የተቀደሰውንም ልብስ ለክብርና ለጌጥ እንዲሆን ለወንድምህ ለአሮን ሥራለት አንተም ካህን ሆኖ እንዲያገለግለኝ አሮን ቅዱስ ይሆን ዘንድ ልብስ እንዲሠሩለት የጥበብ መንፈስ ለሞላሁባቸው በልባቸው ጥበበኞች ለሆኑት ሁሉ ተናገር የሚሠሩኣቸውም ልብሶች እነዚህ ናቸው የደረት ኪስ ኤፉድም ቀሚስም ዝንጉርጉር ሸሚዝም መጠምጠሚያም መታጠቂያም እነዚህም ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ ለወንድምህ ለአሮን ለልጆቹም የተቀደሰ*

*ልብስ ያድርጉ ወርቅንም ሰማያዊና ሐምራዊ ቀይም ግምጃ ጥሩ በፍታም ይውሰዱ::»*

እግዚአብሄር የሙሴን ወንድም አሮንን ሊቀ ክህነት ውስጥ መደበው ክህነት ለሌላ ለማንም ሰው ክፍት አልነበረም እግዚአብሄር ሙሴን አሮንን ሊቀ ካህን አድርጎ እንዲሾመውና እርሱ በገለጠው መሰረትም ትክክለኛ ልብስ እንዲያዘጋጅለት አዘዘው የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሞ መዘንጋት የለብንም::

በዘፀዓት 29:1-9 ላይም እንዲህ ይላል *«እኔንም በክህነት እንዲያገለግሉኝ ትቀድሳቸው ዘንድ የምታደርግባቸው ነገር ይህ ነው ነውር የሌለባቸውን አንድ ወይፈንና ሁለት አውራ በጎች ትወስዳለህ:: ቂጣ እንጀራ በዘይትም የተለወሰ የቂጣ እንጎቻ በዘይትም የተቀባ ስስ ቂጣ ከመልካም ስንዴ ታደርጋለህ በአንድ ሌማትም ታደርጋቸዋለህ ከወይፈኑና ከሁለቱ አውራ በጎች ጋር በሌማቱ ታቀርባቸዋለህ አሮንንና ልጆቹንም ወደ መገናኛው ድንኳን ታቀርባቸዋልህ በውሃም ታጥባቸዋለህ ልብሶችን ወስደህ ለአሮን ሸሚዝና የኤፉድ ቀሚስ ኤፉድም የደረት ኪስም ታለብሰዋለህ በብልሃትም በተጠለፈ ቋድ ታስታጥቀዋለህ መጠምጠሚያው ላይ ታኖራለህ የቅብዓትንም ዘይት ወስደህ በራሱ ላይ ታፍሰዋለህ ትቀባውማለህ ልጆቹንም ታቀርባቸዋለህ ሸሚዞችንም ታለብሳቸዋለህ አሮንንና ልጆቹንም በመታጠቂያ ታስታጥቃቸዋለህ ቆብንም ታለብሳቸዋለህ ለዘላለም ሥርዓትም ክህነት ይሆንላቸዋል እንዲሁም አሮንንና ልጆቹን ትክናቸዋለህ::»*

አሮንንና ልጆቹን በመታጠቂያ ታስታጥቃቸዋለህ በራሳቸውም ላይ ቆቦችን ታደርግላቸዋለህ...ክህነቱም በዘላለም ስርአት የእነርሱ ነው አሮንንና ልጆቹን ትቀድሳቸዋለህ...እግዚአብሄር ክህነቱን ለዘላለም ለማገልገል የሚቀደሱት አሮንና ልጆቹ እንደሆኑ በግልጽ ተናግሮዋል *«ለዘላለም ስርአት»* ብሎ በግልጽ ሲናገር ክህነቱ

ኢየሱስ ወደዚህ አለም ከመጣ በኋላ እንኳን ይሰራል ማለት ነው::

ሉቃስ ዘካርያስ የሊቀ ካህኑ የአሮን ዘር እንደነበር በስፋት አብራርቷል ዘካርያስ በጌታ መቅደስ ውስጥ በእግዚአብሄር ፊት ካህን ሆኖ እያገለገለ ሳለ መልአክ ተገልጦ ጸሎቱ እንደተሰማችለትና ሚስቱም ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ እንደምትወልድለት ነገረው::

ዘካርያስ ይህንን ማመን ስላዳገተው *«ምስቴ በዕድሜዋ አርጅታለችና እንዴት ልጅ መውለድ ትችላለች?»* አለ በጥርጣሬው ምክንያትም እግዚአብሄር ቃሎቹ እንደሚፈጸሙ ሊያሳየው ዲዳ አደረገው::

ጊዜውን ጠብቆም ሚስቱ አረገዘች ከጥቂት ጊዜ በኋላም ድንግሊቱ ማርያምም ደግሞ እንደዚሁ አረገዘች ሁለቱም ክስተቶች እግዚአብሄር ለደህንነታችን ያዘጋጃቸው ስራዎች ነበሩ እርሱ ኀስቋሎቹን ሰዎች ለማዳን ባሪያውን ዮሐንስንና አንድያ ልጁን ኢየሱስን ወደዚህ አለም መላክ ነበረበት::

ስለዚህ እግዚአብሄር በእርሱ የሚያምኑ ሰዎች ይድኑ ዘንድ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለማስተላለፍ ልጁ በዮሐንስ እንዲጠመቅ አደረገው::

## የእግዚአብሔር ልዩ ችሮታ!

*ለቤዛነት ሥራው*
*እግዚአብሔር ከኢየሱስ በፊት*
*ያዘጋጀው ማንን ነበር?*

*አጥማቂውን ዮሐንስን::*

ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ስጋ የተወለደ የሰው ዘር አዳኝ ነበር ማርያም ከይሁዳ ነገድ ለሆነው ለዮሴፍ ታጭታ ነበር አጥማቂው ዮሐንስ ከሊቀ ካህኑ ከአሮን ቤት መወለድ እንደነበረበት ሁሉ ኢየሱስም የእግዚአብሄርን ቃል ኪዳን ለመፈጸም በይሁዳ ዘር በኩል መወለድ ነበረበት፡፡

እግዚአብሄር እነዚህ ሁለቱ በዚህ አለም ላይ እንዲወለዱ አደረገ በዚያ ቅደም ተከተል መሰረትም ዮሐንስ ከኢየሱስ በፊት ተወለደ ዮሐንስ የተወለደው ኢየሱስን ለማጥመቅና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ ለማስተላለፍ ነበር የሊቀ ካህን ዘርም በብሉይና በአዲስ ኪዳናት ላይ የተገባውን የእግዚአብሄር ቃል ኪዳን ለመፈጸም መስዋዕትን ማቅረብ ነበረበት ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድም የኢየሱስ የቤዛነት ወንጌል በትክክል ተግባራዊ መደረግ ነበረበት፡፡

በዘጸአት ውስጥ እግዚአብሄር ለእስራኤሎች ሕጉንና ኪዳኖቹን ሰጣቸው የእግዚአብሄር ሕጎችና የመገናኛው ድንኳን ስርአተ መስዋዕት የካህናቶች ልብሶችና ወደ ካህናት ልጆች የሚተላለፈው የክህነት መተኪያም እንደዚሁ ተሰጥተዋቸው ነበር እግዚአብሄር አሮንንና ዘሮቹን ለዘላለም ሊቀ ካህናት አድርጎ ሾማቸው፡፡

ስለዚህ የአሮን ዘሮች በሙሉ መስዋዕቶችን ማቅረብ ይችሉ ነበር ሊቀ ካህናትም የሚወጡት ከአሮን ቤት ብቻ ነበር ይህ ለምን እንደሆነ አያችሁ?

እግዚአብሄር ከብዙዎቹ የአሮን ዘሮች መካከል ዘካርያስ የተባለን አንድ ካህንና ሚስቱን ኤልሳቤጥን መረጠ እርሱ እንዲህ ብሎዋል *«እነሆ በፊትህ መልዕክተኛዬን እልካለሁ»* እግዚአብሄር ለዘካርያስ ኤልሳቤጥ ልጅ ይኖራት ዘንድ እንደሚያስችላትና ስሙንም ዮሐንስ ብሎ እንደሚሰይመው ነገረው ልጁ እስከሚወለድና ስም እስኪሰጠው ድረስ በእርሱ ትዕዛዝ ዲዳ በመሆኑም በጣም ተገርሞ ነበር፡፡

በእርግጥም በቤቱ ውስጥ ወንድ ልጅ ተወለደ በእስራኤል ልማድ መሰረት ለልጁ ስም የሚሰየምበት ጊዜ ሲደርስ ልጁ በአባቱ ወይም ከዘመዶቹ በአንዱ ሰው ስም ይሰየም ነበር፡፡

*«የኤልሳቤጥ የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ ወንድ ልጅም ወለደች ጎረቤቶችዋም ዘመዶችዋም ጌታ ምሕረቱን እንዳገነነላት ሰምተው ከእርስዋ ጋር ደስ አላቸው በስምንተኛውም ቀን ሕጻኑን ሊገርዙት መጡ በአባቱም ስም ዘካርያስ ሊሉት ወደዱ እናቱ ግን መልሳ አይሆንም ዮሐንስ ይባል እንጂ አለች እነርሱም ከወገንሽ ማንም በዚህ ስም የተጠራ የለም አሉአት አባቱንም ማን ሊባል እንዲወድ ጠቀሱት ብራናም ለምኖ፡- ስሙ ዮሐንስ ነው ብሎ ጻፈ ሁሉም አደነቁ ያን ጊዜም አፉ ተከፈተ መላሱም ተፈታ እግዚአብሔርንም እየባረከ ተናገረ ለጎረቤቶቻቸውም ሁሉ ፍርሃት ሆነ ይህም ሁሉ ነገር በይሁዳ በተራራማው አገር ሁሉ ተወራ የሰሙትም ሁሉ- እንኪያ ይህ ሕጻን ምን ይሆን? እያሉ በልባቸው አኖሩት የጌታ እጅ ከእርሱ ጋር ነበረችና፡፡» (ሉቃስ 1:57-66)*

ልጁ በተወለደ ጊዜ ዘካርያስ ገናም ዲዳ ነበር ለልጁ ስም የመሰየም ጊዜ ሲደርስ ዘመዶቹ ልጁ ዘካርያስ ተብሎ መጠራት እንደሚገባው አሳብ አቀረቡ እናቱ ግን ስሙ ዮሐንስ መሆን እንዳለበት ተሙዋገተች በዚህ ጊዜ ዘመዶች የሆኑት በቤተሰቡ ውስጥ በዚያ ስም የተጠራ ሰው ስለሌለ ልጁ በአባቱ ስም መጠራት እንዳለበት ተናገሩ፡፡

ኤልሳቤጥ ስሙን በሚመለከት በተሟገተች ጊዜ ዘመዶች የሆኑት ወደ ዘካርያስ ሄደው የሕጻኑ ስም ማን መሆን እንዳለበት ጠየቁት ዘካርያስ ገናም ዲዳ ስለነበር መጻፊያ ብራና ለምኖ *«ዮሐንስ»* ብሎ ጻፈ ዘመዶች የሆኑት ሁሉ በዚህ ያልተለመደ የስም ምርጫ ተገረሙ፡፡

ከስም አወጣጡ በኋላ ግን የዘካርያስ አንደበት ወዲያውኑ

ተከፈተ እርሱም እግዚአብሔርን አመሰገነ መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶም ትንቢት ተናገረ።

በዚህም ሉቃስ በዘካርያስ ቤት ስለተወለደው አጥማቂው ዮሐንስ ነግሮናል *«ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበር»* በእግዚአብሄር ልዩ ችሮታ የሰው ዘር ወኪል የአሮን ዘር ለሆነው ለዘካርያስ ተወለደለት።

እግዚአብሄር በአጥማቂው ዮሐንስና በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የሰውን ዘር ደህንነት ፈጸመ እኛ በዮሐንስና በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በተፈጸመው የቤዛነት ስራ በማመን ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ድነናል።

## የኢየሱስ ጥምቀት

*ኢየሱስ በዮሐንስ*
*የተጠመቀው ለምን ነበር?*

*የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ*
*ለመውሰድ ነው።*

አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደነበርና ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደ መሰከረ የእግዚአብሄርን ማዳን ለመመስከር የተላከው የእግዚአብሄር ባርያ የሆነው አጥማቂው ዮሐንስ ነበር ይህ ማለት እግዚአብሄር አዳኛችን እንደሆነ ራሱ አይነግረንም ማለት አይደለም እግዚአብሄር በቤተክርስቲያን ውስጥ በባሪያዎቹና በዳኑት ሕዝቦቹ አንደበት ሁሉ ይሰራል።

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል *«ለኢየሩሳሌም ልብ ተናገሩ የተቀጠረችበት ወራት እንደ ተፈጸመ ኃጢኣትዋም እንደ ተሰረየ ከእግዚአብሔርም እጅ ስለ ኃጢአትዋ ሁሉ ሁለት እጥፍ እንደተቀበለች ወደ እርስዋ ጩኹ ሣሩ ይደርቃል አበባውም ይረግፋል የአምላካችን ቃል ግን ለዘለዓለም ጸንታ ትኖራለች፡፡ (ኢሳይያስ 40፡2,8)*

እግዚአብሄር ክርስቶስ ከመወለዱ ከሰባት መቶ አመታት በፊት አስቀድሞ «ከእንግዲህ ወዲህ ሐጢያተኞች አይደላችሁም ሐጢያቶቻችሁን በሙሉ ይቅር ብያለሁ ጦርነቱም አብቅቷል» በማለት ቃል ገብቷል ስለዚህ የቤዛነት ወንጌል ድምጽ ለእኛ መጮሁን ቀጥሎዋል የመዘጋጀት ወንጌል ተብሎ የሚጠራው ይህ ነው፡፡

የአጥማቂውን ዮሐንስን ስራዎች ስናስተውልና የአለም ሐጢያቶች በሙሉ በአጥማቂው ዮሐንስ አማካይነት ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ በተጨባጭ ስንረዳ ሁላችንም ከሐጢያቶቻችን ነጻ መውጣት እንችላለን፡፡

አራቱም ወንጌሎች በሙሉ ስለ አጥማቂው ዮሐንስ ይነግሩናል የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ነቢይ ሚልክያስም አጥማቂው ዮሐንስ እግዚአብሄር ያዘጋጀው ነቢይ እንደነበር መስክሮዋል አዲስ ኪዳን የሚጀምረው በአጥማቂው ዮሐንስ ውልደትና በእርሱ አማካይነት በተላለፈው ሐጢያት ነው፡፡

ታዲያ ለምን አጥማቂው ዮሐንስ ብለን እንጠራዋለን? እንደዚያ የምንጠራው ኢየሱስን ስላጠመቀው ነው ጥምቀት ማለት ምን ማለት ነው? ጥምቀት ማለት «ማስተላለፍ መቀበር መታጠብ» ማለት ነው ከብሉይ ኪዳን «እጆችን መጫን» ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን አንድ ሰው ሐጢያት ሲሰራ እጆቹን በራሱ ላይ በመጫን ሐጢያቶቹን ነውር በሌለው የመስዋዕት እንስሳ

ላይ ያስተላልፋል መስዋዕቱም እነዚያን ሐጢያቶች ይዞ ይሞታል «እጆችን መጫን» ማለት «ማስተላለፍ» ማለት ነው ስለዚህ «እጆችን መጫን» እና «ጥምቀት» በግልጽ የተለያዩ ቢሆኑም አንድ አይነት አንደምታዎች አሉዋቸው፡፡

ታዲያ የኢየሱስ ጥምቀት ትርጉም ምንድነው? የእርሱ ጥምቀት የሐጢያት ስርየታችንን የምንቀበልበት ብቸኛው መንገድ ነው እግዚአብሄር ሐጢያት «በእጆች መጫን» አማካይነት ወደ መስዋዕቱ የሚተላለፍበትን ሕግ አዘጋጅቷል ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሐጢያተኞች ሐጢያቶቻቸውን በራሱ ላይ ለማስተላለፍ እጆቻቸውን በመስዋዕቱ ራስ ላይ መጫን ነበረባቸው ከዚያ በኋላ ጉሮሮውን ማረድ ነበረባቸው ካህናቱም ደሙን በሚቃጠለው መስዋዕት መሠውያ ቀንዶች ላይ መቀባት ነበረባቸው በየቀኑ የሚሰሩት ሐጢያቶች ስርየት የሚያገኙት በዚህ መልኩ ነው፡፡

ለአመታዊዎቹ ሐጢያቶቻቸውስ ስርየትን የሚያገኙት እንዴት ነበር?

ይህንን በሚመለከት ሊቀ ካህኑ ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ መስዋዕትን ያቀርባል አጥማቂው ዮሐንስ የተወለደው ከአሮን ቤት በመሆኑ ሊቀ ካህን መሆኑ ትክክል ነበር እግዚአብሄርም በገባው የቤዛነት ተስፋው መሰረት የመጨረሻው ሊቀ ካህን ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ወሰነው፡፡

አጥማቂው ዮሐንስ የሰው ዘር ሁሉ ወኪልና የመጨረሻው ሊቀ ካህን የሆነው አዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ በመጠናቀቁ ነው አሮን በብሉይ ኪዳን የሕዝቡን ሐጢያቶች እንዳስተሰረየ ሁሉ በአዲስ ኪዳን የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ማስተላለፍ የቻለ ከአጥማቂው ዮሐንስ ሌላ ማነው? አጥማቂው ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው ሊቀ ካህንና የሰው ዘር ወኪል በመሆኑ አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስን ባጠመቀው ጊዜ

የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ አስተላለፈ፡፡

ዮሐንስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ስላስተላለፈ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን ሊያድነን ይችላል ኢየሱስ ሐጢያተኞችን በሙሉ ለማዳን በግ ሆነ በዚህም እግዚአብሄር እንዳቀደው የቤዛነትን ስራ ፈጸመ ኢየሱስ አጥማቂው ዮሐንስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ ያስተላለፈ የመጨረሻው ሊቀ ካህን እንደሆነ ነግሮናል፡፡

ኢየሱስ ራሱ ይህንን ማድረግ ያልቻለው ለምንድነው? ለምን አጥማቂው ዮሐንስ አስፈለገው? አጥማቂው ዮሐንስ ከኢየሱስ በስድስት ወራት ቀድሞ የተወለደበት ምክንያት አለ ይህም የብሉይ ኪዳንን ሕግና ተስፋዎቹን ለመፈጸም ነበር፡፡

ኢየሱስ ከድንግል ማርያም ተወለደ አጥማቂው ዮሐንስም ኤልሳቤጥ ከተባለች ያረጀችና መካን ሴት ተወለደ፡፡

እነዚህ የእግዚአብሄር ስራዎች ነበሩ ያቀዳቸውም ሐጢያተኞችን በሙሉ ለማዳን ነበር እርሱ እኛን ከሐጢያት ጋር ከሚደረግ የዘላለም ጦርነትና በሐጢያተኛ ተፈጥሮዋችን ከሚገጥሙን መከራዎች ሊያድነን ባርያውን ዮሐንስን ከዚያም ልጁን ኢየሱስን ላከ አጥማቂው ዮሐንስ የተላከው የሰው ዘር ወኪል የመጨረሻው ሊቀ ካህን ሆኖ ነበር፡፡

## ከሴቶች የተወለደ እጅግ ታላቁ ሰው

*በምድር ላይ እጅግ ታላቁ ሰው ማን ነበር?*

*አጥማቂው ዮሐንስ*

ማቴዎስ 11:7-14ን እንመልከት *«እነዚያም ሲሄዱ ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ ሊናገር ጀመረ እንዲህም አለ ምን ልታዩ ወደ ምድረ በዳ ወጣችሁ? ነፋስ የሚወዘውዘው ሸንበቆን? ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ቀጭን ልብስ የለበሰ ሰውን? እነሆ ቀጭን ልብስ የለበሱ በነገሥታት ቤት አሉ ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን? አዎን እላችኋለሁ ከነብይም የሚበልጠውን፡፡ እነሆ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልዕክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነውና እውነት እላችኋለሁ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሳም በመንግስተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል ከመጥምቁም ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግስተ ሰማያት ትገፋለች ግፈኞችም ይናጠቋታል ነቢያት ሁሉና ሕጉ እስከ ዮሐኝስ ድረስ ትንቢት ተናገሩ ልትቀበሉትስ ብትወዱ ሊመጣ ያለው ኤልያስ ይህ ነው፡፡»*

ሰዎች *«እናንተ የእፉኝት ልጆች ንስሐ ግቡ!»* እያለ የሚጮኸውን አጥማቂውን ዮሐንስን ለማየት ወደ ምድረ በዳ ወጡ ኢየሱስም እንዲህ አለ *«ምን ልታዩ ወጣችሁ? ቀጭን ልብስ የለበሰ ሰውን? እነሆ- ቀጭን ልብስ የለበሱ በነገሥታት ቤት አሉ፡፡»*

ኢየሱስም ራሱ የዮሐንስን ታላቅነት መስክሯል «ምን ልታዩ ወጣችሁ? የግመል ጠጉር የለበሰንንና ላንቃው እስኪበጠስ ድረስ የሚጮህን ሰው? እርሱ የግመል ጠጉር መልበስ አለበት ምን ልታዩ ወጣችሁ? ቀጭን ልብስ የለበሰ ሰውን? እነሆ ቀጭን ልብስ የለበሱ በነገሥታት ቤት አሉ እርሱ ግን ከንጉስም ይበልጣል» በማለት ኢየሱስ መሰከረ *«እነሆ- ቀጭን ልብስ የለበሱ በነገሥታት ቤት አሉ ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን? አዎን እላችኋለሁ፣ ከነብይም የሚበልጠውን፡፡»*

በጥንት ዘመን ነቢያት ከነገስታቶች የሚበልጡ ሆነው

ይቆጠሩ ነበር አጥማቂው ዮሐንስም ከንጉስ የሚበልጥ ከነቢይም የላቀ ነበር እርሱ ከብሉይ ኪዳን ነቢያቶችም ሁሉ የሚበልጥ ነበር እንዲያውም የመጨረሻው ሊቀ ካህንና የሰው ዘር ወኪል የሆነው ዮሐንስ ከመጀመሪያ ሊቀ ካህን ከአሮንም የበለጠ ጠቃሚ ሰው ነበር ኢየሱስ ራሱ ዮሐንስ እንደዚህ አይነት ሰው እንደሆነ መስክሮዋል።

የሰው ዘር ወኪል ማነው? ከራሱ ከክርስቶስ ውጭ በምድር ላይ እጅግ ታላቁ ሰው ማነው? አጥማቂው ዮሐንስ ነው *«አዎን እላችኋለሁ ከነብይም የሚበልጠውን። «እነሆ መልክተኛዬን እልካለሁ፣ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል።»*

አጥማቂው ዮሐንስ ከሐጢያት ጋር የሚደረገው ጦርነት እንዳበቃ መስክሮዋል *«እነሆ የአለምን ኃጢያት ሁሉ የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!»* ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች እንደወሰደ የመሰከረው አጥማቂው ዮሐንስ ነበር።

በማቴዎስ 11፡11 እንዲህ ተጽፎዋል *«እውነት እላችኋለሁ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሳም»* ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከአጥማቂው ዮሐንስ የሚበልጥ ተገኝቶ ነበርን?

*«ከሴቶች መወለድ»* ማለት ምን ማለት ነው? ይህ የሚያመላክተው የሰውን ዘር ሁሉ ነው ከአዳምና ከሔዋን በስተቀር ሰዎች ሁሉ ከሴቶች የተወለዱ ናቸው አዎ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከአጥማቂው ዮሐንስ የሚበልጥ ሰው አልተነሳም ስለዚህ እርሱ የመጨረሻው ሊቀ ካህንና የሰው ዘር ወኪል ነው አጥማቂው ዮሐንስ ሊቀ ካህን ነቢይና የሰው ዘር ሁሉ ወኪል ነበር።

በብሉይ ኪዳን አሮንና ልጆቹ ለዘላለም እንዲያገለግሉ በእግዚአብሄር ተሹመው ነበር ሐጢያቶች በሙሉ በአሮንና በልጆቹ አማካይነት መንጻት ነበረባቸው ይህም እግዚአብሄር ባዘዘው መሰረት ነበር።

አንዳንድ ሌሎች ሌዋውያን ቀርበው በእነርሱ ክህነት ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ቢደፍሩ በእርግጥም ይሞታሉ እነርሱ ማድረግ ያለባቸው በመሰውያው ላይ ለሚነደው እሳት ማገዶ መሰብሰብ የእንስሶችን ቆዳ መግፈፍ ስቡን መለየት አንጀቶችን ማጽዳት ቆሻሻውን ከሰፈሩ ውጭ መጣል ነው የካህናትን ስራ ለመስራት ቢደፍሩ ይሞታሉ ይህ የእግዚአብሄር ሕግ ነው መስመሩን ማለፍ አይችሉም::

በምድር ላይ ከአጥማቂው ዮሐንስ የሚበልጥ ሰው አልተነሳም እርሱ ከሚች ሰዎች መካከል እጅግ ታላቅ ሰው ነው *«ከመጥምቁም ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ መንግስተ ሰማያት ትገፋለች ግፈኞችም ይናጠቋታል::»*

የሰው ዘር ቤዛነት የተፈጸመው አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስን ባጠመቀው ጊዜ ነበር በኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎችም በእምነት ጻድቃን ስለሆኑ መንግስተ ሰማይ መግባት ይችላሉ::

አሁን የዮሐንስ አባት ስለ ልጁ የመሰከረውን እንመልከት::

## የዮሐንስ አባት የዘካርያስ ምስክርነት

*ዘካርያስ ስለ ልጁ*
*የተነበየው ምን ነበር?*

*ዮሐንስ ለሕዝቡ የደህንነትን እውቀት*
*በመስጠት የጌታን*
*መንገድ ያዘጋጃል::.*

ሉቃስ 1: 67-80ን እናንብብ *«አባቱ ዘካርያስም መንፈስ*

*ቅዱስ ሞላበትና ትንቢት ተናገረ እንዲህም አለ- የእስራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ፣ ጎብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጎአልና ከጥንት ጀምሮ በነበሩት በቅዱሳን ነቢያት አፍ እንደ ተናገረ በብላቴናው በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነሥቶልናል ማዳኑም ከወደረኞቻችንና ከሚጠሉን ሁሉ እጅ ነው እንደዚህ ለአባቶቻችን ምሕረት አደረገ ለአባታችን ለአብርሃምም የማለውን መሐላውን ቅዱሱን ኪዳን አሰበ በእርሱም ከጠላቶቻችን እጅ ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት በቅድስና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ የልዑል ነቢይ ትባላለህ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና እንደዚህም የኃጢያታቸው ስርየት የሆነውን የመዳን እወቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ ይህም ከላይ የመጣ ብርሃን በጎበኘበት በአምላካችን ምሕረትና ርኅራኄ ምክንያት ነው ብርሃኑም በጨለማና በሞት ጥላ ተቀምጠው ላሉት ያበራል እግሮቻችንንም በሰላም መንገድ ያቀናል ሕጻኑም አደገ በመንፈስም ጠነከረ ለእስራኤልም እስከታየበት ቀን ድረስ በምደረ በዳ ኖረ::»*

ዘካርያስ ሁለት ነገሮችን ተነበየ እርሱ ከቁጥር 68 እስከ 73 ድረስ እግዚአብሄር ተስፋዎቹን እንዳልረሳ ኢየሱስም እግዚአብሄር ለአብርሃም በገባው ቃል መሰረት ዘሮቹን ከወደረኞቻቸው እጅ ለማዳን ከድንግል ማርያም እንደተወለደ ተነበየ::

ከቁጥር 74 በኋላ ደግሞ *«በእርሱም ከጠላቶቻችን እጅ ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት በቅድስና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን»* ይህ እግዚአብሄር ለአብርሃምና ለእስራኤል ሕዝብ የገባውን የተስፋ ቃል የሚያስታውስ ነው::

በመቀጠልም ከቁጥር 76 ጀምሮ ስለ ልጁ ተነበየ: *«ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ የልዑል ነቢይ ትባላለህ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና እንደዚህም የኃጢያታቸው*

*ስርየት የሆነውን የመዳን እወቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ ይህም ከላይ የመጣ ብርሃን በጎበኘበት በአምላካችን ምሕረትና ርኅራኄ ምክንያት ነው ብርሃኑም በጨለማና በሞት ጥላ ተቀምጠው ላሉት ያበራል እግሮቻችንንም በላም መንገድ ያቀናል፡፡»*

እዚህ ላይ እንዲህ ብሎዋል *«እንደዚህም የኃጢያታቸው ስርየት የሆነውን የመዳን እወቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ»* የደህንነት እውቀት የሚሰጠው በማን እንደሆነ ተናገረ? በአጥማቂው ዮሐንስ፡፡ ይህንን ሁሉ ማየት ትችላላችሁን? አጥማቂው ዮሐንስ በእግዚአብሄር ቃሎች አማካይነት ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች የሚወስድ የእግዚአብሄር ልጅ የመሆኑን እውቀት ሊሰጠን ይገባ ነበር፡፡

አሁን ማርቆስ 1ን እንመልከት *«የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ፡፡ እነሆ መንገድን የሚጠርግ መልዕክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ የጌታ መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ተብሎ በነብዩ በኢሳይያስ እንደ ተጻፈ ዮሐንስ በምድረ በዳ እያጠመቀ የንስሐንም ጥምቀት ለኃጢአት ስርየት እየሰበከ መጣ የይሁዳም አገር ሁሉ የኢየሩሳሌምም ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር ኃጢያታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ በእርሱ ይጠመቁ ነበር፡፡» (ማርቆስ 1:1-5)*

እስራኤሎች አጥማቂውን ዮሐንስን በሰሙት ጊዜ የአሕዛቦችን ጣዖታት ከማምለክ ተመልሰው በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቁ ዮሐንስ ግን እንዲህ ሲል መሰከረ «እኔ ወደ እግዚአብሄር ትመለሱ ዘንድ በውሃ አጠምቃችኋለሁ ነገር ግን ሐጢያቶቻችሁ በሙሉ ወደ እርሱ ይተላለፉ ዘንድ የእግዚአብሄር ልጅ መጥቶ በዚሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ይጠመቃል እናንተ እንደተጠመቃችሁት በእርሱ ጥምቀት ብታምኑ በብሉይ ኪዳን በእጆች መጫን አማካይነት ሐጢያቶች እንደተላለፉ ሁሉ

የእናንተም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ ይተላለፋሉ» ዮሐንስ የመሰከረው ይህንን ነበር፡፡

ኢየሱስ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ማለት በሞት ወንዝ ውስጥ ተጠመቀ ማለት ነው እኛ በቀብር ጊዜ እንዲህ እያልን እንዘምራለን *«♪በጣፋጩ ባማረው በዚያ የባህር ዳር እንገናኛለን ባማረው በዚያ የባህር ዳር እንገናኛለን♪»* ስንሞት የዮርዳኖስን ወንዝ እንሻገራለን የዮርዳኖስ ወንዝ የሞት ወንዝ ነው የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በዚያ ስለወሰደ ኢየሱስ በዚህ የሞት ወንዝ ውስጥ ተጠመቀ *«የሐጢያት ደመወዝ ሞት ነው፡፡»*

## ኃጢያቶቻችንን ያስተላለፈ ጥምቀት

*በአዲስ ኪዳን የእጆች ተምሳሌት ምንድን ነው?*

*የኢየሱስ ጥምቀት፡፡*

በማቴዎስ 3:13-17 ይህን እናነባለን *«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃው ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ እርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ፡፡»*

ኢየሱስ ወደ ዮርዳኖስ ሄዶ በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ ዮሐንስንም «አጥምቀኝ» ብሎ አዘዘው ዮሐንስም «እኔ ባንተ መጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን?» አለው የሰማይና የምድር ሊቀ ካህናት ባንድ ላይ ተገናኙ::

በዕብራውያን እንደተወሳው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ መልከጼድቅ ስርአት ለዘላለም ሊቀ ካህን ነው ይህ ማለት ኢየሱስ ሰብአዊ የዘር ግንድ የለውም ማለት ነው እርሱ የአሮን ወይም በምድር ላይ የማንም ዘር አልነበረም እርሱ ፈጣሪያችን የእግዚአብሄር ልጅ ነው እርሱ ያለና የሚኖር ነው ስለዚህ የዘር ግንድ የለውም ኢየሱስ የሰማይን ክብር አውልቆ ሕዝቡን ለማዳን ወደዚህ ምድር መጣ::

እርሱ ወደዚህ ምድር የወረደበት ምክንያት በሰይጣን ማታለያ የተሰቃዩትን ሐጢያተኞች በሙሉ ለማዳን ነው በተጨማሪም በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል *«ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት::»*

*«አሁንስ ፍቀድልኝ»* ፍቀድልኝ! ኢየሱስ የሰው ዘር ሁሉ ወኪል የሆነውን አዘዘውና ለመጠመቅ ራሱን አኀነበሰ በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሄር መስዋዕት ሲቀርብ ሐጢያተኛው ወይም ሊቀ ካህኑ በራሱ ላይ እጆቹን በመጫን ሐጢያቶችን ያስተላልፋል «የአንድን ሰው እጅ መጫን» ማለት «ማስተላለፍ» ማለት ነው::

አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስን አጠመቀው ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚደረገው እጆችን መጫን ጋር ተመሳሳይ ነበር «ማስተላለፍ» «መቀበር» እና «መስዋዕት ማድረግ» እንደዚሁ ተመሳሳይ ናቸው ብሉይ ኪዳን ጥላ ሲሆን አዲስ ኪዳን አካል ነው::

በብሉይ ኪዳን አንድ ሐጢያተኛ እጆቹን በጠቦቱ ላይ ሲጭን ሐጢያቱ ወደ ጠቦቱ ይተላለፋል ጠቦቱም ይታረዳል ጠቦቱ ሲሞት ይቀበራል እጆቹን በጠቦቱ ላይ የጫነው ሰው ሐጢያቶች ወደ መስዋዕቱ እንስሳ ስለተላለፉ በሐጢያቶች ምክንያቱ ጠቦቱ መታረድ ነበረበት! ሐጢያቶቹ ወደ ጠቦቱ ከተላለፉ በስርአተ መስዋዕቱ መሰረት ጠቦቱን ያቀረበው ሰው ያለ ሐጢያት መሆን ይቻለዋልን? አዎ::

ይህ መሃረብ ሐጢያት ይህ ማይክራፎን ደግሞ ጠቦት ነው እንበል እጆቼን በዚህ ማይክራፎን ላይ ስጭን ይህ ሐጢያት ወደ እርሱ ወደ ጠቦቱ ይተላለፋል እንዲህ እንዲሆን የወሰነው እግዚአብሄር ራሱ ነው «እጆችህን ጫን» በብሉይ ኪዳን ዘመን አንድ ሰው ከሐጢያቶች ለመዳን እጆቹን በመስዋዕቱ ራስ ላይ መጫን ነበረበት ከዚያ በኋላ ያለ ሐጢያት መሆን ይችላል ልክ እንደዚሁ የኢየሱስ ጥምቀት የአለምን ሐጢያቶች ማንጻት መቅበርና ወደ እርሱ ማስተላለፍ ነበረበት ትክክለኛው ነገር ይህ ነው::

*ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ማለት ምን ማለት ነው?*

*ሐጢያቶችን ወደ ኢየሱስ በማስተላለፍ ሐጢያቶችን ሁሉ ማንፃት ማለት ነው::*

ስለዚህ ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ በተጠመቀ ጊዜ በእርግጥ ሁሉም ወደ እርሱ ተላልፈው ነበርን? የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል ሰዎችም ሁሉ ተዋጅተዋል ይህም በብሉይ ኪዳን ሐጢያቶችን ወደ

መስዋዕቶች ከማስተላለፍ ጋር ተመሳሳይ ነው ኢየሱስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጥቶ ዮሐንስን እንዲህ አለው *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው።» (ማቴዎስ 3:15)*

ያን ጊዜ ዮሐንስ ኢየሱስን አጠመቀው በእርሱ ጥምቀት ጽድቅን ሁሉ መፈጸም እንደሚገባቸው ለዮሐንስ ነገረው *«ጽድቅን ሁሉ»* ማለት «እጅግ ተገቢና ተስማሚ» ማለት ነው በሌላ አነጋገር «እንዲህ» በጥምቀት አማካይነት ጽድቅ ሁሉ ተፈጸመ ይህ ማለት ዮሐንስ ኢየሱስን ማጥመቁና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ ለማስተላለፍም ኢየሱስ በዮሐንስ መጠመቁ ትክክል ነበር ማለት ነው።

እግዚአብሄር ቤዛነትን የሚሰጠው በኢየሱስ ጥምቀት በመስቀል ላይ መስዋዕቱና በእኛ እምነቶች ላይ ተመስርቶ ነው «ሰዎች ሁሉ በሐጢያት ተቸግረዋል በሐጢያቶቻቸውም ምክንያት በዲያብሎስ ተሰቃይተዋል ስለዚህ እነርሱ እንዲድኑና ሰማይ እንዲገቡ አንተ የሰው ዘር ወኪልና የአሮን ዘር በመሆንህ ለሕዝቡ ሁሉ ልታጠምቀኝ ይገባል እኔም በአንተ እጠመቃለሁ ያን ጊዜ የቤዛነት ስራ ይጠናቀቃል።»

ዮሐንስም «ገብቶኛል» ብሎ መለሰ።

ስለዚህ ዮሐንስ ኢየሱስን አጠመቀው በኢየሱስ ራስ ላይ እጆቹን ጭኖ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ አስተላለፈ በዚህም ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ያነጻ አዳኝ ሆነ አሁን በእርሱ ቤዛነት ማመን ሊያድነን ይችላል ታምናላችሁን?

ኢየሱስ በሰው ዘር ሁሉ ወኪል እጆች አማካይነት በዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በሰውነቱ ተሸክሞ በአገልግሎቱ ውስጥ የመጀመሪያ ይፋ ስራዎች አድርጎ እየተጓዘ ለሶስት አመት ተኩል ወንጌልን ሰበከ።

በምንዝር ለተያዘችው ሴት እንዲህ አላት *«እኔም አልፈርድብሽም»* ሊፈርድባት ያልቻለው ሐጢያቶችዋን በሙሉ በራሱ ላይ ስለወሰደና ለእነርሱም በመስቀል ላይ ለመሞት ስለተዘጋጀ ነበር ጌቴሴማኔ በተባለ ስፍራ ሲጸልይ የአምላክ የፍርድ ጽዋ ከእርሱ እንዲያልፍ ይፈቅድ ዘንድ አብን በመለመን ሦስት ጊዜ ጸለየ ነገር ወዲያውኑ ይህንን ትቶ *«እኔ እንደምፈቅድ ሳይሆን አንተ እንደምትፈቅድ ይሁን»* አለ፡፡ ዝሙት ስትፈፅም እንደተያዘች የተነገረውንም ሴት፣ *«እኔም*

## *«እነሆ! የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!»*

*ኢየሱስ የወሰደው ምን ያህሉን ኃጢያት ነው?*

*የዓለምን ሐጢያቶች በሙሉ ነው፡፡*

ዮሐንስ 1:29 እንዲህ ይላል *«በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶት እንዲህ አለ- እነሆ! የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሐር በግ»* አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስን አጠመቀው በነገውም ኢየሱስ ወደ እርሱ መጣ ስለዚህ ለሕዝቡ *«እነሆ! የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሐር በግ»* በማለት ነገራቸው ይህ የእርሱ ምስክርነት ነበር፡፡

የእግዚአብሄር ልጅ ወደዚህ አለም መጥቶ ሐጢያቶቹን ሁሉ ወሰደ አጥማቂው ዮሐንስ እንደገናም መሰከረ ዮሐንስ 1:35-36

*«በነገው ደግሞ ዮሐንስ ከደቀመዛሙርም ሁለት ቆመው ነበር ኢየሱስም ሲሄድ ተመልክቶ- እነሆ የእግዚአብሔር በግ! አለ።»*

የእግዚአብሄር በግ የሚያመላክተው ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ለእስራኤል ሐጢያቶች እንደሞተ የተጠቀሰው እውነተኛና ትክክለኛ የመስዋዕት እንስሳ የመሆኑን እውነታ ነው የእግዚአብሄር ልጅና ፈጣሪያችን ሐጢያቶቻችንን ከአለም ፍጥረት እስከ ፍጻሜው ድረስ ያሉትን ሐጢያቶች በሙሉ ከአዳም ሐጢያት ጀምሮ እኛ እስከሰራናቸው በደሎች ድረስ ያሉትን ከድካሞቻችንን እስከ ስህተቶቻችን ድረስ ያሉትን ሐጢያቶች ለመውሰድ ለእናንተና ለእኔ ወደ አለም መጣ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ሁላችንንም አዳነን።

ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶ ለእኛ ለምዕመናኖች ፍጹም ቤዛነትን ሰጠን ይህንን አስተዋላችሁን? *«የዓለምን ኃጢያት ሁሉ የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!»*

እርሱ በዚህ ምድር ላይ ከተወለደ 2000 አመታት አልፈዋል በ30 አ.ም ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወሰደ 1 አ.ም ኢየሱስ የተወለደበት አመት ነበር ከክርስቶስ በፊት ያለውን ዘመን ዓመተ ዓለም ብለን እንጠራዋለን ኢየሱስ ወደዚህ አለም ከመጣ ወደ 2000 አመታት ያህል አልፈዋል።

በ30 አ.ም አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስን አጠመቀው በቀጣዩም ቀን ዮሐንስ ለሕዝቡ እንዲህ ሲል ጮኸ *«እነሆ! የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» «እነሆ!»* ሰዎች ሐጢያቶቻቸውን ሁሉ በወሰደው በኢየሱስ እንዲያምኑ ነገራቸው ኢየሱስ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ያዳነን የእግዚአብሄር በግ እንደነበር መሰከረ።

ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወሰደ ከሐጢያት ጋር የምናደርገውም ዘላቂ ጦርነት አበቃ የእግዚአብሄር ልጅ ስለወሰዳቸው እኛ አሁን ያለ ሐጢያት ነን አጥማቂው ዮሐንስ

ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ የእናንተንና የእኔ ሐጢያቶች እንደወሰደ መስክሮዋል *«ሁሉ በእርሱ (ዮሐንስ) በኩል እንዲያምኑ ይህ ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ ለምስክር መጣ::» (ዮሐንስ 1:7)*

ያለ ዮሐንስ ምስክርነት ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደ እንዴት ማወቅ እንችል ነበር? መጽሐፍ ቅዱስ ብዙውን ጊዜ እርሱ ስለ እኛ እንደሞተ ይነግረናል ነገር ግን ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደ በግልጽ የመሰከረው አጥማቂው ዮሐንስ ብቻ ነው::




ኢየሱስ ከሞተ በኋላ እውነቱን ብዙዎች መስክረዋል በሕይወት ሳለ ግን የመሰከረው ዮሐንስ ብቻ ነው የኢየሱስ ደቀ መዛሙርትም የኢየሱስን ቤዛነት መመስከራቸው እርግጥ ነው እነርሱ ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን እንደወሰደና አዳኛችን እንደሆነ መስክረዋል::

ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች ወሰደ አሁን አንባቢ ሆይ ገና 100 አመት አልሆነህም ሆኖሃል እንዴ? ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች የወሰደው በ30 አመቱ ነበር ይህንን ስዕላዊ መግለጫ ተመልከቱ::

ኢየሱስ የዓለምን ኃጢያት በሙሉ አስወግዷል፡፡ አሁን ገና 100 ዓመት አልሞላህም አይደል? ኢየሱስ የዓለምን ኃጢያት የወሰደው እርሱ 30 ዓመት በሞላው ጊዜ ነበር፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ምስል እኒጢን፡-

አዳም ⟶ አብርሃም ⟶ የኢየሱስ ጥምቀት ⟶ አሁን ⟶ መጨረሻ
4000 ዓ.ዓ. 2000 ዓ.ዓ. 30 ዓ.ም. 2000 ዓ.ም. ? ዓ.ም.

⟸ የዓለም ኃጢያቶች በሙሉ ⟹

ሰው የተፈጠረው ኢየሱስ ከመምጣቱ ከ4,000 አመታት በፊት ነው እንበል ኢየሱስ ከመጣ ከ2,000 አመታት ጥቂት አልፎዋል እንበል አለም እስከ መቼ ድረስ እንደሚቆይ አናውቅም መጨረሻው ግን እንደሚመጣ የተረጋገጠ ነው እርሱ እንዲህ ይላል *«አልፋና ዖሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ፡፡» (ራዕይ፡ 22:13)*

ስለዚህ መጨረሻ እንዳለ የተረጋገጠ ነው አሁን እኛ ያለነው 2002 አመት በሚለው ጠቋሚ ላይ ነው ክርስቶስ በ30 አ.ም ሐጢያቶቻችንን ወሰደ ይህም በመስቀል ላይ ከመሞቱ ከ3 አመት በፊት ነው፡

*«እነሆ! የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ»* እርሱ የአለምን ሐጢያቶች የእናንተንና የእኔን ሐጢያቶች ወሰደ እኛ ከኢየሱስ ልደት 2,000 አመታት ርቀን ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን ከወሰደ ከ2,000 አመታት በኋላ ሕይወታችንን እየኖርን ነው አሁንም ድረስ እየኖርንና ቀንና ሌሊት ሐጢያቶችን እየሰራን ነው ነገር ግን ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች አስቀድሞ የወሰደ የእግዚአብሄር በግ ነው፡፡

ከተወለድንበት ቅጽበት ጀምሮ መኖርና ሐጢያት መስራት

እንጀምራለን ከተወለድንበት ቅጽበት ጀምሮ ሁላችንም ሐጢያት እንሰራለን ወይስ አንሰራም? --እንሰራለን-- እስቲ ሒደቱን ሁሉ እንለፍበት ከተወለድንበት ቀን ጀምሮ 10 አመት እስኪሆነን ድረስ ሐጢያት እንሰራለን ወይስ አንሰራም? --እንሰራለን -- ታዲያ እነዚያ ሐጢያቶች ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል ወይስ አልተላለፉም? --ተላልፈዋል--ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ስለተላለፉ እርሱ አዳኛችን ነው እንደዚያ ካልሆነ እንዴት አዳኛ ችን ሊሆን ይችላል? ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል::

ከ11 እስከ 20 አመት ድረስ ሐጢያት ሰርተናል ወይስ አልሰራንም? በልቦቻችንና በምግባሮቻችን ሐጢያት ሰርተናል...ሐጢያት በመስራት የተዋጣልን ነን ሐጢያት እንዳንሰራ ተምረናል ነገር ግን በተፈጥሮ ሐጢያቶች ለመስራት እናዘነብላለን::

እግዚአብሄር እነዚያ ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ ነግሮናል ሐጢያተኞች እንደሆንን ስላወቀ እነዚያን ሐጢያቶች በሙሉ አስቀድሞ ወሰደ::

በዚህ አለም ላይ በተለምዶ የምንኖረው ምን ያህል ነው? 70 አመት አካባቢ ነው እንበል በእነዚያ 70 አመታቶች የሰራናቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ብንጨምር ሸክማችን ምን ያህል ከባድ ይሆናል? 8 ቶን በሚጭኑ የጭነት መኪኖች ውስጥ ብንጠቀጥቃቸው ምናልባትም ከ100 በላይ የጭነት መኪኖች ያስፈልጉን ነበር::

በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ምን ያህል ሐጢያት እንደምንሰራ ለማሰብ ሞክሩ እነዚያ የአለም ሐጢያቶች ናቸው ወይስ አይደሉም? የአለም ሐጢያቶች ክፍል ናቸው ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 10፣ ከ10 እስከ 20፣ ከ20 እስከ 30 አመታችን...እስክንሞት ድረስ ሐጢያት እንሰራለን እነዚያ

ሐጢያቶች በሙሉ ግን በጥምቀቱ አማካይነት ቀድሞውንም ወደ ኢየሱስ በተላለፉት የአለም ሐጢያቶች ውስጥ ተጨምረዋል፡፡

## የሰው አዳኝ ኢየሱስ ክርስቶስ

*ኢየሱስ ያስወገደልን*
*ምን ያህሉን ኃጢያት ነው?*

*የአያቶቻችን የኛን የዘሮቻችንን እንዲሁም*
*እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ያሉ*
*ሐጢያቶችን በሙሉ ነው፡፡*

ኢየሱስ እነዚያን ሐጢያቶች በሙሉ ለማስወገድ በስጋ እንደመጣ ነግሮናል ነገር ግን ኢየሱስ ራሱን ማጥመቅ ስላልቻለ እግዚአብሄር የሰዎች ሁሉ የተመረጠ ወኪል የሆነውን ባርያውን ዮሐንስን አስቀድሞ ላከው እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«ስሙም ድንቅ መካር ሐያል አምላክ ይባላል»* እርሱ በራሱ በጥበቡና በምክሩ የሰውን ዘር ወኪል አስቀድሞ ላከ የእግዚአብሄር ልጅ የሆነው ራሱ ኢየሱስም የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ በስጋ መጣ ይህ የእግዚአብሄርን ጥልቅ ችሮታ የሚያሳይ ድንቅ ደህንነት አይደለምን?

ይህ ድንቅ ነው አይደል? ስለዚህ እርሱ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ ብቻ በመላው አለም የሚኖሩትን የሰው ዘር ሐጢያቶች በሙሉ አንጽቶ ለአንዴና ለመጨረሻ በመሰቀል

እያንዳንዱን ሰው ከሐጢያት አድኖዋል ስለዚህ ነገር አስቡ ከ20 እስከ 30 ከ30 እስከ 40 ከ40 እስከ 60 እስከ 70 እስከ 100 አመት ድረስ ያሉትን የእናንተን ሐጢያቶችና የልጆቻችሁንም ሐጢያቶች በሙሉ ተመልከቱ እርሱ እነዚህን ሐጢያቶች በሙሉ ደምስሶዋል ወይስ አልደመሰሰም? አዎ ደምስሶዋል እርሱ የሰው ዘር አዳኝ ኢየሱስ ነው::

አጥማቂው ዮሐንስ ሐጢያቶችን በሙሉ ወደ ኢየሱስ ስላስተላለፈና እግዚአብሄርም እንዲህ እንዲሆን ስላቀደ በእርሱ በማመን መዳን እንችላለን እናንተና እኔ ሐጢያተኞች ነን? ሐጢያቶቻችን በሙሉ ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል ወይስ አልተላለፉም? ሐጢያቶቻችን ቀድሞውኑም ወደ ኢየሱስ ስለተላለፉ እኛ ከእንግዲህ ወዲያ ሐጢያተኞች አይደለንም?

በዚህ አለም ላይ ሐጢያት አለ ብሎ ለመናገር የሚደፍር ማነው? ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል እርሱ ሐጢያት እንደምንሰራ ስላወቀ የወደፊት ሐጢያቶችንም ሁሉ ወስዶዋል አንዳንዶቻችን ገና 50 አመት አልሆነንም አንዳንዶቻችን የዕድሜያችንን ግማሽ እንኳን ገና አልኖርንም አንዳንዶቻችን ግን እኔንም ጨምሮ ለዘላለም የምንኖር ይመስል ስለ ራሳችን እናወራለን::

አስቸጋሪ ሕይወት የምንኖር ብዙዎች አለን ይህንን በዚህ መንገድ ላብራራው የአንዲት እሳት ራት አጋማሽ የዕድሜ ርዝመት ምን ያህል ነው? 12 ሰአት አካባቢ ነው::

«ኦ አምላኬ! የዝንብ መግደያ ገጥሞኝ ደቅቄ ልሞት ነበር በተጋመሰው ሕይወቴ እንዲህ ያለ ጨካኝ ሰው ገጥሞኝ አያውቅም» የኖርሁት 12 ሰአት ብቻ ነበር ነገር ግን መለፍለፍዋን ማቆም አልቻለችም ነገር ግን ቀድሞውኑም የዕድሜዋ ግማሽ አልፎዋል::

ምሽት 1 ወይም 2 ሰአት ላይ የሕይወቷን ማምሻ

አልፋለች በቅርቡም ትሞታለች አንዳንድ የእሳት ራቶች 20 ሰአት አንዳንዶቹም 21 አንዳንዶቹም ሽምግልና ሊባል በሚችል መልኩ 24 ሰአት ይኖራሉ እነርሱ ስለ ዕድሜ ልምምዶቻቸው ያወሩ ይሆናል ይህ ግን ለእኛ ምን ይመስለናል? እኛ 70 ወይም 80 አመት ስለምንኖር «አታስቁኝ» እንል ይሆናል የእነርሱ ተሞክሮ በአይኖቻችን ፊት ምንም ማለት አይደለም፡፡

ይህንን ምሳሌ በእግዚአብሄርና በእኛ መካከል ባለው ግንኙነት ላይ እናውለው እግዚአብሄር ዘላለማዊ ነው እርሱ ለዘላለም ይኖራል እርሱ የአለምን መጀመሪያና መጨረሻ ወስኖዋል እርሱ ለዘላለም ስለሚኖር ከዘላለም የጊዜ ክልል ውጭ ለዘላለም ይኖራል እኛን የሚመለከተን ከዘላለማዊነቱ ስፍራ አንጻር ነው፡፡

በአንድ ወቅት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ በመስቀል ላይም ሞተ *«ተፈጸመ»* አለ በሶስተኛው ቀን ተነሳ ወደ ሰማይም አረገ አሁን በዘላለማዊነት ውስጥ ይኖራል አሁን ሁላችንንም ከላይ ሆኖ ወደ ታች ይመለከተናል፡፡

አንድ ሰው «ኦ ብዙ ሐጢያት ሰርቻለሁ የኖርሁት 20 አመት ብቻ ቢሆንም በጣም ብዙ ሐጢያት ሰርቻለሁ» «30 አመት ኖሬ በጣም ብዙ ሐጢያት ሰርቻለሁ በጣም ብዙ ነው እንዴት ያለ ሐጢያቶች መኖር እችላለሁ?» ይል ይሆናል፡፡

በዘላለማዊነቱ ውስጥ ያለው ጌታችን ግን «አታስቀኝ እስከ አሁን ድረስ የአንተን ሐጢያቶች ብቻ ሳይሆን አንተ ከመወለድህ በፊት የነበሩትን የቅድመ አያቶችህን ሐጢያቶች አንተ ከሞትህ በኋላ የሚኖሩትን የዘሮችህን ትውልድ ሐጢያቶች በሙሉ ዋጅቻለሁ» ይላል እርሱ ይህንን የሚነግራችሁ ከዘላለም የጊዜ ፋይዳ አንጻር ነው ይህንን ታምናላችሁን? እመኑትና በነጻ የተሰጣችሁን የደህንነት ስጦታ ተቀበሉ መንግስተ ሰማይም ግቡ፡፡

በራሳችሁ አስተሳቦች ራሳችሁን አትሰሩ ነገር ግን

በእግዚአብሄር ቃሎች እመኑ *«ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና»* የአለምን ሐጢያቶች የወሰደው የእግዚአብሄር በግ ቀድሞውኑም ጽድቅን ሁሉ ፈጽሞዋል ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል ወስዶዋል ወይስ አልወሰደም? ወስዶዋል፡፡

*ኢየሱስ በመስቀል ላይ የመጨረሻውን*
*እስትንፋሱን ከመተንፈሱ*
*በፊት ያለው ምን ነበር?*

*«ተፈፀመ፡፡»*

ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱ አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ በጴንጤናዊው ጲላጦስ ችሎትም ሞት ተፈርዶበት በመስቀል ላይ ተሰቀለ፡፡

*«መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወጣ በዚያም ሰቀሉት ከእርሱም ጋር ሌሎች ሁለት፣ አንዱን በዚህ አንዱን በዚያ ኢየሱስንም በመካከላቸው ሰቀሉት ጲላጦስም ደግሞ ጽሕፈት ጽፎ በመስቀሉ ላይ አኖረው ጽሕፈቱም፡- የአይሁድ ንጉስ የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚል ነበር ኢየሱስም የተሰቀለበት ስፍራ ለከተማ ቅርብ ነበርና ከአይሁድ ብዙዎች ይህንን ጽሕፈት አነበቡት በዕብራይስጥና በሮማይስጥ በግሪክም ተጽፎ ነበር፡፡» (ዮሐንስ 19:17-20)*

እርሱ በመስቀል ላይ ከተሰቀለ በኋላ ምን እንደተፈጠረ እንመልከት *«ከዚህም በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉም እንደተፈፀመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ ተጠማሁ አለ»* እርሱ

በመጽሐፍ እንደተጻፈው ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወሰደ *«ከዚህም በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ ነገር እንደ ተፈፀመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈፀም ዘንድ ተጠማሁ አለ በዚያም ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር እነርሱም ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው በሁሶጵም አድርገው ወደ አፉ አቀረቡለት ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ- ተፈጸመ አለ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።» (ዮሐንስ 19:28-30)*

ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ *«ተፈጸመ!»* በማለት ጮኸ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ በእርግጥም ሞቶ ነበር ኢየሱስ ክርስቶስ በሦስተኛው ቀን ተነስቶ ወደ ሰማይ አረገ።

ወደ ዕብራውያን 10:1-9 እንመለስ። *«ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና ስለዚህም በየአመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀርቡትን ሊፈፅም ከቶ አይችልም እንደዚህማ ባይሆን የሚያመልኩት አንድ ጊዜ ነፅተው ከዚያ በኋላ በሕሊናቸው ኃጢያትን ስላላወቁ ማቅረብን በተው አልነበረምን? ነገር ግን በዚያ መስዋዕት በየዓመቱ የኃጢያት መታሰቢያ አለ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ:- መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ስጋን ግን አዘጋጀህልኝ በሙሉ በሚቃጠል መስዋዕት ደስ አላለህም በዚያን ጊዜ:- እነሆ በመፅሐፍ ጥቅልል ስለ እኔ እንደተጻፈ አምላኬ ሆይ ፍቃድህን ላደርግ መጥቻለሁ አልሁ ይላል በዚህ ላይ:- መስዋዕትንና መባን በሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕትንም አልወደድህም በእርሱም ደስ አላለህም ብሎ እነዚህም እንደ ሕግ የሚቀርቡት ናቸው ቀጥሎ:- እነሆ አምላኬ ሆይ! ፍቃድህን ላድርግ መጥቻለሁ ብሎአል ሁለተኛውን ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል።»*

# ዘላለማዊ ቤዛነት

*በኢየሱስ ካመንን በኋላ በየእለቱ የምንሰራቸውን ኃጢያቶች የምናስወግደው እንዴት ነው?*

*ኢየሱስ በጥምቀቱ ቀድሞውኑም ሐጢያትን ሁሉ እንደደመሰሰ በማረጋገጥ ነው።*

በሌላ አነጋገር ሕጉ የመስዋዕቱ ስርአት ሊመጡ ያሉ ነገሮች ጥላ ነው የብሉይ ኪዳን የበጎችና የፍየሎች መስዋዕቶች ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚመጣና ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለመደምሰስም በተመሳሳይ ሁኔታ ሐጢያቶቻችንን እንደሚወስድ ገልጦልናል።

የብሉይ ኪዳን ሰዎች ዳዊት አብርሃም እና ሌሎች ሁሉ የመስዋዕቱ ስርአት ለእነርሱ ምን ማለት እንደሆነ አውቀዋል አምነዋልም የመስዋዕቱ ስርአት መሲሁ ክርስቶስ (ክርስቶስ ማለት «የተቀባ ንጉሥ» ማለት ነው) ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ ለማንጻት አንድ ቀን እንደሚመጣ ይገልጣል እነርሱ በደህንነታቸው አምነው በእምነታቸው ዳኑ።

ሕጉ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ነበር ለሐጢያቶቻቸው በየቀኑና በየአመቱ መስዋዕቶችን ማቅረብ ፈጽሞ ሙሉ በሙሉ ሊበዙዋቸው አልቻሉም ስለዚህ እንከን የሌለበት ፍጹምና ዘላለማዊ ሕላዌ የሆነው የእግዚአብሄር ልጅ ወደ ምድር መምጣት ነበረበት።

ኢየሱስ ስለ እርሱ በመጽሐፍ እንደተጻፈ የአባቱን ፈቃድ ለማድረግ መጣ *«እነሆ አምላኬ ሆይ! ፍቃድህን ላድርግ መጥቻለሁ ብሎአል ሁለተኛውን ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል»* ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንደተጻፈው ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ስለወሰደና እኛም በእርሱ ስለምናምን ከሐጢያቶቻችንን ድነናል::

*ዕብራውያን 10:10ን እናንብብ «በዚህም ፍቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል»* በዚያ ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ በማቅረብ አንድ ጊዜ ተቀድሰናል ተቀድሰናል ወይስ አልተቀደስንም? --ተቀድሰናል--:: *»* በዚህም ፍቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል:: ተቀድሰናል ወይስ አልተቀደስንም? —ተቀድሰናል::—

ይህ ምን ማለት ነው? እግዚአብሄር አብ ልጁን ላከ ሐጢያቶቻችንንም በሙሉ በጥምቀቱ አማካይነት ወደ እርሱ አስተላለፈ ተቀብሎትም በመስቀል ላይም ለዘላለም ፈረደበት ስለዚህ በሐጢያት ስንሰቃይ የነበርነውን ሁላችንን አዳነን የእግዚአብሄር ፈቃድ ይህ ነበር::

መቀደስ እንችል ዘንድ ኢየሱስ እኛን ለማዳን ለአንዴና ለመጨረሻ ራሱን የዘላለም መስዋዕት አድርጎ አቀረበ እኛም ተቀድሰናል ምክንያቱም ኢየሱስ ራሱ እንዳይፈረድብን ለሐጢያቶቻችን ሁሉ መስዋዕት ሆነ ስለ እኛም ሞተ::

የብሉይ ኪዳን መስዋዕት በየቀኑ የሚቀርበው በየቀኑ የሚሰሩት ሐጢያቶች በሙሉ ለመንጻት ሌላ መስዋዕት ያስፈልጋቸው ስለ ነበር ነው::

# ኢየሱስ የጴጥሮስን እግር የማጠቡ መንፈሳዊ ትርጉም

*የንስሐ ጸሎቶች ልናቀርብለት የሚገባን አንዳች ሐጢያት አለን?*

*የለም፡፡*

በዮሐንስ 13 ላይ ኢየሱስ የጴጥሮስን እግር ያጠበበት ታሪክ አለ እርሱ የጴጥሮስን እግር ያጠበው ጴጥሮስ ወደፊትም ሐጢያቶችን እንደሚሰራ ሊያሳየውና ቀድሞውኑም እነዚያን ሐጢያቶች በሙሉ እንደዋጃቸው ሊያስተምረው ነበር ኢየሱስ ጴጥሮስ ወደፊትም ደግሞ ሐጢያት እንደሚሰራ አውቋል ስለዚህ በመታጠቢያው ውስጥ ውሃ አፍስሶ እግሮቹን አጠበ፡፡

ጴጥሮስ አሻፈረኝ ለማለት ቢሞክርም ኢየሱስ «*እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም በኋላ ግን ታስተውለዋለህ*» አለው ይህ ምንባብ «ከዚህ በኋላ እንደገና ሐጢያት ትሰራለህ ሐጢያቶችህን በሙሉ ካነጻሁልህ በኋላ ትክደኛለህ ዳግመኛም ሐጢያት ትሰራለህ እኔ ወደ ሰማይ ካረግሁ በኋላም እንኳን ሐጢያትን ትሰራለህ ስለዚህ አስቀድሞ የወደፊት ሐጢያቶችህንም እንኳን ስለወሰድሁ ሰይጣን እንዳይፈትንህ ለማስጠንቀቅ እግሮችህን አጥባለሁ» ማለት ነው፡፡

እርሱ የጴጥሮስን እግር ያጠበው እኛ በየቀኑ ንስሐ መግባት እንዳለብን ሊነግረን ይመስላችኋልን? አይደለም ለመዳን በየቀኑ ንስሐ መግባት ቢኖርብን ኖሮ ያ ማለት ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ አልወሰደም ማለት ይሆን ነበር፡፡

ኢየሱስ ግን ለዘላለም እንደቀደሰን ተናግሮዋል በየቀኑ ንስሐ መግባት ቢኖርብን ኖሮ ወደ ብሉይ ኪዳን ዘመን መመለስም ይገባን ነበር ታዲያ ማን ይጸድቃል? ሙሉ በሙሉስ ማን ሊድን ይችላል? በእግዚአብሄር ብናምንም ማን ያለ ሐጢያት ሊኖር ይችላል?

ንስሐ በመግባት ማን ሊቀደስ ይችላል? እኛ ያለ ማቋረጥ በየቀኑ ሐጢያት እንሰራለን ስለዚህ ለእያንዳንዱ ሐጢያት ይቅርታ መጠየቅ የምንችለው እንዴት ነው? ቤዛነቶቻችንን ለማግኘት እንዲህ ግድ የለሾች የምንሆነውና እርሱን መነዝነዝ የምንችለው እንዴት ነው? ምሽት ላይ ማለዳ የሰራናቸውን ሐጢያቶች ወደ መርሳት እናዘነብላለን ማታ የሰራናቸውን ሐጢያቶች ደግሞ ጠዋት እንረሳቸዋለን ለሐጢያቶቻችን በሙሉ ፈጽሞ ንስሐ መግባት አይቻለንም፡፡

ስለዚህ ኢየሱስ አንድ ጊዜ ተጠመቀ ሁላችንም በአንድ ጊዜ እንቀደስ ዘንድም ራሱን አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ አቀረበ ይህንን ማስተዋል ትችላላችሁን? እኛ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ተዋጅተናል የምንዋጀው ንስሐ በምንገባበት ጊዜ ሁሉ አይደለም፡፡

ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን የእናንተንና የእኔን ሐጢያቶች በሙሉ እንደወሰደ በማመን ከሐጢያቶቻችን ድነናል፡፡

*«ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢያትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል እርሱ ግን ስለ ኃጢያት አንድን መሥዋዕት ለዘለዓለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደፊት ይጠብቃል አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎኣቸዋልና መንፈስ ቅዱስም ደግሞ ስለዚህ ይመሰክርልናል ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋርም የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ*

*በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እፅፈዋለሁ ብሎ ከተናገረ በኋላ ኃጢያታቸውንና ዓመፃቸውንም ደግሜ አላስብም ይላል የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከእንግዲህ ወዲያ ስለ ኃጢያት ማቅረብ የለም።» (ዕብራውያን 10:11-18)*

ከላይ በቁጥር 18 ላይ *«የእነዚህ ስርየት ባለበት»* ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ማለት ሐጢያት ራሱ ማንኛውም ሐጢያት ምንም ሳይቀር ለዘላለም ስርየትን አግኝቷል ማለት ነው እግዚአብሄር እነርሱን ደምስሶ ሁላችንንም ይቅር ብሎናል ይህንን ታምናላችሁን? *«የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ሐጢያት ማቅረብ የለም።»*

እስከ አሁን ያለውን እያንዳንዱን ነገር እናጠቃለው በሌላ አነጋገር አጥማቂው ዮሐንስ እጆቹን በኢየሱስ ላይ ባይጭን ኢየሱስንም ባያጠምቀው ኖሮ መዳን እንችል ነበርን? ፈጽሞ አንችልም! ወደኋላ ተመልሰን እናስብ ኢየሱስ አጥማቂውን ዮሐንስን የሰዎች ሁሉ ወኪል አድርጎ ባይመርጠውና በእርሱ አማካይነትም ሐጢያት ሁሉ ባይወስድ ኖሮ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ማንጻት ይችል ነበር? አይችልም ነበር።

የእግዚአብሄር ሕግ ጻድቅ ነው መልካምም ነው እርሱ አዳኛችን እንደሆነና ሐጢያቶቻችንን ሁሉ እንደወሰደ ብቻ አልተናገረም ሐጢያቶቻችንን በተግባር መውሰድ ነበረበት አምላክ የሆነው ኢየሱስ በስጋ ለምን ወደ እኛ መጣ? የመጣው የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ በጥምቀቱ አማካይነት ለመውሰድ ነው ኢየሱስ የዘላለም መስዋዕት ሆኖ ለመቅረብ በስጋ እስካልመጣ ድረስ የልባችንና የስጋችን ሐጢያቶች በሙሉ ሊደመሰሱ እንደማይችሉ ያውቅ ነበር።

ኢየሱስ ባይጠመቅ ኖሮ ሐጢያቶቻችን አሁንም ድረስ ይኖሩ ነበር በመጀመሪያ ሐጢያቶቻችንን ሳይወስድ ቢሰቀል ኖሮ ሞቱ ትርጉም አልባ ይሆን ነበር ከእኛ ጋር ምንም የሚያገናኘው

ነገር አይኖረውም ነበር ፈጽሞ ትርጉም የለሽ ይሆን ነበር፡፡

ስለዚህ በ30 አመቱ የአደባባይ አገልግሎቱን ሲጀምር ሊጠመቅ በዮርዳኖስ ወዳለው ወደ አጥማቂው ዮሐንስ ሄደ የእርሱ የአደባባይ አገልግሎት የተጀመረው በ30 አመቱ ያበቃው ደግሞ በ33 አመቱ ነበር 30 አመት ሲሆነው ሊጠመቅ ወደ አጥማቂው ዮሐንስ ሄደ «አሁንስ ፍቀድልኝ ሰዎች ሁሉ መዳንና ጻድቃን መሆን ይችሉ ዘንድ እንዲህ ማድረግ ይገባናልና ለእኛ ይህንን ማድረግ ተገቢ ነገር ነው አሁን አጥምቀኝ» አዎ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች ሁሉ ቤዛነት ተጠመቀ፡፡

ኢየሱስ በመጠመቁና ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በመውሰዱ ሐጢያቶቻችን በሙሉም በአጥማቂው ዮሐንስ እጆች አማካይነት ወደ እርሱ በመተላለፋቸው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሊሞት ሲያጣጥር እግዚአብሄር ራሱ አይኖቹን መለሰ ኢየሱስ የእርሱ አንድያ ልጅ ቢሆንም ልጁን መስዋዕት ማድረግ ነበረበት፡፡

እግዚአብሄር ፍቅር ነው ነገር ግን ልጁ እንዲሞት መፍቀድ ነበረበት ስለዚህ ለሶስት ሰአታት ያህል በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ነበር ኢየሱስም ከመሞቱ ቀደም ብሎ *«ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ?»* በማለት ጮኸ ያም ማለት *«አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?»* ማለት ነው ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ተሸክሞ ስለ እኛ በመስቀል ላይ በይፋ ፍርድን ተቀበለ በዚህም ሁላችንን አዳነን ያለ ኢየሱስ ጥምቀት ሞቱ ትርጉም የለሽ ነው፡፡

*ኃጢያተኛ ነህ ወይስ*
*ጻድቅ ሰው?*

*በልቤ ውስጥ አንዳች ሐጢያት*
*የሌለብኝ ጻድቅ ሰው፡፡*

ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ሳይወስድ በመስቀል ላይ ሞቶ ቢሆን ኖሮ ሞቱ ቤዛነትን አይፈጽምም ነበር ኢየሱስ እኛን ፈጽሞ ለመዋጀት የሰዎች ሁሉ ወኪል በሆነው በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ በእርሱ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ይድኑ ዘንድም በመስቀል ላይ ፍርድን ተቀበለ።

ስለዚህ ከአጥማቂው ዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ መንግስተ ሰማያት ትገፋለች አጥማቂው ዮሐንስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ስላስተላለፈ ሐጢያቶቻችን ስርየትን አግኝተዋል አሁን እናንተና እኔ እግዚአብሄርን አባታችን ብለን መጥራትና በድፍረትም መንግስተ ሰማይ መግባት እንችላለን።

ዕብራውያን 10:18 እንዲህ ይላል *«የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከእንግዲህ ወዲያ ስለ ኃጢያት ማቅረብ የለም»* እናንተ አሁንም ሐጢያተኞች ናችሁን? ኢየሱስ ቀድሞውኑም ዕዳዎቻችሁን በሙሉ ከፍሎ ሳለ አሁንም ገና ዕዳዎቻችሁን መክፈል ይኖርባችኋልን?

ከልክ በላይ የመጠጣት አባዜው ከብዙ አበዳሪዎች እንዲበደር ያደረገው አንድ ሰው ነበር ታዲያ አንድ ቀን ልጁ አዱኛ አገኘና የአባቱን ዕዳዎች በሙሉ ከፈለ አባቱ በዚያ በሚገኝ በእያንዳንዱ መሸታ ቤት ብዙ ዕዳ ቢኖርበትም ዳግመኛ መክፈል የለበትም።

ኢየሱስም ለእኛ ያደረገው ይህንኑ ነው ለሐጢያቶቻችን ከሚገባው በላይ በቅድሚያ ከፈለ በዕድሜ ዘመናችን ለምንሰራቸው ሐጢያቶች ብቻ አይደለም ለአለም ሐጢያቶችም በሙሉ ነው እነርሱ እርሱ በተጠመቀ ጊዜ ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል አሁንም ገና ሐጢያተኞች ናችሁን? አይደላችሁም።

ይህንን ወንጌል ከመጀመሪያው ጀምሮ አውቀነው ቢሆን

ኖሮ በኢየሱስ ማመን እንዴት በቀለለን ነበር ነገር ግን በጣም አዲስ ስለሚመስል ብዙ ሰዎች ግራ ተጋብተውበታል።

ይህ ግን አዲስ ነገር አይደለም ከሰው ታሪክ ጀምሮ የኖረ ነው እኛ ከዚህ በፊት አላወቅነውም የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ሁልጊዜም በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ተመዝግቦ የነበረና ሁልጊዜም ሲተገበር የነበረ ነው ሁልጊዜም እዚያው ነበር እናንተና እኔ ከመወለዳችን በፊትም እዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነበረ ከምድር ፍጥረት በፊትም እዚሁ ነበር።

## የዘላለም ቤዛነት ወንጌል

*በእግዚአብሔር ፊት*
*ምን ማድረግ አለብን?*

*በዘላለማዊው የቤዛነት ወንጌል*
*ማመን አለብን።*

ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ያነጻው ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ያደረገው እናንተና እኔ ከመወለዳችንም በፊት ነው እርሱ ሁሉንም ወስዶዋቸዋል አሁንም ድረስ ከሐጢያት ጋር ናችሁን? --አይደለም-- ነገ የምትሰሩዋቸው ሐጢያቶችስ? እነርሱም በአለም ሐጢያቶች ውስጥ ተጨምረዋል።

የነገን ሐጢያቶች አሁኑኑ እናስወግዳቸው እስከ አሁን ድረስ የሰራናቸው ሐጢያቶችም እንደዚሁ በአለም ሐጢያቶች ውስጥ ተካተዋል አልተካተቱምን? ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል ወይስ አልተላለፉም? አዎ ተላልፈዋል።

ታዲያ የነገ ሐጢያቶችም ወደ እርሱ ተላልፈዋልን? አዎ እርሱ ምንም ሳያስቀር ሁሉንም ወስዶዋል አንድም የተወው ሐጢያት የለም ወንጌል ኢየሱስ በአንድ ጊዜ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደና ለሁሉም ዋጋ እንደከፈለ ከሙሉ ልባችን እንድናምን ይነግረናል፡፡

*«የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ» (ማርቆስ 1:1)* የሰማይ ወንጌል የምስራች ነው እርሱ «እኔ ሐጢያቶቻችሁን በሙሉ ወስጃለሁ እኔ አዳኛችሁ ነኝ በእኔ ታምናላችሁን?» ብሎ ይጠይቀናል እጅግ ብዙ ቁጥር ካላቸው ሰዎች መካከል «አዎ አምናለሁ አንተ እንደነገርከን አምናለሁ በጣም ቀላል ስለሆነ ወዲያውኑ ልረዳው ችያለሁ» ብለው የመለሱት ጥቂቶች ብቻ ናቸው እምነታቸውን እንዲህ የሚመሰክሩ ሰዎች ልክ እንደ አብርሃም ጻድቃን ይሆናሉ፡፡

ሌሎች ግን «ይህንን ማመን አልችልም ለእኔ አዲስና እንግዳ ይመስላል» ይላሉ፡፡

ያን ጊዜ «እስቲ ንገሩኝ ሐጢያቶቻችሁን በሙሉ ወስጃለሁ ወይስ አልወሰድኩም?» በማለት ይጠይቃቸዋል፡፡

«የተማርኩት አንተ የወሰድከው በየቀኑ የምሰራቸውን ሐጢያቶቼን ሳይሆን የአዳምን ሐጢያት ብቻ እንደሆነ ነው፡፡»

«የተነገረህን ለማመን በጣም ብልህ እንደሆንህ አያለሁ የምነግርህ ምንም ነገር ስለሌለ ወደ ሲዖል መሄድ አለብህ፡፡»

በእርሱ ፍጹም ቤዛነት በማመናችን ድነናል ሐጢያት እንዳለባቸው የሚሟገቱ ሁሉ ወደ ሲዖል መውረድ አለባቸው የራሳቸውን ምርጫ መርጠዋል፡፡

የቤዛነት ወንጌል የጀመረው ከአጥማቂው ዮሐንስ ምስክርነት ነው ኢየሱስ ከአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበለው ጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ስላነጻ ስናምን ተቀድሰናል፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ በመልዕክቶቹ ውስጥ ስለ ኢየሱስ ጥምቀት ብዙ ተናግሮዋል በገላትያ 3:27 ላይ እንዲህ ይላል *«ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና»* «በክርስቶስ መጠመቅ» ማለት በእርሱ ጥምቀት በማመን ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆነናል ማለት ነው ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቻችን በሙሉ በአጥማቂው ዮሐንስ አማካይነት ወደ እርሱ ተላልፈው ሙሉ በሙሉ ነጽተዋል::

1ኛ ጴጥሮስ 3:21 እንዲህ ይላል *«ይህም ውኃ ማለት ደግሞ ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም ለእግዚአብሔር የበጎ ህሊና ልመና ነው እንጂ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው::»*

የቤዛነትን ጸጋ ከላይ የሚቀበሉት በአጥማቂው ዮሐንስ ምስክርነት በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ደም የሚያምኑ ሰዎች ብቻ ናቸው::

የኢየሱስን ጥምቀት የደህንነታችን ምሳሌ አድርጋችሁ በልባችሁ በመቀበል ዳኑ:: ✉

# ስብከት 6

## ኢየሱስ ክርስቶስ

---

## የመጣው በውሃ፣ በደምና

---

## በመንፈስ ነው

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡



ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

# ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው በውሃ፣ በደምና በመንፈስ ነው

« **1ኛ ዮሐንስ 5:1-12** »

«ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል ወላጁንም የሚወድ ሁሉ ከእርሱ የተወለደውንም ይወዳል እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ የእግዚአብሔርልጆችነ እንድንወድ በዚህ እናውቃለን ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማነው? በውኃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በውኃውና በደሙ እንጂ በውኃው ብቻ አይደለም መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ ነው የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው ደሙም ሶስት ናቸውና ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ የሰውን ምስክር ከእርሱ ይልቅ ይበልጣል ስለ ልጁ የመሰከረው የእግዚአብሔር ምስክር ይህ ነውና በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው በእግዚአብሔር የማያምን እግዚአብሔር ስለ ልጁ የመሰከረውን ምስክር ስላላመነ ሐሰተኛ አድርጎታል እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው ልጅ ያለው ህይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም።»

*ኢየሱስ የመጣው*
*በምንድን ነው?*

*በውኃ በደምና*
*በመንፈስ ነው::*

ኢየሱስ የመጣው በውኃ ነውን? አዎን እንደዚያ ነበር እርሱ በጥምቀቱ መጣ ውሃው የሚያመለክተው በዮርዳኖስ ወንዝ በአጥማቂው ዮሐንስ የሆነውን የኢየሱስ ጥምቀት ነው ይህም የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ የወሰደበት የቤዛነት ጥምቀት ነበር::

ኢየሱስ በደም መጥቶዋልን? አዎ መጥቶዋል የሰው ስጋ ለብሶ መጣ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድም ተጠመቀ በመስቀል ላይ ደሙን በማፍሰስም የሐጢያትን ደመወዝ ሁሉ ከፈለ ኢየሱስ የመጣው በደም ነው::

ኢየሱስ በመንፈስ መጥቶዋልን? አዎ መጥቶዋል ኢየሱስ አምላክ ነበር ነገር ግን የሐጢያተኞች አዳኝ ለመሆን በስጋ መንፈስ ሆኖ መጣ::

ብዙ ሰዎች ኢየሱስ በውሃ በደምና በመንፈስ እንደመጣ አያምኑም ኢየሱስ በእርግጥም የነገስታት ንጉስና የአማልክቶች አምላክ መሆኑን የሚያምኑ ጥቂቶች ብቻ ናቸው አብዛኛው ሕዝብ አሁንም ድረስ «ኢየሱስ በእርግጥ የእግዚአብሄር ልጅ ነው ወይስ የሰው ልጅ?» በማለት ግራ ተጋብተዋል የስነ መለኮት ምሁራንንና አገልጋዮችን ጨምሮ ብዙዎች ኢየሱስን የሚያምኑት ሰው እንጂ አምላክ አዳኝና ሉአላዊ ሕላዌ አድርገው አይደለም::

እግዚአብሄር ግን ኢየሱስ የነገስታት ንጉስ እውነተኛ አምላክና እውነተኛ አዳኝ መሆኑን የሚያምን ማንኛውም ሰው ከእርሱ እንደሚወለድ ተናግሮዋል እግዚአብሄርን የሚወዱ ሰዎች ኢየሱስንም ይወዳሉ በእውነት በእግዚአብሄር የሚያምኑ ሰዎችም በተመሳሳይ መንገድ በኢየሱስ ያምናሉ፡፡

ሰዎች ዳግም ካልተወለዱ በቀር አለምን ማሸነፍ አይችሉም ስለዚህ ሐዋርያው ዮሐንስ አለምን ማሸነፍ የሚችሉት እውነተኛ ክርስቲያኖች ብቻ እንደሆኑ ነግሮናል ታማኞች አለምን ማሸነፍ የሚችሉት በውሃው በደሙና በመንፈሱ እምነት ስላላቸው ነው አለምን የማሸነፊያው ሐይል ከሰው ፈቃድ ጥረት ወይም ስሜት ሊፈልቅ አይችልም፡፡

*«በሰዎችና በመላእክት አንደበት ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሸው ፅናጽል ሆኜአለሁ ትንቢትም ቢኖረኝ፣ ምስጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፣ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፣ ስጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም፡፡» (1ኛ ቆሮንቶስ 13:1-3)*

እዚህ ላይ የተጠቀሰው «ፍቅር» ኢየሱስ በውሃ በደምና በመንፈስ መጥቶዋል ማለት ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ፍቅር» የሚለው ቃል የሚጠቁመው «የእውነትን ፍቅር» ነው (2ኛ ተሰሎንቄ 2:10) በእርግጥም የእግዚአብሄር ፍቅር በአንድያ ልጁ በኩል ተገልጦዋል፡፡ (1ኛ ዮሐንስ 4:9)

# አለምን ሊያሸንፍ የሚችለው በው “ በደሙ የሚያምን ሰው ብቻ ነው




**1ኛ ዮሐንስ 5:5-6 እንዲህ ይላል:-** *«ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማን ነው? በውኃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በውኃውና በደሙ እንጂ በውኃው ብቻ አይደለም::»*

**አጋር ክርስቲያኖች ሰይጣንንና አለምን ያሸነፈው ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር በኢየሱስ ውሃ በደሙና በመንፈሱ ቃል የሚያምኑ ሰዎችም እንደዚሁ አለምን ማሸነፍ ይችላሉ ኢየሱስ አለምን ያሸነፈው እንዴት ነበር? በውሃው በደሙና በመንፈሱ ቤዛነት አማካይነት ነበር::**

**በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «ውሃ» የሚያመላክተው «የኢየሱስን ጥምቀት» ነው (1ኛ ጴጥሮስ 3:21) ኢየሱስ በስጋ ወደዚህ አለም መጣ የአለምን ሐጢያተኞች ለማዳን መጣ የሐጢያተኞችን ሁሉ ሐጢያቶች ለመውሰደም ተጠመቀ እነዚያን ሐጢያቶች ለማስተሰረይም በመስቀል ላይ ሞተ::**

**በመስቀል ላይ የፈሰሰው ደም እርሱ የሰው ስጋ ለብሶ ወደዚህ አለም የመምጣቱን እውነታ የሚያመላክት ነው እርሱ**

ሐጢያተኞችን ለማዳን በሐጢያተኛ ስጋ ምሳሌ መጣ በውሃም ተጠመቀ ስለዚህ ኢየሱስ በውሃና በደም ወደ እኛ መጣ በሌላ አነጋገር የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በጥምቀቱ ውሃና በሞቱ ደም ወሰደ፡፡

ሰይጣን አለምን የገዛው እንዴት ነበር? ሰይጣን የሰው ዘር የእግዚአብሄርን ቃል እንዲጠራጠር በማድረግ በልቦቻቸው ውስጥ የአለመታዘዝ ዘሮችን ተከለ ሰይጣን ሰዎችን የእግዚአብሄርን ቃል እንዳይታዘዙ በማሳት የእርሱ አገልጋዮች ሊያደርጋቸው ይሞክራል፡፡

ነገር ግን ኢየሱስ ወደዚህ አለም መጥቶ በጥምቀቱ ውሃና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ደመሰሰ እርሱ ሰይጣንን አሸነፈ የአለምንም ሐጢያቶች በሙሉ ደመሰሰ፡፡

ይህ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሐጢያተኞች አዳኝ ስለነበር ነው በውሃና በደም ስለመጣም አዳኛችን ሆነ፡፡

## ኢየሱስ በቤዛነት ጥምቀቱ የአለምን ኃጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል

*የኢየሱስ አለምን ማሸነፍ ምን ማለት ነው?*

*ይህ ማለት የአለምን ኃጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል ማለት ነው፡፡*

ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ ስለተጠመቀና እነርሱንም ለማስተሰረይ ስለሞተ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ሊያድነን ችሎዋል ኢየሱስ የሰዎች ሁሉ ወኪል በሆነው በአጥማቂው ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ስለተጠመቀ የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ ተላልፈዋል እርሱ በሞቱና በትንሳኤው የሰይጣንን ስልጣን አሸነፈ ኢየሱስ የሐጢያቶቻችንን ደመወዝ በሙሉ በሞቱ ከፍሎዋል፡፡

## ኢየሱስ ወደ ኃጢያተኞች የመጣው በጥምቀቱ ውኃና በመስቀሉ ደም ነው

*የሰይጣንን ኃይል ያሸነፈው እንዴት ነበር?*

*በጥምቀቱ፣ በደሙና በመንፈሱ ነው፡፡*

ሐዋርያው ዮሐንስ ቤዛነት በውሃ ብቻ የሚገኝ ሳይሆን በውሃውና በደሙ የሚገኝ እንደሆነ ተናግሮዋል ስለዚህ ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ስለወሰደና ሐጢያቶቻችንንም ለዘላለም ስላስወገደ ሐጢያተኞች በሙሉ በእርሱ በማመንና ለቃሎቹ ታማኝ በመሆን ከሐጢያት ይድናሉ፡፡

ኢየሱስ ወደዚህ አለም በመጣ ጊዜ ሐጢያቶቻችንን ከመውሰዱም በላይ በመስቀል ላይ እስከ ሞት ድረስ ደሙን በማፍሰስ ዋጋቸውንም ከፍሎዋል እርሱ በዮርዳኖስ ወንዝ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱ ወስዶ የእነዚያን ሐጢያቶች

ደመወዝ በመስቀል ላይ ከፍሎዋል እርሱ በሞቱ የሐጢያቶቻችንን ዋጋ ከፈለ *«የኃጢያት ፍርድ ሞት ነው» (ሮሜ 6:23)*የሚለው የእግዚአብሄር ጻድቅ ሕግም ተፈጸመ::

ኢየሱስ አለምን ማሸነፍ ሲል ምን ማለቱ ነበር? አለምን የሚያሸንፈው እምነት ኢየሱስ በውሃውና በደሙ በለገሰን የቤዛነት ወንጌል የሚያምን እምነት ነው እርሱ በስጋ መጥቶ በውሃ ጥምቀቱና በመስቀል ላይ ሞቱ ደህንነትን መሰከረ::

ኢየሱስ አለምን ማለትም ሰይጣንን አሸነፈ የጥንቷ ቤተክርስቲያን ደቀ መዛሙርት ለሮም ንጉሰ ነገስት ወይም ለማናቸውም የዚህ አለም ፈተናዎች ሳያጎበድዱ በሰማዕትነት ፊት እንኳን ጸንተው ቆመዋል::

ይህ ሁሉ ኢየሱስ በውሃና (እርሱ የአለምን ሐጢያቶች ለመውሰድ ተጠምቆዋል) በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ (በሞቱ የሐጢያቶቻችንን ሁሉ ደመወዝ ከፍሎዋል) ላይ ያላቸው አመኔታ ውጤት ነበር::

ኢየሱስ በመንፈስ መጣ (የሰው ስጋ ለብሶ መጣ) ቤዛነትን የምናገኝ ሁሉ አለምን ማሸነፍ እንችል ዘንድ የሐጢያተኞችን ሐጢያቶች በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ወሰደ::

## ይህም ውኃ ደግሞ ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ነው:: «1ኛ ጴጥሮስ 3:21»



በ1ኛ ጴጥሮስ 3:21 ላይ እንዲህ ተብሎዋል *«ይህም ውኃ ደግሞ ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም ለእግዚአብሔር የበጎ ህሊና ልመና ነው እንጂ። ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ነው»* ሐዋርያው ጴጥሮስ ኢየሱስ አዳኝ እንደነበርና በውሃ ጥምቀትና በደም እንደመጣ መስክሮዋል።

ከዚህ የተነሳ በውሃና በደም በመጣው ኢየሱስ ማመን አለብን የኢየሱስ ጥምቀት ውሃም እንደዚሁ የደህንነታችን ምሳሌ እንደሆነ ማወቅ ይገባናል ሐዋርያው ጴጥሮስ የጥምቀት «ውሃ» «ደም» እና «መንፈስ» በቤዛነት ውስጥ ወሳኝ ጉዳዮች እንደሆኑ ነግሮናል።

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት በመስቀሉ ደም አመኑ በደሙ ብቻ ማመን ማለት የእውነተኛ ውን እምነት ግማሽ ብቻ መያዝ ማለት ነው በግማሽ ወይም ባልተሟላ እውነት ላይ የተመሰረተ እምነት ከጊዜ ጋር ያረጃል ነገር ግን በውሃው በደሙና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ሰዎች እምነት ከጊዜ ጋር እየጠነከረ ይሄዳል።

በዚህ ዘመን የደሙ ብቻ የወንጌል ድምጽ በአለም ላይ ማደጉን ቀጥሎዋል ይህ ለምን ሆነ? ሰዎች የእውነትን ቃል የውሃውንና የደሙን ቤዛነት ስለማያውቁ ዳግም ሊወለዱ አልቻሉም።

በአንድ ወቅት የምዕራባውያን ቤተክርስቲያናት የባዕድ አምልኮ ሰለባዎች ሆነው ነበር ለጊዜው ያደጉ መሰሉ የሰይጣን አገልጋዮች ግን እምነታቸውን ወደ ባዕድ አምልኮ በመለወጥ ረገድ አጋዥ ሆኑ።

ባዕድ አምልኮ ማለት አንድ ሰው በወረቀት ላይ ወይም በእንጨት መስቀል ቢሰራ ዲያብሎስ ይሸሻል ሰው በኢየሱስ ላይ ያለውን የእርሱን/እርስዋን እምነት ቢመሰክሩ ሰይጣን ይባረራል

ብሎ ማመን ነው ሰይጣን በእነዚህና በሌሎች የባዕድ አምልኮ አመኔታዎች አማንይነት ሰዎች ማመን ያለባቸው በኢየሱስ ደም ብቻ እንደሆነ እንዲያምኑ አስቶዋቸዋል ሰይጣን ኢየሱስ ለሐጢያተኞች ያደረገው ብቸኛው ነገር በመስቀል ላይ ደሙን ማፍሰስ እንደነበር በመናገር ደሙን እንደሚፈራ ያስመስላል::

ነገር ግን ጴጥሮስና ሌሎች ደቀ መዛሙርት እውነተኛውን የኢየሱስ ጥምቀት ወንጌልና የመስቀሉን ደም መስክረዋል ነገር ግን በዚህ ዘመን ክርስቲያኖች የሚመሰክሩት ምንድነው? የሚመሰክሩት የኢየሱስን ደም ብቻ ነው::

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጻፉት ቃሎች ማመንና በመንፈስ በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ደህንነት እምነት ሊኖረን ይገባል የኢየሱስን ጥምቀት ችላ ብለን ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተልን የመሆኑን እውነታ ብቻ የምንመሰክር ከሆነ ደህንነታችን የተሟላ ሊሆን አይችልም::

## ለእግዚአብሔር የውኃ ደህንነት «የምስክርነት ቃል»




በ1ኛ ዮሐንስ 5:8 ላይ ጌታ እንዲህ ይላል *«የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃውና ደሙም ሦስት ናቸውና»* የመጀመሪያው

መንፈስ ነው ሁለተኛው የኢየሱስ ጥምቀት ውሃ ነው ሦስተኛ ው የመስቀሉ ደም ነው እነዚህ ሶስቱ ነገሮች በሙሉ አንድ ናቸው ኢየሱስ ከእነዚህ ሐጢያቶች ሊያድነን ወደዚህ አለም መጣ እርሱ ከሦስቱ ከጥምቀት ከደምና ከመንፈስ ሁሉ ጋር ብቻውን ይህንን አደረገ።

*«የሚመሰክሩት ሦስት ናቸው»* እግዚአብሄር እንዳዳነን የሚያረጋግጡ ሦስት ነገሮች አሉ እነዚህ ሦስት ማረጋገጫዎች የኢየሱስ ጥምቀት ውሃ ደሙና መንፈሱ ናቸው እነዚህ ሦስት ነገሮች ኢየሱስ በዚህ አለም ላይ ለእኛ ያደረጋቸው ናቸው።

ከእነዚህ ከሶስቱ ነገሮች አንዱ ቢገደፍ ደህንነት ሙሉ አይሆንም በምድር ላይ ሦስት ምስክሮች አሉ መንፈስ ውኃና ደም።

በስጋ ወደ እኛ የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መንፈስና ወልድ ነው እርሱ በሰው ስጋ ውስጥ መንፈስ ሆኖ ወደዚህ አለም ወረደ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ በውሃ ውስጥ ተጠመቀ ሐጢያቶችን ሁሉ በስጋው ወስዶ በመስቀል ላይ እስከ ሞት ድረስ በመድማት እኛን ሐጢያተኞችን አዳነን እርሱ ሙሉ በሙሉ ለሐጢያቶቻችን ሁሉ ዋጋውን ከፈለ ይህ በውሃ በደምና በመንፈስ የሆነ የተሟላ የቤዛነት ወንጌል ነው።

ከእነዚህ አንዱ እንኳን ተገድፎ ቢሆን ኖሮ እኛን ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ያዳነንን የእግዚአብሄር ደህንነት እምቢኝ ከማለት ጋር ተመሳሳይ ይሆን ነበር ዛሬ ከአብዛኞቹ ምዕመናኖች ጋር የምንስማማ ብንሆን ኖሮ «በምድር ላይ የሚመሰክሩ ሁለት አሉ እነርሱም ደሙና መንፈሱ ናቸው» እንል ነበር።።

ሐዋርያው ዮሐንስ ግን ሦስት የሚመሰክሩ ነገሮች እንዳሉ ተናግሮዋል እነርሱም የኢየሱስ ጥምቀት ውሃ በመስቀል ላይ የፈሰሰው ደምና መንፈስ ናቸው ሐዋርያው ዮሐንስ በምስክርነቱ በጣም ግልጽ ነው።

ሐጢያተኛውን የሚዋጀው እምነት የመንፈሱ የውሃውና የደሙ እምነት ነው አንድ ሰው አለምን እንዲያሸንፍ የሚያስችለው እምነት ምን አይነት እምነት ነው? ይህንን እምነት ልናገኝ የምንችለው ከየት ነው? እዚሁ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ በውሃ በደምና በመንፈስ በመጣው ኢየሱስ ማመን ነው ደህንነትንና የዘላለም ሕይወትን ለመቀበል በእነርሱ እምነት ይኑራችሁ።

*ያለ ኢየሱስ ጥምቀት*
*የእግዚአብሔር ደህንነት ፍጹም*
*ይሆን ነበርን?*

*አይሆንም።*

እኔ ዳግም ከመወለዴ ከረጅም ጊዜ በፊት እኔም ደግሞ በመስቀሉ ደምና መንፈስ ብቻ ያመንሁ ክርስቲያን ነበርሁ እርሱ እኔን ከሐጢያቶቼ ሁሉ ለማዳን መንፈስ ሆኖ እንደመጣና በመስቀል ላይም ለእኔ እንደሞተ አምኛለሁ ያመንኩት በእነዚህ ሁለት ነገሮች ብቻ ነበር እነዚህን ለሰዎች ሁሉ ለመስበክም ደፋር ነበርሁ።

ኢየሱስ እንዳደረገው ለጠፉት ነፍሳቶች ልሰራና ልሞት ሚሽነሪ እሆን ዘንድ የስነ መለኮት ትምህርት ለመማር እቅድ ነበረኝ ታላላቅ ነገሮችን ሁሉ አቅጄ ነበር።

ነገር ግን ያመንሁት በሁለት ነገሮች ብቻ ስለነበር በልቤ ውስጥ ሁልጊዜም ሐጢያት ነበረ ከዚህ የተነሳ አለምን ማሸነፍ አልቻልኩም ከሐጢያት ነጻ መሆን አልቻልኩም በደምና በመንፈስ ብቻ አምኜ በነበረ ጊዜ በልቤ ውስጥ ገናም ሐጢያት ነበረብኝ።

በኢየሱስ ያመንኩ ብሆንም ገናም በልቤ ውስጥ ሐጢያት የነበረበት ምክንያቱ ስለ ውሃው ማለትም የኢየሱስ ጥምቀት ስለማላውቅ ነበር በውሃ ጥምቀት በደምና በመንፈስ ላይ ባለኝ የተሟላ እምነት እስከምድን ድረስ ደህንነቴ የተሟላ አልነበረም፡፡

የኢየሱስን ጥምቀት ትርጉም ባለማወቁ የስጋ ሐጢያቶቼን ማሸነፍ አልቻልኩም አሁንም እንኳን ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ያምናሉ ነገር ግን አሁንም ድረስ የስጋ ሐጢያቶችን ይሰራሉ አሁንም ድረስ በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያቶች ስላሉ ለኢየሱስ የነበራቸውን የቀድሞውን ፍቅር ለማነቃቃት ይሞክራሉ፡፡

እነርሱ የመጀመሪያውን የግለት ስሜታቸውን ማነቃቃት አይችሉም ምክንያቱም በውሃው ሙሉ በሙሉ ከሐጢያቶቻቸው በጭራሽ አልነጹም ሐጢያቶቻቸው በሙሉ ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ወደ እርሱ እንደተላለፉ አይገነዘቡም ከውድቀት በኋላም እንደገና እምነታቸው እንዲያገግም ማድረግ አይችሉም፡፡

ይህንን ለሁላችሁም ግልጽ ማድረግ እወዳለሁ በኢየሱስ ስናምን በእምነት መኖርና አለምን ማሸነፍ እንችላለን ጎዶሎዎች ብንሆንም በዚህ አለም ላይ ምንም ያህል ብዙውን ጊዜ ሐጢያት ብንሰራም በጥምቀቱና ባፈሰሰው ደሙ ሙሉ በሙሉ ከሐጢያት ነጻ ያደረገንን ኢየሱስን አዳኛችን አድርገን እስካመንን ድረስ በድል አድራጊነት መቆም እንችላለን፡፡

ነገር ግን ከጥምቀቱ ውሃ ውጭ በኢየሱስ የምናምን ከሆንን ሙሉ በሙሉ ነጻ መውጣት አንችልም ሐዋርያው ዮሐንስ አለምን የሚያሸንፈው እምነት በጥምቀት ውሃ ደምና መንፈስ በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለ እምነት እንደሆነ ነግሮናል፡፡

እግዚአብሄር በጥምቀትና በደሙ የሚያምኑትን ሰዎች ለመዋጀት አንድያ ልጁን ላከ የእግዚአብሄር አንድያ ልጅ የሆነው ኢየሱስ በመንፈስ (በሰው ስጋ) ወደ እኛ መጣ ከዚያም

የሐጢያትን ደመወዝ ለመክፈል በመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰ በዚህም ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ከሐጢያት አርነት አወጣ፡፡

አለምን ወደ ማሸነፍ የሚመራን እምነት የሚመጣው ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ከሐጢያቶች ሁሉ ነጻ ባወጣን በውሃ በደምና በመንፈስ የመጣ የመሆኑን እውነት ከማመን ነው፡፡

የውሃ ጥምቀትና የመስቀሉ ላይ ደም ባይኖሩ ኖሮ እውነተኛ ደህንነትም ባልኖረ ነበር ከሶስቱ ቅምሮች አንዱ ወይም ሌላው ባይኖር እውነተኛ ደህንነት ሊኖረን ባልቻለም ነበር ያለ ውሃው ደሙና መንፈሱ እውነተኛ ደህንነት ላይ መድረስ አይቻልም ስለዚህ በውሃው በመንፈሱና በደሙ ማመን ይኖርብናል ይህንን እወቁ እውነተኛ እምነትም ይኖራችኋል፡፡

## የውሃው የደሙና የመንፈሱ ምስክርነት የሌለው ደህንነት እውነተኛ ደህንነት እንዳልሆነ እነግራችኋለሁ




አንድ ሰው የላይኛውን ጥያቄ እንዲህ ብሎ ያስበው ይሆናል «ኢየሱስ አዳኜ ነው በመስቀሉ ላይ ደም አምናለሁ ሰማዕት ሆኜ መሞትም እፈልጋለሁ በልቤ ውስጥ ሐጢያት ቢኖርም በኢየሱስ አምናለሁ በትጋት ንስሐ ገብቻለሁ በየቀኑም

ጥሩ ቀናና ለጋስ በሆነ መንገድ ለመስራት ጥረት አድርጌአለሁ ሕይወቴንና ያለኝን አለማዊ ሐብት በሙሉ ለአንተ ሰጥቻለሁ ላለማግባትም እንኳን መርጫለሁ እግዚአብሄር እንዴት ሊያውቀኝ አይችልም? ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞቶልኛል ቅዱሱ አምላካችን ሰው ሆኖ በመውረድ በመስቀል ላይ ለእኛ ሞቷል በአንተ አምኛለሁ ለአንተ መስዋዕት ሆኛለሁ ለአንተም በታማኝነት ስራዬን ሰርቻለሁ የማልረባና አሁንም ድረስ በልቤ ውስጥ አንዳንድ ሐጢያት ቢኖርም ኢየሱስ ለዚያ ሲል ሲዖል ይሰደኛልን? አይሰደኝም፡፡»

በዚህ መንገድ የሚያስቡ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ እንደተጠመቀ አያምኑም በኢየሱስ የሚያምኑ ነገር ግን ገናም ሐጢያት ያለባቸው እነዚህ የስም ክርስቲያኖች ሲሞቱ የት ይሄዳሉ? ሲዖል ይወርዳሉ እነርሱ ተራ ሐጢያተኞች ናቸው!

እንዳሻቸው የሚያስቡና እግዚአብሄርም እንደ እነርሱ ማሰብ እንዳለበት የሚገምቱ ሰዎች ሲዖል ይወርዳሉ ከዚህም በላይ አንዳንዶች ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ሐጢያቶችን በሙሉ ስለወሰደ በአለም ላይ ሐጢያት የለም ይላሉ ይህ ሰዎችን ሙሉ ወደሆነ ቤዛነት የሚመራ እምነት አይደለም፡፡

ኢየሱስ በጥምቀቱ ሐጢያቶቻችንን እንደወሰደ እንደተኮነነና ስለ እኛም በመስቀል ላይ ሞቶ ከሙታን በሦስተኛው ቀን ዳግመኛ እንደተነሳ ማመን ይገባናል፡፡

ይህ እምነት ሳይኖር የተሟላ ቤዛነት አይገኝም ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠመቀ በመስቀል ላይ ሞተ ተነሳም ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃ በደምና በመንፈስ ወደ እኛ መጣ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ፡፡

እርሱ በምድር ላይ ላደረገው ደህንነቱ የሚመሰክሩ ሦስት

ዋና ምስክሮች አሉ እነርሱም መንፈስ ውሃና ደም ናቸው፡፡

በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ አምላክ እንደሆነና የሰው ስጋ ለብሶ እንደወረደ ይመስክራል፡፡

ሁለተኛው ምስክር «የውሃው» ምስክር ነው ውሃው ሐጢያቶቻችን ወደ ኢየሱስ የተላለፉበት በዮርዳኖስ በአጥማቂው ዮሐንስ የሆነው የኢየሱስ ጥምቀት ነው እርሱ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቻችን በሙሉ ወደ እርሱ ተላልፈዋል፡፡ (ማቴዎስ 3:15)

ሦስተኛው ምስክር ኢየሱስ የሐጢያቶችን ፍርድ በሐላፊነት የሚቀበልበትን «ደም» ያመላክታል ኢየሱስ ሞተ ስለ እኛም የአባቱን ፍርድ ተቀበለ አዲስ ሕይወትን ሊሰጠንም በሦስተኛው ቀን ተነሳ፡፡

እግዚአብሄር አብ ለቤዛነታችን ምስክር ይሆን ዘንድ መንፈስ ቅዱስን በልጁ ጥምቀትና ደም በሚያምኑ ሰዎች ልቦች ውስጥ ልኮዋል፡፡

ዳግም የተወለዱት ሰዎች አለምን የሚያሸንፉበት ቃል አላቸው የዳኑት ሰይጣንን የሐሰተኛ ነቢያቶችን ውሸቶችና መሰናክሎች ወይም ያለ ማቋረጥ የሚያጠቁዋቸውን የአለም ግፊቶች ያሸንፋሉ እኛ ይህ ሐይል ሊኖረን የቻለበት ምክንያት በልባችን ውስጥ ሦስት ምስክሮች ስላሉን ነው እነርሱም የኢየሱስ ውሃ ደሙና መንፈሱ ናቸው፡፡

*አለምንና ሰይጣንን*
*የምናሸንፈው እንዴት ነው?*

*በሦስቱ ምስክሮች*
*በማመን ነው፡፡*

በመንፈስ በውሃና በደም ስለምናምን ሰይጣንንና አለምን ማሸነፍ እንችላለን በኢየሱስ ጥምቀትና ደም የሚያምኑ ሰዎች የሐሰተኛ ነቢያቶችን ማታለያዎች በሙሉ ማሸነፍ ይችላሉ በምናሸንፍበት በዚህ ሐይል ላይ ያለን እምነታችን ያረፈው በውሃው በደሙና በመንፈሱ ላይ ነው በዚህ ታምናላችሁን?

በኢየሱስ ጥምቀት በደሙና ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅና አዳኛችን በመሆኑ አመኔታ በኩል በቤዛነት ላይ እምነት ከሌላችሁ ዳግም ልትወለዱም ሆነ አለምን ልታሸንፉ አትችሉም በልባችሁ ውስጥ ይህ እምነት አለ?

በልባችሁ ውስጥ መንፈሱና ውሃው አሉን? ሐጢያቶቻችሁ በሙሉ ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ ታምናላችሁን? በልባችሁ ውስጥ በመስቀል ላይ የፈሰሰው ደም አለ?

በልባችሁ ውስጥ የውሃውና የኢየሱስ ደም ካሉ አለምን ታሸንፋላችሁ ኢየሱስ ለእናንተ በመስቀል ላይ እንደሞተና ለእናንተም ፍርድን እንደተቀበለ ብታምኑ ታሸንፋላችሁ::

ሐዋርያው ዮሐንስ አለምን ያሸነፈው እነዚህ ሁሉ ሦስቱ አስፈላጊ ነገሮች በልቡ ውስጥ ስላሉ ነበር እርሱ በስራቸው መሰናክሎችንና ዛቻዎችን ለታገሱት ወንድሞቹ ሁሉም ስለ ቤዛነት ተናግሮዋል እርሱ እንዲህ በማለት መሰከረ «እናንተም ደግሞ አለምን ማሸነፍ የምትችሉት እንደዚህ ነው ኢየሱስ በመንፈስ በውሃና በደም መጣ እርሱ አለምን እንዳሸነፈ ታማኞችም ደግሞ አለምን ማሸነፍ ይችላሉ ታማኞች አለምን የሚያሸንፉበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው::»

በ1ኛ ዮሐንስ 5:8 ላይ እንዲህ ይላል *«የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃውና ደሙም ሦስት ናቸውና ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ»* ብዙዎች አሁንም ድረስ የኢየሱስን የጥምቀት ውሃ ገድፈው ስለ ደምና መንፈስ ብቻ ይናገራሉ «ውሃውን» የሚያስወግዱት ከሆነ አሁንም ድረስ በሰይጣን ተታልለዋል

ራሳቸውን ካታለሉባቸው ማታለያዎች ጀርባ መውጣትና ንስሐ መግባት አለባቸው በኢየሱስ ጥምቀት «ውሃ» ዳግም በመወለድ ማመን ይገባቸዋል::

ማንም በኢየሱስ ውሃና ደም ሳያምን አለምን ማሸነፍ አይችልም ደግሜ አላችኋለሁ ማንም አይችልም! የኢየሱስን ውሃና ደም እንደ ብርቱ መሳርያዎቻችን አድርገን በመጠቀም መዋጋት ይኖርብናል የእርሱ ቃል የመንፈስ ሰይፍ ብርሃንም ነው::

አሁንም ድረስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ባነጻው የኢየሱስ ጥምቀት የማያምኑ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ አሁንም ድረስ በሁለት ነገሮች ብቻ የሚያምኑ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ ስለዚህ ኢየሱስ *«ተነስተው እንዲያበሩ»* ሲነግራቸው ፈጽሞ ማብራት አይችሉም አሁንም ድረስ በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት አለባቸው በኢየሱስ ቢያምኑም አሁንም መጨረሻቸው ሲዖል ነው::

## ሰዎች መስማት ማመንና መዳን እንዲችሉ የኢየሱስ ጥምቀትና ደም ወንጌል በግልጽ መመስከር አለበት



ወንጌልን ስንመሰክር ግልጽ መሆን አለበት ኢየሱስ በመንፈስ በጥምቀትና (ሐጢያቶቻችንን በሙሉ የወሰደበት) በደም (ለሐጢያቶቻችን ሁሉ ዋጋ በከፈለበት) መጣ በእነዚህ በሦስቱ ሁሉ ማመን አለብን፡፡

ካላመንን እየሰበክን ያለነው ወንጌልን ሳይሆን ቀለል ያለ ሐይማኖትን ነው አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የዘመኑን ክርስትና እንደ ሐይማኖት ብቻ አድርገው ይቆጥሩታል ነገር ግን ክርስትና እንደ ሐይማኖት ሊመደብ አይችልም ክርስትና በእውነት ላይ የተመሰረተ የቤዛነት እምነት ወደ እግዚአብሄር ቀና ብሎ የመመልከት እምነት ነው ሐይማኖት ሊሆን አይችልም፡፡

ሐይማኖት በሰዎች የተፈጠረ አንዳች ነገር ሲሆን እምነት ግን እግዚአብሄር የሰጠንን ደህንነት ቀና ብሎ የሚመለከት ነው ይህንን እውነት ችላ ካላችሁ ክርስትናን እንደ ሌላው ሐይማኖት በመቁጠር ሞራሎችን ስነ ምግባሮችንና ትሰብካላችሁ፡፡

ኢየሱስ በዚህ አለም ላይ ሐይማኖትን ሊመሰርት አልመጣም እርሱ በጭራሽ ክርስትና የሚባል ሐይማኖት አልመሰረተም ክርስትና ሐይማኖት ነው ብላችሁ የምታምኑት ለምንድነው? ሁሉም አንድ አይነት ከሆነ ለምን በቡድሃ ሐይማኖት አታምኑም? ይህንን በማለቴ የተሳሳትኩ ይመስላችኋል?

አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስን ሐይማኖታዊ የሕይወት መንገድ አድርገው ያምኑታል በመጨረሻም «ልዩነቱ ምንድነው? ሰማይ ኒርቫና ገነት... ስሞቻቸው ተለያዩ እንጂ ሁሉም ተመሳሳይ ነገር ናቸው የሆኖ ሆኖ የሁላችንም መጨረሻ አንድ ቦታ ነው» ይላሉ፡፡

አጋር ክርስቲያኖች በእውነት ላይ ጸንተን መቆም አለብን *«ተነስተን ማብራት»* አለብን ያለ ምንም ማመንታት እውነቱን መናገር መቻል አለብን፡፡

አንድ ሰው «ያ ወደ ሰማይ የሚያደርስ ብቸኛው መንገድ ሊሆን አይችልም» ሲል እናንተ ግልጽ በሆነ መንገድ «አዎ! ብቸኛው መንገድ ያ ነው ሰማይ መሄድ የምትችለው በውሃ በደምና በመንፈስ በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ስታምን ብቻ ነው» ልትሉት ይገባችኋል ሌሎች ነፍሳቶች የቤዛነትን ቃል ሰምተው ዳግም እንዲወለዱና ሰማይ እንዲገቡ ብሩህ ሆናችሁ ማብራት ይገባችኋል፡፡

## እውነተኛ እምነት ይኑራችሁ
## የኢየሱስን ጥምቀትና የደሙን ቤዛነት የማያውቁ ምላሽ የማይሰጡ ኢየሱስ ወዳጆች ይጠፋሉ




ኢየሱስን በዘፈቀደ ስለማመን መናገር ለኢየሱስ ምላሽ የማይሰጥ ፍቅር መያዝና ክርስቲያን የሆነ ሐይማኖተኛ ለመሆን አቋራጭ የሆነውን መንገድ መቀበል ነው፡፡

ፓስፊክን የሚያቋርጥ አንድ መርከብ ሰምጦ ጥቂት የተረፉ ሰዎች በጎማ መንሳፈፊያ ላይ ሲንሳፈፉ ቆዩ የአደጋ ጥሪ ምልክትም ላኩ ነገር ግን በማዕበል የሚናጠው ባህር ሌሎች መርከቦች እነርሱን ለማዳን እንዳይመጡ ከለከላቸው ከዚያም አንዲት ሔሊኮፕተር መጣችና ገመድ ወረወረች ከሰዎቹ አንዱ

ገመዱን በሰውነቱ ላይ በመጠምጠም ፋንታ በእጆቹ ይዞት ቢቀር ከኢየሱስ ጋር ምላሽ በማይሰጥ ፍቅር የተያዘ ከመሆኑ ጋር የሚመሳሰል ይሆናል እንደወደደ በእግዚአብሄር ያምናል ገና ደህና አይደለም ነገር ግን «አምናለሁ አድነኝ አምናለሁ ስለዚህ እድናለሁ ብዬ እገምታለሁ» ይላል::

የኢየሱስን ጥምቀትና የደሙን እውነት የማያስተውል ሰው ገመዱን ብቻ በመያዝ እንደሚድን ያምናል::

ወደ ላይ ሲሳብ እጆቹ በገመዱ ላይ ያላቸውን ጥብቀት ያጣሉ የሚቆየው በራሱ ጉልበት ብቻ ይሆናል ገመዱን እስከ መጨረሻው ድረስ በእጆቹ ይዞ ለመቆየት ወደቡ በጣም ሩቅ ነው ጉልበቱ ሲሟጠጥ ያሟልጨውና ውቅያኖሱ ውስጥ ይወድቃል::

ከኢየሱስ ጋር ምላሽ በማይሰጥ ፍቅር መቆራኘት ማለት ማለት ልክ እንደዚህ ነው ብዙዎች በእግዚአብሄርና በኢየሱስ እናምናለን በመንፈስ በመጣው ኢየሱስ እናምናለን ይሉ ይሆናል ይህ ግን የስሌቱ ሁሉ አንዱ ክፍል ነው እነርሱ ፍጹም በሆነው ወንጌል በተጨባጭ አያምኑም በእርሱም አይኖሩም ስለዚህ በእርሱ «እንደሚያምኑ» ደጋግመው ለመናገር ራሳቸውን ያስገድዳሉ::

ማመንና ለማመን መሞከር ተመሳሳይ ነገር አይደለም እነርሱ ኢየሱስን እስከ መጨረሻው ድረስ እንደሚከተሉት ይናገራሉ ነገር ግን በልቦቻቸው ውስጥ በቀሩት ሐጢያቶች ምክንያት በመጨረሻው ቀን ይጣላሉ ኢየሱስ በጥምቀቱ በደሙና በመንፈስ እንደመጣ ሳያውቁ ይወዱታል ኢየሱስን የሚወዱት ስለ ደሙ ብቻ ከሆነ ሲዖል ይወርዳሉ::

ነፍሳችሁን እውነተኛ ወንጌል በሆነው በውሃውና በደሙ ወንጌል ገመድ እሰሩዋት ኢየሱስ የመዳንን ገመድ ወደ ታች ሲወረውር ራሳቸውን በውሃ በደምና በመንፈስ የሚያስሩ ሰዎች ይድናሉ::

በሔሊኮፕተሩ ላይ ያለው ነፍስ አዳኝ ሰው በድምጽ ማጉያ «አባካችሁ በጥንቃቄ አድምጡኝ ገመዱን ወደ ታች ስወረውር ከክንዶቻችሁ በታች በደረቶቻችሁ ዙሪያ እሰሩት ባላችሁበትም ቆዩ በደረታችሁ ዙሪያ እሰሩትና ዘና በሉ ያን ጊዜ ትድናላችሁ» በማለት ጮኸ::

የመጀመሪያው ሰው መመሪያዎቹን ተከትሎ ራሱን በገመዱ አሰረና ዳነ ሌላው ሰው ግን «አትጨነቅ እኔ በጣም ጠንካራ ነኝ በአንድ የጤና ክለብ ስሰራ ነበር ተመልከት! ጡንቻዎቼን ማየት ትችላለህን? ብዙ ማይሎችን ተንጠልጥዬ መጓዝ እችላለሁ» አለ ከዚያም ገመዱ ወደ ላይ ሲሳብ ገመዶቹን በእጆቹ ይዞ ተንጠለጠለ::

በመጀመሪያ ሁለቱም ሰዎች ወደ ላይ ተጎትተው ነበር ልዩነቱ ግን መመሪያዎቹን አድምጦ በደረቱ ዙሪያ ገመዱን ያሰረው ሰው ያለ ምንም እንቅፋት ወደ ላይ መጎተቱ ነበር ወደ ላይ ሲጎተት ሕሊናውን ስቶ እንኳን ቢሆን የሆኖ ሆኖ ወደ ላይ ተጎትቷል::

በጉልበቱ የተኩራራው ሰው ጉልበቱ ስለደከመ ውሉ አድሮ የጨበጠውን ለቀቀው ለመስማት አሻፈረኝ ስላለና መመሪያዎቹን ቸል ስላለ ሞተ::

አንድ ሰው ሙሉ ቤዛነት ያገኝ ዘንድ ነፍሳትን ሁሉ ከሐጢያት ባዳነው በእርሱ የጥምቀት ውሃና ደም ቤዛነት ማመን አለበት ደህንነት የሚሰጠው ከሙሉ ልባቸው በቃሉ ለሚያምኑ ሰዎች ነው «እኔ ከአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበልኩት ጥምቀቴና በመስቀል ላይ እስከ ሞት ድረስ ባፈሰስሁት ደሜ ሙሉ በሙሉ አድኛችኋለሁ::»

በደሙ ብቻ የሚያምኑ ሰዎች «አትስጋ አምናለሁ የኢየሱስን ደም እስከ ሕይወቴ ፍጻሜ ድረስ አመሰግናለሁ ኢየሱስን እስከ መጨረሻው ድረስ እከተለዋለሁ አለምንና የቀሪ

ሕይወቴን ሐጢያቶች በሙሉ ለማሸነፍ በደሙ ላይ ያለኝ እምነቴ ብቻውን በቂዬ ነው» ይላሉ::

ነገር ግን ይህ በቂ አይደለም እግዚአብሄር ሕዝቡ እንዲሆኑ የፈቀደላቸው ሰዎች በሦስቱም ምስክሮች በሙሉ ማለትም ኢየሱስ በመንፈስ እንደመጣ እንደተጠመቀ (ኢየሱስ በዮርዳኖስ ጥምቀቱ ሐጢያቶችን ሁሉ ወስዶዋል) የሐጢያቶችን ደመወዝ ለመክፈልም በመስቀል ላይ እንደሞተና በሦስተኛውም ቀን ከሙታን እንደተነሳ የሚያምኑ ሰዎችን ነው::

መንፈስ የሚመጣው በሦስቱም በሙሉ በሚያምኑት ሰዎች ላይ ብቻ ነው ለእነርሱም ይመሰክርላቸዋል «አዎ እኔ አዳኛችሁ ነኝ በውሃና በደም አድኛችኋለሁ እኔ አምላካችሁ ነኝ::»

እግዚአብሄር በሦስቱም በሙሉ ለማያምኑ ሰዎች ደህንነትን አይሰጣቸውም አንዱ ቢጎድል እንኳን እግዚአብሄር «አልዳናችሁም» ይላቸዋል የእርሱ ደቀ መዛሙርት በሙሉ በሦስቱም በሙሉ አምነዋል ኢየሱስ የእርሱ ጥምቀት የደህንነት ምሳሌ ደሙም ፍርድ እንደሆነ ተናግሮዋል::

## ሐዋርያቱ ጳውሎስና ጴጥሮስም ስለ ኢየሱስ ጥምቀትና ደም መስክረዋል



ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ጥምቀት ተናግሮዋል? ስለ ኢየሱስ ጥምቀት ምን ያህል ጊዜ እንደተናገረ እንመልከት በሮሜ 6:3 ላይ እንዲህ ብሎዋል *«ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?»* በ6:5 ላይም እንዲህ ብሎዋል *«ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን::»*

በገላትያ 3:27 ላይም እንዲህ ብሎዋል *«ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና»* የኢየሱስ ሐዋርያት በሙሉ ስለ «ውሃው» ማለትም የኢየሱስ ጥምቀት መስክረዋል *«ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል::» (1ኛ ጴጥሮስ 3:21)*

## የጌታ የቤዛነት ደህንነት የመጣው በኢየሱስ ውኃ እና ደም ነው




ኢየሱስ ለሰው የለገሰው ቤዛነት የኢየሱስ ጥምቀት ውሃና በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደሙ ቤዛነት ነው እኛም በዚያ ቤዛነት

ተነስተን ማብራት እንችላለን እንዴት? እነዚህን ሦስት ነገሮች በመመስከር፡፡

*«ብርሃንሽ መጥቶአልና የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሽና አብሪ፡፡» (ኢሳይያስ 60፡1)* እግዚአብሄር ብርሃኑን በእኛ ላይ አብርቶ እንድናበራ ደግሞ ይነግረናል ያንን ትዕዛዝ መታዘዝ ይገባናል፡፡

እኛ ባለ ሐይላችን ወንጌልን ስንሰብክ ነበር ነገር ግን አሁንም ድረስ በጣም ብዙ ሰዎች አያደምጡም በኢየሱስ እመኑ ትድኑማላችሁ ጻድቃን ትሆናላችሁ ገናም ሐጢያት በልባችሁ ውስጥ ካለ ገና ጻድቃን አልሆናችሁም የአለምን ሐጢያትም ገና አላሸነፋችሁም፡፡

በኢየሱስ ውሃ (የኢየሱስ ጥምቀት) የማታምኑ ከሆነ በልባችሁ ውስጥ ያለውን ሐጢያት በጭራሽ ማስወገድ አትችሉም በኢየሱስ ደም የማታምኑ ከሆነ ፍርድን በጭራሽ ማምለጥ አትችሉም በመንፈስ በመጣው በኢየሱስ የማታምኑ ከሆነ በጭራሽ ልትድኑ አትችሉም በእነዚያ ሦስት ምስክሮች እስካላመናችሁ ድረስ በጭራሽ ሙሉ በሙሉ ጻድቃን ልትሆኑ አትችሉም፡፡

ያልተሟላ ጽድቅ የሚመራው ወደ «ጽድቅ ተብዬ» ብቻ ነው እርሱ/እርስዋ ሐጢያት እንዳለባቸው እየተናገሩ ራሱን/ራስዋን ጻድቃን አድርገው የሚቆጥሩ ማናቸውም ሰዎች ገና በኢየሱስ አይደሉም በዚህ ዘመን አንዳንድ ሰዎች «ጽድቅ ተብሎ በሚጠራ» ነገር አማካይነት ቤዛነት ላይ ለመንጠልጠል ይሞክራሉ እነርሱ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ እጅግ በርካታ የማይረቡ ጽሁፎችን ጽፈዋል፡፡

እግዚአብሄር አሁንም ድረስ በልቡ ውስጥ ሐጢያት ያለበትን ሰው ሐጢያት አልባ ብሎ ይጠራዋልን? ያንን አያደርግም እርሱ ያየውን ያንን ይናገራል እርሱ ሁሉን ቻይ

ነው ነገር ግን ፈጽሞ ሊዋሽ አይችልም ሰዎች የጽድቅን እውነተኛ ትርጉም አይረዱትም አንድን ነገር «ንጹህ» ነው ብለን የምንጠራው ንጹህ ሲሆን ብቻ ነው ሐጢያት እያለ «ጻድቅ» ብለን አንጠራም::

በልባችሁ ውስጥ ሐጢያት ቢኖርም እንኳን በኢየሱስ ጻድቃን ተብላችሁ እንደተጠራችሁ ታስቡ ይሆናል ያ ግን ስህተት ነው::

ኢየሱስ ጻድቃን ብሎ የሚጠራን እርሱን በመንፈስ በውሃ (በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶዋል) እና በደም (እርሱ በስጋ መጥቶ ስለ እኛ ሞተ) የመጣ አድርገን ስናምነው ብቻ ነው::

አጋር ክርስቲያኖች «ጽድቅ ተብሎ የሚጠራው» ነገር ከውሃውና ከደሙ ወንጌል ጋር ምንም ግንኙነት የለውም «ጽድቅ ተብሎ የሚጠራ» ወይም «ጻድቅ ተብሎ መጠራት» ሰዎች የፈጠሩት ዶግማ ነው በልባችሁ ውስጥ ሐጢያት እያለባችሁ እግዚአብሃሃር ጻድቃን ብሎ ይጠራችኋልን? እግዚአብሄር ያ ሰው ምንም ያህል በታላቅ ግለት በኢየሱስ ቢያምንም በልቡ ውስጥ ሐጢያት ካለበት ጻድቅ ብሎ አይጠራውም ኢየሱስ በፍጹም አይዋሽም::

ሆኖም እርሱ በልቡ ውስጥ ሐጢያት ያለበትን ሰው ጻድቅ ብሎ እንደሚጠራው አሁንም ታስባላችሁን? ያ ሰዎች የሚያስቡት እንጂ እግዚአብሄር የሚያስበው አይደለም እግዚአብሄር ውሸቶችን ይጠላል «በመንፈስ» እና «በደም» ብቻ እያመናችሁ እግዚአብሄር ጻድቃን ብሎ ይጠራችኋልን? በፍጹም!

እግዚአብሄር ጻድቃን ብሎ የሚጠራቸው አንድ አይነት ሰዎች ብቻ አሉ እነርሱም በልቦቻቸው ውስጥ ምንም ሐጢያቶች የሌሉባቸውን ሰዎች ነው እርሱ የሚያውቃቸው በሦስቱም ነገሮች በሙሉ ማለትም አምላክ የሆነው ኢየሱስ

በስጋ ወደ አለም ወርዶ በዮርዳኖስ ወንዝ እንደተመቀና ሐጢያቶቻችንንም በሙሉ ለመደምሰስ በመስቀል ላይ ደሙን እንዳፈሰሰ የሚያምኑ ሰዎችን ብቻ ነው፡፡

እግዚአብሄር ጻድቃን እንደሆኑ የሚያውቃቸው በቤዛነት የምስራች የሚያምኑትን ብቻ ነው ትክክለኛ አመኔታ ያላቸው እነርሱ ናቸው እነርሱ እርሱ ለእኛ ባደረጋቸው ነገሮች ሁሉ ሙሉ በሙሉ ያምናሉ ኢየሱስ እንደመጣ ሐጢያቶቻችንን ለመውሰድ እንደተጠመቀ በመስቀል ላይ በመሞትም ስለ እኛ ፍርድን እንደተቀበለና ከሙታንም እንደተነሳ ያምናሉ፡፡

እነዚህ ሁሉ ነገሮች የተደረጉት ከእግዚአብሄር ፍቅር የተነሳ ነው ኢየሱስ ከሰማይ ወርዶ እንዲህ አለ *«እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ» (ማቴዎስ 11:28)* ይህንን ያደረገው ሐጢያቶቻችንን በመውሰድ ነው፡፡ ይህንን ያደረገው ሐጢያቶቻችንን በመውሰድ ነው፡፡

እግዚአብሄር በኢየሱስ ደም ብቻ የሚያምኑትን አያውቃቸውም በኢየሱስ ደም ብቻ የሚያምኑ ሰዎች አሁንም ድረስ በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት አለባቸው ኢየሱስ የተዋጁ አድርጎ የሚያውቃቸው እነማንን ነው?

በኢየሱስ ጥምቀት በደሙና እርሱ አምላክ በመሆኑ እውነታ ማመን ለደህንነት አስፈላጊዎች ናቸው «ወደዚህ ምድር በወርድሁና በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቅሁ ጊዜ ሐጢያቶቻችሁን ሁሉ ወሰድሁ የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እኔ እንደተላለፉ እመሰክራለሁ በመስቀል ላይም የሐጢያቶችን ዋጋ ከፍያለሁ እንዲህም አድኛችኋለሁ፡፡»

ኢየሱስ በሶስቱም በሙሉ ለሚያምኑ ሰዎች እንዲህ ይላል «አዎ ድናችኋል እናንተ ጻድቃንና የእግዚአብሄር ልጆች ናችሁ» እናንተም ደግሞ በኢየሱስ ጥምቀት በደሙና በመንፈሱ

በአጠቃላይ ብታምኑ መዳን ትችላላችሁ በደሙና በመንፈሱ ብቻ የሚያምኑ ሰዎች አሁንም ድረስ በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት አለ::

በእግዚአብሄር መንግስት ውስጥ አንድ እውነት ብቻ አለ ፍትህ ታማኝነት ፍቅርና ደግነትም አለ አንድም የውሸት ነጥብ የለም ውሸቶችና እብለቶች በሰማይ አይገኙም::

*«አመጻን የሚያደርግ» ማነው?*

*በኢየሱስ ጥምቀት የማያምን ሰው ነው::*

*«በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢትን አልተናገርንምን በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን በስምህስ ብዙ ተዓምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል::» (ማቴዎስ 7:22)*

እግዚአብሄር የእነዚያን ሰዎች ስራዎች ወደ እርሱ መንግስት ለመግባት የበቁ አድርጎ በፍጹም አያውቃቸውም *«የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃችሁም እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ::» (ማቴዎስ 7:23)*

«ሁለት ቤቶችን አቀረብኩልህ ሕይወቴንም እንኳን ለአንተ ሰጠሁ እኔ እስከ መጨረሻዋ እስትንፋሴ ድረስ ፈጽሞ አልካድኩህም አታየኝምን? »

«ስለዚህ በልብህ ውስጥ ሐጢያት አለን?»

«አዎ ጌታ ሆይ ጥቂት ሰርቻለሁ::»

«እንግዲያውስ ከእኔ ራቅ! ማንም ሐጢያተኛ እዚህ እንዲገባ አይፈቀድለትም::»

«ነገር ግን ጌታ ሆይ በአንተ ላለኝ እምነት ሰማዕት ሆኜ ሞቻለሁ::»

«ሰማዕት ሆኜ ሞቻለሁ ስትል ምን ማለትህ ነው? የሞትከው በግትርነትህ ብቻ ነው ጥምቀቴንና ደሜን ተቀብለሃልን? አንተ ልጄ እንደሆንህ ለልብህ መስክሬአለሁን? አንተ በእኔ ጥምቀት ስላላመንህ ልጄ እንደሆንህ በፍጹም አልመሰከርኩም ነገር ግን እምነትህ ላይ ተንጠልጥለህ ለዚያ አመኔታህ ሞትክ መቼ ነው ለአንተ መስክሬ የማውቀው? ይህንን በራስህ ላይ ያመጣኸው አንተው ነህ የራስህን ቤዛነት ለማግኘት ወደድህ ብቻህንም ሞከርህ ገባህ? አሁን መንገድህን ቀጥል::»

ኢየሱስ ተነስተን እንድናበራ ነግሮናል የዳኑ ሰዎች በብዙ የስም ክርስቲያኖችና በብዙ ሐሰተኛ ነቢያቶች ፊት ይሸማቀቁና ብሩህ ሆነው ማብራት ይሳናቸው ይሆናል! ነገር ግን ትንሽ ነበልባል ትልቅ እሳት ማስነሳት ትችላለች አንድ ሰው በድፍረት ተነስቶ እውነትን ቢመሰክር መላው አለም ይበራል::

በኢሳያስ 60:1-2 ላይ እንዲህ ይላል- *«ብርሃንሽ መጥቶኣልና የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ አብሪ እነሆም ጨለማ ምድርን ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብን ያሸንፋል ነገር ግን በአንቺ ላይ እግዚአብሔር ይወጣል ክብሩም በአንቺ ላይ ይወጣል::»*

የውሸት ጨለማ ማለትም የሐሰት ወንጌል መላውን አለም በመሸፈኑ እግዚአብሄር ተነስተን እንድናበራ አዞናል ኢየሱስን ሊወዱት የሚችሉት በእርሱ የሚያምኑት ብቻ ናቸው ያልዳኑ ሰዎች ፈጽሞ ኢየሱስን መውደድ አይችሉም እንዴት ይችላሉ? እነርሱ ስለ ፍቅር ብቻ ያወራሉ ነገር ግን ምሉዕ በሆነው እውነት እስካላመኑ ድረስ እርሱን ፈጽሞ ከልባቸው ሊወዱት አይችሉም::

# ለኃጢያተኞች መዳን ምስክሮች የሚሆኑ ሦስት ነገሮች አሉ




*«የሚመሰክሩት መንፈሱ ውኃውና ደሙም ሦስት ናቸውና ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ»* ኢየሱስ ወደ ምድር መጣ በውሃና በደምም ስራውን ሰራ ይህንን አድርጎም አዳነን፡፡

*«የሰውን ምስክር ብንቀበል የእግዚአብሔር ምስክር ከእርሱ ይልቅ ይበልጣል ስለ ልጁ የመሰከረው የእግዚአብሔር ምስክር ይህ ነውና በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው በእግዚአብሔር የማያምን ስለ ልጁ የመሰከረውን ምስክር ስላላመነ ሐሰተኛ አድርጎታል እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠን ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው ልጁ ያለው ሕይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም፡፡» (1ኛ ዮሐንስ 5:9-12)*

ዳግም የተወለዱ የሰውን ምስክርነት ይቀበላሉ እኛ ጻድቃን መሆናችን ይታወቃል ቤዛነትን ያገኙ ዳግም የተወለዱ ሰዎች ስለ ቤዛነት እውነት ስለሚናገሩ ሰዎች ሊቃወሙት አይችሉም ይቀበሉታል እነርሱ እኛ በትክክል እንደምናምንና በእምነታችንም ትክክል እንደሆንን ይናገራሉ እንዴት ዳግም እንደተወለድን ስንነግራቸው የምንመሰክረውን እውነተኛ ወንጌል ማንም መቃወም አይችልም እነርሱ እኛ ትክክል እንደሆንን

ይናገራሉ የሰዎችን ምስክርነት እንቀበላለን፡፡

ይህ ምንባብ እንደዚህም ደግሞ ይላል *«የእግዚአብሔር ምስክር ታላቅ ነው ይህም የእግዚአብሔር ምስክር ነውና»* ቃሉ የእግዚአብሄር ምስክር የልጁ ምስክር ነው ይላል ትክክል? የልጁ ምስክር ምንድነው? እግዚአብሄር እንዳዳነን ምስክሩ ኢየሱስ በመንፈስ በቤዛነት ውሃና በመስቀል ላይ ደሙ መምጣቱ ነው እግዚአብሄር እኛን ያዳነበት መንገድ ይህ እንደሆነና እኛም በዚህ ስለምናምን የእርሱ ልጆች እንደሆንን ይመሰክራል፡፡

*«በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው በእግዚአብሔር የማያምን ስለ ልጁ የመሰከረውን ምስክር ስላላመነ ሐሰተኛ አድርጎታል፡፡»*

ይህ ምንባብ የዳኑት እነማን እንደሆኑ በግልጽ ይነግረናል በእግዚአብሄር ልጅ የሚያምን ሰው በራሱ ምስክርነት እንዳለው ይናገራል በልባችሁ ውስጥ ምስክር አለን? ይህ በእናንተም በእኔም ውስጥ አለ ኢየሱስ ስለ እኛ ወደ ምድር መጣ (እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በማርያም ሰውነት በኩል በስጋ መጣ) 30 አመት ሲሆነው ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለመውሰድ ተጠመቀ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ይዞ በመስቀል ላይ ተፈረደበት የዘላለም ሕይወትን ይሰጠን ዘንድም በሦስተኛው ቀን ተነሳ ኢየሱስ ያዳነን እንዲህ ነው፡፡

እርሱ ትንሳኤን ባያገኝ ኖሮ ምን ይከሰት ነበር? በመቃብር ውስጥ እንዴት ለእኔ ሊመሰክር ይችል ነበር? አዳኜ የሆነው ለዚህ ነው የምናምነውም ይህንን ነው፡፡

እርሱ እንዳለው በጥምቀቱና በደሙ አድኖናል እኛም ስለምናምን እናንተና እኔ ድነናል ምስክሩ በእኔም ውስጥ በእናንተም ውስጥ አለ የዳኑ ሰዎች የእርሱን የጥምቀት «ውሃ» ፈጽሞ ቸል ሊሉት አይችሉም እርሱ እኛን ለማዳን ያደረጋቸውን ነገሮች በፍጹም አንገድፋቸውም፡፡

*«አሁንስ ፍቀድልኝ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና» (ማቴዎስ 3:15)* ኢየሱስ አጥማቂው ዮሐንስ ባጠመቀው ጊዜ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በዮርዳኖስ እንደወሰደ ፈጽሞ አንክድም የዳኑ ሰዎች የኢየሱስን ጥምቀት «ውሃ» በፍጹም ሊክዱት አይችሉም፡፡

## የሚያምኑ ነገር ግን ያልዳኑ ሰዎች የኢየሱስን ጥምቀት እስከመጨረሻው ድረስ ይክዱታል




ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ ሲል ምንኛ ትክክል ነበር ሐዋርያው ዮሐንስ *«በእግዚአብሔር የማያምን እርሱን ሐሰተኛ አድርጎታል»* ሐዋርያው ዮሐንስ አሁን እዚህ ቢኖር ኖሮ ለዛሬዎቹ ክርስቲያኖች ምን ይነግረን ነበር? «ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ የወሰደ» ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ ይጠይቅ ነበር፡፡

አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስ እኛን በጥምቀቱ ስላዳነበት ወንጌል አልመሰከረምን? «እርሱ በእኔ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቻችሁ ወደ ኢየሱስ ራስ ተላልፎ ሐጢያቶቻችሁን በጀርባው አልተሸከመምን?» ስለዚህ እርሱም ኢየሱስ

ሁላችንንም ለማዳን እንደተጠመቀ በግልጽ መስክሮዋል፡፡ (ዮሐንስ 1:29፤ ዮሐንስ 5:4-8)

በሌላ አነጋገር በእግዚአብሄር የማምኑና እኛን ለማዳን ባደረገው ነገር ሁሉ የማያምኑ ሰዎች እርሱን ውሸታም ያደርጉታል እኛ ኢየሱስ ሲጠመቅ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወሰደ ስንል እነርሱ «ኦ ውድዬ! እርሱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ሊወስድ አይችልም! እርሱ የወሰደው የአዳምን ሐጢያት ብቻ ነው ስለዚህ የቀን ተቀን ሐጢያቶቻችን በሙሉ አሁንም ድረስ አሉ፡፡»

ስለዚህ ለመዳን በየቀኑ ለሚሰሩዋቸው ሐጢያቶች የንስሐ ጸሎቶችን ማቅረብ እንዳለባቸው ይሟገታሉ የሚያምኑት ይህንን ነው እናንተም የምታምኑት ይህንን ነውን? ሐጢያቶቻችን በኢየሱስ ጥምቀት እንደተወገዱ የማያምኑ ሰዎች እግዚአብሄርን ውሸታም ያደርጉታል፡፡

## ኢየሱስ ሲጠመቅና በመስቀል ላይ ሲደማ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዋጅቶናል

*የሚዋሸው ማነው?*

*በኢየሱስ ጥምቀት*
*የማያምን ሰው ነው፡፡*

ኢየሱስ ተጠመቀ ሐጢያቶችንም ሁሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ወሰደ እግዚአብሄር በኢየሱስ ጥምቀትና ደም የሚያምኑትን

ሰዎች ሲያድን የማያምኑትን ግን ትቶዋቸዋል እነርሱ ሲያል ይወርዳሉ ስለዚህ መዳናችን ወይም አለመዳናችን የተመሰረተው በምናምነው ነገር ላይ ነው ኢየሱስ አለምን ከሐጢያቶች ሁሉ ነጻ አውጥቶታል የሚያምኑ ሰዎች ድነዋል የማያምኑ ሰዎች እግዚአብሄርን ሐሰተኛ ስላደረጉት ገና አልዳኑም::

ሰዎች ሲያል የሚወርዱት በድክመቶቻቸው ምክንያት ሳይሆን በእምነታቸው ጎዶሎነት ነው *«በእግዚአብሔር የማያምን እርሱን ሐሰተኛ አድርጎታል» (1ኛ ዮሐንስ 5:10)* ሐጢያቶቻቸው በሙሉ ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ የማያምኑ ሰዎች አሁንም ድረስ በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት አለባቸው ሐጢያት እንደሌለባቸው ሊናገሩ አይችሉም::

አንድ ጊዜ ከአንድ ዲያቆን ጋር ተገናኘሁና «ዲያቆን በኢየሱስ ባመንህ ጊዜ ሐጢያቶችህ በሙሉ ተወግደዋልን?» በማለት ጠየቅሁት::

«በእርግጥም ተወግደዋል::»

«እንግዲያውስ ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶ *'ተፈጸመ'* ስላለ ድነሃል ይህ ትክክል አይደለምን?»

«አዎ ድኛለሁ::»

«እንግዲያውስ ያለ ሐጢያት መሆን አለብህ::»

«አዎ ነኝ::»

«እንደገና ሐጢያት ብትሰራ ምን ይከሰታል?»

«እኛ ሰዎች ነን እንዴት ዳግመኛ ሐጢያት ላንሰራ እንችላለን? ስለዚህ በየቀኑ ንስሐ መግባትና ሐጢያቶቻችንን ማንጻት ይኖርብናል::»

ይህ ዲያቆን ምሉዕ የሆነውን የቤዛነት እውነት ባለማወቁ አሁንም ድረስ በልቡ ውስጥ ሐጢያት አለ::»

እርሱን የሚመስሉ ሰዎች በእግዚአብሄር ያላግጣሉ ሐሰተኛም ያደርጉታል አምላክ የሆነው ኢየሱስ የአለምን

ሐጢያቶች በሙሉ ማስወገድ ተስኖታልን? ይህ በጣም የሚያበሳጭ ነው ኢየሱስ ሐጢያቶችን በሙሉ ባያስወግድ ኖሮ እንዴት የደህንነት አምላክ ይሆን ነበር? በእርሱስ እንድናምን እንዴት ሊነግረን ይችል ነበር? እናንተም ሐሰተኛ ታደርጉታላችሁን? ያንን እንዳታደርጉ እመክራችኋለሁ!

መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ እንዳናላግጥ ይነግረናል ይህ ማለት እርሱን ሐሰተኛ አለማድረግና እርሱን ለማታለል አለመሞከር ማለት ነው እርሱ እንደ እኛ አይደለም::

ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ ቤዛነት ወንጌል በግልጽ ነግሮናል ብዙ ሰዎች እግዚአብሄር ለእኛ ባደረጋቸው ነገሮች --ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃ በደምና በመንፈስ በመምጣቱ እውነት ማመን አይፈልጉም::

ሁለት የክርስቲያን ቡድኖች አሉ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው የማያምኑና «እኔ ሐጢያተኛ ነኝ» ብለው የሚመሰክሩ ሰዎችና እግዚአብሄር ለእነርሱ ባደረገላቸው ነገሮች ሁሉ የሚያምኑና በእምነትም «እኔ ጻድቅ ነኝ» ብለው የሚመሰክሩ ሰዎች ናቸው እውነትን የሚናገረው የትኛው ቡድን ይመስላችኋል?

በሌላ አነጋገር እግዚአብሄር ባደረጋቸው ነገሮች የማያምኑና የውሃውን የደሙንና የመንፈሱን ምስክር የማይቀበሉ ሰዎች እየዋሹ ነው የማያምኑ ሰዎች እግዚአብሄርን ሐሰተኛ ያደርጉታል::

እርሱን ሐሰተኛ አታድርጉት ኢየሱስ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ መጥቶ እንዲህ (በመጠመቅ) ጽድቅን ሁሉ ፈጸመ (የአለምን ሐጢያቶች ወሰደ)::

## የማያምኑ ሰዎች የኢየሱስን ጥምቀትና ቅድስናውን ይክዳሉ

*ሰይጣንና ዲያብሎስ*
*የሚቃወሙት ምንን ነው?*

*የኢየሱስን ጥምቀት*

በልጁ የሚያምን ምዕመን በውስጡ ምስክር አለው ዳግም የተወለደ ሰው ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቹ ወደ እርሱ እንደተላለፉና በኢየሱስ ውሃና ደም እንደዳነ ያምናል ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ኢየሱስ በድንግል ማርያም ሰውነት በኩል ወደዚህ አለም እንደተወለደ በመስቀል ላይ ከመሞቱም በፊት በዮርዳኖስ እንደተጠመቀና ትንሳኤን እንዳገኘ ያምናሉ፡፡

ጻድቃን በልቦቻቸው ውስጥ ምስክር አላቸው የደህንነታችን ማረጋገጫው በውሃ በደምና በመንፈስ በመጣው በኢየሱስ ላይ ያለን እምነታችን ነው ምስክሩ በውስጣችሁ አለ በራሳችሁ ምስክር እንዲኖራችሁ እመክራችኋለሁ እላችኋለሁ በውስጣችሁ የደህንነት ማረጋገጫ የሆነው ምስክር ከሌለ ይህ ደህንነት አይደለም፡፡

ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ ብሎዋል *«በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው» (1ኛ ዮሐንስ 5፡10)* በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደም ብቻ ማመን ምስክር መያዝ ነውን? ወይስ ምስክር በውሃ እንጂ በደም አለማመን ነው? እግዚአብሄር እንዲያውቃችሁ በሶስቱም በሙሉ ማመን ይገባችኋል፡፡

ኢየሱስ ‘ድናችኋል’ ብሎ የሚመሰክርላችሁ ያን ጊዜ ብቻ ነው ከሶስቱ በሁለቱ ብቻ ብታምኑ ምስክር እንደሚኖራችሁ እየተናገራችሁ ነውን? ይህ በራሳችሁ መንገድ ማመን ነው ይህ ‘ለራሳችሁ መመስከር’ ይሆን ነበር፡፡

ይህንን መሰል ብዙ ሰዎች አሉ ከሦስቱ በሁለቱ ብቻ የሚያምኑ በጣም ብዙ ሰዎች በአለም አሉ እነርሱ እንደዳኑ ይመሰክራሉ ስለዚሁም መጽሐፎችን ይጽፋሉ ምንኛ አንደበ ርቱዕ ናቸው! ይህ በጣም የሚያስደነግጥ ነው ራሳቸውን «ወንጌላውያን» ደግሞም «ሐይማኖተኛ» ብለው ይጠራሉ በ «ውሃው» አያምኑም ነገር ግን አሁንም ድረስ በደህንነታቸው ይመጻደቃሉ! ሎጂካል ይመስሉ ይሆናል በአእምሮዋቸው ውስጥ ግን የእግዚአብሄር ምስክር የለም መላ ምት ብቻ ነው።

ይህንን እንዴት ደህንነት ብላችሁ ልትጠሩት ትችላላችሁ? የእግዚአብሄርና የሰዎች ምስክር ያላቸው በመንፈስ በውሃና በደም በመጣው ኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች ብቻ ናቸው።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሎዋል *«ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደእናንተ አልመጣምና በእናንተ ዘንድ ስለ እናንተ እንዴት እንደነበርን ታውቃላችሁ» (1ኛ ተሰሎንቄ 1:5)* ሰዎች በኢየሱስ ደም ብቻ ሲያምኑ ሰይጣን ይደሰታል «ኦ እናንተ ሞኞች በእኔ ተታላችኋል ሃ-ሃ!» ሰዎች የኢየሱስን ደም ሲያመሰግኑ ሰይጣን ይሸሻል ብለው የሚያምኑ ብዙ ሰዎች አሉ እነርሱ ሰይጣን መስቀሉን ይፈራ ይሆናል ብለው ያስባሉ ነገር ግን ሰይጣን ስራው ማስመሰል ብቻ እንደሆነ በአእምሮዋችሁ ልትይዙ ይገባል በዚህ መሞኘት አይገባንም።

አጋንንት አንድን ሰው ሲይዝ የተያዘው ሰው ሊረብሽና በአፉ አረፋ ሊደፍቅ ይችላል ይህ ለዲያብሎስ አስቸጋሪ ተግባር አይደለም ምክንያቱም ሰው ማንኛውንም ነገር እንዲያደርግ የሚያስችለው ሐይል አለውና ዲያብሎስ አእምሮውን ጥቂት ብቻ መጠቀም ይበቃዋል እግዚአብሄር ለዲያብሎስ ከመግደል ስልጣን ውጭ ሁሉንም አይነት ስልጣን ሰጥቶታል ዲያብሎስ አንድን ሰው እንደ ዛፍ ቅጠል እንዲንቀጠቀጥ እንዲጮህና በአፉም አረፋን እንዲደፍቅ ሊያደርገው ይችላል።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ ምዕመናን «በኢየሱስ ስም ውጣ! ውጣ!» እያሉ ይጮኻሉ ሰውየው ወደ አእምሮው ሲመለስና ራሱን ሲያውቅ እርሱን ያዳነው ሐይል የኢየሱስ ደም እንደሆነ ይነግሩታል ይህ ግን የደሙ ሐይል አይደለም ይህ የዲያብሎስ «ማስመሰያ» ብቻ ነው፡፡

ሰይጣን በጣም የሚፈራው በጥምቀቱ ባነጻን በደሙም ስለ እኛ ፍርድን በወሰደውና በሦስተኛው ቀን በተነሳው ኢየሱስ የሚያምኑትን ሰዎች ነው ሰይጣን በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ደህንነት ምስክር ዙሪያ ሊቆይ አይችልም፡፡

እንደምታውቁት የካቶሊክ ካህናቶች አንዳንድ ጊዜ ጥንቆላን ይጠቀማሉ ይህንን በፊልሞች ውስጥ አይተናል «ዘ ኦሜን» በሚለው ፊልም ውስጥ አንድ ካህን የእንጨት መስቀል ይዞ ያወዛውዘዋል ነገር ግን ካህኑ ይሞታል ዳግም የተወለደ ሰው በዚህ ሁኔታ አይሸነፍም፡፡

ዳግም የተወለደ አማኝ ስለ ኢየሱስ ደምና ውሃ በድፍረት ይናገራል ዲያብሎስ ሊያሰቃየው ሲሞክር ዲያብሎስን «ኢየሱስ ሐጢያቶቼን በሙሉ እንደወሰደ ታውቃለህን?» ብሎ ይጠይቀዋል ያን ጊዜ ዲያብሎስ ይሸሻል ዲያብሎስ «ዳግም በተወለደ ሰው» ዙሪያ መሆን ይጠላል «አንድ ዳግም የተወለደ ሰው» እዚያ ከተቀመጠ ዲያብሎስ ሊሸሽ ይሞክራል ቃሉ በእግዚአብሄር የማያምኑ እርሱን ሐሰተኛ ያደርጉታል ይላል እነርሱ በልጁ ምስክር በውሃውና በደሙም ምስክር አያምኑም፡፡

*የእግዚአብሐየር ልጅ ምስክርነት ምንድን ነው?*

*ጥምቀቱ፣ ደሙና መንፈሱ ናቸው፡፡*

የእግዚአብሄር ልጅ ምስክር ምንድነው? በመንፈስ መምጣቱና ሐጢያቶቻችንን በውሃው መውሰዱ ነው እርሱ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በራሱ ላይ ወስዶ ለሁላችንም በመስቀል ላይ ደምቷል ያ የውሃ የደምና የመንፈስ ቤዛነት አይደለምን?

ሰዎች የቤዛነት ወንጌል በሆነው በእውነተኛው የውሃና የደም ወንጌል ስለማያምኑ በእግዚአብሄር ፊት ይዋሻሉ ሌሎች ወንጌሎች በሙሉ ሐሰት ናቸው እምነቶቻቸውም ሐሰት ናቸው እነርሱም እነዚህን ወንጌሎች በከንቱ ያሰራጫሉ::

ወደ 1ኛ ዮሐንስ 5 እንመለስ በ11ኛው ቁጥር ላይ እንዲህ ይላል *«እግዚአብሔርም የዘላለምን ህይወት እንደሰጠን ይህም ህይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው»* ይህ እግዚአብሄር የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠን ያም ሕይወት በተቀበለው ሰው ውስጥ እንደሚኖር ይነግረናል እንደዚሁም ይህ ሕይወት በልጁ ውስጥ አለ::

የዘላለምን ሕይወት የሚያገኙ ሰዎች በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ በማመን የተዋጁ ሰዎች ናቸው የዳኑት የዘላለምን ሕይወት አግኝተው ለዘላለም ይኖራሉ የዘላለም ሕይወትን አግኝታችኋልን?

በ12ኛው ቁጥር ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል *«ልጁ ያለው ህይወት አለው የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ህይወት የለውም»* በሌላ አነጋገር ወልድ በምድር ላይ ባደረጋቸው ነገሮች -- በጥምቀቱ በመስቀል ላይ ሞቱና በትንሳኤው -- የሚያምን ሰው የዘላለም ሕይወት አለው ነገር ግን ከእነዚህ አንዱን እንኳን የገደፈ ሰው ሕይወት አይኖረውም ቤዛነትንም አያገኝም::

ሐዋርያው ዮሐንስ የእግዚአብሄርን ሕዝብ ኢየሱስ ባደረጋቸው ነገሮች በውሃው በደሙና በመንፈሱ ላይ ባላቸው እምነት ላይ ተመስርቶ ለይቶዋቸዋል እነዚህ ነገሮች እነርሱ

በውስጣቸው ቃሉ እንዳላቸው ወይም እንደሌላቸው ይነግሩናል እርሱ የዳኑትን በኢየሱስ የጥምቀት ውሃ በደሙና በመንፈሱ ላይ ባላቸው አመኔታ ይለያቸዋል፡፡

## ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች በግን ከፍየል መለየት አይችሉም




ሐዋርያው ዮሐንስ የተዋጁትን ጻድቃን ሰዎች በግልጽ ለይቶዋቸዋል ሐዋርያው ጳውሎስም ደግሞ ይህንኑ አድርጓል የእግዚአብሄር አገልጋዮች በበግና በፍየል መካከል በጥልቀት መለየት የሚችሉት እንዴት ነው? እውነተኛ የሆኑትን የእግዚአብሄር አገልጋዮች ከአስመሳዮች መለየት የሚችሉት እንዴት ነው? በውሃውና በኢየሱስ ደም የሚያምኑ ሰዎች የማየት ሐይል ይቀበላሉ፡፡

አንድ ሰው መጋቢ፣ ወንጌላዊ ወይም ሽማግሌ ቢሆን የተዋጁትን ሰዎች መለየት የማይችል ከሆነ ወይም በበግና በፍየል መካከል መለየት የማይችል ከሆነ ገና ዳግም አልተወለደም በውስጡም ሕይወት የለውም ነገር ግን በእውነት ዳግም የተወለዱ ሰዎች ልዩነቱን በግልጽ ማየት ይችላሉ ሕይወት

አልባ የሆኑ ሰዎች ልዩነቱን ማየትም ሆነ መቀበል አይችሉም።

በጨለማ ውስጥ ቀለማቶችን መለየት ባንችልም አረንጓዴ አረንጓዴ ነጭም ነጭ ነው ነገር ግን አይኖቻችሁን ብትጨፍኑ ቀለማቶችን ማየትም ሆነ ማወቅ አትችሉም።

አይኖቻቸው የተገለጡ ሰዎች ግን በቀለም ውስጥ ያለችውን በጣም ኢምንት ልዩነት እንኳን ማወቅ ይችላሉ ትኛው አረንጓዴ የትኛው ደግሞ ነጭ እንደሆነ መናገር ይችላሉ በተመሳሳይ ሁኔታ በተዋጁትና ባልተዋጁት ሰዎች መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት አለ።

እኛ የቤዛነት ወንጌል የሆነውን የውሃውን የደሙንና የመንፈሱን መስበክ ይኖርብናል ተነስተን ማብራት አለብን እውነተኛውን እምነት ለማሰራጨት ሰዎችን በዙሪያችን ስንሰበስብ የሰዎችን ቃሎች አንናገርም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 1ኛ ዮሐንስ 5 የዚህን ትርጉም ያብራራል ግራ መጋባት እንዳይኖር ደረጃ በደረጃ ልናብራራው ይገባናል።

የምንሰብከው ቃል ማለትም የኢየሱስ የውሃው የደሙና የመንፈሱ ቃል የቤዛነት ብርሃን ነው የኢየሱስን «ውሃ» ለሰዎች ለማስተዋወቅ ብሩህ ሆነን ማብራት አለብን የኢየሱስን «ደም» ማስተዋወቅ ማለት ብሩህ ሆኖ ማብራት ማለት ነው በምድር ላይ ይህንን እውነት የማያውቅ ሰው እንዳይኖር በጣም ግልጽ ልናደርገው ይገባናል።

ዳግም የተወለዱ ሰዎች ተነስተው የማያበሩ ከሆነ ብዙ ሰዎች ቤዛነትን ሳያገኙ ይሞታሉ እግዚአብሄርም አይደሰትም እኛንም ሰነፍ አገልጋዮች ብሎ ይጠራናል እኛ የኢየሱስን የውሃና የደም ወንጌል ማስፋፋት አለብን።

ራሴን ብዙ ጊዜ የምደጋግመው የኢየሱስ ጥምቀት ለደህንነታችን በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ነው ለልጆች ስንናገር ማስተዋላቸውን ለማረጋገጥ ስንል እያንዳንዱን ነጥብ

በመደጋገም ነገሮችን ደጋግመን ማብራራት ይኖርብናል።

አንድ መሃይም የሆነን ሰው ለማስተማር ስንሞክር ምናልባት የምንጀምረው ከሆሄ ነው ከዚያም ቀስ በቀስ በዚህ ሆሄ እንዴት ቃላቶችን መጻፍ እንደሚችል እናስተምረዋለን *«ቀጣት»* የሚለውን አይነት ቃል መጻፍ ሲችል የእነዚህን ቃላቶች ትርጉም ልናብራራለት እንጀምራለን ሰዎች በትክክል ለመረዳታቸው እርግጠኞች እንሆን ዘንድ ልንነግራቸው የሚገባን በትክክል ይህንን ነው።

የኢየሱስን ጥምቀት በግልጽ ማብራራት ይገባናል እርሱ በውሃ በደምና በመንፈስ ወደዚህ አለም መጣ ኢየሱስን አዳኛ ችሁ አድርጋችሁ በማመን እንድትድኑ እጸልያለሁ።

የውሃውና የመንፈሱ ቤዛነት የሚመነጨው በኢየሱስ ጥምቀት በመስቀል ላይ ደሙና ኢየሱስ አምላክና አዳኛችን በመሆኑ አመኔታ ላይ ካለን እምነት ነው። ✉

# ስብከት 7

## የኢየሱስ ጥምቀት

---

## ለሐጢያተኞች የደህንነት

---

## ምሳሌ ነው

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::



ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

# የኢየሱስ ጥምቀት ለሐጢያተኞች የደህንነት ምሳሌ ነው

**« 1ኛ ጴጥሮስ 3:20-22 »**

**«ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውሃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ የእግዚአብሔር ትዕግስት በኖህ ዘመን በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም ይህም ውሃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም ለእግዚአብሔር የበጎ ህሊና ልመና ነው እንጂ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ነው እርሱም መልአክትና ስልጣናት ኃይላትም ከተገዙለት በኋላ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ።»**

*ጻድቃን ልንሆን የምንችለው በምን አማካይነት ነው?*

*በእግዚብሔር ጸጋ አማካይነት ነው።*

እግዚአብሄር በዚህ ምድር ላይ ከመወለዳችን በፊት እንኳን አስቀድሞ አውቆናል ሐጢያተኞች ሆነን እንደምንወለድና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በወሰደው ጥምቀቱ አማካይነት እኛ ን ምዕመናኖች በሙሉ እንደሚያድነን አውቋል እርሱ ምዕመናኖችን ሁሉ አድኖ ሕዝቡ አድርጎዋቸዋል።

ይህ ሁሉ የእግዚአብሄር ጸጋ ውጤት ነው በመዝሙረ

ዳዊት 8:4 ላይ እንዲህ ተብሎዋል *«ታስበው ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?»* ከሐጢያቶች ሁሉ የዳኑት የተዋጁ ሰዎች የእርሱን ልዩ ፍቅር ይቀበላሉ እነርሱ የእርሱ ልጆች ናቸው፡፡

የእግዚአብሄር ልጆች ከመሆናችን በፊት ጻድቃን ከመሆናችንና ድነን እርሱን አባት ብለን የመጥራት መብት ሳይሰጠን በፊት በእርሱ ደምና መንፈስ ብቻ ያመንን ሰዎች ምን ነበርን? እኛ በዚህ አለም ላይ ጤናማ ከሆንን 70 ወይም 80 አመት ለመኖር የተወለድን ሐጢያተኞች ተራ ሐጢያተኞች ነበርን፡፡

ከሐጢያቶቻችን ከመንጻታችን በፊትና በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ወንጌል እምነት ከመያዛችን በፊት መጥፋታችን እርግጥ የሆነ አመጸኛ ሕዝቦች ነበርን፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ እርሱ የሆነውን የሆነው ከእግዚአብሄር ጸጋ የተነሳ እንደሆነ ተናግሮዋል ልክ እንደዚሁ እኛም አሁን የሆንነውን የሆንነው ፈጽሞ ከእርሱ ጸጋ የተነሳ ነው ለጸጋው እናመሰግነዋለን ፈጣሪ ወደዚህ አለም ወርዶ አዳነን የእርሱ ልጆች ሕዝቦቹም አደረገን ስለውሃውና መንፈሱ የደህንነት ጸጋ እናመሰግነዋለን፡፡

የእርሱ ልጆች ጻድቃኖች እንሆን ዘንድ የፈቀደበት ምክንያቱ ምንድነው? ሲያዩን የምናምር ስለሆንን ነውን? ዋጋ ያለን ሰዎች ስለሆንን ነውን? ወይስ በጣም ጥሩዎች ስለሆንን? ስለዚህ ጉዳይ እናስብ ምስጋና ለሚገባውም ምስጋናን እንስጥ፡፡

ምክንያቱ እግዚአብሄር ሕዝቦቹ እንድንሆን ስለፈጠረንና ከእርሱም ጋር በመንግስተ ሰማይ እንድንኖር ስለፈቀደልን ነው እግዚአብሄር ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንድንኖር ይፈቅድልን ዘንድ የእርሱ ሕዝብ አድርጎናል እግዚአብሄር በዘላለም ሕይወት እኛን የባረከበት ብቸኛው ምክንያት ያ ነው የእርሱ ሕዝቦች ያደረገን ውብ ስለሆነን ይበልጥ ዋጋ ያለን ስለሆንን ወይም ከእርሱ

ፍጡራኖች ከማናቸውም ሌሎች ሰዎች ይልቅ የበለጥን ሰናይ ሰዎች ስለሆንን አይደለም ብቸኛው ምክንያት እርሱ እኛን መውደዱ ነው፡፡

*«ይህም ውኃ ደግሞ ጥምቀት ምሳሌ ሆኖ አሁን ያድነናል» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡21) «ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት፡፡» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡20)*

የዳኑት ጥቂቶች ብቻ ማለትም ከአንድ ከተማ አንድ ከአንድ ቤተሰብ ሁለት ናቸው ታዲያ እኛ ከሌሎች የተሻልን ነን? በፍጹም! እኛ ያን ያህል የተለየን አይደለንም ነገር ግን የሆኖ ሆኖ በውሃውና በመንፈሱ ላይ ባለን እምነታችን የተነሳ ድነናል፡፡

የእኛ መዳን ከተአምራቶች መካከል አንዱ ተአምር ነው እርሱን አባታችንና ጌታችን ብለን መጥራት መቻላችንም ከእግዚአብሄር የተሰጠ ወሰን የሌለው ስጦታና በረከት ነው ይህንን በጭራሽ ልንክድ አንችልም ገናም ሐጢያተኞች ብንሆን ኖሮ እርሱን እንዴት አባታችን ወይም ጌታችን ብለን ልንጠራው እንችላለን?

የዳንን ስለመሆናችን እውነቱን ስናስብ እግዚአብሄር ያለ ቅድመ ሁኔታ እንደወደደን እናውቃለን ልናመሰግነው አንችልምን? ከእርሱ ፍቅርና ባርኮቶች የተነሳ ባይሆን ኖሮ ተወልደን ጎስቋላ ሕይወትን ከኖርን በኋላ በመሞት መጨረሻችን ሲያል ይሆን ነበር እግዚአብሄርን ለባርኮ ቶቹና በእርሱ አይኖች ፊት ልጆቹ እንሆን ዘንድ ብቁዎች ስላደረገን ደጋግመን እናመሰግነዋለን፡፡

# በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት የተሰጠን የከበረ ደህንነት




*«ይህም ውኃ ደግሞ ጥምቀት ምሳሌ ሆኖ አሁን ያድነናል»* በ1ኛ ጴጥሮስ ላይ በውሃ አማካይነት ስምንት ሰዎች ብቻ እንደዳኑ ተጽፎዋል በኖህ ዘመን ምን ያህል ሰዎች ነበሩ? ምን ያህል እንደነበሩ የምናውቅበት መንገድ የለም ነገር ግን ወደ ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች ነበሩ ብለን እንገምት ከሚሊዮን ሰዎች መካከል በኖህ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ 8 ሰዎች ብቻ ዳኑ::

ተመዛዛኙቱ ከዛሬው ጋር ተመሳሳይ ይሆናል እነርሱ በአሁኑ ጊዜ በምድር ላይ ከ6 ቢሊዮን ሕዝብ በላይ አለ ይላሉ ዛሬ በኢየሱስ በሚያምኑት ሰዎች መካከል ምን ያህል ሰዎች ከሐጢያቶቻቸው ነጽተዋል? አንድ ከተማን ብቻ ብንመለከት ከእነርሱ በጣም ጥቂቶች ብቻ ይሆናሉ::

250,000 ሰዎችን በያዘችው እኔ በምኖርባት ከተማ ውስጥ ስንቶች ከሐጢያቶቻቸው ተዋጅተዋል? ምናልባት 200? ታዲያ ተመዛዛኝነቱ ምን ያህል ይሆናል? ይህ ማለት የቤዛነትን በረከት የተቀበለው ከሺህው ውስጥ ከአንድም ያነሰ ነው ማለት ነው::

በኮርያ ካቶሊኮችን ጨምሮ ወደ 12 ሚሊዮን የሚጠጉ ክርስቲያኖች እንዳሉ ይገመታል ከእነዚህ ውስጥ ከመካከላቸው

ከውሃና ከመንፈስ የተወለዱት ምን ያህል ናቸው? በኖህ ዘመን ከመላው የምድር ሕዝብ ውስጥ 8 ሰዎች ብቻ እንዳደኑ በአእምሮዋችን መያዝ አለብን ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን እንደወሰደ የሚያምኑ ሰዎችን ሐጢያቶች በሙሉ እንዳነጻ ማወቅና ማመን አለብን፡፡

ኢየሱስ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ሁላችንንም እንደዋጀን የሚያምኑ ብዙዎች አይደሉም ታዋቂ የሆነውን ‘የኢየሱስን ትንሳኤ’ ስዕል ተመልከቱ እዚያ ላይ ምን ያህል የተነሱ ሰዎች ይታያሉ? እነርሱ ከኢየሩሳሌም አምባ እየወረዱ እጆቹን ዘርግቶ ወደሚጠብቃቸው ወደ ኢየሱስ ምስል ሲመጡ ልታዩ ትችላላችሁ ከእነርሱ መካከል ምን ያህሎቹ የስነ መለኮት ሊቃውንት ወይም አገልጋዮች እንደሆኑ ገምቱ፡፡

ዛሬ በአለም ላይ ብዙ የስነ መለኮት ሊቃውንቶች አሉ ነገር ግን የኢየሱስ ጥምቀት ወሳኝ የቤዛነት እውነት መሆኑን የሚያውቁና የሚያምኑ በጣም ጥቂቶች ሆነው እናገኛለን አንዳንድ የስነ መለኮት ሊቃውንት ኢየሱስ የተጠመቀበት ምክንያቱ ትሁት ስለነበር ነው ይላሉ አንዳንዶች ደግሞ እርሱ የተጠመቀው ይበልጥ እኛን ሰዎችን ለመምሰል ነው ይላሉ፡፡

ነገር ግን ጴጥሮስንና ዮሐንስን ጨምሮ ሐዋርያት በሙሉ የኢየሱስ ጥምቀት ሐጢያቶቻችን ወደ እርሱ የተላለፉበት እንደሆነ መመስከራቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎዋል እኛም ደግሞ ይህንኑ እናምናለን፡፡

ሐዋርያት በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ሐጢያቶቻችን በጥምቀቱ ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ መስክረዋል ይህ በዚህ በማመን ብቻ መዳን የምንችል መሆናችንን ለሚመሰክረው የእግዚአብሄር ጸጋ ድንቅ ምስክርነት ነው፡፡

# ስለ ቤዛነት ጥምቀት ምንም አይነት «ምናልባት» የሚባል ነገር የለም

*የእግዚአብሔርን ወሰን የለሽ ፍቅር የሚያገኘው ማነው?*

*በኢየሱስ ጥምቀት እና ደም የሚያምን ሰው:: ሰው ነው::*

ሰዎች በኢየሱስ ማመን ብቻ እንደሚያድነን ለማመን ይፈጥናሉ የሐይማኖት ድርጅቶች በሙሉ በአመኔታዎቻቸው ውስጥ ስለ ደህንነታቸው ተማምነዋል ብዙ ሰዎችም የኢየሱስ ጥምቀት የክርስቲያን ማህበረሰብ ዶግማ ብቻ እንደሆነ ያስባሉ ይህ ግን እውነት አይደለም እኔ ካነበብኳቸው በሺህዎች የሚቆጠሩ መጽሐፎች መካከል በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ቤዛነትና በእግዚአብሄር ደህንነት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያብራራ በደህንነት ላይ የተጻፈ አንድም መጽሐፍ አላገኘሁም::

በኖህ ዘመን 8 ሰዎች ብቻ ዳኑ ዛሬ ምን ያህል እንደሚድኑ አላውቅም ምናልባት ግን ብዙ አይደሉም የዳኑ ሰዎች በኢየሱስ ጥምቀትና ደም የሚያምኑ ሰዎች ናቸው ብዙ ቤተክርስቲያኖችን ስጎበኝ በተደጋጋሚ የእውነት ወንጌል የሆነውን የኢየሱስን ጥምቀት ወንጌል የሚሰብኩ በጣም ጥቂቶች እንደሆኑ ተረድቻለሁ::

በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ቤዛነት ካላመንን ምንም ያህል በታማኝነት ወደ ቤተክርስቲያን ብንሄድ ገናም ሐጢያተኞች ነን አልዳንም በሕይወት ዘመናችን ሁሉ በታማኝነት ቤተክርስቲያን

እንሄድ ይሆናል ነገር ግን ገናም በልቦቻችን ውስጥ ሐጢያት ካለ ገናም ሐጢያተኞች ነን፡፡

ለ50 አመታት ያህል ቤተክርስቲያን ሄደን ከሆነና ነገር ግን አሁንም ድረስ በልቦቻችን ውስጥ ሐጢያት ካለ የ50 አመታት እምነታችን ውሸት እንጂ ምንም ነገር አይደለም የአንድ ቀን እውነተኛ እምነት መያዝ በጣም የተሻለ ነው በኢየሱስ በሚያምኑ መካከል መንግስተ ሰማይ የሚገቡት በኢየሱስ ጥምቀት ትርጉምና በደሙ በትክክል የሚያምኑ ብቻ ናቸው፡፡

እውነተኛ እምነት የእግዚአብሄር ልጅ ወደዚህ ምድር ወርዶ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ የተጠመቀ የመሆኑን እውነት ማመን ነው መንግስተ ሰማያት የሚያስገባን ይህ እምነት ነው ኢየሱስ ለእናንተና ለእኔ በመስቀል ላይ እንደደማም ደግሞ ማመን ይገባናል እርሱን ለማመስገንና ለማክበርም ደግሞ ይህንን ማወቅ ይገባናል፡፡

እኛ ምንድነን? እኛ በኢየሱስ ጥምቀትና ደም የዳንን ወንዶችና ሴቶች ልጆች ነን እንዴት ላናመሰግነው እንችላለን? ኢየሱስ እኛን ለማዳን 30 አመት ሲሆነው በዮርዳኖስ ተጠመቀ በዚህም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶ በመስቀል ላይ ስለ እኛ ፍርድን ተቀበለ፡፡

ስለዚህ ነገር ስናስብ እርሱን በትህትና ከማመስገን በቀር ልናደርገው የምንችለው ነገር የለም ኢየሱስ በዚህ አለም ላይ ያደረገው እያንዳንዱ ነገር ለደህንነታችን የተደረገ ነገር እንደነበር ማወቅ ይገባናል መጀመሪያ ወደዚህ አለም መጣ ተጠመቀ በመስቀል ላይ ተሰቀለ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተነሳ አሁን በእግዚአብሄር ቀኝ ተቀምጦዋል፡፡

የእግዚአብሄር ቤዛነት ያለ ምንም አድልዎ ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጠ ነው የኢየሱስ ደህንነት በሙሉ ለእናንተና ለእኔ ነው ለፍቅሩና ለባርኮቶቹ እግዚአብሄርን እናመሰግናለን፡፡

እንዲህ የሚለውን የወንጌል መዝሙር እናውቀዋለን *«♫ውብ ታሪክ አለ ♫በአለም ላይ ካሉ ብዙ ሰዎች መካከል የእርሱ ፍቅርና ደህንነት ያለኝ እኔ ነኝ ♫ኦ የእርሱ ፍቅር ምንኛ ግሩም ነው! ♫ለእኔ ያለው ፍቅር ለእኔ ያለው ፍቅር ♫ውብ ታሪክ አለ ♫በአለም ላይ ካሉ ብዙ ሰዎች መካከል የእርሱ ፍቅርና ደህንነት ያለን እኛ የዳንንና የእርሱ ሕዝብ የሆንን ሰዎች ነን ♫ኦ የእግዚአብሄር ፍቅር የእግዚአብሄር ጸጋ ♫ኦ ፍቅሩ ምንኛ ግሩም ነው! ለእኔ ያለው ፍቅር!♫»*

ኢየሱስ እናንተንና እኔን ለማዳን መጣ የጥምቀቱም ቤዛነት እንደዚሁ ለእኛ ነው ወንጌል አንዳች ተረት አይደለም ከልፋት ሕይወታችን አውጥቶ ውብ ወደሆነው የእግዚአብሄር መንግስት ከፍ የሚያደርገን እውነት ነው እምነት በእግዚአብሄርና በእናንተ መካከል ያለ ግንኙነት መሆኑን በአእምሮዋችሁ መያዝ ይገባችኋል፡፡

እርሱ እኛን ለማዳን ወደዚህ አለም መጣ ተጠመቀ ሐጢያቶቻችንን ለማንጻትም በመስቀል ላይ ፍርድን ተቀበለ፡፡

ታማኞች እግዚአብሄርን አባታቸው አድርገው መጥራታቸው እንዴት ያለ በረከት ነው! ኢየሱስን አዳኞችን አድርገን ማመን የምንችለውና በእምነታችን ከሐጢያት የምንድነው እንዴት ነው? ይህ የሚቻለው እርሱ ለእኛ ካለው ወሰን የለሽ ፍቅሩ የተነሳ ነው እኛ አስቀድሞ ከወደደን ከእርሱ የተነሳ ድነናል፡፡

## ኢየሱስ ኃጢያቶቻችንን በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አንጽቶልናል

*«ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ*

*ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ህያው ሆነ» (1ኛ ጴጥሮስ 3:18)* ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤዛነታችን ተጠመቀ አመጻኞች የሆንነውን እናንተንና እኔ ለማዳን አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ ሞተ::

*እኛ የዳንነው ለአንዴና ለመጨረሻ ነው ወይስ ቀስ በቀስ?*

*ለአንዴና ለመጨረሻ ነው::*

እኛን ከእግዚአብሄር ፍርድ ለመከላከል ሲል አንድ ጊዜ በዚህ ምድር ላይ ሞተ እኛ መንግስተ ሰማያት እንድንገባና በእግዚአብሄርም ፊት ለዘላለም እንድንኖር በስጋ ወደዚህ አለም መጥቶ በጥምቀቱ በመስቀል ላይ ሞቱና በትንሳኤው ከሐጢያታችን ሁሉ በአንድ ጊዜ አነጻን::

ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱና በደሙ ፈጽሞ እንዳዳነን ታምናላችሁን? በእርሱ ጥምቀትና ደም ወንጌል የማታምኑ ከሆናችሁ ልትድኑ አትችሉም እኛ በጣም ደካሞች ስለሆንን ኢየሱስ በጥምቀቱና በደሙ ለአንዴና ለመጨረሻ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ፈጽሞ እንዳነጻ ካላመንን ዳግም ልንወለድ አንችልም::

እርሱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለመውሰድ ተጠመቀ ስለ እኛም በመስቀል ላይ ተኮነነ ኢየሱስ በጥምቀቱና በደሙ ቤዛነት የሐጢያተኞችን ሐጢያቶች በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ አንጽቷል::

ሐጢያት በሰራን ጊዜ ሁሉ ንስሐ መግባት ሁልጊዜም

ጥሩዎችና ለጋሶች መሆንና ለቤተክርስቲያንም ብዙ ነገሮችን መለገስ ቢኖርብን ኖሮ ሰዎች ነንና ለመዳን አዳጋች ይሆንብን ነበር፡፡

ስለዚህ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደም ማመን ለደህንነታችን ግዴታ ነው በውሃውና በደሙ ማመን አለብን መልካም ስራዎችን መስራት ብቻውን ከሐጢያቶቻችን ስርየት ጋር ምንም የሚያገኛኘው ነገር የለም፡፡

ለድሃው ውድ ልብስ መግዛት ወይም ለመጋቢዎች ጣፋጭ ምግቦችን ማቅረብ ለደህንነታችሁ ምንም የሚፈይደው ነገር የለም ኢየሱስ የሚያድነው በእርሱ ጥምቀትና ደም የሚያምኑትን ብቻ ነው እግዚአብሄር በኢየሱስ አማካይነት በጥምቀቱና በደሙ ለአንዴና ለመጨረሻ እንዳዳነን ብናምን እንድናለን፡፡

አንዳንዶች እግዚአብሄር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ቢልም ተጨማሪ ጊዜ ወስደው ማሰብ የሚኖርባቸው ይመስላቸዋል ይህ የእነርሱ ጉዳይ ነው እኛ ግን በተጻፈው መሰረት በቃሉ ማመን ይገባናል፡፡

ዕብራውያን 10፡1-10 ላይ እርሱ ሁላችንንም ለዘላለም እንዳዳነን ተጽፎዋል እግዚአብሄር በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ያመኑትን ሰዎች ለአንዴና ለመጨረሻ እንዳዳናቸው እውነት ነው እኛም ይህንን ማመን አለብን «♫እርሱ አንድ ጊዜ ሞተ ሁላችንንም በአንድ ጊዜ አዳነን ኦ ወንድሞች እመኑና ዳኑ ሸክሞቻችሁን ከኢየሱስ ጥምቀት በታች አኑሩ♫» ኢየሱስ አንድ ጊዜ በመጠመቅና አንድ ጊዜ ደሙን በማፍሰስ ከአመጻና ከሐጢያቶች ሁሉ አድኖናል፡፡

*«ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡18)* ኢየሱስ ሐጢያት የሌለበት አምላክ ነው እርሱ ፈጽሞ አልበደለም ሰዎችን ከሐጢያቶቻቸው ለማዳን በስጋ ወደ እኛ መጣ

ተጠመቀ ሐጢያቶቻችንንም በሙሉ ወሰደ ከሐጢያትና ከአመጽም አዳነን::

ከውልደት እስከ ሞት ድረስ ያሉት የሰዎች ሐጢያቶች በሙሉ በተጠመቀ ጊዜ ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል እርሱ በመስቀል ላይ ሲደማና ሲሞትም ሁሉም ከፍርድ ድነዋል እርሱ ለሐጢያተኞች ተጠመቀ በእነርሱ ፋንታም በይፋ ሞተ::

ይህ የጥምቀቱ ቤዛነት ነው ኢየሱስ ሐጢያተኞች የነበርነውን ሁላችንንም ለአንዴና ለመጨረሻ አዳነን እያንዳንዳችን ምን ያህል ደካሞች ነን! ኢየሱስ ከውልደታችን እስከ ሞታችን ድረስ ያሉትን ሐጢያቶች በሙሉ ዋጅቶ በመስቀል ላይ ራሱን ለፍርድ አቀረበ በኢየሱስ የሚያምን ሰው እርሱ በጥምቀቱና በደሙ ለአንዴና ለመጨረሻ እንዳዳነን ማመን ይገባዋል::

እኛ ደካሞች ነን ኢየሱስ ግን አይደለም እኛ ታማኞች አይደለንም ኢየሱስ ግን ነው እግዚአብሄር ለአንዴና ለመጨረሻ አድኖናል *«በእርሱ የሚያምን ሁሉ ዘላለማዊ ህይወትን እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና» (ዮሐንስ 3:16)* እግዚአብሄር አንድያ ልጁን ሰጠን ለሰዎች ሁሉ ፍርድን መቀበል ይችል ዘንድ የአለምን ሐጢያቶች ወደ እርሱ ለማስተላለፍ ልጁ እንዲጠመቅ አደረገ::

ይህ ምንኛ አስገራሚ ደህንነት ነው! ይህ ምንኛ አስገራሚ ፍቅር ነው! ለፍቅሩና ለደህንነቱ እግዚአብሄርን እናመሰግናለን እግዚአብሄር በውሃውና በደሙ በኢየሱስ ጥምቀትና ባፈሰሰው ደሙ እንደዚሁም ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ በመሆኑ እውነታ የሚያምኑትን አድኖዋቸዋል::

በኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች በኢየሱስ ጥምቀትና ደም እውነት በማመን መዳንና ጻድቃን ሆነውም የዘላለም ሕይወት

ማግኘት ይችላሉ ሁላችንም ይህንን ማመን አለብን::

ያዳነን ማነው? ያዳነን እግዚአብሄር ነበር ወይስ ያዳነን ከእርሱ ፍጥረቶች አንዱ ነበር? ያዳነን አምላክ የሆነው ኢየሱስ ነበር እኛ የዳንነው በእግዚአብሄር ቤዛነት ስላመንን ነው ይህም የቤዛነት ደህንነት ነው::

## ኢየሱስ የደህንነት ጌታ ነው

*የ«ክርስቶስ» ትርጓሜ ምንድን ነው?*

*ካህን ንጉስና ነቢይ ማለት ነው::*

ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው ኢየሱስ ማለት አዳኝ ማለት ሲሆን ክርስቶስ ማለትም «የተቀባው» ማለት ነው በብሉይ ኪዳን ሳሙኤል ሳኦልን እንደቀባው ነገስታቶች ም ተቀብተዋል ካህናቶችም ተቀብተዋል ነቢይም ተልዕኮውን ለማገልገል መቀባት ነበረበት::

ኢየሱስ ወደዚህ አለም መጥቶ ሦስት ተግባራቶችን ለማከናወን ተቀብቶ ነበር እነዚያ ተግባራቶችም የካህን የንጉስና የነቢይ ተግባራት ነበሩ እርሱ ሰማያዊ ካህን እንደ መሆኑ የሰዎችን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ ተጠመቀ::

እርሱ የአባቱን ፈቃድ በመታዘዝ ራሱን በአብ ፊት የሐጢያት ቁርባን አድርጎ አቀረበ *«እኔ መንገድም እውነትም ህይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ ማንም የለም»*

ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነትና በመስቀል ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በመውሰድ በእርሱ የምናምነውን ሰዎች አዳነን::

*«የስጋ ህይወት በደሙ ውስጥ ነውና» (ዘሌዋውያን 17:11)* ኢየሱስ ከጥምቀቱ በኂላ በመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰ በዚህም እኛ ምዕመናኖች መዳን እንችል ዘንድ ሕይወቱን በእግዚአብሄር ፊት የሐጢያት ደመወዝ አድርጎ አቀረበ::

በመስቀል ላይ ከሞተ በኂላ በሦስተኛው ቀን ተነሳ ወንጌልንም በግዞት ላሉት ነፍሶች ሰበከ ገና ያልተዋጁ ሰዎች በሐጢያት ግዞት ቤት ውስጥ ያሉ መንፈሳዊ እስረኞችን ይመስላሉ ለእነርሱ ኢየሱስ የወንጌልን እውነት የውሃውንና የደሙን ወንጌል ይሰብክላቸዋል እግዚአብሄር እኛን ለማዳን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሰጥቶናል በዚህ የሚያምን ማንኛውም ሰው ዳግም መወለድ ይችላል::

## የኢየሱስ ጥምቀትና ደሙ ኃጢያተኞችን ያድናቸዋል

*በእግዚብሔር ፊት በጎ ሕሊና ሊኖረን የሚችለው እንዴት ነው?*

*በኢየሱስ ጥምቀትና ደም እምነት ሲኖረን ነው::*

ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን ነው በ1ኛ ጴጥሮስ 3:21 ላይ እንዲህ ተመስክሮዋል *«ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ ያድነናል የሰውነትን እድፍ ለማስወገድ አይደለም*

*ለእግዚአብሔር የበጎ ህሊና ልመና ነው እንጂ፣ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ነው»* የኢየሱስ ጥምቀት ውሃ ለሐጢያተኞች ደህንነት ግዴታ ነው::

ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት እነዚህን ሐጢያቶች በራሱ ላይ በመውሰድ የሐጢያተኞችን ሁሉ ሐጢያቶች አስወግዶዋል በኢየሱስ ጥምቀት ታምናላችሁን? ልቦቻችን በእርሱ ጥምቀት አማካይነት ከሐጢያቶች ሁሉ ታጥበው እንደነጹ ታምናላችሁን? ልቦቻችን ከሐጢያቶች ሁሉ ታጥበው ነጽተዋል ስጋችን ግን አሁንም ሐጢያትን ይሰራል::

«ዳግም መወለድ» ማለት ሰውየው ሐጢያት አይሰራም ማለት አይደለም እኛ ዳግም የተወለድን ሰዎችም እንደዚሁ ሐጢያቶችን እንሰራለን ልቦቻችን ግን በእርሱ ጥምቀት ላይ ባለን እምነታችን የተነሳ ከሐጢያት ነጽተው ይቆያሉ ስለዚህ ከላይ የተጠቀሰው ምንባብ እንዲህ ይላል *«የሰውነትን እድፍ ለማስወገድ አይደለም ለእግዚአብሔ የበጎ ህሊና ልመና ነው እንጂ፣ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ነው::» (1ኛ ጴጥሮስ 3:21)*

ኢየሱስ ሐጢያቶቼን ስላነጻና እግዚአብሄርም ፍርድን ለእኔ ስለተቀበለ እንዴት በእርሱ አለማመን እችላለሁ? አምላክ የሆነው ኢየሱስ በጥምቀቱና በደሙ አማካይነት እንዳዳነኝ ካውቅሁ በኋላ እንዴት በእርሱ አለማመን እችላለሁ? እኛ በእግዚአብሄር ፊት ድነናል አሁን ሕሊናችን ንጹህ ነው እግዚአብሄር አይወደንም ብለን መናገር እንደማንችል ሁሉ በእግዚአብሄር ፊትም ዳግመኛ ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን ፈጽሞ አላነጻም ማለት አንችልም::

ዳግም ከተወለድን በኋላ ሕሊናዎቻችን ለሐጢያት ይበልጥ የሚቆጠቁጡ ይሆናሉ ስህተት በምናደርግበት ጊዜም ሁሉ ይነግሩናል ሕሊናዎቻችን ትንሽ እንኳን ከተጨናነቁ ራሳችንን

ስለ ኢየሱስ የጥምቀት ሐይል እስካላስታወስን ድረስ ሙሉ በሙሉ ከሐጢያት ነጻ መሆን አንችልም በጎ ሕሊናዎች ይኖሩን ዘንድ ብቸኛው መንገድ ይህ ነው::

ሕሊናዎቻችን ካስቸገሩን ይህ ማለት አንድ የተሳሳተ ነገር አለ ማለት ነው የኢየሱስ የጥምቀት ውሃ የሐጢያት ቆሻሻን ሁሉ አንጽቷል ኢየሱስ የሕሊናዎቻችንንም ሳይቀር ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱ ወስዶ አንጽቶዋቸዋል ይህንን በትክክል ስናምን ሕሊናዎቻችንንም በእውነት መንጻት ይችላሉ ሕሊናዎቻችን መንጻት የሚችሉት እንዴት ነው? በኢየሱስ ጥምቀትና ደም በማመን ነው እያንዳንዱ ሰው ከውልደቱ ጀምሮ ክፉና ቆሻሻ ሕሊና አለው ነገር ግን ሐጢያቶቻችን በሙሉ ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ ካመንን ያንን ነቁጥ መደምሰስ እንችላለን::

ዳግም የተወለዱ ሰዎች እምነት ይህ ነው ይህ ምናብ፣ አውቃችሁ የምታምኑት አንዳች ነገር አይደለም ሕሊናችሁ ንጹህ ነውን? ንጹህ የሆነው ጥሩ ሕይወት ስለኖራችሁ ነው ወይስ ንጹህ የሆነው ሐጢያቶቻችሁ በሙሉ ወደ ኢየሱስ ስለተላለፉና እናንተም በእርሱ ስለምታምኑ ነው? ንጹሕ ሕሊና ማግኘት የምትችሉት በዚህ እምነት አማካይነት ብቻ ነው::

ሕይወት ያላቸው ቃሎች አሉ ሕይወት የሌላቸውም ቃሎች አሉ የሰዎች ሁሉ ሕሊናዎች መንጻት የሚችሉት እንዴት ነው? እኛ ጻድቃን መሆንና በጎ ሕሊና መያዝ የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ምሉዕ በሆነው የኢየሱስ ቤዛነት ማመን ነው::

በእርሱ ጥምቀት ማመን ይቀድሰናል ማለት የስጋ ርኩሰት ተወግዶዋል ማለት ሳይሆን ሕሊናዎቻችን በእግዚአብሄር ዘንድ ነጽተዋል ማለት ነው እርሱ ለዚያ ሲል መጣ ተጠመቀ በመስቀል ላይ ሞተ ከሙታን ተነሳ አሁን በእግዚአብሄር ቀኝ ተቀምጦዋል::

ጊዜው ሲደርስ እንደገና ወደዚህ አለም ይመጣል *«እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ኃጢያት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢያት ይታይላቸዋል» (ዕብራውያን 9:28)* እርሱን በጉጉት የምንጠብቀውንና በእርሱ ጥምቀትና ደም በማመን ሐጢያት አልባ የሆነውን እኛን ለመውሰድ እንደሚመጣ እናምናለን::

## የእምነት ክሊኒካዊ ሙከራ

*ያለ ኢየሱስ ጥምቀት ልንድን እንችላለንን?*

*በፍጹም::*

እኛ በዳኤጆን ቤተክርስቲያን ክሊኒካዊና ያልታቀደ ሙከራ አድርገናል::

የዳኤጆኑ ቤተክርስቲያን ሬቨረንድ ፓርክ ለሆኑ ጥንዶች የኢየሱስን ጥምቀት ትርጉም ሳይጠቅስ በአለም ላይ ሐጢያት እንደሌለ ነገራቸው ባልየው ሌሎች ቤተክርስቲያኖች በሚሄድበት ጊዜ በስብከቶች ወቅት መተኛት ያዘወትራል ምክንያቱም መጋቢዎቹ ሁሉ በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት የሚገኘውን ቤዛነት በመግደፍ ወንጌል እየሰበኩ በየቀኑ ንስሐ እንዲገባ ያስገድዱት ነበር::

ነገር ግን በዚህ በዳኤጆን ቤተክርስቲያናችን ውስጥ ስብከቱን ያደመጠው ሁለቱንም አይኖቹን በልጥጦ ነበር ምክንያቱም ሐጢያቶቹ በሙሉ ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ

ተነግሮት ነበርና ይህም ሚስቱ ከእርስዋ ጋር አብሮ ቤተክርስቲያን ይሄድ ዘንድ ለማሳመን የምታደርገውን ጥረት አቀለለላት፡፡

አንድ ቀን ቤተክርስቲያን ውስጥ ተቀምጦ ሮሜ 8:1ን ሰማ *«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም»* ያን ጊዜ ወዲያውኑ «አሃ አንድ ሰው በኢየሱስ ካመነ ሐጢያት የለበትም እኔም በኢየሱስ ስለማምን ሐጢያት የለብኝም» ብሎ አሰበ፡፡

ስለዚህ ለዋርሳውና ለብዙዎቹ ጓደኞቹ አንድ በአንድ ስልክ ደውሎ «በልባችሁ ውስጥ ሐጢያት አለን? እንግዲያውስ እምነታችሁ ትክክል አይደለም» አላቸው በዚህ ጊዜ ሬቨረ. ፓርክ ግራ ተጋባ ባልየው ስለ ኢየሱስ ጥምቀት አላወቀም ነገር ግን አሁን ሐጢያት እንደሌለበት ይሚገት ነበር፡፡

ከዚያም ጥንዶቹ ችግሮች ይገጥሙዋቸው ጀመር ሚስቲቱ ይበልጥ ሐይማኖተኛ ነበረች ነገር ግን ባልዋ ሐጢያት እንደሌለበት ሲናገር እርስዋ ግን አሁንም ገና በልብዋ ውስጥ ሐጢያት ነበረባት ባልዋ ቤተክርስቲያን የሄደው ጥቂት ጊዜ ብቻ ነው ነገር ግን ያለ ሐጢያት ነበር፡፡

ሚስት ሁለቱም በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት እንዳለ እርግጠኛ ነበረች ስለዚህ ነገርም መከራከር ጀመሩ ባል *«በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉ አሁን ኩነኔ የለባቸውም»* ስለሚል ሐጢያት እንደሌለበት ተሚገተ ሚስትም አሁንም ገና በልብዋ ውስጥ ሐጢያት እንዳለ ተከራከረች፡፡

ከዚያ አንድ ቀን ሚስቱ በዚህ ጉዳይ በጣም ግራ ስለተጋባች ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ሬቨረ. ፓርክን ሄዳ ለመጠየቅ ወሰነች፡፡

ስለዚህ አንድ ቀን ከምሽት የአምልኮ አገልግሎት በኋላ ባልዋን ወደ ቤት እንዲሄድ ከሸኘችው በኋላ ሬቨረ. ፓርክን

ጥያቄ ለመጠየቅ ወደኋላ ቀረች እንዲህም አለች «አንድ ነገር ልትነግረን እየሞከርህ እንደሆነ አውቃለሁ ነገር ግን አንድ የተደበቀ አስፈላጊ ክፍል እንዳለ እርግጠኛ ነኝ እባክህ ምን እንደሆነ ንገረኝ» ያን ጊዜ ሬቨረ. ፓርክ ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ስለ መወለድ ነገራት::

በሮሜ 8:1 ላይ *«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም»* ተብሎ የተጻፈው ለምን እንደሆነ ወዲያውኑ ተረዳች ወዲያውም አመነችና ዳነች በመጨረሻም በክርስቶስ የሆኑት ሰዎች እንዳይኮነኑ ሐጢያቶቻችን በሙሉ ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ ተረዳች::

የተጻፈውን ቃልም መረዳት ጀመረች በመጨረሻም የቤዛነት ቁልፉ የኢየሱስ ጥምቀት እንደነበርና እኛም በእርሱ ጥምቀት ቤዛነት ጻድቃን መሆን እንደቻልን አወቀች::

ባልዋ ውጭ ሆኖ እርስዋን ሲጠብቃት ስለነበር ወደ ቤቱ አልሄደም ነበር ሐጢያቶችዋ በሙሉ የመንጻታቸውን ምስክርነቷን ሰምቶ በደስታ «አሁን ድነሻልን?» በማለት ጠየቃት::

ነገር ግን መጋቢው ለሚስቱ የነገራትን ከሰማ በኋላ ግራ ተጋባ ከዚህ በፊት ስለ ኢየሱስ ጥምቀት ወንጌል ፈጽሞ ሰምቶ አያውቅም ነበር ያለ ኢየሱስ ጥምቀትም ቢሆን እንኳን ከእንግዲህ ወዲህ በልቡ ውስጥ ሐጢያት እንደሌለ እርግጠኛ ነበር ስለዚህ በቤታቸው ውስጥ እንደገና ተከራከሩ::

በዚህ ጊዜ ሁኔታው ተገለበጠ ሚስት ባልዋን በልቡ ውስጥ ሐጢያት እንዳለ ወይም እንደሌለ ወጥራ ያዘችው በኢየሱስ ጥምቀት ሳያምን እንዴት ያለ ሐጢያት ሊሆን እንደቻለ ጠየቀችው ሕሊናውን በሚገባ እንዲመለከት ገፋፋችው ከዚያም ሕሊናውን ሲመረምር አሁንም ገና በልቡ ውስጥ ሐጢያት እንዳለበት ተገነዘበ::

ስለዚህ ወደ ሬቨረ. ፓርክ ሄዶ በልቡ ውስጥ ሐጢያት እንዳለ ተናዘዘ እርሱም «እጆቻቸውን በሚለቀቀው ፍየል ራስ ላይ በሚጭኑበት ጊዜ ይህንን የሚያደርጉት ከማረዳቸው በፊት ነው ወይስ ካረዱት በኋላ ነው?» ብሎ ጠየቀ እርሱ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በፍጹም ሰምቶ ስለማያውቅ በጣም ግራ ተጋብቶ ነበር።

የዚህ መንፈሳዊ ሙከራ ነጥብ ይህ ነበር ኢየሱስ የአለም ሁሉ ሐጢያቶች ወደ እርሱ እንዲተላለፉ መጠመቅ ነበረበት በመስቀል ላይ መሞት የሚችለው ያን ጊዜ ብቻ ነበር ምክንያቱም የሐጢያት ደመወዝ ሞት ነውና።

«እነርሱ እጆቻቸውን በመስዋዕቱ ራስ ላይ የሚጭኑት ከመገደሉ በፊት ነበር ወይስ በኋላ?» እርሱ ይህንን የጠየቀው ስለ እጆች መጫንና ስለ ኢየሱስ ጥምቀት ግራ ስለተጋባ ነበር ስለዚህ ሬቨረ. ፓርክ የኢየሱስን ጥምቀት ቤዛነት በዝርዝር አብራራለት።

በዚያች ቀን ባልየው ለመጀመሪያ ጊዜ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሰምቶ ተዋጀ አንድ ጊዜ ብቻ ወንጌልን ሰምቶ ዳነ።

ያ የኢየሱስን ጥምቀት በመግደፍ ላይ የተደረገ ሙከራ ነበር ሐጢያት የለብንም እንል ይሆናል ነገር ግን ያለ ኢየሱስ ጥምቀት አሁንም ገና በሕሊናችን ውስጥ ሐጢያት መኖሩ የተረጋገጠ ነው ብዙውን ጊዜ ሰዎች ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ሐጢያቶችን በሙሉ አንጽቷል ይላሉ ነገር ግን በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያት እንደሌለባቸው በተጨባጭ መናገር የሚችሉት በኢየሱስ ጥምቀትና ደም የሚያምኑ ሰዎች ብቻ ናቸው።

ሬቨረ. ፓርክ በኢየሱስ ጥምቀት በእምነት አማካይነት ከሚገኘው ቤዛነት ውጭ ፈጽሞ ከሐጢያቶቻችን መዋጀት እንደማንችል በእነዚህ ጥንዶች አረጋግጦዋል።

# የደህንነት ምሳሌ፡ የኢየሱስ ጥምቀት

*የደህንነት ምሳሌ ምንድን ነው?*

*የኢየሱስ ጥምቀት ነው::*

*«ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ ያድነናል»* ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለማንጻትና ሕሊናችንንም እንደ በረዶ ነጭ ለማድረግ ወደ አለማችን መጣ ኢየሱስ ሁሉንም በጥምቀቱ ስለወሰዳቸው ከሐጢያቶች ሁሉ ነጽተናል እርሱ በጥምቀቱና በደሙ አዳነን ስለዚህ ፍጥረታት በሙሉ በፊቱ መንበርከክ አለባቸው::

በኢየሱስ ማመን ያድነናል በኢየሱስ በማመን የእግዚአብሄር ልጆች እንሆናለን ሰማይም እንገባለን በኢየሱስ በማመን ጻድቃን እንሆናለን እኛ የንጉስ ክህነት ነን እግዚአብሄርን አባታችን ብለን መጥራት እንችላለን የምንኖረው በዚህ አለም ላይ ነው ነገር ግን ነገስታት ነን::

በእርግጥ እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ቤዛነት የምናምነውን ሰዎች እንዳዳነን ታምናላችሁን? ቤዛነታችን ያለ ኢየሱስ ጥምቀት ፈጽሞ ሙሉ ሊሆን አይችልም እግዚአብሄርና ኢየሱስ እውነተኛ ነው ብለው የሚቀበሉት እምነት ሙሉ በሙሉ ባዳነን በእርሱ ጥምቀት በመስቀሉና በመንፈሱ ማመን ነው ብቸኛው እውነተኛ እምነት ይህ ነው::

ሐጢያቶቻችን ኢየሱስ በጥምቀቱ በወሰዳቸው ጊዜ ነጽተዋል እርሱ በመስቀል ላይ ደሙን ባፈሰሰ ጊዜም ሐጢያቶቻችን በሙሉ ዋጋቸው ተከፍሎዋል ክርስቶስ ኢየሱስ በውሃና በመንፈስ አድኖናል አዎ! እናምናለን! ✉

# ስብከት 8

## የተትረፈረፈው ስርየት

---

## ወንጌል

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::



ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።

# የተትረፈረፈው ስርየት ወንጌል

**« ዮሐንስ 13፡1-17 »**

**«ኢየሱስም ከፋሲካ በአል በፊት ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት እንደደረሰ አውቆ በዚህ አለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው፡፡ እራትም ሲበሉ ዲያብሎስ በስምዖን ልጅ በአስቆሮቱ ይሁዳ ልብ አሳልፎ እንዲሰጠው አሳብ ካገባ በኋላ ኢየሱስ አብ ሁሉን በእጁ እንደ ሰጠው ከእግዚአብሔርም እንደወጣ ወደ እግዚአብሔርም እንዲሄድ አውቆ ከእራት ተነሳ ልብሱንም አኖረ ማበሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ በኋላም በመታጠቢያው ውኃ ጨመረ የደቀመዛሙርቱን እግር ሊያጥብና በታጠቀበትም ማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመር ወደ ሰምዖን ጴጥሮስም መጣ እርሱም፡— ጌታ ሆይ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን? አለው ኢየሱስም መልሶ፡—እኔ የማደርገውን አሁን አታውቅም በኋላ ግን ታስተውለዋህ አለው ጴጥሮስም፡- የእኔን እግር ለዘለዓለም አታጥብም አለው ኢየሱስም፡—ካላጠብኩህ ከእኔ ጋር እድል የለህም ብሎ መለሰለት ስምዖን ጴጥሮም፡—ጌታ ሆይ እጄንና ራሴን ደግሞ እንጂ እግሬን ብቻ አይደለም አለው ኢየሱስም፡— የታጠበ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም፣ ሁለንተናው ግን ንፁህ ነው እናንተም ንፁሐን ናችሁ ነገር ግን ሁላችሁ አይደላችሁም አለው አሳልፎ የሚሰጠውን ያውቅ ነበርና ስለዚህ ሁላችሁ ንፁሐን አይደላችሁም አለ፡፡**

**እግራቸውንም አጥቦ ልብሱንም አንስቶ ዳግመኛ ተቀመጠ እንዲህም አላቸው፡—ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? እናንተ**

**መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ እንግዲህ እኔ መምህርና ጌታ ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትጠጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና እውነት እውነት እላችኋለሁ ጌታ ከባርያው አይበልጥም መልዕክተኛም ከላከው አይበልጥም ይህን ብታውቁ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ።»**

ኢየሱስ ከፋሲካ በአል በፊት ባለው ቀን የጴጥሮስን እግር ያጠበው ለምንድነው? እግሮቹን ከማጠቡ በፊት ኢየሱስ እንዲህ አለ *«እኔ የማደርገውን አሁን አታውቅም በኋላ ግን ታስተውለዋለህ አለው»* ጴጥሮስ ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርቶች ምርጥ የተባለ ሰው ነበር ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደነበር አምኖ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደነበርም መስክሮዋል ኢየሱስ እግሩን ሲያጥበው ይህንን ያደረገበት ጥሩ ምክንያት ያለው መሆን አለበት ጴጥሮስ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ያለውን እምነት በመሰከረ ጊዜ ኢየሱስ እርሱን ከሐጢያቶቹ ሁሉ የሚያድነው አዳኝ መሆኑን እንዳመነ መናገሩ ነበር።

*ኢየሱስ ከመሰቀሉ በፊት*
*የደቀመዛሙርቱን እግር*
*ያጠበው ለምንድን ነው?*

*ምክንያቱም የእርሱን ፍጹም*
*ደህንነት እንዲረዱት*
*ስለፈለገ ነበር።*

የጴጥሮስን እግር ለምን አጠበ? ኢየሱስ ጴጥሮስ በቅርቡ ሦስት ጊዜ እንደሚክደውና ወደፊትም ሐጢያት መስራት እንደሚቀጥል ስላወቀ ነበር፡፡

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ጴጥሮስ በልቡ ውስጥ የቀረች አንዲት ሐጢያት ኖሮበት ቢሆን ኖሮ ከኢየሱስ ጋር ሊስማማ አይችልም ነበር ኢሱስ ግን የደቀመዛሙርቱን ድክመቶች በሙሉ ያውቅ ስለነበር ሐጢያቶቻቸው በእርሱና በደቀ መዛሙርቶቹ መካከል ጣልቃ እንዲገቡ አልፈለገም ስለዚህ ሐጢያቶቻቸው በሙሉ ቀድሞውኑም እንደነጹ ሊያስተምራቸው ፈለገ የደቀ መዛሙርቱን እግሮች ያጠበበት ምክንያቱ ያ ነበር ኢየሱስ ከመሞቱና ከእነርሱ ከመለየቱ በፊት በጥምቀቱ ወንጌልና በዕድሜ ዘመናቸው በሙሉ የሰሩዋቸው ሐጢያት ስርየትን በማግኘታቸው ላይ ጸንተው እንደሚቆሙ ማረጋገጥ ፈለገ፡፡

ዮሐንስ 13 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለፈጸመው ፍጹም ደህንነት ይናገራል ኢየሱስ እግሮቻቸውን እያተበ ሳለ ሰዎች ሁሉ ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ስለሚነጹበት የጥምቀቱ ወንጌል ጥበብ ነገራቸው፡፡

«ወደፊት በዲያብሎስ አትታለሉ በዮርዳኖስ ወንዝ በተቀበልኩት ጥምቀዬ ሐጢያቶቻችሁን በሙሉ ወስጃለሁ የእነርሱንም ፍርድ በመስቀል ላይ እቀበላለሁ ከዚያም ከሙታን እነሳለሁ ዳግም የመወለድን ደህንነት ለሁላችሁም እፈጽማለሁ የወደፊት ሐጢያቶቻችሁንም አስቀድሜ እንዳነጻሁ ላስተምራችሁ እውነተኛውን የሐጢያቶች ስርየት ወንጌል ላስተምራችሁ ከመሰቀሌ በፊት እግሮቻችሁን እያጠብሁ ነው ዳግም የመወለድ ወንጌል ምስጢሩ ይህ ነው እናንተም ሁላችሁ በዚህ ማመን አለባችሁ፡፡»

ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግሮች ያጠበበትንና «እኔ

*የማደርገውን አሁን አታውቅም በኋላ ግን ታስተውለዋለህ»* ያለበትን ምክንያት ሁላችንም መረዳት ይገባናል ዳግም በመወለጃው ወንጌል ማመንና ራሳችንም ዳግም መወለድ የምንችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው፡፡

## በዮሐንስ 13፡12 ላይ እንዲህ አለ

*መተላለፎች ምንድን ናቸው?*

*ከድክመታችን የተነሳ*
*በየቀኑ የምንሰራቸው ኃጢያቶች*
*ናቸው፡፡*

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከመሞቱ በፊት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን በአል በማክበር እግሮቻቸውን በራሱ እጆች በማጠብ ስለ ሐጢያቶች ስርየት ወንጌል አሳመናቸው፡፡

*«ኢየሱስ አብ ሁሉን በእጁ እንደ ሰጠው ከእግዚአብሔርም እንደወጣ ወደ እግዚአብሔርም እንዲሄድ አውቆ ከእራት ተነሳ ልብሱንም አኖረ ማበሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ በኋላም በመታጠቢያው ውኃ ጨመረ የደቀመዛሙርቱን እግር ሊያጥብና በታጠቀበትም ማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመር ወደ ሰምዖን ጴጥሮስም መጣ እርሱም፡—ጌታ ሆይ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን? አለው ኢየሱስም መልሶ፡—እኔ የማደርገውን አሁን አታውቅም፤ በኋላ ግን ታስተውለዋህ አለው፡፡» (ዮሐንስ 13፡3-7)*

ለደቀ መዛሙርቱም በጥምቀቱ ውሃ አማካይነት

የጥምቀትንና የሐጢያቶችን ስርየት ወንጌል አስተማራቸው፡፡

በወቅቱ ለኢየሱስ ታማኝ የሆነው ጴጥሮስ ጌታ ኢየሱስ ለምን እግሮቹን እንዳጠበው መረዳት አልቻለም ነበር ጴጥሮስ ኢየሱስ ለእርሱ ያደረገለትን በትክክል ከተረዳ በኋላ በኢየሱስ ያመነበት መንገድ ተለወጠ ኢየሱስ ስለ ሐጢያቶች ስርየት ስለ ጥምቀቱ ውሃ ወንጌል ሊያስተምረው ፈልጎ ነበር፡፡

በሌላ አነጋገር ኢየሱስ ወደፊት ከሚሰራቸው ሐጢያቶቹ ሁሉ ወደፊት በስጋው ከሚሰራቸው ሐጢያቶች የተነሳ ወደ እርሱ ሊቀርብ እንደማይችል ተጨንቆ ነበር ኢየሱስ እግሮቻቸውን ያተበው ዲያብሎስ የደቀ መዛሙርትን እምነት እንዳይነት ነበር በኋላም ጴጥሮስ ምክንያቱን ተረዳ፡፡

ኢየሱስ በእርሱ የጥምቀት ውሃና ደም ያመነ ማንኛውም ሰው ለዘላለም ከሐጢያቶቹ ሁሉ እንዲዋጅ መንገዱን አዘጋጀ፡፡

በዮሐንስ 13 ላይ የኢየሱስን እግሮች እያተበ ሳለ የተናገራቸው ቃሎች ተጽፈዋል እነዚህ ዳግም የተወለዱ ሰዎች ብቻ በትክክል ሊያስተውሉዋቸው የሚችሉዋቸው በጣም አስፈላጊ ቃሎች ናቸው፡፡

ኢየሱስ ከፋሲካ በአል በኋላ የደቀ መዛሙርቶቹን እግሮች ያጠበበት ምክንያት አስቀድሞ የዕድሜ ዘመናቸውን ሐጢያቶች በሙሉ እንዳጠበላቸው እንዲረዱ ለመርዳት ነበር ኢየሱስ «ለምን እግሮችህን እንደማጥብ አሁን አይገባህም ከዚህ በኋላ ግን ይገባሃል» አለ ለጴጥሮስ የተነገሩት እነዚህ ቃሎች በእርሱ ውስጥ ያለውን የዘላለም ቤዛነት እውነት ይዘዋል፡፡

ሐጢያቶቻችንንና በደሎቻችንን ሁሉ ያነጻውን የኢየሱስን ጥምቀት ሁላችንም ማወቅና ማመን አለብን ኢየሱስ በዮርዳኖስ የተቀበለው ጥምቀት እጆችን በመጫን ሐጢያቶችን የማስተላለፍ ወንጌል ነበር ሁላችንም በኢየሱስ ቃሎች ማመን አለብን እርሱ በጥምቀቱ አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች

በሙሉ ወሰደ በመኮነንና በመሰቀልም የሐጢያቶችን ስርየት አጠናቀቀ ኢየሱስ የተጠመቀው ሰዎችን ሁሉ ከሐጢያቶቻቸው ለማላቀቅ ነበር፡፡

## እድሜ ልካችንን የሰራናቸው መተላለፎች ሁሉ ስርየት በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ተፈጽሞዋል

*በጻድቃን ላይ የዲያቢሎስ «ወጥመድ» ምንድን ነው?*

*ዲያብሎስ ጻድቃንን እንደገና ኃጢያተኞች ለማድረግ ሊያታልላቸው ይሞክራል፡፡*

ኢየሱስ ከተሰቀለ ከተነሳና ወደ ሰማይ ካገ በኋላ ዲያብሎስና የውሸት እምነት አራማጆች መጥተው ደቀ መዛሙርትን ለማታለል እንደሚሞክሩ ያውቅ ነበር *«አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ»* በሚለው የጴጥሮስ ምስክርነት እርሱ በኢየሱስ እንዳመነ ማየት እንችላለን ነገር ግን ያም ሆኖ ኢየሱስ ጴጥሮስን የሐጢያቶችን ስርየት ወንጌል በልቡናው ውስጥ ጠብቆ እንዲይዝ ዳግመኛ ሊያስታውሰው ፈለገ ያ ወንጌል የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ የወሰደበት የኢየሱስ ጥምቀት ነበር ይህንንም እንደገና ለጴጥሮስ ለደቀ መዛሙርትና ለእኛም በኋላ ለምንመጣው ማስተማር ፈለገ *«እኔ የማደርገውን አሁን አታውቅም በኋላ ግን ታስተውለዋህ*

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሐጢያት በሚሰሩበት ጊዜ ሁሉ ዲያብሎስ «ተመልከት! አሁንም ድረስ ሐጢያቶችን የምትሰራ ከሆንህ እንዴት ሐጢያት የለብኝም ማለት ትችላለህ? አንተ አልዳንክም አንተ ሐጢያተኛ ነህ» በማለት ይፈትናቸውና ይኮንናቸው ነበር ኢየሱስ የዚህ አይነቱን በሽታ ለመከላከል በኢየሱስ ጥምቀት ላይ ያላቸው እምነት አስቀድሞ የዕድሜ ዘመን -- ያለፈውን የአሁኑንና የወደፊቱን ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ እንዳነጻ ነገራቸው።

«ሁላችሁም እኔ እንደተጠመቅሁ ታውቃላችሁ! እኔ በዮርዳኖስ የተጠመቅሁበት ምክንያቱ የዕድሜ ዘመን ሐጢያቶቻችሁን እንደዚሁም የሰውን ዘር የአዳም ሐጢያት ለማስወገድ ነበር አሁን ለምን እንደተጠመቅሁ ለምን በመስቀል ላይ መሰቀልና መሞት እንደነበረብኝ መረዳት ትችላላችሁን?» ኢየሱስ የደቀ መዛሙርትን እግር ያጠበው ዘወትር የሚሰሩዋቸውን ሐጢያቶች በጥምቀቱ አማካይነት እንደወሰደና የእነርሱንም ፍርድ በመስቀል ላይ እንደሚወስድ ሊያሳያቸው ነበር።

አሁን እናንተና እኔ የሐጢያቶቻችንን ሁሉ ስርየት እንድንቀበል በሚያስችለን በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ወንጌል ባለን እምነታችን ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ድነናል ኢየሱስ ስለ እኛ ተጠመቀ ተሰቀለም በጥምቀቱና በደሙ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ አነጻ የሐጢያቶችን ስርየት የሚያስገኘውን ወንጌል የሚያውቅ የሚያምንና በእውነት የሚያምን ማንኛውም ሰው ከሐጢያቶቹ ሁሉ ይድናል።

ታዲያ ዳግም የተወለዱ ሰዎች ከዳኑ በኋላ ምን ማድረግ አለባቸው? በየቀኑ ሐጢያቶቻቸውን ማመንና ለሐጢያቶቻቸው ሁሉ የስርየት ወንጌል በሆነው የኢየሱስ ጥምቀትና ደም ደህንነት ማመን ይኖርባቸዋል እኛ ዳግም የተወለድን ሰዎች

በአእምሮዋችን ውስጥ በጥልቀት ማተም ያለብን የሐጢያቶች ስርየት የሚገኝበትን ወንጌል ነው፡፡

ዳግመኛ ሐጢያት ስለሰራችሁ ያ ማለት እንደገና ሐጢያተኛ ናችሁ ማለት ነውን? አይደለም ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደ እያወቅን እንዴት እንደገና ሐጢያተኞች ልንሆን እንችላለን? የኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደሙ ለሐጢያቶቻችን ሁሉ ስርየትን ያስገኘ ወንጌል ነበር በዚህ በእውነተኛው የሐጢያቶች ስርየት ወንጌል የሚያምን ማንኛውም ሰው ያለ ምንም መገለል «ጻድቅ ሰው» ሆኖ ዳግመኛ ሊወለድ ይችላል፡፡

## ጻድቃን ዳግመኛ ፈጽሞ ኃጢያተኞች ሊሆኑ አይችሉም

*ጻድቃን ፈጽሞ ዳግም ኃጢያተኞች*
*የማይሆኑት ለምንድን ነው?*

*ምክንያቱም ኢየሱስ የእድሜ ልክ*
*ኃጢያቶቻቸውን በሙሉ አስቀድሞ*
*ስላስተሰረየላቸው ነው፡፡*

የሐጢያቶችን ስርየት በሚያመጣው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እያመናችሁ ነገር ግን አሁንም ገና በየቀኑ በምትሰሩዋቸው መተላለፎች ምክንያት ሐጢያተኛ እንደሆናችሁ የሚሰማችሁ ከሆነ ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለመውሰድ

ወደተጠመቀበት ወደ ዮርዳኖስ መሄድ ይኖርባችኋል የሐጢያቶቻችሁን ስርየት ከተቀበላችሁ በኋላ እንደገና ሐጢያተኞች ከሆናችሁ ኢየሱስ እንደገና መጠመቅ ሊኖርበት ነው በኢየሱስ የጥምቀት ወንጌል ባገኛችሁት የሐጢያቶቻችሁ ስርየት እምነት ሊኖራችሁ ያስፈልጋል ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት በአንድ ጊዜ ሐጢያቶቻችሁን በሙሉ እንደወሰደ ማስታወስ ይኖርባችኋል ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችሁ ስለመሆኑ የማያወላውል እምነት ሊኖራችሁ ይገባል፡፡

ኢየሱስን አዳኛችሁ አድርጋችሁ ማመን ማለት የዕድሜ ዘመናችሁን ሐጢያቶች በሙሉ በወሰደው የኢየሱስ ጥምቀት ማመን ማለት ነው በእርግጥም በእርሱ ጥምቀት መስቀል ሞትና በኢየሱስ ትንሳኤ የምታምኑ ከሆነ ምንም አይነት ሐጢያት ብትሰሩም ዳግመኛ ፈጽሞ ሐጢያተኛ ልትሆኑ አትችሉም በሕይወት ዘመናችሁ ከምትሰሩዋቸው ሐጢያቶች በሙሉ በእምነት ተዋጅታችኋል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ የወደፊት ሐጢያቶችን ከድክመቶቻችን የተነሳ የምንሰራቸውንም ሐጢያቶች ሳይቀር አንጽቶዋቸዋል ኢየሱስ የጥምቀቱን ጠቀሜታ ማጉላት ስለነበረበት የሐጢያቶችን ስርየት ወንጌል ማለትም የእርሱን ጥምቀት ለማመላከት የደቀ መዛሙርቱን እግሮች በውሃ አጠበ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሄር ለአለም ሐጢያቶች በሙሉ ቃል የገባውን የተትረፈረፈ ስርየት ለመፈጸምና የሰውን ዘር ሁሉ ለማዳን ተጠመቀ ተሰቀለ ተነሳ ወደ ሰማይም አረገ ከዚህ የተነሳ የእርሱ ደቀ መዛሙርት የሐጢያቶችን ስርየት ወንጌል የኢየሱስን ጥምቀት መስቀሉንና ትንሳኤውን እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ መስበክ ችለው ነበር፡፡

# የጴጥሮስ ስጋዊ ድክመት

*ጴጥሮስ ኢየሱስን የካደው ለምንድን ነው?*

*ምክንያቱም ደካማ ስለነበረ ነው።*

መጽሐፍ ቅዱስ ጴጥሮስ ከሊቀ ካህኑ ከቀያፋ ባሪያዎች ጋር በተገናኘና ከኢየሱስ ተከታዮች አንዱ እንደነበረ በተከሰሰ ጊዜ «ይህን ሰው አላውቀውም» በማለት ሁለት ጊዜ ካደ ከዚያም ይህንኑ እየማለና እየተገዘተ ለሦስተኛ ጊዜ ተናገረ።

ምንባቡን ከማቴዎስ 26፡69 እናንብበው *«ጴጥሮስም ከቤት ውጭ በአጥሩ ግቢ ተቀምጦ ነበር አንዲት ገረድም ወደ እርሱ ቀርባ አንተ ደግሞ ከገሊላው ከኢየሱስ ጋር ነበርህ አለችው እርሱ ግን፦ የምትይውን አላውቅም ብሎ በሁሉ ፊት ካደ ወደ በሩም ሲወጣ ሌላይቱ አየችውና በዚያ ላሉት ይህ ደግሞ ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር ነበር አለች ዳግመኛም ሲምል፦ ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ካደ ጥቂትም ቆይተው በዚያ የነበሩ ቀርበው ጴጥሮስን፦ አነጋገርህ ይገልጥሃልና በእውነት አንተ ደግሞ ከእነርሱ ወገን ነህ አሉት በዚያን ጊዜ ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ሊራገምና ሊምል ጀመረ ወዲያውም ዶሮ ጮኸ ጴጥሮስም፦ ዶሮ ሳይጮህ ሶስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው የኢየሱስ ቃል ትዝ አለው ወደ ውጭም ወጥቶ መራራ ለቅሶ አለቀሰ።» (ማቴዎስ 26፡69-75)*

ጴጥሮስ በኢየሱስ ማመኑ እርግጥ ነው በታማኝነትም ተከትሎታል ጌታ ኢየሱስ አዳኙና የሚመጣው «ነቢይ»

እንደነበርም አምኖዋል ነገር ግን ኢየሱስ ወደ ጲላጦስ ችሎት በተወሰደና ከኢየሱስ ጋር ያለውን ግንኙነት ለባለስልጣናቱ መግለጡ ለእርሱ አደገኛ ሲሆንበት በእነርሱ ፊት እየተራገመ ካደው::

ጴጥሮስ ኢየሱስን እንደሚክደው አላወቀም ነበር ኢየሱስ ግን እንደሚክደው አውቆ ነበር ኢየሱስ የጴጥሮስን ድክመት በሚገባ አውቆታል ስለዚህ ኢየሱስ የጴጥሮስን እግሮች አጠበ በዮሐንስ 13 ላይ እንደተጻፈውም «አንተ ወደፊትም ሐጢያት ትሰራለህ እኔ ግን አስቀድሜ የወደፊት ሐጢያቶችህንም እንኳን ሳይቀር አስወግጄልሃለሁ» በማለት በትውስታው ውስጥ የደህንነትን ወንጌል ቀረጸ::

ጴጥሮስ ሕይወቱ አደጋ ላይ ሲወድቅ በእርግጥም ኢየሱስን ካደው ይህንን እንዲያደርግ ያደረገው ግን የስጋው ድካም ነበር ስለዚህ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቶቹን ከወደፊት በደሎች ሁሉ ለማዳን ሲል አስቀድሞ እግሮቻቸውን አጠበ::

«እኔ የወደፊት ሐጢያቶቻችሁንም በሙሉ አስወግዳለሁ ስለተጠመቅሁና ሐጢያቶቻችሁን ስለወሰድሁ እስቀላለሁ ለሁላችሁም እውነተኛ አዳኝ ለመሆንም የሁሉንም ሐጢያቶች ዋጋ እከፍላለሁ በጥምቀቴና በደሜም እረኛችሁ እሆናለሁ እኔ የደህንነታችሁ እረኛ ነኝ::»

ኢየሱስ ይህንን እውነት በልቦቻቸው ውስጥ በጽኑ ለመትከል ሲል ከፋሲካ በአል በኋላ እግሮቻቸውን አጠበ የወንጌል እውነት ይህ ነው::

ዳግም ከተወለድን በኋላም ቢሆን ስጋችን ደካማ ስለሆነ እንደገና ሐጢያት እንሰራለን በእርግጥም ሐጢያት መስራት አይገባንም ነበር ነገር ግን ጴጥሮስ እንደገጠመው አይነት ከበድ ያሉ ችግሮች በሚገጥሙን ጊዜ እንደዚያ ለማደረግ ባናስብም ሐጢያትን ወደ መስራት እናዘነብላለን የምንኖረው በስጋ ነው

ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ በሐጢያቶቻችን ወደ ጥፋት እንገሰግሳለን በዚህ ስጋዊ አለም ላይ እስከኖርን ድረስ ስጋ ሐጢያትን ይሰራል ነገር ግን ኢየሱስ እነዚያን ሐጢያቶች በሙሉ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ አስወግዶዋቸዋል፡፡

ኢየሱስ አዳኛችን እንደሆነ አንክድም ነገር ግን በስጋ ስንኖር ከእግዚአብሄር ፈቃድ ጋር የሚቃረኑ ሐጢያቶችን በመስራት እንቀጥላለን ይህ የሆነበት ምክንያት ከስጋ ስለተወለድን ነው፡፡

ኢየሱስ በስጋ ስንኖር ሐጢያቶችን እንደምንሰራ በሚገባ ስላወቀ በጥምቀቱና በደሙ የሐጢያቶቻችንን ዋጋ በመክፈል አዳኛችን ሆነ እርሱ በደህንነቱና በትንሳኤው የሚያምኑ ሰዎችን ሁሉ ሐጢያቶች አስወግዶዋል፡፡

አራቱም ወንጌሎች በሙሉ በአጥማቂው ዮሐንስ በሆነው የኢየሱስ ጥምቀት የሚጀምሩት ለዚህ ነው የእርሱ ሰብአዊ ሕይወት አላማ የደህንነት ወንጌል የሆነውን ዳግም የመወለድ ወንጌል መፈጸም ነበር፡፡

*በስጋ ኃጢያትን የምንሰራው እስከመቼ ነው?*

*እስከምንሞትበት ቀን ድረስ በሕይወታችን ሁሉ ኃጢያትን እንሰራለን፡፡*

ጴጥሮስ አውራ ዶሮ ሳይጮህ በፊት እርሱን አንድ ጊዜ ሳይሆን ሁለት ጊዜም ሳይሆን ሦስት ጊዜ በካደው ጊዜ ልቡ

ምንኛ ተሰብሮ ነበር! ምንኛ አፍሮ ነበር? በኢየሱስ ፊት ፈጽሞ እንደማይክደው ምሎ ነበር ሐጢያት የሰራው ከስጋው ድክመት የተነሳ ነው በድካሙ ተሸንፎ ኢየሱስን አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሦስት ጊዜ በመካዱ ምንኛ የኀስቋላነት ስሜት ተሰምቶት ነበር? ኢየሱስ እንደገና በርህራሄ በተመለከተው ጊዜ ምንኛ የሐዘን ስሜት ተሰምቶት ነበር?

ኢየሱስ ግን እነዚህን ነገሮችና ሌሎችንም አውቆ ነበር ስለዚህ እንዲህ አለ *«ደጋግመህ ሐጢያት እንደምትሰራ አውቃለሁ ነገር ግን ሐጢያቶችህ እንዳያሰናክሉህና ሐጢያተኛ እንዳዳያደርጉህ ወደ እኔ መመለስም እንዳያስቸግርህ እነዚያን ሐጢያቶች በሙሉ አስቀድሜ በጥምቀቴ ወስጃለሁ በመጠመቅና ለሐጢያቶችህ ሁሉ በመኮነን ፍጹም አዳኝህ ሆኛለሁ አምላክህና እረኛህ ሆኛለሁ በሐጢያቶችህ ስርየት ወንጌል እመን የስጋ ሐጢያቶችን በተደጋጋሚ ብትሰራም አንተን መውደዬን እቀጥላለሁ ቀድሞውኑም በደሎችህን ሁሉ አንጽቻለሁ የሐጢያቶች ስርየት ወንጌል ለዘላለም ውጤታማ ነው እኔ ለአንተ ያለኝ ፍቅርም እንደዚሁ ዘላለማዊ ነው፡፡»*

ኢየሱስ ለጴጥሮስና ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል ነገራቸው *«ካላጠብኩህ ከእኔ ጋር እድል የለህም»* እርሱ በዮሐንስ 13 ላይ ስለሚገኘው ስለዚህ ወንጌል የተናገረበት ምክንያት ሰዎች ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ዳግም መወለዳቸው አስፈላጊ ስለሆነ ነበር በዚህ ታምናላችሁን?

በቁጥር 9 ላይ ደግሞ *«ስምዖን ጴጥሮም፦—ጌታ ሆይ እጄንና ራሴን ደግሞ እንጂ እግሬን ብቻ አይደለም አለው ኢየሱስም፦—የታጠበ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም ሁለንተናው ግን ንፁህ ነው እናንተም ንፁሐን ናችሁ ነገር ግን ሁላችሁ አይደላችሁም አለው፡፡»*

ውድ ወዳጆች ወደፊት «የስጋ» ሐጢያቶችን ትሰራላችሁን?

ወይስ አትሰሩም? በእርግጥም ትሰራላችሁ ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ቀድሞውኑም የወደፊት ሐጢያቶችን የስጋችንን በደሎች ሁሉ ሳይቀር በጥምቀቱና በደሙ እንዳነጻ ተናግሮዋል ከመሰቀሉ በፊትም ለደቀ መዛሙርቱ የእውነትን ቃል የስርየትን ወንጌል በግልጽ ነግሮዋቸዋል፡፡

እኛ ከድክመቶቻችን ሁሉ ጋር በስጋችን ስለምንኖር ሐጢያት እንሰራለን ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በጥምቀቱ አንጽቷል እርሱ ያጠበው ራሶቻችንንና ሰውነቶቻችንን ብቻ ሳይሆን እግሮቻችንንም ማለትም የወደፊት ሐጢያቶቻችንንም ሁሉ ነው ዳግም የመወለድ የኢየሱስ ጥምቀት ወንጌል ይህ ነው፡፡

ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ አጥማቂው ዮሐንስ እንዲህ ሲል መሰከረ *«እነሆ! የዓለምን ኃጢያት ሁሉ የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!» (ዮሐንስ 1፡29)* እኛም የአለም ሐጢያቶች በሙሉ በጥምቀቱ ወቅት ወደ ኢየሱስ ተላልፈው እንደነጹ ማመን አለብን፡፡

በዚህ ሐጢያተኛ አለም ላይ ስንኖር ሐጢያት እንሰራለን ያ ግልጽ ሐቅ ነው የስጋ ድክመቶቻችን በሚገለጡበት ጊዜ ሁሉ ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉና የአለምን ሐጢያቶችም በሙሉ በስርየት ወንጌል እንዳነጻና በደሙም ዋጋቸውን እንደከፈለ ራሳችንን ማስታወስ ይኖርብናል ከልባችን ለእርሱ ምስጋናን ማቅረብ ይገባናል ኢየሱስ አዳኛችንና እግዚአብሄር እንደሆነ በእምነት እንናዘዝ ጌታ ይመስገን፡፡

በዚህ አለም ላይ የሚኖር እያንዳንዱ ሰው በስጋው ሐጢያቶችን ከመስራት በቀር ሊያደርገው የሚችለው ነገር የለም ሰዎች በስጋቸው ያለ ማቋረጥ ሐጢያት ይሰሩና በዕድሜ ዘመናቸው በሰሩዋቸው ሐጢያቶች ይሞታሉ፡፡

## በሰዎች ልብ ውስጥ ያሉ ክፉ ሃሳቦች

*ሰውን የሚያረክሰው ምንድን ነው?*

*የተለያዩ ኃጢያቶችና ክፉ ሃሳቦች ናቸው::*

ኢየሱስ በማቴዎስ 15:19-20 ላይ እንዲህ ይላል *«ከልብ ክፉ አሳብ መግደል፣ ዝሙት፣ ምንዝርነት፣ መስረቅ፣ በውሸት መመስከር፣ ስድብ ይወጣልና ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው እንጂ ባልታጠበ እጅ መብላት ሰውን አያረክሰውም»* በሰው ልብ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የሐጢያት አይነቶች እርሱን ያረክሱታል ንፁህ እንዳይሆንም ያደርገዋል::

## አንድ ሰው የራሱን ክፉ ተፈጥሮ ማወቅ አለበት

*በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ያለው ምንድን ነው?*

*አስራ ሁለት አይነት ኃጢያቶች ናቸው::*
*(ማርቆስ 7:21-23)*

እኛ «እነዚያ አስራ ሁለት አይነት ሐጢያቶች በሰዎች

ልቦች ውስጥ አሉ በእኔም ልብ ውስጥ ሁሉም አሉ በውስጤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉት አስራ ሁለት አይነት ሐጢያቶች አሉብኝ» ማለት መቻል ይኖርብናል ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ዳግም ከመወለዳችን በፊት ቀድሞውኑም ሐጢያቶች በልቦቻችን ውስጥ እንዳሉ ማመን ይኖርብናል እኛ በእግዚአብሄር ፊት ሙሉ ሐጢያተኞች እንደሆንን መቀበል ይኖርብናል ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ያንን አናደርግም ብዙዎቻችንን «በልቤ ውስጥ እነዚያ አሳቦች ፈጽሞ አልነበሩም ለጊዜው ተሳስቼ ነበር» በማለት ለሐጢያቶቻችንን ምክንያቶችን እናቀርባለን፡፡

ኢየሱስ ግን ስለ ሰዎች ምን አለ? እርሱ ከሰው ልብ የሚወጣው እርሱን እንደሚያረክሰው በግልጽ ተናግሮዋል ሰዎች በውስጣቸው ክፉ አሳቦች እንዳላቸው ነግሮናል ምን ይመስላችኋል? እናንተ ጥሩ ናችሁ ወይስ ክፉ? እያንዳንዱ ሰው ክፉ አሳቦች እንዳሉት ታውቃላችሁን? አዎ የእያንዳንዱ ሰው አሳቦች ክፉ ናቸው፡፡

ከጥቂት አመታቶች በፊት በሴኡል ያለ አንድ ግዙፍ መጋዘን በድንገት ተደረመሰ ውዶቻቸውን ያጡ ቤተሰቦች ሐዘናቸው ጥልቅ ነበር ነገር ግን ብዙ ሰዎች አሳዛኝ በሆነው ትዕይንት ለመደሰት ወደዚያ ሄደው ነበር፡፡

አንዳንዶች «ምን ያህል ሰዎች ሞቱ? 200? አይደለም ያ ቁጥር ትንሽ ነው ምናልባት 300? የሞቱት ሰዎች ቁጥር ቢያንስ አንድ ሺህ ቢሆን በጣም የሚያስደስትና የሚያስደንቅ በሆነ ነበር...» ብለው አስበዋል የሰዎች ልቦች እንደዚህ ክፉ ሊሆኑ ይችላሉ ይህንን ልንቀበለው ይገባናል ይህ ለሙታን እንዴት ያለ ንቀት ነበር! ለቤተሰቦቻቸውም እንዴት ያለ ዱብ ዕዳ ነበር! አንዳንዶቹ በገንዘብ አቅምም ፈራርሰዋል፡፡

ከተመልካቾቹ አንዳንዶቹ በጣም አስተዛዛኞች አልነበሩም

«ብዙ ሞተው ቢሆን ኖሮ ይበልጥ ያስደስት ነበር! እንዴት ያለ ትዕይንት ነው! በሰዎች በተሞላው ቦልፓርክ ላይ ተመሳሳይ ነገር ቢከሰትስ? በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከፍርስራሽ በታች ይቀበሩ ነበር አይደል? አዎ! ያ በእርግጥ ከዚህም የበለጠ አስደሳች በሆነ ነበር!» ምናልባት አንዳንዶች እንዲህ አይነት አሳቦች ነበሩዋቸው ስለ መኪና አደጋዎችም ተመሳሳይ ነገር ሊሰማ ይችላል የጓጉ ተመልካቾች በትናንሽ ግጭቶች ወደ አለመደሰቱ ያዘነብላሉ፡፡

ሁላችንም አንዳንድ ጊዜ ምን ያህል ክፉዎች እንደምንሆን እናውቃለን እነዚህን ክፉ አሳቦች ፈጽሞ ጮክ ብለን እንደማንናገራቸው የታወቀ ነው በአጋጣሚ አንድ አደጋ ስንመለከት ከንፈሮቻችንን እንመጥና ሐዘኔታችንን እንገልጥ ይሆናል ነገር ግን በድብቅ በልቦቻችን ውስጥ አደጋው ይበልጥ አስገራሚ እንዲሆን እንናፍቃለን ከእኛ ፍላጎቶች ጋር እስካልተቃረነ ድረስ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የሚገደሉባቸው አሰቃቂ አደጋዎችን ማየት እንፈልጋለን የሰዎች ልብ የሚሰራበት መንገድ ይህ ነው አብዛኞቻችን ዳግም ከመወለዳችን በፊት እንደዚህ ነበርን፡፡

## በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ያለ ነፍስ መግደል

*ለምን ኃጢያት*
*እንሰራለን?*

*ምክንያቱም በልቦቻችን ውስጥ*
*ክፉ አሳቦች ስላሉብን ነው፡፡*

እግዚአብሄር በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ነፍስ መግደል እንዳለ ነግሮናል ነገር ግን ብዙዎች «እንዴት እንደዚያ ትላለህ! በልቤ ውስጥ ምንም ነፍስ የማጥፋት አሳብ የለም! እንዴት እንደዚህ አይነት ሰው አድርገህ ትመለከተኛለህ!» በማለት ይህንን በእግዚአብሄር ፊት ይክዳሉ በልቦቻቸው ውስጥ ነፍስ መግደል እንዳለ በጭራሽ አያምኑም ነፍሰ ገዳዮች ከእነርሱ የተለዩ ዘሮች እንደሆኑ ያስባሉ፡፡

«በሌላ ቀን በዜና የተነገረው ክፉ ነፍሰ ገዳይ ከመሬት በታች ባሉት ቤቶቻቸው ውስጥ ሳሉ ሰዎችን የገደሉትና ያቃጠሉት ወሮበሎች በልቦቻቸው ውስጥ ነፍስ ማጥፋት ያለባቸው ሰዎች ናቸው! እነርሱ ልዩ ዲቃላ ናቸው እኔ በፍጹም እነርሱን አልመስልም! እነርሱ አረመኔዎች ናቸው! ነፍሰ ገዳዮች ናቸው!» እነርሱ በወንጀለኞች ላይ ተቆጥተው «ከክፉ ዘር የተወለዱ ሰዎች ከዚህ ምድር ላይ ተጠርገው መወገድ አለባቸው! ሁሉም ሞት ሊፈረድባቸው ይገባል!» በማለት ይጮኃሉ፡፡

ነገር ግን የመግደል አሳብ በእነዚያ የተቆጡ ሰዎች ልቦች እንደዚሁም አረመኔ በሆኑ ገዳዮችና ነፍስ አጥፊዎች ልቦች ውስጥ አሉ እግዚአብሄር በሰዎች ሁሉ ልቦች ውስጥ መግደል እንዳለ ነግሮናል እኛ በልቦናዎቻችን ውስጥ የተደበቁትን ነገሮች እንኳን የሚያውቀውን የእግዚአብሄር ቃል መቀበል አለብን ስለዚህ «እኔ በልቤ ውስጥ የመግደል ሐጢያት ያለብኝ ሰው ነኝ» በማለት ማመን ይኖርብናል፡፡

አዎ እግዚአብሄር በሰዎች ሁሉ ልቦች ውስጥ ነፍስን መግደል ጨምሮ ክፉ አሳቦች እንዳሉ ነግሮናል የእግዚአብሄርን ቃል እንቀበል የሰዎች ትውልዶች ይበልጥ ክፉ ሲሆኑ ሁሉም አይነት ራስን የመጠበቂያ መሳሪያዎች የግድያ መሳሪያዎች ይሆናሉ ይህም በልቦቻችንን ውስጥ ያለው ነፍስን የማጥፋት

ውጤት ነው በቁጣ ወይም በፍርሃት ነፍስ ልታጠፉ ትችላላችሁ እያንዳንዳችን በእርግጥም ሌሎችን እንገድላለን ማለቴ አይደለም ነገር ግን በልቦቻችንን ስለ ግድያ እናስባለን፡፡

ሁላችንም በልቦቻችን ውስጥ ክፉ አሳቦችን ይዘን ተወልደናል አንዳንዶች በእርግጥም ይገድላሉ ይህንን የሚያደርጉት በተለየ ሁኔታ ነፍሰ ገዳዮች ሆነው ስለተወለዱ ሳይሆን ሁላችንም ነፍሰ ገዳዮች የመሆን አቅም ስላለን ነው እግዚአብሄር እኛ በልቦቻችን ውስጥ ክፉ አሳቦችና ነፍስን መግደል እንዳለ ነግሮናል ይህ እውነት ነው ማናችንም ከዚህ እውነት ውጭ አይደለንም፡፡

ስለዚህ እኛ ልንወስደው የሚገባን ትክክለኛው መንገድ የእግዚአብሄርን ቃል መቀበልና መታዘዝ ነው በዚህ አለም ላይ ሐጢያትን የምንሰራው በልቦቻችን ውስጥ ክፉ አሳቦች ስላሉ ነው፡፡

## በልቦቻችን ውስጥ ያለ አመንዝራነት

እግዚአብሄር በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ምንዝርና እንዳለ ተናግሮዋል ትስማማላችሁን? በልባችሁ ውስጥ ምንዝርና እንዳለ ታምናላችሁን? አዎ በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ምንዝርና አለ፡፡

በማህበረሰባችን ውስጥ ሴተኛ አዳሪነትና ሌሎች የግብረ ስጋ ግንኙነት ግድፈቶች የበዙት ለዚህ ነው ይህ በሰው ታሪክ በእያንዳንዱ ዘመን ውስጥ ገንዘብ ከሚገኝባቸው እጅግ አስተማማኝ መንገዶች አንዱ ነው ሌሎች የንግድ ስራዎች በኢኮኖሚ ችግር ሊመቱ ይችሉ ይሆናል እነዚህ የረከሱ የንግድ ስራዎች ግን ብዙም አይጎዱም ምክንያቱም በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ምንዝርና አለና፡፡

# የኃጢያተኞች ፍሬ ኃጢያት ነው

*የሰው ልጅ የሚነጻጸረው*
*ከምን ጋር ነው?*

*የኃጢያት ፍሬዎችን ብቻ ከሚያፈራ*
*ዛፍ ጋር ነው::*

የአፕል ዛፎች አፕልን የፒር ዛፎች ፒርን የቴምር ዛፎች ቴምርን የፐርሲሞን ዛፎችም ፐርሲሞንን ብቻ እንደሚያፈሩ ሁሉ በልቦቻችን ውስጥ 12 ሐጢያቶችን ይዘን ዳግም የተወለድነው እኛም ማፍራት የምንችለው የሐጢያት ፍሬዎችን ነው::

ኢየሱስ ከሰው ልብ የሚወጣው እርሱን እንደሚያረክሰው ተናግሮዋል ትስማማላችሁን? እኛ ከኢየሱስ ቃሎች ጋር ብቻ በመስማማት «አዎ እኛ የሐጢያተኞች ዘሮች ክፉ አድራጊዎች ነን አዎ ጌታ ሆይ አንተ ትክክል ነህ» ማለት እንችላለን አዎ ክፋቶቻችንን ማመን አለብን በእግዚአብሄር ፊት እውነቱን ለራሳችን መቀበል ይኖርብናል::

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄርን ፈቃድ እንደታዘዘ እኛም የእግዚአብሄርን ቃል መቀበልና እርሱን መታዘዝ ይኖርብናል በውሃውና በመንፈሱ አማካይነት ከሐጢያቶቻችንን ሁሉ መዳን የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው እነዚህ ከእግዚአብሄር የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው::

አገሬ በአራት ውብ ወቅቶች ተባርካለች ወቅቶች

ሲለዋወጡም የተለያዩ አይነት ዛፎች ፍሬዎቻቸውን ያፈራሉ በተመሳሳይ መንገድ በልቦቻችን ውስጥ ያሉት አስራ ሁለት ሐጢያቶች እኛን አጥብቀው ይይዙናል ያለ ማቋረጥም ወደ ሐጢያት ይነዱናል ዛሬ ልቦቻችንን ጨብጦ የያዘው ነፍስ ማጥፋት ይሆናል ነገ ደግሞ ምንዝርና ይሆናል፡፡

ከዚያን በቀጣዩ ቀን ክፉ አሳቦች ከዚያም ዝሙት ስርቆት በሐሰት መመስከርና...ወ.ዘ.ተ ይሆናል አመቱን ሙሉ በየወሩ በየቀኑ በየሰአቱ ሐጢያት መስራታችንን እንቀጥላለን አንዳች ሐጢያት ሳንሰራ ቀኑ አያልፍብንም ሐጢያት እንደማንሰራ ለራሳችን እንምላለን ነገር ግን ልንዘልቅበት አንችልም ምክንያቱም የተወለድነው በዚህ መንገድ ነውና፡፡

አንድ የአፕል ዛፍ ማፍራት ስላልፈለገ የአፕል ፍሬዎችን ማፍራት እምቢ ሲል አይታችሁ ታውቃላችሁን? «አፕሎችን ማፍራት አልፈልግም!» ፍሬ ማፍራቱን እምቢ ቢል እንኳን እንዴት አፕሎችን ማፍራት አይቻለውም? በጸደይ አበቦች ማበባቸው አፕሎችም ማደጋቸውና በበጋም ማፍራታቸው አይቀርም በበልግም ፍሬዎቹ ተለቅመው ለመበላት ዝግጁ ይሆናሉ፡፡

ይህ የተፈጥሮ ችሮታ ነው የሐጢያተኞችም ሕይወት እንደዚሁ ተመሳሳይ የሆነ የተፈጥሮ ሕግን መከተል አለበት ሐጢያተኞች የሐጢያትን ፍሬዎች ከማፍራት በቀር ምንም ነገር ማድረግ አይችሉም፡፡

# «የኢየሱስ ጥምቀትና መስቀሉ» ኃጢያቶቻችን ማስተሰረይ ነበረባቸው

*የኢየሱስ «ስርየት»*
*ማለት ምን ማለት ነው?*

*ይህ በኢየሱስ ጥምቀትና (በእጆች መጫን)*
*በመስቀሉ ላይ ደሙ የኃጢያትን*
*ደመወዝ መክፈል ነው::*

የክፉ አድራጊዎች ዘር የሆኑት ሐጢያተኞች በእግዚአብሄር ፊት እንዴት ሐጢያቶቻቸውን ማስተሰረይ እንደሚችሉና ሕይወታቸውንም በደስታ እንደሚኖሩ ለማወቅ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ምንባብ እናንብብ ይህ የሐጢያቶች ስርየት የሚገኝበት ወንጌል ነው::

በዘሌዋውያን 4 ላይ እንዲህ ተብሎዋል *«ከአገሩ ሕዝብም አንድ ሰው ኃጢያትን ሳያውቅ ቢሰራ እግዚአብሔርም አትስራ ያለውን ትእዛዝ ቢተላለፍ ቢበድልም ለእርሱም የሰራው ኃጢኣት ቢታወቀው ስለ ሰራው ኃጢያት ነውር የሌለባትን ፍየል ለቁርባኑ ያመጣል እጁንም በኃጢአት መስዋዕት ራስ ላይ ይጭናል የሚቃጠልም መስዋዕት በሚታረድበት ስፍራ የኃጢያትን መስዋዕት ያርዳል ካህኑም ከደምዋ በጣቱ ወስዶ ለሚቃጠል መስዋዕት በሚሆነው መሠዊያ ቀንዶች ላይ ያደርገዋል ደሙንም ሁሉ ከመሠዊያው በታች ያፈሰዋል ስቡም ከደኅንነት መሥዋዕት ላይ እንደሚወሰድ ስብዋን ሁሉ ይወስዳል ካህኑም ስለ እርሱ ያስተሰርያል እርሱም ይቅር ይባላል::» (ዘሌዋውያን 4:27-31)*

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ለሐጢያቶቻቸው ስርየትን የሚያገኙት እንዴት ነበር? በመጀመሪያ እጆቻቸውን በሐጢያት ቁርባኑ ራስ ላይ ይጭኑና ሐጢያቶቻቸውን ወደ እርሱ ያስተላልፋሉ፡፡

በዘሌዋውያን ላይ እንደተፃፈውም፡- *«ከእናንተ ማናቸውም ሰው ለእግዚአብሔር መባን ሲያቀርብ መባችሁን ከእንስሳ ወገን ከላሞች ወይም ከበጎች ታቀርባላችሁ መባውም የሚቃጠል መሥዋዕት ከላሞች መንጋ ቢሆን ነውር የሌለበትን ተባቱን ያቀርባል በእግዚአብሔር ፊት እንዲሰምር በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ፊት ያቀርበዋል እጁንም በሚቃጠለው መስዋዕት ራስ ላይ ይጭናል ያስተሰርይለትም ዘንድ የሠመረ ይሆንለታል፡፡» (ዘሌዋውያን 1:2-4)*

በዚያ ዘመን የሚኖር አንድ ሰው በልቡ ውስጥ ሐጢያት እንዳለ ካወቀ ለሐጢያት ስርየት ጥቅም ላይ የሚውሉ የሐጢያት ቁርባኖችን ማዘጋጀት ነበረበት የሰራቸውን ሐጢያቶች ለማስተላለፍም በሐጢያት መስዋዕቱ ራስ ላይ «እጆቹን መጫን» ነበረበት በቅዱሱ የመገናኛው ድንኳን አደባባይ ውስጥ የሚቃጠል መስዋዕት መሰውያ ነበር ይህም ሳጥን የሚመስል ከአንድ የምስባክ ጠረጴዛ ትንሽ የሚተልቅ ነበር በእያንዳንዱ ማዕዘን ላይም ቀንዶች ነበሩት የእስራኤል ሕዝብ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት የሚያገኙት ሐጢያቶቻቸውን ወደ ሐጢያት መስዋዕቱ ራስ ላይ በማስተላለፍና ስጋውን በሚቃጠለው መስዋዕት መሰውያ ላይ በማቃጠል ነበር፡፡

እግዚአብሄር በዘሌዋውያን ውስጥ ለሕዝቡ *«በእግዚአብሔር ፊት እንዲሰምር በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ፊት ያቀርበዋል»* ተናግሮዋል እጆቻቸውን በራሱ ላይ በሚጭኑበት ጊዜ የእነርሱ ሐጢያቶች ወደ ሐጢያት መስዋዕቱ ይተላለፉ ነበር ከዚያም ሐጢያተኛው የመስዋዕቱን ጉሮሮ ይቆርጥና ደሙን

በሚቃጠለው መስዋዕት መሰውያ ቀንዶች ላይ ይቀባል፡፡

ከዚያ በኋላ የመስዋዕቱ በድን በውስጡ ካሉት ብልቶቹ ይጸዳና ስጋው ተቆራርጦ በሚቃጠለው መስዋዕት መሰውያ ላይ አመድ እስኪሆን ድረስ ይቃጠላል ከዚያም የስጋው ጣፋጭ ሽታ ለስርየታቸው ይሆን ዘንድ ለእግዚአብሄር ይቀርባል የዘወትር ሐጢያቶቻቸውን የሚያስተሰርዩት እንዲህ ነበር፡፡

እግዚአብሄር ለአመታዊ ሐጢያቶቻቸው ሌላ የስርየት መስዋዕትን ፈቅዶዋል ይህ ለዘወትር ሐጢያቶች ከሚቀርበው የስርየት መስዋዕት ይለያል በዚህ ሁኔታ ሊቀ ካህኑ ብቻ የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ ወክሎ እጆቹን በሐጢያት መስዋዕቱ ላይ ይጭንና በስርየት መክደኛው በስተ ምስራቅ ደሙን ሰባት ጊዜ ይረጨዋል እንደዚሁም ሕያው በሆነው ፍየል ራስ ላይ እጆቹን መጫኑ በየአመቱ በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ይደረጋል፡፡ **(ዘሌዋውያን 16፡5-27)**

*የብሉይ ኪዳን የሐጢያት ቁርባን የሚያመለክተው ማንን ነው?*

*ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፡፡*

አሁን የመስዋዕቱ ስርየት በአዲስ ኪዳን እንዴት እንደተለወጠና የእግዚአብሄር ዘላለማዊ ስርአትም በአመታት ውስጥ እንዴት እንዳልተለወጠ እንመልከት፡፡

ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት የነበረበት ለምንድነው? እግዚአብሄር ልጁ በመስቀል ላይ ይሞት ዘንድ የፈቀደው እርሱ

በምድር ላይ ምን ስህተት ስለሰራ ነበር? በመስቀል ላይ እንዲሞትስ ማን አስገደደው? የአለም ሐጢያተኞች ማለትም ሁላችንም በሐጢያት ውስጥ ወድቀን ሳለን ኢየሱስ ሊያድነን ወደዚህ አለም መጣ::

እርሱ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ ተጠመቀ በሰው ዘር ፋንታም ለሐጢያቶች ሁሉ በመስቀል ላይ ቅጣትን ተቀበለ ኢየሱስ የተጠመቀበትና በመስቀል ላይ ደሙን ያፈሰሰበት መንገድ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካለው የስርየት መስዋዕት በሐጢያት መስዋዕት ላይ ከሚደረገው እጆች መጫንና ከመስዋዕቱ ደም መፍሰስ ጋር ተመሳሳይ ነበር::

በብሉይ ኪዳን ሲደረግ የነበረው እንደዚህ ነበር ሐጢያተኛ በሐጢያት መስዋዕቱ ራስ ላይ እጆቹን ጭኖ «ጌታ ሆይ ሐጢያትን ሰርቻለሁ ነፍስ አጥፍቻለሁ አመንዝሬአለሁ» በማለት ሐጢያቶቹን ይናዘዛል ከዚያም ሐጢያቶቹ ወደ ሐጢያት መስዋዕቱ ይተላለፋሉ::

ሐጢያተኛው ለሐጢያት የቀረበውን መስዋዕት አርዶ በእግዚአብሄር ፊት እንደሚያቀርበው ሁሉ ኢየሱስም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለማስተሰረይ በተመሳሳይ መንገድ ቀረበ ኢየሱስ እኛን ለማዳንና በመስዋዕቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን ሁሉ ለማስተሰረይ ተጠመቀ በመስቀል ላይም ደሙን አፈሰሰ::

እንዲያውም ኢየሱስ የሞተው በእኛ ምክንያት ነው ስለዚህ ነገር ስናስብ እንከን የሌለባቸውን እነዚያን እንስሶች ለ ሕዝቡ ሁሉ ሐጢያቶች መስዋዕቶች አድርጎ የማቅረቡ ትርጉም ምንድነው? እነዚያ እንስሶች በሙሉ ሐጢያት ምን እንደሆነ ያውቁ ነበርን? እንስሶች ሐጢያትን አያውቁም እነርሱ እንከን የሌለባቸው መሆን ነበረባቸው::

እነዚያ እንስሶች ሙሉ በሙሉ ያለ እንከን ስለነበሩ ኢየሱስም እንደዚሁ ሐጢያት የሌለበት መሆን ነበረበት እርሱ

ቅዱስ አምላክ የእግዚአብሄር ልጅ ነው እርሱ ፈጽሞ ሐጢያት አልሰራም ስለዚህ 30 አመት ሲሆነው በዮርዳኖስ ወንዝ በተጠመቀው ጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወሰደ።

ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተው ከእኛ በወሰዳቸው ሐጢያቶች ምክንያት ነው የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ያነጻው የእርሱ የደህንነት አገልግሎት ነበር።

# የሐጢያቶች ስርየት ወንጌል መጀመሪያ

*ኢየሱስ በመጥምቁ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ የተጠመቀው ለምን ነበር?*

*ጽድቅን ሁሉ ለመፈፀም ነበር።*

በማቴዎስ 3 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን፡- እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር ኢየሱስም መልሶ፡- አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው።» (ማቴዎስ 3፡13-15)።*

ኢየሱስ 30 አመት ሲሆነው ለምን እንደተጠመቀ ማወቅና ማስተዋል ይኖርብናል እርሱ የተጠመቀው የሕዝቡን ሁሉ ሐጢያቶች ለማስተሰረይና የእግዚአብሄርን ጽድቅ ሁሉ

ለመፈጸም ነበር እንከን የሌለበት ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ሁሉ ከሐጢያቶቻቸው ለማዳን በአጥማቂው ዮሐንስ መጠመቅ ነበረበት፡፡

በዚህም የአለምን ሐጢያቶች ወሰደ የሰዎችን ሁሉ ሐጢያቶች ለማስተሰረይም ራሱን አቀረበ እኛም ከሐጢያት ለመዳን ምሉዕ የሆነውን እውነት ማወቅና በእርሱ ማመን አለብን በእርሱ ደህንነት ማመንና መዳን የእኛ ፋንታ ነው፡፡

የኢየሱስ ጥምቀት ምን ማለት ነው? ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚደረገው እጆችን መጫን ጋር ተመሳሳይ ነው በብሉይ ኪዳን የሕዝቡ ሁሉ ሐጢያቶች በሊቀ ካህኑ እጆች መጫን ለሐጢያት ወደቀረበው መስዋዕት ራስ ላይ ይተላለፍ ነበር በአዲስ ኪዳንም እንደዚሁ ኢየሱስ ራሱን የሐጢያት መስዋዕት አድርጎ በማቅረብና በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ የአለምን ሐጢያቶች ወስዶዋል፡፡

አጥማቂው ዮሐንስ ከሰዎች መካከል እጅግ ታላቁ ሰው በእግዚአብሄርም የተሾመ የሰው ዘር ወኪል ነበር እርሱ የሰው ዘር ወኪል የሰብአዊ ፍጡራን ሊቀ ካህን በመሆኑ እጆቹን በኢየሱስ ራስ ላይ ጭኖ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ አስተላለፈ «ጥምቀት» የሚያመላክተው «ማስተላለፍን መቀበርንና መታጠብን» ነው፡፡

ኢየሱስ ወደዚህ አለም መጥቶ ለምን በአጥማቂው ዮሐንስ እንደተጠመቀ ታውቃላችሁን? የእርሱን ጥምቀት አውቃችሁ በኢየሱስ ታምናላችሁን? ኢየሱስ የተጠመቀው ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እኛ የክፉ አድራጊ ዘሮች በሕይወት ዘመናችን ሁሉ የሰራናቸውን ሐጢያቶች ለመውሰድ ነበር አጥማቂው ዮሐንስ ለሐጢያቶቻችን የሚሆነውን እውነተኛ ወንጌል ለመፈጸም ኢየሱስን አጠመቀው፡፡

*ማቴዎስ* **3፡13-17** *የሚጀምረው «ያን ጊዜ»* በሚል ቃል

ነው ይህ የሚያመላክተው ኢየሱስ የተጠመቀበትን ጊዜ የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ የተላለፉበትን ጊዜ ነው፡፡

*«ያን ጊዜ»* ኢየሱስ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ ከሦስት አመት በኋላም በመስቀል ላይ ሞተ በሦስተኛው ቀን ተነሳ እርሱ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለማንጻት ለአንዴና ለመጨረሻ ተጠመቀ ለአንዴና ለመጨረሻም በመስቀል ላይ ሞተ ከሙታንም ለአንዴና ለመጨረሻ ተነሳ እርሱ በእግዚአብሄር ፊት ከሐጢያቶቻቸው መዳን ለሚፈልጉ ሰዎች የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ ለአንዴና ለመጨረሻም አዳናቸው፡፡

ኢየሱስ ለምን መጠመቅ አስፈለገው? እንደ አንድ ተራ ወንጀለኛ የእሾህ አክሊልን የደፋውና በጲላጦስ ችሎት የተፈረደበት ለምንድነው? በመስቀል ላይ መሰቀልና እስከ ሞት ድረስ መድማት ያስፈለገውስ ለምን ነበር? ከላይ ለተጠቀሱት ሁሉ ምክንያቱ በጥምቀቱ አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ የእናንተንና የእኔን ሐጢያቶች በሙሉ በራሱ ላይ ስለወሰደ ነው፡፡

እግዚአብሄር እንዳዳነን በሚናገረው የደህንነት ቃል ማመንና እርሱን ማመስገን ይኖርብናል ያለ ኢየሱስ ጥምቀት ያለ መስቀሉና ትንሳኤው ደህንነት አናገኝም፡፡

ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ በዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቻችንን ወስዶ በደህንነት ወንጌሉ የምናምነውን አድኖናል «ኢየሱስ የወሰደው የአዳምን ሐጢያት ብቻ ነው አይደል?» ብለው የሚያስቡ ሰዎች አሉ ነገር ግን ተሳስተዋል፡፡

ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ እንደወሰደ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ተጽፎዋል ሐጢያቶቻችንን በሙሉ የአዳምንም

ሐጢያት ጨምሮ ነጽተዋል ኢየሱስ በማቴዎስ 3፡15 ላይ እንዲህ ብሎዋል *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው»* ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ማለት ሁሉም ሐጢያቶች አንዳችም ሳይቀሩ ከእኛ ተወስደዋል ማለት ነው፡፡

ኢየሱስ የዕድሜ ዘመናችንን ሐጢያቶቻችንን በሙሉ አንጽቷልን? አዎ አንጽቷል በቅድሚያ የዚህን መረጃ በዘሌዋውያን ውስጥ እናግኝ ይህም ስለ ሊቀ ካህኑና ስለ ስርየት ቀን መስዋዕት ይነግረናል፡፡

## ለእስራኤል ህዝቦች አመታዊ ሐጢያቶች የሚቀርበው የስርየት መስዋዕት

*እስራኤላውያን በዚህ ምድር ላይ በሚቀርበው የሐጢያት መስዋዕት ለአንዴና ለመጨረሻ መቀደስ ይችላሉን?*

*በፍጹም፡፡*

*«አሮንም ለእርሱ ያለውን የኃጢያቱ መስዋዕት ወይፈን ያቀርባል ለራሱም ለቤተሰቡም ያስተሰርያል ሁለቱንም አውራ ፍየሎች ወስዶ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ አጠገብ በእግዚአብሔር ፊት ያቆማቸዋል አሮንም በሁለቱ ፍየሎች ላይ እጣ ይጥልባቸዋል አንዱን እጣ ለእግዚአብሔር ሌላውንም እጣ ለሚለቀቅ፡፡ አሮንም የእግዚአብሔር እጣ የሆነበትን ፍየል ያቀርባል ስለ ኃጢያትም መስዋዕት ያደርገዋል የመለቀቅም እጣ*

*የሆነበትን ፍየል ያስተሰርይበት ዘንድ ለመለቀቅም ወደ ምድረ በዳ ይሰድደው ዘንድ በሕይወቱ በእግዚአብሔር ፊት ያቆመዋል» (ዘሌዋውያን 16:6-10)* እዚህ ላይ አሮን የእስራኤሎችን አመታዊ ሐጢያቶች ለማንጻት በመገናኛው ድንኳን በራፍ ላይ ሁለት ፍየሎችን አቅርቦዋል።

*«አሮንም በሁለቱ ፍየሎች ላይ እጣ ይጥልባቸዋል አንዱን እጣ ለእግዚአብሔር ሌላውንም እጣ ለሚለቀቅ።»*

የሐጢያተኛውን ሐጢያት ለመስዋዕት በቀረበው እንስሳ ራስ ላይ እጆቹን በመጫን ወደ እርሱ ለማስተላለፍ ዘወትር ለሚሰሩት ሐጢያቶች ሕጋዊ ስርየትን ለማድረግ አንድ የመስዋዕት እንስሳ ያስፈልግ ነበር ነገር ግን በየአመቱ በሰባተኛ ው ወር በአስረኛው ቀን እስራኤሎች አመቱን በሙሉ ለሰሩዋቸው ሐጢያቶች ሕዝቡን ሁሉ ወክሎ የአመቱን ሐጢያቶች ለሐጢያት በቀረበው መስዋዕት ላይ የሚያስተላልፈው ሊቀ ካህኑ ነበር።

በዘሌዋውያን 16:29-31 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«በሰባተኛው ወር ከወሩም በአስረኛው ቀን ራሳችሁን አስጨንቋት የአገር ልጅም በእናንተ መካከል የተቀመጠም እንግዳ ስራን ሁሉ አትስሩበት በእግዚአብሔር ፊት ከኃጢያታችሁ ሁሉ ትነፃላችሁ ታላቅ ሰንበት ይሆንላችኋል ራሳችሁንም ታዋርዳላችሁ የዘለዓለም ስርዓት ነው።» (ዘሌዋውያን 16:29-31)*

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእስራኤል ሕዝብ ዘወትር ለሚሰሩዋቸው ሐጢያቶች ስርየትን ለማግኘትና «ጌታ ሆይ እንዲህና እንዲህ ያሉ ሐጢያቶችን ሰርቻለሁ እባክህ ይቅር በለኝ» ብለው በመናዘዝ ሐጢያቶቻቸውን ወደ መስዋዕቱ እንስሳ ራስ ለማስተላለፍ የሐጢያት ቁርባንን ያቀርቡ ነበር ከዚያም ለሐጢያት መስዋዕት ሆኖ የቀረበውን እንስሳ በማረድ ደሙን ለካህኑ ይሰጠውና አሁን ከሐጢያቶቹ ነጻ እንደሆነ አምኖ ወደ

ቤቱ ይሄዳል በዚህም ለሐጢያት የቀረበው መስዋዕት ሐጢያቱን በራሱ ላይ ተሸክሞ ለሐጢያተኛው ይሞታል ለመስዋዕት የቀረበው እንስሳ በሐጢያተኛው ፋንታ ይገደላል በብሉይ ኪዳን የሐጢያት መስዋዕቱ ፍየል ጠቦት ጥጃ ወይም ወይፈን ማለትም እግዚአብሄር ከለያቸው የተቀደሱ እንስሶች አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡

እግዚአብሄር ወሰን በሌለው ምህረቱ በሐጢያተኛው ፋንታ ለሐጢያቶቹ እንዲሞትለት የእንስሳ ሕይወት እንዲቀርብ ፈቀደ፡፡

በብሉይ ኪዳን ሐጢያተኞች በዚህ መንገድ በስርየቱ መስዋዕት አማካይነት ሐጢያቶቻቸውን ማስተሰረይ ችለዋል የሐጢያተኛው መተላለፍ በእጆች መጫን ወደ ሐጢያት መስዋዕቱ ተላልፎዋል ደሙም የሐጢያተኛውን ሐጢያት ለማስተሰረይ ለካህኑ ይሰጥ ነበር፡፡

ሆኖም በየቀኑ ሐጢያቶችን ማስተሰረይ አዳጋች ነበር ከዚህ የተነሳ እግዚአብሄር ሊቀ ካህኑ በእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ፋንታ በየአመቱ በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን የአመቱን ሁሉ ሐጢያቶች እንዲያስተሰርይ ፈቀደለት፡፡

ታዲያ በስርየት ቀን የሊቀ ካህኑ ሚና ምን ነበር? በመጀመሪያ ሊቀ ካህኑ አሮን በሐጢያት መስዋዕቱ ላይ እጆቹን በመጫን «ጌታ ሆይ የእስራኤል ሕዝብ እንዲህና እንዲህ ያሉትን ሐጢያቶች ነፍስ መግደልን ምንዝርናን ዝሙትን ስርቆትን በሐሰት መመስከርን ስድብን...ፈጽመዋል» ብሎ የሕዝቡን ሐጢያቶች ይናዘዛል፡፡

ከዚያም የሐጢያት መስዋዕቱን ያርድና ደሙን ወስዶ ያንን ደም በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ባለው የስርየት መክደኛ ላይ ሰባት ጊዜ ይረጨዋል (በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 7 ቁጥር ፍጹም ቁጥር ተብሎ ይቆጠራል)፡፡

የሕዝቡን አመታዊ ሐጢያቶች በእነርሱ ፋንታ ለሐጢያት በቀረበው መስዋዕት ራስ ላይ ማስተላለፍ የእርሱ ተግባር ነበር የሐጢያት መስዋዕቱም በይፋ ይሰዋል፡፡

እግዚአብሄር ጻድቅ ስለሆነ ሰዎችን ሁሉ ከሐጢያቶቻቸው ለማዳን ለሐጢያት የሚቀርበው መስዋዕት በሕዝቡ ፋንታ እንዲሞት ፈቀደ እግዚአብሄር በእውነት መሐሪ ስለሆነ ሕዝቡ በእነርሱ ምትክ የመስዋዕቱን እንስሳ ሕይወት እንዲያቀርቡ ፈቀደላቸው ከዚያም ሊቀ ካህኑ በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን በሚውለው የስርየት ቀን ደሙን በስርየት መክደኛው በስተ ምስራቅ በመርጨት ሕዝቡ ባለፈው አመት የሰሩዋቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ያስተሰርያል፡፡




ሊቀ ካህኑ በስርየት ቀን ለእስራኤል ሕዝብ ሁለት ፍየሎችን ማቅረብ ነበረበት ከእነርሱ አንዱ የሚለቀቅ ፍየል ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ትርጓሜውም «ማጥፋት» ማለት ነው በተመሳሳይ መንገድ የአዲስ ኪዳን የሚለቀቅ ፍየል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው *«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለሙን እንዲሁ ወዶአል፡፡» (ዮሐንስ 3:16)፡፡*

እግዚአብሄር አንድያ ልጁን የመስዋዕት በግ አድርጎ ሰጥቶናል እርሱ ለሰው ዘር የመስዋዕት በግ በመሆኑ በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠምቆ አዳኝ የአለም መሲህ ሆነ ኢየሱስ ማለት «አዳኝ» ማለት ሲሆን ክርስቶስ ማለት ደግሞ «የተቀባው ንጉስ» ማለት ነው ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ማለት «ሁላችንንም ለማዳን የመጣ የእግዚአብሄር ልጅ» ማለት ነው።

በብሉይ ኪዳን የሕዝቡ ሐጢያቶች በስርየት ቀን ስርየትን እንዳገኙ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስም ከ2,000 አመታት በፊት ለሐጢያቶቻችንን ሁሉ የሚሆነውን የስርየት ወንጌል ለማጠናቀቅ ሊጠመቅና በመስቀል ላይ ደሙን ሊያፈስስ ወደዚህ አለም መጣ።

እዚህ ላይ በዘሌዋውያን ላይ የሚገኝ አንድ ምንባብ እናንብብ *«አሮንም ሁለቱን እጆቹን በሕያው ፍየል ራስ ላይ ይጭናል በላዩም የእስራኤልን ልጆች በደል ሁሉ መተላለፋቸውንም ሁሉ ኃጢያታቸውንም ሁሉ ይናዘዛል በፍየሉም ራስ ላይ ያሸክመዋል በተዘጋጀው ሰውም እጅ ወደ ምድረ በዳ ይሰድደዋል ፍየሉም ኃጢያታቸውን ሁሉ ወደ በረሃ ይሸከማል ፍየሉንም በምድረ በዳ ውስጥ ይለቅቀዋል።» (ዘሌዋውያን 16:21-22)*

በዘሌዋውያን 1 ላይ እንደተጠቀሰው የእስራኤሎች ሁሉ ሐጢያቶች በፍየሉ ራስ ላይ እንደተላለፉ ተጽፎዋል *«መተላለፎቻቸውን ሁሉ»* የሚለው የሚያመላክተው በልቦቻቸውና በስጋቸው የሰሩዋቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ነው *«መተላለፎቻቸውም ሁሉ»* በሊቀ ካህኑ እጆች መጫን ለሐጢያት በቀረበው መስዋዕት ራስ ላይ ተጭኖዋል።

# በእግዚአብሔር ሕግ መሰረት ሁላችንም ስለ ኃጢያቶቻችን እውነተኛ እውቀት ሊኖረን ይገባል

*እግዚአብሔር ህግን የሰጠን ለምንድን ነው?*

*የኃጢያትን እውቀት ሊሰጠን ነው::*

የእግዚአብሄር ሕግ 613 ትዕዛዛትን ይዞዋል እንዲያውም ስለዚህ ስናስብ እርሱ አታድርጉ ያለንን እናደርጋለን እንድናደርግ የነገረንንም አናደርግም::

ስለዚህ እኛ ሐጢያተኞች ነን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሄር እነዚያን ትዕዛዛቶች የሰጠን ሐጢያቶቻችንን እንድናውቅ እንደሆነ ተጽፎዋል (ሮሜ 3:20) ይህ ማለት የትዕዛዛት ሕጉን የሰጠን ሐጢያተኞች እንደሆንን ሊያስተምረን ነው ማለት ነው እነርሱን የሰጠን በእነርሱ መኖር ስለምንችል ሳይሆን ሐጢያቶቻችንን እንድናውቅ ነው::

እርሱ ትዕዛዛቱን የሰጠን እንድንጠብቃቸው አይደለም ውሻ እንደ ሰው ይኖር ዘንድ አትጠብቁም በተመሳሳይ መንገድ እኛም ፈጽሞ የእግዚአብሄርን ሕግ በመጠበቅ አንኖርም ነገር ግን በትዕዛዛት ሕጉ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን ብቻ ማወቅ እንችላለን::

እግዚአብሄር እነርሱን የሰጠን የሐጢያት ክምችቶች ስለሆንን ነው ነገር ግን ይህንን በትክክል አልተረዳንም «እናንተ ነፍሰ ገዳዮች አመንዝራዎችና ክፉ አድራጊዎች ናችሁ» እግዚአብሄር በትዕዛዛቱ አማካይነት ውስጠ ወይራ ነገር

ነግሮናል እንዳንገድል ነግሮናል እኛ ግን በልቦቻችንን አንዳንድ ጊዜም በስጋችን እንገድላለን፡፡

ነገር ግን መግደል እንደማይገባን በሕጉ ውስጥ ስለተጻፈ «አሃ ተሳስቼ ነበር እኔ ማድረግ የማይገባኝን ነገር በማድረጌ ሐጢያትን የሰራሁ ሐጢያተኛ ነኝ» በማለት ነፍሰ ገዳዮች መሆናችንን እናውቃለን፡፡

እግዚአብሄር የእስራኤልን ሕዝብ ከሐጢያት ለማዳን በብሉይ ኪዳን የስርየት መስዋዕት እንዲቀርብ ፈቀደ በአመት አንድ ጊዜም ለሕዝቡ የሚያስተሰርየው አሮን ነበር፡፡

በብሉይ ኪዳን በስርየት ቀን ሁለት የሐጢያት መስዋዕቶች ለእግዚአብሄር መቅረብ ነበረባቸው አንዱ በእግዚአብሄር ፊት ሲቀርብ ሌላው እጆች ተጭነውበት የሕዝቡን አመታዊ ሐጢያቶች በሙሉ ከወሰደ በኋላ ወደ ምድረ በዳ ይሰደዳል ፍየሉ በተመረጠው ሰው እጅ ወደ ምድረ በዳ ከመሰደዱ በፊት ሊቀ ካህኑ እጆቹን በሕያው ፍየል ራስ ላይ ጭኖ የእስራኤልን ሐጢያቶች በሙሉ ይናዘዛል «ጌታ ሆይ ሕዝቡ ገድሎዋል አመንዝሮዋል ሰርቋል ጣዖታትን አምልኮዋል...በፊትህ በድለናል፡፡»

የፓለስቲን ምድር በረሃማ ምድረ በዳ ነው የሚለቀቀው ፍየል ማለቂያ ወደሌለው ምድረ በዳ ይሰደድና ውሎ አድሮ ይሞታል ሲሰደድ የእስራኤል ሕዝብ ርቆ እስኪሰወር ድረስ ይመለከቱታል ሐጢያቶቻቸውም ከሚለቀቀው ፍየል ጋር አብሮ እንደተወሰደ ያምናሉ በዚህም ሕዝቡ የእእምሮ ሰላም ያገኛል የሚለቀቀው ፍየልም የሕዝቡን ሁሉ አመታዊ ሐጢያቶች ተሸክሞ በምድረ በዳ ይሞታል፡፡

በዚህ ሁኔታ እግዚአብሄር የአምላክ በግ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ይቅር ብሎዋል ሐጢያቶቻችን በሙሉ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ

ባፈሰሰው ደሙ አማካይነት ፈጽመው ነጽተዋል፡፡

ኢየሱስ አምላክና አዳኛችን ነው እርሱ የሰውን ዘር ሁሉ ከሐጢያት ለማዳን የመጣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው እርሱ በአምሳሉ የሰራንና ከሐጢያት ሊያድነን ወደዚህ ምድር የወረደ ፈጣሪ ነው፡፡

ወደ ኢየሱስ የተላለፉት በስጋችን የምንሰራቸው የዘወትር ሐጢያቶች ብቻ ሳይሆኑ የወደፊት ሐጢያቶቻችንንና የአእምሮዋችንና የስጋችንም ሐጢያቶች ጭምር ናቸው ስለዚህ ለአለም ሐጢያቶች በሙሉ የተሟላ ስርየት የሆነውን የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሁሉ ይፈጽም ዘንድ በአጥማቂው ዮሐንስ መጠመቅ ነበረበት፡፡

ኢየሱስ ከመሰቀሉ ከሦስት አመት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ አገልግሎቱን ሲጀምር በዮርዳኖስ ወንዝ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በማስተሰረይ ለሰው ዘር ደህንነቱን መስጠት የጀመረው በጥምቀቱ ነው፡፡

እስከ ወገብ ድረስ በሚያጠልቀው በዮርዳኖስ ወንዝ አጥማቂው ዮሐንስ እጆቹን በኢየሱስ ራስ ላይ ጭኖ በውሃው ውስጥ አጠለመው ይህ ጥምቀት ከብሉይ ኪዳኑ እጆችን መጫን ጋር ተመሳሳይና ሐጢያቶችን ሁሉ የማስተላለፍ ያው አይነት ውጤት የነበረው ነው፡፡

በውሃ ውስጥ መጥለም ማለት ሞት ማለት ነው ከውሃ ውስጥ መውጣት ማለት ደግሞ ትንሳኤ ማለት ነው ስለዚህ ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ የተልዕኮውን ሦስቱንም ደረጃዎች ማለትም ሐጢያቶችን በሙሉ መውሰድ ስቅለትና ትንሳኤን ፈጸመ ገለጠም፡፡

እኛ መዳን የምንችለው ኢየሱስ እኛን ከሐጢያት ያነፃባቸውን ቃሎች ስንታዘዝ ብቻ ነው እግዚአብሔር በኢየሱስ

በኩል ሊያድነን ወሰነ በብሉይ ኪዳን የገባው ኪዳንም በዚህ ሁኔታ ተፈጸመ ኢየሱስ በዚህ ድርጊት አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በራሱ ላይ ተሸክሞ ወደ መስቀል ሄደ::

*ኢየሱስ ኃጢያቶቻችንን ሁሉ ካወጣልንበኋላ ለኛ የቀረው ስራ ምንድን ነው?*

*የሚያስፈልገን ነገር፣ በእግዚአብሔር ቃል እምነት እንዲኖረን ብቻ ነው::*

በዮሐንስ 1:29 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለው:- እነሆ! የዓለምን ኃጢዓት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ::»* አጥማቂው ዮሐንስ *«እነሆ! የዓለምን ኃጢኣት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!»* በማለት መሰከረ የሰው ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ ወደ እርሱ ተላልፈዋል ይህንን እመኑ! ያን ጊዜ የሐጢያቶቻችሁን ሁሉ ስርየት በማግኘ ት ትባረካላችሁ::

በእግዚአብሄር ቃል ላይ እምነት ሊኖረን ይገባል የራሳችንን አስተሳሰቦችና ግትርነት ትተን የተጻፈውን የእግዚአብሄር ቃል መታዘዝ ይኖርብናል በአጭሩ ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች የወሰደ የመሆኑን እውነት ማመን አለ ብን::

ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል ማለትና ሐጢያቶቻችን በማስተሰረይም የእግዚአብሄርን ጽድቅ ፈጽሞዋል ማለት በትክክል ተመሳሳይ ነገር ነው «እጆችን መጫንና»

«ጥምቀትም» እንደዚሁ ተመሳሳይ ነገር ማለት ናቸው፡፡

«ሁሉም» «እያንዳንዱ ነገር» ወይም «ሙሉ» ብንልም ትርጉሙ ያው ተመሳሳይ ነው በብሉይ ኪዳን «እጆችን መጫን» የሚለው ቃል ትርጉም በምትኩ «ጥምቀት» የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ከመዋሉ በቀር በአዲስ ኪዳንም ያው ተመሳሳይ ነው፡፡

ይህም ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለማስተሰረይ የተጠመቀና በመስቀል ላይ የተኮነነ ወደመሆኑ ቀላል እውነት ይደርሳል በዚህ እውነተኛ ወንጌል ስናምን መዳን እንችላለን፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ «የአለምን ሐጢያት» በሙሉ (ዮሐንስ 1፡29) እንደወሰደ ሲናገር የአለም ሐጢያት ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ማለት ይዘናቸው የተወለድናቸው ሐጢያቶች በሙሉ ማለትም በአእምሮዋችን ውስጥ ያሉ ክፉ አሳቦች ስርቆት ምንዝርና መመኘት ክፋት ስድብ ትዕቢትና ስንፍና ማለት ነው ይህ በስጋና በልብ የምንሰራቸውን መተላለፎችና በደሎች በሙሉ ይጨምራል፡፡

*«የኃጢያት ደመወዝ ሞት ነውና የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ህይወት ነው» (ሮሜ 6፡23) «ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» (ዕብራውያን 9፡22)* በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እንደተባለው ሐጢያቶች በሙሉ ዋጋቸው መከፈል ይኖርበታል ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ዘር በሙሉ ከሐጢያት ለማዳን የራሱን ሕይወት አቀረበ ለአንዴና ለመጨረሻም ስለ እኛ የሐጢያትን ደመወዝ ከፈለ፡፡

ስለዚህ ከሐጢያቶቻችንን ለመላቀቅ እኛ ማድረግ የሚኖርብን በእውነተኛው ወንጌል--በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ እንደዚሁም በመለኮታዊነቱ ማመን ነው፡፡

# ነገ ለሚሰሩ ሐጢያቶች የሚሆን ስርየት

*ዳግመኛ ለሐጢያቶቻችን መስዋዕት ማቅረብ ያስፈልገናልን?*

*ዳግመኛ በፍጹም::*

የነገ የከነገ በስቲያ ሐጢያቶችና እስከ ዕለተ ሞታችን ቀን ድረስ የምንሰራቸው ሐጢያቶችም እንደዚሁ *«በአለም ሐጢያት ውስጥ»* ተጨምረዋል የዛሬው የትናትናውና ከትናትና በፊት የተሰሩት ሐጢያቶችም እንደዚሁ *«በአለም ሐጢያት ውስጥ»* ተጨምረዋል ከውልደት እስከ ሞት ድረስ ሰዎች የሚሰሩዋቸው ሐጢያቶች ሁሉም *«የአለም ሐጢያት»* ክፍል ናቸው የአለም ሐጢያቶችም በጥምቀቱ አማካይነት ፈጽመው ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል እስከ ዕለተ ሞታችን ቀን ድረስ የምንሰራቸው ሐጢያቶች በሙሉ አስቀድመው ከእኛተወስደዋል::

ለመዳን የሚያስፈልገን በዚህ እውነተኛ ወንጌል በተጻፉት የእግዚአብሄር ቃሎች ማመንና እውነትን መታዘዝ ብቻ ነው ከሐጢያቶቻችንን ሁሉ ለመዋጀት የራሳችንን አስተሳሰቦች ማስወገድ ይገባናል «ገና ያልተሰሩትን ሐጢያቶች እንዴት ሊወስድ ይችላል?» ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል እኔም ደግሞ መልሼ እጠይቃችኋለሁ «ሐጢያት በሰራን ጊዜ ሁሉ ኢየሱስ ወደዚህ አለም ተመልሶ መምጣትና ደሙን ደጋግሞ ማፍሰስ ይገባዋልን?»

ዳግም በመወለድ ወንጌል ውስጥ ለሐጢያቶቻችንን ስርየት የሚሆን ሕግ አለ *«ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» (ዕብራውያን*

*9:22)* በብሉይ ኪዳን ዘመን አንድ ሰው ከሐጢያቶቹ ለመዳን በፈለገ ጊዜ እጆቹን በሐጢያት መስዋዕቱ ላይ በመጫን ሐጢያቶቹን ማስተላለፍ ነበረበት ለሐጢያት የቀረበውም መስዋዕት ለሐጢያቶቹ መሞት ነበረበት::

በዚሁ ተመሳሳይ መንገድ የእግዚአብሄር ልጅ የሰውን ዘር ሁሉ ለማዳን ወደዚህ አለም መጣ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለመውሰድም ተጠመቀ የሐጢያቶቻችንን ደመወዝ ለመክፈልም በመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰ *«ተፈጸመ!»* በማለትም በመስቀል ላይ ሞተ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተነሳ አሁን በእግዚአብሄር ቀኝ ተቀምጦዋል በዚህም ለዘላለም አዳኛችን ሆነ::

ሙሉ በሙሉ ከሐጢያቶቻችንን ነጻ ለመውጣት ግትር አሳቦቻችንን መጣልና በየቀኑ በምናቀርባቸው የንስሐ ጸሎቶች ራሳችንን ዘወትር ከምንሰራቸው ሐጢያቶች እንድንዋጅ የሚነግረንን የሐይማኖት ትምህርት መተው ይኖርብናል የሰው ዘር ሐጢያቶች ስርየትን ያገኙ ዘንድ ሕጋዊው መስዋዕት ለአንዴና ለመጨረሻ መቅረብ ነበረበት በሰማይ ያለው አምላክ በጥምቀቱ አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ገዛ ልጁ በማስተላለፍ ስለ እኛ እንዲሰቀል አደረገው እርሱ ከሙታን በመነሳቱም ደህንነታችን ተጠናቋል::

*«እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ ስለበደላችንም ደቀቀ የድህነታችንም ተግሳፅ በእርሱ ላይ ነበር በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን እኛ ሁላችን እንደበጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንንም በደል በእርሱ ላይ አኖረ»* በኢሳይያስ 53 ላይ የአለምና የሰው ዘር መተላለፎችና በደሎች ሁሉ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተላለፉ ተነግሮዋል::

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በኤፌሶን 1:4 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል

*«ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን»* ይህ እርሱ ከአለም ፍጥረት በፊት በእርሱ በኩል እንደመረጠን ይነግረናል አለም ከመፍጠሩ በፊት እንኳን እግዚአብሄር በክርስቶስ የእርሱ ሕዝብ እንከን የሌለብን ጻድቃን ሊያደርገን ወሰነ ከዚህ በፊት ያሰብነው ምንም ነገር ቢኖር አሁን የእግዚአብሄር ቃል የሆኑትን የውሃውን የደሙንና የመንፈሱን ቃሎች ማመንና መታዘዝ ይገባናል::

እግዚአብሄር የእርሱ በግ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የአለምን ሐጢያቶች እንደወሰደና ለሰው ዘር ሁሉ ስርየትን እንደሰጠ ነግሮናል በዕብራውያን 10 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና ስለዚም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሰረት የሚቀርቡትን ሊፈፅም ከቶ አይችልም::» (ዕብራውያን 10:1)*

እዚህ ላይ ቃሉ በየአመቱ የሚያቀርቡዋቸው እነዚያው መስዋዕቶች እነርሱን በጭራሽ ፍጹማን ሊያደርጓቸው እንደማይችሉ ይናገራል ሕጉ ሊመጣ ያለው በጎ ነገር ጥላ እንጂ የእውነተኛው ነገር ትክክለኛ አምሳል አይደለም የሚመጣው መሲህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐጢያቶቻችንን ሁሉ ለማስተሰረይ በመጠመቅና በመሰቀል ለአንዴና ለመጨረሻ (የእስራኤል አመታዊ ሐጢያቶች ለአንዴና ለመጨረሻ እንደሚሰረዩ ሁሉ) ፍጹማን አድርጎናል::

ስለዚህ ኢየሱስ በዕብራውያን 10 ላይ እንዲህ አለ *«ቀጥሎ:- እነሆ አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቻለሁ ብሎአል ሁለተኛውን ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ አንድ ጊዜ ፈፅሞ በማቅረብ ተቀድሰናል ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢያትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መስዋዕቶች*

*ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል እርሱ ግን ስለ ኃጢያት አንድን መስዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደፊት ይጠብቃል አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍፁማን አድርጎአቸዋልና መንፈስ ቅዱስም ደግሞ ስለዚህ ይመሰክርልናልና ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ በልባቸው ህጌን አኖራለሁ በልቦናቸውም እፅፈዋለሁ ብሎ ከተናገረ በኋላ ኃጢያታቸውንና አመፃቸውንም ደግሜ አላስብም ይላል የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለኃጢያት ማቅረብ የለም::» (ዕብራውያን 10:9-18)*

ኢየሱስ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ከአለም ሐጢያቶች ሁሉ እንዳዳነን እናምናለን::

## በልቦቻችንንና በልቦናዎቻችን ላይ የተጻፈው ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድ ደህንነት



ሁላችሁም በእርሱ ፍጹም ደህንነት ታምናላችሁን? --አሜን -- ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እኛን ለማዳን እንደተጠመቀና በመስቀል ላይ ደሙን እንዳፈሰሰ የሚናገሩትን የእግዚአብሄር ቃሎች በእምነት ትታዘዛላችሁን? ዳግም ለመወለድ በእርሱ ቃል ማመን አለብን ኢየሱስ ክርስቶስ በስርየት ወንጌል አማካይነት ከአለም ሐጢያት ጋር አብሮ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንዳነጻ ስናምን መዳን እንችላለን::

የእግዚአብሄርን ሕግ በመጠበቅ ፈጽሞ ሐጢያት አልባ መሆን አንችልም ነገር ግን በእርሱ ስራዎች ላይ ባለን እምነት ፍጹማን ልንሆን እንችላለን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጠመቅ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶ ተፈረደበት በመስቀል ላይም ለሐጢያቶቻችንን ሁሉ ቅጣትን ተቀበለ ይህንን ወንጌል ከሙሉ ልባችን በማመን ከሐጢያቶቻችን ልንድንና ጻድቃን ልንሆን እንችላለን ይህንን ታምናላችሁን?

የኢየሱስ ጥምቀት ስቅለቱና ትንሳኤው ለሰው ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ስርየትን የሚያመጡና ወሰን በሌለውና በሁኔታ ላይ ባልተመሰረተ የእግዚአብሄር ፍቅር ላይ የተመሰረተ የደህንነት ሕግ ናቸው እግዚአብሄር ባለንበት ሁኔታ ወዶናል እርሱ ጻድቅ ነው ስለዚህ አስቀድሞ ጻድቃን አደረገን ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በእርሱ ጥምቀት አማካይነት ወደ ኢየሱስ በማስተላለፍም ጻድቃን አደረገን::

ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለማንጻት አንድያ ልጁን ኢየሱስን ስለ እኛ ወደዚህ አለም ላከው ኢየሱስ በጥምቀቱ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ እንዲወስድ ፈቀደ ከዚያም የሐጢያቶቻችንን ፍርድ በሙሉ ወደ ልጁ አስተላለፈ የእግዚአብሄር አጋፔ በሆነው የውሃና የደም ደህንነት አማካይነት ጻድቅ ልጆቹ አደረገን::

በዕብራውያን 10:16 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል «በልባቸው

*ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እጽፈዋለሁ::»*

እኛ በልቦቻችንንና በአእምሮዋችን በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኞች ነን ወይስ ጻድቃን ነን? በእግዚአብሄር ቃል ላይ እምነት ካለን ጻድቃን እንሆናለን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶ ለእነርሱ ተኮንኖዋል ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን ነው «እኛ በየቀኑ ሐጢያት ስለምንሰራ እንዴት ጻድቃን ልንሆን እንችላለን? እኛ በእርግጥም ሐጢያተኞች ነን» ብላችሁ ታስቡ ይሆናል ነገር ግን ክርስቶስ ኢየሱስ አባቱን እንደታዘዘ በእግዚአብሄር ቃል ስናምን ጻድቃን እንሆናለን::

ቀደም ብዬ እንዳልሁት ዳግም ከመወለዳችን በፊት በልቦቻችን ውስጥ ሐጢያት ነበረብን የሐጢያቶቻችን ስርየት የሆነውን ወንጌል ከወሰድን በኋላ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ዳንን ወንጌልን ሳናውቅ በነበርንበት ጊዜ ሐጢያተኞች ነበርን በኢየሱስ ደህንነት ማመን ስንጀምር ጻድቃንና የእግዚአብሄር ጻድቅ ልጆች ሆንን ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረለት ጻድቃን የመሆን እምነት ይህ ነው የሐጢያት ስርየት በሚያስገኘው ወንጌል ያለን እምነት «ጻድቃን» አድርጎናል::

ሐዋርያው ጳውሎስ አብርሃም የእምነት አባቶችም ጭምር ጻድቃን የሆኑት የሐጢያቶች ስርየት ባርኮቱን በሚናገሩት ቃሎች በእግዚአብሄር ቃል ባላቸው እምነት እንጂ በስራዎቻቸው አይደለም::

ዕብራውያን 10:18 እንዲህ ይላል «የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ሐጢያት ማቅረብ የለም» እንደተጻፈው በሐጢያቶቻችንን እንዳንሞት እግዚአብሄር አዳነን በዚህ ታምናላችሁን? ---አሜን--

በፊልጵስዮስ 2 ላይ *«በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት*

*እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው ከስምም በላይ ያለውን ስም ሰጠው ይህም በሰማይና በምድር ከምድር በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው፡፡» (ፊልጵስዮስ 2:5-11)*

የክብሩ መንጸባረቅና የባህሪው ትክክለኛ መገለጫ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ (ዕብራውያን 1:3) ለራሱ አንዳች ትልቅ ክብርን አልወሰደም በፈንታው ለራሱ የባርያን መልክ ወሰደ በሰው አምሳልም መጣ እርሱ ራሱን አዋረደ እኛን ለማዳንም እስከ ሞት ድረስ ታዘዘ፡፡

ስለዚህ ኢየሱስን እናመሰግነዋለን «እርሱ አምላካችን አዳኝና ንጉስ ነው» እግዚአብሄርን የምናከብረውና ኢየሱስን የምናመሰግነው ኢየሱስ እስከ መጨረሻው ድረስ የአባቱን ፈቃድ ስለታዘዘ ነው እርሱ ባይታዘዝ ኖሮ አሁን የእግዚአብሄርን ልጅ ባላከበርነውም ነበር ነገር ግን የእግዚአብሄር ልጅ የአባቱን ፈቃድ እስከ ሞት ድረስ ስለታዘዘ በዚህ ምድር ላይ ያለ ፍጥረትና ሕዝብ ሁሉ ያከብረዋል ይህንኑም ለዘላለም ያደርገዋል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ የአለምን ሐጢያቶች የወሰደ የእግዚአብሄር በግ ነው እርሱ እነዚህን ሐጢያቶች በጥምቀቱ አማካይነት እንደወሰዳቸውም ተጽፎዋል እርሱ የአለምን ሐጢያቶች ከወሰደ 2000 አመታት ያህል ሆንዋል እናንተና እኔ ከውልደታችን ጀምሮ በዚህ አለም ላይ ስንኖር ነበርን ሐጢያቶቻችንም ሁሉ በአለም ሐጢያቶች ውስጥ ተካተዋል፡፡

*ነገ ኃጢያትን ብንሰራ*
*ኃጢያተኞች*
*እንሆናለን?*

*አንሆንም ምክንያቱም ኢየሱስ ያለፈውን፣*
*ያሁኑንና የወደፊትንም ኃጢያት ሁሉ*
*ወስዶዋል፡፡*

የአዳምን ሐጢያት በዕድሜ ዘመናችን ከሰራናቸው ሐጢያቶች ሳንለይ ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ ሐጢያት አልሰራንምን? ---አዎ ሰርተናል--፡፡

ኢየሱስ ከተወለድንበት ቀን እስከምንሞትበት ቀን ድረስ ሐጢያት እንደምንሰራ ስላወቀ አስቀድሞ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወሰደ አሁን ይህንን ማየት ትችላላችሁን? እስከ 70 አመት ድረስ ብንኖር ሐጢያቶቻችን ከመቶ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ የጭነት መኪናዎች በላይ ይሞሉ ነበር ኢየሱስ ግን ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱ በአንድ ጊዜ ወሰደ ከእርሱም ጋር በመስቀል ላይ ተሸከማቸው፡፡

ኢየሱስ የአዳምን ሐጢያት ብቻ ወስዶ ቢሆን ኖሮ ሁላችንም ሞተን ሲኦል እንወርድ ነበር እርሱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ መውሰድ እንዳልቻለ ቢሰማን እንኳን ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ የመደምሰሱን ሐቅ ፈጽሞ አይለውጠውም፡፡

በዚህ አለም ላይ ምን ያህል ሐጢያት መስራት እንችላለን? የምንሰራቸው ሐጢያቶች በሙሉ በአለም ሐጢያቶች ውስጥ ተካተዋል፡፡

ኢየሱስ ዮሐንስን እንዲያጠምቀው በነገረው ጊዜ በትክክል

የተናገረውን ማለቱ ነበር ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደ ራሱ መስክሮዋል እግዚአብሔር ከኢየሱስ በፊት ባርያውን ልኮ በእርሱ እንዲጠመቅ አደረገው ኢየሱስ የሰው ዘር ወኪል በሆነው በዮሐንስ እንዲጠመቅና ለመጠመቅም በፊቱ ራሱን ዝቅ በማድረግ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ፡፡

ከ20 እስከ 30 ከ30 እስከ 40 እና ወ.ዘ.ተ ዕድሜ ድረስ የሰራናቸው ሐጢያቶችና የልጆቻችንም ሐጢያቶች እንኳን ሳይቀሩ ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት በወሰዳቸው የአለም ሐጢያቶች ውስጥ ተካተዋል፡፡

በዚህ አለም ላይ ሐጢያት አለ ብሎ መናገር የሚችል ማነው? ኢየሱስ ክርስቶስ የአለምን ሐጢያቶች ወስዶዋል ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን ለማስተሰረይ ባደረገው ነገር በጥምቀቱና ባፈሰሰው ክቡር ደሙ ያለ አንዳች ጥርጥር በልቦቻችን ስናምን ሁላችንም መዳን እንችላለን፡፡

ብዙ ሰዎች ሕይወታቸው በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ስለ ሕይወታቸው በመናገር በራሳቸው አስተሳሰቦች ውስጥ ተጠቅልለው ያልተረጋጋ ኑሮ ይኖራሉ ነገር ግን አስቸጋሪ ሕይወት የሚኖሩ ብዙ ሰዎች አሉ ብዙ ሰዎች ያልተረጋጋ ሕይወትን ኖረዋል እኔም ዳግም ከመወለዴ በፊት እንዲህ አይነት ሕይወት ኖሬአለሁ የስርየትን የኢየሱስን ጥምቀትና የደሙን ወንጌል መረዳት ወይም መቀበል እንዴት አትችሉም፡፡

# የኃጢያተኞች ደህንነት ተፈጽሞዋል

*ኢየሱስ የጴጥሮስን እግር ያጠበው ለምንድን ነው?*

*ለዚህ ምክንያቱ እርሱ በጥምቀቱ አማካይነት የጴጥሮስን የወደፊት ኃጢያትም ጭምር እንዳነጻለት ጠንካራ እምነት እንዲኖረው ለማድረግ ነው፡፡*

ዮሐንስ 19ን እናንብብ *«ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎልታ ወደተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወጣ በዚያም ሰቀሉት ከእርሱም ጋር ሌሎች ሁለት አንዱን በዚህ አንዱን በዚያ ኢየሱስንም በመካከላቸው ሰቀሉት ጲላጦስም ደግሞ ፅሕፈት ፅፎ በመስቀሉ ላይ አኖረው ጽሕፈቱም የአይሁድ ንጉስ የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚል ነበር ኢየሱስም የተሰቀለበት ስፍራ ለከተማ ቅርብ ነበርና ከአይሁድ ብዙዎች ይህን ጽሕፈት አነበቡት በዕብራይስጥና በሮማይስጥ በግሪክም ተፅፎ ነበር፡፡» (ዮሐንስ 19:17-20)*

ውድ ወዳጆች ኢየሱስ ክርስቶስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶ በጲላጦስ ችሎት እንዲሰቀል ተፈረደበት አሁን ስለዚህ ትዕይንት አብረን እናስብ፡፡

ከቁጥር 28 ጀምሮ *«ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደተፈፀመ አውቆ የመፅሐፉ ቃል ይፈፀም ዘንድ፡- ተጠማሁ አለ»* ኢየሱስ መጽሐፍ የሚለውን ለመፈጸም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወሰደ *«ተጠማሁ አለ በዚያም ኮምጣጤ የሞላበት እቃ ተቀምጦ ነበር እነርሱም ኮምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው*

*በሁሶፕም አድርገው ወደ አፉ አቀረቡለት ኢየሱስም ኮምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ ተፈፀመ! አለ ራሱን አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ::» (ዮሐንስ 19:28-30)*

ኢየሱስ እንዲህ አለ *«ተፈፀመ!»* ከዚያም በመስቀል ላይ ሞተ ከሦስት ቀናት በኋላም ከሙታን ተነስቶ ወደ ሰማይ አረገ::

ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ መጠመቁና በመስቀል ላይ መሞቱ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር ላይነጣጠሉ የተያያዙ ናቸው አንዱ ከሌላው ተነጥሎ መኖር የሚችልበት ምክንያት የለውም ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ በስርየት ወንጌሉ ስላዳነን እናመስግነው:

የሰው ዘር ስጋ ሁልጊዜም የሚከተለው የስጋን ፍላጎቶች ስለሆነ በስጋችን ሐጢያት ከመስራት ማምለጥ አንችልም ኢየሱስ ክርስቶስ ከስጋችን ሐጢያቶች ሊያድነን ጥምቀቱንና ደሙን ሰጥቶናል በወንጌሉም ከስጋ ሐጢያቶቻችን አዳነን::

ሙሉ የሐጢያቶች ስርየት ያገኙ ሰዎች በቤተልሄም በተወለደው በዮርዳኖስ በተጠመቀው በመስቀል ላይ በሞተውና በሦስተኛው ቀን በተነሳው ኢየሱስ በማመን በማንኛውም ጊዜ መንግስተ ሰማይ መግባት ይችላሉ ጌታን እናመሰግነዋለን ስሙንም ለዘላለም እናከብራለን::

በመጨረሻው የዮሐንስ ምዕራፍ ውስጥ ኢየሱስ ከሙታን ከተነሳ በኋላ ወደ ገሊላ ሄዶ ነበር ወደ ጴጥሮስም ሄዶ እንዲህ አለው *«የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?»* ጴጥሮስም *«አዎ ጌታዬ እንደምወድህ ታውቃለህ»* በማለት መለሰለት ያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለው *«ግልገሎቼን አሰማራ::»*

ጴጥሮስ ሁሉን ነገር የኢየሱስን ጥምቀትና የደሙን የሐጢያቶች ስርየትንም ወንጌል ተረዳ አሁን የሐጢያቶቹን ሁሉ ስርየት በሰጠው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል በማመኑና ኢየሱስም ለምን እግሮቹን እንዳጠበለት በመረዳቱ በኢየሱስ ላይ

ያለው እምነቱ ይበልጥ ብርቱ ሆነ፡፡

እንደገና ዮሐንስ 21፡15ን እናንብብ *«ምሳ ከበሉ በኋላም ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው አዎን ጌታ ሆይ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው እርሱም ግልገሎቼን አሰማራ አለው»* እርሱ ግልገሎቹን በአደራ ለጴጥሮስ መስጠት የቻለው ጴጥሮስ ሙሉ በሙሉ የዳነ የእርሱ ደቀ መዛሙር ስለነበርና ጴጥሮስ ጻድቅና ፍጹም የሆነ የእግዚአብሄር አገልጋይ ስለነበር ነው፡፡

ጴጥሮስ በየቀኑ በሚሰራቸው ሐጢያቶቹ ዳግመኛ ሐጢያተኛ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ኢየሱስ የሐጢያቶች ስርየት የሚገኝበትን ወንጌል እንዲሰብክ ባልነገረውም ነበር ምክንያቱም ሌሎች ደቀ መዛሙርቶችን ጨምሮ እርሱም በስጋ በየቀኑ ሐጢያት ከመስራት ማምለጥ ስለማይችል ነበር ነገር ግን በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ በማመናቸው ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ የደመሰሰውን ወንጌል እንዲሰብኩ ነገራቸው፡፡

## ጌታዬ እንደምወድህ ታውቃለህ

*ዳግመኛ ኃጢያትን ስትሰሩ*
*ዳግመኛ «ኃጢያተኞች»*
*ትሆናላችሁን?*

*አንሆንም ኢየሱስ በዮርዳኖስ*
*የወደፊት ኃጢያቶቼን*
*ቀድሞውኑም ወስዷል፡፡*

ኢየሱስ ለጴጥሮስ ስለተናገራቸው ቃሎች እናስብ *«የዮና ልጅ ስምዖን ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?» «አዎን ጌታዬ እንደምወድህ አንተም ታውቃለህ»* የእርሱ የፍቅር ኑዛዜ የሐጢያቶችን ስርየት በሚያስገኘው ወንጌል ላይ ካለው እምነት የመነጨ እውነተኛ ኑዛዜ ነበር፡፡

ኢየሱስ እግሮቻቸውን በማጠብ ጴጥሮስንና ሌሎቹን ደቀ መዛሙርት የሐጢያቶች ስርየት የሚገኝበትን ወንጌል አስተምሮዋቸው ባይሆን ኖሮ ፍቅራቸውን በዚያ መንገድ መመስከር ባልቻሉም ነበር፡፡

በምትኩ ኢየሱስ ወደ እነርሱ መጥቶ «ከእነዚህ አብልጣችሁ ትወዱኛላችሁ?» ብሎ በጠየቃቸው ጊዜ ጴጥሮስ «ጌታ ሆይ እኔ ጎዶሎ ሰው ብቻ ነኝ እኔ ከእነዚህ ሁሉ ነገሮች በላይ ይበልጥ ልወድህ የማልችል ሐጢያተኛ ነኝ እባክህ ተወኝ» ማለት ይችል ነበር ጴጥሮስ ራሱን ከኢየሱስ ለመደበቀም ሮጦ በሸሸ ነበር፡፡

ነገር ግን እስቲ የጴጥሮስን መልሶች እናስብ እርሱ የሰውን ዘር ሁሉ ባዳነው የሐጢያቶች ስርየት የኢየሱስ ጥምቀትና ደም ወንጌል ተባርኮዋል፡፡

ስለዚህ ጴጥሮስ *«አዎ ጌታ ሆይ እንደምወድህ ታውቃለህ»* ማለት ችሎ ነበር ይህ የፍቅር ኑዛዜ የመነጨው በኢየሱስ ስርየት ወንጌል ላይ ካለው እምነቱ ነበር ጴጥሮስ ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በወሰደበት እውነተኛ የሐጢያቶች ስርየት ወንጌል አምኖዋል ይህም ሰዎች ከጉድለቶቻቸውና ከስጋ ድክመቶቻቸው የተነሳ የሚፈጽሙዋቸውን የወደፊት ሐጢያቶች በሙሉ ይጨምራል፡፡

ጴጥሮስ የሐጢያቶችን ስርየት በሚያስገኘው ወንጌል በጽናት አመነ ኢየሱስ የእግዚአብሄር በግ እንደነበረም ስላመነ ያለ ምንም ማመንታት ለጌታ መልስ መስጠት ቻለ የኢየሱስ ደህንነት የመጣው የሐጢያቶችን ስርየት ከሚያስገኘው ወንጌል

ነው በዚህም ጴጥሮስ በየቀኑ ከሚሰራቸው ሐጢያቶች በሙሉ ዳነ ጴጥሮስ የአለምን ሐጢያቶች ሁሉ በሚያስተሰርየው ወንጌል አማካይነት በደህንነት አመነ፡፡

እናንተም ደግሞ እንደ ጴጥሮስ ናችሁን? ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በስርየቱ በጥምቀቱና በደሙ ወንጌል የወሰደውን ኢየሱስን መውደድና ማመን ትችላላችሁን? እንዴት እርሱን ላታምኑትም ሆነ ላትወዱት ትችላላችሁ? ሌላ መንገድ የለም፡፡ ኢየሱስ የወሰደው ያለፉትን ወይም የአሁኖቹን ሐጢያቶች ብቻ ከሆነና የወደፊት ሐጢያቶችንን ለእኛ ከተወልን አሁን እንደምናመሰግነው ልናመሰግነው ባልቻልንም ነበር ከዚህ በተጨማሪም ሁላችንም ሲዖል እንደምንወርድ የተረጋገጠ ነው ስለዚህ ሁላችንም የሐጢያቶችን ስርየት በሚያስገኘው ወንጌል ማመናችን እንዳዳነን መመስከር አለብን፡፡

ስጋ ሁልጊዜም ሐጢያትን ለመስራት ያዘነብላል ስለዚህ እኛም ሁልጊዜ ሐጢያትን እንሰራለን ከዚህ የተነሳ ኢየሱስ በሰጠን የሐጢያቶችን ስርየት በሚያስገኘው የተትረፈረፈ ወንጌል በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ወንጌል ማመናችን እንዳዳነን መመስከር አለብን፡፡

የኢየሱስ ጥምቀትና ደም በሆነው የስርየት ወንጌል ባናምን ኖሮ ማንም አማኝ ከዕድሜ ልክ ሐጢያቶቹ ባልዳነም ነበር በተጨማሪም በየጊዜው በመናዘዝና ንስሐ በመግባት ከዕድሜ ልክ ሐጢያቶቻችን ሁሉ ድነን ቢሆን ኖሮ ምናልባትም ጻድቃን ሆነን ለመቆየት በጣም ሰነፎችና ሁልጊዜም በልቦቻችን ውስጥ ሐጢያት ያለብን ሰዎች እንሆን ነበር፡፡

ይህ ቢሆን ኖሮ ሐጢያተኛ ወደ መሆን እንመለስና ኢየሱስን አንወደውም ወይም ወደ እርሱ አንቀርብም ነበር በኢየሱስ ደህንነትም ማመንና እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ ድረስም እርሱን መከተል አንችልም ነበር፡፡

ኢየሱስ የሐጢያቶች ስርየት የሚገኝበትን ወንጌል ሰጥቶን የምናምነውን ሰዎች አድኖናል እርሱ ፍጹም የሆነ አዳኝ በመሆን በእውነት እንወደው ዘንድ የዘወትር መተላለፎቻችንን ሁሉ አነጻ፡፡

እኛ ምዕመናኖች የሐጢያቶቻችንን ስርየት ያስገኘውን የኢየሱስን ጥምቀትና ደም ወንጌል ከመውደድ ማምለጥ አንችልም ምዕመናኖች ሁሉ ኢየሱስ በሰጠን የሐጢያቶችን ስርየት በሚያስገኘው ወንጌል አማካይነት ኢየሱስን ለዘላለም መውደድና የደህንነት ፍቅር ምርኮኞች መሆን እንችላለን፡፡

ውዶች! ኢየሱስ ኢምንት ሐጢያትን እንኳን ትቶ ቢሆን ኖሮ በኢየሱስ ማመንና የሐጢያቶችን ስርየት ለሚያስገኘው ወንጌልም ምስክር መሆን ባልቻላችሁ ነበር የእግዚአብሄር አገልጋይ ሆናችሁም መስራት ባልቻላችሁ ነበር፡፡

ነገር ግን የሐጢያቶችን ስርየት በሚያስገኘው ወንጌል ብታምኑ ከሐጢያቶቻችሁ ሁሉ መዳን ትችላላችሁ በኢየሱስ ቃል ውስጥ የተጻፈውን እውነተኛውን የስርየት ወንጌል ስትገነዘቡ ከሐጢያቶቻችሁ ሁሉ እንድትድኑ ይፈቅድላችኋል፡፡

## «ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?»

*ኢየሱስን ከማንኛውም ሌላ ነገር ይበልጥ እንድንወደው ያደረገን ምንድን ነው?*

*ኃጢያቶቻችንን በሙሉ የወደፊት ሐጢያቶቻችንንም ሁሉ ሳይቀሩ ባስወገደልን በጥምቀቱ አማካይነት ለእኛ ያለው ፍቅር ነው፡*

እግዚአብሄር ሙሉ በሙሉ የሐጢያቶችን ስርየት በሚያስገኘው ወንጌል ለሚያምኑ አገልጋዮቹ ጠቦቶቹን በአደራ ሰጥቶዋል ኢየሱስ ሦስት ጊዜ *«ስምዖን የዮና ልጅ ከእነዚህ ይልቅ ትወድደኛለህን?»* በማለት ሲጠይቀው ጴጥሮስ በእያንዳንዱ ጊዜ *«አዎን ጌታዬ እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ»* በማለት መለሰ አሁን ስለ ጴጥሮስ መልሶች እናስብ ይህ የፈቃዱ መግለጫ ሳይሆን የሐጢያቶችን ስርየት በሚያስገኘው ወንጌል ላይ ያለው እምነቱ እንደነበር ማየት እንችላለን።

አንድን ሰው ስንወድና ያም ፍቅር በፈቃዳችን ላይ የተመሰረተ ሲሆን ስንደክም ሊንገዳገድ ይችላል ነገር ግን ያ ፍቅር በእግዚአብሄር ፍቅር ጉልበት ላይ የተመሰረተ ከሆነ ለዘላለም ይኖራል የእግዚአብሄር ፍቅር ማለትም ለሐጢያቶቻችን የሆነው የተትረፈረፈ ስርየት የኢየሱስ ጥምቀት ውሃና መንፈስ ደህንነት ልክ እንደዚያ ነው።

የሐጢያቶችን ስርየት በሚያስገኘው ወንጌል ላይ ያለን እምነታችን ለጌታ ያለን ፍቅርና ስራ መሰረት መሆን አለበት እርሱን የወደድነው በፈቃዳችን ብቻ ከሆነ ነገ ተሰናክለን እንወድቃለን መጨረሻችንም ስለ በደሎቻችን ራሳችንን መጥላት ይሆናል ነገር ግን ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ የአዳምን ሐጢያት ያለፉትን የቀን ተቀን ሐጢያቶቻችንን የዛሬውንና የወደፊቱን ሐጢያቶቻችን እንደዚሁም የሕይወት ዘመን ሐጢያቶቻችንን አንጽቷል እርሱ ከደህንነቱ ማንንም አላስቀረም።

ይህ ሁሉ እውነት ነው ፍቅራችንና እምነታችን የተመሰረቱት በፈቃዳችንና በጽናታችን ላይ ቢሆን ኖሮ በእምነታችን እንወድቅ ነበር ነገር ግን ፍቅራችንና እምነታችን ኢየሱስ በሰጠን የሐጢያቶች ስርየት ወንጌል ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ቀድሞውኑም የእግዚአብሄር ልጆችና ጻድቃን ሆነናል

እኛ በውሃውና በመንፈሱ ደህንነት ስለምናምን ሐጢያት የለብንም።

ደህንነታችን የመጣው በእኛ ዘንድ መልካምነት ስላለ ሳይሆን ከእግዚአብሄር ፍቅርና በሐጢያቶች ስርየት አማካይነት ከእውነተኛው የደህንነት ሕጉ ከመሆኑ እውነታ የተነሳ በሕይወታችን ምንም ያህል ጎዶሎዎች ወይም ደካሞች ብንሆንም ጻድቃን ነን መንግስተ ሰማይ ገብተንም ጌታን ለዘላለም እናመሰግነዋለን ይህንን ታምናላችሁን?

1ኛ ዮሐንስ 4:10 እንዲህ ይላል *«እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለኃጢያታችንም ማስተሰረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም»* በስርየት ወንጌል በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ወንጌል ላይ እምነት ይኖረን ዘንድ ኢየሱስ በውሃና በመንፈስ አዳነን።

እግዚአብሄር የሐጢያቶችን ስርየት በሚያስገኘው ወንጌል ባያድነን ኖሮ ምንም ያህል በግለት ብናምንም መዳን ባልቻልንም ነበር ኢየሱስ ግን በልቦቻችንና በስጋችን የምንሰራቸውን ሐጢያቶች በሙሉ አጠበልን።

እኛ ጻድቃን እንሆን ዘንድ የስርየት ወንጌል በሆኑት የውሃውና የመንፈሱ ቃሎች ላይ ባለን እምነት አማካይነት ስለ ደህንነታችን እርግጠኞች መሆን አለብን የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ያስተሰረየው ወንጌል ከኢየሱስ ጥምቀትና ከደሙ የተዋቀረ ነው የስርየት ወንጌል የእውነተኛ እምነት ይዘት እውነተኛ የደህንነት መሰረትና ወደ እግዚአብሄር መንግስት የመግቢያውም ቁልፍ ነው።

# የራሳችንን የፈቃድ እምነት መተው አለብን




በአንድ ሰው ፈቃድ የተያዘ እምነት ወይም ፍቅር እውነተኛ ፍቅርም ሆነ እውነተኛ እምነት አይደለም በዚህ አለም ላይ መጀመሪያ በበጎ ፈቃድ በኢየሱስ ያመኑ ብዙዎች አሉ በኋላ ግን በልቦቻቸው ውስጥ ካለው የሐጢያት ስቃይ የተነሳ እምነታቸውን ፈጽመው ትተውታል።

ነገር ግን ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ኢምንት የሆኑ በደሎችን ብቻ ሳይሆን ከእውቀት ማነስ የተነሳ የተሰሩ ታላላቅ ሐጢያቶችንም እንዳነጻ መገንዘብ አለብን።

ኢየሱስ በዮሐንስ 13 ላይ የእርሱ ደህንነት ምን ያህል ሁሉን አቀፍና ለዘለቄታውም ውጤታማ እንደሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ለማስተማር ከመሰቀሉ በፊት ደቀ መዛሙርቱን ሰበሰባቸው ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እራት ከበላ በኋላም የተትረፈረፈውን ደህንነቱን እውነት በልቦቻቸው ላይ ለመቅረጽ ተነስቶ እግሮቻቸውን አጠበ ሁላችንም ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግሮች በማጠብ ያስተማራቸውን የስርየት ወንጌል ማወቅና ማመን ይገባናል።

ጴጥሮስ ግን መጀመሪያ ላይ ኢየሱስ እግሮቹን እንዳያጥበው አጽንቶ ተቃውሞ ነበር *«የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም!»* ይህ በራሱ ፈቃድ የያዘው እምነት መግለጫ ነበር ኢየሱስ ግን እንዲህ ሲል ተናገረው *«እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም በኋላ ግን ታስተውዋለህ።»*

አሁን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ከአስተውሎታችን በላይ የነበሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎች መረዳት እንችላለን ሐጢያተኛው በሙሉ ልቡ በማመን ጻድቅ ይሆን ዘንድ የሚፈቅድለት የእውነት ቃል የውሃውና የመንፈሱ የሐጢያቶች ስርየት ወንጌል ይህ ነው።

ጴጥሮስ ኢየሱስን ከማግኘታቸው በፊት ያደርጉ እንደነበረው ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ጋር አሳ ለማጥመድ ሄደ ያን ጊዜ ኢየሱስ በፊታቸው ተገለጠና ጠራቸው ኢየሱስ ቁርስ አዘጋጅቶላቸው ነበር ቁርስ እየበሉ ሳለ ጴጥሮስ ኢየሱስ ቀደም ብሎ የተናገራቸውን ቃሎች ትርጉም ተረዳ *«እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም በኋላ ግን ታስተውለዋለህ»* በመጨረሻ ከዚህ በፊት እግሮቹን ባጠበው ጊዜ ኢየሱስ በእርግጥም ምን ማለቱ እንደነበር ተገነዘበ።

«ጌታ ሐጢያቶቼን በሙሉ አጠበልኝ ከድክመቶቼ የተነሳ የሰራኋቸው ሐጢያቶች በሙሉ ወደፊት የምሰራቸውንም ሐጢያቶች በሙሉ ጨምሮ ነጽተዋል» ጴጥሮስ በራሱ ፈቃድና ውሳኔ የያዘውን እምነት ትቶ የሐጢያቶች ስርየት ወንጌል በሆነው በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ላይ ጸንቶ መቆም ጀመረ።

ከቁርስ በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን እንዲህ ሲል ጠየቀው *«ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?»* አሁን ጴጥሮስ በኢየሱስ ፍቅር በእምነት ተጠናክሮ *«አዎ! እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ»* በማለት መሰከረ ጴጥሮስ መመስከር የቻለው ኢየሱስ *«ከዚህ በኋላ ታስተውለዋለህ»* ሲል ምን ማለቱ እንደነበር ስለተገነዘበ

ነበር እርሱ የሐጢያቶች ስርየት ወንጌል የሆነውን የኢየሱስ ጥምቀትና ደም እምነት እውነተኛ እምነቱን መመስከር ችሎ ነበር፡፡

## ከዚያም በኋላ እርሱ እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆነ

ከዚያ ልምምድ በኋላ ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት እስከ መጨረሻ እስትንፋሳቸው ድረስ ወንጌልን ሰበኩ ክርስቲያኖችን ያለ ምህረት ሲያሳድድ የነበረው ጳውሎስም እንኳን በእነዚያ የሮም ንጉሰ ነገስት ክፉ ቀናቶች ወቅት ወንጌልን መስክሮዋል፡፡

*የእግዚአብሔር እውነተኛ*
*አገልጋይ የምትሆኑት*
*እንዴት ነው?*

*ለሐጢያቶቹ ሁሉ በሆነው*
*ዘላለማዊ ስርየቱ*
*በማመን ነው፡፡*

ከአስራ ሁለቱ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መካከል ይሁዳ ኢየሱስን ሸጠው በኋላም ራሱን ሰቀለ የእርሱን ቦታ የወሰደው ሐዋርያው ጳውሎስ ነበር ደቀ መዛሙርት በመካከላቸው ማትያስን መርጠው ነበር ነገር ግን እግዚአብሄር የመረጠው ጳውሎስን ነበር ስለዚህ ጳውሎስ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ሆኖ

ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ጋር የሐጢያቶችን ስርየት የሚያስገኘ ውን ወንጌል ሰበከ፡፡

አብዛኞቹ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሞቱት ሰማዕታት ሆነው ነው የሞት ዛቻ ሲደርስባቸው እንኳን እምነታቸውን አልካዱም እውነተኛውን ወንጌል መስበካቸውን ቀጠሉ፡፡

እንዲህ በማለት ሰብከው ይሆናል «ኢየሱስ ክርስቶስ የስጋችሁን ሐጢያቶች በሙሉ በጥምቀቱና በደሙ ማለትም የሐጢያቶችን ስርየት በሚያስገኘው ወንጌሉ አንጽቶዋል ኢየሱስ በዮርዳኖስ ጥምቀቱ ሐጢያቶቻችሁን በሙሉ ወስዶ ስለ እናንተ በመስቀል ላይ ፍርድን ተቀብሎዋል በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ወንጌል ደሙ እመኑና ዳኑ፡፡»

እውነተኛውን ወንጌል መስማትና በእርሱ ማመን በእርግጥም ብዙዎችን አድኖዋል ይህ በኢየሱስ ጥምቀት በደሙና በመንፈስ ወንጌል ላይ ያለ የእምነት ሐይል ነበር፡፡ ደቀ መዛሙርት «ኢየሱስ አምላክና አዳኝ ነው» በማለት የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሰበኩ እናንተና እኔ አሁን የኢየሱስን ጥምቀትና ደም ወንጌል ደህንነታችን አድርገን መስማት የቻልነውና ከሐጢያት የዳንነው እነርሱ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ስለመሰከሩ ነው ከእግዚአብሄር ወሰን የለሽ ፍቅርና ከኢየሱስ የተሟላ ደህንነት የተነሳ ሁላችንም የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሆነናል፡፡

ሁላችሁም ታምናላችሁን ኢየሱስ አብዝቶ ስለወደደን የሐጢያቶች ስርየት የሆነውን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሰጠን እኛም ጻድቃን የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሆነን ኢየሱስ እውነተኛውን የስርየት ወንጌል ለማስተማር የደቀ መዛሙርቱን እግሮች አጠበ፡፡

ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግሮች ያጠበው የአለም ሐጢያቶች በሙሉ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ የምንሰራቸውን ሐጢያቶች ጨምሮ እርሱ በተጠመቀና በመስቀል ላይ ደሙን

ባፈሰሰ ጊዜ ሙሉ በሙሉ እንደነጹ እነርሱንና እኛን ለማስተማር ነው ለፍቅሩና ለስርየት ወንጌሉ ኢየሱስን እናመሰግነዋለን።

ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግሮች በማጠብ ሁለት ነገሮችን አስተምሮናል የመጀመሪያው *«እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቀውም በኋላ ግን ታስተውለዋለህ»* ብሎ በተናገረው መሰረት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ የስርየት ወንጌል በሆነው የኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ መንጻታቸውን ለማስተማር ነበር

ሁለተኛው ትምህርት ኢየሱስ ሐጢያተኞችን ለማዳንና ጻድቃን ለማድረግ ራሱን ዝቅ እንዳደረገ እኛ ዳግም የተወለድን ሰዎች የስርየትን ወንጌል በመስበክ ሌሎችን ማዳን የሚገባን መሆኑ ነው መጀመሪያ የመጣነው እኛ በኋላ የሚመጡትን እነርሱን ማገልገላችን ተገቢ ነው።

ኢየሱስ በፋሲካው በአል ቀን የደቀ መዛሙርቱን እግሮች ያጠበባቸው ሁለቱ ምክንያቶች ግልጽ ናቸው እነርሱ አሁንም በእርሱ ቤተክርስቲያን ውስጥ ይገኛሉ።

ደቀ መዝሙር በፍጹም ከመምህሩ አይበልጥም ስለዚህ እኛ ም ወንጌልን ለአለም እንሰብካለን ኢየሱስን እንደምናገለግል ሆነንም እናገለግለዋለን ቀደም ብለን የዳንን ሰዎች ከእኛ በኋላ የሚመጡትን ልናገለግላቸው ይገባናል ኢየሱስ ይህንን ለማስተማር የደቀ መዛሙርቱን እግሮች አጠበ በተጨማሪም የጴጥሮስን እግሮች በማጠብ ዳግመኛ በፍጹም በዲያብሎስ እንዳንሳሳት እርሱ ፍጹም አዳኝ እንደሆነ አሳየን።

ሁላችሁም የሐጢያቶችን ስርየት በሚያስገኘው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን መዳን ትችላላችሁ ኢየሱስ በጥምቀቱ በስቅለቱና በትንሳኤው ሐጢያቶቻችንን በሙሉ አንጽቷል ለዘላለም ከአለም ሐጢያቶች መዳን የሚችሉት በእርሱ ወንጌል የሚያምኑ ብቻ ናቸው።

# የየዕለቱን ኃጢያቶቻችን በሙሉ ባጠበልን ወንጌል እምነት ይኑራችሁ

የስርየት ወንጌል በሆነው የውሃውና የመንፈሱ ቃሎች በማመን የዲያብሎስን ማታለያዎች በሙሉ መቁረጥ እንችላለን ሰዎች በቀላሉ በዲያብሎስ ይታለላሉ ዲያብሎስም ሁልጊዜ በጆሮዎቻቸው ያንሾካሹካል የሰዎች ስጋ በአለም ላይ ያለ ማቋረጥ ሐጢያቶችን እንደሚሰራ ከታወቀ እንዴት ያለ ሐጢያት ሊሆኑ ይችላሉ? ሰዎች ሁሉ ሐጢያተኞች ናቸው፡፡

እኛ ግን መልሱን እናውቃለን «ኢየሱስ በጥምቀቱ የስጋችንን ሐጢያቶች በሙሉ እንደወሰደ ካወቅን በኋላ አንድ አማኝ እንዴት ሐጢያት ሊኖርበት ይችላል? ኢየሱስ የሐጢያትን ደመወዝ ሙሉ በሙሉ ከፍሎዋል ስለዚህ ለእኛ የቀረልን ምን የምንከፍለው ደመወዝ አለ?»

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የማናምን ከሆንን የዲያብሎስ ቃሎች ምክንያታዊ ይመስላሉ ነገር ግን ወንጌል ከእኛ ወገን ከሆነ በእግዚአብሄር ቃል እውነት ላይ የማይናወጥ እምነት ሊኖረን ይችላል፡፡

ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ዳግም የመወለድ ወንጌል እምነት ሊኖረን ይገባል እውነተኛ እምነት በኢየሱስ ጥምቀት በመስቀል ላይ ደሙ በሞቱና በትንሳኤው ወንጌል ማመን ነው፡፡

የተቀደሰውን የመገናኛ ድንኳን ሞዴል ስዕል አይታችሁ ታውቃላችሁን? ይህ ትንሽዬ የድንኳን ቤት ነው ቤቱ በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን ውጭኛው ክፍል ቅድስት ስፍራ ውስጠኛው ክፍል ደግሞ የስርየት መክደኛው ያለበት ቅድስተ ቅዱሳን የተባለው መቅደስ ነው፡፡

በተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን ውጫዊ አደባባይ ላይ የቆሙ በአጠቃላይ 60 ምሰሶች አሉ ቅድስቱ ስፍራ 48 ሳንቃዎች አሉት የእግዚአብሄርን ቃሎች ትርጉም ለመረዳት የተቀደሰውን

የመገናኛው ድንኳን በአእምሮዋችን መሳል ይገባናል፡፡

## የመገናኛው ድንኳን አደባባይ የመግቢያ በር የተሰራው ከምንድነው?

*የመገናኛው ድንኳን አደባባይ የመግቢያ በር የተሰራው ከምንድን ነው?*

*የተሰራው ከሰማያዊ ከኃምራዊ ከቀይ ግምጃና ከጥሩ በፍታ መጋረጃ ነው፡፡*

የመገናኛው ድንኳን አደባባይ የመግቢያ በር በዘጸአት 27:16 ላይ ተገልጦዋል *«ለአደባባዩም ደጅ ከሰማያዊ ከኃምራዊ ከቀይም ግምጃ ከጥሩ በፍታም በጥልፍ አሰራር የተሰራ ሃያ ክንድ መጋረጃ ይሆናል ምሰሶዎቹም አራት እግሮችም አራት ይሆናል»* ለመገናኛው ድንኳን አደባባይ የመግቢያ በር ጥቅም ላይ የዋሉት ቁሶች ሰማያዊ ሐምራዊና ቀይ ግምጃ እንደዚሁም ጥሩ በፍታ ነበሩ ይህም በደንብ የተፈተለና በጣም ውብ ነበር፡፡

እግዚአብሄር እያንዳንዱ ሰው የመግቢያውን በር ለማግኘት ቀላል እንዲሆንለት የመግቢያውን በር በሰማያዊ በሐምራዊና በቀይ ግምጃ በቀለም አሸብርቆ እንዲፈትል ሙሴን አዘዘው ከሰማያዊ ከሐምራዊ ከቀይ ግምጃና ከጥሩ በፍታ የተሰራው የመግቢያው በር በአራት ምሰሶች ላይ ተንጠልጥሎ ነበር፡፡

እነዚህ አራቱ ቁሳ ቁሶች እግዚአብሄር በኢየሱስ ጥምቀትና ደም አማካይነትና እርሱ አምላክ ስለመሆኑ በልጁ ያመኑትን ሰዎች

ሁሉ የሚያድንበትን የእግዚአብሄርን የደህንነት ንድፍ ያመላክታሉ::

የተቀደሰውን የመገናኛ ድንኳን ለመስራት ጥቅም ላይ የዋሉት እያንዳንዱ ቁሳቁሶች የተለየ ትርጉም አላቸው የሰውን ዘርም በኢየሱስ አማካይነት ለማዳን ያለውን የእግዚአብሄር ቃልና የእርሱን እቅዶች ያመላክታሉ::

ለተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን አደባባይ የመግቢያ በር ጥቅም ላይ የዋሉት ምን ያህል የተለያዩ ቁሳቁሶች ነበሩ? አራት የተለያዩ ቁሳቁሶች ጥቅም ላይ ውለዋል እነርሱም ሰማያዊ ሐምራዊ ቀይ ግምጃና ጥሩ በፍታ ነበሩ እነዚህ አራቱ ዳግም በምንወለድበት ወንጌል ላይ ያለንን እምነት በማጠንከር ረገድ በጣም ወሳኝ ናቸው አስፈላጊ ባይሆኑ ኖሮ ይህ መረጃ እንዲህ ባለ ዝርዝር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባልተጻፈ ነበር:: ለተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን አደባባይ የመግቢያ በር ጥቅም ላይ የዋሉት ቁሳቁሶች በሙሉ የደህንነታችንን አቢይ ትርጉሞች ያመላክታሉ ስለዚህ እግዚአብሄር እነዚህን ነገሮች ለሙሴ ገለጠለትና በትክክል እንደተነገረው እንዲያደርግ ነገረው::

## ሰማያዊ፣ ኃምራዊና ቀይ ግምጃ በእግዚአብሔር ወንጌል ውስጥ ምን ማለት ናቸው?

*ለመገናኛው ድንኳን ጥቅም ላይ የዋሉት ቁሶች የሚያመለክቱት ምንድን ነው?*

*በጥምቀቱና በደሙ አማካይነት የሆነውን የኢየሱስን ደህንነት ነው::*

በተቀደሰው የመገናኛ ድንኳን ውስጥ በቅድስቱና በቅድስተ ቅዱሳኑ መካከል ለተንጠለጠለው መጋረጃ ሰማያዊ ሐምራዊ ቀይ ግምጃና ጥሩ በፍታ ዳግም ጥቅም ላይ ውለዋል በአመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባው ሊቀ ካህን የሚለብሳቸው ልብሶችም ከተመሳሳይ ቁሳ ቁሶች የተሰሩ ነበሩ፡፡

ሰማያዊው ግምጃ የኢየሱስን ጥምቀት ያመላክታል በ1ኛ ጴጥሮስ 3፡21 ላይ እንዲህ ይላል *«ይህም ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል»* ጴጥሮስ በዚህ ቁጥር ላይ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ የወሰደበት የኢየሱስ ጥምቀት የስርየት ደህንነት ምሳሌ እንደሆነ አረጋግጦዋል ሐጢያቶቻችን በሙሉ በጥምቀቱ አማካይነት ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል ስለዚህ የኢየሱስን ጥምቀት የሚያመላክተው ሰማያዊ ግምጃ የደህንነት ቃል እጅግ አስፈላጊ ክፍል ነው፡፡

ቀዩ ግምጃ የኢየሱስን ደም ያመላክታል ሐምራዊው ግምጃም የእርሱን መለኮታዊነት ---ኢየሱስ ንጉስና አምላክ የመሆኑን ማዕረግ ያመላክታል የግምጃው ሦስቱ ቀለማት በኢየሱስና በደህንነቱ ላይ ላለን እምነታችን አስፈላጊ ነበሩ፡፡ ሊቀ ካህኑ ከውጭ የሚለብሰው ያማረ መጎናጸፊያ ኤፉድ ተብሎ ይጠራል የኤፉዱ ቀሚስም እንደዚሁ ሰማያዊ ነበር ሊቀ ካህኑ በንጹህ የወርቅ ምልክት ላይ «ቅድስና ለእግዚአብሄር» የሚል የተቀረጸበት ጥምጣም በራሱ ላይ አድርጎዋል ምልክቱ በሰማያዊ ፈትል ከጥምጣሙ ጋር ተያይዞዋል፡፡

# በሰማያዊው ግምጃ የተገለፀው እውነት

*ሰማያዊ ግምጃ ምንን ያመለክታል?*

*የኢየሱስን ጥምቀት።*

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰማያዊውን ግምጃ ትርጉም ተመልክቻለሁ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰማያዊ ምን ይላል? በሰማያዊ በሐምራዊና በቀይ ግምጃዎች መካከል ያለውን ሰማያዊውን ግምጃ ማስተዋል ይኖርብናል።

ሰማያዊ ግምጃ «ውሃውን» ማለትም የኢየሱስን ጥምቀት ያመላክታል ኢየሱስ ክርስቶስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠምቆዋል። (ማቴዎስ 3:15)

ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በጥምቀቱ ባይወስድ ኖሮ በእግዚአብሄር ፊት መቀደስ ባልቻልንም ነበር ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ ወደዚህ አለም መምጣትና በዮርዳኖስ ወንዝ በአጥማቂው ዮሐንስ መጠመቅ ነበረበት።

በተቀደሰው የመገናኛ ድንኳን አደባባይ የመግቢያ በር ላይ ሰማያዊ ግምጃ የተደረገበት ምክንያት ያለ ኢየሱስ ጥምቀት መቀደስ ስለማንችል ነው።

ቀዩ ግምጃ የእርሱን ደም የኢየሱስን ሞት ያመላክታል ሐምራዊው የኢየሱስን አምላክነት ማለትም የኢየሱስን ማዕረግ ያመላክታል *«ብፁዕና ብቻውን የሆነ ገዥ፣ የነገስታት ንጉስና የጌቶች ጌታ» (1ኛ ጢሞቴዎስ 6:15)*

እውነቱ ቀዩ ግምጃ ለሰው ዘር ሁሉ የሐጢያትን ደመወዝ ለመክፈል በመስቀል ላይ የደማውን የክርስቶስ ደም የሚያመላክት መሆኑ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱ አማካይነት የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ በስጋ ወደዚህ አለም መጣ ራሱን በመስቀል ላይ መስዋዕት በማድረግም የሐጢያትን ደመወዝ በሙሉ ከፈለ የኢየሱስ ጥምቀትና ደም በብሉይ ኪዳን በተቀደሰው የመገናኛ ድንኳን ላይ ጥቅም ላይ በዋሉት ግምጃዎች ቀለማት አማካይነት የተተነበየ እውነተኛ የስርየት ወንጌል ነው፡፡

የመገናኛው ድንኳን ምሰሶዎች ከግራር እንጨት መያዣዎቹም ከናስ የተሰሩ ነበሩ የናሱ መያዣዎች በብር ማሰሪያዎች ተሸፍነው ነበር፡፡

ሐጢያተኞች በሙሉ ለሐጢያቶቻቸው የተፈረደባቸው የሐጢያት ደመወዝ ሞት ስለሆነ ነው በብሉይ ኪዳን ዘመን አንድ ሰው አዲስ ሕይወት ለማግኘት በእግዚአብሄር መባረክ ከመቻሉ በፊት ለኃጢያቶቹ/ቿ መስዋዕት ማቅረብ ነበረበት፡፡

ነገር ግን በአዲስ ኪዳን በተቀደሰው የመገናኛ ድንኳን ሰማያዊ ግምጃ የተመሰለው የኢየሱስ ጥምቀት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶዋል ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን ወደ መስቀል ወሰደ ደማ ለእነርሱም ተፈረደበት እንዲህ በማድረጉም በስርየት ወንጌል እምነት ያለንን ሰዎች ሁሉ አዳነን እርሱ የነገስታት ንጉሥና ቅዱስ አምላክ ነው፡፡

የተወደዳችሁ ክርስቲያኖች የኢየሱስ ጥምቀት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በመውሰድ ያዳነን የኢየሱስ ማዳን ነው አምላክ የሆነው ኢየሱስ በስጋ ወደ አለም መጣ (ሐምራዊው ግምጃ) የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድም ተጠመቀ (ሰማያዊው ግምጃ) በእኛ ፋንታ ፍርድን ለመቀበልም በመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰ (ቀዩ ግምጃ) የኢየሱስ ጥምቀት እርሱ

ለሰው ዘር ሁሉ እውነተኛ አዳኝ እንደሆነ ያለጥርጥር ያስተምረናል፡፡

ይህንን ለተቀደሰው የመገናኛ ድንኳን የመግቢያ በር ጥቅም ላይ በዋሉት ቀለማቶች ውስጥም ማየት እንችላለን፡፡ ከሰማያዊ ከሐምራዊ ከቀይ ግምጃና ከጥሩ በፍታ የተ ፈተለው የመግቢያው በር መጋረጃ የእግዚአብሄርን ደህንነት እውነት በግልጽ የሚነግረን ነበር ይህ ለስርየት ደህንነት ፈጽሞ አስፈላጊ ነበር፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ሐጢያተኞችን ያለ እቅድ እንዲያው በዘፈቀደ እንዳላዳነን ለተቀደሰው የመገናኛ ድንኳን የመግቢያ በር ጥቅም ላይ ከዋሉት ተመሳሳይ ቁሳቁሶች ማየት እንችላለን እርሱ የእግዚአብሄርን ዝርዝር እቅድ በጥንቃቄ በመታዘዝ የሰውን ዘር ደህንነት ለመፈጸም ተጠመቀ ተሰቀለ ከሙታንም ተነሳ ኢየሱስ የስርየት ወንጌል ቁሳቁሶች በሆኑት በሰማያዊው በሐምራዊውና በቀዩ ግምጃ በእርሱ ማዳን ያመኑትን ሁሉ አዳናቸው፡፡

## የብሉይ ኪዳኑ የናስ የመታጠቢያ ሰን በአዲስ ኪዳን የጥምቀት ጥላ ነበር

*ካህናቱ ወደ ቅድስቱ ክፍል*
*ከመግባታቸው በፊት እጃቸውንና*
*እግራቸውን ለምን ይታጠባሉ?*

*ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት ያለ ኃጢያት*
*መቆም ስለነበረባቸው ነው፡፡*

የመታጠቢያው ሰንም የተሰራው ከናስ ነበር ናስ የሚያመላክተው ኢየሱስ የተሰቃየበትን ፍርድ ነው የውሃ መያዣው ሐጢያቶቻችን በሙሉ እንደነጻ የሚነግረንን የወንጌል ቃል ያመላክታል::

ይህም በየቀኑ የምንሰራቸው ሐጢያቶች እንዴት እንደተወገዱ ያሳየናል የሰው ዘር በየቀኑ የሚሰራቸው ሐጢያቶች በኢየሱስ ጥምቀት ቃሎች እምነት አማካይነት መንጻት ይችላሉ::

የሚቃጠል መስዋዕት መሠውያው ፍርድን ያመላክታል በሌላ አነጋገር ሰማያዊ የሆነው የኢየሱስ ውሃ የሐጢያቶች ስርየት በአጥማቂው ዮሐንስ የሆነው የኢየሱስ ጥምቀት ወንጌል ነው (ማቴዎስ 3:15፤1ኛ ዮሐንስ 5:5-10) ይህም በስርየት አማካይነት የደህንነትን ወንጌል የሚመሰክር የምስክርነት ቃል ነው::

በ1ኛ ዮሐንስ 5 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ አለምን ያሸንፋልና አለምን የሚያሸንፈው እምነታችን ነው የሚመሰክሩት መንፈሱ፣ ደሙና ውኃው ሶስት ናቸውና ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ»* እርሱ በእግዚአብሄር ልጅ የሚያምን ሰው በውስጡ የውሃው የደሙና የመንፈስ ምስክርነት እንዳለው ይነግረናል::

እግዚአብሄር በስርየቱ ወንጌል እምነት አማካይነትና ወደተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን በመግባት እንድንቀደስ ፈቅዶልናል ስለዚህ አሁን በእምነት መኖር የእግዚአብሄርን ቃሎች መመገብ በእርሱ መባረክና የጻድቃን ሕይወትን መኖር እንችላለን የእግዚአብሄር ሕዝብ መሆን ማለት በስርየት ወንጌል እምነት አማካይነት መዳንና በተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን ውስጥ መኖር ማለት ነው::

ዛሬ ብዙ ሰዎች በተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን የመግቢያ በር ላይ ስላለው ስለ ሰማያዊው ሐምራዊውና ቀይ ግምጃ

ትርጉም ሳያስቡ ማመን ብቻ በቂ ነው ይላሉ አንድ ሰው እነዚህን ነገሮች ሳያውቅ በኢየሱስ አምኖ ከሆነ በልቡ ውስጥ አሁንም ገና ሐጢያት ስላለ እምነቱ እውነተኛ አይሆንም ይህ ሰው በስርየት በውሃ በደምና በመንፈስ ወንጌል አማካይነት ዳግም የመወለድን እውነት ባለማመኑ አሁንም ድረስ በልቡ ውስጥ ሐጢያት አለበት::

አንድ ሰው የማያውቀውን ሰው እንዲመዝን ቢጠየቅ አድማጩን ለማስደሰት ሲል «አዎ ይህንን ሰው አምነዋለሁ በእርግጥ ፈጽሞ አግኝቼው አላውቅም ነገር ግን አምነዋለሁ» ይላል አድማጩ ይህንን በመስማት የሚደሰት ይመስላችኋልን? ምናልባት አንዳንዶቻችሁ በሰዎች ጉዳዮች ውስጥ እንዲህ ታደርጉ ይሆናል ይህ ግን እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው መታመን አይደለም::

እግዚአብሔር በሰማያዊው (የኢየሱስ ጥምቀት) በሐምራዊው (የኢየሱስ መለኮታዊነት) እና በቀዩ (የኢየሱስ ደም) ግምጃ አማካይነት የኢየሱስ ደህንነት በሆነው የሐጢያቶች ስርየት ወንጌል እንድናምን ይፈልግብናል በኢየሱስ ከማመናችን በፊት እኛን ከሐጢያቶች ሁሉ እንዴት እንዳዳነን ማወቅ ይገባናል::

በኢየሱስ ስናምን እንዴት በውሃ (የኢየሱስ ጥምቀት) በደም (ሞቱ) እና በመንፈስ (ኢየሱስ አምላክ መሆኑ) ከሐጢያቶቻችንን ሁሉ እንዳዳነን ማወቅ ይገባናል::

በትክክል ስንረዳ እውነተኛና ሙሉ እምነት ይኖረናል እውነተኛ እምነት የሚመጣው የኢየሱስን ደህንነት የስርየትን ወንጌልና ኢየሱስ እውነተኛ የሰው ዘር አዳኝ የመሆኑን ምስክርነት በመረዳት ብቻ ነው::

በኢየሱስ ላይ የሚያላግጥ እምነትስ ምን ይመስላል? እስቲ እንመልከት::

# በኢየሱስ የሚያላግጥ እምነት

*ለእምነት እጅግ የሚያስፈልገው ምንድን ነው?*

*ትክክለኛ የሆነ የኢየሱስ ጥምቀት እውቀት*

ኢየሱስን በዘፈቀደ ማመን በእርሱ ማላገጥ እንደሆነ መገንዘብ ይኖርባችኋል «ማመን አስቸግሮኛል ነገር ግን እርሱ አምላክና የእግዚአብሄር ልጅ ስለሆነ የሆኖ ሆኖ በእርሱ ማመን ይኖርብኛል» ብላችሁ የምታስቡ ከሆነ በኢየሱስ ላይ እያላገጣችሁ ነው በእርግጥ ዳግም መወለድ የምትፈልጉ ከሆነ የስርየት ወንጌል በሆነው የኢየሱስ ጥምቀትና ደም ማመን አለ ባችሁ::

የስርየትን ወንጌል ሳያውቁ በኢየሱስ ማመን ጨርሶ በኢየሱስ ከአለማመንም የከፋ ነው የኢየሱስን ደም ወንጌል ብቻ መስበክ እውነትን ሳያውቁ በከንቱ መልፋት ነው::

ኢየሱስ ማንም ሄዶ በዘፈቀደ ያምን ዘንድ ወይም ያለ ምክንያት በእርሱ እምነት እንዲኖረው አይፈለግም እርሱ የስርየትን ወንጌል አውቀን በእርሱ እንድናምን ይፈልግብናል:: በኢየሱስ ስናምን የስርየት ወንጌል የኢየሱስ ጥምቀትና ደም እንደሆነ ማመን ይኖርብናል በኢየሱስ ስናምን በቃሉ አማካይነት የስርየትን ወንጌል መረዳትና ሐጢያቶቻችንንም ሁሉ እንዴት እንዳነጻልን በግልጽ ማወቅ ይኖርብናል::

በተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን የመግቢያ በር ላይ ያሉት ሰማያዊ ሐምራዊና ቀይ ግምጃ የሚያመላክቱት ምን እንደሆነ

ማወቅ ይኖርብናል ያን ጊዜ ለዘላለም የሚኖር እውነተኛ እምነት ሊኖረን ይችላል::

## የሰማያዊው የሐምራዊውና የቀዩ ግምጃ መገለጫ በሆነው በኢየሱስ ሳናምን ፈጽሞ ዳግም መወለድ አንችልም

*ወደ ቅደስቱ ስፍራ ከመግባታቸው*
*በፊት ካህናቱ ምን ያደርጋሉ?*

*በናሱ የመታጠቢያ ሰን ውስጥ ባለው ውሃ*
*እጃቸውንና እግራቸውን ይታጠባሉ::*

ጌታችን ኢየሱስ አድኖናል እንዴት ፈጽሞ እንዳዳነን ስንመለከት ጌታን እናመሰግናለን የተቀደሰውን የመገናኛውን ድንኳን መመልከት ይገባናል እርሱ በተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን ሰማያዊ ሐምራዊና ቀይ ግምጃ አማካይነት የስርየትን ወንጌል ቃሎች ሰጥቶናል ጌታን እናመሰግነዋለን እናወድሰዋለንም::

ሐጢያተኞች አስፈሪ በሆነ ፍርድ ውስጥ ሳያልፉ ወደ ቅድስቱ መግባት አይችሉም በሐጢያቶቹ ሳይፈረድበት ቅድስቱ ክፍል ውስጥ መግባት የሚችል ማነው? ይህ የማይቻል ነው ይህ ሰው ወደተከለከለው ስፍራ ከገባ በዚያው ቅጽበት እዚያው ይሞታል ሐጢያተኛ ቅድስቱ ስፍራ ገብቶ ፈጽሞ በሕይወት መኖር ሊጠብቅ አይችልም::

ጌታችን በተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን የመግቢያ በር ውስጥ በተደበቀው ምስጢር በኩል አድኖናል እርሱ በሰማያዊ በሐምራዊና በቀይ ግምጃዎች እንደዚሁም በጥሩ በፍታ አድኖናል በእነዚህ ነገሮች አማካይነትም የማዳኑን ምስጢር ነግሮናል፡፡

እናንተና እኔ የዳንነው በዚያ መንገድ አይደለምን? በሰማያዊው በሐምራዊውና በቀዩ ግምጃ ቃሎች ካላመናችሁ በስርየቱ ወንጌል አማካይነት ደህንነት ሊኖር አይችልም ሰማያዊው ቀለም እግዚአብሄርን አያመላክትም የሚያመላክተው ሌላ ምንም ሳይሆን የኢየሱስን ጥምቀት ነው ይህም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ የወሰደ የኢየሱስ ጥምቀት ነው፡፡

አንድ ሰው በሰማያዊው ግምጃ ሳያምን የሚቃጠለው መስዋዕት መሰውያ እስካለበት ስፍራ ድረስ መሄድ ይችላል ነገር ግን እግዚአብሄር ወደሚኖርበት ቅድስት ስፍራ መግባት አይችልም፡፡

ስለዚህ በተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን በር ውስጥ ከመግባታችን በፊት በሰማያዊው ግምጃ (የኢየሱስ ጥምቀት) በቀዩ ግምጃ (በመስቀሉ ደም) እና በሐምራዊ ግምጃ (ኢየሱስ አምላክና የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑ) ማመን ይኖርብናል እግዚአብሄር የሚቀበለንና የቅድስተ ቅዱሳኑን መጋረጃ አልፈን እንድንገባ የሚፈቀድልን ስናምን ብቻ ነው፡፡

አንዳንዶች ወደ መገናኛው ድንኳን አደባባይ ገብተው ውስጥ እንዳሉ ያስባሉ ይህ ግን ደህንነት አይደለም ለመዳን ምን ያህል ርቀን መሄድ ይኖርብናል? ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት መቻል አለብን፡፡

ወደ ቅደስተ ቅዱሳን ለመግባት የናሱን የመታጠቢያ ሰን ማለፍ ይኖርብናል የናሱ መታጠቢያ ሰን የሚያመላክተው የኢየሱስን ጥምቀት ነው በኢየሱስ ጥምቀት በየቀኑ

ከምንሰራቸው ሐጢያቶች በሙሉ መንጻትና ወደ ቅድስቱ ስፍራ በመግባት መቀደስ ይኖርብናል::

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካህናት ከመግባታቸው በፊት ራሳቸውን መታጠብ ነበረባቸው በአዲስ ኪዳንም ኢየሱስ የዕድሜ ዘመናቸውን ሐጢያቶች ማንጻቱን ለማመላከት የደቀ መዛሙርቱን እግሮች አጥቦዋል::

የእግዚአብሄር ሕግ እንዲህ ይላል *«የኃጢያት ደሞዝ ሞት ነው ነገር ግን የእግዚአብሔር ስጦታ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘላለማዊ ሕይወት ነው» (ሮሜ 6:23)* እግዚአብሄር ምንም ሳይቀር የሰዎችን ሐጢያቶች ኮንኖዋል ነገር ግን እነርሱን ወደ ልጁ አስተላልፎ እርሱ ላይ ፈረደበት ይህ የእግዚአብሄር ፍቅር የእርሱ ደህንነት ነው እውነተኛ ደህንነት የሚገኘው የኢየሱስን ጥምቀት ደም ሞትና ትንሳኤ የያዘውን የስርየት ወንጌል በማመን ብቻ ነው::

## ***አንድ ሰው ዳግም ይወለድ ዘንድ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በሆነው የሐጢያቶች ስርየት ወንጌል ላይ በጭራሽ ማላገጥ የለበትም***

*እኛ እንድናደርገው የተተወልን ብቸኛው ነገር ምንድን ነው?*

*በተፃፉት የእግዚብሔር ቃሎች በወንጌሉ ማመን ነው::*

እኔ ፈጽሞ በሌሎች ሰዎች አላላግጥም አንድ ሰው እኔ የማላውቀውን አንዳች ነገር ሲናገር እንዲያብራራልኝ በትህትና እጠይቀዋለሁ ነገር ግን ስለ ተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን እንደምታዎች በጠየቅሁ ጊዜ ማንም ሊነግረኝ አልቻለም።

ታዲያ ምን ላደርግ እችላለሁ? ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መመለስ ነበረብኝ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን የተነገረው የት ቦታ ላይ ነው? በዝርዝር የተብራራው በዘጸአት ውስጥ ነው አንድ ሰው ይህንን መጽሐፍ በጥንቃቄ ቢያነብ በተጻፉት የእግዚአብሄር ቃሎች አማካይነት ትርጉሙን መረዳት ይችላል።

ውድ ወዳጆች በደፈናው በኢየሱስ በማመን መዳን አትችሉም በየጊዜው ቤተክርስቲያን በመሄድም ዳግም ልትወለዱ አትችሉም ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ ምን እንደነገረው እናውቃለን *«እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም...አንተስ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን?» (ዮሐንስ 3:5,10)*

በኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ በሰማያዊው ግምጃ (ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ ተላልፈዋል) ቀይ ግምጃ (ለሐጢያቶቻችን ሁሉ የሆነው የኢየሱስ ሞት) እና ሐምራዊ ግምጃ (ኢየሱስ አዳኝ አምላክና የእግዚአብሄር ልጅ ነው) ማመን አለባቸው።

ኢየሱስ የአለም ሐጢያተኞች ሁሉ አዳኝ እንደሆነ ማመን ይኖርብናል ከዚህ እምነት ውጭ ሰው ፈጽሞ ዳግም ሊወለድ አይችልም ወደ እግዚአብሄር መንግስት ቅዱስ ስፍራም መግባት አይችልም ያለዚህ ማንም ሰው በዚህ አለም ላይ በታማኝነት መኖር እንኳን አይችልም።

ሰው በኢየሱስ በማመን ብቻ ዳግም መወለድ ቢችል በጣም ቀላል አይሆንም ነበርን? ---አዎ-- *«♫ድነሃል ድኛለሁ ሁላችንም*

ድነናል♫» እንዴት ግሩም ነው! ነገር ግን በእውነት «ዳግም ሳይወለዱ» በኢየሱስ የሚያምኑ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን እውነት ልናውቅና በኢየሱስም ላይ እምነት ሊኖረን ይገባል ወደ ተቀደሰው የመገናኛው ድንኳን ውስጥ ለመግባትና በእምነት ግዛት ውስጥ ከእግዚአብሄር ጋር ለመሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የሐጢያት ስርየት ወንጌልና የሰማያዊውን የሐምራዊውንና የቀዩን ግምጃ ትርጉም መረዳት አለብን በእምነት ድንኳን ውስጥ ኢየሱስ ወደ መንግስቱ ሊወስደን ዳግመኛ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ አብረን በደስታ መኖር እንችላለን በትክክለኛው መንገድ በኢየሱስ ማመን ለእኛ አስፈላጊ ነው።

## እውነተኛው ወንጌል በሰማያዊው ግምጃ ቅድስናን ይወልዳል




ሰዎች ስህተቶችን ሳይሰሩ ፍጹም ሆነው መኖር እንደሚችሉ ወደ ማሰብ ያዘነብላሉ ነገር ግን አብዝተው መልካም ነገር ለማድረግ በሞከሩ ቁጥር ወዲያው ጉድለቶቻቸውን አብልጠው ይገነዘባሉ ሰዎች በጣም ጎዶሎዎች ናቸው ስለዚህ ሐጢያት መስራት አይቻላቸውም ኢየሱስ

የስርየት ወንጌል በሆነው ሰማያዊ ሐምራዊና ቀይ ግምጃ ስላዳነን መቀደስና ወደ እግዚአብሄር ቅዱስ ስፍራ መግባት እንችላለን፡፡

እግዚአብሄር በሰማያዊ በሐምራዊና በቀይ ግምጃ ባያድነን ኖሮ በራሳችን ፈጽሞ ወደ ቅድስቱ ስፍራ መግባት ባልቻልን ነበር ለዚህ ምክንያቱ ምንድነው? ወደ ቅድስቱ ስፍራ መግባት የሚችሉት በስጋቸው ፍጹማን ሆነው የሚኖሩ ሰዎች ብቻ ቢሆኑ ኖሮ ብቁ የሚሆን ማንም ባልኖረ ነበር አንድ ሰው እውነተኛውን ወንጌል ሳያውቅ በኢየሱስ ቢያምን የሚጨምረው ነገር በልቡ ላይ ተጨማሪ ሐጢያቶችን መጨመር ብቻ ነው፡፡

ኢየሱስ ያዳነን በጥንቃቄ ባቀደው ደህንነቱ ነው ይህም የሰማያዊው የሐምራዊው የቀዩ ግምጃና ጥሩ በፍታ ደህንነት ነው እርሱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ አንጽቷል በዚህ ታምናላችሁን? ---አዎ--- በልባችሁ ውስጥ የሐጢያት ስርየት ወንጌል አለ ለእርሱም ትመሰክራላችሁን? --አዎ--፡፡

*«ቅድስና ለእግዚአብሄር»* የሚለውን ምልክት በግምባራችሁ ላይ ማድረግ የምትችሉትና *«የንጉስ ካህን» (1ኛ ጴጥሮስ 2፡9)* ጋር የምትቀላቀሉት ወንጌልን ስትመሰክሩ ብቻ ነው በሰዎች ፊት ቆማችሁ የንጉስ ካህን ሆናችሁ የምትሰሩ የእግዚአብሄር ባርያ እንደሆናችሁ ልትነግሩዋቸው የምትችሉት ያን ጊዜ ብቻ ነው፡፡

የሊቀ ካህኑ ጥምጣም የወርቅ ምልክት አለው ምልክቱም በሰማያዊ ፈትል ተያይዞዋል ለምን ሰማያዊ? ምክንያቱም ኢየሱስ በስርየት ወንጌል አድኖናል በጥምቀቱ አማካይነትም ሐጢያቶቻችንን ወስዶ ሐጢያት አልባ አድርጎናል በአዲስ ኪዳን ያለው ጥምቀት ከብሉይ ኪዳን እጆችን መጫን ጋር እኩል ነው፡፡

ምንም ያህል በትጋትና በታማኝነት በኢየሱስ ብናምንም

የሰማያዊውን ሐምራዊውንና ቀዩን ግምጃ የምስጢር ቃሎች ሳናውቅ *«ቅድስና ለእግዚአብሄር»* የሚለው ጽሁፍ የተቀረጸበትን ምልክት ማግኘት አንችልም::

ጻድቃን የሆነንው እንዴት ነው? በማቴዎስ 3:15 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና»* ኢየሱስ ተጠምቆ ከአለም ሐጢያቶች ሁሉ አድኖናል እርሱ በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶዋል እኛ ምዕመናኖችም ጻድቃን ሆነናል::

የኢየሱስ ጥምቀት ባይኖር ኖሮ እንዴት ያለ ሐጢያት ነን ማለት እንችል ነበር? በኢየሱስ ብናምንና የመስቀሉን ሞት በማሰብ ብናለቅስም በዚህ አለም ላይ ያሉ እንባዎች በሙሉ ሐጢያቶቻችንን ሁሉ ማንጻት አይችሉም ምንም ያህል አብዝተን ብናለቅስና ንስሐ ብንገባ ሐጢያቶቻችን በውስጣችን ይቀራሉ::

*«ቅድስና ለእግዚአብሄር::»* እርሱ በጥምቀቱና በደሙ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ስለወሰደ ጌታ የእኛ የሐጢያተኞች ሐጢያቶች ወደ ኢየሱስ እንዲተላለፉ ፈቅዶዋል የደህንነት ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጻፈ ሐጢያቶችና ድክመቶች ቢኖሩብንም በእምነታችን ጻድቃን ሆነናል::

ስለዚህ አሁን በእግዚአብሄር ፊት መቆም እንችላለን አሁን ጻድቃን ሆነን መኖርና ወንጌልን ለአለም መስበክ እንችላለን *«♪ድኛለሁ ድነሃል ሁላችንም ድነናል♪»* በእግዚአብሄር የምህረት ዕቅድ መሰረት ድነናል::

በልባችሁ ውስጥ የስርየት ወንጌል ቃል ከሌለ ምንም ያህል በርትታችሁ ብትሞክሩም ደህንነት የለም ይህ ምላሽ ስለማይሰጥ ፍቅር ከሚዘመረው ታዋቂ የኮርያ መዝሙር ጋር ተመሳሳይ ነው *«♫ኦ እርስዎን ባየኋት ጊዜ ሁሉ በቀረብሁዎት ጊዜ ሁሉ ልቤ ያለ ምክንያት በፍጥነት ይመታል ምላሽ በማይሰጥ ፍቅር*

*ውስጥ ያለሁ መሆን አለብኝ♫»* ልቤ በፍጥነት ይመታል የእርስዋ ግን አይመታም ፍቅሬ ፈጽሞ አልተመለሰም በጣም ብዙ ክርስቲያኖች አሁንም ድረስ ለእግዚአብሄር ያላቸው ፍቅር ምላሽ የማይሰጥ ፍቅር መሆኑ ያሳዝናል፡፡

ሰዎች ደህንነት ለብዙ የተለያዩ ሰዎች በብዙ የተለያዩ መንገዶች ይመጣል ብለው ለማሰብ ያዘነብላሉ «በጥምቀት ወንጌል አማካይነት ብቻ መምጣት ያለበት ለምንድነው?» በማለትም ይጠይቃሉ ነገር ግን ደህንነት በኢየሱስ የጥምቀት ወንጌል በኩል ካልሆነ በቀር ፈጽሞ የተሟላ ደህንነት መሆን ባልቻለም ነበር በእግዚአብሄር ፊት ጻድቃን መሆን የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ መንጻት የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነውና፡፡

## ኢየሱስ የሰጠን የሰማያዊው ግምጃ ደህንነት ምንድን ነው?




በሰማያዊው በሐምራዊውና በቀዩ ግምጃ አማካይነት የመጣው ደህንነት እግዚአብሄር ለሰው ዘር ሁሉ የሰጠው ስጦታ ነው ይህ ስጦታ ወደተቀደሰው የመገናኛ ድንኳን እንድንገባና

በሰላም እንድንኖር አስችሎናል ጻድቃንም አድርጎናል በቤተክርስቲያን ውስጥ እንድንኖርና በቤተክርስቲያን አማካይነትም በቅዱሳት መጻህፍት እንድንሰለጥን አስችሎናል፡፡

በእግዚአብሄር ፊት ለመጸለይ በምንቀርብበት ጊዜ ሁሉ ወንጌል በእርሱ ፍቅር ይባርከናል ደህንነት ለእኛ እንዲህ ክቡር የሆነው ለዚህ ነው ኢየሱስ የእምነትን ቤት «በአለት» ላይ እንድንገነባ ነግሮናል አለቱ የጥምቀቱ ወንጌል ነው ሁላችንም መዳን፣ በደህንነት መኖር፣ ሰማይ መሄድ፣ የዘላለምን ሕይወት ማግኘትና የእግዚአብሄር ልጆች መሆን ይገባናል፡፡

ውድ ወዳጆች ከስርየት ወንጌል የተነሳ በእምነት ወደ ተቀደሰው የመገናኛ ድንኳን መግባት እንችላለን ከሐጢያቶቻችን መንጻትና (የኢየሱስ ጥምቀት) በመስቀል ላይ ከሆነው ፍርድ የተነሳ በኢየሱስ ጥምቀት ወንጌል ላይ ባለን እምነት ድነናል፡፡

ለሐጢያቶቻችን ሁሉ የሆነው የተትረፈረፈ ስርየት የኢየሱስ ጥምቀትና ደም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ያነጻ ወንጌል ነው ይህንን ታምናላችሁን? እውነተኛው ወንጌል ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ፈጽሞ ያነጻ ሰማያዊ ወንጌል ነው፡፡

በስርየት ወንጌል በማመን ዳግም ተወልደናል ኢየሱስ የዕለት ሐጢያቶቻችንንና የወደፊት ሐጢያቶቻችንንም ሁሉ ሳይቀር ያነጻውን የስርየት ወንጌል ሰጥቶናል ጌታ ይመስገን ሐሌሉያ!

የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል (የውሃውና የደሙ ወንጌል) በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመና የተሰበከ እውነተኛ ወንጌል ነው ይህ መጽሐፍ የተጻፈው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል የሆነውን የኢየሱስን ወንጌል ምስጢር ለመግለጥ ነበር፡፡

ብዙ ሰዎች ሙሉ የሆነውን እውነት ሳያውቁ በኢየሱስ ስለሚያምኑ አሁን በክርስቲያን የስነ መለኮት አለም (ፍልስፍናዊ ስነ መለኮት ተብሎ የሚጠራ) ውስጥ ወግ አጥባቂዎች ወይም

ሐይማኖተኛ ብዙሃኖች አድርገው ይመጻደቃሉ በአጭሩ በመናፍቅነትና በውዥንብር ውስጥ ይኖራሉ ስለዚህ ወደኋላ ተመልሰን በእውነተኛው ወንጌል ማመን አለብን ገና በጣም አልረፈደም፡፡

ከውሃና ከመንፈስ ዳግም ስለመወለድ ወንጌል ጥያቄዎች ላሉዋቸው ሰዎች በሁለተኛው መጽሐፍ ላይ ይበልጥ በዝርዝር እገባለሁ፡፡ ✉

# አባሪ 1

## የደህንነት ምስክርነቶች

---

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፓውል ሲ.ጆንግግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::



ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።።

# የደህንነት ምስክርነቶች

## በኃጢያቶቹ ተሰቃይቼ ነበር

**ወንድም ጄይ-ዶንግ ፓርክ፣ ኮሪያ**

*«ኢየሱስም መልሶ:- አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው::» (ማቴዎስ 3:15)*

በሐጢያቶቹ ለሲዖል ታጭቶ የነበረው ሰው ድኖዋል ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን!

*«ከአስማቶችሽና ከህፃንነትሽ ጀምረሽ ከደከምሽበት ከመተቶችሽ ብዛት ጋር ቁሚ»* (ኢሳይያስ *47:12)* ይህንን አደርጌ ነበር::

የተወለድሁት ታማኝ የቡዲስት እምነት ተከታይ ከሆነችው እናቴ በወግ አጥባቂ ቤተሰብ ውስጥ ነበር እያደግሁ ስሄድ በቡዲስት ካምፖቻቸው ውስጥ እየተሳተፍሁና የቡዲስት ጥቅሶችን በአእምሮዬ እያስታወስሁ በጉጉት ወደ መቅደስ እሄድ ነበር አብዛኞቹ ሴቶች የሚከተሉትን የቡድሃን ባዕድ አምልኮ እየነቀፍሁ ለሕይወቴ ትርጉም የሚሰጠኝን አንዳች ሌላ ነገር ለማግኘት ሞከርሁ ነገር ግን በልቤ ውስጥ አሁንም ድረስ የሐጢያት ጭነት ይሰማኝ ነበር ስለዚህ ባህሪዬን ለማረምና በዙሪያዬ ካሉት ሰዎችም ምስጋናን ለማግኘት ሞከርሁ::

በሶኮቺ ከተማ ወደሚገኘው ኮሌጅ ስገባ ክርስቲያን ከሆነ ወ ዳጅ ጋር ተገናኘሁ ያም የሕይወቴ ወሳኝ ቅጽበት ነበር ይህንን ግንኙነት ያቀደው እግዚአብሄር ነበር በኋላም ያ ወዳጅ በታላቅ

ግለት ራሱን በሐይማኖታዊ ስርአቶች ውስጥ ዘፈቀ በሕይወቱ ግን ምንም እርካታ አላገኝም ይህም ለእርሱ እንዳዝንለት አደረገኝ በቤተክርስቲያን ውስጥም በግዴታ የተገኘው መልካም ዝንባሌዬ ሃጢያት እንደነበር ተረዳሁ::

*«ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ፣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው::» (ማርቆስ 7:21-22)*

አእምሮዬ በክፉ ነገሮች የተሞላ ስለነበር እውነተኛ በጎነትን ማፍራት እንደማልችልም ተገንዝቤአለሁ ከሐጢያት ጋር ያለኝ ችግርም አልተፈታም ነበር ወደ ሲዖል እየነጎድሁ ነበር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሐጢያቶቼ ቆዝሜ መጋቢዬ እንዲረዳኝ ለመጠየቅ ወሰንሁ ከእርሱም ኢየሱስ *«የአለምን ሐጢያት ሁሉ የወሰደ» (ዮሐንስ 1:29)* አምላክ መሆኑን ሐጢያቶቼን እንደወሰደና የእነርሱንም ዋጋ እንደከፈለ ተማርሁ ይህም በአያሌው አሳረፈኝ ምስኪኑ አእምሮዬም ከሰማይ ወደመጣው እረፍት የሚገባ መሰለ::

በኋላም ከሬቨረ. ፖውል ሲ. ጆንግ ጋር ተገናኘቼ ኢየሱስ እንዴት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንዳነጻና የእስራኤል ሕዝብም በብሉይ ኪዳን እንዴት መስዋዕቶችን ያቀርቡ እንደነበር ተማርሁ በተጨማሪም በመንፈስ ቅዱስ የተጸነሰው ኢየሱስ (ማቴዎስ 1:20) ለምን እንደተረገመና በእንጨት ላይ እንደተሰቀለ (ገላትያ 3:13) ተገነዘብሁ *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና» (ማቴዎስ 3:15)* አጥማቂው ዮሐንስ የመጨረሻው ሊቀ ካህን በመሆን እንከን የሌለበት የእግዚአብሄር በግ የሆነውን ኢየሱስን አጠመቀው ሐጢያቶችንም በሙሉ ወደ እርሱ አስተላለፈ ከዚያም ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሐጢያቶቻችንን ሁሉ ደመወዝ ከፈለ እኔን ያነቃቃኝና ጻድቅ

ያደረገኝ እውነተኛ ወንጌል ይህ ነበር በአንድ ወቅት ሐጢያተኛ የነበርሁት እኔ ጻድቅ ሆኛለሁ፡፡

*«ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌው ነገር አልፎኣል እነሆ ሁሉም ነገር አዲስ ሆኖአል» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17)* ይህ ለእኔም ተመሳሳይ ነበር በሕይወቴ ተጸጸትሁ (የሐዋርያት ስራ 11፡18) በክርስቶስም ተጠመቅሁ ኩነኔም የለብኝም (ሮሜ፡ 8፡1) በእርሱ ጸጋ ተጠምቄአለሁ እግዚአብሄር ስላዳነኝ አመሰግነዋለሁ በሐጢያቶቻቸው የሚቆዝሙና ኢየሱስን የሚሹ ሰዎች ሁሉ በእርሱ የቤዛነትን ወንጌል ያግኙ! ሃሌሉያ! ✉

# ከባዕድ አምልኮ ወደ እውነተኛ የእግዚአብሐር እምነት

**እህት ሱንግ- ኒኦ ኪም፣ ኮሪያ**

ያገባሁት በ19 አመቴ ነበር የባለቤቴ ቤተሰቦችም በጣም ድሆች ነበሩ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፈጽሞ ደህና ኑሮ አልኖርኩም ባለቤቴም ወዶኝ አያውቅም የሚወዱዋቸው ባሎች ባላቸውና ሐብታሞች በሆኑ ሴቶች ሁልጊዜም እቀና ነበር የባለቤቴ ቤተሰቦች በተራራ ላይ በሚገኙ አምላኮች ያምኑ ነበር የባለቤቴም አባት ጠንቋይ ነበር ባለቤቴ በሰራዊቱ ውስጥ የተመዘገበው በተጋባን በ3ኛው ቀን ነበር ዋርሳዬም በ22 አመቱ የአእምሮ ሕመምተኛ ሆነ አማቼም በ50 አመቷ አካባቢ እውር ሆነች እነዚያ ቀኖች ለእኔ በእርግጥም አስከፊ ነበሩ፡፡

ትምህርት ስላልነበረኝና መልኬም ውብ ስላልነበረ በሳል አእምሮ ወይም እውቀት ስላልነበረኝ መላውን ሕይወቴን በዚህ መልኩ መኖር ዕጣ ፈንታዬ ነው ብዬ አሰብሁ አማቼ ቀዶ ጥገና ማድረግ ብትፈልግም በጭራሽ ሆስፒታል ወስጃትም ሆነ መድሃኒት ገዝቼላት አላውቅም ታማ በቅርቡ እንደምትሞት ተስፋ አድርግ ነበር፡፡

አሁን 54 አመቴ ነው አማቼም ከሁለት አመት በፊት ሞታለች በሬሳ ሳጥን ውስጥ ለሟች ሰው ትራስ ማንተራስ መጥፎ እድል ነው የሚባል አባባል አለ እኔ ግን በወቅቱ ስለማላውቅ የቀበርኋት ከትራስዋ ጋር ነበር፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሁልጊዜም በሕልሞቼ ትመጣብኛለች ትራስዋን በሬሳ ሳጥኑ ውስጥ በማኖሬም አዝናለሁ በሕይወት ሳለችም ክፉ ሆኜባት ስለነበርም አዝናለሁ ሌሎች ሰዎች ለአማቾቻቸውም ጥሩዎች ይመስላሉ እኔ ግን እርስዋን

ከመጥላት ራሴን ማቆም አልቻልሁም በቅዠቶችና በተወቀሰ ሕሊና ተሰቃየሁ::

አንድ ወንድና አራት ሴቶች ልጆች አሉኝ በአንዱ ወንድ ልጄ ላይ የሆነ መጥፎ ነገር ይደርስበታል ብዬ እፈራለሁ ለጎረቤቶቼ ሕልሞቼን ስነግራቸው መጥፎው መንፈስ በጥንቆላ መውጣት እንዳለበት ነገሩኝ ሻማኖችን ጎበኘሁ ያለ ማቋረጥ ለመንበርከክ ወደ መቅደሶች ሄድሁ እረፍትን ለመንሁ ነገር ግን ዋጋ አልነበረውም ከሕሴናዬ ለመሸሽ ራሴን ማጥፋት እንዳለብኝም ተሰማኝ::

ኢየሱስን ባላገኝና ባልድን ኖሮ ዛሬ በሕይወት ባልኖርኩም ነበር አንድ ቀን ከቤነ ወጥቼ ለማረፍና አንዳንድ የናህል መድሃኒቶች ለመውሰድ ወደ ሴት ልጆቼ ቤት ሄድሁ እግዚአብሄር የሕይወትን መንገድ ያሳያኝ ያኔ ነበር ከሴት ልጆቼ አንዷ ዳግም የተወለደች ክርስቲያን ስለነበረች የመጋቢዋን ሚስት ለእኔ ብላ ጋበዘቻት እርስዋም ከሌሎች ሴት ጋር አብራ መጥታ አነጋገረችኝ::

እኔ ስለ እግዚአብሄር የማውቀው ምንም ነገር አልነበረም ነገር ግን ኢየሱስ ሐጢያቶቼን እንደወሰደ ሲነግሩኝ በቃሉ ለማመን ወሰንሁ እኔ ሴት ልጆቼን ቤተክርስቲያን እንዳይሄዱ አዘውትሬ እነግራቸው ነበር ምክንያቱም በአንድ ቤት ሁለት አምላኮችን ማስተናገድ መጥፎ እድል ያመጣል ብዬ እስብ ነበርና ነገር ግን ነገሮች ከዚህ በላይ ሊከፉ አይችሉም ብዬ ስላሰብሁ ሐጢያተና ሆኜ መሞት አልፈለግሁም::

የመጋቢው ባለቤት ሰዎች ሁሉ ሐጢያተኞች ሆነው እንደተወለዱ እግዚአብሄር ግን በኢየሱስ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደና በኢየሱስ ብናምን ከእንግዲህ ወዲህ ሐጢያተኞች እንደማንሆን ነገረችኝ ስለዚህ በየጊዜው ቤተክርስቲያን መሄድና ቃሉን መስማት ሞከርሁ ነገር ግን የተባለውን አብዛኛውን ነገር መረዳት አልቻልኩም ጊዜ

እየነጎደ ሲሄድ ግን የእርሱ ቃሎች በሙሉ ስሜት ሊሰጡኝ ጀመሩ ሐጢያተኛ ሆኜ እንደተወለድሁ ተገነዘብሁ ከአዳም ሐጢያት የተነሳ ሐጢያተኛ ከመሆን ማምለጥ አልቻልኩም በአእምሮዬ ያሉት ክፉ አሳቦችም እንደዚሁ በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያቶች እንደሆነ ተረዳሁ::

በብሉይ ኪዳን ይቀርቡ የነበሩት መስዋዕቶች እርሱ ሊመጡ ያሉትን በጎ ነገሮች ለእኛ የሚያሳይበት መንገዱ ነበር ኢየሱስም በብሉይ ኪዳን ለመስዋዕት በቀረበው እንስሳ ራስ ላይ እንደሚደረገው እጆች መጫን በዮሐንስ ተጠመቀ በዮርዳኖስም ሐጢያቶቼ በሙሉ ወደ እርሱ ተላለፉ እርሱ ሐጢያቶቼን በሙሉ ወሰደ ለእነርሱም ዋጋ ለመክፈል በመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰ::

በመጨረሻም ሐጢያት እንደሌለብኝና ማንም ሊኮንነኝ እንደማይችል አመንሁ ከዚያን ጊዜም ጀምሮ በሰላም መተኛት ቻልሁ::

*«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» (ሮሜ 8:1)* በልቤ ውስጥ ባለው ሐጢያት ብዙ ተሰቃይቼ ነበር አሁን ሐጢያት ተወግዶዋል ከእንግዲህ የሚያቃዠኝ ቅዠቶች አይኖሩም::

እንዴት በደንብ እንደማነብ ስለማላውቅ ስሜቶቼን በሚገባ መጻፍ አልቻልሁም ነገር ግን ኢየሱስ ሐጢያቶቼን ሁሉ እንዴት ከልቤ ውስጥ እንደወሰደ ለማንም ሰው መናገር እችላለሁ ኢየሱስ እኔን እንዳዳነኝ ባለቤቴንና ሌሎች የቤተሰብ አባሎችን እንዲያድን እጸልያለሁ ይህ ምስክርነትም ሌሎች በኢየሱስ ቤዛነትን ያገኙ ዘንድ እንደሚረዳቸው ተስፋ አደርጋለሁ::

እግዚአብሄር ስላዳነኝ አመሰግነዋለሁ ወንጌልን ለብዙ ሰዎች ማሰራጨት በመቻሌም በጣም ደስተኛ ነኝ አሁን በሐብታሞች ወይም በተማሩ ሰዎች አልቀናም:: ✉

# በሞስኮ በተሰበከው እውነተኛ ወንጌል

እህት ቢሎቫ ሊሳ
ሞስኮ፣ ራሺያ

በኮርያ ላሉ አገልጋዮች ሁሉ በኢየሱስም ስም ሰላም ልላቸውና ሕይወቴን ፈጽሞ የለወጠውን ክስተት ላካፍላችሁ እወዳለሁ::

ከሁለት አመት በፊት በሞስኮ በተደረገ አንድ ሴሚናር የእግዚአብሄርን አስገራሚ ቃሎች ሰማሁ በቀጣዩ አመት በኮርያ በአንድ የስልጠና ሴሚናር ላይ ስሳተፍ ስለ እግዚአብሄር ቃል በተለይም ዳግመኛ ከውሃና ከመንፈስ ስለመወለድ ብዙ ትምህርቶችን ሰማሁ በእርግጥኝነት ከሐጢያቶቼ ሁሉ ነጻ መውጣቴን በግልጽ ማየት ምንኛ የሚያስደስት ነው!

በኢየሱስ ማመን ከጀምርሁ 6 አመታት ሆነዋል «በትክክል ዳግም ከመወለዴ» ቀደም ብሎ ትልቅ ሐጢያተኛ እንደሆንሁና ሁልጊዜም ንስሐ መግባት እንደሚኖርብኝ ተምሬ ነበር እኔም በተደጋጋሚ እየጸለይሁ ንስሐ እገባ ነበር የውሃ ጥምቀትን ወስጃለሁ ነገር ግን ገናም ዳግም አልተወለድሁም ነበር ሐጢያተኛ እንደሆንሁና በልቤም ውስጥ ብዙ ሐጢያት እንዳለብኝ አውቄአለሁ ያለ ማቋረጥም እግዚአብሄር ይቅር እንዲለኝ ተማጽኛለሁ ሁልጊዜም በሐጢያቶቼ እሰቃይ ነበር ነገር ግን እግዚአብሄር በዚህ ሐዘን ውስጥ እንደማይተወኝና በመጨረሻ በዚህም ሆነ በዚያ እንደሚያድነኝ ከልቤ አምን ነበር::

ከዚያም እግዚአብሄር ዳግም ከተወለደ አገልጋይ ጋር አገናኘ

ኝ በእርሱ በኩልም በዚህ አለም ላይ እጅግ ክቡር የሆነውን ብቸኛና እውነተኛ የደህንነት ወንጌል መስማት ቻልሁ ኢየሱስ በጥምቀቱና በመስቀሉ ሐጢያቶቼን በሙሉ እንዳስወገደ እኔም አሁን ሐጢያት እንደሌለብኝ ተማርሁ፡፡

አሁን ዳግመኛ ሐጢያተኛ አይደለሁም ልቤም በደስታ ተሞልቷል አሁን የንስሐ ጸሎቶችን በማቅረብ ፋንታ በየቀኑ ታላቁን ምስጋናዬን ለእግዚአብሄር አቀርባለሁ ሕይወቴም በጣም ሰላማዊና በጣም ደስተኛ ሆንዋል አሁን ከዚህኛው የሚበልጥ ሌላ እውነተኛ ወንጌልና ሌላ እምነት እንደሌለ አውቃለሁ እምነቴ እንዲጠነክር እጸልያለሁ በየቀኑም ለእግዚአብሄር ምስጋና አቀርባለሁ ከዚህ ይበልጥ ክቡር የሆነ እምነት እንደሌለም አምናለሁ፡፡

ሕይወቴ ሲያበቃ መንግስተ ሰማይ እንደምገባ ስለማውቅ ሰላም አለኝ አሁን ለእግዚአብሄር እሰራለሁ በዙሪያዬ ላሉት ለሌሎችም ወንጌልን እሰብካለሁ የእግዚአብሄርን ፍቅር ከአለም ሕዝብ ሁሉ ጋር በመጋራት በማያቋርጥ ደስታ ውስጥ እኖራለሁ፡፡✉

# አሁን በክርስቶስ ጠንካራ እምነት አለኝ

**ፒተር ክሪስ፣ የክርስቶስ ልጆች፣ ናይጄሪያ**

ትክክለኛውን የእግዚአብሄር ጽድቅ መረዳት ከሚሰጠው ከዚህ መጽሐፍ ያስተዋልሁት ነገር ቢኖር የኢየሱስን ጥምቀትና መስቀል ነው ሁለቱም የደህንነታችንን የተሟላ መጠይቅ ለማምጣት መጣመር አለባቸው የሰውን ዘር ሁሉ ከሚያመላክተው ከአጥማቂው ዮሐንስ የተሰጠው የኢየሱስ ጥምቀት (ውሃ) በጥምቀት ውስጥ በማለፍ (እጆችን በመጫን ስርአት) በራሱ ላይ የሰውን ዘር ሁሉ ሐጢያቶች ወሰደ ሐጢያቶችን በራሱ ላይ በመውሰዱም ለእነርሱ ፍርድን ለመቀበል በመስቀል ላይ ተሸከማቸው ወደ መስቀል የነዳውን የእርሱን ጥምቀት ካልተቀበልሁ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያገኘው ድል ምንም ያህል ፍጹም ቢሆንም ደህንነቴ የተሟላ ሊሆን አይችልም፡፡

ክርስቶስን የተቀበልሁ ሰው ብሆንም አሁንም ድረስ ሐጢያትን እሰራለሁ ነገር ግን ሐጢያተኛ አይደለሁም ምክንያቱም ሐጢያትን የማያውቀው ክርስቶስ እኛ የእግዚአብሄር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ሐጢያተኛ ሆንዋልና አሁን ከመጽሐፍህ በተረዳሁት መሰረት ያለፈውን አሁን ያለውንና የወደፊቱን ሐጢያቴን ዋጋ በከፈለው የእርሱ ጥምቀትና መስቀል (ውሃና ደም) አማካይነት በክርስቶስ የደህንነት ስራ ብርቱ እምነት አለኝ እግዚአብሄር ሐጢያቶቼን በሙሉ አንጽቶ በክርስቶስ አማካይነት ኮንኖዋቸዋል፡፡

ዳግም የተወለድሁ ክርስቲያን በመሆኔ ወደ ሐጢያት የሚመራኝን ማንኛውንም ነገር ለማስወገድ የምችለውን ሁሉ

አድርጋለሁ ክርስቶስ ስለ እኛ የሐጢያቶችን ሁሉ ዋጋ እንደከፈለ እኛ ግን በሐጢያት እንደማንደሰት መገንዘብ ይገባናል ምክንያቱም በሐጢያት የምንደሰት ከሆንን በእርሱ የሚያድን ጸጋ ላይ እያላገጥን ነውና፡፡✉

# ኢየሱስ ሐጢያቶቼን በራሱ ላይ ወስዷል

**ፓስተር ቲሞቲ ካቶላ፣ ኬንያ**

«በውኑ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ዳግመኛ ተወልዳችኋልን?» የሚለውን መጽሐፋቸውን ለሚያነቡ አንባቢዎች እውነተኛውን ወንጌል በበለጠ ግልጽነት በማቅረባቸው እግዚአብሄር ሪቨረ. ፖውል ሲ. ጆንግን ይባርካቸው ከጥቂት ሳምንታት በፊት ይህንን መጽሐፍ ካነበብሁ በኋላ በአዳችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የመጣው የቤዛነት መልዕክት በሕይወቴ ውስጥ ይበልጥ ጥርት ያለ ሆነ በዮርዳኖስ ወንዝ በአጥማቂው ዮሐንስ ሐጢያቶችን በሙሉ ያስተላለፈው የጥምቀቱ እውነት አንድ ጊዜ ወንጌልን ስናምን የሐጢያት ሸክም ሁሉ እንደሚወገድ ለእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ማረጋገጫን ሰጥቶዋል፡፡

አጥማቂው ዮሐንስ ለእስራኤሎች ሐጢያቶች መስዋዕትን ያቀርብ ለነበረው የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህን የአሮን ጥላ ነበር አሮን እስራኤሎች ለሰሩዋቸው ሐጢያቶች ይቅርታን በመለመን ለእግዚአብሄር መስዋዕቶችን ያቀርብ ነበር እጆቹን በሚለቀቀው ፍየል ራስ ላይ በመጫንም የእስራኤሎችን ሐጢያቶች ወደ እርሱ አስተላልፎዋል ልክ እንደዚሁ ኢየሱስም በጥምቀቱ አጥማቂው ዮሐንስ እጆቹን በራሱ ላይ በጫነ ጊዜ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶዋል ሊቀ ካህናት በየአመቱ የሚለቀቁ ፍየሎችን ማቅረብ ነበረባቸው *«ነገር ግን በዚያ መሥዋዕት በየዓመቱ የኃጢኣት መታሰቢያ አለ፤ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና» (ዕብራውያን 10:3-4)* ኢየሱስ ከክርስቶስ ግን ይህንን ለሰዎች ሁሉ ለአንዴና ለመጨረሻ አደረገው አንድ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ

ክርስቶስ ስናምን የሐጢያቶቻችንን ስርየት ለአንዴና ለመጨረሻ እንቀበላለን፡፡

ፖውል ሲ. ጆንግ ሐጢያቶቻችን እንዴት በኢየሱስ ላይ እንደተጫኑ በግልጽ አሳይቶናል ሐጢያትም ከእንግዲህ ወዲህ በሕይወታችን ውስጥ ችግር ሊሆን እንደማይገባም አሳይቶናል ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቼን በራሱ ላይ ከወሰደና በእኔ ምትክም ከሞተ በኋላ አሁን ዳግመኛ ሐጢያተኛ አይደለሁም፡፡

ዛሬ የሰው ሁሉ እጅግ ትልቁ ችግር ከሐጢያተኛ ተፈጥሮው መላቀቅ ነው ይህ መጽሐፍ እውነተኛውን የኢየሱስ ወንጌል ስናምን እንዴት ሐጢያትና ኩነኔ የሌለበትን ሕይወት መኖር እንደምንችል በግልጽ ያሳየናል እግዚአብሄር ለባርያው ለፖውል ሲ. ጆንግ ስለሰጠው መገለጡ የተመሰገነ ይሁን፡፡ ✉

# ዋው! ያስገርማል!

ሚሲዮናዊት ብሩሲላ ጆንሰን፣ ዩ.ኤስ.ኤ.

ክቡርና ድንቅ በሆነው በጌታችንና በአዳችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላምታን አቀርብላችኋለሁ ይህ ከጥቂት ቀናቶች በፊት «አጥማቂው ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ በኢየሱስ ላይ እጆቹን ለምን ጫነ?» በሚል በኢሜል ለጠየቃችሁን ጥያቄ የሚሆን መልስ ነው።

ይህ በብሉይ ኪዳን የስርየት ሕግ ነበር ይህ እግዚአብሄር ሙሴን ወንድሙን አሮንን የመጀመሪያ ሊቀ ካህን አድርጎ እንዲሾመው በመስዋዕቱ እንስሳ (ፍየል) ላይም እጆቹን እንዲጭንና የእስራኤል ልጆችን አስፈሪ ሐጢያቶችና መተላለፎቻቸውን እንዲናዘዝ ያዘዘው ትዕዛዝ ነበር (ኢሳይያስ 53:3-5) ከዚያ በኋላ ፍየሉ የእስራኤሎችን በደሎችና መተላለፎች በራሱ ላይ ተሸክሞ ፍየሉን በምድረ በዳ በሚለቀው የተመረጠ ሰው ይሰደዳል። (ዘሌዋውያን 16:21-22)

አጥማቂው ዮሐንስም በተመሳሳይ ሁኔታ ኢየሱስ በይፋ አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት እጆቹን በኢየሱስ ራስ ላይ ጫነ ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶችና መተላለፎች በሙሉ ይወስድ ዘንድ በዚህ መንገድ በዮሐንስ ለመጠመቅ ፈቃደኛ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደረገ።

ሐጢያቶቻችንንና መተላለፎቻችንንም ሁሉ በራሱና በጫንቃው ላይ ተሸከመ (ሊቀ ካህንና ፍየል ኢሳይያስ 53:3-5፤ማቴዎስ 3:13-17)

ጥምቀት (ውሃ ውስጥ መጥለም) ይህ ነው ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በራሱ ላይ ወሰደ ወይም ተሸከመ እነዚያም ሐጢያቶች አሁን በጥምቀት ስርአት ጠርተዋል

ነጽተዋል ታጥበዋል:: (ዮሐንስ 1:29)

*መፅሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል- «ቢወድቅም ለድንጋጼ አይጣልም» (መዝሙረ ዳዊት 37:23-24) «ሁሉ ኃጢያትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል» (ሮሜ 3:23) «ቻርነት የሚያደርግ የለም አንድስ እንኳ የለም» (ሮሜ 3:10-12)::*

ኦ! እግዚአብሄር ይመስገን ሐሌሉያ! ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን *«ጸጋው በእምነት አድኖዋችኋልና» (ኤፌሶን 2:8፤1ኛ ዮሐንስ 1:9)* የእግዚአብሄር በግ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ሞቱ አማካይነት የዚህን አለም ሐጢያቶች ደመወዝ ወስዶ በራሱ ላይ ተሸክሞዋል:: (ዮሐንስ 1:29)

በእምነት አማካይነት በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ስለዳንሁ ሐጢያት የለብኝም በእግዚአብሄር በግ ጥምቀትና በደሙ አማካይነት በኢየሱስ ክርስቶስ ታጥቤ ነጽቻለሁ::

አሁን «ወደ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል» መመለስ ይገባናል ወደ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል መመለስ ማለት በተዋረደ መንፈስ በተሰበረ ልብና በአንደበት ኑዛዜ መቅረብ ማለት ነው ጌታ ኢየሱስም በእውነተኛው የውሃና የመንፈስ ወንጌል ሐጢያቶቻችንን ይቅር ይለናል ከሕመሞቻችን ከደዌያችንና ከአመጻችን ይፈውሰናል (1ኛ ዮሐንስ 1:9፤2ኛ ዜና 7:14፤3ኛ ዮሐንስ 2) ወደ ውሃውና ወደ መንፈሱ ወንጌል መመለስ ማለት «እውነተኛ የሐጢያት ኑዛዜ» ማድረግና በእግዚአብሄር መንፈስ በአእምሮ መታደስና በመንፈስ ቅዱስ «መጠመቅ» ማለትም ደግሞ ነው:: (የሐዋርያት ሥራ 1:5)

ቃሉን በጥልቅት እንድረዳና አብርሆት እንዳገኝ ያደረጉኝን እነዚህ መጽሐፎች በማንበቤ ሐሴት አደርጋለሁ እደሰትማለሁ እነዚህ ድንቅና ብርቱ የሆኑ መሳሪያዎች የማላውቀውንና ያልተረዳሁትን እውቀትና ቃል ሰጥተውኛል ዋው! አስገራሚ ነው! ✉

# ተስፋ የቆረጥኩ ኃጢያተኛ ነበርኩ

**ወ/ሪት አልደርማን፣ ዩ.ኤስ.ኤ.**

በመጀመሪያ እግዚአብሄር ልጁን ያጠምቅ ዘንድ ባርያውን አጥማቂውን ዮሐንስን የላከው ዮሐንስ የደህንነትን መንገድ መጥረግ ይችል ዘንድ ነው አጥማቂው ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ላይ እጆቹን በኢየሱስ ላይ ጫነ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ የወሰደው የአንድ ሰው ስራ ነበር ኢየሱስ በመጠመቅ የዚህን አለም ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ ኢየሱስ የሐጢያትን ደመወዝ ለመክፈል ሕይወቱን በመስቀል ላይ ሰጠ በመስቀል ላይ ሞቱም የሐጢያትን ደመወዝ ከፍሎዋል።

ሐጢያቶቻችንን ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል እርሱ የሰውን ዘር ለማዳን በእኛ ፋንታ ተኮነነ ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን መውሰድና ለእነርሱም መሞት ነበረበት ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትና መስቀል የማያምኑ ከሆኑ ያሉት በሐጢያት ውስጥ ነው ስለዚህ የእግዚአብሄርን ቃል አለመቀበልና ከእውነት ወደ ተሳሳቱ ጽንሰ ሐሳቦች ማፈንገጥ ሐጢያት ነው ኢየሱስ እኛን ከሐጢያቶቻችን ነጻ ለማውጣት ስለመጠመቁ በመስቀል ላይ ስለ መሞቱና ስለ መነሳቱ የተጻፈውን ቃል አለማመን ሐጢያት ነው።

ንስሐ በመግባት ራሳችንንም ፈጽመን ሐጢያተኞች እንደሆንን በመቀበልና የእግዚአብሄር ልጅ የሆነውን ኢየሱስን ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ያዳነን አዳኛችን መሆኑን በማመን ፈጽሞ ከሐጢያት መላቀቅ እንችላለን ስለዚህ ሁላችንንም ከሐጢያቶቻችን በሚያነጻን የኢየሱስ ጥምቀትና ደም ማመን አለብን።

እኔ በኢየሱስ ጥምቀት ከማመኔ በፊት ተስፋ ቢስ የሆንሁ ሐጢያተኛ ነበርሁ! ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ ባይጠመቅ ኖሮ ሐጢያተኛ ሆኜ በቀረሁና በጠፋሁ ነበር። 🖂

# አሁን በእግዚአብሔር ፊት መቆም እችላለሁ

**ፓስተር ስቲቨን አይከ፣ ኢንግላንድ**

በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህኑ ሐጢያትን ለማስተላለፍ እጆቹን በመስዋዕት እንስሶች ራስ ላይ ይጭን ነበር (ዘሌዋውያን 16:3-4) እጆችን መጫን የስርየት ቀን አስፈላጊ ክፍል ነበር እንደዚያ ባደረግ ኖሮ መስዋዕትን ማቅረብ ሊከናወን አይችልም ነበር ምክንያቱም የሐጢያት ስርየት ያለ እጆች መጫን ሊከናወን ስለማይችል የእስራኤሎችን አመታዊ ሐጢያቶች በሐጢያት መስዋዕቱ ላይ ማስተላለፍም አይቻልም ነበር፡፡

በዘሌዋውያን 16:21 ላይ እንዲህ ይላል *«አሮንም ሁለቱን እጆቹን በህያው ፍየል ራስ ላይ ይጭናል በላዩም የእስራኤልን ልጆች በደል ሁሉ መተላለፋቸውንም ሁሉ ኃጢአታቸውንም ሁሉ ይናዘዛል፤ በፍየሉም ራስ ላይ ያሽክመዋል በተዘጋጀውም ሰው እጅ ወደ ምድረ በዳ ይሰድደዋል፡፡»*

እርሱ ከሕዝቡ ለሐጢያት መስዋዕቶች ሁለት ፍየሎችንና አንድ አውራ በግም ለሚቃጠል መስዋዕት ወሰደ ከዚያም በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ በእግዚአብሄር ፊት ሁለት ፍየሎችን በማቅረብ አንዱ «ለጌታ» ሌላው ደግሞ «የሚለቀቅ ፍየል» እንዲሆን ለመምረጥ ዕጣዎችን ይጥላል ለእግዚአብሄር የሆነው የሐጢያት መስዋዕት ሆኖ ይቀርባል የሚለቀቀው ፍየልም የእስራኤልን ሕዝብ አመታዊ ሐጢያቶች ለማስተሰረይ በሕይወት እያለ በጌታ ፊት ይቀርብና ወደ ምድረ በዳ ይሰደዳል፡፡ (ዘሌዋውያን 16:7-10)፡፡

የእስራኤል ሐጢያት በእጆች መጫን ወደሚለቀቀው ፍየል መተላለፍ ነበረበት ከዚያም የእስራኤልን ሐጢያቶች

በሙሉ የወሰደው የሚለቀቀው ፍየል በሕዝቡና በእግዚአብሄር መካከል ሰላም ይሆን ዘንድ ወደ ምድረ በዳ ይሰደዳል በዚህም የእስራኤል አመታዊ ሐጢያቶች ነጽተዋል በአዲስ ኪዳንም በተመሳሳይ መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ የሊቀ ካህኑ አሮን የመጨረሻ ዘር በሆነው በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠምቆ (በብሉይ ኪዳን እጆች መጫን) የእግዚአብሄርን ደህንነት ለመፈጸም የመስዋዕት በግ ሆኖ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል:: (ዘሌዋውያን 20:22፤ማቴዎስ 3:15፤ዮሐንስ 1:29,36)::

በብሉይ ኪዳን ዕጣዎች ከመጣላቸው በፊት አሮን ለራሱና ለቤተሰቡ የሐጢያት መስዋዕት የሚሆን ወይፈን ያርዳል (ዘሌዋውያን 16:11) ከዚያም በእግዚአብሄር ፊት በእሳት የተሞላ ማዕጠንት ወስዶ ያማረ ጣፋጭ ዕጣን በእጆቹ ይዞ መጋረጃውን አልፎ ይገባል የዕጣኑ ጢስ በስርየቱ መክደኛ ላይ ይሰፍፍ ዘንድ በእግዚአብሄር ፊት ዕጣኑን በእሳት ላይ ያኖረዋል ከወይፈኑም የተወሰነ ደም ይወስድና በስርየቱ መክደኛ ላይና በፊቱ ሰባት ጊዜ በጣቱ ይረጫል:: (ዘሌዋውያን 16:12-19)

በስርየት ቀን አሮን እጆቹን በመስዋዕቱ ራስ ላይ መጫኑን መተው አይኖርበትም አሮን እጆቹን በፍየሉ ላይ ጭኖ የእስራኤሎችን ሐጢያቶች በራሱ ላይ ያስተላልፋል ከዚያም የተመረጠ ሰው ፍየሉን ወደ ምድረ በዳ ይስደውና እዚያው ይለቀዋል የሚለቀቀው ፍየልም የእስራኤልን ሐጢያቶች ይዞ በምድረ በዳ ይቀበዘበዝና በመጨረሻም ይሞታል በብሉይ ኪዳን የ ስርየቱ መስዋዕት ይህ ነበር::

በጥምቀቱ ባፈሰሰው ደሙና ስለ እኛ በመስቀል ላይ በመሞት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በራሱ ላይ ከወሰደው የሚለቀቅ ፍየል ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር በአዲስ ኪዳንም ተመሳሳይ ነው::

ስለዚህ አሁን ከሐጢያቶች መዳን ሰማያዊ ሊቀ ካህን

ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትና ስቅለት ውጭ ሊገኝ አይችልም ይህ ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ዳግም የመወለድ ደህንነት ፍጻሜ ነው::

*«የአለምን ሐጢያት የወሰደው» (ዮሐንስ 1:29)* ኢየሱስ ነበር እርሱ የእኔንም ሐጢያቶች ወስዶ ለእነርሱም ደግሞ ዋጋ ከፍሎዋል በብሉይ ኪዳን የእስራኤል ሕዝብ እንዳቀረቡዋቸው መስዋዕቶች ኢየሱስም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ አስወግዶዋል ከመንፈስ ቅዱስ የተጸነሰው ኢየሱስ (ማቴዎስ 1:20) የተረገመውና በእንጨት ላይ የተሰቀለው ለዚህ ነበር (ገላትያ 3:13) *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና» (ማቴዎስ 3:15)*

አጥማቂው ዮሐንስ የመጨረሻው ሊቀ ካህን ሆኖ እንከን የሌለበትን የእግዚአብሄር በግ ኢየሱስ ክርስቶስን በማጥመቅ ሐጢያቶችን ሁሉ ወደ እርሱ አስተላለፈ ከዚያም ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሐጢያቶችን ዋጋ ከፈለ ያነቃኝና ጻድቅ ያደረገኝ እውነተኛ ወንጌል ይህ ነው እኔ በአንድ ወቅት ሐጢያተኛ የነበርሁ ሰው ጻድቅ ሆኛለሁ::

*«አሮጌው ነገር አልፎአል እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል» (2ኛ ቆሮንቶስ 5:17)* በሕይወቴ ተጸጸትሁ (የሐዋርያት ስራ 11:18) በክርስቶስም ተጠመቅሁ ኩነኔም የለብኝም (ሮሜ፡ 8:1) በእርሱ ጸጋ ተጠምቄአለሁ እግዚአብሄር ስላዳነኝ አመሰግነዋለሁ ሐጢያት ብሰራም እንኳን ኢየሱስ ቀድሞውኑም ዋጋዬን ስለከፈለልኝ በጸጋውና በምህረቱ አማካይነት ይቅርታን እንደማገኝ አውቃለሁና ወደ ኢየሱስ ጥምቀት እመለሳለሁ እግዚአብሄር ይመስገን!!!

በየቀኑ ሕይወቴ ሐጢያቶችን ከመስራት ማምለጥ ባልችልም አሁን ሐጢያት የለብኝም እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«የኃጢያት ፍርዱ ሞት ነው» (ሮሜ 6:23)* ሐጢያቶቼን

በሙሉ ይገፔ በእግዚአብሄር ፊት ፈጽሞ መቅረብ እንደማልችል ተረድቻለሁ ልቤ ቢከብድም እግዚአብሄር ይወደኛል እርሱ ያድነን ዘንድ ልጁን ልኮዋል *«እነሆ! የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!» (ዮሐንስ 1:29)* የአለም ሐጢያቶች ማለት የእኔንም ጨምሮ ሁሉም ሐጢያቶች ማለት እንደሆነ ተረድቻለሁ እርሱ የወሰደው የትናንትናና የዛሬ ሐጢያቶችን ብቻ ሳይሆን የነገን ሐጢያቶችንም ጭምር ነው ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወሰዶዋል፡፡

*«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት፡፡» (ማቴዎስ 3:15)*

በመጨረሻም ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቼ በሙሉ ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ አምኛለሁ በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜም የሐጢያቶቼ ዋጋ በሙሉ ተከፍሎዋል *«የስጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና ደሙም ከህይወቱ የተነሳ ያስተሰርያልና በመሰዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት» (ዘሌዋውያን 17:11)* ኢየሱስ ዝም ብሎ አልሞተም ነገር ግን *«ተፈጸመ!» (ዮሐንስ 19:30)* አለ ከዚያም ጎኑ ተወጋ ውሃም ፈለቀ (ዮሐንስ 19:34) እግዚአብሄርንና ሰውን የለያየውም ግድግዳ ፈረሰ አሁን በእውነት ስለዳንሁ በእግዚአብሄር ፊት መቆም እችላለሁ፡፡ ✉

# አሁን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሙሉ በሙሉ አምናለሁ

**ወንድም ጋድሰን፣ ሕንድ**

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ኢየሱስ ጥምቀት ግልጽ የሆነ ማብራሪያን ማግኘት እንችላለን ዮሐንስ 3:5 እንዲህ ይላል *«ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም»* እዚህ ላይ የተጠቀሰው ውሃ የኢየሱስ ጥምቀት ነው የላይኛው ቁጥር ወደ እግዚአብሄር መንግስት የምንገባበትን ብቸኛውን መንገድ እንደሚያዋቅር ያሳየናል ስለዚህ በኢየሱስ ጥምቀት ላይ እምነት ሳይኖረን መዳን አንችልም ሐዋርያው ጴጥሮስም ይህ *«አሁን የሚያድነን ምሳሌ» (1ኛ ጴጥሮስ 3:21)* እንደሆነ ይናገራል።

በኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞት በማመን ብቻ በእግዚአብሄር ፊት መዳን አንችልም በብሉይ ኪዳን እስራኤሎች እጆቻቸውን በመስዋዕቱ ላይ ሳይጭኑ መስዋዕትን አቅርበው ቢሆን ኖሮ ትክክል ባልሆነም ነበር በተመሳሳይ መንገድ አጥማቂው ዮሐንስ የሰዎች ሁሉ ወኪል ሆኖ ኢየሱስን ባጠመቀው ጊዜ እጆቹን ጭኖበት ነበር ይህም ሐጢያቶቻችን በሙሉ ወደ ኢየሱስ ለመተላለፋቸው ስሜትን የሚሰጥ ነው።

አሁን ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት የእግዚአብሄርን ጽድቅ ለሰዎች ሁሉ በቀናነትና በተገቢው መንገድ እንደፈጸመ ግልጽ ሆኖልናል ስለዚህ አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስን ባጠመቀ በበነጋው እንዲህ ሲል መሰከረ *«እነሆ! የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!» (ዮሐንስ 1:29)* ኢየሱስ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ በጫንቃዎቹ ላይ ተሸክሞ ወደ

መስቀል በመሄድ በጥምቀቱ አማካይነት በራሱ ላይ ለወሰዳቸው ሐጢያቶች በሙሉ ፍርድን ተቀበለ ከዚያም *«ተፈጸመ!» (ዮሐንስ 19:30)* በማለት በመስቀል ላይ ሞተ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከመወለዳችንም በፊት እንኳን ሐጢያቶቻችንን በሙሉ አንጽቷል ሁሉንም አስወግዶዋቸዋል ነገ የምንሰራቸው ሐጢያቶችም እንደዚሁ በአለም ሐጢያቶች ውስጥ ተካተዋል የአለም ሐጢያቶች በሙሉም ከ2000 አመታት በፊት ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል እርሱ አንድም ያስቀረው ሐጢያት የለም ወንጌል ኢየሱስ ያለፉትንና የወደፊት ሐጢያቶችን በሙሉ በአንድ ጊዜ ወስዶ ዋጋቸውን እንደከፈለ ከሙሉ ልባችን እንድናምን ይነግረናል።

*«በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና» (ገላትያ 3:27)* በኢየሱስ ውስጥ መጠመቅ ማለት በእርሱ ጥምቀት ላይ ባለን እምነታችን ከክርስቶስ ጋር ተባብረናል ማለት ነው ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቻችን በአጥማቂው ዮሐንስ አማካይነት ወደ እርሱ ተላልፈዋል በሌላ አነጋገር ሐጢያቶቻችን ነጽተዋል አሁን ሐጢያት የለብንም የኢየሱስን ጥምቀት በልባችን ውስጥ ከተቀበልንበት ቅጽበት ጀምሮ ጻድቃን ሆነናል።

በዚህ ዘመን ብዙ ሰዎች ሐጢያቶቻቸው ይቅር እንደተባሉ ወይም እንዳልተባሉ እርግጠኞች አይደሉም አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸውን ሁሉ በእንቆቅልሽ ያሳልፋሉ ነገር ግን ራሳችንን ለእውነተኛው ወንጌል ብናስገዛ አሁን ሐጢያት የለብንም ብለን በድፍረት መናገር እንችላለን።

ኢየሱስ ለዘላለም እንደቀደሰን ተናግሮዋል በየቀኑ ንስሐ ብንገባ ወደ ብሉይ ኪዳን ዘመንም ልንመለስ እንችል ይሆናል ስለዚህ ፈጽሞ ጻድቃን አንሆንም በእግዚአብሄር ብናምንም እንኳን ሐጢያት ሳንሰራ መኖር አንችልም በመሐሉም ንስሐ

በመግባት አንቀደስም እኛ በየቀኑ ያለ ማቋረጥ ሐጢያት እንሰራለን ስለዚህ ከሐጢያቶቻችንን ሙሉ በሙሉ መመለስ አይቻለንም::

በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ እዳችን በአንድ ጊዜ እንደተከፈለ ማግኘት እንችላለን ስለዚህ በአንድ ጊዜ እንቀደስ ዘንድ ኢየሱስ አንድ ጊዜ ተጠመቀ ራሱንም በመስቀል ላይ አቀረበ ንስሐ በምንገባበት ጊዜ ሁሉ አንድንም ነገር ግን ከሐጢያቶቻችን ለአንዴና ለመጨረሻ ድነናል *«በዚህም ፍቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ አንድ ጊዜ በማቅረብ ተቀድሰናል» (ዕብራውያን 10:10)* በመጨረሻም እኛ ማድረግ ያለብን ነገር የእርሱን ጥምቀትና ስቅለት ማመን ብቻ ነው::

አሁን እውነተኛ ወንጌል እንደሆነ በማምነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ሙሉ በሙሉ አምናለሁ ኢየሱስን ከማንኛ ውም ነገር ይበልጥ ስለምወደውም የምትሰጡኝን ስራ ሁሉ በታማኝነት ለመስራት ቃል እገባለሁ ለእርሱ ማድረግ የምችለው ብቸኛው ነገር ይህ ነው:: ✉

# አባሪ 2

# ተጨማሪ ማብራርያ

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።



ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

# ተጨማሪ ማብራርያ

## • ቤዛ

የተጠየቀውን ዋጋ በመክፈል በምላሹ ንብረትን ወይም ግለሰብን ማስለቀቅ፣ ለዚህ መለቀቅ የተጠየቀ ወይም የተከፈለ የገንዘብ ዋጋ ወይም ክፍያ፣ብዙውን ጊዜ መዋጀትን በአዎንታዊ መልኩ ለመግለጥ ጥቅም ላይ የዋለ (ለምሳሌ፡- ዘፀአት 21፡30 'ረብጣ ገንዘብ' ፣ በዕዝራ 35፡31-32፣ በኢሳይያስ 43፡3 ላይ «ቤዛ») በአዲስ ኪዳን በማቴዎስ 20፡28 እና በማርቆስ 10፡45 ላይ ቤዛን «የገንዘብ ክፍያ» አድርገው አብራርተውታል፡፡

## • ማስተሰረይፐስርየት

የሰዎችን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ የማስተላለፍ ስርአት፡፡ በብሉይ ኪዳን ስርየት እጆችን በራሱ ላይ በመጫን ሐጢያትን ወደ መስዋዕቱ ማስተላለፍ ነበር በአዲስ ኪዳን ስርየት ማለት በአጥማቂው ዮሐንስ የሆነው ጥምቀት ማለት ነው በዕብራይስጥና ግሪክ ይህ ቃል ሐጢያተኞች ከእግዚአብሄር ጋር ትክክለኛ ወደሆነ ዝምድና ውስጥ ይገቡ ዘንድ ሐጢያትን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ማስተላለፍ የሚል ፍቺ አለው አዲስ ኪዳን ለስርየት የሚቀርበውን መስዋዕት በሚገባ አብራርቶታል ይህም የኢየሱስ ጥምቀትና የመስቀል ላይ ሞቱ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን፡ *«ስርየት»* የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ 100 ጊዜ ያህል ጥቅም ላይ ውሎዋል ሁልጊዜም

በዕብራይስጥ የተገለጠው (በዘሌዋውያን 23:27፤25:9፤ በዘኍልቁ 5:8) *«ካፋር»* (ብዙውን ጊዜ የተጻፈው «ስርየት ማድረግ» ተብሎ ነው) ስርየት እጆችን በሕያው ፍየል ራስ ላይ በመጫንና የእስራኤሎችን በደሎች ሁሉ በእርሱ ላይ በመናዘዝ የሐጢያቶችን ማስተላለፍ የሚያመላክት የዕብራይስጥ ቃል ትርጉም ነው:: (በዘሌዋውያን 16:20)::

ስርየት *«ሔፕር»* ከሚለው የአራማይክ ቃል ጋር ተዛምዶ ያለው ሲሆን ትርጓሜውም መሸፈን ማለት ነው ይህም ማለት በአዲስ ኪዳን የኢየሱስ ቤዛነት ጥምቀት ማለት ነው ኢየሱስ የሰውን ዘር ደህንነት ለመፈጸም ወደዚህ አለም መጥቶ በ30 አመቱ ተጠመቀ::

- **መጽሐፍ ቅዱሳዊው ስርየት**

*ሀ.* በብሉይ ኪዳን ስርየት ብዙውን ጊዜ የሚሰጠው በአንድ እንስሳ መስዋዕትነት አማካይነት ነው:: (ምሳሌ:- ዘፀአት 30:10፣ ዘሌዋውያን 1:3-5፣ 4:20-21፣ 16:6-22)::

*ለ.* በአዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን የስርየት መስዋዕት እሳቤ በዋናነት ድጋፍ አግኝቷል ነገር ግን የሰው ዘር ሁሉ ቤዛነት ሊፈጸም የሚችለው የእግዚአብሄር ልጅ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ በማቅረብ ብቻ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐጢያቶቻችን እንደሞተ ተናግሮዋል:: (1ኛ ቆሮንቶስ 15:3)

ስርየት የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው የአዳምን ሐጢያት ለማስተሰረይ የሆነውን የክርስቶስን ሞት ለማመላከት ብቻ ሳይሆን የሰዎችን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድም ነው የአለም ሐጢያቶች ወደ ኢየሱስ ከተላለፉበት ጥምቀት በኋላ

(ማቴዎስ 3፡15) እርሱ በመስቀል ላይ ደሙን በማፍሰስ የሰውን ዘር ሁሉ አዳነ፡፡ (ዘሌዋውያን 1፡1-5፣ ዮሐንስ 19፡30)

ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡14 ላይ *«አንዱ ስለ ሁሉ እንደሞተ»* ያብራራና ከዚያም በቀጣዩ ቁጥር 21 ላይ ይህም *«ስለ እኛ»* እንደነበር ያወሳል በገላትያ 3፡13 ላይም እንደዚሁ *«ስለ እኛ እርግማን ሆነ»* ይለናል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኢየሱስን እንደ መስዋዕት የሚጠቁሙት ጥቂት ቁጥሮች ብቻ ናቸው (ለምሳሌ፡- ኤፌሶን 5፡2) ዮሐንስ 1፡29,36 («በግ» -- አጥማቂው ዮሐንስ) እና 1ኛ ቆሮንቶስ 5፡7 («ፋሲካችን» -- ሐዋርያው ጳውሎስ)፡፡

ነገር ግን ጳውሎስ ኢየሱስ በዮርዳኖስ የተቀበለው ጥምቀት ለአለም ሁሉ ሐጢያቶች የሆነ ስርየት እንደነበር በግልጽ ያስቀምጣል በሮሜ 6 ላይ የአለም ሐጢያቶች በሙሉ በአጥማቂው ዮሐንስ በሆነው ጥምቀት አማካይነት ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ አብራርቷል፡፡

እርሱ የኢየሱስ ስቅለት የሐጢያት ፍርድና ካሳ እንደነበር የስርየት መስዋዕትም ለሰዎች ሁሉ ነፍስ እንደቀረበ ማብራራቱን ይቀጥላል፡፡

የኢየሱስ ሞት በብሉይ ኪዳን የስርየት መስዋዕት የተመለከተው የእግዚአብሄር ዕቅድ መታወቂያ ነበር በብሉይ ኪዳን የነበረው የእጆች መጫንና በአዲስ ኪዳን ያለው የኢየሱስ ጥምቀት በእግዚአብሄር ሕግ መሰረት የሆኑ ናቸው፡፡ (ኢሳይያስ 53፡10፣ ማቴዎስ 3፡13-17፣ ዕብራውያን 7፡1-10፣ 18፣ 1ኛ ጴጥሮስ 3፡21)

አዲስ ኪዳን በኢየሱስ ጥምቀትና ሞት አያበቃም ነገር ግን የደህንነት ፍጻሜ አሮጌው ማንነታችን ከእርሱ ጋር ይሞት ዘንድ በሚያስችለን በክርስቶስ ውስጥ መጠመቅ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ (ሮሜ 6፡3-7፣ ገላትያ 2፡19-20)

አጥማቂው ዮሐንስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ

እንዲወስድ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳጠመቀውና ከዚህ የተነሳም እንደተሰቀለ ይነግረናል ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱና በደሙ አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች ከማንጻቱም በላይ በሰው ዘር ፋንታ ቅጣትን በመቀበልና ስቃይን በመታገስ ከሰይጣን ሐይል አድኖን ወደ እግዚአብሄር ሐይል መልሶናል::

ስለዚህ የኢየሱስ ቤዛነት ሰዎች ወደ እግዚአብሄር እንዳይቀርቡ ያግዳቸው የነበረውን የሐጢያት ችግር ፈቶዋል ይህ ጠቃሚ ሁነት ደህንነትን ደስታን (ሮሜ 5:11) ሕይወትን (ሮሜ 5:17-18) እና ቤዛነትን (ማቴዎስ 3:15፣ ዮሐንስ 1:29፣ ዕብራውያን 10:1-20፣ ኤፌሶን 1:7፣ ቆላስያስ 1:14) በአንድ ጊዜ በማምጣት በሕዝቡና በእግዚአብሄር መካከል ሰላምንና ስምምነትን አምጥቶዋል::

## • የስርየት ቀን

በዕብራይስጥ ይህ እሳቤ «የሽፋን» ወይም «የዕርቅ» ቀን ማለት ነው ለአይሁዶች እጅግ አስፈላጊው ቀን በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን የሚውለው የስርየት ቀን ነበር (ዘሌዋውያን 23:27፣ 25:9) ሊቀ ካህኑም እንኳን በዚያ ቀን የሚደረጉትን ግልጽ የሆኑ ስርአቶች ሳይፈጽም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት እንደማይችል ከዘሌዋውያን 16 ማየት እንችላለን::

ራሱ ቅድስተ ቅዱሳኑ እንደዚሁም የእስራኤል ሕዝብ ስርየት ያስፈልጋቸው ነበር ስለዚህ ሊቀ ካህኑ እጆቹን በመስዋዕቱ ራስ ላይ በመጫን ሐጢያቶችን ለማስተላለፍ መስዋዕትን ማቅረብ ነበረበት እስራኤሎች በስርየት ቀን ስለ እግዚአብሄር ቅድስናና ስለ ሐጢያቶቻቸው ያስቡ ነበር::

በዚያ ቀን 15 መስዋዕቶችን ያህል የበዙ (የሚለቀቀውን

ፍየል ጨምሮ) 12 የሚቃጠሉ መስዋዕቶችና 3 የስርየት መስዋዕቶች ለእግዚአብሄር ይሰዉ ነበር (ዘሌዋውያን 16:5-29፣ ዘኁልቁ 29:7-11) በዘሁልቁ 28:8 ላይ የተጠቀሰውን *«ሌላውን ጠቦት»* ከቆጠርን 13 የሚቃጠሉ መስዋዕቶችና 4 የስርየት መስዋዕቶች ይኖራሉ፡፡

እስራኤሎች የአመቱን ሐጢያቶች ለማስተሰረይ የሚጠቀሙ በት ቀን ሰባተኛው ወር አስረኛው ቀን ነበር በተመሳሳይ ሁኔታም ለአለም ሁሉ የሚሆነው የስርየት ቀን ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ የተጠመቀበት ቀን ነበር ይህ በእርግጥም ለሰው ዘር ሁሉ የስርየት ቀን ነው ይህ ቀን እግዚአብሄር የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ያስወገደበት ቀን ነው (ማቴ 3:13-17) እግዚአብሄር *«እንዲህ...ጽድቅን ሁሉ የፈጸመበት»* የስርየት ቀን ነበር፡፡

- **የስርየት መስዋዕት**

በብሉይ ኪዳን፡ ልክ እንደ ሌሎቹ መስዋዕቶች ሁሉ እስራኤሎችን ሁሉ የሚቀድሰው የቅድስና መስዋዕት በመገናኛ ው ድንኳን ውስጥ ይቀርብ ነበር ሊቀ ካህኑ ራሱን አንጽቶ ስርአቶችን ለማከናወን በሚለብሳቸው የተለመዱ መደበኛ ልብሶች ፋንታ ቅዱስ የሆኑትን የበፍታ መጎናጸፊያዎች ይለብሳል ለእርሱና ለቤተሰቡም የሐጢያት ቁርባን ይሆን ዘንድ ወይፈን የሚቃጠል መስዋዕት ይሆን ዘንድም አውራ በግ ይመርጣል (ዘሌዋውያን 16:3-4) ሊቀ ካህኑ የሕዝቡን አመታዊ ሐጢያቶች ለማስተላለፍ እጆቹን በመስዋዕቶቹ ራስ ላይ ይጭናል፡፡

እጆችን መጫን የስርየት ቀን አስፈላጊው ክፍል ነበር

ባይከናወን ኖሮ መስዋዕቶችን ማቅረብ አይከናወንም ነበር ምክንያቱም የሐጢያት ስርየት ያለ እጆች መጫን ሊፈጸም ስለማይችል የእስራኤሎችን አመታዊ ሐጢያቶች ወደ ሐጢያት መስዋዕቱ ማስተላለፍም አይከናወንም ነበር።

በዘሌዋውያን 16:21 *«አሮንም ሁለቱን እጆቹን በሕያው ፍየል ራስ ላይ ይጭናል በላዩም የእስራኤልን ልጆች በደል ሁሉ መተላለፋቸውንም ሁሉ ኃጢያታቸውንም ሁሉ ይናዘዛል በፍየሉም ራስ ላይ ያሽክመዋል በተዘጋጀውም ሰው እጅ ወደ ምድረ በዳ ይሰድደዋል።»*

እርሱ የሐጢያት መስዋዕቶች ይሆኑ ዘንድ ሁለት ፍየሎችን የሚቃጠል መስዋዕት ይሆን ዘንድም አንድ አውራ በግ (ዘሌዋውያን 16:5) ወሰደ ከዚያም በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ላይ በጌታ ፊት ሁለት ፍየሎችን ያቀርብና አንዱን *«ለእግዚአብሄር»* ሌላውን *«ለሚለቀቅ ፍየል»* አድርጎ ለመለየት ዕጣዎችን ይጥላል።

ለጌታ የሆነው ፍየል የሐጢያት መስዋዕት ሆኖ ይቀርብ ነበር የሚለቀቀው ፍየልም የእስራኤልን ሕዝብ አመታዊ ሐጢያቶች ለማስተሰረይ በጌታ ፊት ሕያው ሳለ ይቀርብና ከዚያም ወደ ምድረ በዳ ይሰደዳል። (ዘሌዋውያን 16:7-10)

የእስራኤል ሐጢያቶች በሊቀ ካህኑ እጆች መጫን ወደሚለቀቀው ፍየል መተላለፍ ነበረባቸው ከዚያም የእስራኤልን ሐጢያቶች በሙሉ በራሱ ላይ የወሰደው የሚለቀቀው ፍየል ሕዝቡና እግዚአብሄር ይታረቁ ዘንድ ወደ ምድረ በዳ ይሰደዳል በዚህም የእስራኤል አመታዊ ሐጢያቶች ይነጹ ነበር።

በአዲስ ኪዳን፡ በተመሳሳይ መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ (በብሉይ ኪዳን እጆች መጫን) ተጠመቀ የእግዚአብሄርን ማዳን የሚፈጽም የመስዋዕት በግ ሆኖ የአለምን

ሐጢያቶች በሙሉ ወሰደ:: (ዘሌዋውያን 20:22፣ ማቴዎስ 3:15፣ ዮሐንስ 1:29, 36)

በብሉይ ኪዳን ዕጣዎቹ ከመጣላቸው በፊት አሮን ለራሱና ለቤተሰቡ ወይፈኑን ያርዳል (ዘሌዋውያን 16:11) ከዚያም በጌታ ፊት ካለው መሰውያ ላይ በተወሰደ የእሳት ፍም የተሞላ ጥና ወስዶ ከተወቀጠው ከጣፋጭ ዕጣን እጁን ሙሉ ይወስድና ከመጋረጃው በስቲያ ይዞት ይገባል ከዚያም የዕጣኑ ጢስ በስርየት መክደኛው ላይ ይሰፍፍ ዘንድ በጌታ ፊት ዕጣኑን በእሳቱ ላይ ይጨምረዋል ከወይፈኑ ደም የተወሰነውን ወስዶ በስርየት መክደኛው ፊት ሰባት ጊዜ በጣቱ ይረጨዋል:: (ዘሌዋውያን 16:12-19)

በስርየት ቀን አሮን በመስዋዕቶቹ ራስ ላይ የሚጭናቸው እጆቹ መቋረጥ የለባቸውም አሮን እጆቹን በፍየሉ ራስ ላይ ጭኖ የእስራኤልን ሐጢያቶችና በደሎች ሁሉ በራሱ ላይ ያስተላልፋል ከዚያም ፍየሉ በተመረጠው ሰው እጅ ወደ ምድረ በዳ ይወሰድና ይለቀቃል የሚለቀቀው ፍየል የእስራኤልን ሐጢያቶች ይዞ በምድረ በዳ ይቅበዘበዝና በመጨረሻም ለእነርሱ ሲል ይሞታል በብሉይ ኪዳን ዋናው የስርየት መስዋዕት ይህ ነበር::

ይህ በአዲስ ኪዳንም የሚለቀቀው ፍየል በጥምቀቱ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በወሰደው ስለሁላችንም በመስቀል ላይ ደሙን ባፈሰሰውና በሞተው በኢየሱስ ክርስቶስ ከመተካቱ በቀር ተመሳሳይ ነው::

ስለዚህ አሁን ከሐጢያቶች ሁሉ መዳን ሰማያዊ ሊቀ ካህን ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትና ስቅለት ውጭ ሊመጣ አይችልም ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድ ደህንነት ፍጻሜ ይህ ነው::

## • እጆችን መጫን፣ ሹመት

በብሉይ ኪዳን ሐጢያትን ለማስተላለፍ እግዚአብሄር የሰጠው ዘዴ ይህ ነበር (ዘሌዋውያን 4:29፣ 16:21) በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሄር ሰዎች በመገናኛው ድንኳን ውስጥ እጆቻቸውን በሐጢያት መስዋዕቶች ራሶች ላይ በመጫን ሐጢያቶቻቸውን እንዲያስተሰርዩ ፈቅዶላቸዋል ይህም በአዲስ ኪዳን የሚመጣውን የኢየሱስን ጥምቀት ለመግለጥ ነበር፡፡

## • ጥምቀት

ጥምቀት ማለት ① መታጠብ ② መቀበር (መጥለም) በመንፈሳዊ ትርጉምም ③ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንደተደረገው እጆችን በመጫን ኃጢያትን ማስተላለፍ ማለት ነው፡፡

በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ የተጠመቀው የአለምን ሐጢያት በሙሉ ለማንጻት ነበር *'የኢየሱስ ጥምቀት'* የሰውን ዘር ሁሉ ሐጢያቶች የመውሰድና የአለምን ሐጢያቶች የማንጻት ትርጉም አለው፡፡

ኢየሱስ የሰዎች ሁሉ ወኪልና ከአሮን የዘር ግንድ በሆነው ሊቀ ካህን በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በራሱ ላይ ወስዶዋል የእርሱ ጥምቀት አላማው ይህ ነበር፡፡

*'ጥምቀት'* የሚለው ቃል መንፈሳዊ ትርጉም *'ማስተላለፍ፣ መቀበር'* ማለት ነው ስለዚህ «የኢየሱስ ጥምቀት» ማለት የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል እርሱም በእኛ ፋንታ ተኮንኖዋል ማለት ነው ኢየሱስ የሰውን ዘር ለማዳን ሲል በጥምቀቱ ሐጢያቶቻችንን መውሰድና ለእነርሱም መሞት ነበረበት፡፡

ስለዚህ የእርሱ ሞትም እንደዚሁ የእናንተና የእኔ የአለም ሐጢያተኞችም ሁሉ ሞት ነው የእርሱ ትንሳኤም የሰዎች ሁሉ ትንሳኤ ነው የእርሱ መስዋዕትነት የሐጢያተኞች ደህንነት ነው የእርሱ ጥምቀት የሰው ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ለመወገዳቸው ዋና ምስክር ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ *«ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል» (1ኛ ጴጥሮስ 3:21)* ይላል የኢየሱስ ጥምቀት ሐጢያቶቻችንን በማስወገድ ሰዎችን ሁሉ የማዳኛው የጽድቅ መንገድ ነው::

- ## ኃጢያት

እግዚአብሄርን የሚቃወም ነገር ሁሉ ሐጢያት ነው ይህ የአዳምን ሐጢያትና እኛ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ የምንሰራቸውን መተላለፎች ጨምሮ ሐጢያቶችን ሁሉ ይመለከታል::

ሐጢያት በግሪክ *'ሐማርቲያ'* ነው ግሳዊ መልኩም *'ሐማርታኖ'* ሲሆን ትርጓሜውም 'ኢላማን መሳት' ነው ስለዚህ እጅግ አስከፊ ከሆኑት ሐጢያቶች አንዱ በተሳሳተ መንገድ በኢየሱስ ማመንና የመዳን አቅም ማጣት ነው እውነትን አለማወቅም ሆነ አለማመን የአለመታዘዝን ሐጢያት መስራትና እግዚአብሄርን መሳደብ ነው::

በእግዚአብሄር ፊት በእውነት እንዲህ ያለ ሐጢያት መስራት የማንፈልግ ከሆነ የእርሱን ቃሎች በትክክል መረዳትና ኢየሱስ አዳኛችን የመሆኑን እውነት መገንዘብ ይኖርብናል::

በእግዚአብሄር ቃሎች አማካይነት የኢየሱስን ጥምቀትና መስቀሉን ማመን ይገባናል የእግዚአብሄርን ቃል አለመቀበል ከእውነት ማፈንገጥና የሐሰት ጽንሰ ሐሳቦችን ማመን ሐጢያት ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ‘ወደ ሞት የሚመራው ሐጢያት’ (1ኛ ዮሐንስ 5:16) ማለትም እጅግ አደገኛው ሐጢያት እግዚአብሄር የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ እንዳስወገደ አለማመን እንደሆነ ይነግረናል በኢየሱስ ውልደት በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያትን ማስወገዱንና ደሙን በመስቀል ላይ በማፍሰስም ሕይወቱን ለእኛ መስጠቱን ማመን ይኖርብናል አንድ ሰው ኢየሱስ እኛን ከሐጢያቶቻችንን ሁሉ ለማላቀቅ እንደተጠመቀ በመስቀል ላይ እንደሞተና እንደተነሳ በሚናገሩት የተጻፉ ቃሎች የማያምን ከሆነ ሐጢያት ነው::

- ## ንስሐ

ከእግዚአብሄር የራቀ ሰው ሐጢያቶቹን ተገንዝቦ ኢየሱስ እንዳስወገዳቸው እርሱን በማመስገን ወደ እግዚአብሄር ሲመለስ ይህ ንስሐ ተብሎ ይጠራል::

ሁላችንም የሐጢያት ክምሮች ነን እውነተኛ ንስሐ ቀጣዩን እውነት መቀበል ነው እኛ በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኞች እንደሆንን፣ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ሐጢያት እንደምንሰራና ስንሞት ሲዖል እንደምንወርድ፣ ኢየሱስ እንደ እኛ አይነት ሐጢያተኞችን ለማዳን ወደዚህ አለም እንደመጣ በማመን እርሱን አዳኛችን አድርገን መቀበል እንደሚኖርብን፣ እኛን ለማዳንም ሐጢያቶችን ሁሉ (በጥምቀቱ አማካይነት) እንደወሰደ እንደሞተና እንደተነሳ ማመን አለብን እውነተኛ ንስሐ የራሳችንን አስተሳሰቦች መተውና ወደ እግዚአብሄር መመለስ ነው:: (የሐዋርያት ሥራ 2:38)

ንስሐ ሐጢያቶቻችንን ማመንና ከሙሉ ልባችንም የውሃውንና የደሙን ደህንነት ለመቀበል ወደ እግዚአብሄር ቃል

መመለስ ነው፡፡ (1ኛ ዮሐንስ 5፡6)

እውነተኛ ንስሐ እኛ ፈጽመን ሐጢያተኞች መሆናችንን መቀበልና ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ያዳነንን የእግዚአብሄር ልጅ ኢየሱስን አዳኛችን አድርገን ማመን ነው ለመዳንና ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ለመንጻት በራሳችን ስራዎች አማካይነት ለመቀደስ መሞከርን ማቆምና እኛ በእግዚአብሄርና በሕጎቹ ፊት ፈጽመን ሐጢያተኞች መሆናችንን ማመን አለብን ከዚያም ኢየሱስ በጥምቀቱና በደሙ የሰጠንን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የደህንነቱን እውነት መቀበል ይኖርብናል፡፡

አንድ ሐጢያተኛ የራሱን አስተሳሰቦች ሁሉ መተውና ፈጽሞ ወደ ኢየሱስ መመለስ አለበት የኢየሱስ ጥምቀት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በራሱ ላይ የወሰደበት እንደሆነ ወደ ማመን ስንመጣ እንድናለን፡፡

በሌላ አነጋገር የኢየሱስ ጥምቀት ስቅለቱና ትንሳኤው ለሐጢያተኞች ሁሉ ደህንነት የእግዚአብሄርን ጽድቅ ፈጽመዋል ኢየሱስ በስጋ መጣ ሐጢያቶቻችንን ሁሉ ለማስወገድም ተጠመቀ ተሰቀለ እውነተኛ ንስሐና ትክክለኛ እምነት በእነዚህ ሁሉ ላይ ሙሉ እምነት መያዝና ኢየሱስ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ አዳኝ ለመሆን እንደተነሳ ማመን ነው፡፡

## • ደህንነት

በክርስትና ውስጥ ደህንነት ማለት ‘ከሐጢያት ሐይል ወይም ቅጣት መዳን’ ማለት ነው ለሐጢያቶቻችን ሲያል እንደምንወርድ ስንቀበልና ኢየሱስ በውልደቱ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ እንዳዳነን ስናምን ደህንነትን እንቀበላለን፡፡

በኢየሱስ ደህንነት በኢየሱስ ጥምቀትና ደም በማመን ሐጢያት አልባ የሆኑ ሰዎች ‘የዳኑ፣ ዳግም የተወለዱና ጻድቃን’ ተብለው ይጠራሉ::

*‘ደህንነት’* የሚለውን ቃል በኢየሱስ በማመን የአዳምን ሐጢያትና በየቀኑ የሚሰሩዋቸውን ሐጢያቶች ጨምሮ ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ለዳኑ ሰዎች ልናውለው እንችላለን እየሰጠመ ያለው ሰው እንደሚድን ሁሉ በአለም ሐጢያት ውስጥ እየሰጠመ ያለ ሰውም ኢየሱስን አዳኙ አድርጎ በማመን የመንፈሳዊ እውነት ቃሎች በሆነው የእርሱ ጥምቀትና ደም በማመን መዳን ይችላል::

- **ዳግም መወለድ**

ይህ ማለት *‘ለሁለተኛ ጊዜ መወለድ’* ማለት ነው አንድ ሐጢያተኛ ዳግም የሚወለደውና ጻድቅ የሚሆነው በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ በማመን በመንፈሳዊ መልኩ ሲድን ነው::

በኢየሱስ ጥምቀትና ደም በማመን በመንፈሳዊ መልኩ ዳግም መወለድ እንችላለን ዳግም የተወለዱ ሰዎች ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ የነጹና *«ያድናቸው ዘንድ ሁለተኛ ጊዜ ያለ ሐጢያት ይታይላቸው ዘንድ እርሱን የሚጠባበቁት»* ናቸው:: *(ዕብራውያን 9:28)*

- **የኃጢያቶች ስርየት**

ይህ ጠቃሚ እሳቤም እንደዚሁ የሐጢያቶች ይቅርታ ተብሎ ይታወቃል እኛ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት

ለአንዴና ለመጨረሻ ከሐጢያቶች ሁሉ ስንነጻ ሐጢያቶች ይቅር ይባላሉ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እምነት ቅጥልጣል በሆኑ እውነቶች ማመን ነው እነዚህም የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊነት የእግዚአብሄር ልጅ ስጋ መልበስ ለሁላችንም ደህንነት የሆኑት የእርሱ ጥምቀት ስቅለትና ትንሳኤ ናቸው።

ኢየሱስ የሰጠን ቤዛነት በእርሱ ጥምቅትና ደም በማመን የእኛ ሊሆን ይችላል በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንደተተነበየው ኢየሱስ ራሱ ሰዎችን ሁሉ ከሐጢያት አድኖዋቸዋል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ቤዛነት በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ላይ ባለው እምነት አማካይነት የሆነውን የሐጢያቶች መንጻት ይጠቁማል ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ በሰው ዘር ልብ ውስጥ ሐጢያት የለም።

ራሳችንን የዳንንና ጻድቃን ብለን መጥራት የምንችለው በእርሱ ጥምቀት ላይ ባለን እምነት አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወደ ኢየሱስ ስናስተላልፍ ብቻ ነው።

## • ኢየሱስ ክርስቶስ

**ኢየሱስ፡** *‘ሰዎችን ሁሉ ከሐጢያቶቻቸውና ከእነዚያም ሐጢያቶች ቅጣት ያዳነ አዳኝ’* ኢየሱስ የሚያመላክተው ሰዎችን ሁሉ ከሐጢያቶቻቸው ያዳነውን አዳኝ ነው።

**ክርስቶስ፡** *‘የተቀባ’* በእግዚአብሄር ፊት በስራ ማዕረጎች ላይ መቀባት የነበረባቸው ሦስት አይነት ሰዎች ነበሩ ① ነገስታት ② ነቢያት እና ③ ካህናት። ኢየሱስ ሁሉንም ፈጽሞዋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን ሁሉ ነበር የእነዚህን ስራ ሁሉ ሰርቷል ኢየሱስ ቤዛነትንና ደህንነትን ያመጣልን ንጉስ ነቢይና ካህን እንደሆነ ማመን አለብን ስለዚህ *‘ኢየሱስ ክርስቶስ’* ብለን

እንጠራዋለን እርሱ በጥምቀቱና በደሙ ከአለም ሐጢያቶች ሁሉ ያዳነን ሰማያዊ ሊቀ ካህን ነበር፡፡

ስለዚህ እርሱ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ንጉስ ነው በፊቱ ስንቀርብ ሐጢያቶቻችንን እንድንገነዘብ ያደርገናል ከቅድመ አያቶቻችን ጀምሮ ሐጢያተኞች እንደሆንን የሐጢያተኞች ዘሮች በመሆናችንም ሐጢያተኞች ሆነን እንደተወለድንና ከዚህ የተነሳም ከእግዚአብሄር ፍርድ በታች እንደሆንን አስተምሮናል፡፡

በእርሱ ጥምቀትና ደም አማካይነትም ከሐጢያቶቻችን እንደነጻንም አስተምሮናል እነዚህን ስራዎች ሁሉ የሰራው ለእኛ ለሐጢያተኞች ነው፡፡

## • የእግዚአብሔር ልጅ ለምን ሰው ሆነ?

እርሱ ሰው የሆነው አዳኝ ለመሆንና ሐጢያተኞችን ሁሉ ከሐጢያትና ከሲዖል እሳት ፍርድ ለማዳን ነው፡፡

### • ኢየሱስ ማነው?

በዘፍጥረት 1፡3 እና በዮሐንስ 1፡1-3 ላይ እንደተጠቀሰው እርሱ ፈጣሪ፣ እውነተኛ አምላክ፣ ሐጢያተኞችን ሁሉ ከአለም ሐጢያቶች ያዳነ የዩኒቨርስ ሁሉ አምላክ ነው *(ፊልጵስዩስ 2፡6፣ «እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም» ዮሐንስ 1፡2-3 «ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሐር ዘንድ ነበር ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም»)* ኢየሱስ የፍጥረት አምላክ የዩኒቨርስ ጌታ ነው፡፡

ሆኖም ብዙ ሰዎች በስጋ ወደዚህ አለም በመጣው በኢየሱስ ፍቅርና ደህንነት ባለማመን መዳን አቅቶዋቸዋል ነገር ግን ሌሎች ብዙዎች ደህንነትን ተቀብለው የእግዚአብሄር ሕዝብ ሆነዋል በእርሱ በማመንም የዘላለምን ሕይወት አትርፈዋል ጻድቃን ሆነዋል፡፡

## • በእግዚአብሔር የጸኑት ሕጎች ምንድን ናቸው?

እግዚአብሄር እቅድ አውጭ፣ ብቸኛ፣ እውነተኛ አምላክና ሉአላዊ ሕላዌ ነው ስለዚህ ለሚከተሉት አላማዎች ሲል በአለም ላይ ሕግን አጸደቀ፡፡

① ሐጢያተኞችን ከሐጢያቶቻቸው ለማዳን ሕጉንና ትዕዛዛቱን ሰጣቸው *«ሐጢያት በሕግ ይታወቃልና፡፡» (ሮሜ 3:20)*

② ሁለተኛው ሕግ ሐጢያተኞችን የሚያድን የእምነት ሕግ ነው ይህም አዳኛችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ደህንነትን የሚሰጥ 'የሕይወት መንፈስ ሕግ' ነው (ሮሜ 8:2) ኢየሱስ ይህንን ሕግ ለመፈጸም ወደዚህ አለም መጣ ተጠመቀ በመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰ ከዚያም ተነሳ ኢየሱስ የአለምን ሐጢያተኞች ሁሉ ለማዳን የደህንነትን ሕግ መሰረተ፡፡

እግዚአብሄር በውሃውና በመንፈሱ ደህንነት ለሚያምኑ ሰዎች የእምነትን ሕግ አጸና ለመዳንና የእግዚአብሄር ልጅ ለመሆን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው እግዚአብሄር ባዘጋጀው የእምነት ሕግ ማመን ይኖርበታል ወደ ደህንነት የሚያደርሰው ብቸኛው መንገድ ይህ ነው በዚህም በዚህ ሕግ መሰረት በመንፈሳዊው የደህንነት እውነት የሚያምኑ ሰዎች ሰማይ እንዲገቡ ፈቅዶዋል፡፡

# • የእግዚአብሔር ሕግ፡ አሥርቱ ትዕዛዛት

በእግዚአብሄር ሕግ ውስጥ የቀን ተቀን ሕይወትን የሚመለከቱ 613 የሕግ አንቀጾች አሉ ነገር ግን የእነዚህ መሰረቱ በእግዚአብሄር ፊት ልንጠብቃቸው ያሉት አስርቱ ትዕዛዛት ናቸው «ይህንን አድርግ» «ያንን አታድርግ» የሚሉ ትዕዛዞችና ክልከላዎች አሉ እነዚህ የኑሮ መመሪያዎች ናቸው የእግዚአብሄር ትዕዛዛት የተሰጡን ሐጢያቶቻችንን እንድናውቅ ነው በተጻፉት የእግዚአብሄር ትዕዛዛቶች አማካይነት ምን ያህል እርሱን እንደማንታዘዘው መገንዘብ እንችላለን:: (ሮሜ 3:19-20)

እግዚአብሄር ትዕዛዛቱን የሰጠበት ምክንያት ሐጢያቶቻችንን እንድንገነዘብ ነው የእርሱን ትዕዛዛቶች በሙሉ በፍጹም መጠበቅ አንችልም ስለዚህ በኢየሱስ ከማመናችን በፊት ሐጢያተኞች የመሆናችንን እውነት በትህትና መቀበል አለብን እኛ ሁላችን ሐጢያተኞች ነን እግዚአብሄርም በእርሱ ሕግ መሰረት ፈጽሞ መኖር እንደማንችል ያውቃል ስለዚህ ሰው ሆኖ ወደዚህ አለም መጣ ተጠመቀ በመስቀል ላይም ተኮነነ በእርሱ ትዕዛዛቶች ለመኖር መሞከር የዕብሪት ሐጢያት ነው ያንን ማድረግ አይገባንም::

ሕጉ እግዚአብሄር ምን ያህል ፍጹምና ቅዱስ እንደሆነና ሰዎችም በእርግጥ ምን ያህል ደካሞች እንደሆኑ ያሳየናል በሌላ አነጋገር የእግዚአብሄር ቅድስናና ፍጽምና በእግዚአብሄር ሕግ ውስጥ ተገልጦዋል::

# • በኢየሱስ ማመን አለብን?

አዎ ማመን ይኖርብናል ምክንያቱም እርሱ እጅግ ጻድቅ

የሆነ ጌታችንና ይህም የእርሱ ፈቃድ ነውና *«መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (የሐዋርያት ሥራ 4:12)* ሌላ አዳኝ የለም ኢየሱስ ብቸኛው አዳኛችን ነው መዳንና ዳግም መወለድ የምንችለው በእርሱ በማመን ብቻ ነው ሰማይ መግባትና ለዘላለም መኖር የምንችለው በእርሱ በማመን ብቻ ስለሆነ በእርሱ እምነት ሊኖረን ይገባል።

## • እኛ ክርስትያኖች አሁንም ድረስ ኃጢያተኞች ልንሆን እንችላለን?

አንችልም ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስን ከማግኘቱ በፊት የነበሩትን ቀናቶች በማስታወስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 1:15 ላይ *«ከሐጢያተኞች ዋና»* ከሆኑት አንዱ እንደነበር ተናግሮዋል ዛሬም በክርስቲያን ማህበረሰቦች ውስጥ በኢየሱስ ካመኑ በኋላም እንኳን ሐጢያተኞች እንደሆኑ የሚያስቡ ብዙ ሰዎች አሉ ይህ ግን እውነት አይደለም።

ሁላችንም በኢየሱስ ከማመናችን በፊት ሐጢያተኞች ነን ነገር ግን አንድ ጊዜ በቃሉ መሰረት በኢየሱስ ስናምን ወዲያውኑ ጻድቃን እንሆናለን ሐዋርያው ጳውሎስም ኢየሱስን ከማወቁ በፊት የነበረውን ጊዜ አስታውሶ ከሐጢያተኞች ዋና እንደነበር መሰከረ።

ጳውሎስ ሳውል እየተባለ ይጠራ በነበረ ጊዜ በደማስቆ መንገድ ኢየሱስን ተገናኘው ኢየሱስ አዳኙ እንደሆነ በመገንዘብም አመነ እርሱንም አመሰገነው ከዚያም በቀሪ ዘመኑ የእግዚአብሄር ጽድቅ የሆነው የኢየሱስ ጥምቀት የአለምን ሐጢያቶች እንደወሰደና የአለምን ሐጢያቶች

ለመደምሰስም መሞት እንደነበረበት መሰከረ፡፡

በሌላ አነጋገር እርሱ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የሰበከ የእግዚአብሄር አገልጋይ ሆነ ሆኖም ብዙ ክርስቲያኖች አሁንም ድረስ ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስን ከተገናኘ በኋላ እንኳን ሐጢያተኛ እንደነበረ አሁንም ድረስ ያስባሉ ገና ዳግም ካልተወለዱ ክርስቲያን ሐጢያተኞች አመለካከት ተነስተው ይህንን ምንባብ በተሳሳተ መንገድ ተረድተውታል፡፡

ነገር ግን እውነቱ እርሱ ኢየሱስን ከተገናኘ በኋላ ዳግም ሐጢያተኛ ያልነበረ ነገር ግን በፈለገ ጊዜ ሁሉ ኢየሱስን መገናኘት የቻለ ሰው መሆኑ ነው ቀሪ ዘመኑን የደህንነትን ወንጌልና የኢየሱስን ጥምቀትና ደም ቤዛነት ለመስበክ አሳልፎ ሰጠ እርሱ ከሞተ በኋላ እንኳን የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ከጥንቷ ቤተክርስቲያን ጀምሮ እውነተኛ ወንጌል እንደነበር የሚመሰክሩ መልዕክቶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለእኛ ቀርተውልናል ስለዚህ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡15 ላይ ያለው የሐዋርያው ጳውሎስ ምስክርነት የቀድሞው ዘመኑ ትውስታና ለጌታም የቀረበ ምስጋና ነበር፡፡

እርሱ በኢየሱስ ካመነ በኋላ ሐጢያተኛ ነበር? አልነበረም ዳግም ከመወለዱ በፊት ሐጢያተኛ ነበር ኢየሱስን አዳኙ አድርጎ ባመነበት ቅጽበት፣ የአለም ሐጢያቶች በእርሱ ጥምቀት አማካይነት ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ ባመነበት ቅጽበት፣ በእርሱ የመስቀል ላይ የስርየት ደም ባመነበት ቅጽበት ጻድቅ ሆንዋል፡፡

እርሱ ራሱን የሐጢያተኞች ዋና ብሎ የጠራው የኢየሱስን ተከታዮች ያሳደደበትን ዘመን በማስታወስና እጅግ ተስፋ ቢስ የሆነውን ሐጢያተኛ እርሱን በማዳኑም እግዚአብሄርን ማመስገኑ ነበር፡፡

እርሱን አሁንም ድረስ ሐጢያተኛ ብሎ የሚጠራው ማነው? የኢየሱስን ጥምቀትና ደም ደህንነቱ አድርጎ በማመን

ጻድቃን የሆነውን ሰው ማን ሐጢያተኛ ብሎ ሊጠራው ይችላል? ያንን የሚያደርጉት የቤዛነትን እውነት የማያውቁ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ በኢየሱስ አማካይነት በሆነው ደህንነት በማመን ጻድቅ ሆነ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም የእግዚአብሄር አገልጋይ በመሆን የእግዚአብሄርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝ አድርጎ በማመን ጻድቅ የመሆንን ወንጌል ለሁሉም ሰበከ ሐዋርያው ጳውሎስ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሐጢያተኛ አልነበረም ነገር ግን ጻድቅ የእግዚአብሄር አገልጋይ ወንጌልን በመላው አለም ለሚኖሩ ሐጢያተኞች የሰበከ እውነተኛ አገልጋይ ነበር፡፡

ሐጢያተኛ ለሌሎች መስበክ ይችላልን? ይህ ፈጽሞ አይሰራም ሰው እርሱ ራሱ የሌለውን እንዴት ለሌሎች መስበክ ይችላል! ሰውየው ያልዳነ ሆኖ ሳለ እንዴት ሌሎችን ማዳን ይችላል!

እየሰጠመ ያለ ሰው አጠገቡ ያለውን ሌላውን እየሰጠመ ያለ ሰው ለመርዳት ቢሞክር የሁለቱም መጨረሻው ውሃ ውስጥ መስጠም ይሆናል ሐጢያተኛ እንዴት ሌሎችን ማዳን ይችላል? እርሱ ከራሱ ጋር ሲያል ይዞዋቸው ይወርዳል አንድ የታመመ ሰው ሌላውን የታመመ ሰው እንዴት ተሳክቶለት ሊንከባከበው ይችላል? በሰይጣን የተታለለ ሰው እንዴት ሌላውን ሊያድን ይችላል?

ሐዋርያው ጳውሎስ ሐጢያተኛ ነበር ነገር ግን በኢየሱስ ጥምቀትና ደም አምኖ ከሐጢያት በዳነ ጊዜ ጻድቅ ሆነ ስለዚህ የእግዚአብሄር አገልጋይ በመሆን ለአለም ሐጢያተኞች ወንጌልን መስበክ ቻለ በእግዚአብሄር ጽድቅም ብዙ ሐጢያተኞችን አዳነ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም እርሱ ራሱ ሐጢያተኛ አልሆነም፡፡

እርሱ ዳግም ተወልዶ በሕግ ጽድቅ ሳይሆን በእግዚአብሄር ጽድቅ ዳነ እርሱ የእግዚአብሄር ጽድቅ አገልጋይና ሰባኪ ሆነ

ለእግዚአብሄርም እጅግ ብዙ ነፍሳቶችን ማረከ እርሱ የእግዚአብሄር ጽድቅ ሰባኪ እንጂ የገዛ ራሱን ግለት ወይም የሕግን ጽድቅ የሚሰብክ ሰባኪ አልነበረም።

እርሱ በመጨረሻ ሐጢያተኛ ነበር? አልነበረም ጻድቅ ሰው ሆኖ የእግዚአብሄር እውነት ሐዋርያ ሆነ እርሱን ሐጢያተኛ ብላችሁ አትጥሩት ምክንያቱም ይህ እግዚአብሄርን መሳደብ እንደዚሁም እውነትን በተሳሳተ መንገድ መረዳት ይሆናልና እርሱ ጻድቅ ነበር ከዚህ የተለየ ነገር በማሰብ እርሱን ወይም ኢየሱስን ፈጽሞ መሳደብ አይገባንም።

እርሱ ከኢየሱስ ጋር ከተገናኘ በኋላ ገናም ሐጢያተኛ ነበር የምንል ከሆነ ይህ ኢየሱስን ውሸታም ብሎ መጥራት ነው ኢየሱስ ጻድቅ አድርጎታል የራሱ ጽድቅ አገልጋይ ያደረገውም ኢየሱስ ነበር።

## • የንስሐ ጸሎቶች ኃጢያቶቻችንን ማስወገድ ይችላሉን?

ቤዛነት ፈጽሞ በስራዎቻችን አማካነት ስለማይመጣ የንስሐ ጸሎቶችም ሐጢያቶቻችንን በፍጹም ማንጻት አይችሉም ሐጢያቶቻችንን ፈጽሞ ለዘለቄታው ይነጹ ዘንድ በኢየሱስ ጥምቅትና ደም እንደዚሁም ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ ማመን ይኖርብናል እውነተኛ ቤዛነት የሚሰጠው ኢየሱስ አዲስ ሕይወትን ይሰጠን ዘንድ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ደሙን በማፍሰሱ ሐጢያቶቻችንን እንዳነጻ ለሚያምኑ ሰዎች ነው።

የንስሐ ጸሎቶችን በማቅረብ በየቀኑ የምንሰራቸውን ሐጢያቶች ማንጻት እንችላለን? አንችልም በሕይወታችን የሰራናቸው ሐጢያቶች በሙሉ ኢየሱስ በጥምቀቱ በወሰዳቸው

ጊዜ ቀድሞውኑም ከ2000 አመታት በፊት ነጽተዋል እኛም በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ለዘላለም ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ነጽተናል እርሱ ለእኛ ለምዕመናን የመስዋዕት በግ ሆነ ሐጢያቶቻችንንም በሙሉ አስወገደ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ደሙም የሁሉንም ዋጋ ከፈለ፡፡

በኢየሱስ ካመንን በኋላ የምንሰራቸው ሐጢያቶችም እንኳን የቤዛነት እውነት በሆነው የጥምቀቱ ደህንነት ምንጭ እምነት ተወግደዋል ኢየሱስ ቀድሞውኑም አዳኛችን ሆኖ እስከ ዕለተ ሞታችን ድረስ የምንሰራቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል ኢየሱስ ወደዚህ አለም መጥቶ *«እንዲህ» (ማቴዎስ 3፡15)* በመጠመቅ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶ ጽድቅን ሁሉ ፈጸመ የእግዚአብሄር ልጅ በጥምቀቱ የሐጢያቶቻችንን ሐላፊነት ወሰደ፡፡

የኢየሱስ ጥምቀት *«መታጠብ»* የሚል ትርጉም አለው ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወደ እርሱ ስለተላለፉ እኛ ፈጽሞ ከሐጢያቶቻችንን ነጽተናል ይህም ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ነጻ አውጥቶናል፡፡

ጥምቀት ማለት *«መጥለም፣ መቀበር»* ማለትም ነው ሐጢያቶቻችን በሙሉ ወደ ኢየሱስ ስለተላለፉ እርሱ ለእኛ ለሐጢያተኞች መሞት ነበረበት ሐጢያቶች በሙሉ በእርሱ ጥምቀት አማካይነት ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ የሚያምኑ ሰዎች ለዘላለም ሐጢያት አልባ ሆነዋል፡፡

እውነተኛ እምነት ሐጢያቶቻችን በሙሉ አሁንና ወደፊት የምንሰራቸውም ሐጢያቶች እንኳን ኢየሱስ ጥምቀትን ከዮሐንስ በተቀበለና *«እንዲህ»* የእግዚአብሄርን ጽድቅ ሁሉ በፈጸመ ጊዜ ከ2000 አመታት በፊት ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ በሙሉ ልብ ማመን ነው፡፡

እርሱ ቀድሞውኑም በጥምቀቱ ሐጢያቶቻችንን ከረጅም

ጊዜ በፊት ባያስወግድ ኖሮ አሁን እኛ ከሐጢያቶቻችን የምንነጻበት መንገድ አይኖረንም ነበር ኢየሱስ ከረጅም ጊዜ በፊት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንዳስወገደ አስታውሱ::

ዛሬ እውነተኛ እምነትና መንፈሳዊ ደህንነት ማለት «እነዚህን ሐጢያቶችም ደግሞ አስወግደሃል አይደል?» በማለት ቀድሞውኑም መንጻታቸውን ለማረጋገጥ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በኢየሱስ ፊት ማቅረብ ማለት ነው ይህ ማለት እርሱን ማመንና ማመስገንም ማለት ነው ወደ ምድር የመጣው፣ የተጠመቀው፣ በመስቀል ላይ የሞተው ፣ከዚያም በሦስተኛው ቀን የተነሳውና በዚህም አዳችን የሆነው ለዚህ ነው::

ሐጢያቶቻችንን ባነጻው የኢየሱስ ጥምቀት በማመን ሐጢያቶቻቸውን ያስወገዱ ሰዎች የተባረኩ ናቸው ይህ በየቀኑ ከምንሰራቸው ሐጢያቶች የመንጻት እውነት ነው እውነተኛ እምነት በጥምቀቱ አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በወሰደው በኢየሱስ ማመን ነው::

## • ሮሜ 8:30 እንዲህ ይላል *«አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው»* ታዲያ ይህ ምንባብ በሒደት የሚሆን ቅድስናን ይደግፉልን?

ይህ ምንባብ በሒደት ስለሚሆን ቅድስና አያስተምርም ብዙ የስነ መለኮት ምሁራንና ሐሰተኛ ሰባኪዎች «በኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች ቀስ በቀስ ይለወጡና በስጋና በመንፈስ ሙሉ በሙሉ ይቀደሳሉ» ብለው አስተምረዋል ብዙዎችም ይህንን አምነዋል::

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ገና ዳግም ያልተወለዱ ክርስቲያኖች ራሰቸውን ይበልጥ ግትር ሆነው ያገኙታል በልባቸው ውስጥ ያለው ሐጢያት እያረጁ ሲሄዱ ያድጋል ቅድስናችን እንዴት በጊዜ ላይ የሚመሰረት ሊሆን ይችላል? «በሒደት መቀደስ» የሚሉት ቃሎች እግዚአብሄር አብዝቶ የሚጠላቸውና ዲያብሎስም ሊጠቀምባቸው የሚወዳቸው ቃሎች ናቸው::

እኛ ጻድቃን መሆን የምንችለው በራሳችን መውጭያ መንገድ በማይኖረን ጊዜ ነው ኢየሱስ በጥምቀቱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ስላስወገደና ለእነርሱም ዋጋ ለመክፈል ራሱን መስዋዕት ስላደረገ ጽድቃችን የተመሰረተው በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ብቻ ላይ ነው ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በራሱ ላይ በመውሰዱ እውነታ ላይ ባለን እምነት አማካይነት ጻድቃን ሆነናል::

*«ቅድስና»* የሚለው ቃል *«ቅዱስ መሆን»* ማለት ነው በራስ ቅዱስ ለመሆን መሞከር በእውነት ማመን ሳይሆን በራስ ደካማ ስጋ መታመን ነው::

ቀስ በቀስ በሚሆን ቅድስና ላይ ተስፋ ማድረግ የሚመጣው ከራሳችን መንፈሳዊ ፍላጎቶች ነው እያንዳንዱ ሐይማኖት የራሱ የሆነ የቅድስና ቃል አለው ነገር ግን እኛ በኢየሱስ የምናምን ሰዎች በቃሉ ላይ ፈጽሞ ጠቀሜታን ማኖር አይገባንም::

በኢየሱስ በማመን ቀስ በቀስ አንቀደስም የመንፈሳዊ ግርዘት እውነት በሆነው የኢየሱስ ጥምቀትና ደም በማመን ለአንዴና ለመጨረሻ ጻድቃን እንሆናለን በእውነት ጻድቃን የሆኑ ሰዎች በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ወንጌል እምነት ዳግም የተወለዱ ሰዎች ናቸው::

## • ኃጢያቶቻችንን መናዘዝ ሐጢያቶቻችን እንዲጠፉ ሊያደርጋቸው ይችላልን?

አይችልም ሐጢያቶች በኑዛዜ አይወገዱም የሚወገዱት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል እምነት ነው ሐጢያቶቻችን ሊወገዱ የሚችሉት ከሐጢያቶቻችን ባነጻን በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ስናምን ብቻ ነው በዮርዳኖስ በጥምቀቱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ያነጻው የኢየሱስ መንፈሳዊ ደህንነት ወንጌል ይህ ነው::

የሐጢያቶች ኑዛዜ አንድ ሰው የእግዚአብሄርን ሕግ የሚያውቅበት ብቸኛው መረጃ ነው ነገር ግን ቤዛነት ሊሰጠን የሚችለው በኢየሱስ ጥምቀትና መስቀል ስናምን ብቻ ነው::

እርሱ የተጠመቀበት ውሃና የኢየሱስ ደም ሰዎችን ሁሉ ከሐጢያት ያዳነ የሰማይ እውነት ነው ደህንነታችን የተመሰረተው ኢየሱስ የሰዎችን ሁሉ ሐጢያት እንደወሰደ በማመን ላይ እንጂ በሐጢያቶች ኑዛዜ ላይ አይደለም የኢየሱስ ስቅለት ከእኛ ከሐጢያተኞች ለወሰዳቸው ለእነዚያ ሐጢያቶች በሙሉ የተቀበለው ቅጣት ነው::

ስለዚህ እውነተኛው ደህንነታችን ያለው በዮርዳኖስ በሆነው ጥምቀትና በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደም ላይ ነው እኛ ከሐጢያቶቻችንን ሁሉ የነጻነው ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ባነጻው በኢየሱስ በማመናችን ነው::

ሐጢያቶቻችንን በመናዘዝ መዳን እንደምንችል የሚሰብኩ ሰዎች የእግዚአብሄርን ደህንነት የማያውቁ ሰዎች ናቸው::

ስለዚህ የእግዚአብሄር ደህንነት በሆነው የኢየሱስ ጥምቀትና ደም ማመን አለብን መቼም ቢሆን የሰው ዘር ሐጢያቶች እነርሱን ለእግዚአብሄር በመናዘዝ ይቅር ሊባሉ ይችላሉ አትበሉ::

ሐጢያቶቻችን ሲያል እንዳስቀመጡን እወቁ ነገር ግን

ባዳነንና በእግዚአብሄር ፊት ጻድቃን ባደረገን በኢየሱስ በጥምቀቱና በደሙ ማመናችን ሐጢያቶቻችንን ማስወገድ ይችላል ከሐጢያቶቻችን ሁሉ መዳን የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው ሁላችንም በአንድ ጊዜ ከሐጢያቶቻችን የነጻነው የውሃውና የደሙን የእውነት ቃሎች በማመናችን መሆኑን እንወቅ:: (1ኛ ዮሐንስ 5:4-8)

በተናዘዝን ጊዜ ሁሉ ሐጢያቶቻችንን አይደመሰሱም በኑዛዜ ላይ በመደገፍ ሙጭጭ የምትሉ ከሆነ መጨረሻችሁ ሲዖል ይሆናል በልባችን ውስጥ ያሉት ሐጢያቶች ይነጹ ዘንድ በእውነተኛው ወንጌል እንመን በጭንቅላታችሁ ብቻ ሳይሆን በልባችሁም እመኑ ለዘላለምም ከሐጢያቶቻችሁ ነጻ ሁኑ::

## • እውነተኛው ወንጌል ምንድን ነው?

እውነተኛው ወንጌል በእርሱ ስናምንበት ሙሉ በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ከሐጢያቶቻችን ነጻ መውጣት የሚያስችለን ወንጌል ነው የእግዚአብሄር ወንጌል ሐይል ልክ እንደ ድማሚ ት ነው::

የእግዚአብሄር ወንጌል «ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱን እዳ መ ክፈል የማይችለውን የባለ ዕዳውን (ሐጢያተኛውን) ዕዳ የከፈለበት» ነው ይህ ወንጌል ‘ድማሚት’ ተብሎ የተጠራው እኛ ለሐጢያቶቻችን መሞትና ለኩነኔም ወደ ሲዖል መሄድ ሲገባን የእግዚአብሄር ልጅ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለመደምሰስ የመስዋዕት ቁርባን በመሆኑ ነው::

እርሱ ወደዚህ አለም መጥቶ በዮርዳኖስ ወንዝ በተቀበለው ጥምቀቱ አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በመውሰድ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለዘላለም አስወገዳቸው::

በዮርዳኖስ ወንዝ በተቀበለው ጥምቀቱና በመስቀል ላይ ሞቱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በመውሰድ የሐጢያቶቻችንን ደመወዝ ከ ፈለ ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱና በደሙ ልክ እንደ ድማሚት አፈነዳቸው እውነተኛው ወንጌል ይህ ነው።

እውነተኛው ወንጌል ኢየሱስ ወደዚህ አለም መጥቶ በመጠመቅና በመስቀል ላይ ደሙን በማፍሰስ በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ማዳኑ ነው።

በ1ኛ ዮሐንስ 5:6 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«በውኃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በውኃውና በደሙ እንጂ በውኃው ብቻ አይደለም መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ ነው።»*

## • ኢየሱስ በመስቀል ላይ ራሱን መስዋዕት ያደረገው ለምንድን ነው?

ኢየሱስ መስዋዕት የሆነው በጥምቀቱ አማካይነት ለወሰዳቸው ሐጢያቶቻችን ነበር ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ቅጣት ነጻ መውጣት እንችል ዘንድ ለሐጢያቶቻችን ዋጋ ለመክፈል ስጋውን ሰጠን።

እኛ ማወቅ ያለብን ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን ለመውሰድ በዮርዳኖስ መጠመቁን ነው ኢየሱስ በዚህ ምክንያት በመስቀል ላይ እንደሞተ ማመን ይኖርብናል።

ኢየሱስ ከመሰቀሉ በፊት ባይጠመቅ ኖሮና በመስቀል ላይ ባይሞት ኖሮ ሐጢያቶቻችን በሙሉ ከኛ ጋር ይቀሩ ነበር ስለዚህ በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ማመን አለብን ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ የመስዋዕት በግ ስለሆነ ሐጢያቶቻችንን

በሙሉ ለመደምሰስ መስዋዕት ሆነ፡፡

ሁላችንም ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድም እንደተጠመቀና ለሐጢያቶቻችንም እንደተሰቀለ ማመን ይገባናል ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለመውሰድ ተጠመቀ እኛ ሐጢያተኞችም ከሐጢያቶቻችን ሁሉ እንድንነጻና ከቅጣት እንድናመልጥ ተሰቀለ፡፡

## • ኢየሱስን ያጠመቀው አጥማቂው ዮሐንስ ማነው?

እግዚአብሄር ለእስራኤል በሙሴ አማካይነት ሕጉንና የመስዋዕት ስርአቱን የሰጣቸው ለሐጢያቶቻቸውና ለበደሎቻቸው ስርየትን ያገኙ ዘንድ ነው አርሱ የሙሴ ታላቅ ወንድም የነበረውን አሮንን ሊቀ ካህን አድርጎ በመሾም የእስራኤሎች አመታዊ ሐጢያቶች በሙሉ ይነጹ ዘንድ የስርየት ቀን በሆነው በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን የስርየትን መስዋዕት እንዲያቀርብ አደረገው፡፡ (ዘሌዋውያን 16)

እግዚአብሄር በስርየት ቀን የሚቀርበው መስዋዕት በአሮንና በእርሱ ዘሮች መካከል ባሉ የእርሱ ምትክ ሊቀ ካህናት ብቻ እንዲቀርቡ ግልጽ አድርጎዋል እግዚአብሄር እስራኤሎች አሮን በሚለቀቀው ፍየል ራስ ላይ በሚጭናቸው እጆቹ አማካይነት ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ እንዲያስተሰርዩ መንገድን ከፈተላቸው እግዚአብሄር የመሰረተላቸው የስርየት ሕግ ይህ ነው፡፡

በዚህ ጥላ ኢየሱስ የሰው ዘር አዳኝ እንደነበር በግልጽ እንዲታወቅ አደረገ እግዚአብሄር በአዲስ ኪዳን ዘመን የአሮን ዘር (ማቴዎስ 11፡11-13) የብሉይ ኪዳን የመጨረሻ ሊቀ ካህን (1ኛ ዜና 24፡10፤ሉቃስ 1፡5) የሆነውን አጥማቂውን ዮሐንስን ላከው አጥማቂው ዮሐንስ እግዚአብሄር የላከው ነቢይ የሰው

ዘር ወኪልና ሊቀ ካህን በመሆኑ ሐጢያተኞችን ለማዳን በመጣው በእግዚአብሄር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ለማስተላለፍ ኢየሱስን አጠመቀው፡፡

ሰዎች ሁሉ በአጥማቂው ዮሐንስ አማካይነት ሐጢያቶቻቸውን ወደ ኢየሱስ ማስተላለፍ በመቻላቸው በእርግጥም ተባርከዋል የዮሐንስ ሚና የሰውን ዘር የወከለ ሊቀ ካህንና ሐጢያቶችን ሁሉ ወደ ኢየሱስ ያስተላለፈ የእግዚአብሄር አገልጋይ መሆን ነበር፡፡

አጥማቂው ዮሐንስ በእግዚአብሄር የተላከ የሰው ዘር ወኪልና ሊቀ ካህን ከኢየሱስ 6 ወር በፊት ቀድሞ የተላከም መልዕክተኛ ነበር በሌላ በኩል ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ የወሰደ የእግዚአብሄር በግ ሲሆን አጥማቂው ዮሐንስ ደግሞ በጥምቀት አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች ወደ ኢየሱስ ያስተላለፈ የመጨረሻው ሊቀካህን ነበር አጥማቂው ዮሐንስ የእግዚአብሄር ባርያ ነበር፡፡

## • ኢየሱስ የተጠመቀበት የዮርዳኖስ ወንዝ

የዮርዳኖስ ወንዝ በፍጥነት ወደ ሙት ባህር ይፈስሳል የሙት ባህር ወለል ከባህር ጠለል በ400 ሜትር ዝቅ ያለ ነው ስለዚህ የሙት ባህር ውሃ ወደ የትም ስፍራ መፍሰስ አይችልም በሙት ባህር ውስጥ የተቆለፈ ነው፡፡

የሙት ባህር ጨዋማነት ሌሎች ተራ ባህሮች ካላቸው የጨውነት ባህርይ 10 ጊዜ ያህል ከፍተኛ ነው በዚያ ውስጥ ምንም አይነት ፍጥረት አይኖርም ስለዚህ የሙት ባህር ተብሎ ተጠራ ኢየሱስ በሞት ባህር (በዮርዳኖስ ወንዝ) ውስጥ በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ ይህም በልባቸው ውስጥ

ሐጢያት ከሌለባቸው ሰዎች ውጭ ያሉ ሰዎች በመጨረሻ ለሐጢያቶቻቸው የዘላለም ኩነኔን እንደሚቀበሉ ያመላክታል።

ስለዚህ የዮርዳኖስ ወንዝ ሐጢያቶች የሚነጹበት ሐጢያተኞችም የሚሞቱበት ወንዝ ነው በአጭሩ የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ በተላለፉበት የእርሱ ጥምቀት አማይነት የተላለፉበት የቤዛነት ወንዝ ነው።

## • በብሉይ ኪዳን ለዕለታዊ ኃጢያቶች የሚቀርበው መስዋዕት ምን ነበር?

አንድ ቀን ለሚሰራ ሐጢያት የሚቀርብ የስርየት መስዋዕት አለ ለአንድ ቀን ሐጢያት ስርየትን ለማግኘት አንድ ሰው ወደ መገናኛው ድንኳን ጠቦት፣ በግ፣ ወይፈን ወይም ዋኖስ ማምጣትና ሐጢያቶቹን ወደ መስዋዕቱ ለማስተላለፍ እጆቹን በመስዋዕቱ ላይ መጫን ነበረበት በእግዚአብሄር ሕግ ውስጥ በአንድ ቀን ለሚሰሩ ሐጢያቶች የሚቀርበው የስርየት መስዋዕት ይህ ነበር። (ዘሌዋውያን 3:1-11)

## • በብሉይ ኪዳን ለዓመት ኃጢያቶች የሚቀርበው የስርየት መስዋዕት ምን ነበር?

ይህ እስራኤሎች አመቱን ሙሉ ለሰሩዋቸው ሐጢያቶች በአንድ ጊዜ የሚቀርብ የስርየት መስዋዕት ነበር ሊቀ ካህኑ እጆቹን በፍየሉ ራስ ላይ ይጭንና የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ የአመት ሐጢያቶች በአንድ ጊዜ ያስተላልፋል። (ዘሌዋውያን 16:1-34)

ኢየሱስ ክርስቶስም በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያትን ሁሉ

በራሱ ላይ ለመውሰድ የእግዚአብሄር በግ በሆነ ጊዜ የየቀኑን ሐጢያትና የአመቱን ሐጢያቶች መስዋዕትነቶች አሟላ።

## • ዘለቄታ ላለው ስርየት የሚቀርበው መስዋዕት ምን ነበር?

ይህ በኢየሱስ በማመን በአንድ ጊዜ ለአለም ሐጢያቶች በሙሉ የሆነ ስርየት ነበር ኢየሱስ ለዘላለም የሚኖር የእግዚአብሄር ልጅና ጌታችን ስለሆነ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለዘላለም መውሰድ ይችላል እርሱ ሐጢያቶቻችንን ለዘላለም የወሰደው እንዴት ነበር?

ይህን ያደረገው

① የሰው ስጋ ለብሶ በመወለድ፣

② በዮርዳኖስ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ ፣

③ በእኛ ፋንታ ፍርድን ሁሉ ለመውሰድ በመስቀል ላይ በመሰቀል ነው።

የእግዚአብሄር ልጅ የሰው ስጋ ለብሶ ወደዚህ አለም መጣ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድም በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ የሰውን ዘር ለዘላለም ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ለማዳንም በመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰ። **(ዘሌዋውያን 16:6-22፤ ማቴዎስ 3:13-17፤ ዮሐንስ 1:29፤ ዕብራውያን 9:12፤10:1-18)**

## • የኃጢያት ስርየት የተሰጠው ባንዴ ነው ወይስ ቀስ በቀስ?

ይህ በአንድ ጊዜ የተሰጠ ነው ምክንያቱም ኢየሱስ አንድ

ጊዜ በመጠመቅና ፍርድንም አንድ ጊዜ በመውሰድ ሐጢያቶቻችንን ወስዶዋልና በማቴዎስ 3:15 ላይ እንደተመዘገበው እርሱ *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል»* ብሎዋል፡፡

በዮሐንስ 1:29 ላይ አጥማቂው ዮሐንስ እንዲህ አለ *«እነሆ! የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ»* እንዲሁም በዮሐንስ 19:30 ላይ ኢየሱስ *«ተፈጸመ!»* አለ፡፡

ዕብራውያን 10:9-18 እንዲህ ይላል *«ቀጥሎ፡- እነሆ አምላኬ ሆይ ፍቃድህን ላደርግ መጥቻለሁ ብሎአል ሁለተኛውን ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢያትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞኣል እርሱ ግን ስለ ኃጢኣት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደ ፊት ይጠብቃል አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎኣቸዋልና መንፈስ ቅዱስም ደግሞ ስለዚህ ይመሰክርልናልና ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ፤ በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እፅፈዋለሁ ብሎ ከተናገረ በኋላ ኃጢአታቸውንና ዓመፃቸውንም ደግሜ አላስብም ይላል የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢያት ማቅረብ የለም፡፡»*

የኢየሱስ ጥምቀትና ደም የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለዘላለም ደምስሶዋል፡፡

## • የኃጢአት ደመወዝ ምንድን ነው?

የሐጢያት ደመወዝ ሞት ነው ይህ ምንም ይሁን እያንዳንዱ ሐጢያት በእግዚአብሄር ፊት መኮነን አለበት ለአንዲት ሐጢያት እንኳን ፍርዱ ሞት ነው የእስራኤል ሕዝብ ሐጢያቶቻቸውን ለማስተሰረይ ነውር የሌለበትን በግ ማቅረብ ነበረባቸው ነገር ግን እነዚህ መስዋዕቶች ሐጢያቶቻቸውን ለዘላለም ማንጻት የሚችሉ አልነበሩም *«የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና::» (ዕብራውያን 10:4)*

ስለዚህ እግዚአብሄር ሕዝቡን ሁሉ ከሐጢያቶቻቸው ለማዳን ጠቦትን አዘጋጀ እያንዳንዱ የመስዋዕት እንስሳ ሐጢያትን ሁሉ ለመውሰድና ከዚያም በእነርሱ ምትክ ለመሞት እጆች ሊጫኑበት ይገባ ነበር።

በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ የእግዚአብሄር በግ ሆኖ በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በመውሰድ ስለ እኛ ሞቷል *«የኃጢያት ደመወዝ ሞት ነው የእግዚብሔር የጸጋ ሥጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው::» (ሮሜ 6:23)*

የሐጢያት ደመወዝ ሞት ነው ኢየሱስ ግን በእኛ ፋንታ በመሞትና ለአለም ሐጢያተኞች በሙሉ የዘላለም ሕይወት ስጦታን በማዘጋጀት ፍቅሩን ገለጠ።

## • ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተው ለምንድን ነው?

የኢየሱስ ሞት በጥምቀቱ አማካይነት ለተወሰዱት ሐጢያቶች በሙሉ የተከፈለ ክፍያ ነበር ሰዎች ለሐጢያቶቻቸው ዘላለማዊ የሲዖል እሳት ተጋፍጦዋቸው ነበር

ነገር ግን ኢየሱስ ስለወደደን ሐጢያቶቻችን በሙሉ ወደ ራሱ የተላለፉበትን ጥምቀት ተቀብሎ እኛን ለማዳን በመስቀል ላይ ሞተ።

እርሱ እኛን ከሐጢያትና ከሲዖል እርግማን ለማዳን ራሱን መስዋዕት አደረገ የእርሱ ሞት ለሰው ዘር ሐጢያቶች የተከፈለ ክፍያ ነበር እርሱ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ ተጠመቀ ሁላችንንም ከሐጢያት፣ ከሞት፣ ከፍርድና ከኩነኔ ለማዳንም በመስቀል ላይ ራሱን ለፍርድ ሰጠ።

ኢየሱስ የሞተው ለሰው ዘር ሐጢያቶች ፍርድን ይቀበል ዘንድ በዮርዳኖስ በራሱ ላይ ለወሰዳቸው የአለም ሐጢያቶች ነበር እርሱ በመስቀል ላይ ሞተ ዳግመኛ ጻድቃን ሆነን እንድንኖር ሊፈቅድልን ከሙታን ተነሳ።

## • በኢየሱስ ስናምን ምን እናገኛለን?

① እኛ የሐጢያቶቻችንን ስርየት ተቀብለን ጻድቃን ሆነናል። የኃጢያቶቻችንን ስርየት በማግኘት ቅዱሳን እንሆናለን። (ሮሜ 8:1-2)

② የእርሱን መንፈስና የዘላለም ሕይወትም ተቀብለናል። (የሐዋርያ ሥራ 2:38፤1ኛ ዮሐንስ 5:11-12)

③ የእግዚአብሄር ልጆች የምንሆንበትን ስልጣን ተቀብለናል። (ዮሐንስ 1:12)

④ ወደ እግዚአብሄር መንግስት መንግስተ ሰማያት የመግባት ዕድል አግኝተናል። (ራዕይ ምዕራፍ 21-22)

⑤ የእግዚአብሄርን በረከቶች ሁሉ ተቀብለናል። (ኤፌሶን 1:3-23)

## • በኢየሱስ ማመን ያለብን ለምንድን ነው?

በኢየሱስ ማመን ያለብን፡
① የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለመፈጸም፣
② ከኃጢያቶቻችን ሁሉ ለመዳን፣
③ ከጌታ ጋር ለዘላለም እንኖር ዘንድ መንግስተ ሰማይ ለመግባት ነው።

ሁላችንም በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ከሌለን ሲዖል የምንገባ ሐጢያተኞች ነን ከሲዖል ሊያድነን የሚችለው አዳኛችን ኢየሱስ ብቻ ነው በኢየሱስ ማመን ያለብን እውነተኛ አዳኝ እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው።

• በኢየሱስ የሚያምኑና ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ የዳኑ ሰዎች መጨረሻቸው የት ነው? ---ሰማይ ነው።---

• በኢየሱስ የማያምኑና ያልዳኑ ሰዎች መጨረሻቸው የት ነው? ---ለሐጢያቶቻቸው ሲዖል በእሳትና በዲን ወደሚቃጠል ባህር ይጣላሉ ---- (ራዕይ 21፡8)

• የእግዚአብሄር በጎች እነማን ናቸው? ---በኢየሱስ ጥምቀትና ደም በማመን የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ያገኙ ሰዎች ናቸው።---

*«ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ» (ዮሐንስ 10፡16)* የተባሉት ፍየሎች ናቸው ምክንያቱም በደመ ነፍስ የሚረዱትን በዘፈቀደ ያምናሉ አሁንም ደረስ ሐጢያተኞች ናቸው በኢየሱስ ጥምቀትና ደም የሚያምኑ ሰዎች በአንድ ጊዜ ድነው የእግዚአብሄር በጎች ይሆናሉ።

## • የእግዚአብሔር እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ምንድናት?

የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን በኢየሱስ ጥምቀትና ደም በክርስቶስ የዳኑና የተቀደሱ ጻድቃን ሰዎች ተሰብስበው እግዚአብሄርን የሚያመልኩባት ስፍራ ነች (1ኛ ቆሮንቶስ 1:2) በኤፌሶን 4:5 ላይ እንደተመዘገበው እውነተኛዋ የእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን ምዕመናኖች ሁሉ *«አንድ ጌታ አንድ እምነት አንዲት ጥምቀትንና አንድ አምላክና የሁሉ አባት»* የሆነውን የሚያምኑበት ስፍራ ነች::

## • በመፅሐፍ ቅዱስ መናፍቅ ማነው?

መናፍቅ በኢየሱስ እያመነ በልቡ ውስጥ ሐጢያት ያለበት ሰው ነው በቲቶ 3:11 ላይ እንዲህ ይላል *«መለያየትን የሚያነሳ ሰው ጠማማ እንዲሆን በራሱም ላይ አውቆ ኃጢአትን እንደሚያደርግ አውቀህ፣»*

ኢየሱስ በጥምቀቱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶዋል መናፍቅ ግን የእግዚአብሄር ለጋስ ስጦታ በሆነው በዚህ በተባረከ የውሃ ወንጌል (የቤዛነት ጥምቀት በሆነው የኢየሱስ ጥምቀት) አያምንም በፋንታው ፍጹም የሆነውን ደህንነት በመናቅ ራሱን ሐጢያተኛ አድርጎ ይኮንናል::

መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እነዚህ አይነት ሰዎችን በኢየሱስ የሚያምኑ ነገር ግን ራሳቸውን እንደ ሐጢያተኛ የሚኮንኑ «መናፍቃን» ብሎ ይገልጣቸዋል (ቲቶ 3:11) እናንተ ራሳችሁ መናፍቅ እንደሆናችሁ ወይም እንዳልሆናችሁ ትገረሙ ይሆናል በኢየሱስ እያመናችሁ ነገር ግን አሁንም ድረስ ራሳችሁን ሐጢያተኛ ብላችሁ የምትጠሩ ከሆናችሁ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መንፈሳዊ እውነት አላወቃችሁም::

በኢየሱስ የምታምኑ ነገር ግን አሁንም ድረስ ራሳችሁን ተስፋ ቢስ እንደሆነ ሐጢያተኛ የምትቆጥሩ ከሆናችሁ መናፍቅ ናችሁ ይህ ማለት እውነተኛው የውሃና የመንፈስ ወንጌል ሐጢያቶቻችሁን በሙሉ ለመደምሰስና እናንተን የእርሱ ልጆች ለማድረግ በጣም ደካንማ እንደሆነ ታስባላችሁ ማለት ነው እናንተ ከእነዚያ ሰዎች አንዱ ከሆናችሁ ማለትም ይቅርታን ለማግኘት በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያቶቻችሁን የምትናዘዙና አሁንም ድረስ ሐጢያተኞች መሆናችሁን የምትቀበሉ መናፍቃን ከሆናችሁ እምነታችሁን እንደገና በሚገባ ማጤን አለባችሁ።

ኢየሱስ ሐጢያቶቻችሁን በሙሉ ወስዶ ሳለ እንዴት አሁንም ድረስ ሐጢያተኞች ልትሆኑ ትችላላችሁ? ዕዳችሁ ለእናንተ የተሰጠ ስጦታ ሆኖ ቀድሞውኑም በኢየሱስ ተከፍሎ ሳለ ዕዳችሁን ለመክፈል የምትፍጨረጨሩት ለምንድነው? ዕዳውን ራሳችሁ ለመክፈል ሙጭጭ የምትሉ ከሆነ መናፍቅ ናችሁ ምክንያቱም እምነታችሁ እግዚአብሄር ከሰጠው እምነት የተለየ ነውና በኢየሱስ የሚያምን ነገር ግን ዳግም ያልተወለደ ማንኛውም ክርስቲያን መናፍቅ ነው እውነቱን ማወቅ አለባችሁ እግዚአብሄር የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል የእርሱን ደህንነት ቸል ካላችሁ መናፍቅ ናችሁ።

በሌላ አነጋገር መናፍቅ ራሱን ሐጢያተኛ ብሎ የሚጠራ ራሱን የኮነነ ሰው ነው ቅዱስ እግዚአብሄር ሐጢያተኛን የእርሱ ልጅ አድርጎ ሊቀበለው እንደሚችል ታስባላችሁን? ቅዱስ በሆነው አምላክ እያመናችሁ ራሳችሁን ሐጢያተኛ ብላችሁ የምትጠሩ ከሆነ መናፍቅ ናችሁ መናፍቅ ላለመሆን የኢየሱስን ጥምቀትና በመስቀል ላይ ያፈሰሰውን ደሙን ጥቅል እውነት አድርጋችሁ ማመን ይኖርባችኋል።

እናንተ መዳን የምትችሉት በአንድ ጊዜ በሁለቱም ማለትም በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ስታምኑ ብቻ ነው። 🖂

# አባሪ 3

## ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

---

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።



ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

# ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

**<u>ጥያቄ 1</u>: በደግነትህ የላክልኝን መጽሐፎች ሳነብ በኢየሱስ ጥምቀት ላይ ያሉህ አንዳንድ እሳቤዎች አስደሳች ሆነው አግኝቼአለሁ የእኛ ጥምቀት ከኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ሞትና ትንሳኤ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ልትነግረኝ ትችላለህን?**

**<u>መልስ</u>:** ከሁሉ በፊት በዕብራውያን 6:2 ላይ እንደተጻፈው *«የጥምቀቶችን ትምህርት»* ልናተኩርበት ይገባናል በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት ሦስት የተለያዩ ጥምቀቶች አሉ እነርሱም የዮሐንስ የንስሐ ጥምቀት፣ ኢየሱስ ከአጥማቂው ዮሐንስ የተቀበለው ጥምቀትና እኛ እንደ ስርአት የምንወስደው የውሃ ጥምቀታችን ናቸው::

እኛ የምንወስደው ጥምቀት በኢየሱስ ጥምቀት ያለንን እምነት የምንመሰክርበት ነው ይህ ማለት እኛ የምንጠመቀው ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለመውሰድ እንደተጠመቀና እነርሱንም ደግሞ ለማስተሰረይ በመስቀል ላይ እንደሞተ እንደምናምን እምነታችንን ለመመስከር ነው *«አሁንስ ፍቀድልኝ ሁላችን እንዲህ ፅድቅን መፈፀም ይገባናልና»* የሚለውን ማቴዎስ 3:15ን መረዳት ትችላለህ እዚህ ላይ *«እንዲህ»* ማለት ኢየሱስ ራሱ የሰው ዘር ሁሉ ወኪል በሆነው በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ተሸክሞዋል ማለት ነው::

ይህ እኛን ከማናመልጥበት የሐጢያት ወጥመድ ለማዳን እግዚአብሄር ያቀደው ጥልቅ ዕቅድ ነው ጌታ እግዚአብሄር *«የሁላችንንም በደል በእርሱ ላይ አኖረ» (ኢሳይያስ 53:6)*

የእርሱንም ጽድቅ ሰጠን እዚህ ላይ *«ጽድቅ»* ማለት በግሪክ *«ዲካዮሱኔ»* ማለት ሲሆን የሚያመላክተውም «ትክክለኛነትንና ፍትህን» ነው ይህም ኢየሱስ በእጆች መጫን መልክ በመጠመቅ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ እጅግ ትክክለኛ ጻድቅ በሆነ መንገድ እንደተሸከመ ይነግረናል፡፡

የዳንነው በኢየሱስ ጥምቀት በመስቀል ላይ ሞቱና ትንሳኤው ላይ ባለን ጠንካራ እምነት ነው ሐጢያቶችን ሁሉ ከልባችን ውስጥ ቆርጦ የጣለው የጥምቀቱ መንፈሳዊ ግርዘት ሐይል (ሮሜ 2፡29) በልባችን ውስጥ ያሉትን ሐጢያቶች አንጽቶዋል ስለዚህ በበአለ ሐምሳ ቀን ሐዋርያው ጴጥሮስ ለሕዝቡ እንዲህ አላቸው *«ንሰሐ ግቡ እያንዳንዳችሁ ኃጢያታችሁ ይሰረይ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ፡፡» (የሐዋርያት ሥራ 2፡38)*

ሐጢያተኞች በሙሉ በኢየሱስ ስም በማመን በልቦቻቸው ውስጥ የሐጢያቶችን ይቅርታ መቀበል ይገባቸዋል የስሙ ትርጉም ምንድነው? *«እርሱ ህዝቡንም ከኃጢያታቸው ያድናቸዋል፣ ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ» (ማቴዎስ 1፡21)* ኢየሱስ የሚለው ስም ሕዝቡን ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ የሚያድን «አ

ዳኝ» ማለት ነው ከሐጢያቶቻችንን ሁሉ ያዳነን እንዴት ነበር? ኢየሱስ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ያዳነን በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ሞቱ አማካይነት ነው፡፡

የኢየሱስ ሐዋርያት ወንጌልን በሰበኩ ጊዜ የኢየሱስን ጥምቀትና መስቀል ግልጽ የሆነ መረዳት አረጋግጠው እውነተኛ ውን ወንጌል አስተማሩ ከዚያም በዚህ የሚያምኑትን አጠመቁ እኛ የምንጠመቀው በልቡናችን ጥልቅ ውስጥ በኢየሱስ ጥምቀትና ሞት እንደምናምን በይፋ ለመመስከር ነው ስንጠመቅ «ጌታ ሆይ ተመስገን አንተ በጥምቀትህ አማካይነት ሐጢያቶቼን

በሙሉ ተሸከምህ ስለ እኔም ሞትህ እኔን ለማዳንም ዳግመኛ ተነሳህ በወንጌልህ አምናለሁ» ብለን እንመሰክራለን እርሱ በአጥማቂው ዮሐንስ እንደተጠመቀ ሁሉ እኛም በኢየሱስ ጥምቀትና በመሰቀል ላይ ሞቱ ላለን እምነት ምልክት ይሆን ዘንድ በአገልጋዮች በውሃው ውስጥ እንጠመቃለን ስለዚህ በጥንት ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩ ቅዱሳን በወንጌል ላይ ያላቸውን እምነት ከመሰከሩና የሐጢያቶቻቸውን ይቅርታ ማለትም ቤዛነት ከተቀበሉ በኋላ ለእምነታቸው ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ ተጠምቀዋል፡፡

የጥምቀት ስርአት ለመዳን አስፈላጊ የሆነ ሁኔታ አይደለም እምነታችንን ግልጽ ማድረጉ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም የውሃ ጥምቀቶቻችን ከደህነታችን ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም መዳን የምንችለው በውሃውና በደሙ ወንጌል በማመን ብቻ ነው መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ ጥምቀት ባመንን ጊዜ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ እንደተጠመቅን (ሮሜ 6:3፤ገላትያ 3:27) ይናገራል፡፡

ታዲያ እንዴት *«በእርሱ ልንጠመቅ»* ቻልን? ይህ የሚቻለው በእርሱ ጥምቀት ስናምን ብቻ ነው ምክንያቱም ስጋ፣ አሮጌው ማንነታችን ከኢየሱስ ጋር ሊተባበርና ከእርሱ ጋር ሊሰቀል የሚችለው በእርሱ ጥምቀት ላይ ባለን እምነት ብቻ ነው ስለዚህ ኢየሱስ በጥምቀቱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ስለተሸከመ ሞቱ የበደላችን ፍርድ ነበር በመሆኑም እኛም ደግሞ ከእርሱ ጋር በመስቀል ላይ ሞተናል በሌላ አነጋገር እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ሐጢያቶችን የሚሰራው ስጋችን ለሐጢያት ሞቶዋል እኛም በጥምቀቱ አማካይነት ከኢየሱስ ጋር በመተባበራችን ከ በደሎቻችን ሁሉ ድነናል፡፡

በእርሱ ጥምቀትና ሞት ከኢየሱስ ጋር የተባበሩ ሰዎች ከትንሳኤውም ጋር ደግሞ መተባበር ይችላሉ የእርሱ ትንሳኤ

እኛ ከሐጢያት ሞት የተነሳንበት ትንሳኤ ብቻ ሳይሆን በእርሱ ፊት ቅዱሳን፣ ንጹህና ሐጢያት የሌለብን የእግዚአብሄር ልጆች ሆነን ዳግም እንድንወለድም ፈቅዶልናል፡፡

የእርሱን ጥምቀት ተጠራጥረን ሐጢያቶቻችንን ወደ እርሱ ባናስተላልፍ ኖሮ ሞቱና ትንሳኤው ከእኛ ደህንነት ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ትርጉም አልባ ይሆኑብን ነበር በእምነት ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ በእርሱ ላይ ያኖሩ ሰዎች ጻድቃን ሆነው ዳግም እንዲወለዱ ከሚፈቅድላቸው ከእርሱ የመስቀል ሞት ጋር የተባበሩ ሰዎች ናቸው ነገር ግን የእርሱን ጥምቀት ባለማመን ሐጢያቶቻቸውን በእርሱ ላይ ያላኖሩ ሰዎች ከእርሱ ሞትና ትንሳኤ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም፡፡

አንድ ባልና ሚስት በጋብቻ ስርአት አማካይነት ሕጋዊ ጥንዶች መሆናቸውን እንደምንቀበል ሁሉ የምዕመናን ጥምቀትም እንደዚሁ የታመነ ነው የቅዱሳን እምነት እንዲህ ያለውን ውስጣዊ እምነት የሚገልጡበት ውጫዊ መግለጫ ነው በእግዚአብሄር፣ በቅዱሳንና በአለም ፊት በእርሱ ጥምቀትና መስቀል ላይ ያለንን እምነት ስናውጅ እምነታችን ይበልጥ የማይናወጥ ይሆናል፡፡

ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ የተቀበለውን ጥምቀት እውነተኛ ትርጉም በተሳሳተ መንገድ ከተረዳን በኋላ በእርሱ ጥምቀትና በፋይዳው ባናምን መዳን እንደምንችል ልናምን አይገባንም ይህ በአጭሩ የዲያብሎስ ብልጣ ብልጥ ማታለያ ነው በራሳችን ጥምቀት በማመን ፋንታ በኢየሱስ ጥምቀት በትክክል በልባችን በማመን የሐጢያቶቻችንን ስርየት መቀበልና ሰማይ መግባት እንችላለን፡፡

**<u>ጥያቄ: 2</u> በየቀኑ ሐጢያትን እየሰራሁ እንዴት «ጻድቅ ነኝ» ማለት እችላለሁ?**

<u>መልስ:</u> እኛ ሰዎች እንደመሆናችን ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ እስከምንሞትበት ጊዜ ድረስ ሐጢያቶችን እንሰራለን እንደ እውነቱ ከሆነ የዚህ ምክንያቱ መሰረታዊው ተፈጥሮዋችን ነው ከመጀመሪያ ጀምሮ ሐጢያት እንሰራለን ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል *«ጻድቅ የለም አንድስ እንኳ» (ሮሜ 3:10)* ሐዋርያው ጳውሎስ በእግዚአብሄር ፊት እንዲህ ያለው ለዚህ ነው ሐዋርያው *«ኃጢያተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው::» (1ኛ ጤሞቲዎስ 1:15)*

*«አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ፅድቅ ያለ ሕግ ተገልጦኣል እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ፅድቅ ነው:: ልዩነት የለምና ሁሉ ኃጢያትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በፀጋው ይፀድቃሉ::» (ሮሜ 3:21-24)*

ይህ የእግዚአብሄር *«ጽድቅ»* ማለት አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስን በዮርዳኖስ ማጥመቁ ነው እርሱ በተጠመቀ ጊዜ ዮሐንስን እንዲህ አለው *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ፅድቅን መፈፀም ይገባናልና» (ማቴዎስ 3:15)* የሰው ዘር ሁሉ ወኪል የነበረው አጥማቂው ዮሐንስ ባጠመቀው ጊዜ የአለምን ሐጢያቶች እጅግ ተገቢና ቀና በሆነ መንገድ ተሸከመ በዚህም ዮሐንስ ኢየሱስን ባጠመቀው ማግስት እንዲህ አለ *«እነሆ! የዓምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ::» (ዮሐንስ 1:29)*

ታዲያ እዚህ ላይ *«የአለም ሐጢያት»* ማለት ምን ማለት

ነው? ይህ የሚያመላክተው በምድር ላይ የመጀመሪያዎቹ የሰው ፍጡራን ከሆኑት ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ በዚህ አለም ላይ እስከሚኖረው የመጨረሻው ሰው ድረስ ያሉትን የሰዎች ሁሉ ሐጢያቶች ነው ያለፉትም ሰዎች የአለም ክፍል ናቸው አሁን ያሉት ሰዎችም የአለም ክፍል ናቸው ወደፊ ት የሚኖሩትም ሰዎች እንደዚሁ የአለም ክፍል ናቸው አልፋና ያሜጋ የሆነው ኢየሱስ በዮርዳኖስ በጥምቀቱ አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ በመሸከም ለሁሉም ዘመን ሐጢያቶች አንድን መስዋዕት አቀረበ በመስቀል ላይም ሞተ *«በዚህም»* ተቀድሰናል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንዲህ ይላል *«በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈፅሞ በማቅረብ ተቀድሰናል» (ዕብራውያን 10፡10)* ይህ የተጻፈው ተፍጻሜትን በሚያመላክት የአሁን ጊዜ እንደሆነ ልብ በሉ እኛ በእግዚአብሄር ካመንበት ቅጽበት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ለሁልጊዜም ፈጽመን ተቀድሰናል ሐጢያት አልባም ሆነናል ጌታ ሁሉን ቻይ አምላክ ስለሆነ የአለምን ጅማሬና ፍጻሜ በወፍ በረር አይን እይታ ያያል እርሱ ከተጠመቀ 2000 አመታት ያህል ቢሆነውም ሰዎች ከአለም ጅማሬ እስከ ፍጻሜ ድረስ የሚሰሩዋቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል ስለዚህ በመስቀል ላይ ከመሞቱ በፊት *«ተፈጸመ!»* አለ (ዮሐንስ 19፡30) እርሱ ከ2000 አመታት በፊት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶ እነዚያን ሐጢያቶች ለማንጻት በመስቀል ላይ ሞተ፡፡

ከዳንን በኂላም እንኳን ቢሆን ሐጢያትን እንሰራለን ምክንያቱም ስጋችን ደካማ ነውና ነገር ግን ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካነት ሐጢያቶችን በሙሉ በሰውነቱ ላይ በመሸከም ካለፉት አሁን ካሉትና ከወደፊት ሐጢያቶች በሙሉ ታድጎን ለእነዚህ ሐጢያቶች በመስቀል ላይ ተኮነነ ይህ ምሉዕና ጻድቅ የሆነ

የእግዚአብሄር ማዳን ነው፡፡

ኢየሱስ ወደፊት የምንሰራቸውን ሐጢያቶች በራሱ ላይ ባይወስድ ኖሮ አንድም ሰው በየቀኑ ከሚሰራቸው ሐጢያት አይድንም ነበር *«የኃጢያት ደመወዝ ሞት» (ሮሜ 6:23) ያዕቆብና ኤሳው ገናም በእናታቸው ማህጸን ውስጥ ሳሉ ምንም መልካም ወይም ክፉ ነገር ሳይሰሩ እግዚአብሄር ሁለት ሕዝብ አድርጎ ለያቸው ያዕቆብን ወደደው ኤሳውንም ጠላው እንዲህም አለ «ታላቁ ታናሽየውን ያገለግል» (ዘፍጥረት 25:23)* ይህ ምንባብ የእግዚአብሄር ደህንነት ከእኛ ምግባሮች ጋር ምንም እንደማይገናኝ ነገር ግን በእርሱ ጥምቀትና ስቅለት በኩል ፍጹም በሆነው የእግዚአብሄር ደህንነት ለሚያምኑ ሰዎች እንደተሰጠ ይጠቁማል፡፡

እኛ ሰዎች ከተወለድንበት ቅጽበት ጀምሮ እስከ ምንሞትበት ቅጽበት ድረስ ሐጢያተኛ ፍጡራን ሆነን ለሲዖል የታጨን ነን እግዚአብሄር ግን ሐጢያቶቻችንን በአንድ እይታ አስቀድሞ አይቶ ስለወደደን በኢየሱስ ጥምቀትና መስቀል ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ አስወገደ የምንኖረው በተባረከ ዘመን ነው ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ አለ *«ለኢየሩሳሌም ልብ ተናገሩ የተቀጠረችበት ወራት እንደተፈጸመ፣ ኃጢያቷም እንደተሰረየ፣ ከእግዚአብሔርም እጅ ስለ ኃጢያቷ ሁሉ ሁለት እጥፍ እንደተቀበለች ወደ እርሷ ጮኹ፡፡» (ኢሳይያስ 40:2)* ስለዚህ የሐጢያት ባርያ የነበርንበት ዘመን በኢየሱስ ጥምቀትና መስቀል ወንጌል አማካይነት አብቅቷል በወንጌል የሚያምን ማንኛውም ሰው ከሐጢያቶቹ መዳን ይችላል *«ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ፡፡ በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ በልቦናቸውም እፅፈዋለሁ ብሎ ከተናገረ በኋላ ኃጢያታቸውንና ዓመፃቸውንም ደግሜ አላስብም ይላል የእነዚህን ስርየት ባለበት*

*ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢያት ማቅረብ የለም፡፡» (ዕብራውያን 10:16-18)*

እግዚአብሄር ከእንግዲህ ወዲህ በየቀኑ ለምንሰራቸው ሐጢያቶች አይፈርድብንም ምክንያቱም አስቀድሞ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ አንጽቶ በኢየሱስ አማካይነት ኮንኖዋቸዋልና፡፡

ከዚህ የተነሳ በሕይወታችን አሁንም ድረስ ሐጢያቶችን ብንሰራም እንኳን ሐጢያት የሌለብን ጻድቃን ሆነን የጌታን ምጽአት መጠበቅና ቃሉን መከተል እንችላለን፡፡

## ጥያቄ 3: የዮሐንስ የንስሐ ጥምቀት ምንድነው?

<u>መልስ:</u> አጥማቂው ዮሐንስ ከኢየሱስ 6 ወራት በፊት ቀደም ብሎ የተወለደና በብሉይ ኪዳን ውስጥም በሚልክያስ የመጨረሻው ነቢይ እንደሆነ የተተነበየለት የእግዚአብሄር ባርያ ነበር፡፡

*«ለእስራኤል ሁሉ ሥርዓትንና ፍርድን አድርጌ በኮሬብ ያዘዝሁትን የባርያዬን የሙሴን ሕግ አስቡ እነሆ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነብዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል፡፡» (ሚልኪያስ 4:6-8)*

ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሄርን ኪዳን ቃሎች ትተው ለእንግዳ አማልክቶች ይሰግዱ ነበር እውርና ነውር ያለባቸውን እንስሶች መስዋዕቶች አድርገው ያቀርቡ ነበረ የእግዚአብሄርንም መቅደስ የንግድ ስፍራ አድርገውት ነበር ኢየሱስ ክርስቶስም እንደዚሁ በሙሴ ሕግና

በነቢያት ተተንብዮለታል ሕጉ ሰዎች ምን ያህል ሐጢያተኞች እንደሆኑ በማሳየት የሐጢያትን እውቀት ሰጥቶዋቸዋል (ሮሜ 3፡20) በሕጉ መጽሐፍ ውስጥ በተጻፈው አንድ ትዕዛዝ አለመኖር ሐጢያት ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን ከሕጉ አንቀጾች አንዳቸውን የተላለፈ ሐጢያተኛ በመገናኛው ድንኳን ፊት የሐጢያት መስዋዕት ያቀርብና ሐጢያቶቹን ወደ እርሱ ለማስተላለፍ በሐጢያት መስዋዕቱ ራስ ላይ እጆቹን ይጭናል የሐጢያት ይቅርታን ለማግኘትና እንደገና ከእግዚአብሄር ጋር ለመስማማት የሐጢያት መስዋዕቱን ያርደዋል ከዚያም ካህኑ ከደሙ የተወሰነውን ይወስድና በሚቀጣለው መስዋዕት መሰውያ ቀንዶች ላይ ይቀባዋል የቀረውንም ደም ከመሰውያው በታች ያፈስሰዋል፡፡

ሆኖም የእስራኤል ሕዝብ በየቀኑ በርካታ መስዋዕቶችን ቢያቀርቡም ከሐጢያቶቻቸው መዳን አልቻሉም ስለዚህ እግዚአብሄር የዘላለም ስርአት የሆነውን የስርየት ቀን አደረገላቸው እግዚአብሄር በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን አመታዊ ሐጢያቶቻቸውን ይቅር የሚለው በዚህ ጊዜ ነበር በዚያ ቀን ሊቀ ካህኑ አሮን ሁለት ፍየሎችን ወስዶ ዕጣ ይጥልባቸዋል አንዱ ለእግዚአብሄር ሌላው ደግሞ ለሚለቀቅ ፍየል ይሆናል ከዚያም የእስራኤልን ሕዝብ አመታዊ ሐጢያቶች በሙሉ በእርሱ ላይ ለማኖር በፍየሉ ራስ ላይ እጆቹን ይጭናል አሮንም ያርደውና ደሙን ወስዶ በስርየት መክደኛው ላይና ፊት ለፊት ሰባት ጊዜ ይረጨዋል፡፡

ቅድስቱን ስፍራ ማስተሰረይ ከፈጸመ በኋላም ሌላውን እንስሳ ያቀርባል በሕያው ፍየሉ ላይ እጆቹን በመጫንም የእስራኤሎችን አመታዊ ሐጢያቶች ይናዘዝበታል በዚህ ዘዴ አመታዊ ሐጢያቶቻቸው በሙሉ ወደ እርሱ ይተላለፉሉ

በተመረጠው ሰው እጅም ወደ ምድረ በዳ ይሰደዳል እስራኤሎችም በዚህ መንገድ ከአመታዊ ሐጢያቶቻቸው ይድኑ ነበር::

ሆኖም በብሉይ ኪዳን ሕግ መሰረት የቀረበው መስዋዕት በየአመቱ ያለ ማቋረጥ መስዋዕቶችን ያቀረቡትን ፍጹማን ሊያደርጋቸው አልቻለም ይህ ሊመጡ ያሉ (የመሲሁ የጽድቅ ምግባሮች) በጎ ነገሮች ጥላ ብቻ ነበር (ዕብራውያን 10:1) የእስራኤል ሕዝብ አዳኙን ኢየሱስ ክርስቶስን አልጠበቁትም በፋንታው በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉትን የነቢያቶች ቃሎች ትተው የሐጢያተኛውን አለም እንግዳ አማልክቶች አመለኩ::

ስለዚህ እግዚአብሄር የእስራኤሎችን ልብ ለማደስ ወደ እርሱ ለመመለስና ልባቸውም ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲቀበል ለማዘጋጀት አጥማቂውን ዮሐንስን እንደሚልክ ተነበየ አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስን ከማጥመቁ በፊት በይሁዳ ምድረ በዳ ሕዝቡን በንስሐ ጥምቀት አጠመቀ::

እነርሱን በውሃ ያጠምቅ የነበረበት አላማው ኢየሱስን እንዲጠብቁና እንዲያምኑበት ለመምራት ነበር እርሱ አዳኙ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ በእጆች መጫን መንገድ በእርሱ እንደሚጠመቅና እነርሱን ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ለማዳን እንደሚሰቀል አስተማረ እርሱ ኢየሱስ እንደሚመጣና ያለፉትን ጎዶሎ መስዋዕቶች ወስዶ በስጋው የዘላለም መስዋዕት እንደሚያቀርብ ተናግሮዋል የእስራኤል ሕዝብ ነውር የሌለበትን የሐጢያት መስዋዕት በማቅረብ እጆቻቸውን በእርሱ ላይ በመጫንና በብሉይ ኪዳን ውስጥ ባለው የመስዋዕት ስርአት መሰረት በማረድ እንደዳኑ ሁሉ እርሱም በጥምቀት አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶዋል::

ብዙ እስራኤላውያን ሐጢያቶቻቸውን ተናዘውና ንስሐ ገብተው በእርሱ ተጠምቀዋል «ንስሐ» ማለት «አእምሮን ወደ

እግዚአብሄር መመለስ» ማለት ነው እነርሱ የብሉይ ኪዳንን ሕግ በማስታወስ ወደ ዮሐንስ መጥተው እስከሚሞቱ ድረስ ሐጢያቶችን ከመስራት በቀር ምንም ማድረግ ያልቻሉ ተስፋ ቢስ ሐጢያተኞች እንደነበሩ ተናዘዙ በሕጉ መሰረት በመልካም ምግባሮቻቸው መንግስተ ሰማይ መግባት እንደማይችሉም ተናዘዘው ሐጢያቶቻቸውን ለአንዴና ለመጨረሻ በመደምሰስ የመንግስተ ሰማይን በር ወለል አድርጎ ወደሚከፍትላቸው ኢየሱስ ክርስቶስ አእምሮዋቸውን መለሱ::

አጥማቂው ዮሐንስ ለእስራኤል ሕዝብ የሰጠው ጥምቀት የሚከተለው ነበር በሕይወታቸው ምን ያህል ሐጢያት እንደሰሩ እንዲናዘዙ ንስሐ እንዲገቡና ልክ እነርሱን እንዳጠመቀውም የሰው ዘር ወኪልና ሊቀ ካህን በሆነው በእርሱ የተጠመቀውንና ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ሊያድናቸውም የተሰቀለውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲመለከቱ ፈቀደላቸው እውነተኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንስሐ ይህ ነው::

ስለዚህ ዮሐንስ ሕዝቡን እንዲህ አላቸው *«እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል::» (ማቴዎስ 3:11)*

አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ እንደሚወስድና (ዮሐንስ 1:29) ለእነርሱም በይፋ እንደሚሞት በመመስከር የሕዝቦቹን አእምሮ ወደ ኢየሱስ መለሰ በዚህም ኢየሱስ ራሱ ዮሐንስ የጽድቅን መንገድ ሊያሳየን እንደመጣ መሰከረ:: (ማቴዎስ 21:32)

**<u>ጥያቄ 4</u>: በወንጌል ውስጥ የኢየሱስን ጥምቀት የደህንነት ግዴታ አድርጎ መረዳት በመስቀል ላይ የሆነውን የእርሱን ሞት ከንቱ የሚያደርገው አይመስልህምን?**

<u>መልስ:</u> የኢየሱስ ጥምቀትና የመስቀል ላይ ሞቱ በእኩል ደረጃ ለደህንነታችን አስፈላጊ ናቸው አንዱ ከሌላው ይበልጥ አስፈላጊ ነው ማለት አንችልም ነገር ግን ችግሩ ዛሬ ብዙዎቹ ክርስቲያኖች የሚያውቁት ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያፈሰሰውን ደሙን ብቻ መሆኑ ነው እነርሱ ይቅርታን ያገኙት እርሱ በመስቀል ላይ ስለሞተ እንደሆነ ያምናሉ ነገር ግን ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች የወሰደው በመስቀል ላይ ብቻ አይደለም እርሱ በአጥማቂው ዮሐንስ ስለተጠመቀና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በጀርባው ስለተሸከመ የመስቀል ላይ ሞቱ በተግባር የሐጢያቶቻችን ሁሉ ፍርድ ነው::

ያለ ኢየሱስ ጥምቀት በመስቀሉ ብቻ ማመን እጆችን በላዩ ላይ ሳይጭኑ ለጌታ መስዋዕትን እንደ ማቅረብ ነው እንዲህ አይነት መስዋዕቶችን ያቀረቡ ሰዎች ከሐጢያቶቻቸው መዳን አይችሉም ምክንያቱም መስዋዕቱ እግዚአብሄር አምላክ ሊቀበለው የማይችለው ሕገወጥ መስዋዕት ነው እግዚአብሄር ከመገናኛው ድንኳን ሆኖ ሙሴን ጠርቶ እንዲህ በማለት ተናገረው *«መባውም የሚቃጠል መስዋዕት ከላሞች መንጋ ቢሆን ነውር የሌለበትን ተባዕቱን ያቀርባል በእግዚአብሔር ፊት እንዲሰምር በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ፊት ያቀርበዋል እጁንም በሚቃጠለው መስዋዕት ራስ ላይ ይጭናል ያስተሰርይለትም ዘንድ የሰመረ ይሆንለታል::» (ዘሌዋውያን 1:3-4)*

ጌታ ጻድቅና ሕጋዊ ነው ሐጢያቶቻችንን ለማስወገድም ተገቢና ቀና የሆነ የመስዋዕት ስርአትን ደንግጎዋል ሕጋዊ መስዋዕት ስናቀርብ መስዋዕቱ ለእኛ ስርየትን ያመጣልን ዘንድ

በጌታ ተቀባይነት ያገኛል ያለ እጆች መጫን ምንም መስዋዕት በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት የለውም ልክ እንደዚሁ በእርሱ ላይ ካለን እምነት የኢየሱስን ጥምቀት ብንገድፍ በዚያ አይነቱ እምነት የሐጢያቶቻችንን ስርየት መቀበል አንችልም፡፡

የዘመኑ ክርስቲያኖች ከሚያምኑባቸው እጅግ የተለመዱ ውሸቶች አንዱ ጌታ ፍቅር ስለሆነ ኢየሱስን አዳኛቸው አድርገው በመመስከር ብቻ መዳን የሚችሉ መሆናቸው ነው በእርግጥም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል *«የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» (የሐዋርያት ስራ 2:21፤ሮሜ 10:13)* ደግሞም እንዲህ ይነግረናል *«በሰማያት ያለውን የአባቴን ፍቃድ የሚፈፅም እንጂ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፡፡» (ማቴዎስ 7:21)*

ኢየሱስ አዳኛችን እንደሆነ ለመመስከር እግዚአብሄር የደነገገውን የደህንነት ሕግ ማወቅ ይገባናል በኢየሱስ በማመን ብቻ መዳን የምንችል ብንሆን ኖሮ ቅዱሳት መጻህፍት ስለ ብሉይ ኪዳን የመስዋዕት ስርአትና በማቴዎስ 7:21 ላይም አመጻን ስለሚያደርጉ ሰዎች የሚጽፉበት ምንም ምክንያት ባልኖራቸውም ነበር፡፡

ነገር ግን አስገራሚና ፍጹም የሆነው የጌታ የደህንነት መንገድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ተመዝግቦዋል በእርግጥም አንድ ሐጢያተኛ የሐጢያትና የደህንነት መስዋዕቶችን ሲያቀርብ ሐጢያቶቹን በራሱ ላይ ለማስተላለፍ እጆቹን በመስዋዕቱ ራስ ላይ መጫን ማረድና ደሙን መርጨት እንደነበረበት ከዘሌዋውያን ምዕራፍ 3 እና 4 በግልጽ ማየት እንችላለን ነበረበት ያለ እጆች መጫን መስዋዕትን ማቅረብ ወይም ነውር ያለበትን መስዋዕት ማቅረብ ስርየትን የማያስገኝ በጣም ሕገ ወጥ ነው፡፡

የብሉይና የአዲስ ኪዳናት ቃሎች እርስ በርሳቸው

የሚጣጣሙ አምሳያዎች አሉዋቸው (ኢሳይያስ 34:16) ኢየሱስ በዮርዳኖስ የተቀበለው ጥምቀት በብሉይ ኪዳን ሐጢያተኛ ለሐጢያት በሚቀርበው መስዋዕት ራስ ላይ ከሚጭናቸው እጆቹ ጋር የሚመሳሰል ነው ኢየሱስ በዮርዳኖስ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ እንዲህ አለ *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ፅድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና።» (ማቴዎስ 3:15)*

እዚህ ላይ *«ጽድቅን ሁሉ»* ማለት «ፍትህና ትክክለኛነት» ማለት ነው ይህ ማለት ኢየሱስ በዚያ ዘዴ ለሰው ዘር የሐጢያት መስዋዕት መሆኑ ተገቢ ነው ማለት ነው እግዚአብሄር በብሉይ ኪዳን በመሰረተውና በእጆች መጫንና ደም በተዋቀረው የመስዋዕት ስርአት መሰረት የአለምን ሐጢያቶች እጅግ ትክክለኛ በሆነ መንገድ በእጆች መጫን መልክ በአጥማቂው ዮሐንስ መጠመቁ ለእርሱ ተገቢ ነበር።

በመስቀሉ ብቻ ማመን ማለት የእርሱ ሞት ከሐጢያቶቻችን ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ማለት ነው ምክንያቱም ሐጢያቶቻችን ያለ ኢየሱስ ጥምቀት ፈጽመው ወደ እርሱ መተላለፍ አይችሉም ነበርና የዚህ ውጤቱም የእርሱን ደም እንደ ርኩስ ነገርና ማንጻት እንደማይችል መቁጠር ነው። (ዕብራውያን 10:29)

ስለዚህ የእርሱ ደም በምዕመናን ልብ ውስጥ ያሉትን ሐጢያቶች በትክክል ለማንጻት ብቃት የሚኖረው አጥማቂው ዮሐንስ በእጆች መጫን አማካይነት እርሱን ባጠመቀው ጊዜ ሐጢያቶቻቸው በሙሉ በእርሱ ላይ እንደተጫኑ ሲያምኑ ብቻ ነው ስለዚህ ሐዋርያው ዮሐንስ ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነና በውሃውና በመንፈሱ የሚያምን ሰው አለምን እንደሚያሸንፍ መስክሮዋል ኢየሱስ የመጣው በውሃና በደም እንጂ በውሃ ወይም በደም ብቻ አይደለም። (1ኛ ዮሐንስ 5:4-6)

ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ እርሱን

የሚመለከቱትን ነገሮች ሁሉ ለደቀ መዛሙርቱ አብራርቷል እርሱ ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያለው የሐጢያት መስዋዕት ራሱ እንደነበር አሳየ ዳዊት ስለ እርሱ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ እንዲህ ብሎዋል *«እነሆ መጣሁ ስለ እኔ በመፅሐፍ ራስ ተፅፎኣል አምላኬ ሆይ ፍቃድህን ለማድረግ ወደድሁ።» (መዝሙር 40:7፤ዕብራውያን 10:7)*

ከዚህ የተነሳ የእርሱ ጥምቀት መስቀሉን ከንቱ አላደረገውም ነገር ግን የመስቀሉን ትርጉም የሚያጠናቅቅና የሚፈጽም የጌታ ወንጌል አስፈላጊ ክፍል ነው ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትና ክቡር ደም እስከሌለ ድረስ ቤዛነት ልናገኝ እንደማንችል ያስተምረናል መዳን ስትል በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ በማመን የሐጢያቶችን ስርየት ማግኘትና የመንፈስ ቅዱስን ሥጦታ መቀበል ማለትህ ነው። (1ኛ ዮሐንስ 5:8፤የሐዋርያት ሥራ 2:38)

**<u>ጥያቄ 5:</u> የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ማብራሪያ ልታቀርብልኝ ትችላለህን?**

**<u>መልስ:</u>** መርፌ ውጭ አንድ ቦታ ላይ ቢወድቅብን ምናልባትም በጠፋበት አካባቢ እንፈልገው ይሆናል ነገር ግን ውስጥ ብሩህ ስለሆነ ብለን ቤት ውስጥ መፈለጋችን ፈጽሞ የማይመስል ነገር ነው በዘመኑ ቤተክርስቲያኖች ውስጥም እንዲህ ያሉ ግራ የሚያጋቡ አንዳንድ ሰዎች አገኛለሁ ስለ ምዕመናን የውሃ ጥምቀት ፍጻሜ በሌላቸው መከራከሪያዎች ውስጥ በቀላሉ ተሳትፈው እያሉ «ኢየሱስ ለምን በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ?» የሚለውን ይህንን አስፈላጊ ጥያቄ ፈጽሞ አይጠይቁም እንዲህ ካለው ዝንባሌ የተነሳ በዛሬው የክርስቲያን

ማህበረሰብ ውስጥ ብዙ የቤተክርስቲያን ድርጅቶችና አንጃዎች አሉ፡፡

ማብቂያ የሌላቸውን እነዚህን ክርክሮች ወደ ፍጻሜ ለማምጣት ራሳችንን ከግርግሩ መንደር ማውጣትና መርፌያችንን ወደጣልንበት ስፍራ መመለስ ይገባናል እውነትን ከልባችን የምንሻ ከሆንን ራሳችንን ከአካባቢው ማራቅ አለብን ምክንያቱም ይህንን በሐይማኖት መንደር ውስጥ ልናገኘው አንችልምና ሐዋርያት በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ላይ ብዙ ትኩረት ያደረጉት ለምንድነው? እነርሱ ከኢየሱስ የተቀበሉት የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ምስጢራዊ እውነት በመላው አለም ተሰብኮ ነበር፡፡

ኢየሱስ እንዲህ አለ *«እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም» (ዮሐንስ 3:5)* መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ከሐጢያቶቻችንን ሁሉ ሊያድነን በውሃና በደም እንደመጣ ይነግረናል (1ኛ ዮሐንስ 5:6) የደሙ ትርጉም የመስቀል ላይ ሞቱ ነው ታዲያ «ውሃ» ስትል ምን ማለትህ ነው? አጥማቂው ዮሐንስ ለምን ኢየሱስን አጠመቀው? ከጥምቀቱ በፊትስ ለምን *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ፅድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና» (ማቴዎስ 3:15) )* ብሎ አወጀ?

የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በተለይም የኢየሱስን ጥምቀት እንደተረዳህና እንደምታምን ከልቤ ተስፋ አደርጋለሁ እርሱ ለደቀ መዛሙርቱ ስለሰጣቸው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል አንዳንድ አጫጭር ማብራሪያዎች ይኸውልህ ሐዋርያት ወንጌልን በሰበኩ ጊዜ በኢየሱስ ጥምቀት ላይ እጅግ ታላላቅ ትኩረቶችን አድርገዋል ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ አለ *«እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢያታችን ሞተ፣*

*ተቀበረም፣ መጽሐፍም እንደሚል በሶስተኛው ቀን ተነሳ፡፡» (1ኛ ቆሮንቶስ 15:3-4)*

*«መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢያታችን ሞተ»* ምን ማለት ነው? ይህ ማለት የእርሱ ሞት በብሉይ ኪዳን እግዚአብሄር በሰጠው ዘዴ መሰረት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ አስተሰርዮዋል ማለት ነው ዕብራውያን 10:1 እንዲህ ይላል *«ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና»* በዘሌዋውያን 1:3-5 ላይ ያለውን አይነተኛ መስዋዕት እንመልከት ሐጢያተኛው የሐጢያቶቹን ስርየት ለማግኘት የሚቃጠለውን መስዋዕት ሦስት ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይገባዋል፡፡

1) ነውር የሌለበት መስዋዕት ማቅረብ ነበረበት፡፡ (ዘሌዋውያን 1:3)

2) እጆቹን በመስዋዕቱ ራስ ላይ መጫን ነበረበት (ዘሌዋውያን 1:4) እዚህ ላይ የእግዚአብሄርን ሕግ ግልጽ ማድረግ ይገባናል በመስዋዕቱ ራስ ላይ እጆችን መጫን ሐጢያቶቹን ወደ እርሱ ላይ ለማስተላለፍ የእግዚአብሄር ሕግ ነበር፡፡

3) ሐጢያቱን ለማስተሰረይ መስዋዕቱን ማረድ ነበረበት፡፡ (ዘሌዋውያን 1:5)

አሮን በስርየት ቀን ሁለቱንም እጆቹን ሕያው በሆነው ፍየል ራስ ላይ ጭኖ ሐጢያቶቻቸውን ሁሉ በሚመለከት የእስራኤልን ልጆች በደሎችና መተላለፎች ሁሉ በእርሱ ላይ ይናዘዛል በፍየሉም ራስ ላይ ያኖራቸዋል (ዘሌዋውያን 16:21) በዚያን ዘመን አሮን የእስራኤል ወኪል ነበር እጆቹን በፍየሉ ራስ ላይ የሚጭነው እርሱ ብቻ ነው የእስራኤሎች (ወደ 2-3 ሚሊዮን አካባቢ) አመታዊ ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ ይተላለፉ ነበር የብሉይ ኪዳን መስዋዕት ሊመጡ ያሉ በጎ

ነገሮች ጥላ ነበር ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት ሊቀድሰን በእግዚአብሄር ፈቃድ ራሱን አቀረበ::

በመጀመሪያ ኢየሱስ ነውር የሌለበት የእግዚአብሄር በግ ለመሆን የሰው ስጋ ለብሶ መጣ እርሱ የእግዚአብሄር አንድያ ልጅና *«የባሕርዩ ምሳሌ» (ዕብራውያን 1:3)* ነው ስለዚህ ለሰው ዘር ሁሉ የሚሆን የሐጢያት መስዋዕት ለመሆን ብቁ ሆነ::

ሁለተኛ አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስን በዮርዳኖስ አጠመቀው ጥምቀት የተሰጠው «እጆችን በመጫን» መልክ ነው አጥማቂው ዮሐንስም የአሮን ዘርና የሰው ዘር ሁሉ ወኪል ነው ዮሐንስ በኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ላይ እጆቹን ሲጭን እግዚአብሄር በደነገገው ሕግ መሰረት የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ ተላለፉ ኢየሱስ ዮሐንስን *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና»* በማለት አጠመቀው በመጨረሻ ሐጢያቶቻችን በሙሉ ወደ እርሱ ተላለፉ በማግስቱ ዮሐንስ እንዲህ ብሎ ጮኸ *«እነሆ! የአለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ::» (ዮሐንስ 1:29)*

ሶስተኛ ኢየሱስ *«ተፈጸመ!» (ዮሐንስ 19:30)* በማለት ለሐጢያቶቻችን ሁሉ ስርየት በመስቀል ላይ ሞተ በእግዚአብሄር ፊትም እኛን ጻድቃን ለማድረግ ዳግመኛ ከሙታን ተነሳ የሐጢያት መስዋዕት የሚቀርበው ለሐጢያቶች ይቅርታ እንደሆነ ይታወስ አንድ ሐጢያተኛ መስዋዕቱን ከማረዱ በፊት እጆቹን በራሱ ላይ መጫን ነበረበት በሌላ አነጋገር አንዲት ደረጃ ቢረሳ እጆቹን በመስዋዕቱ ራስ ላይ ማድረጉን ቢገድፍ አመጽን በማድረጉ ምክንያት አይድንም ነበር አንድ ክርስቲያን የኢየሱስ ጥምቀት ምን ማለት እንደሆነ የማያውቅ ከሆነ ይህ ሰው በልቡ ውስጥ ሐጢያቶች ያሉበት መሆን ስላለበት በራሱ እምነት መዳን አይችልም::

አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የሚያውቁት የእርሱን ገሚስ

የጽድቅ ምግባር ብቻ ነው ሐዋርያው ዮሐንስ በመጀመሪያው መልዕክቱ ውስጥ ወንጌልን ግልጽ አድርጎታል *«በውኃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በውኃውና በደሙም እንጂ በውኃ ብቻ አይደለም መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረውም መንፈስ ነው» (1ኛ ዮሐንስ 5:6)* የእርሱ ጥምቀት ለደህንነታችን ያለውን የጽድቅ ምግባሩን ለማጠናቀቅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የሚደግፉ ብዙ ምንባቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ወደ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል መመለስ ይገባቸዋል::

**<u>ጥያቄ 6</u>: «ሐዋርያት በኢየሱስ ጥምቀት ላይ ትልቅ ትኩረት ለማድረጋቸው» መረጃን የሚሰጡት ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው?**

**<u>መልስ:</u>** በአብዛኛው የእኛን ጥምቀት ትርጉም ከኢየሱስ ጥምቀት ትርጉም መለየት ይገባናል የውሃ ጥምቀትን በመቀበል ብቻ ዳግም ልንወለድ አንችልም ዳግም መወለድ የምንችለው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው እንደ ጥምቀት ወይም ግርዘት ያሉ ስርአቶች ለእግዚአብሔር ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች አይደሉም መጽሐፍ ቅዱስ የምዕመናኖችን የውሃ ጥምቀት ለደህንነታቸው ግዴታ አድርጎ አይገለጥውም በፋንታው ኢየሱስ ከአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበለው ጥምቀት ላይ ትልቅ ትኩረት ያደርጋል::

የኢየሱስ ጥምቀት ለደህንነታችን ወሳኝና አስፈላጊ እንደሆነ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ይደግፋሉ በመጀመሪያ የእርሱ ጥምቀት በአራቱም ወንጌሎች በእያንዳንዳቸው ውስጥ ምሉዕ ለሆነው የጽድቅ ስራው እንደ መግቢያ ሆኖ ታውጆዋል ለምሳሌ

የማርቆስ ወንጌል የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የሚጀምረው በቀጥታ ከኢየሱስ ጥምቀት ነው ዮሐንስም ወንጌልን የጻፈው ኢየሱስ ከተጠመቀበት ቀን ጀምሮ *«በነገውም» (1:29)* እና *«በሦስተኛውም ቀን» (2:1)* የሚሉ ቃላቶችን በመጠቀም ነው። አጥማቂው ዮሐንስ *«እነሆ! የአለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (ዮሐንስ 1:29)* በማለት ኢየሱስ በተጠመቀ ማግስት የእግዚአብሄርን ቃል ተናገረ ከዚያም «ተፈጸመ» (ዮሐንስ 19:30) በማለት ለሐጢያቶቻችን ስርየት በመስቀል ላይ ሞተ በሦስተኛውም ቀን ዳግመኛ ከሙታን ተነሳ።

ሐዋርያው ጳውሎስም እንዲህ ብሎዋል *«መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢያታችን ሞተ» (1ኛ ቆሮንቶስ 15:3)* እዚህ ላይ መጽሐፍ የሚያመላክተው ብሉይ ኪዳንን ነው በብሉይ ኪዳን አንድ ሐጢያተኛ ይቅርታን ለማግኘት መስዋዕትን ማቅረብ የሚችለው እንዴት ነበር? መስዋዕቱን ከማረዱ በፊት በሐጢያት መስዋዕቱ ራስ ላይ እጆቹን ይጭናል «በሐጢያት መስዋዕቱ ራስ ላይ እጆችን የመጫን» ሒደት ባያደርግ ሕገ ወጥ የሆነ መስዋዕት በማቅረቡ ይቅርታን ማግኘ ት አይችልም ነበር።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሎዋል *«ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?» (ሮሜ 6:3)* ታዲያ እኛ በኢየሱስ መጠመቃችን የሚቻለው እንዴት ነው? በክርስቶስ ኢየሱስ መጠመቅ ማለት በእኛ የውሃ ጥምቀት ሳይሆን በዮርዳኖስ በሆነው በእርሱ ጥምቀት ማመን ነው አጥማቂው ዮሐንስ እጆቹን በኢየሱስ ራስ ላይ በመጫን ሐጢያቶቻችንን ሁሉ ወደ እርሱ ያስተላለፈ የመሆኑን እውነታ ስናምን በእርሱ ውስጥ እንጠመቃለን።

*«ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ*

*ክርስቶስን ለብሳችኋልና» (ገላትያ 3:27)* በአጥማቂው ዮሐንስ አማካነት በእምነት ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ ወደ ኢየሱስ ያስተላለፉ ሰዎች ሐጢያት አልባ የእግዚአብሄር ልጆች ይሆናሉ::

*«የሥጋንም ሰውነት በመግፈፍ በክርስቶስ መገረዝ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆነቻሁ ደግሞ ተገረዛችሁ» (ቆላስያስ 2:11)* የስጋን የሐጢያቶች ሰውነት በማስወገድ ከሐጢያት የመዳን መንገድ በእጅ ባልተደረገ መንፈሳዊ ግርዘት መገረዝ ነው *(በሮሜ 2:29 ላይም «መገረዝም የልብ መገረዝ ነው» ተብሏል)* ያም ማለት ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረው በልባችን ውስጥ ያሉትን ሐጢያቶች መቁረጥ በሆነው በኢየሱስ ጥምቀት ማመን ነው::

*«ይህም ውሃ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል የሰውነትን ዕድፍ ማስወገድ አይደለም ለእግዚአብሄር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ነው» (1ኛ ጴጥሮስ 3:21)* ጥምቀት የሚያድነን ምሳሌ ነው ቀድሞውኑም እንደምናውቀው በኖህ ዘመን ሰዎች በውሃ ባለማመናቸው ጠፍተዋል ዛሬም ቢሆን በኢየሱስ ቢያምኑም የሚጠፉ አመጸኛ ሰዎች አሉ ምክንያቱም ውሃ በሆነው የኢየሱስ ጥምቀት አያምኑምና::

ሐዋርያው ዮሐንስ በመጀመሪያው ወንጌሉ ላይ እንዲህ ብሎ በመጻፍ ስለ ወንጌል ሁሉን ነገር ተናግሮዋል *«በውኃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በውኃውና በደሙም እንጂ በውኃ ብቻ አይደለም መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረውም መንፈስ ነው» (1ኛ ዮሐንስ 5:6)* ኢየሱስ እኛን ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ለማዳን በጥምቀቱና በመስቀሉ ወደ እኛ መጣ ዮሐንስ እንዲህም ደግሞ ብሎዋል *«በምድር የሚመሰክሩት ሶስት ናቸው እነርሱም መንፈሱ፣ ውኃውና*

*ደሙም ሶስት ናቸው:: እነዚህም በአንድ ይስማማሉ» (1ኛ ዮሐንስ 5:8)* ይህም የኢየሱስ ጥምቀት መስቀሉና መንፈሱ ሁሉ በአንድ ላይ አንድ ፍጹም የሆነ ደህንነትን እንደሚያዋቅሩ ይነግናል::

ኢየሱስ ኒቆዲሞስን እንዲህ አለው *«እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም» (ዮሐንስ 3:5)* እኛ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም ተወልደናል ለመዳንና መንፈስ ቅዱስን እንደ ስጦታ ለመቀበል የሚያስፈልጋችሁ ነገር ቢኖር በእርሱ የውሃ ጥምቀትና መስቀል ማመን ነው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ «ዳግም መወለድ» የሚናገረው ይህንን ነው::

ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ ብሎዋል *«ንስሐ ግቡ ኃጢያታችሁ ይሰረይ ዘንድም እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ::» (የሐዋርያት ሥራ 2:38)* የሐጢያቶችን ሁሉ ይቅርታና የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ለማግኘት ከሙሉ ልባችሁ በኢየሱስ ጥምቀት የማይናወጥ እምነት ሊኖራችሁ ይገባል ሌላ ምን ማለት እንችላለን? የእርሱ ጽድቅ ለደህንነታችን የሚሆን ወሳኝ ምግባር እንደሆነ ብዙ ምንባቦች የሚደግፉት መሆኑን አትካድ ክርስትና ወደ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል መመለስ አለበት::

*«ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ መሠረትን ደግመን አንመሥርት እርሱም ከሞተ ሥራ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት ስለ ጥምቀቶችና እጆችንም ስለ መጫን ስለ ሙታንም ትንሳኤ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው» (ዕብራውያን 6:1-2)* እዚህ ላይ የጥንቷን ቤተክርስቲያን እውነተኛ ወንጌል ለማግኘት ፍንጭ ማግኘት እንችላለን እነርሱ የጥምቀቶችን እጆችን የመጫን ከሙታን የመነሳትና ክርስቲያን የሆኑትም

የሚገጥማቸውን የዘላለም ፍርድ ትምህርቶች አስተምረዋል ሁላችንም ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደና በእግዚአብሄር የጽድቅ ሕግ መሰረት ለሐጢያቶቻችን ለመኮነን በመስቀል ላይ እንደሞተ በልባችን ማመን ይገባናል::

**<u>ጥያቄ 7</u>: አንተ ብዙውን ጊዜ ቸል በሚባለው የኢየሱስ ጥምቀት ላይ ትኩረትን ከማድረግህ በስተቀር ይህ እኔ ቀድሞውኑም ሳምነው የነበረ ነገር ነው ታዲያ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እንዲህ ልዩ የሚያደርገው ምንድነው?**

**<u>መልስ</u>:** «መዳን» ማለት የሐጢያቶችን ሁሉ ስርየት መቀበል ማለት ነው ዳግም መወለድም ማለት ደግሞ ነው አንድ ሐጢያተኛ በሕይወት ወንጌል በማመን ጻድቅ ሰው ሲሆን «እርሱ/እሷ በኢየሱስ ደህንነት አማካይነት ከውሃና ከመንፈስ ተወለደ/ች» እንላለን መንፈስ ቅዱስ በተዋጁትና ዳግም በተወለዱት ላይ ይወርድና የእግዚአብሄር ልጆች እንደሆኑ ይመሰክራል ስለዚህ ሁሉም ተመሳሳይ ነው የሐጢያቶችን ስርየት መቀበል፣ መንፈስ ቅዱስን መቀበል፣ መዳን፣ ዳግም መወለድ፣ የእግዚአብሄር ልጅ መሆንና ጻድቅ ሰው መሆን ሁሉም ተመሳሳይ ነገሮች ናቸው::

ኢየሱስ እንዲህ አለ *«እኔ መንገድም፣ እውነትም ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ማንም ወደ አብ አይመጣም» (ዮሐንስ 14:6)* ይህ የሚያመላክተው እኛ ወደ እግዚአብሄር መንግስት መግባት የምንችለው የእግዚአብሄር አንድያ ልጅ በሆነው በኢየሱስ ብቻ መሆኑን ነው ስለዚህ ኢየሱስ እንዴት ሐጢያቶቻችንን ሁሉ እንዳነጻና ወደ እርሱ መንግስት መግባት

የሚገባን የእርሱ ሕዝቦች አድርጎ እንደቆጠረን ማወቅ ይኖርብናል፡፡

ሆኖም አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የእርሱን ስም መጥራት ብቻ ሊያድናቸው እንደሚችል አሁንም ያስባሉ መጽሐፍ ቅዱስን ሳይገልጡ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ሊያድነን ያደረገውን ነገር ሳያውቁ በኢየሱስ ያምናሉ እግዚአብሄር መለወጥ ወይም የጥላ መዞር የሌለበት መንፈስና ቅዱስ አምላክ ነው እኛ ግን የምንኖረው ሐጢያተኛ ሕይወትን ነው ወደ ጌታ መንግስት መግባት የሚቻለው በኢየሱስ አማካይነት ብቻ ነው *«በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው የመንፈስ ሕይወት ሕግ» (ሮሜ 8፡1-2)* ባለው እምነት አማካይነት በእርሱ ማመን እንችላለን፡፡

ብዙ ሰዎች ኢየሱስ ለደህንነት ምን እንዳደረገ እንኳን አያውቁም በፋንታው «ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ!» በማለት ዕውር ሆነው በከንቱ በእርሱ ያምናሉ የዳኑ እንደሆኑም ያስባሉ ነገር ግን በልባቸው ውስጥ አሁንም ሐጢያቶች አሉባቸው በኢየሱስ ላይ እምነት ቢኖራችሁም በልባችሁ ውስጥ አሁንም ሐጢያት ካለ ታዲያ የዳናችሁት ከምንድነው? አንድ ሰው «ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን እንዴት አነጻ?» ብሎ ቢጠይቅ ብዙ ሰዎች « ምናልባትም በመስቀል ላይ ሳያነጻቸው አይቀርም» ብለው ይመልሳሉ «በልባችሁ ውስጥ ሐጢያት አለን» ለሚለው ሌላ ጥያቄም «በእርግጠኝነት! በዚህ ምድር ላይ ፈጽሞ ከሐጢያት መላቀቅ የሚችል ማን ነው?» ይላሉ፡፡

የኢየሱስ ስም *«ሕዝቡን ከሐጢያቶቻቸው የሚያድን አዳኝ»* (*ማቴዎስ 1፡21)* ማለት ነው ከሐጢያት ለመዳን በኢየሱስ እናምናለን፡፡

ነገር ግን በኢየሱስ ብናምንም አሁንም ድረስ በልቦቻችን ውስጥ ሐጢያት ካለ አሁንም ለሐጢያት ባርነት የተሸጥንና በዚያው መሰረትም የምንኮነን ሐጢያተኞች ነን ሐዋርያው

ጳውሎስ እንዲህ ብሎዋል *«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» (ሮሜ 8:1)* ስለዚህ በልቡ ውስጥ ሐጢያት ያለበት ሰው ገናም ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ አልሆነም አሁንም ድረስ በኢየሱስ ቢያምኑም ያልዳኑና ከደህንነት የራቁ ሐጢያተኞች ሆነው ለምን ይቀራሉ? በኢየሱስ ጥምቀት ሐጢያቶቻቸውን በእርሱ ላይ ሳያኖሩ በመስቀሉ ደም ብቻ ስለሚያምኑ ነው ስለዚህ አሁንም ድረስ በልባቸው ውስጥ ሐጢያት አለ ኢየሱስም ሐጢያቶቻቸው ምንም ቢሆን በመስቀል ላይ ሞቷል፡፡

በኢየሱስ ጥምቀት በሚያምኑ ክርስቲያኖችና በእርሱ በማያምኑ ሰዎች መካከል አቢይ የሆነ ልዩነት አለ አንዳንዶች በኢየሱስ ጥምቀት ላይ እምነትን ይዘው ቤዛነትን አግኝተው ጻድቃን ሲሆኑ ሌሎች ግን አሁንም ድረስ በዚህ ላይ እምነት ሳይኖራቸው አሁንም ድረስ ሐጢያተኞች ሆነው ቀርተዋል መንፈስ ቅዱስ በሐጢያተኛ ላይ አይመጣም እርሱ የሚመጣው በውሃውና በመንፈሱ ዳግም በተወለደ ጻድቅ ሰው ላይ ነው፡፡

ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ አለ *«ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?» (ሮሜ 6:3)* ብዙ ሰዎች ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሐጢያቶቻችንን እንደወሰደ ያምናሉ ነገር ግን በኢየሱስ ጥምቀት ካላመንን ሐጢያት አልባ የሆነ ልብ እንዳለን መመስከር በፍጹም አንችልም እንደዚያ ብናደርግ ከሕሊናችን ጋር የሚጋጭ ውሸት ለእግዚአብሄር እየነገርነው ነው፡፡

በእርሱ ጥምቀት በማመን ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወደ ኢየሱስ ካላስተላለፍን አሁንም ድረስ በልቦቻችን ውስጥ ሐጢያት አለ የኢየሱስን ጥምቀትና መስቀል ወንጌል የማያምኑ ሰዎች ሕግ አክራሪነት ውስጥ ወደ መውደቅ ያዘነብላሉ የከፉ

ሐጢያተኞችም ይሆናሉ ስለዚህ ምንም ነገር ቢያደርጉም ጥቅጥቅ ባሉ ተራሮች ላይ ሄደው ቢጸልዩ ወይም በጸሎት ስብሰባዎች ላይ ይቅርታን ለማግኘት ከልባቸው ቢጸልዩም አሁንም ድረስ በልባቸው ውስጥ የቀሩ ሐጢያቶችን ያገኛሉ፡፡

ኢየሱስ እንዲህ ብሎዋል *«በሰማያት ያለውን የአባቴን ፍቃድ የሚፈፅም እንጂ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! በስምህ ትንቢትን አልተናገርንምን? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተዓምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል የዚያን ጊዜም፡- ከቶ አላውቃችሁም እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ፡፡» (ማቴዎስ 7፡21-23)*

*«አመጸኞች»* የሚለው የሚያመላክተው ማንን ነው? ይህ የሚያመላክተው በመስቀሉ ብቻ ስላመኑ በልባቸው ውስጥ ፍጹም የሆነውን ቤዛነት ያልተቀበሉትን ሰዎች ነው ያ ከእግዚአብሄር ያልሆነ ግርድፍ እምነት ነው ኢየሱስ በጥምቀቱና በመስቀሉ አማካይነት እንዳዳነን እውነቱን ካላመንን አመጸኞች ነን የኢየሱስን ጥምቀትና መስቀል ከማወቃችንና ከማመናችን በፊት ትክክለኛ እምነት አለን ማለት አንችልም፡፡

ኢየሱስ ሰዎች ዳግም መወለድ የሚፈልጉ ከሆነ ያ የሚቻለው በውሃና በመንፈስ አማካይነት ብቻ እንደሆነ ተናግሮዋል ሰዎች መዳን የሚችሉት በኖህ መርከብ ውስጥ ገብተው ቢሆን ኖሮ ብቻ እንደሆነ ሁሉ እናንተም የሐጢያቶቻችሁን ሁሉ ስርየት መቀበልና እውነተኛ የታመነ ሕይወት መኖር የምትችሉት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ስታምኑ ብቻ ነው ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ውጭ የሐጢያቶቻችሁን ይቅርታ መቀበልም ሆነ የእግዚአብሄር ልጆች መሆን አትችሉም፡፡

**<u>ጥያቄ 8:</u> በኢየሱስ ማመን እንዳዳነኝ እርግጠኛ ነበርሁ በልቤ ውስጥ ባሉት አመኔታዎችም ሰላም ነበርሁ አሁን ግን በመልዕክቶችህ ግራ ተጋብቻለሁ ለመዳን የእርሱን ጥምቀት ከመስቀሉ ጋር አብሬ ማመን ይገባኛልን?**

<u>መልስ:</u> በኢየሱስ ጥምቀት የማታምን ከሆንህ በልብህ ውስጥ ሐጢያት መኖሩ እርግጥ ነው ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ ብሎዋል *«ኃጢያት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በኛ ውስጥ የለም» (1ኛ ዮሐንስ 1:8)* በኢየሱስ ጥምቀት ባለማመንህ ምክንያት በእርግጥም ሐጢያት እያለብህ እንኳን ሐጢያት የለብኝም የምትል ከሆነ የራስህን ሕሊና እያታለልህ ነው እውነት በውስጥህ የሌለ ለመሆኑም ማስረጃ ነው የደህንነት ማረጋገጫ ከልባችን የሚወጣው በኢየሱስ ጥምቀትና መስቀል በማመን የሐጢያቶቻችንን ስርየትና የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ስንቀበል ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሎዋል *«...ሌላ ወንጌል....» (ገላትያ 1:7)* ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ሊያድነን የሚችለው ሐዋርያት ከኢየሱስ የተቀበሉትና ለሰዎች የሰበኩት የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ነው ሐዋርያት የሰበኩትን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ካላመንን በእርግጥም አሁንም ድረስ በውስጣችን ሐጢያት አለብን::

አሁንም ድረስ በውስጣችን ሐጢያት እያለብን በደህንነት ማረጋገጫ መኖር የምንችለው እንዴት ነው? ገና ዳግም ያልተወለዱ ክርስቲያኖች በእግዚአብሄር ፊት ጥሩ ሆነው ሲታዩ ስለ ደህንነታቸው በሙሉ ደስታና አመኔታ እርግጠኞች ይሆናሉ ነገር ግን አንዳንድ ከበድ ያሉ ሐጢያቶችን በሚሰሩበት ጊዜ በልባቸው ውስጥ ባለው የሐጢያት ሸክም የተነሳ ድፍረት አጥተው ይፈራሉ ይህ በእግዚአብሄር ላይ ሳይሆን በራሳቸው

አስተሳሰቦችና ስሜቶች ላይ የተመሰረተ አስመሳይ ደህንነት ነው ቀስ በቀስ ለመቀደስና በቀላሉ የሚናወጡ ደህንነቶቻቸውን ለመጠበቅ ሲሉ በየቀኑ የንስሐ ጸሎቶችን ለማድረግ ያዘነብላሉ፡፡

በዚህ የሐሰት ደህንነት የሚያምኑ ሰዎች እግዚአብሔርን በየቀኑ ይቅርታ በመጠየቅና በምግባሮቻቸውም ሕጉን በመጠበቅ ቅዱስ ሕይወትን የሚኖሩ ከሆኑ በመጨረሻ አንድ ቀን ፈጽመው እንደሚድኑ ያምናሉ ሆኖም በእርሱ ጥምቀት ላይ ባለ እምነት አማካይነት ሐጢያቶቻቸውን በኢየሱስ ላይ ካላኖሩ አሁንም ድረስ ሐጢያተኞች ናቸው፡፡

እግዚአብሄር ያዘጋጀው ደህንነት ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ በተጠመቀው ጥምቀቱ አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ እንደወሰደና በመስቀል ላይ እንደደመሰሳቸው የሚነግረን ፍጹም ደህንነት ነው፡፡

ስለዚህ ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ አለ *«በኃጢያታችን ብንናዘዝ ኃጢያታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» (1ኛ ዮሐንስ 1:9)* ሐጢያቶቻችን በሙሉ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ይቅር ባይባሉ ኖሮ በእርሱ ብናምንና በሐጢያቶቻችን ምክንያት ሲያል ለመውረድ የታጨን መሆናችንን ብናውቅም አሁንም ድረስ ሐጢያተኞች መሆናችንን በጌታ ፊት መናዘዝ ይኖርብን ነበር እውነተኛ የሐጢያት ኑዛዜ ይህ ነው ሐጢያቱ ምንም ያህል ትንሽ ቢሆንም ሐጢያት ያለ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል ሊነጻ አይችልም በዚህ መንገድ ስንናዘዝ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በአንድ ጊዜ ያስወግድና ጻድቃን ያደርገናል፡፡

የተወደደው ሰዓት አሁን ነው (2ኛ ቆሮንቶስ 6:2) በኢየሱስ ጥምቀትና መስቀል የሚያምን ማንኛውም ሰው ከሐጢያቶቹ ሁሉ ይድናል ጻድቅ ይሆናል ጌታ በማንኛውም ጊዜ ቢመጣ

መንግስተ ሰማይ ለመግባት ሁልጊዜም ዝግጁ እንደሆነ ጠንካራ እምነት ይኖረዋል ከእውነተኛው ወንጌል ውጭ በትምህርቶችና በስነ መለኮቶች የሚያምን ማንኛውም እምነት ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ሊያድነን አይችልም እነዚያ ዲያብሎስ በሰዎች አሳቦች ውስጥ ያስቀመጣቸው ብልጣ ብልጥ ማታለያዎች ናቸው ወደ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል መመለስና በልባችሁ እውነተኛውን የሐጢያቶች ደህንነት መቀበል ይገባችኋል ይህም እርሱንና ስራውን መውደድ ነው፡፡

**<u>ጥያቄ 9:</u> «የውሃና የመንፈስ» ግንዛቤህ ትክክል ከሆነ በመስቀል ላይ የተሰቀለው ሌባ ደህንነትን አያገኝም ነበር በመስቀል ላይ የተሰቀለው ሌባ በልዩ ሁኔታ የሚታይ ከሆነ እግዚአብሄር ቅን አይሆንም ምክንያቱም ወደ መንግስቱ ለመግባት ራሱ ያወጣውን ሕግ ጥሶዋልና በመስቀል ላይ የተሰቀለው ሌባ ያገኘውን ደህንነት እንዴት ልታብራራው ትችላለህ?**

**<u>መልስ:</u>** በዚያ ዘመን አይሁዶች በሙሉ ትንቢት የተነገረለትን መሲህ ይጠብቁ ነበር ስለዚህ እነርሱ ከማንኛውም ሌላ ሕዝብ ይበልጥ እግዚአብሄር በሙሴ አማካይነት ስለሰጠው «ሕግና የመስዋዕት ስርአት» በሚገባ ያውቁ ነበር እነርሱ መሲሁ በእግዚአብሄር የማስተሰርያ ሕግ መሰረት እንደሚመጣና ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ እንደሚያላቅቃቸው አምነዋል፡፡

ነገር ግን በአጥማቂው ዮሐንስ የሆነው የኢየሱስ ጥምቀት ከእግዚአብሄር እንደነበረና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በኢየሱስ ላይ የሚያኖር እንደነበር (ማርቆስ 11:27-33) አላመኑም

በፋንታው እርሱን የተመለከቱት ሕዝቡን የሚያስት ሰው አድርገው ስለነበር ሰቀሉት።

ሮማውያን በሮም ሕግ መሰረት ከመገረፍ ወይም ከመሰቀል ከለላ ስለነበራቸው (የሐዋርያት ስራ *22:25-29፤23:27*) በመስቀል ላይ የተሰቀሉት ወንበዴዎች አይሁዶች እንጂ ሮማውያኖች እንዳልነበሩ እናውቃለን *«ጌታ ሆይ! በመንግስትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ» (ሉቃስ 23:42)* ከሚሉት ቃሎቹ የተነሳም ሌባው እግዚአብሄርን የፈራ አይሁድ እንደነበርም እናውቃለን አይሁዳዊው ሌባ እግዚአብሄር ለሙሴ የሰጠውን ሕግና የመስዋዕት ስርአት ቀድሞውኑም የሚያውቅ ነበር ስለዚህ መሲሁ በእግዚአብሄር የስርየት ሕግ መሰረት እንደሚመጣ አምኖዋል። .

ወደ እግዚአብሄር የሚቀርቡ ሰዎች በሐጢያቶቻቸው ምክንያት ሲያል ለመውረድ የታጩ ሐጢያተኞች እንደሆኑ መናዘዝ አለባቸው ሌባው

*«ስላደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና ለእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው» (ሉቃስ 23:41)* በማለት ሐጢያቶቹን ተናዘዘ ሌባው እግዚአብሄርን እንደፈራና ተስፋውም መንግስተ ሰማይ መግባት እንደሆነ *«ጌታ ሆይ! በመንግስትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ» (ሉቃስ 23:42)* ከሚሉት ቃሎቹ እናውቃለን።

እርሱም እንዲህ አለ *«ይህ ሰው ምንም ስህተት አልሰራም» (ሉቃስ 23:41)* ሌባው ኢየሱስ ስላደረገው ነገር እንዴት አወቀ? ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ እንደተጸነሰ፣ ከድንግል ማርያም እንደተወለደ፣ የሰው ዘር ሁሉ ወኪል በሆነው በአጥማቂው ዮሐንስ እንደተጠመቀ፣ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ እንደወሰደና እንደተሰቀለ አምኖዋል በምድር ላይ ለሰራቸው ምግባሮች ዋጋውን ለመክፈል ቢሰቀልም ኢየሱስ እርሱን ጨምሮ ለሕዝቡ ሁሉ ያደረገውን ያመነ አይሁድ ነበር።

በዮሐንስ ጥምቀት አማካይነት ሐጢያቶቻቸውን የተናዘዙ ሰዎች ሐጢያቶቻቸው በእርሱ ጥምቀት አማካይነት ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ ሲሰሙ የእግዚአብሄርን ጽድቅ ተቀብለዋል ነገር ግን የዮሐንስን የንስሐ ጥምቀት ያልተቀበሉ ሰዎች የእግዚአብሄርን ፈቃድ ንቀዋል ምክንያቱም በኢየሱስ ጥምቀት አላመኑምና:: (ሉቃስ 7:28-30)

በተቃራኒው የዳነው ሌባ ኢየሱስ ያደረገው ነገር ሁሉ ትክክልና ጻድቅ እንደነበር ሲናዘዝ ሌላው አይሁዳዊ ሌባ ግን ያንን አላደረገም እርሱ በመካከላቸው የተፈጸሙትን እነዚያን ነገሮች በሙሉ ከሰሙ አይሁዶች አንዱ ይሆናል (ሉቃስ 1:1) በመጨረሻም ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት የእርሱን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ማመን ስለመጣ ኢየሱስ ጻድቅና ትንቢት የተነገረለት መሲህ እንደነበር መናገር ቻለ በዚህም ዳነ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በማመንም ድኖዋል እግዚአብሄር ጻድቅ ስለሆነ በሕይወት መንፈስ ሕግ መሰረት በኢየሱስ ጥምቀትና መስቀል የሚያምኑትን ያጸድቃል::

**<u>ጥያቄ 10</u>: እግዚአብሄር ባለጸጋና ርህሩህ ስለሆነ በልባችን ውስጥ ሐጢያት ቢኖርብንም በኢየሱስ ብናምን ጻድቅ አድርጎ አይመለከተንምን?**

**<u>መልስ</u>:** እግዚአብሄር ፍቅር ነው ጻድቅም ደግሞ ነው ስለዚህ ምንም ይሁን ሐጢያትን በቅንነት ይፈርዳል *«የኃጢያት ደመወዝ ሞት ነው::» (ሮሜ 6:23)* ይህ ማለት አንድ ሐጢያተኛ ከተፈረደበት በኋላ ለሲዖል የታጨ ነው ማለት ነው እርሱ ብርሃንን ከጨለማ እንደለየ ጻድቃንን ከሐጢያተኞች ይለያል እግዚአብሄር ኢየሱስ በጥምቀቱና በስቅለቱ አማካይነት

ሐጢያቶቻቸውን ሁሉ እንዳስወገደ በማመን ሐጢያት የሌለባቸውን ሰዎች ጻድቃን ብሎ ይጠራቸዋል፡፡

ሆኖም በኢየሱስ ጥምቀት ባለማመን አሁንም ድረስ በውስጣቸው ሐጢያት ያለባቸው ሰዎች በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኞች ናቸው በሌላ አነጋገር በኖህ ዘመን የነበሩት ሰዎች እንዳደረጉት እነርሱም በውሃው በኢየሱስ ጥምቀት የማያምኑ ሰዎች ናቸው እግዚአብሄር አሁንም ድረስ ሐጢያት ያለባቸውን ሐጢያተኞች ጻድቃንና ሐጢያት አልባ አድርጎ የሚያያቸው ከሆነ እየዋሸ መሆን አለበት ስለዚህ ፍጥረቶቹን ሁሉ ሊኮንን ወይም ሊገዛ አይችልም፡፡

እርሱ እንዲህ አለ *«እኔ ኃጢያተኛውን አላፀድቅምና» (ዘፀዓት 23:7)* ሐጢያተኞች እግዚአብሄር እኛን እጅግ ቀናና ተገቢ በሆነ መንገድ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ያዳነበትን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ትተው የሰዎችን ትውፊት የሚከተሉና የሚደገፉ ሰዎች ናቸው ኢየሱስ እንዲህ ብሎዋል *«ስለ ኃጢያት፣ በእኔ ስለማያምኑ ነው» (ዮሐንስ 16:9)* አሁን በዚህ ምድር ላይ የቀረው ብቸኛው ሐጢያት ኢየሱስ በጥምቀቱና በመስቀሉ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደወሰደና አዳኛችን እንደሆነ እውነቱን አለማመን ነው ይህ ፈጽሞ ይቅር የማይባል መንፈስ ቅዱስን የመሳደብ ሐጢያት ነው መንፈስ ቅዱስን የሚሳደቡ ሰዎች የሚድኑበት ፈጽሞ ሌላ መንገድ የለም ምክንያቱም ኢየሱስ ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ እንዳስወገደላቸው አያምኑምና፡፡

ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ አለ *«ኃጢያትን የሚያደረግ ሁሉ ዓመፅን ያደርጋል ኃጢያትም አመፅ ነው እርሱም ኃጢያትን ሊያስወግድ እንደተገለጠ ታውቃላችሁ በእርሱም ኃጢያት የለም በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢያትን አያደርግም ኃጢያትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም አያውቀውምም፡፡» (1ኛ*

*ዮሐንስ 3:4-6)* ኢየሱስ በጥምቀቱና በመስቀሉ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ የመውሰዱን እውነት አለማመን አመጸኝነት ነው እርሱ እንዲህ ያለውን አመጽ የሚያደርጉ ሰዎችን በመጨረሻው ቀን አይቀበላቸውም::

በእርሱ የሚኖሩ ሰዎች ሐጢያት የለባቸውም በእርሱ ውስጥ በመጠመቅም ከኢየሱስ ጋር ተጣምረዋል የሕይወት ዘመናቸውን ሐጢያቶች በሙሉ በጥምቀቱ ላይ ባላቸው እምነታቸው አማካይነት በእርሱ ላይ ያኖሩ ሰዎች አሁንም ድረስ ከስጋቸው ድክመቶች የተነሳ ሐጢያት ቢሰሩም ሐጢያት የለባቸውም::

እግዚአብሄር ሐጢያቶቻቸውን በኢየሱስ ላይ ያኖሩትንና በሕይወት መንፈስ ሕግ የተቀደሱትን ሰዎች ጻድቃን ብሎ ይጠራቸዋል እርሱ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ይሰጣቸዋል መንፈስ ቅዱስ በልባቸው ውስጥ ሐጢያት ባለባቸው ሰዎች ላይ ፈጽሞ አይመጣም ዳዊት በመዝሙረ ዳዊት ላይ እንዲህ ብሎዋል *«አንተ በደልን የማትወድ አምላክ ነህና ክፉ ከአንተ ጋር አያድርም» (መዝሙረ ዳዊት 5:4)* የእግዚአብሄር ቅዱስ መንፈስ በውስጣቸው ሐጢያት ባለባቸው ሰዎች ልብ ውስጥ ፈጽሞ አይኖርም በውስጡ መንፈስ ቅዱስ የሌለበት ሐጢያተኛ እንኳን በሐይማኖት ትምህርቶችና በራሱ አስተሳሰቦች ላይ ተመርኩዞ ከሐጢያት እንደዳነ ይናገር ይሆናል ነገር ግን ሰው ሕሊናው ስለሚወቅሰው በእምነት ሐጢያት የለብኝም ጻድቅ ነኝ ማለት አይችልም::

ስለዚህ ይህ ሰው በሌሎች ሰዎች ፊት ሐጢያተኛ እንደሆነ ይናገራል በእግዚአብሄር ፊት ደግሞ በእርግጥም ጻድቅ ሰው እንደሆነ ያስባል እግዚአብሄር ግን ሐጢያተኛውን ፈጽሞ ጻድቅ ብሎ አይጠራውም ሐጢያተኛ ለእግዚአብሄር ፍርድ የተመደበ ነው ሐጢያተኛ ለመዳን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን አለበት::

<u>ጥያቄ 11፡</u> በአንተ አባባል መሰረት ኢየሱስ ያለፉትን አሁን ያሉትንና የወደፊት ሐጢያቶችን በሙሉ ቀድሞውኑም አስወግዶዋል ካልን በኢየሱስ ጥምቀትና መስቀል በማመን ቀድሞውኑም ሐጢያቶቹ ይቅር የተባሉ የመሆኑን እውነታ በማሰብ ያለ ማቋረጥ ሐጢያትን ቢሰራ የግለሰቡ ዕጣ ፈንታ እንዴት ይሆናል? ይህ ሰው ሌላ ሰው ቢገድል እንኳን በኢየሱስ አማካይነት በመስቀል ላይ ለዚህ አይነቱ ሐጢያትም እንኳን ይቅርታን እንዳገኘ ያውቃል ስለዚህ ኢየሱስ ወደፊት የሚሰራቸውን እነዚህን ሐጢያቶች ቀድሞውኑም እንዳስወገደለት በማመን ያለምንም ማመንታት ሐጢያት በመስራት ይቀጥላል እባክህ ስለ እነዚህ ነገሮች አብራራልኝ፡፡

<u>መልስ፡</u> በመጀመሪያ ስለ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል ጥያቄዎችን ስላነሳህ አመሰግንሃለሁ ያነሳሃቸው ጥያቄዎች ብዙ ክርስቲያኖች ዳግም ከመወለዳቸው በፊት የጠየቁዋቸው ጥያቄዎች ናቸው ዳግም የተወለደ ሰው ፍጹም በሆነው ወንጌል ተመቻችቶ ያለ ማቋረጥ ሐጢያት ይሰራል ብለህ እንደምትጨነቅ አውቃለሁ ነገር ግን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ሰዎች አንተ የምንትጨነቅለትን እንደዚህ ያለውን ሕይወት ወደ መኖር እንደማያዘነብሉ ነገር ግን በምትኩ የጽድቅ ሕይወትን እንደሚኖሩ ልነግርህ እፈልጋለሁ፡፡

በመጀመሪያ ስለዚህ ነገር ልታስብ ይገባሃል በእርግጥ መንፈስ ቅዱስ በውስጥህ ካለ እንደዚያ ማድረግ ባትፈልግም እንኳን የተቀደሱ ፍሬዎችን ታፈራለህ በሌላ በኩል መንፈስ ቅዱስ በውስጥህ ከሌለ ምንም ያህል ጠንክረህ ብትሞክርም አንዳች የመንፈስ ፍሬዎችን ማፍራት አትችልም ሰው በኢየሱስ ቢያምንም እንኳን በልቡ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ከሌለው እንዴት የመንፈስን ፍሬዎች ማፍራት ይቻለዋል? ይህ የማይቻል ነው

ጌታ ክፉ ዛፍ በፍጹም መልካም ፍሬዎችን ሊያፈራ እንደማይችል ተናግሮዋል:: (ማቴዎስ 7:17-18)

አሁን ይህንን ጥያቄ ልጠይቅህና አንተም መልሱን ልትሰጠኝ እፈልጋለሁ አንተ በኢየሱስ ታምናለህ ነገር ግን ሕይወትህን የምትኖረው በእርግጥ አለማዊ ሐጢያቶችን አሸንፈህ ነውን? አለማዊ ሐጢያቶችን እያሸነፍህ ጌታን አብዝተህ እያገለገልህና የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ለእነርሱ በማቅረብ ሌሎች ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ እንዲድኑ በመፍቀድ ጻድቅ የእግዚአብሄር አገልጋይ ሆነህ እየኖርህ ነውን? ለዚህ ጥያቄ አዎ የሚል መልስ እንድትሰጥ የሚፈቅድልህ ብቸኛ እምነትና ወንጌል ጌታ በብሉይና በአዲስ ኪዳናት ውስጥ የመሰከረለት የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ነው::

በኢየሱስ ካመንን በኋላም እንኳን በአለም ላይ ሐጢያት መስራት እንቀጥላለን ሆኖም ጌታችን ከአለም ሐጢያቶች በሙሉ እኛን ለማዳን በዮሐንስ ተጠምቆ በመስቀል ላይ ደሙን አፍስሶዋል ስለዚህ ጌታ ለእኛ የጽድቅ ስራን ሰርቶልናል እኛም ሐጢያቶቻችንን ባስወገደው በእግዚአብሄር ጽድቅ በጌታ ጥምቀትና ደም አማካይነት ከሐጢያቶቻችን ድነናል::

እንደገና አንዳንድ ጥያቄዎችን ልጠይቅህ እፈልጋለሁ ከሕሊናህ ሐጢያቶች ነጻ ነህን? ከዚህ ቀደም በእርሱ ታምን እንደነበረው ሁሉ በኢየሱስ ካመንህ በኋላ እንኳን ሐጢያተኛ አልነበርህምን? ይህ እውነት ከሆነ ለዚህ ምክንያቱ ምናልባትም ስለ ውሃውና ስለ መንፈሱ ወንጌል አለማወቅህ ነው ስለዚህ በልብህ ውስጥ መንፈስ ባለመኖሩ ከስጋ በተወረሱ ችግሮችና ውዥንብሮች ውስጥ ወድቀሃል ምንም ያህል የታመንህ ምዕመን ብትሆንም ከስጋ አስተሳሰቦች ማምለጥ የምትችለው ልብህን ባዶ በማድረግና የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመውሰድ ነው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እውነት የመሆኑን ሐቅ ለመረዳት

ስጋዊ አስተሳሰቦችን መጣልና ወደ ተጻፉት የእግዚአብሔር ቃሎች መመለስ ይገባሃል።

በዚህ አለም ላይ ጌታን በአንደበታቸው ቢጠሩትም ጌታ የደነገገውን የደህንነት ሕግ በፈለጉት በማንኛውም መንገድ የሚለውጡ ብዙ ሰዎች አሉ አንተ ከእነዚህ አይነት ሰዎች አንዱ ከሆንህ ጌታ በመጨረሻው ቀን ይተውሃል አንተ ሊያድንህ የሚችለው ብቸኛው ነገር ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደም እንደሆነ የማታምንና ጥያቄዎችንም የጠየቅኸው ቀሪ የሕይወት ዘመንህን ከሐጢያት ተላቀህ ለመኖር ካለህ ፍላጎት ከመነሳት ይሆን ዘንድ እጸልያለሁ

ሆኖም አስተሳሰቦችህ *«ለእግዚአብሔር ሕግ የማይገዛ ሊገዛም የማይችል» (ሮሜ 8:8)* የስጋ አስተሳሰቦች ናቸው በእርግጥ እግዚአብሔርን የሚያስደስት እምነት እንዲኖርህ ከፈልግህ ጌታ በድንግል ማርያም በኩል ወደዚህ አለም በመምጣት በዮርዳኖስ ወንዝ በአጥማቂው ዮሐንስ በተቀበለው ጥምቀት አማካይነት የሰውን ዘር ሐጢያቶች እንደወሰደና በዚህም የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሁሉ እንደፈጸመ በጌታ አስደናቂ ስራ ማመን ይገባሃል።

የእግዚአብሔርን የጽድቅ ስራ ማከናወን የሚችለው ማን ይመስልሃል ጻድቅ ሰው ወይስ ሐጢያተኛ? ሐጢያተኛ በእግዚአብሔር ፊት የሐጢያቶችን ስርየት ስላልተቀበለ አሁንም ድረስ በሐጢያት ውስጥ ነው ስለዚህ ይህንን ሰው የሚጠብቀው ብቸኛው ነገር ለሐጢያቶቹ የሚቀበለው ፍርድ ነው እግዚአብሔር ሐጢያተኞች ወደ መንግስቱ እንዲገቡ አይፈቅድም ምክንያቱም *«አንተ በደልን የማትወድድ አምላክ ነህና» (መዝሙረ ዳዊት 5:4)* እግዚአብሔር ሐጢያተኛ ወደ እርሱ መጥቶ ከእርሱ አንድ ነገር ቢጠይቀው የሐጢያተኛውን ጸሎቶች አይሰማም ምክንያቱም *«በደሎቻችሁ ከእግዚአብሔር*

*ለይተዋችኋልና»* *(ኢሳይያስ 59:1-2)* የሐጢያት ደመወዝ ሞት ስለሆነ ሐጢያተኛ ሲጎል መውረዱ የተረጋገጠ ነው።

የጽድቅ ስራዎችን መስራት የሚችሉት ቅዱስ የሆኑና በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት የሌለባቸው ጻድቃን ሰዎች ብቻ ናቸው በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስ የሚኖረው የኢየሱስን ጥምቀትና መስቀል ካመኑ በኋላ ሐጢያት በሌለባቸው ሰዎች ልብ ውስጥ ነው ሐዋርያው ጴጥሮስ በበአለ ሐምሳ ቀን እንዲህ አለ *«ንስሐ ግቡ እያንዳንዳችሁ ኃጢያታችሁ ይሰረይ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።» (የሐዋርያት ሥራ 2:38)*

ይህ ምንባብ እያለ ያለው እውነተኛ እምነት እንዲኖርህና በእምነትም የሐጢያቶችህን ሁሉ ስርየት ማግኘት ከፈለግህ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ደሙ ማመን ይገባሃል ነው እንዲህ ያለው እምነት *«በኢየሱስ ስም እንድትጠመቅ»* ይፈቅድልሃል ይህ ማለት በእርሱ የጽድቅ ምግባሮች በማመን የሐጢያቶችህን ስርየት ትቀበላለህ ማለት ነው የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በእርሱ ጥምቀትና መስቀል እምነት የነበራቸውን ዳግም የተወለዱ ምዕመናን እንዳጠመቁዋቸው የታወቀ ነው ኢየሱስ ሰውን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ ደቀ መዛሙርቱን አዞዋቸዋል። (ማቴዎስ 28:19)

ከዚህም በላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሎዋል *«የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም» (ሮሜ 8:9)* እግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስን ለጻድቃን የሰጠው የእርሱ ልጆች መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው መንፈስ ቅዱስ በፍጹም በሐጢያተኞች ውስጥ አይኖርም ምክንያቱም እነርሱ ሐጢያት አለባቸውና መንፈስ ቅዱስ ሐጢያትን አይወድም የሚመርጠው ቅድስናን (ከሐጢያት መለየትን) ነው መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን በጽድቅ መንገድ ይመራቸዋል የአብንም

ፈቃድ እንዲከተሉ ይመራቸዋል ታዲያ የእግዚአብሄር ፈቃድ ምንድነው? የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በየአገሩ ላሉ ሰዎች ሁሉ ማሰራጨትና በታላቁ ተልዕኮ መሰረትም እነርሱን ማጥመቅ ነው::

የጻድቃንና የሐጢያተኞች ስጋ እስከሚሞቱበት ቀን ድረስ ሐጢያትን ይሰራል ሆኖም ጌታ በጥምቀቱና በደሙ ሰዎች በስጋቸውና በልባቸው የሚሰሩትን ሐጢያቶች በሙሉ የማስወገዱን የጽድቅ ስራ ሰርቷል ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ተጽፎዋል *«ጻድቅ በእምነት (በእውነተኛው ወንጌል) ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈ የእግዚአብሔር ፅድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና» (ሮሜ 1:17)* በእግዚአብሄር ጽድቅ በማመን የሐጢያቶችን ስርየት ያገኘ ሰው *«የሐጢያትና የሞት ሕግን»* አሸንፎ የእርሱን ጽድቅ ይከተላል ይህ የሚቻለው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በሚያምኑ ሰዎች ላይ በሚወርደውና በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው::

የጻድቅ ሰው ያለፉት አሁን ያሉትና የወደፊት ሐጢያቶች በሙሉ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀበት ጊዜ ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል የጻድቃን ስጋም እንደዚሁ ከኢየሱስ ጋር ሞቷል አንድ ሰው በዚህ ሲያምን ከኢየሱስና ከሞቱ ምሳሌ ጋር ይተባበራል ይህም ለሐጢያቶቹ ሁሉ ፍርድ ይሆናል:: (ሮሜ ምዕራፍ 6)

ስለዚህ የአንድ ጻድቅ ሰው ስጋ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ያለ ማቋረጥ ሐጢያት ቢሰራም መንፈስን መከተል ይችል ዘንድ በልቡ ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ይመራዋል አንድ ጻድቅ ሰው መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ስለሚኖር መንፈስ ቅዱስን ይከተላል የእግዚአብሄርንም ስራ ይሰራል::

በሐዋርያት ዘመንም እንኳን ብዙ ሰዎች ዳግም የተወለዱ ሰዎችን ምክንያታዊ ባልሆነ መንገድ መውቀስ ያዘወትሩ ነበር

ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ ይመሩ የነበሩትን ዳግም የተወለዱ ሰዎች በሚኖሩት ሕይወት ይጨነቁ ነበርና ነገር ግን የዚህ አይነት ሰዎች ሐዋርያት የሰበኩትን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ከስጋ የመነጩ ግብታዊ እሳቤዎች አድርገው በተሳሳተ መንገድ የተረዱ ሰዎች ናቸው ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ለእነዚህ ሰዎች እንዲህ አለ *«እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ፀንተን እንኑርን? አይደለም ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?» (ሮሜ 6:1-2)* ጨምሮም *«በኢየሱስ ክርስቶስ ለጌታችን ምስጋና ይሁን እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ በስጋዬ ግን ለኃጢአት እገዛለሁ::» (ሮሜ 7:25)*

በመጨረሻ የጻድቃን ስጋ አሁንም ድረስ ጎዶሎ ነው በየጊዜው ሐጢያት ከመስራት በቀር ምርጫ የለውም ነገር ግን እነርሱ አሁንም ወንጌልን በመላው አለም በመስበክ መንፈስ ቅዱስን ይከተላሉ ጻድቃን ልቦቻቸው በጸጋው እርፍ ስላሉ በመንፈስ ይመላለሳሉ *«እንግዲህ ምን ይሁን? ከጸጋ በታች እንጂ ከህግ በታች ስላይደለን ኃጢኣትን እንስራን? አይደለም ለመታዘዝ ባርያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባርያዎች እንደሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት ኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባርያዎች ናችሁ::» (ሮሜ 6:15-16)*

እውነተኛ አበቦች ከሰው ሰራሽ አበቦች በጣም የተለዩ እንደሆኑ ሁሉ በጻድቅ ሰው ልብ ውስጥ ያለው ጌታና በሐጢያተኛ ሰው ልብ ውስጥ ያለው ጌታ እርስ በርሳቸው የተለያዩ ናቸው በጻድቅ ሰው ልብ ውስጥ ያለው ጌታ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ሰውየው በመንፈስ መመላለስና በሕይወቱ ውስጥም እግዚአብሄርን የሚያስደስተውን የጽድቅን እውነት መከተል ይችላል በሌላ በኩል ሐጢያተኛ በውስጡ ያለው ጌታ

ራሱ ሐጢያት ስለሆነ ሐጢያትን ከመከተል ውጭ ምርጫ የለውም ሐጢያተኛ በብዙ ሐጢያቶቹ ምክንያት መንፈስ ስለሌለው የተቀደሰ ሕይወትን መኖር አይችልም።

በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ሰዎች የተቀደሰ ሕይወትን መኖር አይችሉም የሚለው ግምት ከስጋ ግብታዊ እሳቤዎች የመነጨ ስህተት ነው እግዚአብሄር እንዲህ በማለት ያስጠነቅቃቸዋል *«እነዚህ ግን የማያውቁትን ሁሉ ይሳደባሉ አእምሮም እንደሌላቸው እንስሶች በፍጥረታቸው በሚያውቁት ሁሉ በእርሱ ይጠፋሉ» (ይሁዳ 1:10)* ዛሬ ብዙ ሰዎች የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል እውነተኛ ወንጌል መሆኑን ቢያውቁም የጻድቃኖችን ሕይወት አይረዱም ምክንያቱም ወንጌሉን ሙሉ በሙሉ ስላላወቁትና በልባቸው ውስጥ ስላልተቀበሉት ነው።

ዳግም የተወለዱ ቅዱሳን የሚሰሩትን የጽድቅ ስራዎች በሚመለከት ምን ታስባለህ? እነርሱ ወንጌልን በመላው አለም ለማስፋፋት በጎ ስራ ያላቸውን ክቡር ነገሮች ራሳቸውንም ጭምር ሕያው መስዋዕቶች አድርገው አቅርበዋል በአንተ እሳቤዎች መሰረት በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ምዕመናኖች ሆነ ብለው በወንጌል ሽፋን ሐጢያት እንደሚሰሩ የምታስበው ለምንድነው?

ጻድቃን በእውነት ብርሃንና በእግዚአብሄር ጽድቅ መካከል በጎ ስራዎችን ይሰራሉ የእግዚአብሄርን ጽድቅ የሚያደርጉ ሰዎች ከእግዚአብሄር ተወልደዋል ሐጢያተኞች በሙሉ ኢየሱስ በጥምቀቱና በደሙ ሐጢያቶቻቸውን ወዳስወገደበት ወንጌል እንዲመለሱ ተስፋ እናደርጋለን።

አዎ ልባዊ ምኞታችን አንተም በእውነት ከልብህ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን የሐጢያቶችን ስርየት እንድትቀበልና እስከ መጨረሻው ቀን ድረስም ያለ ሐጢያት ሆነህ ጌታን እንድትጠብቅ ነው። ✉

This **eBook** was created to preach the gospel of the Water and the Spirit all over the world through **Paul C. Jong's Christian Book Series .**

For more information on
Paul C. Jong's Christian Book Series,
visit us on the Web at "**www.bjnewlife.org**" **&**
"**www.nlmission.com**"

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::